# መጽሐፈ ፡ ግብረ ፡ ሕማማት ።

## በግእዝና ፡ በአማርኛ ።

አ·አ· ፲፱፻፺፯ ዓ·ም·

Scanned by CamScanner

## ምዕራፍ፡፶፩።

### ትእዛዝ።

ወእምዝ፡ይትጋብኡ፡ካህናት፡ውስተ፡ቤተ፡ክርስቲያን፡ቅድስት፡በዕለተ፡ዓርብ፡ጽባሕ፡ለሥርዓተ፡ጸሎት፡ወይጸልዩ፡ጸሎተ፡በከመ፡ጸለዩ፡በዕለተ፡ሐሙስ፡ወይበል፡መራሒ፡እዝል፡በ፱፡ ነአምን፡ነአምን፡ነአምን፡ሕማሞ፡ ለዘኢየሐምም፡ ርግዘተ፡ ገቦሁ፡ነአምን፡ወቅንዋተ፡እደዊሁ፡ነአምን፡ዩ፡ዩ፡ዩ፡ነአምን፡ሞቶ፡ወትንሣኤሁ።

ወይበሉ፡ለከ፡ኃይል።

### ክፍል፡፩።

### ምንባብ።

### ኦሪት፡ዘዳግም።

ምዕ፡፰፡፲፰-፲፱።

፲፰፡ ወለእመ፡ረሲዓ፡ረሳዕካሁ፡ለእግዚአብሔር፡አምላክከ፡ ወሖርከ፡ ድኅረ፡ ባዕዳን፡ አማልክት፡ ወአምለክሆሙ፡ ወሰገድከ፡ ሎሙ፤ አሰምዕ፡ ላዕሌከ፡ ዮም፡ ሰማየ፡ ወምድረ፡ከመ፡ጠፊአ፡ትጠፍእ።

፲፱፡ በከመ፡አሕዛብ፡ኵሎሙ፡እለ፡ደምሰሶሙ፡እግዚአብሔር፡እምቅድመ፡ገጽከ፡ከማሁ፡ትደመሰስ፡ለእመ፡ኢሰማዕከ፡ቃለ፡እግዚአብሔር፡አምላክከ።

ምዕ፡፱፡፩-፳፬።

፩፡ ስማዕ፡እሥራኤል፡ናሁ፡ተዓድዎ፡አንተ፡ዮም፡ ለዮርዳኖስ፡ ከመ፡ ትሑር፡ ትትቀረሶሙ፤ ለአሕዛብ፡ ዓበይት፡ እለ፡ ይጸንዑከሙ፤ ወለአህጉር፡ዓበይት፡እለ፡ዓረፍተ፡ቅጽሮን፡ይበጽሕ፡እስከ፡ሰማይ።

፪፡ ሕዝብ፡ዐቢይ፡ወነዊኃን፡ደቂቀ፡ዔናቅ፡እለ፡ትብሎሙ፡አንተ፡ወአንተ፡ሰማዕከ፡መኑ፡



## ምዕራፍ፡፶፩።

### ትእዛዝ።

ከዚህ፡ በኋላ፡ ለጸሎት፡ ሥርዓት፡ ዓርብ፡በነግህ፡ካህናቱ፡በከበረች፡ቤተ፡ክርስቲያን፡ውስጥ፡ተሰብስበው፡ሐሙስ፡ጥዋት፡እንደ፡ጸለዩ፡ ይጸልዩ፤ መሪው፡ በዘጠኝ፡ ሃሌታ፡ይበል፡በመለኮቱ፡የማይታመም፡በሥጋው፡የታመመ፡የእርሱን፡ሕማሙን፡እናምናለን፡የጐኑን፡መወጋት፡የእጆቹን፡መቸንከር፡እና ምናለን፡ ወዮ፡ ወዮ፡ ወዮ፡ ሞቱንና፡ትንሣኤውን፡እናምናለን።

ከሃሊነት፡ለአንተ፡ይገባል፡ይበሉ።

### ክፍል፡፩።

### ምንባብ።

### ኦሪት፡ዘዳግም።

ምዕ፡፰፡፲፰-፲፱።

፲፰፡ ፈጣሪህ፡ እግዚአብሔርን፡ መርሳትን፡ብትረሳው፡ ልዩ፡ የሆኑ፡ ጣዖታትን፡ተከትለህ፡ብትሄድ፡ብታመልካቸውና፡ብትሰግድላቸው፡ ፈጽመህ፡ እንድትጠፋ፡ዛሬ፡ሰማይና፡ምድርን፡አዳኝብሃለሁ።

፲፱፡ የፈጣሪህ፡ የእግዚአብሔርን፡ ቃል፡ካልሰማህ፡ከፊትህ፡እንዳጠፋቸው፡አሕዛብ፡ሁሉ፡እንደዚሁ፡ትጠፋለህ።

ምዕ፡፱፡፩-፳፬።

፩፡ እስራኤል፡ ሆይ፡ ስማ፤ የሚጸኑብህ፡አሕዛብን፡ ልትወርሳቸው፡ ትሄድ፡ ዘንድ፡እነሆ፡ አሁን፡ አንተ፡ ዮርዳኖስን፡ ትሻገ ዋለህ፤የቅጽራቸውን፡ግንብና፡እስከ፡ሰማይ፡የሚደርሱ፡ ታላላቅ፡ አምባዎችንም፡ ታፈርሳለህ።

፪፡ ይኸውም፡ ታላቅ፡ብዙ፡ወገን፡አንተ፡የአርበኞች፡ ልጆች፡ የምትላቸው፡ ረጃጅሞች፡

ዘዓርብ፡ጽባሕ።

ይትቀወም ፡ ቅድመ ፡ ገጸ ፡ ደቂቀ ፡ ዓናቅ።

ወተአምር ፡ ዮም ፡ ከመ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክከ፡የሐውር፡ቅድመ፡ገጽከ፡እሳት፡ ዘይደድእ፡ውእቱ ፡ ወውእቱ ፡ ይሤርዎሙ ፡ ወውእቱ፡ያነትዮሙ፡እምቅድመ፡ገጽከ፡ወያ ጠፍዮሙ፡ወይደመስሶሙ፡ፍጡነ፡በከመ፡ ይቤለከ፡እግዚአብሔር።

ወኢትበል፡በልብከ፡ሶበ፡አጥፍኦሙ፡እግዚ አብሔር፡ለውእቶሙ፡አሕዛብ፡እምቅድመ፡ ገጽከ፡በበይነ፡ጽድቅየ፡አብአኒ፡እግዚአ ብሔር፡እትዋረሳ፡ለዛቲ፡ምድር፡ቡርክት፤ አኮ፡በበይነ፡ጽድቅከ፡ወአኮ፡በበይነ፡ንጽሐ፡ ልብከ ፡ ዘትበውእ ፡ አንተ ፡ ትትዋረሳ ፡ ለምድሮሙ።

አላ ፡ በበይነ ፡ ኃጢአቶሙ ፡ ለውእቶሙ ፡ አሕዛብ ፡ ያጠፍኦሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ እምቅድመ፡ገጽከ፡ከመ፡ያቅም፡ኪዳኖ፡ ዘመሐለ እግዚአብሔር፡ለአበዊከ፡ለአብ ርሃም፡ወለይስሐቅ፡ወለያዕቆብ።

ወተአምር፡ዮም፡ከመ፡አኮ፡በበይነ፡ጽድቅከ፡ ዘይሁበከሃ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክከ ፡ ትትዋረሳ፡ለይእቲ፡ምድር፡ቡርክት፡አኮኑ፡ ሕዝብ፡ዘያገዝፍ፡ክሣዶ፡አንተ።

ወተዘከር፡ወኢትርሣዕ፡ሚ፡መጠነ፡አምዐ ዕካሙ፡ለእግዚአብሔር፡አምላክከ፡በገዳም፡ እምአመ፡አውፅአከ፡እምነ፡ምድረ፡ግብጽ፡ እስከ፡በጻሕክሙ፡ውስተ፡ዝንቱ፡መካን፡ እንዘ፡ትከሀድዎ፡ለእግዚአብሔር፡አምላ ክክሙ።

ወበኮሬብኒ ፡ አምዐዕክምዎ ፡ ለእግዚአ ብሔር፡ወተምዐ፡እግዚአብሔር፡ላዕሌክሙ፡ ከመ፡ያጥፍእክሙ።

አመ፡ዓረጉ፡አነ፡ውስተ፡ደብር፡ከመ፡ እንሣእ፡ክልኤ፡ጽላተ፡ዘእብን፡ጽላተ፡ ዘኪዳን ፡ ዘተካየደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምስሌክሙ።

የዓርብ፡ነግህ።

ከፊታቸው ፡ የሚቆምና ፡ ማንም ፡ የሚቃወ ማቸው፡እንደሌለ፡አንተ፡ሰምተሃል።

፫፤ አሁንም፡በፊትህ፡የሚሄድ፡ፈጣሪህ፡እግዚአ ብሔር፡እንደሆነ፡ታውቃለህ፤የሚያጠፋም፡ እሳት፡ነው፤እሱም፡ከፊትህ፡ፈጽሞ፡ያጠፋ ቸዋል፤አጠፋቸዋለሁ፡ብሎ፡እግዚአብሔር፡ እንደ፡ነገረህ፡ፈጥኖ፡ያጠፋቸዋል።

፬፤ እግዚአብሔር፡እለዚያን፡አሕዛብ፡ከፊትህ፡ ባጠፋቸው፡ጊዜ፡በልብህ፡ያቺን፡የከበረች፡ አገር፡እወርሳት፡ዘንድ፡ስለ፡እውነተኛነቴ፡ አገባኝ፡አትበል፤አገራቸውን፡ትወርሳት፡ ዘንድ ፡ አንተ ፡ የምትገባ ፡ ስለ ፡ ልቡናህ ፡ ንጽሕናና፡ስለ፡እውነተኝነትህ፡አይደለም።

፭፤ ለአባቶችህ ፡ ለአብርሃም ፡ ለይሥሐቅ ፡ ለያዕቆብ፡የማለውን፡መሐላ፡ያጸና፡ዘንድ፡ እግዚአብሔር፡እነዚያን፡አሕዛብ፡በኃጢአ ታቸው፡ምክንያት፡ከፊትህ፡አጠፋቸው፡ እንጂ።

፮፤ አንተ፡ክሣደ፡ልቡናውን፡የሚያደነድን፡ ወገን፡ነህና፤ያቺን፡የተባረከች፡አገር፡ ትወርሳት፡ዘንድ፡እግዚአብሔር፡አምላክህ፡ የሚሰጥህ፡ስለ፡ጽድቅህ፡እንዳይደለ፡አሁን፡ ታውቃለህ።

፯፤ ከግብጽ፡ምድር፡ከወጣህ፡ጀምሮ፡ፈጣሪ ያችሁ፡እግዚአብሔርን፡ካዳችሁት፤ወደዚህ፡ ቦታ፡እስክትደርሱ፡ድረስ፡በምድረ፡በዳ፡ ፈጣሪህ፡እግዚአብሔርን፡ምን፡ያህል፡እንዳ ሳዘንከው፡አስብ፤አትዘንጋ።

፰፤ በኮሬብም፡እግዚአብሔርን፡አሳዘናችሁት፤ እግዚአብሔር፡ያጠፋችሁ፡ዘንድ፡በእናንተ ተቈጣ።

፱፤ እግዚአብሔር ከእናንተ፡ጋር፡የተማማለባ ቸውን፡የቃል፡ኪዳን፡ጽላቶችን፡ዐሠርቱ፡ ቃላት፡የተጻፈባቸውን፡ሁለት የዕንቍ፡ ጽላቶችን፡ልቀበል፡እኔ፡ወደ፡ተራራ፡ በወጣሁ፡ጊዜ።

| | ዘዓርብ፡ጽባሕ። | የዓርብ፡ነግህ። |
|---|---|---|
| ፱ | ወነበርኩ፡ውስተ፡ደብር፡አርብዓ፡መዓልተ፡ ወአርብዓ፡ሌሊተ፡እክለ፡ኢበላዕኩ፡ወማየ፡ ኢሰተይኩ። | እህል፡ሳልበላ፡ውኃ፡ሳልጠጣ፡አርባ፡ቀን፡ አርባ፡ሌሊት፡በተራራው፡ላይ፡ተቀመጥኩ። |
| ፲ | ወወሀበኒ፡እግዚአብሔር፡ክልኤ፡ጽላተ፡ ዘዕብን፡ዘተጽሕፋ፡በአጽባእቱ፡ለእግዚአ ብሔር፡ወጽሑፍ፡ውስቴቶን፡ኵሉ፡ቃል፡ ዘነገረኒ፡እግዚአብሔር፡በውስተ፡ደብር፡ አመ፡ተጋባዕክሙ። | እግዚአብሔርም፡በእርሱ፡እጅ፡የተቀረፁ፡ የዕንቍ፡ጽላቶችን፡ሰጠኝ፡በተሰበሰባችሁ፡ ጊዜ፡እግዚአብሔር፡በተራራው፡ላይ፡ የነገረኝ፡ነገር፡ሁሉ፡በነሳቸው፡ላይ፡ ተጽፏል። |
| ፲፩ | በአርብዓ፡መዓልት፡ወበአርብዓ፡ሌሊት፡ ወሀበኒ፡እግዚአብሔር፡ክልዔ፡ጽላተ፡ ዘዕብን፡ጽላተ፡ዘኪዳን። | በአርባው፡ቀንና፡በአርባው፡ሌሊት፡እግዚ አብሔር፡አሥሩ፡ቃላት፡የተጻፈባቸው፡ ሁለቱን፡የኪዳን፡ጽላትና፡የዕንቍ፡ጽላት፡ እግዚአብሔር፡ሰጠኝ። |
| ፲፪ | ወይቤለኒ፡እግዚአብሔር፡ተንሥእ፡ወሑር፡ ፍጡነ፡እምዝየ፡እስመ፡አበሰ፡ሕዝብከ፡ዘአ ውፃእከ፡እምነ፡ምድረ፡ግብጽ፡ወፍጡነ፡ ክሕዱ፡እምውስተ፡ፍኖት፡እንተ፡አዘዝ ካሆሙ፡ወገብሩ፡ሎሙ፡ስብከ። | ከግብጽ፡ምድር፡ያወጣሃቸው፡ወገኖችህ፡ በድለዋልና፡ከአዘዝኳቸውም፡ሥርዓት፡ ወጥተው፡ፈጥነው፡ክደዋልና፡ጣዖትም፡ሠ ተዋልና፡እግዚአብሔር፡ከዚህ፡ቦታ፡ፈጥነ ሂድ፡አለኝ። |
| ፲፫ | ወይቤለኒ፡እግዚአብሔር፡እቤለከ፡ምዕረ፡ ወካዕበ፡እንዘ፡እብል፡ርኢክዎ፡ለዝንቱ፡ ሕዝብ፡ከመ፡ሕዝብ፡ግዙፈ፡ክሣድ፡ውእቱ። | እግዚአብሔር፡ይህ፡ወገን፡ክሣደ፡ልቡናው፡ የደነደነ፡ወገን፡እንደሆነ፡አየሁት፡ብዬ፡ አንድ፡ጊዜ፡ሁለት፡ጊዜ፡ነገርኩህ፡አለኝ። |
| ፲፬ | ኅድገኒ፡አጥፍኦ፡ወእደምስስ፡ስሞ፡ እምታሕተ፡ሰማይ፡ወእገብረከ፡ውስተ፡ ሕዝብ፡ዐቢይ፡ወጽኑዕ፡ወዘይበዝኀ፡እምነ፡ ዝንቱ፡ፈድፋደ። | አጠፋው፡ዘንድ፡ስሙንም፡ከሰማይ፡በታች፡ አጠፋ፡ዘንድ፡ተወኝ፡ገናና፡ጽኑ፡በሆነ፡ ከዚህም፡ፈጽሞ፡በሚበዛ፡ወገን፡መካከል፡ እሾምሃለሁ፡አለኝ። |
| ፲፭ | ወተመየጥኩ፡ወወረድኩ፡እምነ፡ደብር፡ ወደብሩሰ፡ይነድድ፡በእሳት፡ወእልኩኒ፡ ክልዔ፡ጽላት፡ውስተ፡ክልኤሆን፡እደውየ። | እኔም፡ተመልሼ፡ከተራራው፡ወረድኩ፡ ተራራውም፡እንደ፡እሳት፡ይነድ፡ነበር፡ እነዚያም፡ሁለቱ፡ጽላቶች፡በሁለቱ፡እጆቼ፡ ነበሩ። |
| ፲፮ | ወሶበ፡ርኢኩ፡ከመ፡አበስክሙ፡ቅድመ፡እግ ዚአብሔር፡አምላክክሙ፡ወገበርክሙ፡ ለክሙ፡ስብከ፡ወኀደግሙ፡ፍኖተ፡እንተ፡ አዘዘክሙ፡እግዚአብሔር፡ነሣእክዎን፡ ለእልኩ፡ክልኤ፡ጽላት፡ወገደፍክዎን፡ እምውስተ፡ክልኤሆን፡እደውየ፡ወቀጥቀጥ ክዎን፡በቅድሜክሙ። | በፈጣሪያችሁ፡በእግዚአብሔር፡ፊት፡እንደበ ደላችሁ፡ለእናንተም፡ጣዖትን፡እንደሠ ራችሁ፡እግዚአብሔርም፡ያዘዛችሁን፡ ሥርዓት፡እንደተዋችሁ፡ባየሁ፡ጊዜ፡ ሁለቱን፡ጽላት፡አምጥቼ፡ከሁለቱ፡እጆቼ፡ ጥዬ፡በፊታችሁ፡ሰበርኳቸው። |
| ፲፰ | ወሰአልኩ፡ዳግመ፡ቅድመ፡እግዚአብሔር፡ በከመ፡ቀዲሙ፡አርብዓ፡ዕለተ፡ወአርብዓ፡ ሌሊተ፡እክለ፡ኢበላዕኩ፡ወማየ፡ኢሰተይኩ፡ በእንተ፡ኵሉ፡ኀጣውኢክሙ፡ዘአበስክሙ፡ | ስለ፡በደላችሁና፡ስለሠራችሁት፡ኃጢአት፡ ሁሉ፡እሱንም፡ለማስቆጣት፡በፈጣሪያችሁ፡ በእግዚአብሔር፡ፊት፡ክፉ፡የሆነውን፡ነገር፡ ስለአደረጋችሁ፡እህል፡ሳልበላ፡ውኃ፡ |

Scanned by CamScanner

ዘዓርብ፡ጽባሕ።

ወዘገብርከሙ ፡ እኩየ ፡ ቅድመ ፡ እግዚአ
ብሔር፡አምላክክሙ፡ከመ፡ታምዕዕዎ።

ወፈራህኩ፡በእንተ፡መዓት፡ዘተምዐ፡እግዚአ
ብሔር ፡ ላዕሌክሙ ፡ ከመ ፡ ያጥፍእክሙ ፡
ወሰምዐኒ ፡ እግዚአብሔር ፡ በውእቱ ፡
መዋዕል።

ወላዕለ ፡ አሮንሂ ፡ ተምዐ ፡ እግዚአብሔር ፡
ጥቆ፡ ከመ ፡ ይሥርዎ ፤ ወጸለይኩ ፡ ላዕለ ፡
አሮንሂ፡በውእቱ፡መዋዕል፤ወበእንተ፡ጌጋይ
ከሙሂ፡ለዘገብርክሙ፡ላሕመ።

ወነሣእክዎ ፡ ወቀጥቀጥክዎ ፡ ወሐረጽክዎ ፡
ጥቀ፡እስከ፡አድቀቅዎ ፡ ጥቀ ፡ በሕቁ ፡ ወኮነ ፡
ከመ፡ጸበል ፡ ወወደይክዎ ፡ ለውእቱ ፡ ሐሪዕ ፡
ውስተ፡ነቅዕ፤ዘይወርድ፡እምነ፡ደብር።

ወበነበ ፡ ውእየትኒ ፡ ወአመ ፡ መንሱትኒ ፡
ወበነበ ፡ መቃብረ ፡ ፍትወትኒ ፡ አመዓዕ
ክምዎ፡ለእግዚአብሔር፡አምላክክሙ።

ወአመሂ፡ፈነወክሙ፡እግዚአብሔር፡እምነ፡
ቃዴስ፡በርኔ፡ይቤለክሙ፡እርጉ፡ወተዋረስዋ፡
ለይእቲ፡ምድር፡እንተ፡እሁበክሙ፡ወክህ
ድክሙ፡ቃለ፡እግዚአብሔር፡አምላክክሙ፡
ኢአመንክምዎ፡ወኢሰማዕክሙ፡ቃሎ።

ወኮንክሙ ፡ ከሐድያነ ፡ በእግዚአብሔር ፡
እምይእቲ፡ዕለት፡እንተ፡ተአምረ፡ለክሙ።

ዘያመልክ፡በፍጡር፡ርጉም፡ውእቱ፡በል።

ዘኢሳይያስ፡ነቢይ፡በረከተ፡አምላኩ፡ትኩን፡
ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ምዕ፤፩፤፪–፱።

ስማዕ፡ሰማይ፡ወአጽምዒ፡ምድር፡እስመ፡
እግዚአብሔር፡ነበበ፡ከመዝ፡ወይቤ፡ውሉደ፡
ወለድኩ፡ወአልሃቁ፡እሙንቱሰ፡አለዉኒ።
ላሕምኒ ፡ አእመረ ፡ ዘአጥረዮ ወአድግኒ ፡
ሞቅሖ ፡ ወቤተ ፡ እግዚኡ ፡ እሥራኤልሰ ፡
ኢያእመሩኒ፡ወሕዝብየኒ፡ኢጠየቁኒ።

የዓርብ፡ነግህ።

ሳልጠጣ ፡ እንደ ፡ ቀድሞው ፡ አርባ ፡ ቀንና ፡
አርባ፡ ሌሊት ፡ ዳግመኛ ፡ በእግዚአብሔር ፡
ፊት፡ለመንኩ።

፲፱፤ ያጠፋችሁ ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ስለ ፡
ተቆጣው ፡ ቍጣ ፡ ፈራሁ ፡ በዚያም ፡ ወራት ፡
እግዚአብሔር፡ልመናዬን፡ሰማኝ።

፳፤ ያጠፋው ፡ ዘንድ ፡ በአሮንም ፡ ላይ ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ አጥብቆ ፡ ተቆጣ ፡ እኔም ፡ በዚያ ፡
ወራት፡ስለ፡አሮን፡ጸለይኩ፤የላም፡ምስል፡ስለ
ሠራችሁበት፡ኃጢአታችሁም፡ለመንኩ።

፳፩፤ አንሥቼም ፡ ሰበርኩት ፤ ፈጽሞ ፡ እስኪደቅ ፡
ድረስ ፡ ፈጨሁት ፤ እንደ ፡ ትቢያም ፡ ሆነ ፤
ከተራራው ፡ በሚወርድ ፡ ውኃ ፡ ውስጥም ፡
ጨመርሁት።

፳፪፤ እሳትም፡በተነሣበት፡ቦታ፡በጥፋትም፡ጊዜ፡
በምኞት ፡ መቃብርም ፡ ፈጣሪያችሁ፡እግዚአ
ብሔርን፡አሳዘናችሁት።

፳፫፤ እግዚአብሔርም፡ከቃዴስ፡በርኔ፡በላካችሁ፡
ጊዜ፡የምሰጣችሁን፡ያችን፡አገር፡ወጥታችሁ፡
ውረስዋት ፡ ባላችሁም ፡ ጊዜ ፡ የፈጣሪያችሁ ፡
የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ካዳችሁ ፤ አላመናች
ሁትም፤ቃሉንም፡አልሰማችሁም።

፳፬፤ ለእናንተ፡ከተገለጠላችሁ፡ከዚያችም፡ቀን፡
ጀምራችሁ ፡ በእግዚአብሔር ፡ አመፀኞች ፡
ነበራችሁ።

በፍጡር፡የሚያመልክ፡የተረገመ፡ነው፡በል።

የአምላኩ ፡ በረከት ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ለዘላለም ፡
ትሁንና ፡ ነቢዩ ፡ ኢሳይያስ ፡ የተናገረው ፡
ትንቢት፡ይህ፡ነው።

ምዕ፤፩፤፪–፱።

፪፤ እግዚአብሔር፡ ልጆችን፡ወልጄ፡አሳደግሁ፤
እነሳቸው ፡ ግን ፡ አመፁብኝ ፡ ብሎ ፡ ተናግሮ
አልና፤ሰማይ፡ስማ፤ምድርም፡አድምጪ።

፫፤ በሬ ፡ የገዛውን ፡ አወቀ ፤ አህያም ፡ የጌታውን ፡
ቤትና፡ገለባ፡የሚበላበትን፡አወቀ፤እስራኤል፡
ግን፡አላወቁኝም፡ወገኖቼም፡አልተረዱኝም።

Scanned by CamScanner

ዘዓርብ፡ጸባሕ።

፬፡ አሌ፡ሎ፡ለሕዝብ፡ኃጥእ፡ሕዝብ፡ዘምሉዕ፡
ዓመፃ፡ዘርዕ፡እኩያን፡ወውሉድ፡ጸልሐዋን፡
ሐደግምዎ፡ ለእግዚአብሔር፡ ወአመዓዕ
ክምዎ፡ለቅዱስ፡እሥራኤል።

፭፡ እፎ፡ እንከ፡ ትቴስሉ፡ እንዘ፡ ትዌስኩ፡
ኃጢአተ፡ በዲበ፡ ኃጢአት፡ ኵሉ፡ ርእስ፡
ለሕማም፡ወኵሉ፡ልብ፡ለሐዘን።

፮፡ እምእግር፡ እስከ፡ ርእስ፡ ዘኢኮነ፡ ቍስለ፡
ወዘኢኮነ፡ ፍቅዐተ፡ ወዘኢኮነ፡ ዕልዓ፡
ዘይመግል፡ ወአልቦ፡ ከመ፡ ይጠይዕዎ፡
ሥራየ፡ወኢያጸምምዎ፡ወኢይቀብዕዎ።

፯፡ ምድርክሙኒ፡በድወት፡ወአሕጉሪክሙኒ፡
ውዑያ፡በእሳት፡ወለእክለ፡በሐውርቲክሙኒ፡
ፀር፡ይበልዖ፡በቅድሜክሙ፡ያማስኖ፡ወያመ
ዘብሮ፡ፀር፡ነኪር።

፰፡ ወትትኃደግ፡ወለተ፡ጽዮን፡ከመ፡ልገተ፡
አቃቤ፡ቀምሕ፡ወከመ፡ዳስ፡ዐቃቤ፡ወይን፡
ወከመ፡ሀገር፡ሕጽርት።

፱፡ ወሶበ፡ አኮ፡ እግዚአብሔር፡ ጸባኦት፡
ዘአትረፈ፡ለነ፡ዘርዓ፡ከመ፡ሰዶም፡እምኮነ፡
ወከመ፡ገሞራ፡እመሰልነ።

ትርጓሜ፡ትንቢተ፡ኢሳይያስ፡ነቢይ።

፩፡ ስማዕ፡ሰማይ፡ወአጽምኢ፡ምድር፡እስመ፡
እግዚአብሔር፡ ነበበ፡ ዘንተ፡ ዘይቤ፡
ይትረጐም።

፪፡ በከመ፡መላእክት፡ይሰምዑ፡ነገረ፡እግዚአ
ብሔር፡ ወይትልውዎ፡በፍርሃት፡ወበረዓድ፤
ከማሁ፡ ይደሉ፡ ካዕበ፡ ለደቂቀ፡ ዕጓለ፡
እመሕያው፡ከመ፡ያጽምዑ፡ለሰሚዐ፡ቃለ፡
እግዚአብሔር፡ ወይዕቀብዎ፡ በአልባቢ
ሆሙ።

፫፡ እስመ፡ ብሂሎቱሰ፡ ሰማይ፡ ወምድር፡
ይትረጐም፡ እለ፡ ይነብሩ፡ ሰማየ፡
ወምድረ።

የዓርብ፡ነግህ።

፬፡ ዐመፅን፡ ለተመላ፡ ለኃጢአተኛ፡ ወገን፡
ወዮለት፡ እናንተ፡ ክፉዎች፡ ከዳተኞች፡
ልጆች፡ እግዚአብሔርን፡ እንዴት፡
ተዋችሁት? በእስራኤል፡ዘንድ፡የተመሰገነ፡
እግዚአብሔርንስ፡እንዴት፡አሳዘናችሁት።

፭፡ በኃጢአት፡ላይ፡ኃጢአት፡እየጨመራችሁ፡
እንዴት፡ በመከራ፡ ላይ፡ መከራ፡ ትቀበላ
ላችሁ? የሰው፡ ሁሉ፡ ራስ፡ ለሕማም፡ ሆነ፤
የሰውም፡ሁሉ፡ልብ፡ለሐዘን፡ሆነ።

፮፡ ከእግር፡ጀምሮ፡እስከ፡ራስ፡ድረስ፡ቍስልን፡
ግምሳትን፡ መድኃኒት፡ ቀብተው፡ የሚያድ
ኑትና፡የሚያደርቁት፡ያይደለ፡የሚመግል፡
ቍስልን፡ያልሆነ፡የለም።

፯፡ ምድራችሁ፡ ምድረ፡ በዳ፡ ሆነች፤ ከተሞቻ
ችሁም፡ በእሳት፡ ተቃጠሉ፤ የምድራች
ሁንም፡እህል፡በፊታችሁ፡ጠላት፡ይበላዋል፤
ጠላትም፡ፈጽሞ፡ያጠፋችኋል።

፰፡ የጽዮን፡ልጅ፡እንደ፡ወይን፡ጠባቂ፡ዳስና፡
እንደ፡ ተክል፡ ጠባቂ፡ ጎጆ፡ በጦር፡እንደ፡
ተከበበች፡ከተማ፡ሆና፡ትቀራለች።

፱፡ አሸናፊ፡እግዚአብሔር፡ ዘርን፡ያስቀረልን፡
ባይሆን፤እንደ፡ሰዶም፡በሆንን፡ነበር፤እንደ፡
ገሞራም፡በመሰልን፡ነበር።

የነቢዩ፡ኢሳይያስ፡ትንቢት፡ምሥጢራዊ፡
ትርጓሜ።

፩፡ እግዚአብሔር፡ ተናግሮአልና፤ሰማይ፡ስማ፤
ምድርም፡አድምጪ፡ያለውን፡ይህን፡ይተረ
ጐማል።

፪፡ መላእክት፡የእግዚአብሔርን፡ቃል፡በመፍ
ራትና፡በመንቀጥቀጥ፡እንደሚሰሙትና፡እን
ደሚፈጽሙት፡ እንዲሁ፡ ደግሞ፡ የሰው፡
ልጆች፡በልቡናቸው፡ሊጠብቁት፡የእግዚአ
ብሔርን፡ቃል፡ ለመስማት፡ያደምጡ፡ዘንድ፡
ይገባል።

፫፡ ሰማይ፡ ምድር፡ ያለውንም፡ በሰማይ፡ ያሉ፡
መላእክትን፡ በምድር፡ የሚኖሩት፡ ደቂቀ፡
አዳምን፡እንደሆነ፡ይተረጐማል።

Scanned by CamScanner

ዘዓርብ፡ጽባሕ።

ወይቤ፡ውሉደ፡ወለድኩ፡ወአልሐቁ፡ወእሙ
ንቱ፡ዐለዉኒ፡ ይትረጐም ፡ ውእቶሙ፡
ደቂቀ፡እስራኤል።

እስመ ፡ አቅረቡሙ ፡ ኀቤሁ ፡ ዘእንበለ ፡
ዘሰአሙ፡ አሕዛብ ፡ ወከናሙ ፡ ለሙ ፡ ከመ ፡
አብ፡መሃኪ፡ወአልዓሎሙ፡ዲበ፡ዐሮሙ።

ወእምድኅረ ፡ ውእቱ ፡ ኢአምኑ ፡ ቦቱ ፡
ወአግብኡ ፡ መድ፡ንኒሆሙ ፡ ለሞት ፡ በቅን
ዓቶሙ፡ላዕሌሁ።

ይቤ፡ላሕምኒ፡አእመረ፡ዘአጥረዮ፡ወአድግኒ፡
ምቅማሁ ፡ ወቤተ ፡ እግዚኡ ፡ እስራኤልሰ ፡
ኢየአመሩኒ፡ይትረጐም፡ከመ፡ለእመ፡ኮነ፡
እንስሳ፡እንተ፡አልቦ፡ልብ፡ቆመ፡ኀበ፡ወሰን፡
ዘሠርዖ ፡ ውእቱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወዘሰ ፡
አክበሮ፡በልቡና፡ወአግረረ፡ሎቱ፡ኵሎ፡
ዘኮነ፡ከሀዶ፡ውኀለፈ፡ትዕዛዞ፡ወበእንተ፡
ዝንቱ፡ዘለፎሙ፡ነቢይ፡ዘበእንስሳ።

ይቤ፡ወሕዝብየኒ፡ኢጠየቁኒ፡ይትረጐም፡
ከመ፡ውእቶሙ፡ኀደጉ፡እምኒሆሙ፡
አእምሮ፡ወኮኑ፡አብዳነ፡ውስተ፡አእምሮ፡
ፈጣሪሆሙ።

ይቤ፡አሌ፡ሎ፡ለሕዝብ፡ኃጥእ፡ዘምሉዕ፡
ዐመፃ፡ዘርዕ፡እኩያን፡ወውሉድ፡ጽልሕዋን፡
ወሀበ፡ወይሌ፡ለሕዝበ፡አይሁድ፡እስመ፡ኮኑ፡
ውእቶሙ፡ምሉኣነ፡ሕሊና፡እኪት፡ላዕለ፡መድ
ኀኒሆሙ።

ይቤ፡ዘርዕ፡እኩያን፡ወውሉድ፡ጽልሕዋን፡
አከ፡ዘርዕ፡እኩያን፡ዘእምኀቤሁ፡ለአብ
ርሃም፡ዳዕሙ፡ዘርዐ፡እኩይ፡ዲያብሎስ፡
አብሆሙ፡እስመ፡ተወልዱ፡እምኔሁ፡
በገቢረ፡ፈቃዱ፡ሎቱ።

ወበእንተ፡ውእቱኬ፡ይቤ፡በወንጌል፡ቅዱስ፡
አንትሙሰ፡እምአቡክሙ፡ሰይጣን፡አንትሙ፡
ወትፈቅዱ፡ለአቡክሙ፡ትገብሩ፡ፍትወቶ።

የዓርብ፡ነግህ።

፬፡ ልጆችን፡ወልጄ፡አሳደግሁ፡እነርሱ፡ግን፡ከዱኝ፡አለ፡እነዚህም፡የእስራኤል፡ልጆች፡እንደሆኑ፡ይተረጐማል።

፭፡ ከአሕዛብ፡ሁሉ፡በቀር፡ወደርሱ፡አቅርቧቸው፡ነበርና፡ለእነርሱም፡እንደ፡ርኅሩኅ፡አባት፡ሆናቸው፡በጠላቶቻቸውም፡ላይ፡ከፍ፡ከፍ፡አድርጓቸው፡ነበር።

፮፡ ከዚህም፡በኋላ፡አላመኑበትም፡በእርሱም፡ላይ፡ቀንተው፡መድኀኒታቸውን፡ለሞት፡አሳልፈው፡ሰጡ።

፯፡ ላም፡(በሬ)፡የገዛውን፡ዐወቀ፡አህያም፡ገለባ፡የሚበላበትንና፡የጌታውን፡ቤት፡ዐወቀ፡እስራኤል፡ግን፡አላወቁኝም፡አለ፡ይኸንም፡ልብ፡የሌለው፡እንስሳ፡ስንኳ፡እግዚአብሔር፡በወሰነለት፡ጸንቶ፡ሲኖር፡አእምሮ፡ሰጥቶ፡አክብሮ፡የፈጠረው፡ሁሉን፡እንዲያስገዛለት፡የሆነ፡ሰው፡ክዶ፡ትእዛዙን፡እንደ፡ተላለፈ፡ይተረጐማል፡ስለዚህም፡ነቢዩ፡ከእንስሳ፡አሳንሶ፡ዘለፋቸው።

፰፡ ወገኖቼ፡አላወቁኝም፡አልተረዱኝም፡አለ፡ይህንንም፡እነርሱ፡ፈጣሪያቸውን፡ከማወቅ፡ዘንግተው፡አእምሮአቸውን፡አጥተው፡ደናቍርት፡እንደሆኑ፡ይተረጐማል።

፱፡ ዐመፅን፡ለተመላ፡ኃጢአተኛ፡ወገን፡ወዮለት፡ክፋዎች፡ዘሮች፡ከዳተኞች፡ልጆች፡ናቸው፡አለ፡ወዮታን፡ለአይሁድ፡ወገኖች፡ሰጠ፡እነርሱም፡በመድኀኒታቸው፡ክርስቶስ፡ላይ፡ክፉ፡ሐሳብን፡የተመሉ፡ሁነዋልና።

፲፡ ክፉ፡ዘሮችና፡የሸንጋዮች፡ልጆች፡አለ፡ክፉ፡ዘሮችና፡ሸንጋዮች፡ከአብርሃም፡ወገን፡የተገኙ፡አይደሉም፡የክፉ፡የዲያብሎስ፡ዘር፡ናቸው፡እንጂ፡እነርሱ፡ከእርሱ፡ተወልደ ፈቃዱን፡በመፈጸም፡ቀልና።

፲፩፡ ስለዚህም፡የከበረ፡ወንጌል፡እናንተ፡ከአባታችሁ፡ከሰይጣን፡ናችሁ፡የእርሱንም፡ፈቃድ፡ለመፈጸም፡ትሻላችሁ፡ይላል።

Scanned by CamScanner

፩ዮ፫

## ዘዓርብ፡ጽባሕ።

፫፡፰ ወአጠየቀ፡ከመ፡ኵሉ፡ዘይገብር፡ምኑነ፡ኮነ፡ ተወልደ፡እምሰይጣን፤ ወኵሉ፡ዘይገብር፡ ትሩፋተ፡ኮነ፡ተወልደ፡እምእግዚአብሔር፡ ወመሠረተ፡ትሩፋትሰ፡ሃይማኖት፡ዘእግ ዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ።

፫፡፱ እስመ፡ይብል፡ሐዋርያ፡ወኵሉ፡ዘየአምን፡ ከመ፡ኢየሱስ፡ውእቱ፡ክርስቶስ፡ተወልደ፡ ውእቱ፡እምእግዚአብሔር።

፫፡፲ ወከማሁ፡ይቤ፡ካዕበ፡ሐዋርያ፡ወኵሉ፡ ዘተወልደ፡እምእግዚአብሔር፡ኢይገብራ፡ ለኃጢአት፡በእንተ፡ዘርዕ፡ዘይነብር፡ቦቱ፡ ወኢይክል፡አብሶ፤ እስመ፡እምእግዚአ ብሔር፡ተወልደ።

፫፡፲፩ ወበዝንቱ፡ይትአወቁ፡እሙራነ፡ደቂቀ፡እግ ዚአብሔር፡ወደቂቀ፡ጋኔን።

፫፡፲፪ ይቤ፡ውሉድ፡ጽልሕዋን፡ይተረጐም፡ ውእቱ፡ ከመ፡ናፈቁ፡ውእቶሙ፡ላዕለ፡ እግዚእ፡ በዐሊዎቶሙ፡ሎቱ፡ወኢተለውዎ፡ ለእግዚአብሔር፡ወተለውዎ፡ለሰይጣን፡በተ አዝዞቶሙ፡ሎቱ።

፫፡፲፫ ይቤ፡ወኀደግምዎ፡ለእግዚአብሔር፡ወአምዐ ዕክምዎ፡ለቅዱስ፡እሥራኤል፡ይተረጐም፡ ከመ፡አእተቱ፡እምአልባቢሆሙ፡ፍርሀተ፡ እግዚአብሔር፡ወሀደጉ፡ትዕዛዛቲሁ፡ለእግዚ አብሔር፡ወሕገጋቲሁ፡ካዕበ፡አምዕዕዎ፡በም ግባራቲሆሙ፡ርኩሳት።

፫፡፲፬ ይቤ፡ይእዜኒ፡ይትሜጠዉ፡ቍስላተ፡እስመ፡ ይዌስኩ፡ኃጢአተ፡በዲበ፡ኃጢአት፡ ይተረጐም፡ከመ፡ውእቱ፡በእንተ፡አዝል ፎቶሙ፡ላዕለ፡ኃጣውእ፡ወሕፀተ፡ሃይማ ኖቶሙ፡ወንስሐሆሙ፡እስመ፡ወሰኩ፡ኵሎ፡ ዕለተ፡ኃጢአተ፡እስመ፡ዘያዘልፍ፡ላዕለ፡ ኃጣውእ፡ኵሎ፡ሰዓተ፡ትትከዓበት፡ላዕሌሁ፡ ኃጣውኢሁ፡ወበእንተ፡ውእቱ፡ይርሕቅ፡እግ ዚአብሔር፡እምኔሆሙ፡ወያገብእሙ፤ ለዘኢ ይምሕሮሙ፡ወይረክቡ፡ሕማማተ፡ወምንዳ ቤያተ።

## የዓርብ፡ነግህ።

፫፡፰ የተናቀ፡ኃጢአትን፡የሚሠራ፡ሁሉ፡ ከሰይጣን፡የተወለደ፡እንደሆነ፡እስረዳ፡ ትሩፋትን፡የሚሠራ፡ሁሉ፡ከእግዚአብሔር፡ የተወለደ፡ነው፤ የትሩፋትም፡መሠረት፡ በጌታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡የሆነች፡ ሃይማኖት፡ናትና።

፫፡፱ ሐዋርያው፡ኢየሱስ፡መሲሕ፡እንደ፡ሆነ፡ የሚያምን፡ሁሉ፡ከእግዚአብሔር፡ተወለደ፡ ብሏልና።

፫፡፲ እንዲሁም፡ሐዋርያው፡ዳግመኛ፡ከእግዚአ ብሔር፡የተወለደ፡ሁሉ፡ኃጢአትን፡አይሠ ራትም፤ የተቀደሰው፡ዘር፡ክርስቶስ፡በእርሱ፡ ስለሚኖር፡ኃጢአትን፡መሥራት፡አይችልም፤ ከእግዚአብሔር፡ተወልዷልና፡አለ።

፫፡፲፩ ስለዚህም፡የእግዚአብሔር፡ልጆችና፡የጋኔን፡ ልጆች፡ተለይተው፡ይታወቃሉ።

፫፡፲፪ ሸንገላን፡የተመሉ፡ልጆች፡አለ፤ ይህንንም፡ እነርሱ፡ጌታን፡በመጠራጠራቸው፡እንደ፡ ከዱትና፡እግዚአብሔርን፡እንዳልተከተሉት፡ ለሰይጣን፡በመታዘዛቸው፡ተከታዮቹም፡ እንደሆኑ፡ይተረጐማል።

፫፡፲፫ በእሥራኤል፡ዘንድ፡የተመሰገነ፡እግዚአብ ሔርን፡እንዴት፡አሳዘናችሁት? እንዴትስ፡ ተዋችሁት፡አለ፤ ይኸንንም፡እግዚአብ ሔርን፡መፍራትን፡ከልባቸው፡እንዳስወ ገዱና፡ሕጉንም፡እንደተዉ፤ በረከሰች፡ይተረ ሥራቸው፡ዳግመኛም፡እንዳሳዘኑት፡ይተረ ጐማል።

፫፡፲፬ አሁንም፡ቍስልን፡ይቀበላሉ፤ እነርሱ፡ በኃጢአት፡ላይ፡ኃጢአትን፡ይጨምራሉና፡ አለ፤ ይኸንንም፡እነርሱ፡በኃጢአት፡ላይ፡ ኃጢአትን፡እንደ፡ማዘውተራቸውና፡ሃይማኖታ ቸውም፡ጎደሎ፡እንደሆነ፡ንስሐም፡እንደማ ይገቡ፡ይተረጐማል፤ ሁልቀን፡ኃጢአትን፡ ይጨምራሉና፤ በየሰዓቱ፡ኃጢአትን፡የሚያ ወትር፡በኃጢአቱ፡ላይ፡ኃጢአት፡እጥፍ፡ ድርብ፡ትሆናለች፤ ስለዚህም፡እግዚአብሔር፡ ከእርሱ፡ይርቃል፤ ለማይራራላቸውም፡አሳልፎ፡ ይሰጣቸዋል፤ ጽኑ፡መከራም፡ያገኛቸዋል።

ዘዓርብ፡ጽባሕ።

ይቤ፡ኵሉ፡ርእስ፡ለሕማም፡ወኵሉ፡ልብ፡
ለሐዘን፡እምእግር፡እስከ፡ርእስ፡ሕማም፡
ወቍስላት፡ይተረጐም፡ርእሰ፡ወልበ፡ነበ፡
ካህናት፡ወመኳንንት፡ወጠቢባን፡ወነገሥት፡
ወምዕማን፡ወእግረ፡በእንተ፡ሕዝብ፡
ዘያሀተ፡እደዊሆሙ፡እስመ፡እግዚአብሔር፡
ልዑል፡ይርሕቅ፡እምኔሆሙ፡እስከ፡
ያሐምሞሙ፡መዓት፡ለኵሎሙ፡እም ሕዝብ፡
እስከ፡ልዑል፡ወእመኰንን፡እስከ፡
መሰፍን።

ይቤ፡ወይጠይዕዎ፡ወኢያዐምምዎ፡
ይተረጐም፡ከመ፡አልቦ፡ዘይባልሆሙ፡
እመዓት፡እግዚአብሔር፡ወኢይረክቡ፡በም
ንዳቤሆሙ፡ነዛዜ።

ይቤ፡ምድርክሙኒ፡በድወት፡ወአህጉሪ
ክሙኒ፡ውእያ፡በእሳት፡ወለእክለ፡በሓውር
ቲክሙኒ፡ዐር፡ይቦልዖ፡በቅድሜክሙ፡
ተርጐመ፡ዘንተ፡በእንተ፡ዘረከብዎ፡
እምንጉሠ፡ሮም፡እስመ፡ውእቱ፡አውአየ፡
አህጉሪሆሙ ወረሰየ፡ምድሮሙ፡መዝበረ፡
ወበገቶሙ፡ወበልዓ፡ኵሎ፡እክለ፡በሐውር
ቲሆሙ፡እንተ፡ሎሙ፡እንዘ፡ውእቶሙ፡
ስጉታን፡ወቀተለ፡መብዝሕቶሙ፡በሰይፍ።

ይቤ፡ወትትኃደግ፡ወለተ፡ጽዮን፡ከመ፡
ዳስ፡ዐቃቢ፡ቀምሕ፡ወከመ፡ሀገር፡
ቅትልት፡ይተረጐም፡ከመ፡እለ፡ኮኑ፡
ወአምኑ፡ከመ፡ዐቀቦሙ፡እግዚአብሔር፡
እምአፈ፡ሰይፍ፡ወኮኑ፡ልዑላነ፡ውስተ፡
ማዕከሎሙ፡ለደቂቀ፡እሥራኤል፡
ዘውእቶሙ፡ወይን።

ይቤ፡ሶበ፡አኮ፡እግዚአብሔር፡ጸባኦት፡
ዘአትረፈ፡ለነ፡ዘርዐ፡ከመ፡ሰዶም፡እምኮነ፡
ወከመ፡ገሞራ፡እመሰልነ፡ይተረጐም፡ከመ፡
እግዚአብሔር፡ኢያህጐሎሙ፡ዳዕሙ፡
አትረፈ፡ዘርዕ፡እምኔሆሙ፡በእንተ፡

የዓርብ፡ነግህ።

፲፱፤ የሰው፡ሁሉ፡ራስ፡ለሕማም፡የሰው፡ሁሉ፡ልብ፡ለሐዘን፡ሆነ፤ከእግር፡ጀምሮ፡እስከ፡ራስ፡ድረስ፡ሕማምና፡ቍስል፡ሆነ፡አለ፤ራስና፡ልብን፡ስለ፡ካህናቱ፡ስለ፡መኳንንቱ፡ስለ፡ሊቃውንቱ፡ስለ፡ሹማምንቱና፡ስለ፡ነገሥታቱ፡እግር፡ያለውንም፡ከሥልጣናቸው፡በታች፡ስላሉት፡ስለ፡ሕዝቡ፡ይተረጐማል፤ልዑል፡እግዚአብሔርም፡በረድኤት፡ከእርሳቸው፡ይርቃልና፡ከሕዝቡ፡እስከ፡ካህናቱ፡ከመኳንንቱ፡እስከ፡መሳፍንቱ፡ድረስ፡ሁሉንም፡በመዐት፡ይቀጣቸዋልና።

፳፤ መድኃኒት፡ቀብተው፡የሚያድኑት፡የሚያደርቁት፡አይደለም፡አለ፤ይኸንንም፡ከእግዚአብሔር፡ቁጣ፡የሚያድናቸው፡እንደሌለ፤በመከራቸውም፡የሚያጽናናቸው፡እንደማያገኙ፡ይተረጐማል።

፳፩፤ አገራችሁም፡ምድረ፡በዳ፡ሆነች፤ከተሞቻችሁም፡በእሳት፡ተቃጠሉ፤የሀገሮቻችሁንም፡እህል፡ጠላት፡በፊታችሁ፡ይበላዋል፡አለ፤ይኸንንም፡ከሮም፡ንጉሥ፡ስለ፡አገኙት፡መከራ፡ይተረጐማል፤እርሱ፡ከተሞቻቸውን፡አቃጥሎ፡አገራቸውን፡ጠፍ፡አድርጓልና፡እነርሱንም፡ከብቦ፡የሀገራቸውን፡እህል፡ዘርፎአልና፡እነርሱም፡የተከበቡ፡ሲሆኑ፡ብዙዎቻቸውን፡በሰይፍ፡አጥፍቷልና።

፳፪፤ የጽዮን፡ልጅ፡እንደ፡ወይን፡ጠባቂ፡ዳስና፡እንደ፡ተክል፡ጠባቂ፡ጎጆ፡በጦር፡እንደ፡ጠፋች፡ከተማ፡ሁና፡ትቀራለች፡አለ፤ይኸንንም፡የአመኑትን፡እግዚአብሔር፡ከሰይፍ፡ስለት፡እንደሚጠብቃቸው፡በእስራኤልም፡ልጆች፡መካከል፡ከፍ፡ከፍ፡ብለው፡እንደነበር፡እነርሱም፡የወይን፡ተክል፡እንደ፡ተባሉ፡ይተረጐማል።

፳፫፤ አሸናፊ፡እግዚአብሔር፡ዘርን፡ያስቀረልን፡ባይሆን፡ኖሮ፡እንደ፡ሰዶም፡በሆንን፡ነበር፤እንደ፡ገሞራም፡በመሰልን፡ነበር፡አለ፤ይኸንንም፡ጌታ፡ሁሉንም፡ስለ፡ኃጢአታቸው፡ሕጻጽና፡ከዚያ፡በኋላ፡በሃይማኖት፡

ዘዓርብ፡ጽባሕ።

ሐበዐ፡ኃጢአቶሙ፡ወበእንተ፡አእምሮቱ፡
በእንተ፡ተመይጦቶሙ፡ኃቤሁ፡በሃይማ
ኖቶሙ፡ቦቱ፡እምድኅረ፡ውእቱ፡ወዛቱ፡
ይእቲ፡ዘርዕ፡እንተ፡ዘከረ፡ነቢይ።

፳፱፡ ወንስአሎ፡ **ለእግዚእነ**፡ከመ፡ያርህቅ፡
እምኔነ፡መዓቶ፡ወይሣሃል፡ላዕሌነ፡
በምሕረቱ፡ሎቱ፡ስብሐት፡ለዓለመ፡ዓለም፡
ወያንቅህነ፡ለገቢረ፡ፈቃዱ፡አሜን።

ዘኢሳይያስ፡ነቢይ፡በረከተ፡አምላኩ፡ትኩን፡
ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ምዕ፡፴፫፡፭–፳፬።

፭፡ **ቅዱስ፡እግዚአብሔር**፡ዘየኀድር፡ውስተ፡
ጽዮን፡ወውስተ፡አርያም፡ወመልዐት፡
ጽዮን፡ጽድቀ፡ወርትዐ።

፮፡ ወያስተጋብእዎሙ፡በሕግ፡ውስተ፡
መዛግብተ፡መድኃኒት፡መጽእት፡ጥበብ፡
ወምክር፡ወጽድቅ፡በኀበ፡**እግዚአብሔር**፡
እስመ፡ተረክበት፡መዛግብተ፡ጽድቅ።

፯፡ ናሁ፡እምግርማክሙ፡ፈርሁክሙ፡እለ፡
ቀዲሙ፡ትፈርህዎሙ፡አንትሙ፡ወትርዕዱ፡
እምኔሆሙ፡ወይትፈነዉ፡ሐዋርያት፡እንዘ፡
መሪረ፡ይበክዩ፡ወይስእሉ፡ሰላመ።

እስመ፡ማሰነ፡ፍናዊሆሙ፡ወኀለፈ፡
ግርማሆሙ፡ለአሕዛብ፡ወተሠዐረ፡
ኪዳኖሙ፡ወኢትረስይዎሙ፡ከመ፡ዕደው።

ለሐወት፡ምድር፡ወተኀፍረ፡ሊባኖስ፡ዖመ፡
ኮነ፡ሳሮን፡ወተዐውቀ፡ገሊላ፡ወቀርሜ
ሎስኒ።

ናሁ፡ይእዜ፡እትነሣእ፡ይቤ፡**እግዚአብሔር**፡
ይእዜ፡እሴባሕ፡ወይእዜ፡እትሌዓል፡አነ።

ይእዜ፡ትሬእዩ፡ወይእዜ፡ታኀክሩኒ፡
ይከውን፡ከንቶ፡ኃይለ፡መንፈስክሙ፡
ወእሳት፡ትበልዐክሙ።

የዓርብ፡ነግህ።

ወደ፡እርሱ፡መመለሳቸውን፡ስለሚያውቅ፡
እንዳላጠፋቸው፡ይተረጕማል፡ነቢዩም፡
ያወሳት፡የተናገራት፡ዘር፡ይህች፡ሥጋዊ
ናት።

፳፱፡ በመሐሪነቱ፡መዐቱን፡ከእኛ፡አርቆ፡ይቅር፡
ይለን፡ዘንድ፡**ጌታችንን**፡እንለምነው፡
ለእርሱም፡ክብር፡ምስጋና፡ለዘላለም፡
ይሁን፤እርሱ፡የሚወደውንም፡ለመሥራት፡
ያነቃቃን፡አሜን።

የአምላኩ፡በረከት፡ከእኛ፡ጋራ፡ለዘላለም፡
ትኑርና፡ነቢዩ፡ኢሳይያስ፡የተናገረው፡
ትንቢት፡ይህ፡ነው።

ምዕ፡፴፫፡፭–፳፬።

፭፡ በከፍታና፡በጽዮን፡የሚኖር፡**የተመሰገነ፡እግ
ዚአብሔር**፡በመካከላችሁ፡በረድኤት፡
ይኖራል፤ጽዮንም፡የቀና፡ፍርደኝ፡
እውነት፡ነገርን፡ተመላች።

፮፡ ድኅነት፡ወደሚደረግባት፡ወደ፡ኢየሩሳሌም፡
በሕግ፡ይሰበስቧቸዋል፤**ከእግዚአብሔር**፡
ዘንድ፡እውነት፡ጥበብ፡ምክርም፡መጣች፡
እውነት፡ተገኝታለችና።

፯፡ ቀድሞ፡እናንተ፡ትፈሩዋቸውና፡ከእነርሳ
ቸውም፡የተነሣ፡ትንቀጠቀጡ፡የነበረ፡
አሕዛብ፡እነሆ፡ከግርማችሁ፡የተነሣ፡
ፈሩዋችሁ፡መልእክተኞችም፡ጽኑ፡ልቅሶን፡
እያለቀሱ፡ይላካሉ፡ሰላምን፡ይለምናሉ።

፰፡ ጐዳናቸው፡ጠፍቷልና፡የአሕዛብ፡መፈራት
ቸውም፡ቀርቷልና፤መሐላቸውም፡
ፈርሷልና፡እንደ፡ወንዶች፡አታድርጓቸው።

፱፡ ምድር፡አለቀሰች፤ሊባኖስም፡አፈረ፡
(ንጉሡ)፡አክርማው፡ዛፍ፡ሆነ፤ገሊላም፡ከቀ
ርሜሎስ፡ጋራ፡በጥፋት፡ታወቀ።

፲፡ ያን፡ጊዜ፡**እግዚአብሔር**፡በረድኤት፡
እነሣለሁ፤አሁንም፡እመሰገናለሁ፤አሁንም፡
እኔ፡ከፍ፡ከፍ፡እላለሁ፡አለ።

፲፩፡ አሁን፡ታዩኛላችሁ፤ዛሬ፡ታደንቁኛላችሁ፡
የልቡናችሁም፡ዕውቀት፡ከንቱ፡ይሆናል፡
እሳትም፡(ጦር)፡ታቃጥላችኋለች።

## ዘዓርብ፡ጽባሕ።

፲፱ ወይከውኑ ፡ አሕዛብ ፡ ከመ ፡ ዋዕየ ፡ ሦክ ፡
ዘነደም፡ውዑያን፡ወግዱፋን።

፳ ወይሰምዑ ፡ ዘገበርኩ ፡ እለሂ ፡ እምርሑቅ ፡
ወእለሂ፡እምቅሩብ፡ወየአምሩ፡ኃይልየ።

፳፩ ወለዉ ፡ እለ ፡ ውስተ ፡ ሰማርያ ፡ ወአመፀኒ ፡
ወናሁ፡ይእኀዞሙ፡ረዓድ፡ለኃጥአን፡ወለአማ
ጽያን ፡ መኑ ፡ ይነግረክሙ ፡ ከመ ፡ እሳት ፡
ትነድድ፡መዐትየ።

፳፪ ወመኑ ፡ ይነግረክሙ ፡ ብሔረ ፡ ዘለ
ዓለም ፡ ዘየሐውር ፡ በጽድቅ ፡ ወዘይ
ነብብ ፡ ርትዐ ፡ ዘይጸልእ ፡ ፍኖተ ፡
በመፃ ፡ ዘይጸልእ ፡ ኃጢአተ፡ ወጽልሑተ ፡
ወዘይመይጥ ፡ እደዊሁ ፡ እምሕልያን ፡ ዘይ
መይጥ ፡ እዝኖ ፡ ከመ ፡ ኢይስማዕ ፡ ኵነኔ ፡
ነፍስ ፤ ወዘይከድን ፡ ዐይኖ ፡ ከመ ፡ ኢይ
ርአይ፡ግፍዐ።

፳፫ ዘከመዝኬ ፡ ይነብር ፡ ውስተ ፡ ልዑል ፡ በአተ
ኵሐ ፡ ጽኑዕ ፡ ወይትወሀቦ ፡ እክልሂ ፡
ወማይሂ፡በጽድቅ።

፳፬ ወትሬእይዎ ፡ ለንጉሥ ፡ ምስለ ፡ ስብሐት ፡
ወይሬእያ፡አዕይንቲክሙ፡ምድረ፡ርሁቀ።

፳፭ ወትትሔዘብ ፡ ነፍስክሙ ፡ ፍርሃተ ፡ አይቴ ፡
ሀለዉ ፡ ጸሐፍት ፡ ወአይቴ ፡ እሙንቱ ፡
መማክርት። ወአይቴ ፡ ሀሎ ፡ ብዝሖሙ ፡ ለዐላ
ውያን፡ንዑሱ፡ወዐቢዩ።

፳፱ ወአመጽእ ፡ ላዕሌክሙ ፡ አሕዛበ ፡ እለ ፡
ኢተአምሩ ፡ ወትሰምዑ ፡ ነገረ ፡ እሙቀ ፡
ሕዝብ፡ ዐላውያን ፡ ወዘኒ ፡ ይሰምዕ ፡ ከመ ፡
ዘአልቦ፡ልብ።

፴ ነየ፡ጽዮን፡ሀገረ፡መድኃኒትነ፡ወትሬእዩ፡
በአዕይንቲኪ፡ኢየሩሳሌም፡ሀገር፡ብዕልት፡
ወአብያቲሃኒ ፡ ዘኢያንቀለቅሉ ፡ ወዘኢይት
ሐወስ፡መታክሊ፡ደብተራሃ፡ለዓለመ፡ዓለም፤
ወአሕባሊሃኒ፡ዘኢይትበተኩ።

## የዓርብ፡ነግህ።

፲፱፤ አሕዛብም ፡ እሳት ፡ እንዳቃጠለው ፡ እንደ ፡
ምድረ ፡ በዳ ፡ እሾኽ ፡ የወደቁ ፡ የታቀጠሉ ፡
ይሆናሉ።

፳፤ በሩቅ ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡ ያደረግሁትን ፡ ይሰማሉ ፤
በቅርብም፡ያሉ፡ኃይሌን፡ያውቃሉ።

፳፩፤ በሰማርያ ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ወነጀሉኝ ፤
(በደሉኝ)፡እነሆ፡በደለኞችና፡ኃጢአተኞች፡
ሰዎችን ፡ እንቅጥቅጥ ፡ ይይዛቸዋል ፤ ቁጣዬ ፡
እንደ፡እሳት፡እንድትነድ፡ማን፡በነገራችሁ።

፳፪፤ በእውነት ፡ ሥራ ፡ ጸንቶ ፡ የሚኖር ፤ የቀና ፡
ነገርንም፡ የሚናገር ፡ የበደልንም ፡ ሥራ ፡
የሚጠላ፡ ሽንገላንና ፡ ኃጢአትንም ፡ የሚጠላ ፡
እጁንም ፡ መማለጃ ፡ ከመቀበል ፡ የሚሰበስብ ፡
የነፍስን ፡ ፍርድ ፡ እንዳይሰማ ፡ ጆሮውን ፡
የሚመልስ፡የድኃውን፡ግፍ፡እንዳያይ፡ዐይኑን፡
የሚሸፍን ፡ ሰው ፡ በአገሩ ፡ ለዘላለሙ ፡ በተድላ ፡
በደስታ፡እንዲኖር፡ማን፡በነገራችሁ።

፳፫፤ እንዲህ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ በጽኑ ፡ ዋሻ ፡
ይኖራል ፤ እኽል ፡ ውኃም ፡ በእውነት ፡
ይሰጠዋል።

፳፬፤ ንጉሡንም ፡ ከጌትነቱ ፡ ጋራ ፡ ታዩታላችሁ ፤
ዐይኖቻችሁም፡በሩቅ፡ያለች፡አገርን፡ያያሉ።

፳፭፤ ልቡናችሁ ፡ መፍራትን ፡ ትጠራጠራለች ፤
ጸሐፊዎች፡ወዴት፡አሉ?መካሮችስ፡ወዴት፡
አሉ ? የታላቁና ፡ የታናሹ ፡ ወንጀለኞች ፡
ብዛትስ፡ወዴት፡አለ?

፳፱፤ የማታውቋቸው ፡ አሕዛብን ፡ አመጣባች
ኋለሁ፤እናንተ ፡ ወንጀለኞች ፡ ሰዎች ፡ ጥልቅ ፡
ነገርን ፡ ትሰማላችሁ ፤ ዕውቀት ፡ ያለውም ፡
ዕውቀት፡እንደሌለው፡ይሆናል።

፴፤ ድኅነታችን ፡ የሚደረግባት ፡ ዐይኖቿ ፡ የጠላ
ቶቿን ፡ ጥፋት ፡ የሚያዩ ፡ በአዝርዕት ፡ በአት
ክልት፡የከበረች፡ቤቶቿ፡የማይነዋወጡ፡የድ
ንኳኗም ፡ ካስማ ፡ ለዘላለሙ ፡ የማይነቀሉ ፡
አውታሮቿም ፡ የማይቆረጡ ፡ ጽዮን ፡ ኢየሩ
ሳሌም፡እነኋት።

Scanned by CamScanner

## ዘዓርብ፡ጽባሕ።

፳፩፡ እስመ፡ስመ፡እግዚአብሔር፡ዐቢይ፡ለክሙ፡ ወይከውን ፡ ብሔርክሙ ፡ አፍላገ ፡ ማይ ፡ ወሙሐዘ፡ማይ፡ዐቢይ፡ወርሒብ፡ወስፉሀ፡ ወዘኢየሐውሩ ፡ እንከ ፡ ዛተ ፡ ፍኖተ ፡ አሕማርኒ፡ኢየሐውራ።

፳፪፡ እስመ ፡ ዐቢይ ፡ ውእቱ ፡ አምላክነ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወኢይትሔየየነ ፡ እግዚአብሔር ፡ መኰንንነ፡እግዚአብሔር፡አምላክነ፡ወእግዚአብሔር ፡ ንጉሥነ ፡ ውእቱ ፡፡ ወእግዚአብሔር፡ያድኅነነ።

ዘኤርምያስ ፡ ነቢይ ፡ በረከተ ፡ አምላኩ ፡ ትኩን፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን።

ምዕ፡፳፪፡፳፱-፴።

፳፱፡ ምድር፡ምድር፡ምድር፡ስምዒ፡ቃለ፡እግዚአብሔር።

፴፡ ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡ጸሐፎ፡ለዝ፡ብእሲ፡ከመ፡ዘሞተ፡እስመ፡ኢይሤራሕ፡በመዋዕሊሁ ፡ ወኢይሤራሕ ፡ እምዘርዑ ፡ ዘይነብር፡ውስተ፡መንበረ፡ዳዊት፡መኰንነ፡እንከ፡ለይሁዳ።

ምዕ፡፳፫፡፩-፯።

፩፡ ወይ ፡ ለክሙ ፡ ለኖሎት ፡ ቀታልያነ ፡ እለ ፡ ትዘርዉ፡አባግዐ፡መርዔትየ፡ይቤ፡እግዚአብሔር።

፪፡ በእንተ፡ዝንቱ፡ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡አምላከ፡እሥራኤል፡በእንተ፡ኖሎት፡እለ፡ይርእይዎሙ፡ለሕዝብየ፡አንትሙ፡ዘረውክምዎሙ፡ለአባግዕየ፡ወሰደድክምዎሙ፡ወኢሐለይክምዎሙ፡አንትሙ። ናሁ፡አነ፡እትቤቀለክሙ፡በከመ፡እከየ፡ምግባሪክሙ፡ይቤ፡እግዚአብሔር።

፫፡ ወአነ፡አስተጋብእሙ፡ለእለ፡ተርፉ፡ሕዝብየ፡እምኵሉ፡በሐውርት፡ኀበ፡ዘረውክምዎሙ፡ውነበ፡ወሰድክምዎሙ፡ህየ፡ወአገብኦሙ፡ውስተ፡ጊዶቶሙ፡ወይበዝኁ፡ወይመልኡ።

## የዓርብ፡ነግህ።

፳፩፤ የእግዚአብሔር፡ስም፡ለእናንተ፡ደግ፡ነውና፡ አገራችሁ፡የውኃ፡መፍሰሻ፡የመስኖ፡አገር፡ ሰፊ ፡ ይሆናል ፡ እንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ በዚች፡ ጐዳና ፡ አይሄዱም ፡ መርከቦችም ፡ በዚች፡ ጐዳና፡አያልፉም።

፳፪፤ ፈጣሪያችን፡እግዚአብሔር፡ታላቅ፡ነውና፡ ቸል፡አይለንም፤እግዚአብሔር፡ገዢያችን፡ ነው፤እግዚአብሔር፡ፈጣሪያችን፡ነው፡እግዚአብሔር፡ንጉሣችን፡ነው፤እርሱ፡እግዚአብሔርም፡ከመከራ፡ያድነናል።

የአምላኩ፡በረከት፡ከእኛ፡ጋር፡ለዘላለሙ፡ ትኑርና ፡ ነቢዩ ፡ ኤርምያስ ፡ የተናገረው፡ ትንቢት፡ይህ፡ነው።

ምዕ፡፳፪፡፳፱-፴።

፳፱፤ ምድር ፡ ምድር ፡ ምድር ፡ የእግዚአብሔርን፡ ቃል፡ስሚ።

፴፤ እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለ፤በዘመኑ፡አይከናወንምና ፡ ከልጁም ፡ በዳዊት ፡ ዙፋን፡ የሚቀመጥ ፡ አይነሣምና ፡ እንግዲህ ፡ ወዲህም፡ ለይሁዳ ፡ ገዥ ፡ አይሾምምና፡ ይኸንን፡ሰው፡እንደ፡ሞተ፡ቁጠረው፡አለ።

ምዕ፤፳፫፡፩-፯።

፩፤ እግዚአብሔር ፡ ነፍስ ፡ ለምትገድሉ ፡ የበጎቼንም ፡ መንጋ ፡ ለምትበትኑ ፡ ለናንተ፡ ለእረኞች፡ለመምህሮች፡ወዮላችሁ፡አለ።

፪፤ ስለዚህ፡የእስራኤል፡ፈጣሪ፡እግዚአብሔር፡ ወገኖቼን ፡ ስለሚጠብቁ ፡ እረኞች ፡ (መምህራን)፡ እንዲህ ፡ ይላል ፤ እናንተ፡ በጎቼን፡ በተናችኋቸው ፤ አስማረካችኋቸው፤ አላሰባችኋቸውም፤እንደ፡ሥራችሁ፡ክፋት፡ መጠን ፡ እነሆ ፡ በመዐት ፡ እጐበኛችኋለሁ፡ ይላል፡እግዚአብሔር።

፫፤ ከሞት ፡ የቀሩ ፡ ወገኖቼን ፡ ከበተናችኋቸው፡ አስማርኳ ፡ ከአስወሰድኋቸው ፡ ከእነዚያ፡ አገሮች፡ሰብስቤ፡ወደ፡በረታቸው፡እመልሳቸዋለሁ፤በዚያም፡በዝተው፡ይመላሉ፡አለ።

Scanned by CamScanner

ዘዓርብ፡ጽባሕ።

፬ ወእሠይም ፡ ሎሙ ፡ ኖሎተ ፡ እለ ፡ ይርዕይዎሙ፡ ወይርዕይዎሙ ፡ ወኢ ይፈርሁ ፡ እንከ፡ ወኢይደነግፁ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር።

፭ ናሁ ፡ ይመጽእ ፡ መዋዕል ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር፡ ወአቀውም ፡ ለዳዊት ፡ ሠርፀ ፡ ጽድቅ ፡ ወይነግሥ ፡ ንጉሥ ፡ ዘይሄሊ ፡ ወይገብር ፡ ጽድቀ ፡ ወርትዐ ፡ በዲበ፡ምድር።

፮ ወበመዋዕሊሁ ፡ ይድኅን ፡ ይሁዳ ፡ ወእሥራኤልኒ ፡ ይነብር ፡ ተአሚኖ ፡ ወዝውእቱ ፡ ስሙ ፡ ዘሰመዮ ፡ እግዚአብሔር፡ኢዮሴዴቅ።

ትርጓሜ፡ትንቢተ፡ኤርምያስ።

ምድር፡ምድር፡ምድር፡ስምዒ፡እስከ፡ኀበ፡ ይብል፡ይነብር፡ተአሚኖ።

፩ ይቤ፡መተርጕም፡ምድር፡ስምዒ፡ቃለ፡እግዚአብሔር፡ ኢኮነ፡ ነቢይ፡ ዘይብል፡ በእንተ፡ ምድር፡ ባሕቲታ ፡ አላ ፡ በእንተ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው፡እለ፡ይነብሩ፡ዲበ፡ምድር፡እስመ፡ ዐቀቦሙ፡ከመ፡ያጽምዑ፡ለሰሚዐ፡ቃለ፡እግዚአብሔር፡ዘይትነገር፡ቦቱ፡በልሣኑ።

፪ ይቤ፡ጸሐፊዮ፡ለዝንቱ፡ብእሲ፡ከመ፡ዘሞተ፡ እስመ፡ ኢይሤራሕ፡ በመዋዕሊሁ፡ ወኢይሤራሕ፡ እምዘርዑ ፡ ዘይነብር ፡ ውስተ ፡ መንበረ፡ ዳዊት፡ መኰንን፡ እንከ፡ ለይሁዳ፡ ይተረጐም፡ በእንተ፡ ብእሲ፡ ኀበ፡ ነገሥተ፡ እሥራኤል፡ ወለእመኒ፡ ተናገረ፡ በእንተ፡ አሐዱ፡እስመ፡ቃል፡ያኀብሮሙ፡ለኵሎሙ።

፫ ወካዕበ፡ ለዝ፡ ብእሲ፡ ምኑን፡ ዘውእቱ፡ ነገሩ፡ ምኑናተ፡ ቅድመ፡ እግዚአብሔር፡ ወአሰምዑ፡ ላዕሌሆሙ፡ ነቢያት፡ በመጻሕፍቲሆሙ ፡ ከመ፡ እኩያን ፡ ወምኑናን ፡ ውእቶሙ።

፬ ይቤ፡ወኢይከውን፡ሎቱ፡ዘርዕ፡እምከርሡ፡ ይተረጐም፡ ከመ፡ እምድኅረ፡ ምጽአተ፡ ክርስቶስ፡ኢኮነ፡ሎሙ፡መንግሥት፡ወኢይ

የዓርብ፡ነግህ።

፬፡ የሚጠብቋቸው ፡ እረኞችን ፡ እሾማለሁ ፡ ነቅተው፡ተግተው፡ይጠብቋቸዋል፤ከዚያም፡ በኋላ፡አይፈሩም፤አይደንግጡም፡ይላል፡እግዚአብሔር።

፭፡ እግዚአብሔር፡እነሆ፡እንዲህ፡ያለ፡ወራት፡ ይመጣል፡አለ፡ለዳዊት፤ዕውነተኛ፡ልጅ፡አስነሣለሁ፤ አስቦ፡ ዕውነት፡ ፍርድንና፡ የቀና፡ ሥራንም፡የሚሠራ፡ንጉሥ፡በምድር፡ላይ፡ ይነግሣል።

፮፡ በርሱም ፡ ዘመን ፡ ይሁዳ ፡ ይድናል ፤ እስራኤልም፡ ተዘልሎ፡ ይኖራል፤እግዚአብሔር፡ ያወጣለት፡ ስሙም፡ ይህ፡ ነው፤ ኢዮሴዴቅ፡ ይባላል።

የኤርምያስ፡ትንቢት፡ትርጓሜ።

ምድር ፡ ምድር ፡ ምድር ፡ ስሚ ፡ ከሚለው ፡ ጀምሮ፡ተዘልሎ፡ይኖራል፡እስከሚለው።

፩፡ ተርጓሚው፡ምድር፡የእግዚአብሔርን፡ቃል፡ ስሚ ፡ አለ ፤ ነቢይ ፡ ስለምድር ፡ ብቻ ፡ ይህን ፡ ያለ፡ አይደለም ። በምድር ፡ ላይ ፡ ስለሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በአንደበቱ ፡ የሚናገር በትን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ለመስማት ፡ ያደምጡ፡ዘንድ፡አሳውቋቸዋልና።

፪፡ በዘመኑ፡አይከናወንምና፡ከልጁም፡በዳዊት፡ ዙፋን፡የሚቀመጥ፡አይነሣምና፡ለይሁዳም፡ ገዢ ፡ እንግዲህ ፡ አይነሣምና ፡ ይህን ፡ ሰው ፡ እንደሞተ ፡ ቁጠሪው ፡ አለ ፤ ከእስራኤል ፡ ነገሥታት፡ስለ፡ነገሠው፡ሰው፡ይተረጐማል፤ ስለ፡ሌላውም፡ስለ፡አንዱ፡ሰው፡ቢናገርም፡ ቃሉ፡አንድ፡ያደርጋቸዋል።

፫፡ ሁለተኛም፡ለዚህ፡ለተናቀ፡ሰው፡የሚለው፡ ይህ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ የተናቀ ፡ ኃጢአትን፡ ሠርተዋልና፤ እነርሱ፡ የተናቁ፡ ክፉዎች ፡ እንደሆኑ ፡ በመጻሕፍቶቻቸው ፡ ነቢያት፡መስክረውባቸዋል።

፬፡ ለእርሱ፡ዘር፡አይወጣለትም፡አለ፤ክርስቶስ፡ ከመጣ ፡ በኋላ ፡ ከዘራቸው ፡ የሚነግሥላ ቸውና፡ተስፋ፡የሚያደርጉትም፡መንግሥት፡

Scanned by CamScanner

ዘዓርብ፡ጽባሕ።

ሴፌዉ፡እምዘርዖሙ፡ዘይነግሥ፡ላዕሌሆሙ፡
ይቤ ፡ ወኢይነብር ፡ እምይእዜ ፡ መኰንን ፡
ላዕለ፡ቤተ፡ይሁዳ፡ወኢለካልኡ።

፭፡ ይቤ፡ወይ፡ለክሙ፡ለኖሎት፡ቀታልያን፡እለ፡
ትዘርዉ ፡ ዓባግዐ ፡ መርዔትየ ፤ ይተረጐም ፡
በእንተ፡ኖሎት፡ኀበ፡ካህናት፡ወምእመናን፡
ዘለደቂቀ፡እሥራኤል፡እስመ፡በቅንአቶሙ፡
አኅጐሉ ፡ ነፍሳቲሆሙ ፡ ወነፍሳተ ፡
መርዔቶሙ ፡ እስመ ፡ ለመርዔቶሙሰ ፡ ኮነ ፡
ያስተርኢ ፡ ሎሙ ፡ ጽድቅ ፡ ወአምኑ ፡ በክር
ስቶስ።

፮፡ ወኮኑ ፡ ያጸንዕዎሙ ፡ ወያጌብርዎሙ ፡ ከመ ፡
ይክሀድዎ፡ሎቱ፡ወይቤልዎሙ፡ርኢክሙኑ፡
ከመ፡አሐዱሂ፡እምጸሐፍት፡ወእምካህናት፡
ዘአምነ፡ቦቱ፡እንበለ፡ዘኢየአምሩ፡መጽሐፈ፡
ወአሕረሙ ፡ እመቦ ፡ ዘአምነ ፡ በክርስቶስ ፡
ያውጽእዎ፡እምኵራቦሙ።

፯፡ ይቤ፡በእንተ፡ዝንቱ፡ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአ
ብሔር ፡ ለእለ ፡ ይርዕይዎሙ ፡ ለሕዝብ ፡
አንትሙ ፡ ዘረውክሙ ፡ አባግዕየ ፡ ወሰደድክ
ምዎሙ ፡ ወኢዋሐይክምዎሙ ፤ ናሁ ፡ አነ ፡
እትቤቀለክሙ፡በከመ፡እከየ፡ምግባሪክሙ።

፰፡ ይተረጐም ፡ ከመ ፡ እግዚአብሔር ፡
ይትቤቀል፡ እምአርእስት ፡ እለ ፡ ያማስኑ ፡
አልባበ ፡ ሕዝቦሙ ፡ ወያጌብርዎሙ ፡ ከመ ፡
ይግበሩ፡ተዓድዎ፡ጽድቅ፡ወያጐይይዎሙ፡
እምፈቃደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወኢፈቀዱ ፡
ከመ፡ ይዋሕይዎሙ ፡ ወኢሜጥዎሙ ፡ ኀበ ፡
አእምሮ፡እግዚአብሔር፡ልዑል።

፱፡ ይቤ፡ወእትቤቀለክሙ፡በከመ፡እከየ፡ምግባ
ሪክሙ ፡ ዝ ፡ ውእቱ ፡ ዘይፈድዮሙ ፡ በእንተ ፡
ኃጣውኢሆሙ ፡ ወበእንተ ፡ ኃጣውአ ፡
ሕዝቦሙ ፡ እስመ ፡ ኢጣይዕዎሙ ፡ በትም
ሀርት፡አምላካዊት።

የዓርብ፡ነግህ።

ለእነርሱም፡እንደማይሆን፡ይተረጐማል፡ከእ
ንግዲህ ፡ ለይሁዳ ፡ ወገን ፡ ለባልንጀራውም፡
ገዢ፡አይኖርም።

፭፡ ለእናንተ ፡ ለነፍስ ፡ ገዳዮች ፡ የበጎቼንም፡
መንጋ ፡ ለምትበትኑ ፡ ወዮላችሁ ፡ አለ፤
ይኸንንም ፡ ስለ ፡ እስራኤል ፡ ልጆች ፡
ካህናትና፡ ምእመናን ፡ ይተረጐማል ፤
እነርሱም ፡ በመቅናታቸው ፡ የራሳቸውንና፡
የመንጋዎቻቸውን ፡ ነፍስ ፡ አጥፍተዋልና፤
መንጋዎቻቸው፡ግን፡እውነት፡ነገር፡ተገልጾ
ላቸው፡በክርስቶስ፡አመኑ።

፮፡ ካህናቶቻቸውም፡የሕዝቡን፡ልብ፡እያጠነከሩ፡
ይክዱት ፡ ዘንድ ፡ ግድ ፡ ይሏቸዋል ፤ እንዲህም፡
አሏቸው ፤ ከእነዚህ ፡ መጻሕፍትን ፡ ከማያውቁ፡
ሰዎች ፡ በቀር ፡ ከካህናትና ፡ ከጸሐፍት ፡ አንድ፡
እንኳ ፡ ያመነበት ፡ አይታችኋልን? ከማኅበ
ቸውም፡ጋር፡በክርስቶስ፡ያመነ፡ቢኖር፡ከምኩ
ራባቸው፡ያስወጡት፡ዘንድ፡ወሰኑ።

፯፡ ሕዝቡን ፡ የሚጠብቁትን ፡ መምህራን፡
እናንተ፡በጎቼን፡በተናችኋቸው፡አስማረካች
ኋቸው ፤ አልጐበኛችኋቸውም ፤ እኔም፡እንደ
ሥራችሁ፡ክፋት፡እበቀላችኋለሁ፡ብሎ፡እግ
ዚአብሔር፡እንደዚህ፡ተናገረ፡አለ።

፰፡ ከጽድቅ ፡ መንገድ ፡ ይተላለፉ ፡ ዘንድ ፡
የሕዝቡን፡ ልቡና ፡ የሚያበላሹ ፤ ከአለቆች፤
ጀምሮ ፡ እግዚአብሔር ፡ እርሱ ፡ እንደሚበቀ
ላቸው፡ይተረጐማል፤እነርሱ፡ልዑል፡እግዚአ
ብሔርን፡ወደማወቅ፡አስተምረው፡አይመል
ሷቸውም፤ጽድቅን፡ተላልፈው፡ኃጢአትን፤
ይሠሩ ፡ ዘንድ ፡ ያስገድዷቸዋል ፤ የእግዚአብ
ሔርን፡ፈቃድ፡ከመፈጸም፡ያርቋቸዋል፡እንዲ
ይጐበኟቸውም፡ዘንድ፡አይወዱም።

፱፡ እንደሥራችሁ፡ክፋት፡እበቀላችኋለሁ፡አለ፤
ይኸውም፡ስለ፡ኃጢአታቸውና፡ስለ፡ሕዝቡ፡
ኃጢአት ፡ የሚከፍላቸው ፡ ፍዳ ፡ ነው ፤
ከአምላክ ፡ በተገኘች ፡ ትምህርት ፡ አስተ
ምረው፡አላዳኑአቸውምና።

Scanned by CamScanner

ዘዓርብ፡ጽባሕ።

ይቤ፡እግዚእነ፡አነ፡ካዕበ፡እከውኖሙ፡
ናባዪ፡ለእለ፡ተርፉ፡ሕዝብየ፡አስተጋ
ብኦሙ፡እምኵሉ፡ምድር፡እለ፡ተክዕዉ፡
ውስቴታ፡ወአስተጋብኦሙ፡ኀበ፡ፂዖቶሙ፡
ወይበዝኁ፡ወይትባዝኁ።

ይትረጎም፡ከመ፡ሶበ፡መጽአ፡እግዚእነ፡
ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡አስተጋብኦሙ፡
ለኵሎሙ፡አሕዛብ፡እለ፡ክዕዋን፡ውስተ፡
ኵሉ፡አልጫቅዕ፡ወኮኑ፡አሐደ፡ሕዝበ፡
በእሙ፤ወውእቱ፡በከመ፡ቃሉ፡በውስተ፡
ወንጌል፡ቅዱስ፡ወብየ፡አባግዕ፡ካልዓት፡
ዘኢኮና፡እምዝንቱ፡መርዔት፡ወይደልወኒ፡
ከመ፡አምጽኦን፡ወይሰምዓኒ፡ቃልየ፡
ወይከውና፡አሐደ፡መርዔተ፡ለአሐዱ፡
ኖላዊ።

ይቤ፡ወእሠይም፡ሎሙ፡ኖሎተ፡እለ፡ይርዕ
ይዎሙ፡ወኢይፈርሁ፡እንከ፡እምይእዜ፡ወኢ
ይደነግፁ፤ይትረጎም፡በእንተ፡ኖሎት፡ኀበ፡
አርድእት፡እስመ፡ሤሞሙ፡ኖሎተ፡ላዕለ፡
መሐይምናን፡ቦቱ።

ወኢይከውን፡እምይእዜ፡ፍርሀት፡ወኢይደ
ነግፁ፡ይትረጎም፡ከመ፡ኢኮነ፡ግብሮሙ፡
ለአርድእት፡ምስለ፡ሕዝብ፡እስመ፡ግብረ፡
ሊቃነ፡አይሁድ፡ኮኑ፡የሀውክዎሙ፡በሕገ
ዚአሆሙ፡ዘያማስኑ፡ባቲ፡ልቡናቲሆሙ።

ወሐዋርያትሰ፡ትሩፋን፡እስመ፡በአማን፡
ኖሎት፡እሙንቱ፡እስመ፡ለእመ፡ርእይዎ፡
ለአሐዱ፡ዘተሐጕለ፡ኢየኀድግዎ፡ዳዕሙ፡
ይፈልጢ፡ለአግብአቱ፡ኀበ፡መርዔት፡ነባቢ፡
በትምህርታቲሆሙ፡ማኅየውያት።

ይቤ፡ይመጽእ፡መዋዕል፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡
ወአቀውም፡ቃልየ፡እንተ፡ተካየድኩ፡ኪያሃ፡ለኢ
ስራኤል፡ወቤተ፡ይሁዳ፡ይትረጎም፡

የዓርብ፡ነግህ።

፲፤ ጌታችን፡በውስጥዋ፡ከፈሰሱባት፡ምድር፡ሁሉ፡የተረፉትን፡ወገኖች፡እኔ፡ሁለተኛ፡ጠባቂ፡እሆናቸዋለሁ፤ የተበተኑትንም፡ከአራቱ፡ማዕዘን፡እሰበስባቸዋለሁ፤በመስካቸውም፡አሰማራቸዋለሁ፤ ፈጽመውም፡ይበዛሉ፡አለ።

፲፩፤ ይኸንንም፡ጌታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡በሚመጣ፡ጊዜ፡በአራቱ፡ማዕዘን፡የተበተኑትን፡አሕዛብን፡ሁሉ፡እንደሚሰበስባቸውና፤ በስሙም፡አንድ፡ወገኖች፡እንደሚሆኑ፡ይተረጕማል፤እርሱም፡በቅዱስ፡ወንጌል፡ከዚህ፡መንጋ፡ያልሆኑ፡ሌሎች፡በጎች፡አሉኝ፤እነርሱንም፡አመጣቸው፡ዘንድ፡አለኝ፤ቃሌንም፡ይሰማሉ፤ለአንድ፡እረኛም፡አንድ፡መንጋ፡ይሆናሉ፡እንዳለ።

፲፪፤ የሚጠብቋቸውን፡እረኞች፡(መምህራን)፡እሾምላቸዋለሁ፤እንግዲህም፡አይፈሩም፤ከዚህ፡በኋላም፡አይደነግጡም፡አለ፤ስለ፡እረኞች፡ያለውን፡ስለ፡ሐዋርያት፡ያተረጕማል፤የእርሱ፡በሆኑ፡ምእመናን፡ላይ፡ጠባቆች፡እረኞች፡(መምህራን)፡አድርጎ፡ሾሟቸዋልና።

፲፫፤ ከእንግዲህም፡ፍርሃት፡አይሆንም፤አይደነግጡም፡ያለውንም፡ይተረጕማል፤ሐዋርያት፡እንደ፡አይሁድ፡ሊቃነ፡ካህናት፡ሥራ፡የሚሠሩ፡አልሆኑም፤እነርሱ፡በሕጋቸው፡ያውኳቸዋልና፤ልባቸውንም፡ያጠፉባቸው፡ነበርና።

፲፬፤ ፍጹማን፡ሐዋርያት፡ግን፡በእውነት፡ጠባቂዎች፡ናቸውና፤አንዱን፡ተሰናክሎ፡ቢያዩት፡አይተዉትም፤ሕያው፡ወደሆነው፡መንጋ፡ሕያው፡በሆነ፡ትምህርታቸው፡ለመመለስ፡ይዘጋጃሉ፡እንጂ።

፲፭፤ ወራት፡ይመጣል፡አለ፤ለኢየሩሳሌምና፡ለይሁዳ፡ወገን፡የገባኋትን፡ቃል፡ኪዳን፡እርሷን፡አጸናለሁ፡ብሏል፡እግዚአብሔር፡

ዘዓርብ፡ጽባሕ።

በእንተ፡ዝንቱ፡በእንተ፡ትሥግዎተ፡አምላክ፡
ቃል፡ዘተሠገወ፡እምዘርዐ፡ዳዊት፡ወይሁዳ።

፲፮፡ ይቤ ፡ ዘተካየድኩ ፡ ይትረጐም ፡ መሐለ ፡
ወይቤ፡ ኪያሁ ፡ ለዳዊት ፡ እስመ ፡ እምፍሬ ፡
ከርሥከ፡አነብር፡ዲበ፡መንበርከ።

፲፯፡ ይቤ ፡ ወበውእቱ ፡ መዋዕል ፡ አቀውም ፡
ለዳዊት፡ ሠርዐ ፡ ጽድቅ ፡ ውእቱኬ ፡ በከመ ፡
ዘከርነ ፡ በእንተ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡
ክርስቶስ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ሠርዐ ፡ ጽድቅ ፡
ወውእቱ፡እምዘርዐ፡ዳዊት።

፲፰፡ ወበመዋዕሊሁ፡ይድኀን፡ይሁዳ፡ወእሥራ
ኤልኒ፡ይነብር፡ተአሚኖ፡ይትረጐም፡ከመ፡
እለ፡የአምኑ፡በክርስቶስ፡ይድኅኑ፡እሙንቱ፡
እምነቶሉ፡ኃጣውኢሆሙ።

፲፱፡ ወያነድሮሙ ፡ ውስተ ፡ ገነተ ፡ ትፍሥሕት ፡
ምስለ ፡ አብርሃም ፡ አቡሆሙ ፡ ወውእቶሙ ፡
ተአሚኖሙ ፡ በፀዓቶሙ ፡ እምዝንቱ ፡ ዓለም ፡
ወውእቶሙ ፡ ንጹሓኒሆሙ ፡ እምርስሐተ ፡
ኃጢአት።

፳፡ ስብሐት ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡
እስከ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ሰቆቃወ ፡ ኤርምያስ ፡ ነቢይ ፡ በረከቱ ፡
አምላኩ፡ ትኩን ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡
አሜን።

ምዕ፡፭፡፩–፳።

፩፡ ወይቤሎ ፡ ኤርምያስ ፡ ለጳስኮር ፡ አንትሙ ፡
በኵሉ ፡ መዋዕሊክሙ ፡ ምስለ ፡ አበዊክሙ ፡
ትትቃረንዎ ፡ ለጽድቅ ፡ ወደቂቅክሙኒ ፡ እለ ፡
ይመጽኡ፡እምድኅሬክሙ።

፪፡ ወእሙንቱሰ ፡ ይገብሩ ፡ ኃጢአተ ፡ ፈድ
ፋደ ፡ እምኔክሙ ፡ እስመ ፡ እሙንቱ ፡ ይሠ
ይጥዎ ፡ ለአዘልበ ፡ ሜጥ ፡ ወያሐምምዎ ፡ ለዘይ
ፌውስ ፡ ሕማማተ ፡ ወይኴንንዎ ፡ ለዘይሠሪ ፡
ኃጢአተ።

የዓርብ፡ነግህ።

አለ ፡ ከይሁዳ ፡ ወገን ፡ ከዳዊት ፡ ዘር ፡ አምላክ፡
ሰው ፡ ስለሆነ ፡ ስለዚህ ፡ ስለ ፡ ሥጋዌው ፡ ይተረ
ጒማል።

፲፮፡ የተማማልኩት ፡ አለ ፡ ከአብራክህ ፡ የተገ
ኘውን ፡ ልጅህን ፡ በዙፋንህ ፡ አስቀምጠዋለሁ፡
ብሎ ፡ ይህን ፡ መሐላ ፡ እንደ ፡ ማለ ፡ ይተረ
ጒማል።

፲፯፡ በዚያ ፡ ወራት ፡ ለዳዊት ፡ የጽድቅ ፡ በቃየ፡
አቆማለሁ ፡ አለ ፡ ይኸውም ፡ አስቀድመን፡
ስለ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የተናገ
ረውን ፡ ነው ፡ እርሱ ፡ ከዳዊት ፡ ዘር ፡ የጽድቅ፡
መገኛ ፡ እንደሆነ ፡ ይተረጐማል።

፲፰፡ በዘመኑም ፡ ይሁዳ ፡ ይድናል ፡ እስራኤልም፡
ጠላት ፡ ጠፍቶለት ፡ ተዘልሎ ፡ ይኖራል ፡ አለ፡
በክርስቶስ ፡ ያመኑ ፡ እነርሱ ፡ ከኃጢአታቸው፡
እንደ ፡ ዳኑ።

፲፱፡ ተድላ ፡ ባለበት ፡ ገነት ፡ ከአባታቸው ፡
አብርሃም ፡ ጋር ፡ እንደሚያኖራቸው ፡
እነርሱም ፡ በመውጣታቸው ፡ ታምነው ፡
ይኖራሉ ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ በወጡ ፡ ጊዜ ፡
ከኃጢአት ፡ እድፍ ፡ ንጹሐን ፡ ሁነው ፡ እንደ
ሚኖሩ ፡ ይተረጐማል።

፳፡ ለጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ክብር ፡
ምስጋና ፡ ለዘላለሙ ፡ ይሁን ፡ አሜን።

የአምላኩ ፡ በረከት ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ለዘላለሙ ፡
ይኑርና ፡ የነቢዩ ፡ የኤርምያስ ፡ ሰቆቃው ፡
(ልቅሶ) ፡ ይህ ፡ ነው።

ምዕ፡፭፡፩–፳።

፩፡ ኤርምያስ ፡ ጳስኮርን ፡ እናንተስ ፡ ባለ
ዘመናችሁ ፡ ሁሉ ፡ እውነትን ፡ እንደ ፡ አባቶ
ቻችሁ ፡ ትጣሏታላችሁ ፡ ከእናንተም ፡ በኋላ ፡
የሚመጡ ፡ ልጆቻችሁ ፡ አይጠብቋትም።

፪፡ እነርሱ ፡ ግን ፡ ከአባቶቻችሁ ፡ ይልቅ ፡ እጅግ፡
ኃጢአትን ፡ ይሠራሉ ፡ እነርሱ ፡ መሸጥ ፡ የሌለ
በትን ፡ ክርስቶስን ፡ ይሸጡታልና ፡ ከበሽታ ፡
የሚያድን ፡ ጌታን ፡ እንዲታመም ፡ (መከራ ፡
እንዲቀበል ፡ ያደርጉታል) ፡ ኃጢአት ፡ የሚያስ
ተሠርይ ፡ እሱንም ፡ ይፈርዱበታልና።

## ዘዓርብ፡ጽባሕ።

ወይነሥኡ፡ሠላሳ፡ብሩረ፡ሤጦ፡ለክቡር፡ ወይሠይጥዎ፡ ለደቂቀ፡ እስራኤል፤ ወይሁብዎ፡ለወእቱ፡ብሩር፡ውስተ፡ዐጸደ፡ ለብሓዊ።

በከመ፡ አዘዘኒ፡ **እግዚአብሔር**፡ ከማሁ፡ አነብብ።

ወበእንተዝ፡ ይነብር፡ ላዕሌሆሙ፡ ኵነኔ፡ ወሙስና፡ እስከ፡ ለዓለም፡ ወላዕለ፡ ውሉዶሙ፡ እስከ፡ ድኅሬሆሙ፡ እስመ፡ ከዐዉ፡ደመ፡ንጹሐ፡ውስተ፡ኵነኔ።

ትርጓሜ፡ሰቆቃወ፡ኤርምያስ፡ወይቤሎ፡ ኤርምያስ፡እስከ፡ኀበ፡ይብል፡ውስተ፡ኵነኔ።

ይቤ፡ መተርጕም፡ ይቤሎ፡ ኤርምያስ፡ ለጳስኮር፡አንትሙ፡በኵሉ፡መዋዕሊክሙ፡ ምስለ፡አበዊክሙ፡ትትቃረንዋ፡ለጽድቅ፡ ኢይቤ፡ነቢይ፡ዘንተ፡ በእንተ፡ አሐዱ፡ ብእሲ፡ ወባሕቱ፡ ለሕዝብ፡ እንተ፡ ይሔንዎሙ፡በእንተ፡**እግዚአብሔር፡ልዑል**።

ይቤ፡አንትሙሰ፡ ኵሎ፡ መዋዕሊክሙ፡ አንትሙሰ፡ምስለ፡አበዊክሙ፡ትትቃረንዋ፡ ለጽድቅ፤ይተረጐም፡ከመ፡ውእቶሙ፡ኮኑ፡ ዕሉያን፡በግብረ፡ውርዙቶሙ፡እስመ፡ኮኑ፡ ይሬእይዎሙ፡ለአበዊሆሙ፡ላዕለ፡ስሕተት፡ ወየኀብርዎሙ፤እስመ፡ገደፉ፡ቃለ፡ነቢያት።

ዘይሔንውዎሙ፡ በእንተ፡ **እግዚአብሔር፡ ልዑል**፤ ወሰደድዎሙ፡ ወኢተመይጡ፡ ለጽድቅ፤ወበልሀቅናሆሙ፡ይኤጽሩ፡እበደ፡ ደቂቆሙ፡ወየኀብርዎሙ።

ወካዕበ፡ዓዲ፡ ተነበየ፡ ውእቱ፡ በእንተ፡ ደቂቆሙ፡እለ፡ይመጽኡ፡እምድኅሬሆሙ፡ ሌሊ፡ኮኑ፡ ያነጽሑ ነፍሳቲሆሙ ወይብሉ፡ ለሊሁ፡ሀሎነ፡በአዝማነ፡አበዊነ፡እምኢኀበር ምሙ፡ውስተ፡ደመ፡ነቢያት፡በከመ፡ነገረ፡ ወንጌል፡ቅዱስ።

## የዓርብ፡ነግህ።

፲፪፤ የክቡር፡**የክርስቶስን**፡ዋጋ፡ሠላሳውን፡ብር፡ ወስደው፤ ለእሥራኤል፡ ልጆችም፡ ይሸጡታል፤ ያንንም፡ብር፡ለሸክላ፡ሠሪ፡ ቦታ፡ዋጋ፡አድርገው፡ይሰጡታል።

፲፫፤ **እግዚአብሔር**፡ እንዳዘዘኝ፡ እንዲሁ፡ እናገ ራለሁ።

፲፬፤ ፈረደው፡ንጹሕ፡ደምን፡አፍሰዋልና፤ይህን፡ ስለ፡አደረጉ፡ጥፋቱና፡መከራው፡አስቀድሞ፡ በእነርሱ፡ከእነርሱም፡በኋላ፡በልጆቻቸው፡ ይወርድባቸዋል።

የኤርምያስ፡ሰቆቃው፡(ልቅሶ)፡የምሥጢር፡ ትርጓሜ፤ ወይቤሎ፡ ኤርምያስ፡ ካለው፡ ጀምሮ፡ውስተ፡ኵነኔ፡እስካለው፡ድረስ።

፲፭፤ ተርጓሚው፡ኤርምያስ፡ጳስኮርን፡እናንተስ፡ ባለ፡ዘመናችሁ፡ሁሉ፡እውነትን፡እንደ፡አባ ቶቻችሁ፡ ትጣሏታላችሁ፡ አለው፡ አለ፤ ነቢይ፡ ይኸን፡ ስለ፡ አንድ፡ ሰው፡ አልተና ገረም፤ ነገር፡ ግን፡ ስለ፡**ልዑል፡እግዚአብ ሔርና**፡ስለሚያስተምራቸው፡ለሕዝቡ፡ሁሉ ነው፡እንጂ።

፲፮፤ እናንተስ፡ባለ፡ዘመናችሁ፡ሁሉ፡እንደ፡አባቶ ቻችሁ፡ እውነትን፡ ትጣሏታላችሁ፡ አለ፤ ይህንንም፡ እነርሱ፡ አባቶቻቸውን፡ በስሕተት፡ ሥራ፡ ላይ፡ የሚያዩዋቸው፡ ስለሆኑና፡ተባብረውም፡ስለሚሠሩት፡በጕል ምስናቸው፡ሥራ፡ክፉዎች፡እንደ፡ሆኑ፡ይተ ረጐማል።

፲፯፤ ስለ፡**ልዑል፡እግዚአብሔር**፡የሚነግሩአቸውን፡ የነቢያትን፡ቃል፡ጥለዋልና፤ነቢያትን፡አሳደዱአ ቸው፤ወደ፡እውነት፡አልተመለሱም፤በሽምግል ናቸው፡የሚሠሩትንም፡ድንቁርና፡ልጆቻቸው፡ አይተው፡ተመልክተው፡ይተባበሩአቸዋል።

፲፰፤ ዳግመኛም፡ ከእነርሱ፡ በኋላ፡ ስለሚነሡ፡ ልጆቻቸው፡ እኛ፡ በአባቶቻችን፡ ዘመን፡ ኑረንስ፡ቢሆን፡በነቢያት፡ደም፡ባልተባበርና ቸውም፡ነበር፡በማለት፡የከበረ፡ወንጌል፡እን ደተናገረ፤ ራሳቸውን፡ንጹሕ፡ስለሚያደርጉ፡ ደግሞ፡ትንቢት፡ተናገረ።

## ዘዓርብ፡ጽባሕ።

፭፡ ወሶበ ፡ መጽአሙ ፡ እግዚአሙ ፡ ለነቢያት ፡ ወገብረ ፡ ሎሙ ፡ ተአምራተ ፡ ወመንክራተ ፡ ዘኢገብረ ፡ ባዕድ ፡ ካልዕ ፡ ዘምስለ ፡ አእምሮቶሙ ፡ ስምዖሙ ፡ ለነቢያት ፡ በእንቲአሁ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ መድኃኒሆሙ ፡ ወምስለ ውእቱ፡ክህድዎ፡ሎቱ።

፮፡ ይቤ ፡ ወእሙንቱሰ ፡ ይገብሩ ፡ ኃጢአተ ፡ ፈድፋደ ፡ እምኔክሙ ፡ በአማንኬ ፡ ከመ ፡ እልክቱ፡ሰደድዎሙ፡ለነቢያት፡ወኢአምኑ፡ ቃላቲሆሙ።

፯፡ ወእሙንቱሰ ፡ አግብዑ ፡ እግዚአ ፡ ነቢያት ፡ ለሞት፡ወኃጢአቶሙኬ፡የዐቢ፡ፈድፋደ።

፰፡ ወእሙንቱሰ ፡ ይሠይጥዎ ፡ ለዘአልቦ ፡ ሤጥ ፡ ይትረጐም ፡ ዘንተ ፡ ከመ ፡ ሶበ ፡ መጽአሙ ፡ ይሁዳ፡ወይቤሎሙ፡ምንተ፡ትሁቡኒ፡ወአነ፡ አገብአ፡ለክሙ፡ወአጽንዑ፡ምስሌሁ፡ሠላሳ፡ ብሩረ ፡ ወሠምረ ፡ ምስሌሆሙ ፡ በዝንቱ ፡ መጠን ፡ ከመ ፡ ይትፈጸም ፡ ቃለ ፡ እግዚአ ብሔር፡ላዕለ፡ልሳነ፡ነቢይ።

፱፡ ወእመ ፡ አኮሰ ፡ ለእመ ፡ ኃሠሠ ፡ እምኔሆሙ ፡ ካዕበቶ ፡ ለዝ ፡ መጠን ፡ እምኮኑ ፡ ይሁብዎ ፡ በእንተ ፡ ተቀይሞቶሙ ፡ ላዕሌሁ ፡ ወቅን ዓቶሙ፡ቦቱ።

፲፡ ወቦ፡እመተርጐማን፡ዘነገረ፡በእንተ፡ሠላሳ፡ ብሩር፡ከመ፡ይእቲ፡ሠላስ፡ሰቅል፡በሰቅል፡ ዘኢየሩሳሌም፡ወኮነ፡አሐዱ፡ሰቅል፡ዘኢየሩ ሳሌም፡በውእቱ፡ጊዜ፡ዐሠርቱ፡ሰቅል።

፲፩፡ ወውእቱሰ፡ሤጠ፡ሎሙ፡ወነሥአ፡ሤጠ፡ለዘ አልቦቱ ፡ ሤጥ ፡ እስመ ፡ ፈጣሬ ፡ ሰማያት ፡ ወምድር፡ወመላእክት፡ወዕጓለ፡እመሕያው፡ ዘያስተርኢ ፡ ወዘኢያስተርኢ ፡ ወኵሎሙ ፡ ሳእካን፡ወአግብርት፡ሎቱ።

፲፪፡ ወውእቶሙሰ ፡ በዕበዲሆሙ ፡ ተሐዘብዎ ፡ ከመ፡ ኢተረክበ ፡ በውስተ ፡ ዕደዊሆሙ ፡ ወኢክህሉ፡ላዕሌሁ፡ዘእንበለ፡ዛቲ፡ምክር።

## የዓርብ፡ነግህ።

፭፡ የነቢያትም ፡ ጌታ ፡ በመጣላቸው፡ጊዜ፡ሌላ፡ የማያደርገውን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ አስደናቂዎች፡ ተአምራትን ፡ አደረገላቸው ፤ ስለ ፡ እርሱ፡ መድኃኒታቸው ፡ እንደሆነ፡ነቢያት፡የመሰከ ሩለትን ፡ ከማወቃቸውም ፡ ጋር ፡ ከዚህ፡ ከሥራው፡ጋር፡ካዱት።

፮፡ እነርሱ ፡ ከእናንተ ፡ ይልቅ ፡ ኃጢአትን፡ አብልጠው ፡ ይሠራሉ ፡ አለ ፤ በእውነትም፡ እነዚያ ፡ ነቢያትን ፡ አሳደዱአቸው ፤ ቃላቸ ውንም፡አልተቀበሏቸውም።

፯፡ እነዚህ ፡ ግን ፡ የነቢያትን ፡ ጌታ ፡ ለሞት፡ አሳልፈው ፡ ሰጡ ፤ ስለዚህ ፡ ኃጢአታቸው፡ እጅግ፡የበዛ፡ነው።

፰፡ እነርሱ ፡ ግን ፡ መሸጥ ፡ የሌለበትን ፡ ክርስ ቶስን፡ይሸጡታል፡አለ፤ይሁዳ፡መጥቶ፡ክርስ ቶስን ፡ አሲዛችኋለሁ ፤ ምን፡ትሰጡኛላችሁ፡ እንዳላቸው ፤ እነርሱም ፡ ሠላሳ ፡ ብር፡ ሊሰጡት፡ ውል ፡ እንዳጸኑ ፡ የእግዚአብ ሔርም፡ ቃል ፡ ይፈጸም ፡ ዘንድ ፡ በነቢይ፡ አንደበት ፡ እንደተነገረ ፡ በዚሁ ፡ መጠን፡ እንደ፡ተስማሙ፡ይህን፡ይተረጕማል።

፱፡ ያም፡ባይሆን፡ግን፡ከእነሱ፡ቢፈልግ፡ጌታን፡ ስለሚጠሉትና፡ስለሚቀኑበት፡የሠላሳውን፡ ብር፡እጥፍ፡አድርገው፡በሰጡት፡ነበር።

፲፡ ከተርጓሚዎችም ፡ ስለ ፡ ሠላሳ ፡ ብር ፡ በኢየሩ ሳሌም ፡ ሚዛን ፡ ሦስት ፡ ሰቅል ፡ እንደሆነች፡ የተናገረ፡አለ፤በዚያን፡ጊዜ፡አንዱ፡ብር፡በኢ የሩሳሌም፡ዓሥር፡ሰቅል፡ነበርና።

፲፩፡ እርሱ፡ግን፡የማይሸጠውን፡ጌታ፡ክርስቶስን፡ ሸጠ ፡ ዋጋውን ፡ ወሰደ ፤ ሰማይና ፡ ምድርን፡ ሰውና፡መላእክትን፡የሚታየውንና፡የማይታ የውን፡የፈጠረ፡ፍጥረቱ፡ሁሉ፡ለእርሱ፡አገ ልጋዮችና፡ባሮች፡የሚሆኑለት፡ናቸውና፡የማ ይሸጠውን፡አለ።

፲፪፡ እነርሱ፡ግን፡በድንቁርናቸው፡ይሁዳ፡ካላሳ ዛቸው ፡ በቀር ፡ ያለዚች ፡ ምክር ፡ በእጃቸው፡ ለማስገባት፡እንደማይችሉ፡ተጠራጠሩ።

Scanned by CamScanner

## ዘዓርብ፡ጸባሕ።

ወዛቲ፡ምክር ፡ ወዛቲ ፡ ድኅርም ፡ እንተ ፡
ወሀብዎ፡ለይሁዳ፡ወኢኮነ፡ግብር፡ከመ፡ትሕ
ዝብሉ፡እስመ፡እግዚእ፡ለሊሁ፡ስብሐት፡
ዘንተ ፡ ዝንቱ ፡ ሥርዓት ፡ ወበእንተ ፡
መድኅኒት ፡ አዳም ፡ ወዘርዑ ፡ ሐዋርያን ፡
(ኃጥኣን)፡ወመጻእያን፡ወነዳያን፡መጠወ፡
ነፍሶ፡ቤዛ፡በእንቲአሆሙ፡እስመ፡ምሕረት፡
አምጽኡ፡ሎቱ፡ሙ።

ይቤ፡ወየሐምምዎ፡ለዘይፈውስ፡ሕማማተ፤
ወአዘዘ ፡ ለመፃጉዕ ፡ እምድኅረ ፡ ብዙኅ ፡
ዓመታት፡ከመ፡ይፁር፡ዓራቶ፡ወይሑር፡ወዘ
እንሥአ ፡ ለአልዓዛር ፡ እምድኅረ ፡ ጺዓቲ ፡
እምውታን ፡ ያረ ፡ እምኔሆሙ ፡ ቅንዋተ ፡
ውስተ፡ ዕደዊሁ ፡ ወእገሪሁ ፡ ወተዓገሠ ፡
ርግዘተ፡ገቦሁ፡በኲናት፡በእንተ፡ግዕዛነ፡
ነፍሳቲነ፡ወሥርየተ፡ኃጣውኢነ።

ይቤ፡ወይነሥእ፡ ሠላሳ ፡ ብሩረ ፡ ሤጦ ፡
ለክቡር፡ወይሠይጥዎ፡ለደቂቀ፡እስራኤል፡
ወይሁብዎ፡ውስተ፡ዐጸደ፡ለብሐዊ።

ይተረጎም፡ዘንተ፡ከመ፡ሶበ፡ርእየ፡ይሁዳ፡
ርጉም ፡ ግብሮ ፡ ዕኩየ ፡ ሖረ ፡ ኀቤሆሙ ፡
ወአግብአ ፡ ዘነሥአ ፡ እምኔሆሙ ፡ ወሖረ ፡
ወሐነቀ ፡ ነፍሶ ፡ ወሞተ ፡ ሞተ ፡ እኩየ ፤
ወተኰነኑ ፡ ምስለ ፡ ቀታልያን ፡ እስመ ፡
አግብአ፡ለእግዚኡ፡ እምድኅረ ፡ አእምሮቱ ፡
ሎቱ፡ወቀተለ፡ነፍሶ።

ወይቤሉ፡በበይናቲሆሙ፡ዝንቱ፡ሤጠ፡ደም፡
ውእቱ፡ንሣየጥ፡ገራህተ፡ደም፡ቦቱ።

ወወሀብዎ ፡ ለገራህተ ፡ ለብሐዊ ፡ ከመ ፡
ይትፈጸም፡እግዚእ፡ዘይቤ፡በአፈ፡ነቢይ።

ወይቤ ፡ ከመዝ ፡ እብል ፡ ናሁ ፡ ይነብር ፡
ላዕሌሆሙ ፡ ኵነኔ ፡ ወሙስና ፡ ወላዕለ ፡
ውሉዶሙ ፡ እስመ ፡ ከዐዉ ፡ ደመ ፡ ንጹሐ ፡
ውስተ፡ኵነኔ።

## የዓርብ፡ነግህ።

፲፫፤ ይህችም፡ለይሁዳ፡የሰጡት፡ገንዘብ፡እንርሱ፡
እንደሚጠራጠሩት ፡ ግዴታ ፡ አይደለም ፤
የክብር ፡ ባለቤት ፡ ጌታ ፡ ስለዚህ ፡ ሥርዓት ፡
አዳምና ፡ ልጆቹን ፡ ስለማዳን ፡ ያለፉትንም ፡
የሚመጡትንም፡ድኆችንም፡ስለማዳን፡ስለ፡
እነርሱ፡ነፍሱን፡ቤዛ፡አድርጎ፡ሰጠ፤ከእርሱ፡
የተገኘች፡ምሕረት፡ለእነርሱ፡ናትና።

፲፬፤ በሽታዎችን ፡ የሚያድን ፡ እርሱን ፡ እንዲ
ታመም፡አደረጉት፡አለ፤ብዙ፡ዘመን፡ታሞ፡
የነበረ ፡ መፃጉዕን ፡ አልጋውን ፡ ተሸክሞ ፡
እንዲሄድ፡አዘዘው፤አልዓዛርን፡በመቃብር፡
ውስጥ ፡ ከተላና ፡ ከሸተተ ፡ በኋላ ፡ ያስነሣው ፡
እጆቹንና ፡ እግሮቹን ፡ በችንካር ፡ የመቸንከር ፡
ሥቃይ ፡ ተሸከመ ፤ ስለ ፡ ኃጢአታችን ፡
ሥርየትና ፡ ስለ ፡ ነፍሳችን ፡ ነፃነት ፡ በጦር ፡
መወጋትንም፡ታገሠ።

፲፭፤ የእሥራኤል፡ልጆች፡የተስማሙበት፡
ቶስን ፡ ዋጋ ፡ ሠላሳውን ፡ ብር ፡ ይቀበሉታል፤
ያንንም ፡ ብር ፡ ለሸክላ ፡ ሠሪ ፡ ቦታ ፡ ዋጋ ፡
አድርገው፡ይሰጡታል፡አለ።

፲፮፤ ይኸንንም፡እንዲህ፡ይተረጉሟል፤የተረገመ፡
ይሁዳ፡ራሱ፡የሠራውን፡ክፉ፡ሥራ፡በተመ
ለከተ፡ጊዜ፤ወደ፡እነርሱ፡ሄዶ፡ከእነርሱ፡የወ
ሰደውን ፡ ሠላሳ ፡ ብር ፡ መልሶ ፡ ሰውነቱን ፡
አንቆ፡በክፉ፡ሞት፡ሞተ፤ከነፍስ፡ገዳዮችም፡
ጋር ፡ ተቈጠረ፤ጌታውን ፡ አሳልፎ ፡ ለሞት ፡
ሰጥቶ ፡ ክፉ ፡ የሆነ ፡ ሥራውንም ፡ ከአወቀ ፡
በኋላ፡ራሱን፡በራሱ፡ገድሏልና።

፲፯፤ እርስ፡በርሳቸውም፡ይህ፡የደም፡ዋጋ፡ነውና፡
የደም፡ቦታ፡እንግዛበት፡አሉ።

፲፰፤ ጌታ ፡ በነቢይ ፡ አፍ ፡ የተናገረው ፡ ይፈጸም ፡
ዘንድ፡ለሸክላ፡ሠሪ፡ቦታ፡ሰጡት።

፲፱፤ እነሆ ፡ ፈርደው ፡ ንጹሕ ፡ ደምን ፡ አፍሰዋልና ፡
ይህን፡ስለ፡አደረጉ፡ጥፋቱና፡መከራው፡አስቀ
ድሞ ፡ በእነርሱ ፤ ከእነርሱም ፡ በኋላ ፡ በልጆቻ
ቸው፡ይወርድባቸዋል፡እንደዚህ፡እላለሁ፡አለ።

## ዘዓርብ፡ጽባሕ።

፳፡ ወከመዝ ፡ ኮነ ፡ እምድኅረ ፡ ዕርገቱ ፡ ለእግ
ዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ሐፀሮሙ፡ንጉሠ፡
ሮም ፡ ወአርኀወ ፡ አናቅጸ ፡ ሀገር ፡ ወቀተለ ፡
ምዕተ፡ወእስራ፡ረበዋተ፡ወለለዙሉ፡ዕሥራ፡
ምዕተ፡ወእስራ፡ረበዋተ፡ወለለዙሉ፡ዕሥራ፡
ረበዋት ፡ በበዐሠርቱ ፡ ምዕት ፤ ወአመዝበረ ፡
ምኵራብ ፡ ወበጠለ ፡ ቍርባኖሙ ፡ ወጽንሓ
ሓሆሙ።

፳፩፡ ወንስአሎ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡
ከመ ፡ ኢይፍድየነ ፡ በኃጣውኢነ ፡ ወከመ ፡
ኢይኅድገነ፤ሎቱ፡ስብሐት፡ለዓለመ፡ዓለም፡
አሜን።

ዘኤርምያስ ፡ ነቢይ ፡ በረከተ ፡ አምላኩ ፡
ትኩን፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ምዕ፤፲፪፤፩–፰።

፩፡ ጻድቅ፡አንተ፡ እግዚኦ ፡እስመ፡እትዋቀሥ፡
በኀቤከ፡ወባሕቱ፡ፍትሐ፡እነግረከ፤ለምንት፡
ፍኖተ ፡ ኃጥአን ፡ ድሉት ፤ ወተፈሥሑ ፡
ኵሎሙ፡ዐላውያን፡በማዕሌት።

፪፡ ወተከልኮሙ፡ወሰፍሐ፡ሥረዊሆሙ፡ወለዱ፡
ወገብሩ ፡ ፍሬ ፡ ቅሩብ ፡ አንተ ፡ ውስተ ፡
አፉሆሙ፡ወርሑቅ፡እምነ፡ኵልያቲሆሙ።

፫፡ ወለሊከ፡ እግዚኦ ፡ተአምረኒ፡ወትሌብወኒ፡
ወፈተንከ፡ለልብየ፡በቅድሜከ፡ትጸንሆሙ፡
ከመ ፡ በግዕ ፡ ለተጠብሖ ፡ ወትቄድሶሙ ፡
ለዕለተ፡ቀትል።

፬፡ እስከ ፡ ማዕዜኑ ፡ ትላሁ ፡ ምድር ፡ ወየብሰ ፡
ሣዕረ፡ ገዳም ፡ በእከዮሙ ፡ ለእለ ፡ ይነብሩ ፡
ውስቴታ ፤ ወኀልቁ ፡ እንስሳ ፡ ወአዕዋፍ ፡
እስመ፡ይቤሉ፡አልቦ፡ዘይሬኢ፡ድኅረተነ።

፭፡ እገሪከ ፡ ይረውጺ ፡ ወይደክማ ፤ ለምንት ፡
ታስተሬሲ ፡ አፍራሰ ፡ በብሔረ ፡ ሰንዕ ፡
ተአመንከ ፤ በእፎ ፡ ትገብር ፡ በኀሳረ ፡
ዮርዳኖስ።

፮፡ እስመ፡አኃዊከኒ፡ወቤተ፡አቡከ፡እሙንቱኒ፡
ክሕዱከ፡ወውዑ፡ወበድኅሬከ፡አንገለጉ፡ኢት

## የዓርብ፡ነግህ።

፳፡ እንዲህም፡ሆነ፤ ጌታችን፡ኢየሱስ፡ክርስ
ከዐረገ፡በኋላ፡የሮም፡ንጉሥ፡የከተማውን
በር ፡ ከፍቶ ፡ መቶ ፡ ሃያ ፡ አለቆችን ፡ ገደለ፡
በየሃያው ፡ ሁሉ ፡ አለቆች ፡ አንዳንድ ፡ ሺ፡
መምህራንን፡ገድሎ፡ምኵራባቸውን፡ሁሉ፡
አፈረሠ ፤ መሥዋዕታቸውንም ፡ ቍርባኖ
ውንም፡አጠፋ።

፳፩፡ እንደ፡ኃጢአታችንም፡ፈርዶ፡ፍዳን፡እንዳ
መጣብን ፡ በመከራም ፡ እንዳይጥለን ፡
ጌታችን፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡እንለምነው፡
ለእርሱም ፡ ክብር ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡
ለዘላለሙ፡አሜን።

የአምላኩ ፡ በረከት ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ለዘላለሙ፡
ትኑርና ፡ ነቢዩ ፡ ኤርምያስ ፡ የተናገረው፡
ትንቢት፡ይህ፡ነው።

ምዕ፤፲፪፤፩–፰።

፩፡ በአንተ ፡ ዘንድ ፡ እከራከራለሁና ፡ አቤቱ፡
አንተ ፡ እውነተኛ ፡ ዳኛ ፡ ነህ ፤ ነገር ፡ ግን፡
ፍርድን፡እጠይቃለሁ፤የኃጥአን፡ሥራቸው፡
ለምን፡ተዘጋጀች፤ወንጀለኞችስ፡ሁሉ፡በወን
ጀላቸው፡ለምን፡ደስ፡አላቸው።

፪፡ አንተም፡አጸናሃቸው፤አባትነታቸውም፡በዛ፤
ልጅም ፡ ወለዱ ፤ በአፋቸው ፡ አንተ ፡ ቅርብ፡
ነህ፤ከልቡናቸው፡ግን፡ርቀሃል።

፫፡ አቤቱ ፤አንተስ ፡ እኔን ፡ ፈጽመህ ፡ ታውቀ
ኛለህ፤ ልቡናዬንም ፡ በፊትህ ፡ መረመርከው፡
ሊያርዱት፡በግን፡እንዲጠብቁት፡ትጠብቃቸ
ዋለህ፤ለሰልፍም፡መቼ፡ቀን፡ትለያቸዋለህ።

፬፡ ምድር ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ድረስ ፡ ታለቅሳለች!
በርሷ ፡ በሚኖሩባት ፡ ሰዎች ፡ ክፋትም፡
የምድረ፡በዳው፡ሣር፡ደረቀ፤ፍጻሜያችንን፡
የሚያውቅ ፡ የለም ፡ ብለዋልና ፤ አዕዋፍና፡
እንስሳም፡አለቁ።

፭፡ እግሮችህ ፡ ሮጠው ፡ ይደክማሉ ፤ ተዘልለ፡
በምትኖር ፡ አገር ፡ ፈረሶችን ፡ ለምን ፡ ታስ
ጣለህ፤ከዮርዳኖስስ፡በታች፡ለምን፡እንዳይ
ታደርጋለህ።

፮፡ ወንድሞችህ ፡ ያባትህም ፡ ወገኖች ፡ እነርሱ፡
ከደውኻልና ፤ ብዙ ፡ ጠላቶችህም ፡ በኋላህ፡

ዘዓርብ፡ጽባሕ።

...ምሙ፡እመ፡ሠናየ፡ነበበ፡ላዕሌከ።

...ገ፡ቤትየ፡ወነደገ፡ርስትየ፡ወሀብክዋ፡
...ቅርተ፡ነፍስየ፡ውስተ፡እደ፡ፀሬ።

...ተኒ፡ሊተ፡ርስትየ፡ከመ፡አንበሳ፡
...ም፡ጥሕረት፡ላዕሌየ፡በእንተ፡ዝንቱ፡
...ኩዋ።

...ብ፡ሰሎሞን፡በረከተ፡አምላኩ፡ትኩን፡
...ስ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ምዕ፡፪፡፲፫–፳፫።

...፡ንቅትሎ፡ለጻድቅ፡እስመ፡ዕፁብ፡
...ውእቱ፡ለነ፡ወይትቃወሞን፡ለምግ
...ነ፡ወይዘነጕጐነ፡በኃጢአ፡ሕግ።

...ለነ፡አበሳ፡ትምህርትነ፡ወይብል፡
...ር፡እግዚአብሔር፡ብየ፡ወወልደ፡እግዚ
...ር፡ይሬሲ፡ርእሶ፡ወኮነነ፡መዝለፈ፡
...ነ።

...ውእቱ፡ለነ፡በራእዩኒ፡እስመ፡ኢይ
...ል፡ምስለ፡ባዕድ፡ንብረቱ፡ወፍሉጥ፡
...ቱ።

...ነ፡ኮነ፡በኃቢሁ፡ወይርሕቅ፡እምፍ
...፡ከመ፡ዘእምርኩስ፡ይርሕቁ፡ወያስተ
...፡ደኃሪቶሙ፡ለጻድቃን፡ወይትሜካህ፡
...እግዚአብሔር፡አቡሁ።

...ይ፡ለእመ፡ነገሩ፡ኮነ፡ሕልወ፡
...ክር፡ዘይከውን፡እምርእየቱ።

...ለ፡ጻድቅ፡ወልዱ፡ለእግዚአብሔር፡
...፡ወይባልሆ፡እምእደ፡እለ፡ይትቃ
...።

...ት፡ወበሕማም፡ንሕትቶ፡ከመ፡
...፡የውሀቶ፡ወናመክር፡ትዕግሥቶ፡
...።

...፡ኅሱር፡ንኰንኖ፡እመ፡ይከውኖ፡
...፡በከመ፡ቃሉ።

የዓርብ፡ነግህ።

ተከትለው፡ደንፍተዋል፤ዶልተውብሃልና፡በአ
ንተ፡በጎ፡ነገር፡ቢነግሩህ፡አትመናቸው፡አለ።

፯፡ ቤቴን፡ተውኩ፤ርስቴንም፡ተውኩ፤ልቡናየ፡
የሚወዳት፡ቤተ፡እስራኤልንም፡በጠላቷ፡
እጅ፡አሳልፌ፡ሰጠኋት።

፰፡ ርስቴ፡ኢየሩሳሌም፡በቃችኝ፤በምድረ፡በዳ፡
እንዳለ፡አንበሳም፡ጮኸችብኝ፤ስለዚህ፡
ነገር፡ጠላኋት።

የአምላኩ፡በረከት፡ከእኛ፡ጋር፡ለዘላለሙ፡
ትሁንና፡የሰሎሞን፡የጥበብ፡ነገር፡ይህ፡ነው።

ምዕ፡፪፡፲፫–፳፫።

፲፫፡ ጻድቁን፡ሰው፡(ክርስቶስን)፡ኑ፡እንግደለው፡
አሉ፤ለኛ፡ጽኑ፡ጭንቅ፡ሆኖብናልና፡ሥራዎ
ቻችንንም፡ይቃወማቸዋልና፡ሕግን፡
በማጣት፡ይሣለቅብናልና።

፲፬፡ የትምህርታችን፡በደልነቱን፡ያስተምረናል፤
እግዚአብሔርንም፡ማወቅ፡በእኔ፡አለ፡ይላል፤
የእግዚአብሔርም፡ልጅ፡ነኝ፡ይላል፤ልቡናች
ንንም፡የሚዘልፍ፡ሆኗልና።

፲፭፡ በመልኩም፡ለኛ፡ጭንቅ፡ሆኖብናል፤አነዋ
ወሩም፡ከፍጡራን፡ጋራ፡አይመሳሰልም፤
ሥራው፡ልዩ፡ነውና።

፲፮፡ በሱ፡ዘንድም፡የተናቅን፡ሁነናል፤ከኃጢአት፡
እንዲርቁ፡ከሥራችን፡ይርቃል፤የደጋግ፡
ሰዎች፡መጨረሻቸውን፡ያመሰግናል፤እግዚ
አብሔርም፡አባቱ፡እንደሆነ፡ይመካልና።

፲፯፡ ነገሩ፡ቀዋሚ፡እንደሆነ፡እንይ፤ከመልኩ፤
ማማር፡የተነሣ፡በመከራ፡እንፈትነው፡አሉ።

፲፰፡ የእግዚአብሔር፡እውነተኛ፡የባሕርይ፡
ልጁስ፡ከሆነ፡ያድነው፤ከሚቃወሙትም፡
እጅ፡ይቤዠው።

፲፱፡ ቅንነቱን፡እናውቅ፡ዘንድ፡ትዕግሥቱንም፡
እንፈትነው፡ዘንድ፡እየሰደብን፡በመከራ፡እን
መርምረው።

፳፡ እንደ፡ቃሉ፡ረዳት፡ይሆነው፡እንደሆነ፤የከፋ፡
የውርደት፡ሞትን፡እንፍረድበት፡አሉ።

Scanned by CamScanner

## ዘዓርብ፡ጽባሕ።

፳፰ ወዘንተ፡ንባበ፡ኃለዩ፡ወቦ፡ስሕቱ፡እስመ፡
እንቈረቆሙ፡እከዮሙ።

፳፱ ወኢያእመሩ፡ኅቡአቲሁ፡ለእግዚአብሔር፡
ወኢተሰፈዉ፡ዐስበ፡ጽድቅ።

፴ ወኢፈለጡ፡ዕበየ፡ክብረ፡ነፍሳት፡ንጹሐት፡
እለ፡አልቦን፡ነውር፡እስመ፡እግዚአብሔር፡
ፈጠሮ፡ለሰብእ፡እንበለ፡ሙስና፡ወገብሮ፡
በአርአያ፡ዚአሁ።

ትርጓሜ ፡ ጥበበ ፡ ሰሎሞን ፡ ንቅትሎ ፡
ለጻድቅ ፡ እስከ ፡ ኀበ ፡ ይብል ፡ ለነፍሳት ፡
ንጹሐት።

፩ ይቤ ፡ መተርጕም ፡ እስመ ፡ ኢይጥዕም ፡
ውስተ፡ ልብነ ፡ ይተረጐም ፡ ዘንተ ፡ ከመ ፡
አይሁድ ፡ ሶበ ፡ ርእዩ ፡ ትእምርተ ፡ ወመን
ክራተ ፡ እንተ ፡ ኮነ ፡ ይገብሮን ፡ እግዚእነ ፡
ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ቀንዐ፡ላዕሌሁ፡በእንተ፡
ዐሊዎቶሙ ፡ ለውእቱ ፡ ጻድቅ ፡ ወኮኑ ፡ ይትዓ
ቀብዎ ፡ በኵሉ ፡ ጊዜ ፡ ከመ ፡ ይርከቡ ፡
ምክንያተ፡በላዕሌሁ፡ከመ፡ያሥግርዎ፡ባቲ።

፪ ወበእንተ፡እቅበተ፡ሢመቶሙ፡ኢኮና፡አልባ
ቢሆሙ ፡ ያስተጥዕማ ፡ ምንተኒ ፡ ዘኮነ ፡
ይገብሮ፡መድኀን፡ዳእሙ፡ኮኑ፡ይብሉ፡ከመ፡
ዝንቱ፡ኵሉ፡ኮነ፡እምሰይጣን፡ምስለ፡አእም
ሮቶሙ፡ከመ፡ጽድቅ፡ይእቲ፡ወይተነትኑ፡
እምኔሃ።

፫ በከመ ፡ ይቤ ፡ በወንጌል ፡ ቅዱስ ፡ እስመ ፡
ብዙኃን፡እምሊቃውንት፡ወእምፈሪሳውያን፡
አምኑ፡ቦቱ፡ወባሕቱ፡ኢያግሀዱ፡ኪያሁ፡
እስመ፡አብደሩ፡ስብሐተ፡ሰብእ፡ፈድፋደ፡
እምስብሐተ፡እግዚአብሔር።

፬ ይቤ፡ወውእቱ፡ይትቃወሞን፡ለምግባራቲነ፡
ወውእቱ፡ይዘነጕጎነ፡በኃጣውኢነ፡ውስተ፡
ሕግ ፡ ይተረጐም ፡ ዘንተ ፡ ከመ ፡ እግዚእ ፡
ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ኮነ ፡ ይፈቅድ ፡
ይምሀሮሙ፡ገቢረ፡ትምህርት፡ትርፍተ።

## የዓርብ፡ነግህ።

፳፰ ይህን ፡ ነገር ፡ አሰቡ ፤ ክፋታቸው ፡ የልብ
ዕውሮች፡አድርጋቸዋለችና፡በዚህም፡ሳቱ።

፳፱ እግዚአብሔር ፡ ሠውሮ ፡ ለጻድቁ ፡ የማለ
ጠውን ፡ አላወቁም ፤ ደግ ፡ ሰው ፡ የሚያገ
ውንም፡ዋጋ፡ተስፋ፡አላደረጉም።

፴ በሱ ፡ አምሳል ፡ ያለ ፡ ኃጢአት ፡ ሰውን፡ፈጥሮ
ታልና ፤ ነውር ፡ የሌለባቸው ፡ ንጹሐት
ነፍሳት ፡ የሚቀበሉት ፡ ብዙ ፡ ክብርን ፡
አላወቁም።

የሰሎሞን ፡ ጥበብ ፡ የምሥጢር ፡ ትርጓሜ፤ጻድ
ቁን ፡ ሰው ፡ (ክርስቶስን) ፡ እንግደለው ፡ካለው፡
ጀምሮ፡ንጹሐት፡ነፍሳት፡እስከ፡አለው፡ድረስ፡

፩ ተርጓሚው ፡ ለልባችን ፡ ደስ ፡ አያሰኝምና፡
ይላሉ ፡ አለ ፤ አይሁድ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ፡
ክርስቶስ ፡ የሚያደርጋቸውን ፡ አስደናቂ፡ተአ
ምራቶች ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ ከሐዲዎች ፡ ስለሆኑ፡
በእርሱ፡ላይ፡እንደ፡ቀኑ፡የባሕርይ፡አምላክ፡
እርሱንም ፡ ሊያጠምዱት ፡ በእርሱ ፡ ላይ፡
ምክንያት ፡ ያገኙ ፡ ዘንድ ፡ ሁል ፡ ጊዜ፡እንደሚ
ጠባበቁት፡ይተረጐማል።

፪ ሹመታቸውንም ፡ ስለ ፡ መጠበቅ ፡ መድኀኒ
የሚሠራው ፡ ሥራ ፡ ልቡናቸውን ፡ ደስ፡የሚያ
ሰኛቸው ፡ ምንም ፡ አልሆነም ፤ ይህ ፡ ሁሉ፡
ከሰይጣን ፡ በኩል ፡ የሚሠራ ፡ ምትሐት፡ነው፡
የሚሉ ፡ ሆኑ ፡ እንጂ ፤ ሥራው ፡ እውነት፡
መሆንዋን፡እያወቁ፡ከእርስዋ፡ፈቀቅ፡አሉ።

፫ በከበረ ፡ ወንጌል ፡ ከሊቃውንቱና ፡ ከፈሪሳ
ውያን ፡ ብዙዎች ፡ አመኑበት ፤ ነገር፡ግን፡እም
ነታቸውን ፡ ግልጽ ፡ አላደረጉም ፤ ከእግዚአ
ብሔር ፡ ክብር ፡ ይልቅ ፡ የሰውን ፡ ክብር፡መር
ጠዋልና፡እንዳለ።

፬ እሱ ፡ ሥራዎቻችንን ፡ ይቃወማቸዋል ፤ ሕግ
በማጣታችንም ፡ ይሣለቅብናል ፡ አለ ፤
ጌታችን፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ፍጹምነት
የሆነች ፡ ትምህርትን ፡ ሊያስተምራቸው
እንደ፡ወደደ፡ይህንን፡ይተረጐማል።

Scanned by CamScanner

ዘዓርብ፡ጽባሕ።

መሆነት ፡ ልበሙ ፡ ጽንዕተ ፡ ወጽንንተ ፡
ለግቢረ፡እከይ፤ውእቱኬ ፡ በእንተ ፡ ውእቱ ፡
ኮነት ፡ ምግባሩ ፡ ትትቃወሞን ፡ ለምግባራ
ቲሆሙ።

ወካዕበ፡በእንተ፡ቃሉ፡ወይዘነጉጉነ፡በስህ
ተትነ፡ውስተ ፡ ሕግ ፡ ይትረጐም ፡ ከመ ፡
እግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ ኢኀደገ፡ሎሙ፡
ምክንያተ ፡ በዘያመክንዩ ፡ ባቲ ፡ በእንተ ፡
ሃይማኖት ፡ ኢእምግቢረ ፡ ተአምራት ፡
መድምምተ ፡ አልባብ ፡ ወኢካልአተኒ ፡
ወኢእምኑ።

ወዘለፎሙ፡ወይቤሎሙ፡ኅሡ፡መጻሕፍተ፡
እንተ፡ትትሔዘቡ፡አንትሙ፡ከመ፡ይከውን፡
ለከሙ ፡ በሙ ፡ ሕይወት ፡ ዘለዓለም ፡
ወእሙንቱ፡ሰምዕ፡በእንቲአየ።

ወአዘዞሙ ፡ እግዚእነ ፡ ለኀሢሥኒ ፤ አኮ ፡
በአንብቦ፡ባሕቲቱ ፡ አላ ፡ ከመ ፡ ያእምሩ ፡
ትርጓሜ፡ነገረ፡ነቢያት ፡ ዘይመስል ፡ በእን
ቲአሁ፡ከመ፡ውእቱ፡መድኃኒሆሙ።

ይቤ፡ካዕበ፡ሶበሰ፡አመንክምዎ፡ለሙሴ፡እም
አመንክሙኒ፡ኪያየኒ፡እስመ፡ጸሐፈ፡ሙሴ፡
በእንቲአየ።

ወውእቱ ፡ ኮነ ፡ ይዘልፎሙ ፡ በእንተ ፡
ስሕተቶሙ ፡ ውስተ ፡ ሕግ ፤ እፎ ፡ ኢይት
መየጡ፡ወኢየኀሥሥዋ፡ለጽድቅ።

ይቤ፡ወንሕነ፡ነአምር፡ከመ፡አእምሮ፡እግዚ
አብሔር ፡ ምስሌሁ ፤ ወውእቱኬ ፡ በከመ ፡
ዘከርነ፡ከመ፡ውእቶሙ፡ኮኑ፡የአምሩ፡ከመ፡
አምላክ፡ውእቱ፡ወይተነትኑ፡እምሃይማኖት፡
ቦቱ፡በእንተ፡ፈቃደ፡ዚአሆሙ።

ይቤ፡ወወልደ፡እግዚአብሔር፡ይብል፡ርእሶ፡
ወተናገረ፡ትንቢት፡ቀደመት፡በአፈ፡ነቢይ፡
በእንተ፡እግዚእነ፡ ከመ፡ይሰመይ፡ውእቱ፡
ወልደ፡እግዚአብሔር ፡ በከመ ፡ ይቤላ ፡
መልአክ፡ለእግዝእትነ፡ማርያም፡ንጽሕት፡

የዓርብ፡ነግህ።

፴፮፤ ልባቸው ፡ ግን ፡ የጸናችና ፡ ለክፉ ፡ ሥራ ፡
የተገዛች፡ሆነች፤ይህ፡ነው፡ስለዚህ፡የእርሱ፡
ሥራ ፡ የእነርሱን ፡ ሥራዎች ፡ የምትቃወ
ማቸው፡ሆነች።

፴፯፤ ዳግመኛም ፡ ሕግን ፡ ስለመሳታችን ፡ ይሣለቅ
ብናል ፡ አለ ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡
ስለ፡ ሃይማኖትም ፡ ሆነ ፡ ለልብ ፡ ስለሚያስ
ደንቁ ፡ ተአምራት ፡ ስለ ፡ ሌላውም ፡ ሥራ ፡
ቢሆን ፡ በሚያመካኙባት ፡ ገንዘብ ፡ ምንም ፡
እንዳልተወ፡ነገር፡ግን፡እንዳላመኑበት።

፴፱፤ በእነርሱ ፡ የዘላለም ፡ ሕይወት ፡ እናገኝባቸ
ዋለን ፡ ብላችሁ ፡ የምትጠራጠሩአቸውን ፡
መጻሕፍት ፡ መርምሩ ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡
ዘለፋቸው፡ይተረጐማል፤እነርሱም፡ስለ፡እኔ፡
ምስክር፡ናቸው፡አለ።

፵፭፤ ጌታም ፡ እንዲመረምሩ ፡ አዘዛቸው ፤
በማንበብ፡ብቻ፡አይደለም፤እርሱ፡መድኃኒ
ታቸው፡እንደሆነ፡ስለ፡እርሱ፡የተነገረ፡የነ
ቢያትን፡ትንቢትና፡የምሳሌውን፡ትርጓሜ፡
ያውቁ፡ዘንድ፡ነው፡እንጂ።

፵፮፤ ዳግመኛ ፡ ሙሴንስ ፡ የአመናችሁት ፡ ከሆነ ፡
እኔንም፡ባመናችሁኝ፡ነበር፤ሙሴ፡ስለ፡እኔ፡
ጽፏልና፡አለ።

፶፤ እርሱም ፡ በኦሪት ፡ መጽሐፉ ፡ ውስጥ ፡
እንዴት፡ተመልሰው፡እውነትን፡አይሿትም፡
ብሎ፡ይዘልፋቸው፡ጀመረ።

፶፬፤ እግዚአብሔርን፡ማወቅ፡እንዳለው፡እኛ፡እና
ውቃለን ፡ ብለዋል ፡ አለ ፤ ይኸም ፡ አስቀ
ድመን፡እንደተናገርነው፡እነርሱ፡አምላክ፡
እንደሆነ፡አውቀው፡ሳለ፡በእርሱ፡ከማመን፡
ተፍገመገሙ ፤ ፈቃደ ፡ ሥጋቸውን ፡ ስለ ፡
መፈጸም፡ብለው።

፶፮፤ ራሱን፡የእግዚአብሔር፡ልጅ፡ነኝ፡ይላል፡አለ፤
የእግዚአብሔር፡ልጅ፡ተብሎ፡እንደሚጠራ፡
ስለ ፡ ጌታችን ፡ በነቢዩ ፡ አፍ ፡ ትንቢት፡
አስቀድሞ ፡ ተነገረ ፤ መልአኩ ፡ ቅዱስ ፡
ገብርኤል፡እመቤታችን፡ንጽሕት፡ማርያምን፡

Scanned by CamScanner

ዘዓርብ፡ጽባሕ።

እስመ፡ዘይትወለድ፡እምኔኪ፡ቅዱስ፡ውእቱ፡
እስመ፡ዘይትወለድ፡እምኔኪ፡ቅዱስ፡ውእቱ፡ወልደ፡እግዚአብሐር፡ይሰመይ።

፲፫፡ ይቤ፡ወንብረቱ፡ኢይትማሰል፡ምስለ፡ባዕድ፡ ወፍሉጥ፡ፍኖቱ፡ይተረጐም፡ዘንተ፡ከመ፡ መሐይምናን፡በክርስቶስ፡ኢኮና፡ፍናዊሆሙ፡ ወሑረቶሙ፡በሕገ፡ክርስቶስ፡ከመ፡ሕገ፡ ሰብእ፡ብሊት፤እስመ፡ሕገ፡ጽድቅ፡ይእቲ፡ ሕገ፡ብሊትኒ።

፲፬፡ ወሕገ፡ክርስቶስኒ፡ይእቲ፡ትርፍት፡ እልክቱሰ፡ዕቡያን፡ወእሉሰ፡ትሑታን።

፲፭፡ እልክቱሰ፡ያፀውርዎ፡ለሰብእ፡ክቡዳተ፤ ወእሉሰ፡ወሀቡ፡ነፍሳቲሆሙ፡በእንተ፡ ሰብእ፡ይርብሕዎሙ።

፲፮፡ እልክቱ፡ይጸልዑ፡ዘይዔምፆሙ፡ወእሉሰ፡ ይመይጡ፡መላትሒሆሙ፡ለዘይጸፍዕዎሙ፡ በእንተ፡ፍቅረ፡እግዚኦሙ።

፲፯፡ ይቤ፡ወይርሕቅ፡እምፍናዊነ፡ከመ፡ዘእምአ ራዊት፤ይተረጐም፡ከመ፡እግዚእነ፡ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ኮነ፡ይከልአሙ፡ለመሀይምናን፡ ቦቱ፡ከመ፡ይርሐቁ፡እምፍኖተ፡ዐላውያን።

፲፰፡ ወበእንተ፡ውእቱ፡ይቤ፡ለአርዳኢሁ፡ ተዓቀቡ፡እምብሑአሙ፡ለፈሪሳውያን፡ወሰ ዱቃውያን፡ዘውእቱ፡አድልዎ።

፲፱፡ ይቤ፡ከመ፡ዘእምአራዊት፡ይተረጐም፡ከመ፡ ዘይቀርብ፡እምአርዌ፡መሣጢ፡ያህጕል፡ ሥጋሁ፡ወከማሁ፡ኵሉ፡ዘይቀርብ፡ እምፍኖተ፡ዐላውያን፡ወየሐውር፡ውስቴታ፡ እስመ፡ያህጕላ፡ለነፍሱ።

፳፡ ይቤ፡ወይትሜከህ፡ከመ፡እግዚአብሔር፡ አቡሁ፡ወንርኢ፡ከመ፡ነገሩ፡ሐለው፡ ወናመክሮ፡ከመ፡ንርአይ፡ዘይከውን፡ በደኃሪቱ፤ይተረጐም፡ዘንተ፡ከመ፡ውእቶሙ፡

የዓርብ፡ነግህ።

ከአንቺ፡የሚወለደው፡ቅዱስ፡ነው፤የእግዚአብሔርም፡ልጅ፡ተብሎ፡ይጠራል፡እንዳላት።

፲፫፡ ኑሮው፡ከሌላ፡ጋር፡አይመሳሰልም፡ መንገዱም፡ልዩ፡ነው፡አለ፤ይኸንንም፡ እንዲህ፡ይተረጕማል፤በክርስቶስ፡ያመኑ፡ ምእመናን፡በክርስቶስ፡ሕግ፡አካሄዳቸውና፡ ሥራቸው፡እንደ፡አሪት፡ሰዎች፡ሕግ፡እንዳ ይደለ፡ይህንን፡ይተረጕማል፤የአሪት፡ሕግ፡ እውነተኛ፡ሕግ፡ነበረችና።

፲፬፡ ሕገ፡ክርስቶስ፡ወንጌል፡ግን፡ፍጽምት፡ሕግ፡ ናት፤እነዚያ፡ትዕቢተኞች፤እነዚህ፡ግን፡ ትሑታን፡ናቸው።

፲፭፡ እነዚያ፡ሰውን፡ከባድ፡ነገር፡ያሸክሙታል፤ እነዚህ፡ግን፡ይጠቅሟቸው፡ዘንድ፡ስለ፡ ሰዎች፡ነፍሳቸውን፡ይሰጣሉ።

፲፮፡ እነዚያ፡የሚገፉቸውን፡ይጠላሉ፤እነዚህ፡ ግን፡ስለ፡ጌታ፡ፍቅር፡ለሚጸፏቸው፡ጉንጫ ቸውን፡አዞረው፡ይሰጣሉ።

፲፯፡ ሰው፡ከአራዊት፡እንደሚርቅ፡ከመንገዳችን፡ ይርቃል፡አለ፤ጌታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ የእርሱ፡የሆኑ፡ምእመናን፡ከወንጀለኞች፡ መንገድ፡ይርቁ፡ዘንድ፡እንዲከለክላቸው፡ ይህንን፡ይተረጕማል።

፲፰፡ ስለዚህም፡ነገር፡ደቀ፡መዛሙርቱን፡ከፈሪሳ ውያንና፡ከሰዱቃውያን፡እርሾ፡ተጠበቁ፡ አለ፤ይኸውም፡ግብዝነት፡ነው።

፲፱፡ ከአራዊት፡እንደሚሸሽ፡አለ፤ወደ፡ነጣቂ፡ አውሬ፡የሚቀርብ፡ሥጋው፡በአውሬ፡ይተረ ተበልቶ፡እንደሚጠፋ፡ይህንን፡ይተረ ጕማል፤ወደ፡ወንጀለኞች፡መንገድ፡የሚቀ ርብና፡በውስጧም፡የሚሄድ፡ሁሉ፡ነፍሱን፡ ያጠፋታልና፡እንዲሁ፡ነው።

፳፡ እግዚአብሔርም፡አባቱ፡እንደሆነ፡ይመካል፤ ነገሩ፡ቀዋሚ፡እንደሆነ፡እንይ፤ከመልኩ፡ ማማር፡የተነሣ፡በመከራ፡ኛንፈትነው፡አለ፤ እነርሱ፡እነሆ፡እርሱ፡የእግዚአብሔር፡ልጅ፡

Scanned by CamScanner

ዎ፡ይትማከሩ፡በበይናቲሆሙ፡ወይብሉ፡
አስመ፡ዝንቱ፡ናሁ፡ሰመየ፡ከመ፡እግዚአ
ብሔር፡አቡሁ፡ወንመጥዎ፡እንከሰ፡ለሞት፡
ገሕነ፡ወንርአይ፡ዘይከውን፡በደኃሪቱ።
፲፪ አስመ፡ከኑ፡ይሰምዐ፡እመድኅን፡እንዘ፡
ወትቱ፡ይብል፡አመ፡አልዓልክምዎ፡
ለወልደ፡ዕጓለ፡እመሕያው፡አሜሃ፡ተአምሩ፡
ከመ፡አነ፡ወልዱ፡ለእግዚአብሔር።

ንኝ፡ብሏልና፡እንግዲህ፡ለሞት፡አሳልፈን፡
እንስጠው፡በመጨረሻው፡የሚሆነውን፡
እንይ፡ብለው፡እርስ፡በርሳቸው፡እንደተ
ማከሩ፡ይተረጉማል።

፳፩፡ መድኅን፡ጌታ፡የሰው፡ልጅ፡ክርስቶስን፡
ከምድር፡ከፍ፡አድርጋችሁ፡በሰቀላችሁት፡
ጊዜ፡እኔ፡የእግዚአብሔር፡ልጅ፡እንደ
ሆንኩ፡ያን፡ጊዜ፡ታውቃላችሁ፡ሲል፡
ይሰሙት፡ነበርና፡ለሞት፡አሳልፈን፡
እንስጠው፡መጨረሻውን፡እንይ፡ተባባሉ።

፲ ይቤ፡ወእመሰ፡ወልደ፡እግዚአብሔር፡
ወእቱ፡ዘበአማን፡ያድኅኖ፡ወይባልሖ፡
እምእለ፡ይቀውሙ፡በዕርፈት፡ወበዕዕለት፡
ዘንተ፡ይቤ፡ነቢይ፡በእንተ፡ዘኮነ፡ጊዜ፡
ሕማመ፡እግዚእ፡ማሕየዊት፡ጊዜ፡ብህሉ፡
አይሁድ፡ሎቱ፡ለእመ፡ኮንከ፡ወልደ፡እግዚአ
ብሔር፡ረድኬ፡እመስቀልከ።

፳፪፡ በእውነት፡እርሱ፡የእግዚአብሔር፡ልጅ፡
ከሆነ፡በጥላቻና፡በስድብ፡ከተነሡበት፡እጅ፡
ያድነው፡አለ፡አይሁድ፡የእግዚአብሔር፡
ልጅስ፡ከሆንክ፡ከመስቀል፡ውረድ፡ያሉትን፡
ሕይወት፡በሆነች፡በጌታ፡ሕማም፡ጊዜ፡ስለ፡
ሆነው፡ነቢይ፡ይህን፡ተናገረ።

፲ ወብህሉ፡እለ፡ተሰቅሉ፡ምስሌሁ፡ካዕበ፡
ለእመሰ፡ኮንከ፡ወልደ፡እግዚአብሔር፡
አድኅን፡ርእሰከ፡ወለነኒ፡ባልሐነ፡ወኮነ፡
አመክሮቶሙ፡ሎቱ፡በዝንቱ፡ቃል፡አኮ፡
ለኀሢሠ፡ጽድቅ፡አላ፡ተሣልቆት።

፳፫፡ ከእርሱ፡ጋር፡የተሰቀሉትም፡የእግዚአ
ብሔር፡ልጅ፡ከሆንክ፡ራስህን፡አድን፡
እኛንም፡አድነን፡አሉ፡መፈታተናቸው፡
እውነትን፡ለመፈለግ፡አይደለም፡ለመዘበት፡
ነው፡እንጂ።

፲ ይቤ፡በሞት፡ኅሡር፡ንኰንኖ፡ይተረጎም፡
ከመ፡ፈትሐ፡ላዕለ፡ወልደ፡እግዚአብሔር፡
በስቅለት፡እስመ፡ውእቱ፡ጽሑፍ፡ውስተ፡
ሕጎሙ፡ርጉም፡ኵሉ፡ዘተሰቅለ፡ዲበ፡
ዕፅ።

፳፬፡ የከፋ፡የውርደት፡ሞትን፡እንፍረድበት፡አሉ፡
በእግዚአብሔር፡ልጅ፡ላይ፡በስቅላት፡
እንዲሞት፡እንደ፡ፈረዱበት፡ይተረጉማል፡
በዕንጨት፡የተሰቀለ፡ሁሉ፡የተረገመ፡
እንደሆነ፡በኦሪታቸው፡ተጽፎአልና።

፲ ወእግዚእነሰ፡ያረ፡እምኔሆሙ፡ውእቱ፡
ወፈጸመ፡ፈቃዶ፡ቅድስተ፡ወረሰየ፡ለነፍሱ፡
መርገመ፡በከመ፡ይቤ፡ሐዋርያ፡ከመ፡
ይሠዐር፡እምኔነ፡መርገመ፡እንተ፡ዘእም
ቀዳሚ።

፳፭፡ ጌታችንም፡ከእርሱ፡ይህን፡ርግማን፡
ተሸክሞ፡ልዩ፡ፈቃዱን፡ፈጸመ፡ሰውነ
ቱንም፡የተረገመች፡አሰኛት፡ሐዋርያው፡
አስቀድሞ፡በእኛ፡ዘንድ፡የነበረውን፡
መርገም፡ያጠፋ፡ዘንድ፡ሰውነቱን፡
ለርግማን፡ሰጠ፡እንዳለ።

፲ ይቤ፡ዘንተ፡ሐለዩ፡ወስሕቱ፡ወአንቈረቶሙ፡
እከዮሙ፡ዘከረ፡ነቢይ፡ዘኮነ፡ላዕሌሆሙ፡እም

፳፮፡ ይህን፡ነገር፡አሰቡ፡ክፋታቸው፡የልብ፡
ዕውሮች፡አደርጋቸዋለችና፡አለ፡ነቢዩ፡

## ዘዓርብ፡ጽባሕ።

ተዘክሮ፡ሙስና፡ቀዲሙ።

፳፯ ካዕበ፡ይቤ፡ዘንተ፡ሐለዩ፡ወስሕቱ፡ዘውእቱ፡ ስሕቱ ፡ እሙንቱ ፡ እምፍኖተ ፡ መድኃኒት ፡ በእንተ ፡ ዘገብርዎ ፡ ወሐለዩ ፡ ቦቱ ፡ ወኮኑ ፡ ዕውራነ፡ወስኩራነ፡እምቅንዓት።

፳፰ ይቤ ፡ ወኢየአምሩ ፡ ኅቡዓቲሁ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ዘውእቱ ፡ ኢየእመሩ ፡ ውእቶሙ ፡ ከመ፡ዝንቱ፡ዘፈጸሙ፡ፈቃዶሙ፡ዘውእቱ፡ መድኃኒሆሙ፡ወውእቱ፡አምላክ፡ኵሉ።

፳፱ ይቤ፡ወዐስበ፡ዘጽድቅ፡ኢተሰፈዉ፡ዘውእቱ፡ ኢተመጠዉ፡በጽድቅ፡ወኢኮኑ፡ረድአ፡ለእ ግዚአብሔር፡ወኢተሰፈዉ፡ዕሤቶሙ፡ከመ፡ አርድእት፡ኅሩያን፡ወኢያድምዑ፡እምክብር፡ ወኢዘይትልዎ።

፴ ይቤ፡ወኢሐለዩ፡በእንተ፡ነፍሳት፡ንጹሐት፡ እለ ፡ ኖሙ ፡ ይትረጐም ፡ ከመ ፡ ኢኮነ ፡ ኅሊናሆሙ፡ዘእንበለ፡ውስተ፡ዛቲ፡ዓለም፡ ኃላፊት፡ወኢይኄልዩ፡ውስተ፡ዝ፡ሞት፡ ወኢይገብሩ፡ለነፍሳቲሆሙ፡ግብረ፡ሠናየ፡ ከመ፡ይፃዑ፡እምዝንቱ፡ሥጋ፡ዘእንበለ፡ ደነስ፤ወይኩን፡ሞቶሙ፡ፍልሰተ፡ኀበ፡ ገነት፤አኮ፡እንዘ፡ምውታን፡ውስተ፡ገሀነም።

፴፩ ወንስአሎኬ፡ለእግዚእነ፡ከመ፡ይጸግወነ፡ ገቢረ፡ፈቃዱ፡ወከመ፡ንርከብ፡በፀዓትነ፡ እምዝንቱ፡ዓለም፡ንህነ፡ንጹሐኒነ፡እምር ስሐተ፡ኃጢአት።

ዘሎቱ፡ስብሐት፡ወክብር፡ለዓለመ፡ዓለም፡ አሜን።

ዘዘካርያስ፡ነቢይ፡በረከተ፡አምላኩ፡ ትኩን፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡ አሜን።

## የዓርብ፡ነግህ።

ከቀድሞው፡ጥፋታቸው፡የተነሣ፡በእነርሱ፡ ላይ፡የሆነውን፡ይህን፡አስታወሰ።

፳፯ ዳግመኛም፡ይህን፡አስበው፡ሳቱ፤ይህም፡ እነርሱ፡የሳቱት፡የድኅነትን፡መንገድ፡ነው፤ እነርሱ፡በቅንዓት፡ሰክረው፡ከልቡና፡ ማስተዋል፡የታወሩ፡ሁነው፡ስለፈጸሙት፡ ስሕተት፡ነው፡አለ።

፳፰ እግዚአብሔር፡ሠውሮ፡ለጻድቁ፡የሚሰ ጠውን፡ዋጋ፡አላወቁም፡አለ፤ይኸውም፡በፈ ቃዳቸው፡የሞት፡ፍርድን፡የፈጸሙበት፡ እርሱ፡የሁሉ፡ፈጣሪና፡መድኃኒታቸው፡ እንደሆነ፡ስላላወቁ፡ነው።

፳፱ ደግ፡ሰው፡የሚያገኘውንም፡ዋጋ፡ተስፋ፡አላደ ረጉም፡አለ፤ይኸውም፡በእውነት፡ተቀብለው፡ ለእግዚአብሔር፡ደቀ፡መዛሙርት፡አልሆኑም፤ እንደ፡ተመረጡት፡ሐዋርያት፡ዋጋቸውን፡ ተስፋ፡አላደረጉም፤ከክብርና፡ከሚመስለው፡ ሁሉ፡ምንም፡አላገኙም።

፴ በሞት፡የተለዩ፡ንጹሓት፡ነፍሳት፡የሚቀበ ሉትን፡ብዙ፡ክብርን፡አላሰቡምና፡አለ፤ አሳባቸው፡ለኀላፊው፡ዓለም፡በቀር፡እንዳ ልሆነ፡ወደዚህ፡ሞት፡እንደማያስቡ፤ከዚህ፡ ሥጋ፡ያለ፡ኃጢአት፡ይወጡ፡ዘንድ፡በጎ፡ ሥራን፡ለነፍሳቸው፡እንደማይሠሩ፡ ሞታቸውም፡ወደገነት፡መሄጃ፡እንዲሆን፡ ይኸንን፡ይተረጕማል፤በገሃነም፡ሙታን፡ እንዲሆኑ፡አይደለም።

፴፩ ጌታችንንም፡ፈቃዱን፡መፈጸምን፡ይሰጠን፡ ዘንድ፡እንለምነው፤ከዚህም፡ዓለም፡ በምንለይ፡ጊዜ፡ያለ፡ኃጢአት፡እኛ፡ ንጹሓን፡ሁነን፡እንገኝ፡ዘንድ።

ለእርሱ፡ክብር፡ምስጋና፡ይሁን፡ለዘላለሙ፡ አሜን።

የአምላኩ፡በረከት፡ከእኛ፡ጋር፡ለዘላለሙ፡ ትኑርና፡ነቢዩ፡ዘካርያስ፡የተናገረው፡ ትንቢት፡ይህ፡ነው።

Scanned by CamScanner

ዘዓርብ፡ጽባሕ።

ምዕ፡፲፩፡፲፩-፲፬።

...ወተመየጥ፡ይእተ፡አሚረ፡ወየአምርዎን፡
...ከነዓን፡ለአባግዕየ፡እለ፡ተዓቅባ፡እስመ፡ቃለ፡
እግዚአብሔር፡ውእቱ።

...ወእብለሙ፡እመ፡አሥመርኩክሙ፡በቅድ
...ሚክሙ፡ሀቡኒ፡ዐስብየ፡ወእመ፡አኮ፡ኅድጉ፡
...ወድልዉ፡ሊተ፡አስብየ፡ሠላሳ፡ብሩረ።

...ወይቤለኒ፡እግዚአብሔር፡ደዮ፡ውስተ፡
...ልንቅርት፡ወፍትኖ፡ለእመ፡ጽሩይ፡ውእቱ፡
...ከመ፡አመከርዎ፡እሙንቱ፤ወነሣእኩ፡
...ሥላሳ፡ብሩረ፡ወወደይክዎ፡ውስተ፡
...ልንቅርት፡በቤተ፡እግዚአብሔር።

...ወገደፍኩ፡ካልእተ፡በትርየ፡ሐብለ፡ከመ፡
...እሚጥ፡ኪዳንየ፡ወምክናን፡ዘማዕከለ፡ይሁዳ፡
...ወማዕከለ፡ኢየሩሳሌም።

...ሚክያስ፡ነቢይ፡በረከተ፡አምላኩ፡ትኩን፡
...ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ምዕ፡፯፡፪-፬።

...እሌ፡ሎሙ፡እስመ፡ኀልቀ፡ኄር፡እምድር፡
...ወአልቦ፡ሰብእ፡ዘያረትዕ፡ፍትሐ፤ኵሉ፡
...ደማ፡ወኵሉ፡ያጠውቅ፡ቢጾ፡ወያመ
...ንድብ።

...ወንሥኡ፡ዕደዊሆሙ፡ለዕኩይ፡መልአክኒ፡
...ይስእል፡ወመኰንን፡ይየውህ፡ከመ፡ይርከብ፡
...ትወተ፡ነፍሱ።

...ወአጠፍአ፡ለበረከቶሙ፡ከመ፡ብልዓ፡ፃፄ፡
...ወየሐልፅ፡ወየዓርግ፡ዲበ፡ንዋይ፤በዕለተ፡
...ኦ፡እሌ፡ለኪ፡እስመ፡በጽሐኪ፡ዕለተ፡
...ዘይእዜ፡ይበጽሐሙ፡ገዐር።

የዓርብ፡ነግህ።

ምዕ፡፲፩፡፲፩-፲፬።

፲፩፤ እኔም፡ያን፡ጊዜ፡ከምሕረት፡ወደ፡መዓት፡
እመለሳለሁ፤ የእግዚአብሔር ፡ ትእዛዝ ፡
ነውና፡የተጠበቁ፡በጎቼን፡የከነዓን፡ሰዎች፡
ያውቋቸዋል።

፲፪፤ በፊታችሁ፡አገልግሎቱ፡ደስ፡አሰኝቷችሁ፡
ከሆነ፡ዋጋዬን፡ስጡኝ፤ያለዚያ፡ግን፡ተዉት፡
አልኳቸው፤እነሱም፡ለዋጋዬ፡ሠላሳ፡ብር፡
መዘኑ።

፲፫፤ እግዚአብሔርም ፡ እነርሱ ፡ ፈጣሪያቸውን ፡
እንደ፡ተፈታተኑት፡የጠራ፡ብር፡እንደሆነ፡
ወደ ፡ ከውሩ ፡ አግብተህ ፡ ፈትነው ፡ አለኝ፤
እኔም፡ያን፡ሠላሳ፡ብር፡አንሥቼ፡በእግዚአ
ብሔር ፡ ማደሪያ ፡ በቤተ ፡ መቅደስ ፡ ባለ ፡
ከውር፡ጨመርሁት።

፲፬፤ በኢየሩሳሌምና፡በይሁዳ፡መካከል፡ያለ፡አገዛ
ዜንና፡መሐላዬን፡አጠፋ፡ዘንድ፡የበትሬን፡
ሁለተኛ፡የምትሆን፡ገመድን፡ጣልኋት፡አለ፤
(ንጉሥን)።

የአምላኩ፡በረከት፡ከእኛ፡ጋር፡ለዘላለሙ፡
ትኑርና ፡ ነቢዩ ፡ ሚክያስ ፡ የተናገረው ፡
ትንቢት፡ይህ፡ነው።

ምዕ፡፯፡፪-፬።

፪፤ ከዚህ፡ዓለም፡በጎ፡ሰው፡ጠፍቷልና፤በዚህ፡
ዓለም ፡ ፍርድ ፡ የሚያቀና ፡ ሰው ፡ የለምና ፡
ወዮላቸው!ሁሉ፡ይበድላል፤ሁሉም፡ባልንጀ
ራውን፡ያስጨንቃል።

፫፤ ለክፉም፡ነገር፡እደ፡ልቡናቸውን፡ያነሣሉ፤
ልቡናው ፡ የወደደችውን ፡ ያገኝ ፡ ዘንድ ፡
አለቃው ፡ ይለምናል ፤ አገረ ፡ ገዥውም ፡
ያታልላል።

፬፤ ብል፡ነቀዝ፡በጨለማ፡ቀን፡ወደ፡ብስጡ፡እን
ብል፡ነቀዝ፡እንደ፡በላው፡ልብስ፡አድ
ዴወጣ፡ብል፡ነቀዝ፡እንደ፡በላው፡ልብስ፡አድ
ርጌ፡ያጠራቀሟት፡ገንዘባቸውን፡አጠፋታለሁ፤
ዛሬ፡በዘመዶችሽ፡ጩኸት፡የሚያርስባቸውን፡
ፍዳ፡የምትቀበይበት፡ቀን፡ደርሷልና፡ወዮልሽ።

Scanned by CamScanner

| ዘዓርብ፡ጽባሕ። | የዓርብ፡ነግህ። |
|---|---|
| ፭፤ ኢትትአመንዎሙ፡እንከ፡ለአእርክቲክሙ፡ ወኢትትወከልዎሙ፡ለመላእክት፤ወእምብ እሲትከ፡ዘውስተ፡ሕፅንከ፡ተዓቀብ፡ከመ፡ ትዕበዮ። | ፭፤ እንግዲህስ፡ወዳጆቻችሁን፡አትመኗቸው፤አለቆቻችሁንም፡ተስፋ፡አታድርጓቸው፤ጣዖት፡እናምልክ፡ብትልህ፡እምቢ፡ትላት፡ዘንድ፡አጠገብህ፡ከምትተኛ፡ሚስትህም፡ተጠበቅ። |
| ፮፤ እስመ፡ወልድኒ፡የኀሥር፡አባሁ፡ወወለትኒ፡ ትትነሣእ፡ዲበ፡እማ፡ወመርዓትኒ፡ላዕለ፡ ሐማታ፤ወኵሉ፡ሰብአ፡ቤቱ፡ይፃረሮ፡ ለሰብእ። | ፮፤ በዚያ፡ወራት፡ልጅ፡አባቱን፡ያዋርዳል፤ሴት፡ልጅም፡በእናቷ፡ላይ፡በጠላትነት፡ትነሣለች፤ምራትም፡በአማቷ፡ላይ፡ቤተሰቦችም፡አሳዳሪያቸውን፡ይጣሉታልና። |
| ፯፤ ወአንሰ፡ዲበ፡እግዚአብሔር፡እአርግ፤ ወእሴፎ፡ለአምላኪየ፡ወመድኃኒየ፤ወይሰ ምዓኒ፡አምላኪየ። | ፯፤ እኔ፡ግን፡በእግዚአብሔር፡አምኜ፡አርፋለሁ፤የሚያድነኝ፡ፈጣሪዬንም፡አምነዋለሁ፤ፈጣሪዬም፡ይሰማኛል። |
| ፰፤ ወኢይከውን፡ሰላቀ፡ለጸላዕትየ፤እመኒ፡ ድኀፅኩ፡እትነሣእ፡ወእመኒ፡ነበርኩ፡ ውስተ፡ጽልመት፡እግዚአብሔር፡ያበርህ፡ ሊተ። | ፰፤ እኔም፡ለጠላቶቼ፡መዘባበቻ፡አልሆንም፤በመከራውም፡ብሰነካከል፡እነሣለሁ፤በመከራ፡ጨለማ፡ውስጥም፡ብቀመጥ፡እግዚአብሔር፡ብርሃነ፡ረድኤቱን፡ያበራልኛል። |
| ዘአሞጽ፡ነቢይ፡በረከቱ፡አምላኩ፡ትኩን፡ ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን። | የአምላኩ፡በረከት፡ከእኛ፡ጋር፡ለዘላለሙ፡ትኑርና፡ነቢዩ፡አሞጽ፡የተናገረው፡ይህ፡ነው። |
| ምዕ፥፪፥፬–፲፪። | ምዕ፥፪፥፬–፲፪። |
| ፬፤ ከመ፡ዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡በእንተ፡ሠላስ፡ ኃጢአቶሙ፡ለደቂቀ፡ይሁዳ፡ወበእንተ፡ አርባዕ፤ኢይትመየጠሙ፡እስመ፡ዐለዉ፡ ሕገ፡እግዚአብሔር፡ወኢዐቀቡ፡ትእዛዞ፤ወአ ስሐቶሙ፡ከንቶሆሙ፡ዘገብሩ፡አበዊሆሙ፡ ወእሙንቱኒ፡ተለዉ፡ድኅሬሆሙ። | ፬፤ እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለ፤ኢታምልከን፡አፍርሰዋልና፤ዘጠኙንም፡ሕግጋት፡አልጠበቁምና፤አባቶቻቸው፡የሠሩት፡ጣዖታቸው፡አስቷቸዋልና፡እነርሱም፡አባቶቻቸውን፡ተከትለዋልና፡ለይሁዳ፡ልጆች፡ስለ፡ሦስቱና፡ስለ፡አራቱ፡ኃጢአታቸው፡አልመለስላቸውም። |
| ፭፤ ወእፌኑ፡እሳተ፡ላዕለ፡ይሁዳ፡ወትበልዕ፡ መሠረታቲሃ፡ለኢየሩሳሌም። | ፭፤ በይሁዳ፡ወገኖችም፡ጦር፡መቅሠፍት፡አመጣለሁ፤የኢየሩሳሌምንም፡ሥር፡መሠረቷን፡ታጠፋለች። |
| ፮፤ ከመ፡ዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡በእንተ፡ሠላስ፡ ኃጢአቶሙ፡ለእስራኤል፡ወበእንተ፡አርባዕ፡ ኢይትመየጠሙ፤እስመ፡ሤጡ፡ጻድቀ፡ በወርቅ፡ወነዳየ፡በአሣዕን፤በዘይከይዱ፡ ምድረ። | ፮፤ እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለ፤ጻድቁን፡በወርቅ፡ሸጠውታልና፤ድኃውንም፡ምድርን፡በሚረግጡበት፡ጫማ፡ረግጠውታልና፤ስለ፡ሦስቱና፡ስለ፡አራቱ፡ኃጢአታቸው፡አልመለስላቸውም። |
| ፯፤ ወይኰርዑ፡አርእስተ፡ነዳያን፡ወይመይጡ፡ ፍትሐ፡ምስኪናን፡አብ፡ወወልድ፡ይበውኡ፡ ኀበ፡አሐቲ፡ብእሲት፡ከመ፡ያርኵሱ፡ሕገ፡ አምላኮሙ። | ፯፤ የድኆችንም፡ራስ፡ቀጥቅጠዋልና፤የድኆችንም፡ፍርድ፡ለውጠዋልና፤አባትና፡ልጅም፡የፈጣሪያቸውን፡ሕግ፡ያፈርሱ፡ዘንድ፡ከአንዲት፡ሴት፡ይደርሳሉና። |
| ፰፤ ወየአሥሩ፡አልባሲሆሙ፡ወይገብሩ፡መንጦ ላዕተ፡ውስተ፡ምሥዋዕ፡ወይሰትዩ፡ወይነ፡ ትዕግልት፡በቤተ፡አምላኮሙ። | ፰፤ ልብሳቸውንም፡ከዓምድ፡እስከ፡ዓምድ፡አስረው፡ለጣዖቱ፡መሠዊያ፡መጋረጃ፡ያደርጋሉ፤ሰርቀው፡ቀምተው፡አምጥተው፡በፈጣሪያቸው፡ቤት፡በቤተ፡መቅደስ፡ወይንን፡ይጠጣሉ። |

ዘዓርብ፡ጽባሕ።

ወአነ፡አጥፋዕክዎ፡ለአሞሬዎን፡እምቅድ
ሆሙ፡ዘኑኁ፡ከመ፡ኑኃ፡አርዝ፡ወጽንዐ፡
ም፡ጽኑዕ፡አውልዕ፡ወአጥፋዕኩ፡ፍሬሁ፡
ምልዕሉ፡ወሥርዎሂ፡በታሕቴሁ።

ወአነ፡አውጻእኩክሙ፡እምድረ፡ግብጽ፡ወወ
ሰድኩክሙ፡ገዳመ፡አርብዓ፡ዓመተ፡ከመ
ትወርስክሙ፡ምድረ፡አሞሬዎን።
ወአንሣእኩ፡እምደቂቅክሙ፡ነቢያተ፡ወእምወ
ራዙቲክሙ፡እለ፡ይቄድሱ፡ሊተ፡ኢኮነሁ፡
ዝንቱ፡ደቂቀ፡እስራኤል፡ይቤ፡እግዚአ
ብሔር።
ወአስተይክምዎሙ፡ወይነ፡ለቅዱሳንየ፡ወትከል
ክምዎሙ፡ለነቢያት፡ወትብልዎሙ፡ኢትት
ነበዩ፡ለነ።
በእንተ፡ዝንቱ፡ናሁ፡አነ፡አንከረክረክሙ፡
በታሕቴክሙ፡ከመ፡ያንኰረኵር፡ሠረገላ፡
ሐሠር።
ወኢይክል፡ረዋጺ፡አምሥጦ፡ወኃያልኒ፡
ኢያጸንዕ፡በጽንዑ፡ወመስተቃትልኒ፡
ኢያድኅን፡ነፍሶ።
ወቀስታዊኒ፡ኢይቀውም፡ወረዋጺኒ፡
ኢያመሥጥ፡ወመስተጽዕንኒ፡ኢያወጽእ፡
ነፍሶ።
ወኃያልኒ፡ዘበ፡ልብ፡ኢይቀውም፡በዕለተ፡
ቀትል፡አላ፡ዕራቆ፡ይጐይይ፡ይእተ፡አሚረ፡
ይቤ፡እግዚአብሔር።

ምዕ፡፫፡፩–፭።

ስምዑ፡ዘንተ፡ነገረ፡ዘእቤለክሙ፡አነ፡እግዚ
አብሔር፡ቤቶ፡እስራኤል፡ወኵሉ፡ሕዝብ፡
ዘአውጻእኩክሙ፡እምድረ፡ግብጽ፡እንዘ፡
እብል።
ዘእንበለ፡ክሙ፡ኪያክሙ፡አእመርኩ፡እምኵሉ፡
አሕዛበ፡ምድር።
በእንተ፡ዝንቱ፡እትቤቀለክሙ፡በእንተ፡
ኵሉ፡ኃጢአትክሙ፡የሐውሩኑ፡ክልዔቱ፡
ኅቡረ፡እንዘ፡ኢይትረአዩ።
ይጥሕርኑ፡አንበሳ፡በከ፡በውስተ፡ግቡ፡
እንበለ፡ዘይበልዕ፡ይጥሕርኑ፡ዕጓለ፡
አንበሳ፡በውስተ፡ግቡ፡በከ፡እንዘ፡ቦ፡
ዘመሥጥ።

የዓርብ፡ነግህ።

፱፡ እኔ፡ግን፡ርዝመቱ፡እንደ፡ዝግባ፡ጽናቱ፡
እንደ፡ወይራ፡ጽንዓት፡የሚሆን፡አሞሬ
ዎንን፡ከፊታቸው፡አጠፋሁላቸው፤ከበላዩ፡
ያለ፡ፍሬውን፡(ልጁን)፡ከበታቹም፡ያለ፡
ሥሩን፡(አባትነቱን)፡አጠፋሁ።
፲፡ የአሞሬዎንን፡ርስት፡አወርሳችሁ፡ዘንድ፡
ከግብጽ፡ምድር፡አወጣኋችሁ፤አርባ፡
ዓመትም፡በምድረ፡በዳ፡አዞርኋችሁ።
፲፩፡ ከልጆቻችሁ፡ነቢያትን፡ከጐልማሶቻችሁ፡
እኔን፡የሚያመሰግኑ፡ሌዋውያንን፡መረጥሁ፤
የእስራኤል፡ልጆች፡ሆይ፡ነገሩ፡እንዲህ፡አይ
ደለምን?አለ፡እግዚአብሔር።
፲፪፡ ለቅዱሳኖቼ፡ወይንን፡ታጠጧቸዋላችሁ፤ነቢ
ያትንም፡ማስተማርን፡ትከለክሏቸዋላችሁ፤
ትንቢቱንም፡አትናገሩብን፡ትሏቸዋላችሁ።
፲፫፡ ስለዚህ፡ሠረገላ፡ብዕሩን፡እንዲያደቅ፡በበታ
ቻችሁ፡ባለ፡መሬት፡እኔ፡አደቃችኋለሁ።

፲፬፡ የሚሮጥ፡ሰው፡ማምለጥ፡አይችልም፤ኃይለ
ኛውም በጉልበቱ፡ሩጦ፡አይዝም፤አርበ
ኛውም፡ነፍሱን፡አያድንም።
፲፭፡ ቀስተኛ፡አይቆምም፤የሚሮጥም፡አያመ
ልጥም፤በፈረስም፡የተቀመጠ፡ሰው፡ነፍሱን፡
ከመከራ፡አያድንም።
፲፮፡ እግዚአብሔር፡ልበ፡ሙሉ፡ጐበዝ፡በሰልፍ፡
ቀን፡ጋሻ፡ጦሩን፡ጥሎ፡ያን፡ጊዜ፡ይሸሻል፡
እንጂ፡አይቆምም፡አለ።

ምዕ፡፫፡፩–፭።

፩፡ ከግብጽ፡ያወጣኋችሁ፡የእስራኤል፡ወገኖች፡
ሕዝቡም፡ሁሉ፡እኔ፡እግዚአብሔር፡እንዲህ፡
ብዬ፡የነገርኋችሁን፡ይህን፡ነገር፡ስሙ።

፪፡ በዚህ፡ዓለም፡ካሉ፡አሕዛብ፡ሁሉ፡ይልቅ፡
እናንተን፡ብቻ፡ወደድሁ።
፫፡ ይህን፡ስለ፡አደረጋችሁ፡በኃጢአታችሁ፡
ሁሉ፡እበቀላችኋለሁ፤ሁለቱ፡ሰዎች፡አንድ፡
ላይ፡ሳይተያዩ፡ይሄዳሉን?
፬፡ አንበሳ፡በጉድጓድ፡ውስጥ፡የሚበላው፡ሳለ፡
በብላሽ፡ይጮኻልን?የአንበሳ፡ደቦልስ፡
በብላሽ፡ይጮኻልን?በጉድጓዱ፡ሳለ፡በከንቱ፡
የነጠቀው፡
ይጮኻልን?

Scanned by CamScanner

## ዘዓርብ፡ጸባሕ።

ይወድቅኑ፡ዖፍ፡ውስተ፡ምድር፡ዘኢ.ተሠግረ፡

፮፡ ትትጋባዕኑ፡መሥገርት፡ዘእንበለ፡ተአኀዝ።
ይነፍኑኑ፡ቀርነ፡በሀገር፡ወኢይደነግፁኑ፡

፯፡ አሕዛብ፡ይመጽእኑ፡ዕኩይ፡ውስተ፡ሀገር፡
ዘእግዚአብሔር፡ኢ.ገብረ።

፰፡ እስመ፡አልቦ፡ዘይገብር፡እግዚአብሔር፡
ዘኢ.ከሠተ፡ወዘኢ.ነገረ፡ለአግብርቲሁ፡
ነቢያት።

ዘሆሴዕ፡ነቢይ፡በረከተ፡አምላኩ፡ትኩን፡
ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ምዕ፡፲፡፮-፲።

፮፡ ከመ ሣዕር፡ዘመልአ፡ውስተ፡ገራህት፡
ለላሕም፡ከማሁ፡ቤቱ፡ውስተ፡ቤተ፡አዎን፡
ሰብአ፡ሰማርያ፡እስመ፡ለሐውዎ፡ሕዝብ፤
ወበከመ፡እእመርዎ፡ከማሁ፡ይሥሕቁ፡
ዲበ፡ክብሩ፡እስመ፡ሰለብዎ፡ወፈለሰ፡
እምኔሁ።

፯፡ ወኪያሁኒ፡ኀመይዎ፡ወወሰድዎ፡ብሔረ፡
ፋርስ፡አምኃሁ፡ለኢያሪም፡ንጉሥ፡ዐገውዎ፡
ወመጠውዎ፤ ወተሐፍረ፡እስራኤል፡
በምክሩ።

፰፡ ገደፈቶ፡ሰማርያ፡ለንጉሣ፡ከመ፡ሐሠር፡
ውስተ፡ገጸ፡ማይ።

፱፡ ወይትከሠት፡ወግረ፡ጣዖቱ፡ለእስራኤል፡
ሦከ፡ወአሜከላ፡ይበቍል፡ውስተ፡ምሥዋዓ
ቲሆሙ። ወይብልዎሙ፡ለአድባር፡ደቁ፡
ላዕሌነ፡ወለአውግርኒ፡ድፍኑነ።

፲፡ በእንተ፡ዘአበሰ፡እስራኤል፡በአውግሪሁ፤
በኀበ፡ቆማ፡እገሪሆሙ፡በሀየ፡ይረክቦሙ፡
ቀትል፡በውስተ፡አውግር።
ዘተወክፈ፡ነቢየ፡በል።

### ክፍል፡፳፪።

ጸሎት፡እንተ፡ስምዖን፡ዓምዳዊ።

፩፡ **አ፡እግዚእየ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡** ዘአሠሩከ፡
ወወሰዱከ፡ኀበ፡ዐጸደ፡ሊቀ፡ካህናት፡እሥረኒ፡
ወሰሐበኒ፡እስከ፡ኀበ፡ዐጸድከ፡ማኅየዊት።

፪፡ **አ፡እግዚእየ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡** ዘተአሰርከ፡
እንዘ፡አንተ፡አሳሪሆሙ፡ለዕመቃት፡ወለልዐ

## የዓርብ፡ነግህ።

፮፡ ወፍስ፡ባልተጠመደ፡ወጥመድ፡ይያዛልን?
ወጥመድስ፡ሳትይዝ፡ትሰበሰባለችን?

፯፡ በሀገር፡ውጋ፡ውጋ፡የሚል፡ነጋሪት፡
ይመታሉን? ያን፡ጊዜ፡አሕዛብ፡አይደነግ
ጡምን?**እግዚአብሔር፡** ያላዘዘው፡መከራስ፡
በሀገር፡ይመጣልን?

፰፡ **እግዚአብሔር፡** የሚያደርገውን፡ነገር፡ለአገ
ልጋዮቹ፡ለነቢያት፡ገልጦ፡ያልተናገረው፡
የለምና፤**እግዚአብሔር፡** ያላዘዘው፡መከራስ፡
በሀገር፡ይመጣልን?

የአምላኩ፡በረከት፡ከእኛ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡
ትኑርና፡ነቢዩ፡ሆሴዕ፡የተናገረው፡ትንቢት፡
ይህ፡ነው።

ምዕ፡፲፡፮-፲።

፮፡ በእርሻ፡መካከል፡ያለ፡ሣርን፡ለበሬ፡ከበው፡
እንዲያበሉት፡እንደዚሁም፡የሰማርያ፡
ሰዎች፡የጣዖቱን፡ቤት፡ከበው፡አደሩ፤
ለንጉሡ፡ሕዝቡ፡አለቀሱለት፤ጌጡን፡ገፈው
ታልና፡ባለጸግነቱም፡ከእርሱ፡ጠፍቷልና፡
እንደሚያውቁት፡መጠን፡ክብሩን፡በማጣቱ፡
ይዘብቱበታል።

፯፡ እርሱን፡(ኤፍሬምን)፡ወደ፡ፋርስ፡አገር፡
አስረው፡ወስደው፡ለንጉሡ፡ለስልምናሶር፡
እጅ፡መንሻ፡አድርገው፡ሰጡት፡እስራኤል፡
በምክሩ፡አፈረ።

፰፡ ጥራጊን፡በውኃ፡ላይ፡እንዲጥሉ፡ሰማርያ፡
ንጉሥዋን፡በመከራ፡ጣለችው።

፱፡ እስራኤል፡ጣዖቱን፡ያቆመበት፡ኮረብታ፡
ይገለጣል፤ መሠዊያቸውም፡ፈርሶ፡እሾህ፡
አሜከላ፡ይበቅልበታል፤ተራሮችን፡ውደቁብን፡
ኮረብቶችንም፡ተጫኑን፡ይሏቸዋል።

፲፡ እስራኤል፡በኮረብታው፡ስለበደለ፡
እግራቸው፡በቆመበት፡በዚያ፡በኮረብታው፡
ሰልፍ፡ያገኛቸዋል።
ነቢዩን፡የተቀበለ፡በል።

### ክፍል፡፳፪።

ሰውነቱን፡በምሰሶ፡ላይ፡ያሰረ፡የስምዖን፡
ጸሎት፡ይህ፡ነው።

፩፡ ወደ፡ሊቀ፡ካህናቱ፡ግቢ፡አስረው፡የወሰዱህ፡
**ጌታዬ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ሆይ፡** ማኅየዊት፡
ወደሆነች፡ዐጸድህ፡ድረስ፡አስረህ፡ሳበኝ።

፪፡ **ጌታዬ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ሆይ፡** ጥልቆችንና፡
ከፍተኞችን፡ፍጥረታት፡በቃልህ፡አስረህ፡

Scanned by CamScanner

| ዘዓርብ፡ጽባሕ። | የዓርብ፡ነግህ። |
| --- | --- |
| ሠያጢ፡በቃልከ፡እስረኒ፡በፍቅርከ፡ከመ፡ እሰብሕ፡ዘንተ፡ዓለመ፡ወረስየኒ፡እትሉ፡ ስመ፡ቅዱስ፡ወእትቀደስ፡ብከ፡**አ፡ቅዱስ፡ ቅዱሳን**። | ያጸናህ፡ይህን፡ዓለም፡እጠላ፡ዘንድ፡ በፍቅርህ፡እሰረኝ፤**የቅዱሳን፡ቅዱስ፡ሆይ**፡ ባንተ፡ንጹሕ፡እሆን፡ዘንድ፡የተቀደሰውን፡ ሰማያዊ፡ዓለም፡እንድከተል፡አድርገኝ። |
| **እ፡እግዚእየ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ**፡ዘተአሰርከ፡ የሐ፡ዐምድ፡እስረኒ፡በፍቅርከ፡ወአንድዶ፡ ለልብየ፡በእሳተ፡ፍቅርከ፡ወፍትሖን፡ለመታ ዕቅትየ፡እምኵሉ፡ፍትወታተ፡ዝንቱ፡ዓለም፡ ከመ፡እብጻሕ፡ኀቤከ፡ወኩነኒ፡ሊተ፡ቀርነ፡ መድኀኒት። | ፫፤ **ጌታዬ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ሆይ**፡ከግንድ፡ ጋር፡እንደ፡ታሰርክ፡በፍቅርህ፡እሰረኝ፤ልቡና ዬንም፡በፍቅርህ፡እሳትነት፡አሙቀው፤ትከ ሻዎቼንም፡ከዓለማዊ፡ፍላጎት፡ማሰሪያ፡ ሁሉ፡ፍታቸው፤ወዳንተ፡እደርስ፡ዘንድ፡ ለእኔ፡የድኅነት፡ኃይል፡ሁነኝ። |
| **እ፡እግዚእየ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ**፡ዘተአሰርከ፡ ከመ፡ታድኅኖ፡ለአዳም፡እማእሰረ፡ሞት፡ ፍትሐኒ፡እማእሰረ፡ፍቅረ፡ዝንቱ፡ዓለም፡ ወእስረኒ፡በፍቅርከ፡ዘለዓለም። | ፬፤ **ጌታዬ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ሆይ**፡አዳምን፡ ከሞት፡ማሰሪያ፡ፈትተህ፡ታድነው፡ዘንድ፡ እንደ፡ታሰርክ፡ከዚህ፡ዓለም፡ፍቅር፡ማሰሪያ፡ ፍታኝ፤በዘላለማዊ፡ፍቅርህም፡እሰረኝ። |
| **እ፡እግዚእየ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ**፡ዘቆምከ፡ ቅድመ፡ጲላጦስ፡አቅመኒ፡በቅድሜከ፡ ዘንበለ፡ነውር፡አንተ፡ውእቱ፡**ሕያው፡ ወቅዱስ**። | ፭፤ በጲላጦስ፡ፊት፡የቆምክ፡**ጌታዬ፡ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ሆይ**፡ያለ፡ነውር፡በፊትህ፡ አቁመኝ፤አንተ፡**ሕያወ፡ባሕርይ፡ንጹሐ፡ ባሕርይ፡ነህና**። |
| **እ፡እግዚእየ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ**፡ዘቆምከ፡ ከመ፡ይፍታሕ፡ብከ፡ጲላጦስ፡**ኪሩቤል፡ ወሱራፌል**፡ዘይሰግዱ፡ቅድመ፡ዕበይከ፡እፎ፡ ቆምከ፡ቅድመ፡ልህኩት፡እዴከ፡ከመ፡ ይፍታሕ፡ላዕሌከ። | ፮፤ **ጌታዬ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ሆይ**፡ይፈርድብህ፡ ዘንድ፡በጲላጦስ፡ፊት፡ቆምክ፤**ሱራፌልና፡ ኪሩቤልም**፡በገናናው፡ጌትነትህ፡ፊት፡ የሚሰግዱ፡ሲሆን፡ይፈርድብህ፡ዘንድ፡እጅህ፡ በሰራችው፡ሸክላ፡ፊት፡እንዴት፡ቆምክ? |
| ስብሐት፡ለከ፡ወስብሐት፡ለትሕትናከ፡**እ፡ እግዚእየ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ**፡ሀበኒ፡መንፈሰ፡ ትሕትናከ፡እንተ፡ይእቲ፡ሥጋዌ፡**እምላ ከነት**። | ፯፤ ለአንተ፡ክብር፡ምስጋና፡ለትሕትናህም፡ ጌትነት፡ይሁን፤**ጌታዬ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ሆይ**፡ የትሕትናህን፡መንፈስ፡ስጠኝ፤ይኸቺውም፡ **አምላክነትህ**፡የተዋሐዳት፡ሥጋዌህ፡ናት። |
| ሃይማኖተ፡አበው። ምዕ፡፲፮፡፱–፲። | የአባቶች፡ሃይማኖት። ምዕ፡፲፮፡፱–፲። |
| ዘአባ፡ቅዱስ፡እለእስክንድሮስ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡ ዘሀገረ፡እስክንድርያ፡ወውእቱ፡ሊቅ፡ ዘማኅበረ፡ኒቅያ፡በውስተ፡ድርሳኑ፡ዘደረሰ። | በኒቅያ፡ለተሰበሰቡት፡ማኅበር፡አፈ፡ጉባኤ፡ የሆነ፡የእስክንድርያ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡እለእስክ ንድሮስ፡የምሥጢረ፡ሥጋዌን፡ነገር፡በተናገ ረበት፡ድርሳኑ፡እንዲህ፡አለ። |
| ወይቤ፡አጽሐቆ፡**እግዚአብሔር፡ቃል**፡ ወረደ፡ውስተ፡ምድር፡ወይሠገው፡**እምቅ ድስት፡ድንግል**፡ወይጠብለል፡በአጽርቅት፡ ወተላወደይ፡ውስተ፡ኀል፡ወይጥቡ፡ሐሊበ፡ | ፱፤ **እግዚአብሔር፡ቃል**፡ወደዚህ፡ዓለም፡ይመጣ፡ ዘንድ፡**ከንጽሕት፡ድንግል፡ማርያም**፡ሥጋን፡ ይዋሐድ፡ዘንድ፡በጨርቅ፡ይጠቀለል፡ዘንድ፡ በበረት፡ይጣል፡ዘንድ፡**ከድንግል**፡ብላቴና፡ |

እምአጥባተ ፡ ብእሲት ፡ ወይጠመቅ ፡ በዮር
ዳኖስ።
፫፤ ወይትቃጸቦ ፡ ጲላጦስ ፡ ዐላዊ ፡ ሕግ ፡
ወይሰቀል፡ዲበ፡ዕፅ፡ወይትወደይ፡ውስተ፡
መቃብር ፡ ወይትነሣእ ፡ በሣልስት ፡ ዕለት ፡
አኮኑ፡ውእቱ፡በእንቲአነ፡ከመ፡ያንሥአነ፡
ለነ፡ለእለ፡ማስነ።

፬፤ ወካዕበ፡ይቤ፡ዝንቱ፡አብ፡እለእስክንድሮስ፡
በውስተ ፡ ድርሳኑ ፡ ዘደረሰ ፡ በእንተ ፡
ሕማማቲሁ፡ለእግዚእነ።
፭፤ አ፡ለዝንቱ፡ምሥጢር፡ሐዲስ፡ዘኢይትነገር፡
ቦቱ ፤ ለመኰንን ፡ ኰነንዎ ፡ ወለዘይፈትሕ ፡
ማዕሠረ፡ኃጢአት፡አሠርዎ፡ወለዘይእኅዝ፡
ዓለመ፡አኀዝዎ።

፮፤ ወለዘይሁብ፡ሕይወተ፡ለሰብእ፡አስተይዎ፡
ሐሞተ ፤ ወሞተ ፡ ማሕየዊ ፡ ወተቀብረ ፡ ዘያነ
ሥኦሙ፡ለምውታን።
፯፤ አንከሩ፡ኃይላተ፡ሰማይ፡አሚሃ፡ወተደሙ፡
መላእክት፡ወደንገፁ፡ኵሉ፡አናስረ፡ፍጥረት፡
ወአንከሩ፡ኵሎሙ፡ፍጡራን።
፰፤ ወይቤሉ ፡ አይሁድ ፡ ናሁ ፡ መኰንን ፡
ይትኴነን፡እንዘ፡ውእቱ፡ያረምም፤ወዘኢያስ
ተርኢ ፡ ተርእየ ፡ ወኢያውሥአ ፤ ወዘኢይት
አኀዝ፡ተእኅዘ፡ወኢተምዐ።
፱፤ ወዘኢየሐምም፡ሐመ፡ወኢተበቀለ፤ወዘኢይ
መውት፡ሞተ፡እንዘ፡ይትዔገሥ፤ወሰማያዊ፡
ሰከበ፡ውስተ፡መቃብር፡በትዕግሥት።

፲፤ አንከሩ ፡ ኵሉ ፡ ፍጥረት ፡ እስመ ፡ በእንተ ፡
ሰብእ፡ ሐመ ፡ ዝንቱ ፡ ዘኢየሐምም ፡
ወኰነንዎ፡ለመኰንነ፡መኳንንት፤ወነጸርዎ፡
ለዘኢይትኔጸር ፤ አሞትዎ ፡ ለዘኢይመውት ፤
ወሰማያዊ፡ተወድየ፡ውስተ፡መቃብር።

ምዕ፤፲፰፡፳፩–፴፪።
፳፩፤ ዓዲ ፡ እመልእክተ ፡ ሲኖዲቆን ፡ ዘአቡነ ፡ አባ፡
ዘካርያስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘእለእስክንድርያ ፡
ኀበ፡ አቡነ፡ አባ፡ዮሐንስ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡ዘአን
ጾኪያ፡በ፴ቱ፡ምዕት፡ወሠለስቱ፡እምዓመተ፡



ጡት ፡ ወተትን ፡ ይጠባ ፡ ዘንድ ፡ በዮርዳኖስም፣
ይጠመቅ፡ዘንድ፡ምን፡አተጋው?
፫፤ ሕግ፡አፍራሽ፡ጲላጦስ፡ይዘብትበት፡ዘንድ፣
በመስቀል ፡ ይሰቀል ፡ ዘንድ ፣ በመቃብር ፣
ይቀበር ፡ በሦስተኛውም ፡ ቀን ፡ ይነሣ ፡ ዘንድ፣
ምን ፡ አተጋው? በፍዳ ፡ ተይዘን ፡ የነበርን ፣
እኛን ፡ ያድነን ፡ ዘንድ ፡ ለእኛ ፡ ብሎ ፡ አይደ
ለምን?
፬፤ ዳግመኛም ፡ የጌታችንን ፡ የሕማሙን ፡ ነገር፣
በተናገረበት ፡ ድርሳኑ ፡ ይህ ፡ ቅዱስ ፡ አባት፣
እለእስክንድሮስ፡እንዲህ፡አለ።
፭፤ በእርሱ ለማይነገር ፡ ለዚህ ፡ እንግዳ ፣
ምሥጢር፡አንክሮ፡ይገባል፡ፈራጅ፡እርሱን፣
ፈረዱበት ፤ ከማእሠረ ፡ ኃጢአት ፡ የሚፈታ፣
እርሱን ፡ አሰሩት ፤ ዓለምን ፡ በእጁ ፡ መሐል፣
የያዘ፡እርሱን፡ያዙት።
፮፤ ለሰው ፡ ሕይወትን ፡ ለሚሰጥ ፡ ለእርሱ ፣
ሐሞትን፡አጠጡት፤የሚያድን፡እርሱ፡ሞተ፤
ሙታንን፡የሚያስነሣቸው፡እርሱ፡ተቀበረ።
፯፤ በሰማይ፡ያሉ፡ኃይላት፡ያን፡ጊዜ፡አደነቁ፤መላ
እክትም ፡ በተደሞ ፡ ፈዘዙ ፤ በፍጥረት ፡ ላይ፡
የተሾሙ፡ሁሉ፡ደንገጡ፤ፍጡራንም፡አደነቁ።
፰፤ አይሁድም ፤ ገዥ ፡ እነሆ ፡ ይፈረድበታል፡
አሉ፤የማይታየው፡ታየ፤የማይያዘው፡ተያዘ፤
በምን ፡ ዕዳዬ ፡ ብሎ ፡ አልመለሰም ፤ አልተቆ
ጣምም፤(አልፈረደምም)።
፱፤ የማይታመመው ፡ ታመመ ፤ አልተበቀለም፤
የማይሞት ፡ እርሱ ፡ በፈቃዱ ፡ ሞተ ፤
ሰማያዊው ፡ በትዕግሥት ፡ ይሁን ፡ ብሎ ፡
በመቃብር፡አደረ።
፲፤ ፍጥረት፡ሁሉ፡አደነቁ፤የማይታመም፡እርሱ፡
ለሰው ፡ ብሎ ፡ መከራ ፡ ተቀብሏልና ፡
በፈራጆች፡ ላይ ፡ በሚፈርድ ፡ በእርሱ ፡
ፈረዱበት ፤ የማይታይ ፡ እርሱን ፡ ራቁቱን ፡
ሰቀለው ፡ አዩት ፤ የማይሞተውን ፡ ገደሉት ፡
ሰማያዊ፡እርሱ፡በመቃብር፡አደረ፡ተቀበረ።

ምዕ፤፲፰፡፳፩–፴፪።
፳፩፤ ሰማዕታት ፡ በተነሡ ፡ በዘጠኝ ፡ መቶ ፡ ሦስት ፡
ዓመት ፡ የእስክንድርያው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡
አባታችን ፡ አባ ፡ ዘካርያስ ፡ ወደ ፡ አንጾኪያ ፡
ሊቀ፡ ጳጳሳት ፡ ወደ ፡ አባ ፡ ዮሐንስ ፡ ጽፎ ፡

Scanned by CamScanner

## ዘዓርብ፡ጽባሕ።

ማኅሌት፡ ንሕነሰ ፡ እምይእዜ ፡ ነአምን ፡
ሐዱ፡ አፍ፡ እንበለ ፡ ተፈልጦ ፡ ወኢተ
ለዎ፡ በኃይሉ፡ ወበረድኤቱ ፡ ለእግዚእነ ፡
ወአምላክነ ፡ ወመድኃኒነ ፡ ኢየሱስ ፡
ክርስቶስ።

፳፫ ወአእምን ፡ ዓዲ ፡ በጥበብ ፡ ወበሕሊና ፡
በአሐዱ፡ አምላክ ፡ አብ ፡ አኀዜ ፡ ኵሉ ፡
ወገባሬ፡ኵሉ፡ፍጥረታት፡ዘያስተርኢ፡ወዘ
ኢያስተርኢ፤ወበወልዱ፡ዋህድ፡እግዚእነ፡
ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ወበመንፈስ፡ቅዱስ፡
እግዚእነ፡ወሀቢ፡ሕይወት፤ሥላሴ፡እለ፡
ዕሩያን፡በአካላት፡በአሐቲ፡ክብር፡ወአሐዱ፡
መለኮት፡ወአሐዱ፡ሕላዌ፡እንበለ፡ተፈልጦ፡
ወኢተሌልዮ፡ሠለስቱ፡አካላት፡ንጹሐን፡
እንዘ፡አሐዱ፡አምላክ፡በገቢር፡ወኃይል፡
ወአሐዱ፡መንግሥት፡ወአሐቲ፡ምክር፡
ወአሐቲ፡ስባሔ፡ወአሐዱ፡ምልክና፡
ወአሐዱ፡ሀሉና፡ወአሐዱ፡ሥልጣን፡
ወአሐዱ፡እግዚእና፡ዘሠለስቱ፡አካላት፡
ወሠለስቱ፡ገጻት፡ዘውእቶሙ፡አብ፡
ወወልድ፡ወመንፈስ፡ቅዱስ።

፳፬ ለሰመ፡ለተዋሕዶተ፡መንፈስ፡ቅዱስ፡
ምስለ፡ምስለ፡አብ፡ወወልድ፡ለሊሁ፡
እግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ከሠቶ፡ለነ፡
በወንጌሉ፡ቅዱስ፡ኀበ፡ይብል፡አነ፡እስእሎ፡
ለአብ፡ከመ፡ይፈኑ፡ለክሙ፡ጰራቅሊጦስሃ፡
መንፈሰ፡ካልአ፡ዘከማየ፤ይትነፈሩ፡እንከሰ፡
ይእዜ፡ዝየ፡አብስልዲስ፡ወመቅዶንዮስ፡
ኦሎሙ፡እለ፡ኢይሁቡ፡ክብረ፡ስብሐት፡
ለመንፈስ፡ቅዱስ፤እስመ፡ብሂልሰ፡ካልእ፡
ዘከማየ፡ይከሥት፡ለነ፡ፍልጠተ፡አካላት፡
ወብሂለ፡ቃልሂ፡እፌኑ፡ለክሙ፡ጰራቅሊ
ጦስሃ፡እምዝአየ፡ይነሥእ፡ወይነግረክሙ፤
ያመሀርነ፡በዝንቱ፡ሱታፌ፡ተዋሕዶተ፡
መለኮት፡ወዝንቱሰ፡ቃል፡ይዘልፎሙ፡ለሰባ
ልዮሳውያን፡ወለአርዮሳውያን፡ዐላውያን፡
ዘይፈልጥዎ፡ሥሉስ፡ቅዱስ፡እለ፡ዕሩያን፡
በመለኮት።

## የዓርብ፡ነግህ።

ከላከው፡መልእክት፡እኛስ፡ዛሬ፡በጌታችን፡
በፈጣሪያችን፡በመድኃኒታችን፡በኢየሱስ፡
ክርስቶስ፡ አጋዥነት፡ ከሃሊነት፡ ያለ፡
መለያየት፡ያለ፡መከፋፈል፡አንድ፡ልብ፡
አንድ፡አፍ፡ሁነን፡እናምናለን።

፳፫፤ እንዲሁም፡በጥበብ፡በዕውቀት፡ጸንተን፡የሚታ
የውንና፡የማይታየውን፡ፍጥረቱን፡ሁሉ፡
በፈጠረ፡ሁሉን፡በሚገዛ፡በአንድ፡አምላክ፡
በአብ፡ተቀዳሚ፡ተከታይ፡በሌለው፡በልጁ፡
በጌታችን፡በኢየሱስ፡ክርስቶስና፡ሕይወትን፡
በሚያድል፡በጌታችን፡በመንፈስ፡ቅዱስም፡
እናምናለን፤ሥላሴ፡በአንድ፡ክብር፡በአንድ፡
መለኮት፡በአንድ፡ባሕርይ፡ፈጽሞ፡ባለመ
ለየት፡አንድ፡የሚሆኑ፡ንጹሓን፡ባሕርይ፡
ሦስት፡አካላት፡ናቸው፤ፍጥረትን፡በመፍጠር፡
በከሃሊነት፡አንድ፡አምላክ፡ሲሆን፤የሦስቱ፡
አካላት፡የሦስቱ፡ገጻት፡ጌትነት፡አንድ፡ነው፤
ሥልጣናቸው፡አንድ፡ነው፡አኗኗራቸው፡
አንድ፡ነው፡አገዛዛቸው፡አንድ፡ነው፡ክብራ
ቸው፡አንዲት፡ናት፤ምክራቸው፡አንዲት፡ናት፤
መንግሥታቸውም፡አንድ፡ነው፤እነዚህም፡
አብ፡ወልድ፡መንፈስ፡ቅዱስ፡ናቸው።

፳፬፤ መንፈስ፡ቅዱስ፡ከአብ፡ከወልድ፡ጋር፡አንድ፡
መሆኑንም፡ጌታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ለደቀ፡
መዛሙርቱ፡እንደ፡እኔ፡ያለ፡በአካል፡ልዩ፡
የሆነ፡ጰራቅሊጦስን፡ይሰድላችሁ፡ዘንድ፡እኔ፡
አባቴን፡እለምነዋለሁ፡ብሎ፡በተናገረበት፡
በወንጌል፡ለእኛ፡ገልጦልናል፤እንኪያስ፡
ለመንፈስ፡ቅዱስ፡ክብርና፡ምስጋና፡የማያ
ቀርቡ፡እነዚህ፡መቅዶንዮስና፡አብስልዲስ፡
አሁን፡ይፈሩ፤እንደኔ፡ያለ፡ሌላ፡ማለት፡የአካ
ላትን፡ሦስትነት፡ያስረዳል፤አካላዊ፡ቃልም፡
ጰራቅሊጦስን፡እሰድላችኋለሁ፤ቃልነትንም፡
ከእኔ፡ገንዘብ፡አድርጎ፡ይነግራችኋል፡ማለቱ፡
በዚህ፡በመለኮት፡ አንድነት፡ ያለውን፡
አንድነት፡ ያስተምረናል፤ ይህም፡ ቃል፡
በመለኮት፡አንድ፡የሚሆኑ፡ሥሉስ፡ቅዱስን፡
የሚቃወሙ፡የአርዮስና፡የሰባልዮስ፡ወገኖች፡
የሚሆኑ፡መናፍቃንን፡ይዘልፋቸዋል።

Scanned by CamScanner

## ዘዓርብ፡ጽባሕ።

፳፯፡ ንሀነስ ፡ ነአምን ፡ በሙ ፡ ወንሴብሖሙ ፡ አሐተ፡ ስባሔ ፡ ወናመልኮሙ ፡ እንበለ ፡ ሌልዮ፡ በአሐዱ ፡ መለኮት ፡ ወበአሐቲ ፡ ስግደት ፤ ወእለሰ ፡ ይፈልጥዎሙ ፡ ለሥሉስ ፡ ቅዱስ ፡ ወይሴብሖ ፡ ካልአ ፡ አምላከ ፡ እምዝንቱ፡ወይትአመኑ፡ነኪራን፡ወውጉዛን እሙንቱ፡ወምኑናን፡በኀቤነ።

፳፰፡ ወይእዜኒ ፡ ይደልወነኬ ፡ ከመ ፡ ንትናገር ፡ በእንተ ፡ ትሥጉቱ ፡ ለመድኃኔ ፡ ዓለም ፡ ዘውእቱ ፡ አሐዱ ፡ ዘእምቅድስት ፡ ሥላሴ ፡ ዘኢፍጡር ፡ ወኢግቡር ፡ ወኢፍሉጥ ፡ እመለኮተ ፡ አቡሁ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ አምላክ ፤ ንሀነሰ ፡ ክርስቶሳውያን ፡ ነአምን ፡ ዘእንበለ፡ጽነት፡ወኢተወላውሎ፡በወልድ፡ ዋህድ፡ቀዳማዊ፡ዘአልቦ፡ጥንት፡ቃለ፡እግዚ አብሔር፡አብ፡ዘዕሩይ፡በመለኮቱ፡ዘኢይት ገመር፡ወልድ፡ዋህድ፡ዘሀሎ፡እምቅድመ፡ ዓለም ፡ ዘተወልደ ፡ እምአብ ፤ ወበደኀሪ ፡ መዋዕል ፡ በእንቲአነ ፡ ወበእንተ ፡ መድኃ ኒትነ፡ ተወልደ ፡ እምእግዝእትነ ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ እንበለ ፡ ውላጤ ፡ ወኢሙስና ፡ በከመ ፡ መሐረነ ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ሐዋርያ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ ወሶበ ፡ ቀርበ ፡ ተፍጻሜተ ፡ ዘመን ፡ ፈነወ ፡ እግዚአ ብሔር ፡ ወልዶ ፡ ወተወልደ ፡ እምብእሲት ፡ ወኮነ፡ምስሌነ።

፳፱፡ ውእቱሰ፡ወልደ፡እግዚአብሔር፡በመንፈስ፡ ወወልደ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው ፡ በሥጋ ፤ ወኢንቤ፡ ለዝንቱ ፡ ወልድ ፡ ዋሕድ ፡ ቦቱ ፡ ክልኤቱ ፡ ህላዌያት ፡ ለአሐዱ ፡ ዘንሰግድ ፡ ሎቱ፡ ወለካልኡ ፡ ዘኢንሰግድ ፡ ሎቱ ፤ ወባሕቱ፡ንብል፡በእንቲአሁ፡አሐዱ፡ህላዌ፡ ዘእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ዘተሠገወ ፡ እንበለ ፡ ተፈልጦ፡ወንሰግድ፡ሎቱ፡ምስለ፡ሥጋሁ፡ አሐተ፡ስግደተ።

፴፡ ወቅዱስ፡አትናቴዎስ፡ሐዋርያዊ፡ይብል፡ ከመዝ፡ኢኮነ፡ክልኤተ፡አሐዱ፡አምላክ፡ ዘንሰግድ ፡ ሎቱ ፡ ወካልኡ ፡ ብእሲ ፡ ዘእ ማርያም፡ዘኢንሰግድ፡ሎቱ፤ወባሕቱ፡ዘእም እግዚአብሔር ፡ ውእቱ ፡ እግዚአብሔር ፡

## የዓርብ፡ነግህ።

፳፯፡ እኛ ፡ ግን ፡ እናምንባቸዋለን ፤ አንዲት ፡ ምስጋናን ፡ እናመሰግናቸዋለን ፤ በአንድ ፡ መለኮት ፡ በአንዲት ፡ ስግደት ፡ ባለመለያየት ፡ እናመልካቸዋለን ፤ ሦስቱን ፡ አካላት ፡ በማበ ላለጥ ፡ የሚከፋፍሏቸው ፡ ከዚህ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ አምላክን ፡ የሚያመልኩ ፡ የሚታመኑ ፡ ግን ፡ በማኅበራችን ፡ ተወግዘው ፡ የተለዩ ፡ የተጠሉ ፡ ናቸው።

፳፰፡ አሁንም ፡ የዓለም ፡ መድኃኒት ፡ ሰው ፡ የመሆኑን ፡ ነገር ፡ ልንናገር ፡ ይገባናል ፤ ይኸውም ፡ ከሦስቱ ፡ አካላት ፡ አንዱ ፡ አካል ፡ ያልተፈጠረ ፡ ከአባቱ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ባሕርይ ፡ ያልተለየ ፡ አምላክ ፡ ቃል ፡ ነው ፤ እኛ ፡ ክርስቲያን ፡ ግን ፡ ሳንጠራጠር ፡ ሳናወላውል ፡ ጥንት ፡ የሌለው ፡ ቀዳማዊ ፡ በሚሆን ፡ በወልድ፡ ዋሕድ ፡ እናምናለን ፤ የእግዚአ ብሔር ፡ አብ ፡ ቃል ፡ በማይወሰን ፡ ጌትነቱ ፡ ከአብ ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ ነው ፤ ዓለም ፡ ሳይፈጠር ፡ የነበረ ፡ ከአብ ፡ የተወለደ ፡ ወልድ ፡ ዋሕድ ፡ በኋላ ፡ ዘመን ፡ ስለ ፡ እኛ ፡ እኛን ፡ ስለማዳን ፡ ያለ፡ መለወጥ ፡ ከእመቤታችን ፡ ከቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ ተወለደ ፤ ሐዋርያው ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ የዘመኑ ፡ ፍጻሜ ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ ልጁን ፡ ላከ ፤ ከድን ግልም ፡ ተወለደ ፤ የሰውነትንም ፡ ሥራ ፡ ሠራ ፡ ብሎ ፡ እንዳስተማረን።

፳፱፡ እርሱስ ፡ በመለኮት ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ነው ፤ በሥጋ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ነው ፤ ለዚህ ፡ ለአንድ ፡ ወልድ ፡ ለአንዱ ፡ የሚሰገድለት ፡ ለአንዱ ፡ የማይሰገድለት ፤ ሁለት ፡ ባሕርይ ፡ አለው ፡ አንልም ፤ ስለ ፡ እርሱ ፡ ስንናገር ፡ ሰው ፡ የሆነ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ያለ ፡ መከፈል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ነው ፡ እንላለን ፡ እንጂ ፤ ከሥጋውም ፡ ሳንለይ ፡ አንዲት ፡ ስግደትን ፡ እን ሰግድለታለን ፡ እንጂ።

፴፡ ሐዋርያው ፡ ቅዱስ ፡ አትናቴዎስ ፡ አንዱ ፡ የም ንሰግድለት ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ፤ ሁለተ ኛውም ፡ ከማርያም ፡ የተገኘ ፡ የማንሰግድለት ፡ ዕሩቅ ፡ ብእሲ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ከሁለት ፡ የሚከፈል ፡ ሁለት ፡ አይደለም ፡ ብሏል ፤

Scanned by CamScanner

## ዘዓርብ፡ጽባሕ።

ወወልደ፡እግዚአብሔር፡ወአኮ፡ውእቱ፡
አሐዱ፡ምስለ፡ካልኡ፤ወባሕቱ፡አሐዱ፡
ወልድ፡ውእቱ፡ዘተወልደ፡ቅድመ፡እምአብ፤
ወበደኃሪ፡መዋዕል፡ተወልደ፡እምእግዝ
እትነ፡ቅድስት፡ድንግል፡ማርያም።

፴፩ ጠመ፡ትቤሎ፡ለገብርኤል፡መልአክ፡
ንጽሕት፡ድንግል፡በኵሉ፡ጊዜ፡ወላዲተ፡
አምላክ፡ማርያም፡እፎኑ፡ይከውነኒ፡ዝንቱ፡
እንዘ፡ኢየአምር፡ብእሴ፤አውሥአ፡መልአክ፡
ወይቤላ፡መንፈስ፡ቅዱስ፡ይመጽእ፡ላዕሌኪ፡
ወኃይለ፡ልዑል፡ይጼልለኪ፤ወዘኒ፡
ይትወለድ፡እምኔኪ፡ቅዱስ፡ውእቱ፡
ወይሰመይ፡ወልደ፡እግዚአብሔር፡ልዑል፤
ዝንቱ፡ቃል፡ወልዱ፡ወአርአያ፡አካሉ፡ለእግዚ
አብሔር፡አብ፡ወተሠገወ፡እመንፈስ፡ቅዱስ፡
ወእማርያም፡እምቅድስት፡ድንግል፡ዘእንበለ፡
ዘርዓ፡ብእሲ።

፴፪ ወነሥአ፡እምኔሃ፡ሥጋ፡ዘይትዔረየነ፡ወዘየ
ሐምም፡ከማነ፡ዘቦቱ፡ነፍስ፡ነባቢት፡
ወለባዊት፡እንዘ፡ይትዋሐድ፡ምስሌሁ፡
መለኮት፡ወውእቱ፡ወልዱ፡ዋሕድ፡ለእግዚ
አብሔር፡አብ፡በመለኮት፡ወወልደ፡ዕጓለ፡
እመሕያው፡በሥጋ።

ኢያምጽአ፡ሥጋ፡ምስሌሁ፡እምሰማይ፡
እምህላዌ፡መለኮቱ፡አላ፡ነሥአ፡እምእግዝ
እትነ፡ቅድስት፡ድንግል፡ማርያም።

ንብል፡እንከሰ፡እስመ፡ውእቱ፡ገብረ፡
ኃይላተ፡ወመንክራተ፡በመለኮቱ፡ወሐመ፡
ሕማመ፡ዚአነ፡በትስብእቱ።

ወሰበ፡ንቤ፡ዘንተ፡ኢይምሰልክሙ፡
ዘንፈልጦ፡ለትስብእት፡እምነ፡መለኮት።

ሐሰ፡ወኢይደሉ፡ይክፍልዎ፡ለአሐዱ፡ኀበ፡
ክልኤቱ፡ህላውያት፡ወኢኀበ፡ክልኤቱ፡
አካላት፡ወኢኀበ፡ክልኤቱ፡ገጻት፡ወኢኀበ፡
ክልኤቱ፡ፈቃድ።

ወኢንቤ፡እስመ፡ህላዌ፡መለኮት፡ይገብር፡
ግብረ፡መለኮት፡ወትስብእትሂ፡ይገብር፡
ግብረ፡ትስብእት፡እለሰ፡ይብሉ፡ከመዝ፡
ውጉዛን፡እሙንቱ፡ወውፁአን፡እምትም

## የዓርብ፡ነግህ።

ከእግዚአብሔር፡የተገኘ፡እግዚአብሔር፡የእ
ግዚአብሔር፡የባሕርይ፡ልጅም፡ነው፡እንጂ፤
አንዱ፡ከሌላው፡ጋር፡በኅብረት፡እንደ
ሚኖር፡አይደለም፤ቅድመ፡ዓለም፡ከአብ፡
ድኅረ፡ዓለም፡ከእመቤታችን፡ከቅድስት፡
ድንግል፡ማርያም፡የተወለደው፡እርሱ፡
አንድ፡ወልድ፡ነው፡እንጂ።

፴፩ ሁልጊዜ፡ንጽሕት፡ድንግል፡የምትሆን፡
አምላክን፡የወለደች፡ማርያም፡ገብርኤልን፡
ወንድ፡ሳላውቅ፡ይህ፡እንደምን፡ይሆን
ልኛል፡ብትለው፡እርሱ፡መልሶ፡መንፈስ፡
ቅዱስ፡ያድርብሻል፤የአብ፡ኃይሉም፡
ያጸናሻል፤ካንቺ፡የሚወለደውም፡የባሕርይ፡
አምላክ፡ነው፤የልዑል፡እግዚአብሔር፡
ልጅ፡ይባላል፡አላት፤ይህ፡ቃል፡እግዚአ
ብሔር፡አብን፡በመልክ፡የሚመስለው፡
በባሕርይ፡የሚተካከለው፡ልጁ፡ነው፤ያለ፡
ዘርዓ፡ብእሲ፡ከቅድስት፡ድንግል፡ማርያም፡
በግብረ መንፈስ፡ቅዱስ፡ሰው፡ሆነ።

፴፪ ለባዊት፡ነባቢት፡ነፍስ፡ያለችውን፡መለኮት፡
ተዋሕዶት፡ሳለ፡እኛን፡የሚመስል፡እንደ፡
እኛ፡የሚታመም፡ሥጋን፡ከእሷ፡ነሣ፤
በመለኮቱ፡ተቀዳሚ፡ተከታይ፡የሌለው፡የእ
ግዚአብሔር፡አብ፡ልጅ፡ነው፤በሥጋው፡
የሰው፡ልጅ፡ነው።

ከባሕርየ፡መለኮቱ፡ከሰማይ፡ሥጋን፡
አላመጣም፤ከእመቤታችን፡ከቅድስት፡
ድንግል፡ማርያም፡ሥጋን፡ነሣ፡እንጂ።

እንኪያስ፡አምላክ፡በመሆኑ፡ተአምራትን፡
እንደ፡አደረገ፡ሰው፡በመሆኑም፡የእኛን፡
መከራ፡እንደ፡ተቀበለ፡እንናገራለን።

ይህንንም፡በምንናገርበት፡ጊዜ፡ሥጋን፡
ከመለኮት፡የምንለየው፡አይምሰላችሁ፤
ተለየ፡አንልም።

አንዱን፡ወደ፡ሁለት፡ባሕርይ፡ወደ፡ሁለት፡
አካል፡ወደ፡ሁለት፡ገጽ፡ወደ፡ሁለት፡
ፈቃድ፡ሊከፍሉት፡አይገባም።

የመለኮት፡ባሕርይ፡የአምላክነትን፡ሥራ፡
ይሠራል፤የሥጋ፡ባሕርይ፡የሥጋን፡ሥራ፡ይሠ
ራል፡አንልም፤እንዲህ፡የሚሉስ፡ሐዋርያት፡ከሰ
በሰቡአት፡ከአንዲት፡ቅድስት፡ቤተ፡ክርስቲያን፡

## ዘዓርብ፡ጽባሕ።

ሀርተ፡ቅድስት፡ቤተ፡ክርስቲያን፡አሐቲ፡
ጉባዔ፡እንተ፡ሐዋርያት።
ጸሎቶሙ፡ወበረከቶሙ፡ለእሉ፡መምህራን፡
የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

### አንቀጽ፡ዕሥራ፡ወተሰዐቱ።

አንቀጽ፡ዕሥራ፡ወተሰዐቱ፡እመጽሐፈ፡ዲድ
ስቅልያ፡ዘአበዊነ፡ሐዋርያት፤በረከቶሙ፡
ትኩን፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

፩፤ ወሌሊተ፡አውዕእዎ፡ወወሰድዎ፡ኀበ፡ሐና፡
ሐሙሁ፡ለቀያፋ፡ሊቀ፡ካህናት።

፪፤ ወገብሩ፡ላዕሌሁ፡ብዙኀ፡እከየ፤ወአግብእዎ፡
ኀበ፡ጲላጦስ፡መኰንነ፡ሮሜ፡ወአሜሃ፡
ዐርብ፡ዕለታ።

፫፤ ወአስተዋደይዎ፡በብዙኀ፡ግብር፡ዘኢመ
ፍትው፡ለነጊር።

፬፤ ወሰሚዖ፡ጲላጦስ፡መኰንነ፡ሮሜ፡
ኢአምኖሙ፡አላ፡ይቤሎሙ፡ኢረከብኩ፡
በላዕሌሁ፡ለዝ፡ብእሲ፡ጌጋየ፡በዘይመውት።

፭፤ ወእምዝ፡አምጽኡ፡ክልኤተ፡ሰማዕተ፡እለ፡
ይብሉ፡ወይነቡ፡ሐሰተ፡ላዕለ፡ክርስቶስ፡
ወአእመረ፡ጲላጦስ፡ከመ፡ኢኀብረ፡
ስምዖሙ።

፮፤ ወእሙንቱሰ፡ኢተመይጡ፡ወመከሩ፡ነገረ፡
በዘያፈርህዎ፡ለጲላጦስ፡ወይቤሉ፡ዝ፡
ብእሲ፡ይሬሲ፡ርእሶ፡ንጉሠ፡ወይከልአነ፡
ለንጉሥ፡ተቀንዮ።

፯፤ ሐሰዉ፡ወፈትሑ፡ላዕሌሁ፡ዐመፃ፡ከልሑ፡
ወይቤሉ፡ስቅሎ፡ስቅሎ፡ከመ፡ይትፈጸም፡
ላዕሌሁ፡ቃለ፡ነቢይ፡ዘይቤ፡ተንሥኡ፡
ላዕሌየ፡ሰማዕተ፡ዓመፃ፡ወዘኢየአምር፡
ነበቡ፡ላዕሌየ፤ፈደዩኒ፡እኪተ፡ህየንተ፡
ሠናይት።

፰፤ ወካዕበ፡ይቤ፡ዐገቱኒ፡ከለባት፡ብዙኃን፡
ወአኀዙኒ፡ማኅበሮሙ፡ለእኩያን።

፱፤ ወሶበ፡ሰእነ፡ጲላጦስ፡አድኅኖቶ፡ለኢየሱስ፡
በእንተ፡ፍርሀቶሙ፡ለአይሁድ፡መከረ፡
ይግበር፡ፈቃዶሙ፡ለሕዝብ፡እስመ፡ቀዲሙ፡

## የዓርብ፡ነግህ።

አንድነት፡የወጡና፡የተለዩ፡ናቸው።

የእሊህ፡መምህራን፡በረከትና፡ጸሎት፡ከእኛ፡
ጋራ፡ለዘላለሙ፡ይኑር፡አሜን።

### ሃያ፡ዘጠነኛው፡አንቀጽ።

የአባቶቻችን፡ሐዋርያት፡በረከታቸው፡
ከእኛ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡ትኑርና፤ከአባቶ
ቻችን፡ከሐዋርያት፡ከሥርዓት፡መጽሐፍ፡
የተገኘ፡ሃያ፡ዘጠነኛው፡አንቀጽ፡ይህ፡ነው።

፩፤ በሌሊት፡አውጥተው፡የሊቀ፡ካህናቱ፡
የቀያፋ፡አማት፡ወደሆነው፡ሐና፡ወሰዱት።

፪፤ ብዙ፡የሆነ፡ክፉ፡ሥራ፡አደረጉበት፤ወደ፡
ሮማዊው፡ገዥ፡ወደ፡ጲላጦስም፡አሳልፈው፡
ሰጡት፤ያን፡ጊዜ፡ቀኑ፡ዐርብ፡ነበር።

፫፤ ሊነገርም፡በማይገባ፡በብዙ፡ነገር፡አሳጡት፤
ወነጀሉት፤ሰንበትን፡ሻረ፡አሉት።

፬፤ ጲላጦስም፡ሰምቶ፡ለሞት፡የሚያበቃ፡በደል፡
በእርሱ፡ላይ፡አላገኘሁም፡አላቸው፡እንጂ፡
አላመናቸውም።

፭፤ ከዚህ፡በኋላም፡ሐሰትን፡የሚናገሩ፡በክር
ስቶስ፡ላይ፡በሐሰትም፡የሚመሰክሩ፡ሁለት፡
ምስክሮችን፡አመጡ፤ጲላጦስም፡ምስክርነ
ታቸው፡አንድ፡እንዳልሆነ፡አወቀ።

፮፤ እነርሱ፡ግን፡አልተመለሱም፤ጲላጦስን፡
የሚያስፈራሩበትን፡ነገር፡መክረው፡ይህ፡
ሰው፡ንጉሥ፡ነኝ፡ይላል፤ለንጉሥም፡
መገዛትን፡ይከለክለናል፡አሉ።

፯፤ በሐሰት፡በግፍ፡ፈረዱበት፤ነቢዩ፡የሐሰት፡
ምስክሮች፡በጠላትነት፡ተነሡብኝ፤በኔ፡
ላይም፡የማላውቀውን፡ተናገሩብኝ፤በጎ፡ስለ፡
አደረግሁላቸውም፡ፈንታ፡የክፉ፡ብድራት፡
መለሱልኝ፡ያለው፡ይፈጸም፡ዘንድ፡ስቀለው፡
ስቀለው፡ብለው፡ጮኹ።

፰፤ ዳግመኛም፡ብዙ፡የሆኑ፡ውሾች፡ከበቡኝ፤
ክፉዎች፡አይሁድ፡በአንድነት፡ያዙኝ፡
ያለውም፡ይፈጸም፡ዘንድ።

፱፤ ጲላጦስም፡ጌታ፡ኢየሱስን፡ማዳን፡በተሳነው፡
ጊዜ፡አይሁድን፡ስለ፡ፈራ፡የሕዝቡን፡ፈቃድ፡
ይፈጽም፡ዘንድ፡ክልቡ፡መከረ፤አስቀድሞ፡

Scanned by CamScanner

## ዘዓርብ፡ጽባሕ።

ሰምዑ፡ከነ፡ጲላጦስ፡ወይቤ፡አልቦ፡ዘረከብኩ፡
ቦቱ፡ጌጋዩ፡በዘይመውት፤ ወአይሁድሰ፡
አኩያን፡ሰቀልዎ፡ዲበ፡ዕፀ፡መስቀል።
ወለሮምስ፡በሙ፡ሥርዓት፡ወኢይቀትሉ፡
ወኢመነሂ፡ዘእንበለ፡ይትመዋእ፡በፍትሕ፡
በኀበ፡መኰንን።
ወባሕቱ፡ሐራ፡ሰገራት፡ነሥእዎ፡**ለእግዚእ፡**
**ኢየሱስ፡እግዚእ፡**ስብሐት።

ድርሳን፡ወትምህርት፡ዘአበዊነ፡ሐዋርያት፡
ቅዱሳን፡ዘመሀሩነ።

ወውእተ፡ጊዜ፡ሰሐብዎ፡**ለእግዚእ፡ኢየሱስ፡**
ወጸርዎ፡ወአብጽሕዎ፡ኀበ፡ዐውደ፡ቅሥት፡
ዘምኵናን፡ጲላጦስ፡ከመ፡ይፍትሑ፡ፍትሐ፡
ሞት፡ላዕሌሁ።
ወውእቱ፡ዕለተ፡ዐርብ፡ነግህ፡በዓለ፡ፋሲካ፡
ዘይገብሩ፡አይሁድ።
ወሶበ፡ርእዮ፡ጲላጦስ፡**ለእግዚእ፡ኢየሱስ፡**
አንከረ፡እምራእዩ፡እስመ፡ኮለንታሁ፡
ብርሃን፡ወየዓውዶ፡ኃይል፡ወስብሐት።

ወይቤሎ፡ጲላጦስ፡አይኑ፡ኃጢአት፡
ዘገበርከ፡ወኵሎሙ፡ሕዝበ፡አይሁድ፡
አንከሩከ፡ወይሣለቁ፡ላዕሌከ፡ወይፀርፉከ፡
ወአነ፡እሬእዮሙ፡ከመ፡አራዊት፡ይጥሕሩ፡
ላዕሌከ።
ወይቤሎ፡እፎ፡ትሴአለኒ፡በዝ፡ነገር፡ወመኑ፡
ስምዐ፡ዘይከውን፡ላዕሌየ፡በእንተ፡ኃጢአት፡
ወኢሐሰት፡ውስተ፡አፉየ።
ወበእንተዝ፡መጻእኩ፡ከመ፡እጹር፡አነ፡
ኃጢአተ፡በእንተ፡ዘፄወዎሙ፡ሰይጣን።

ወአውሥአ፡ጲላጦስ፡ወይቤሎ፡ብየ፡
ሥልጣን፡እቅትልከሂ፡ወአሕዩከሂ።

ወይቤሎ፡**እግዚእ፡ኢየሱስ፡**እምአይቴ፡ለከ፡
ሥልጣን፡ትቅትለኒ፡ወታሕይወኒ፡እመ፡
ኢተውህበ፡ለከ፡እምሰማይ።
ወበእንተዝ፡መጻእኩ፡አነ፡ከመ፡እፌጽም፡
ጽሑፍ፡በእንቲአየ።
ወይሁዳ፡ቀዊሞ፡ይሰምዕ፡ዘይትናገሩ፡
ሕዝበ፡አይሁድ፡ወውእቱ፡ረድኡ፡ዘይበልዕ፡

## የዓርብ፡ነግህ።

እርሱን፡ለሞት፡የሚያበቃው፡በደል፡አላገኘ
ሁበትም፡ብሎ፡መስክሮ፡ነበርና፤ከፋዎች፡
አይሁድ፡ግን፡በዕንጨት፡ላይ፡ሰቀሉት።
፲፤ ለሮማውያን፡ግን፡ሥርዓት፡ነበራቸው፤
በዳኛ፡ዘንድ፡በፍርድ፡ካልተረታ፡በቀር፡
ማንንም፡አይገድሉም፡ነበር።
፲፩፤ የወታደር፡ጭፍሮች፡ግን፡የክብር፡ባለቤት፡
**ጌታ፡ኢየሱስን፡**ወስደው፡ሰቀሉት።

የተከበሩ፡አባቶቻችን፡ሐዋርያት፡የደረ
ሱትና፡ያስተማሩን፡ትምህርት፡ይህ፡ነው።
፩፤ በዚያን፡ጊዜም፡የሞት፡ፍርድ፡ይፈርዱበት፡
ዘንድ፡የጲላጦስ፡ዙፋን፡ወደ፡አለበት፡
የፍርድ፡አደባባይ፡**ጌታ፡ኢየሱስን፡**
በመጐተት፡አደረሱት።
፪፤ እርሱም፡ቀኑ፡አይሁድ፡ፋሲካ፡የሚያደር
ጉበት፡ዐርብ፡ጥዋት፡ነበር።
፫፤ ጲላጦስም፡**ጌታ፡ኢየሱስን፡**በአየው፡ጊዜ፡
ከመልኩ፡የተነሣ፡አደነቀ፤ሁለመናውን፡
ብርሃን፡ከቦታልና፡ግርማና፡የጌትነት፡
ክብርም፡በዙሪያው፡ነበር።
፬፤ ጲላጦስም፡የሠራኸው፡ኃጢአት፡የቱ፡ነው፤
የአይሁድ፡ወገኖች፡ሁሉም፡አንተን፡
ለይተው፡ይዘብቱብሃል፤ይሰድቡሃል፤ስመለ
ከታቸውም፡እንደ፡አራዊት፡በአንተ፡ላይ፡
ይጮኻሉ፡አለው።
፭፤ **ጌታም፡**በዚህ፡ነገር፡እንዴት፡ትጠይቀኛለህ?
በእኔ፡ላይ፡ኃጢአት፡ወይም፡በአንደበቴ፡
ሐሰት፡እንዳለ፡ምስክር፡የሚሆን፡ማነው?
፮፤ ስለዚህም፡ሰይጣን፡ስለ፡ማረካቸው፡ሰዎች፡
ኃጢአታቸውን፡ልሸከም፡እኔ፡መጣሁ፡
አለው።
፯፤ ጲላጦስም መልሶ፡እንዲህ፡አለው፤
ልገድልህ፡ወይም፡ላድንህ፡ሥልጣን፡አለኝ፡
አለው።
፰፤ **ጌታ፡ኢየሱስም፡**ከሰማይ፡ካልተሰጠህ፡
በቀር፡ልትገድለኝስ፡ልታድነኝስ፡ሥልጣን፡
ከወዴት፡አለህ፡አለው።
፱፤ ስለዚህም፡ስለ፡እኔ፡የተጻፈውን፡ልፈጽም፡
እኔ፡መጥቻለሁ።
፲፤ የአይሁድ፡ወገኖች፡የሚናገሩትን፡ይሁዳ፡
ቆሞ፡ይሰማ፡ነበር፤እርሱም፡አብሮት፡

ዘዓርብ፡ጸባሕ።

ወይሰቲ፡ ምስሌሁ፡ ዘአግብኦ፡ ወመጠዎ፡
ለሞት።
፲፩ ወሶበሂ፡ሖረ፡ይሁዳ፡ውስተ፡ቤቱ፡ወነሥአ፡
ሠላሳ፡ ብሩረ፡ ወአግብአ፡ ሎሙ፡ ለሊቃነ፡
ካህናት፡ ወጸሐፍት፡ ወይቤሎሙ፡ ንሥኡ፡
ብሩረክሙ፡ወኀድግዎ፡ለኢየሱስ።
፲፪ ወይቤልዎ፡ ኢንነሥእ፡ ንህነ፡ አላ፡ አንተ፡
ንሥእ፡ለሤጠ፡ደም።
፲፫ ወሶበ፡ አበይዎ፡ አግብአ፡ ወገደፎ፡ ውስተ፡
ቤተ፡መቅደስ።
፲፬ ወሐዘነ፡ወሖረ፡ኀበ፡ዕፅ፡ወሰቀለ፡ሐብለ፡
ወተሐንቀ፡ወሞተ፡ውስተ፡ገሀነም፡ለዓለመ፡
ዓለም።
፲፭ ወይቤሎሙ፡ ጲላጦስ፡ ለአይሁድ፡ ተሰአ
ልክዎ፡ ወአልቦ፡ ዘረከብኩ፡ ጌጋይ፡ በዘይ
መውት፡ኅድግዎ፡ናሕዩ፡ደመ፡ንጹሐ፡ወኢ
ታግብኡ፡ላዕሌክሙ።
፲፮ ወውእቶሙ፡ ሊቃነ፡ ካህናት፡ ወጸሐፍት፡
ወዐበይተ፡አይሁድ፡ከልሑ፡ወይቤሉ፡ደሙ፡
ላዕሌነ፡ወላዕለ፡ውሉድነ፤ወአንተሰ፡ፍታሕ፡
ፍትሐ፡ ሞት፡ ላዕሌሁ፡ እስመ፡ ውእቱ፡
ዕድውነ፡ወፀርነ፡ወኢንሰምዕ፡እምኔሁ።
፲፯ ወካዕበ፡አውሥአሙ፡ጲላጦስ፡ለአይሁድ፡
ወይቤሎሙ፡ ለውእቱ፡ ሄሮድስ፡ ቦቱ፡
ሢመት፡ራብዕተ፡እድ፡ውስተ፡ዝንቱ፡ሀገር፡
አርኬላዎስኒ፡ ወውእቶሙ፡ ላእካን፡
እምታሕተ፡መንግሥተ፡ቄሣር።
፲፰ ወአንሰ፡ ኢያፈትሕ፡ ዘእንበለ፡ ምክረ፡
ውእቶሙ፡ ተዓገሡ፡ ንስቲተ፡ ወንሰዶ፡
ለኢየሱስ፡ኀበ፡ሄሮድስ፡ከመ፡ይርአዮ፡ወይ
ትናገር፡ምስሌሁ።
፲፱ እስመ፡ እምኍንዱይ፡ መዋዕል፡ ይፈቅድ፡
ይርአዮ፡ወይሕትቶ፡ወአነ፡እልእክ፡ኀቤሁ፡
ከመ፡ይእትት፡ጋዕዝ፡እማዕከሌነ።
፳ ወውእተ፡ ጊዜ፡ መጠዎ፡ ለአሐዱ፡ ሀቤ፡
ምዕት፡ ሖራ፡ ወአብጽሕዎ፡ ኀበ፡ ሄሮድስ፡
ሥዩመ፡ ራብዕተ፡ እድ፤ ወሶበ፡ ርእዮ፡
ሄሮድስ፡አስተዐጸበ፡ወአንከረ፡ሥነ፡ራእዩ፡

የዓርብ፡ነግህ።

የሚበላ፡የሚጠጣ፡ደቀ፡መዝሙሩ፡ሲሆን፡
ለሞት፡አሳልፎ፡የሰጠው፡ነው።
፲፩ በዚያን፡ጊዜ፡ይሁዳ፡ወደ፡ቤቱ፡ሂዶ፡ያን፡
ሠላሳ፡ብር፡አምጥቶ፡ለካህናት፡አለቆችና፡
ለጸፎች፡መለሰላቸው፤ብራችሁን፡ውሰዱና፡
ኢየሱስን፡ልቀቁት፡አላቸው።
፲፪ እነርሱም፡የደም፡ዋጋህን፡አንተ፡ውሰደው፡
እኛ፡አንቀበልህም፡አሉት።
፲፫ እምቢ፡አንቀበልም፡ባሉትም፡ጊዜ፡መልሶ፡
በቤተ፡መቅደሱ፡ውስጥ፡በተነው።
፲፬ እያዘነም፡ ሂዶ፡ በእንጨት፡ ላይ፡ ገመድ፡
ሰቅሎ፡ለዘላለሙ፡በገሃነም፡ለመኖር፡ታንቆ፡
ሞተ።
፲፭ ጲላጦስም፡ አይሁድን፡ መረመርኩት፤
ለሞት፡የሚያበቃ፡ያገኘሁበት፡ነገር፡የለም፤
ተዉት፡ንጹሕ፡ደም፡አናፍስ፤በራሳችሁ፡
በደል፡አታምጡ፡አላቸው።
፲፮ እነዚያም፡የካህናት፡አለቆች፡ጸፎች፡የአይ
ሁድም፡ ታላላቆች፡ ደሙ፡ በእኛና፡ በልጆ
ቻችን፡ ላይ፡ ይሁን፤ እርሱ፡ ባላጋራችንና፡
ጠላታችን፡ ነውና፡ አንተ፡ የሞት፡ ፍርድ፡
ፍረድበት፡እንጂ፤ስለ፡እርሱ፡ሌላ፡ምንም፡
ነገር፡አንሰማም፡ብለው፡ጮኹ።
፲፯ ዳግመኛም፡ ጲላጦስ፡ ለአይሁድ፡ መልሶ፡
እንዲህ፡አላቸው፡ለዚያ፡ለሄሮድስ፡በዚች፡
አገር፡ከአራት፡አንድ፡እጅ፡ሹመት፡አለው፡
አርኬላዎስም፡እንዲሁ፡ከቄሳር፡መንግሥት፡
በታች፡ሥልጣን፡ያላቸው፡መልእክተኞች፡
ናቸው።
፲፰ ያለ፡እነርሱ፡ምክር፡እኔ፡አልፈርድምና፡
ጥቂት፡ ታገሡ፤ ያየውና፡ ከርሱ፡ ጋር፡
ይነጋገር፡ዘንድ፡ኢየሱስን፡ወደ፡ሄሮድስ፡
እንውሰደው፡አላቸው።
፲፱ እርሱ፡ከብዙ፡ቀን፡ጀምሮ፡ያየውና፡ይመረ
ምረው፡ዘንድ፡ይፈልግ፡ነበርና፤ከመካከላ
ችንም፡ያለ፡ጠብ፡ክርክር፡ይወገድ፡ዘንድ፡
እኔ፡ወደ፡እርሱ፡እልካለሁ፡አለ።
፳ በዚያን፡ጊዜም፡ለአንዱ፡የመቶ፡አለቃ፡
ሰጠው፤ ከአራት፡ አንድ፡ እጅ፡ ገዥ፡
ወደ፡ ሆነው፡ ሄሮድስም፡ አደረሱለት፤
ሄሮድስም፡መልኩንና፡የመልኩንም፡ደም፡

Scanned by CamScanner

## ዘዓርብ፡ጽባሕ።

ወላሕየ፡ገጹ።

፳፩ ወውእቱ ፡ ቀዳሚ ፡ ሰምዐ ፡ እምሕዝበ ፡
አይሁድ፡እለ፡ምሁራን፡አሪተ፡ሙሴ፡ከመ፡
ውእቱ፡ኢየሱስ ፡ንጉሠ ፡ አይሁድ ፡ ሀለዎ ፡
ለሄሮድስ ፡ ሐዘን ፡ ላዕለ ፡ ኢየሱስ ፡ እስመ ፡
እግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ ያስተማስሎ ፡ በአምሳለ ፡
ቀንጽል ፡ ወሶበ ፡ ገብአ ፡ ውስተ ፡ እዴሁ ፡
ፈቀደ፡ከመ፡ይቅትሎ።
፳፪ ወእዘዘሙ፡ለሐራሁ፡ይዝብጥዎ፡በጥብጣቤ፡
እስከ፡ይውኅዝ፡ደሙ፡ላዕለ፡ምድር፡ከመ፡
ማይ።
፳፫ ወእምዝ፡አግብእዎ፡ወአልበስዎ፡ቀይሐ፡
ልብሰ፡ለመድኅን፡ወመጠውዎ፡ለጲላጦስ፡
መኰንን፡እንዘ፡ይብሉ፡ይደልዎ፡ሞት።
፳፬ ወሶበ፡አብጽሕዎ፡ለእግዚእ፡ኢየሱስ፡ርእየ፡
ገጸ፡ሐዘኑ፡በእንተ፡ቅሥፈት፡ዘቀሠፎ፡
ሄሮድስ፡ወሐዘነ፡ዐቢየ፡ሐዘነ፡በልቡ።

፳፭ ወጸሐፈ፡ጲላጦስ፡መጽሐፈ፡መልእክት፡
ኀበ፡ሄሮድስ፡እንዘ፡ይብል፡አነ፡እነግረከ፡
በእንተ፡ዝንቱ፡ጻድቅ፡ዘይብልዎ፡ኢየሱስ፡
አኀዘዎ፡አይሁድ፡ወአምጽእዎ፡ኀቤየ፡
ከመ፡እፍታሕ፡ላዕሌሁ፡ፍትሐ፡ሞት።
፳፮ ወአነ፡ሐተትክዎ፡በሕገ፡አይሁድ፡ወአሪት፡
ሠለስተ፡ጊዜ፡ወአልቦ፡ዘረከብኩ፡ጌጋይ፡በዘ
ይመውት።
፳፯ ወለእመ፡ፈቀድከ፡ንኅድጎ፡ወናሕይዎ፡
ወእመኒ፡ኢትፈቅድ፡ንኅድጎ፡አነ፡ንጹሕ፡
እምደሙ፡ለዝንቱ፡ጻድቅ።
፳፰ ወሶበ፡አንበበ፡ሄሮድስ፡ወነጸረ፡መጽሐፈ፡
መልእክት፡ዘጲላጦስ፡ካዕበ፡ጸሐፈ፡
ውእቱኒ፡መልእክተ፡እንዘ፡ይብል፡አነ፡አስ
ተዐጽብ፡ፍትሐከ፡አ፡ጲላጦስ፡መኰንን፡
ወአንተሰ፡ትፈቅድ፡ታሕዩ፡ብእሴ፡ዐመፃ፡
ወለውእቱ፡ይደልዎ፡ሞት፡አማን፡እምኢያ
ገብእዎ፡አይሁድ፡ኀቤከ።
፳፱ ወውእቱ፡ይብል፡ወልደ፡እግዚአብሔር፡
አነ፡ወአነ፡ንጉሥ፡ወይፈቅድ፡ነቢረ፡ኀበ፡
መንበረ፡ምኵናን፡ዘመሳፍንት።
፴ ወውእቶሙ፡ዐበይተ፡አይሁድ፡ዘያስተ

## የዓርብ፡ነግህ።

ግባት ፡ በአየ ፡ ጊዜ ፡ ዕፁብ ፡ ዕፁብ ፡ ብሎ ፡
አደነቀ።
፳፩ እርሱ ፡ ሄሮድስ ፡ ጌታ ፡ ኢየሱስ ፡ የአይሁድ ፡
ንጉሥ ፡ እንደሆነ ፡ የሙሴን ፡ አሪት ፡ ከተማሩ ፡
አይሁድ ፡ አስቀድሞ ፡ ሰምቶ ፡ ነበርና ፡ ስለ ፡
ጌታ ፡ ኢየሱስ ፡ ሥጋት ፡ ነበረበት ፡ ጌታ ፡
ኢየሱስም ፡ በቀበሮ ፡ ይመስለው ፡ ነበር ፡
በእጁ፡በገባለትም፡ጊዜ፡ሊገድለው፡ወደደ።

፳፪ ደሙ፡በምድር፡ላይ፡እንደ፡ውኃ፡እስኪፈስ፡
ድረስ ፡ በጅራፍ ፡ ይገርፉት ፡ ዘንድ ፡ ወታደ
ሮቹን፡አዘዘ።
፳፫ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ መድኅን ፡ ክርስቶስን ፡ ቀይ ፡
ልብስ፡አልብሰው፡ሞት፡ይገባዋል፡እያሉ፡
መልሰው፡ለመኰንኑ፡ለጲላጦስ፡ሰጡት።
፳፬ ጌታ ፡ ኢየሱስንም ፡ ወደ ፡ ጲላጦስ ፡ በአደ
ረሱት ፡ ጊዜ ፡ ሄሮድስ ፡ ስለ ፡ አስገረፈው ፡
ግርፋት ፡ ፊቱን ፡ አዝኖ ፡ አየውና ፡ በልቡ ፡
እጅግ፡አዘነ።
፳፭ ጲላጦስም፡ወደ፡ሄሮድስ፡እንዲህ፡የምትል፡
መልእክት ፡ ጻፈ ፡ ኢየሱስ ፡ ስለሚሉት ፡
ስለዚህ፡ጻድቅ፡እኔ፡እነግርሃለሁ፡ይሙት፡
በቃ፡ልፈርድበት፡አይሁድ፡ይዘው፡ወደ፡
እኔ፡አመጡት።
፳፮ እኔም፡በአይሁድ፡ሕግ፡በኦሪታቸው፡እንደ
ታዘዘው፡ሦስት፡ጊዜ፡መረመርሁት፡ለሞት፡
የሚያደርስ፡በደል፡አላገኘሁበትም።
፳፯ ብትወድ ፡ እንተወው ፡ እናድነው ፡ እንድን
ተወው ፡ ካልወደድክ ፡ እኔ ፡ በዚህ ፡ ጻድቅ ፡
ሰው፡ደም፡ንጹሕ፡ነኝ፡ብሎ፡ጻፈ።
፳፰ ሄሮድስም፡በአነበበ፡ጊዜ፡ከጲላጦስ፡የተላ
ከውን ፡ ጽሑፍ ፡ ተመልክቶ ፡ እርሱም ፡
ዳግመኛ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ መልእክት ፡ ጻፈ ፡
መኰንን ፡ ጲላጦስ ፡ ሆይ ፡ ፍርድህን ፡ አደን
ቃለሁ፡አንተ፡ዐመፅ፡የሚያስነሣውን፡ሰው፡
ልታድን፡ትወዳለህ፡ለእርሱም፡በእውነት፡
ሞት፡ይገባዋል፡እንዲህ፡ባይሆን፡አይሁድ፡
ወዳንተ፡ባላመጡት፡ነበር።
፳፱ እርሱም፡የእግዚአብሔር፡ልጅ፡ነኝ፡እኔም፡
ንጉሥ ፡ ነኝ ፡ ይላል ፡ በመሳፍንት ፡ ወንበር ፡
ላይ፡ሊቀመጥ፡ይወዳል።
እነዚህም ፡ የአይሁድ ፡ ታላላቆች ፡ በእኔ ፡
፴

## ዘዓርብ፡ጽባሕ።

ዋድዩ፡ ኀቢየ፡ በእንቲአሁ፡ ከመ፡ ውእቱ፡ ይሔገዝ፡ኢየሀቡ፡ጸባሕተ፡ለቄሣር፡ ለነሰ፡ አልብነ፡ንጉሥ፡ዘእንበለ፡ቄሣር።

፴፩፡ ሰማዕከኑ፡ብእሴ፡ዘይሬሲ፡ርእሶ፡ አምላከ፡ እግዚአብሔርሃ፤ ወአንተሰ፡ አግብእ፡ ሎሙ፡ እንዘ፡ሰብእ፡ውእቱ፡ወይፈቅድ፡ይኩን፡ ይሰቅልዎ።

፴፪፡ ወሶበ፡አንበበ፡ጲላጦስ፡መጽሐፈ፡ሄሮድስ፡ ዘይብል፡ ሀቦሙ፡ ለኢየሱስ፡ ይሰቅልዎ፤ ሐዘነ፡ጲላጦስ፡ዐቢየ፡ሐዘነ።

ማህሉ፡ወምሕረቱ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ ዓለም፡አሜን።

ተግሣፅ፡ ዘዮሐንስ፡ አፈ፡ ወርቅ፡ በረከቱ፡ ትኩን፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

፩፡ ምንተ፡ንብል፡አ፡አኃው፡ፍቁራን፡በእንተ፡ ዘከሀደ፡ ይሁዳ፡ ወዘአግብአ፡ ለእግዚኡ፡ ይብል፡ መጽሐፍ፡ እሐዱ፡ እምዐሠርቱ፡ ወክልዔቱ፡ ዘውእቱ፡ ይሁዳ፡ አስቆሮታዊ፡ ሖረ፡ኀበ፡ሊቃነ፡ካህናት፡ወይቤሎሙ፡ ሚ፡ መጠነ፡ትሁቡኒ፡እመ፡ለክሙ፡አገብአ።

፪፡ ወተናገሩ፡የሀብዎ፡ሠላሳ፡ብሩረ፡ዝ፡ውእቱ፡ ሥርዉ፡ለኵሉ፡እከይ፡እስመ፡ፈተወ፡ሤጠ፡ መምህሩ።

፫፡ ሥርዋ፡ለዕኪት፡አፍቅሮ፡ብሩር፡ወይእቲ፡ እመ፡ኵሉ፡እኪት፡ወእመ፡ሰይጣን።

፬፡ ወነፍሳት፡ ዘተዓሥሩ፡ ባቲ፡ ይሰክሩ፡ ወየዓብዱ፡ወኢይትመየጡ፡ያእምሩ፡አሐደ።

፭፡ ወየኀድጉ፡ ሕገ፡ ምግባሮሙ፡ ወይከውን፡ ልቦሙ፡ ዝሉፈ፡ ወእንቡዘ፡ ወእንቅጥቁጠ፡ ወእቡደ።

፮፡ ነጽሩ፡ሚ፡መጠን፡ሠናይት፡በብሩር፡ዘተነ ሥአት፡ እምነ፡ ይሁዳ፤ እስመ፡ እግዚእነ፡ ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ኮነ፡ይነግሮሙ፡ለዝሉፉ፡ በእንተ፡ መንግሥተ፡ ሰማያት፡ ወበእንተ፡ ገሀነም፤ወይኤምሮሙ፡ኵነኔ፡ዘኃጥአን።

## የዓርብ፡ነግህ።

ዘንድ፡ሲከሱት፡ለቄሳር፡ግብር፡እንዳይሰጡ፡ እንደሚያዝዝ፡ ነው፤ እኛ፡ ግን፡ ከቄሳር፡ በቀር፡ንጉሥ፡የለንም።

፴፩፡ ሰው፡ ሲሆን፡ ራሱን፡ አምላክ፡ የሚያደርግ፤ እግዚአብሔርንም፡ ይሆን፡ ዘንድ፡ የሚወድ፤ ሰው፡ ሰምተሃልን? አንተ፡ ግን፡ ይሰቅሉት፡ ዘንድ፡አሳልፈህ፡ስጣቸው።

፴፪፡ ጲላጦስም፡ ይሰቅሉት፡ ዘንድ፡ ኢየሱስን፡ ስጣቸው፡ የሚል፡ የሄሮድስን፡ ጽሑፍ፡ በአነበበ፡ጊዜ፡እጅግ፡አዘነ።

ይቅርታው፡ቸርነቱ፡ከእኛ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡ ይኑር፡አሜን።

በረከቱ፡ ከእኛ፡ ጋራ፡ ለዘላለሙ፡ ትኑርና፡የዮ ሐንስ፡አፈወርቅ፡ምክርና፡ተግሣፅ፡ይህ፡ነው።

፩፡ የተወደዳችሁ፡ ወንድሞች፡ ሆይ፤ ጌታውን፡ ስለ፡ አሲያዘውና፡ ስለካደው፡ ይሁዳ፡ ምን፡ እንላለን፤ መጽሐፍ፡ ከዐሥራ፡ ሁለቱ፡ አንዱ፡ ይኸውም፡ የአስቆሮቱ፡ ይሁዳ፡ ወደ፡ ሊቃነ፡ ካህናት፡ ሂዶ፡ ኢየሱስን፡ ባስይዛችሁ፡ ምን፡ ያህል፡ትሰጡኛላችሁ፡አለ፡ይላል።

፪፡ እነርሱም፡ ሠላሳ፡ ብር፡ ሊሰጡት፡ ተነጋገሩ፤ የክፋት፡ ሁሉ፡ ሥሩ፡ ይህ፡ ነው፤ መምህሩን፡ ለመሸጥ፡ተመኝቷልና።

፫፡ የክፋት፡ ሥርዋ፡ መሠረቷ፡ ገንዘብ፡ መውደድ፡ ነው፤ እርስዋም፡ የክፉ፡ ነገር፡ ሁሉና፡የሰይጣንም፡እናት፡ናት።

፬፡ በእርስዋም፡ የተያዙ፡ ሰውነቶች፡ ይሰክራሉ፤ ያብዳሉ፤አንድን፡ነገር፡ያውቁ፡ዘንድ፡አይመ ለሱም።

፭፡ የሥርዓታቸውን፡ ሕግ፡ ይተዋሉ፤ ልባ ቸውም፡ ደፋርና፡ እንቡዝ፡ የተርበደበደና፡ ያበደ፡ይሆናል።

፮፡ በገንዘብ፡ምክንያት፡ከይሁዳ፡የተነሣች፡ጸጋ፡ ምን፡ ያህል፡ መልካም፡ እንደ፡ ነበረች፡ ተመልከቱ፤ ጌታችን፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ስለ፡ መንግሥተ፡ ሰማያት፡ ተድላ፡ ክብር፤ ስለ፡ ገሃነም፡ሥቃይ፤ሁል፡ጊዜ፡ይነግራቸውና፡የኃ ጥአንንም፡ፍርድ፡ያመለክታቸው፡ነበርና።

Scanned by CamScanner

## ዘዓርብ፡ጽባሕ።

ወይንዕዶ ፡ ለኵሉ ፡ ዘይጠብዕ ፡ በእንተ ፡
መድኃኒተ፡ነፍሱ።
ወለነኒ፡ያድኅነነ፡በብዝኃ፡ምሕረቱ፡ወይር
ድአነ፡ከመ፡ንትጋደል፡ወናጥብዕ፡ወንት
ባደር፡ወንሩጽ፡በእንተ፡መድኃኒተ፡ነፍስነ፡
አሚነነ፡ኪያሁ፡ዘከዓወ፡ደሞ፡በእንቲአነ።
ወንክዐው ፡ ደመነ ፡ በእንተ ፡ **እግዚእነ** ፡
**ኢየሱስ** ፡ **ክርስቶስ** ፡ **መድኃኒነ** ፡ ሎቱ ፡
ስብሐት፡በአፈ፡ኵልነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡
አሜን።

### ተግሣጽ፡ዘዐርብ፡ነግህ፡ ዘይትነበብ።

ነዋ፡አእመርነ ፡ ይእዜ ፡ ከመ ፡ ኀሢሠ ፡
ትምክህት፡ወሢመት፡ወፍቅረ፡ምግባራተ፡
ዓለም፡ምክንያት፡ይእቲ፡ለኵሉ፡እከይ፡
ወታወርድ፡ውስተ፡ሲኦል።
ንትዓቀብኬ፡አ፡ፍቁራንየ፡ከመ፡ኢይት
ረከብ፡እምውስቴትነ፡ብእሲ፡መስተሐምም፡
ወኢጽልሕው፡ወኢዐላዊ፡ሕግ፡ትሩፍ፡ከመ፡
ኢንደቅ፡ኀበ፡መካነ፡ሀጕል።
ርኢክሙኑ ፡ እለ ፡ ተወልዱ ፡ በምዕዳን ፡
ወተጸለሉ ፡ በደመና ፡ ወኮነ ፡ ሎሙ ፡
መንግሥት ፡ ወትንቢት ፡ ወመሥዋዕት ፡
ወቍርባን፡ወሰሚዐ፡ነገረ፡**መለኮት**።
ወሶበ፡ኢተእኅዙ፡በሕጎሙ፡ወኢተወከፉ፡
ትእዛዘ፡**እግዚአብሔር**፡ወኢሖሩ፡በፍኖተ፡
ርትዕ፡ወእፎ፡አያሮሙ፡ትምክህቶሙ፡ወአስ
ከሮሙ ፡ ሢመት ፡ ወተዐቅፉ ፡ በዕብነ ፡
ዕቅፍት፡ ወወድቁ ፡ ውስተ ፡ መርበብተ ፡
ሰይጣን፡እስመ፡ዐሊወ፡ትእዛዘ፡**እግዚአ
ብሔር**፡ምክንያት፡ይእቲ፡ለኵሉ፡እከይ።
ስማዕ፡ዘይቤ፡ልዑል፡እንዘ፡ይወቅሥ፡
ድቀቶሙ፡ይቤ፡ከመዝ፡እንዘ፡ይዘልፎሙ፡
ወለእመ፡አንትሙ፡ኢሰማዕክሙ፡ወኢገበ
ርክሙ፡ትእዛዝየ፡ዘንተ፡ወዐለውክሙ፡
ሥነዩ፡ወኢዐቀብክሙ፡ኵሎ፡ትእዛዝየ፡
ወአብጠልክሙ፡ኪዳንየ፡አነሂ፡እትቤቀ
ለክሙ፡በዘከመዝ።
ወአመጽእ፡ኀቤክሙ፡ፍጡነ፡ኀጢአ፡
ፍሬያት፡ወዝልጋሴ፡ወአበቀ፡ወጸልዐ፡

## የዓርብ፡ነግህ።

፯፤ ስለ፡ነፍሱ፡ድኅነት፡ጨክኖ፡የሚጋደለውን፡
ሁሉ፡ያመሰግነው፡ነበርና።
፰፤ እኛንም ፡ በቸርነቱ ፡ ብዛት ፡ ያድነን ፤
ጨክነን፡ስለ፡ነፍሳችን፡ድኅነት፡እንጋደል፡
ዘንድ ፡ እንሮጥ ፡ እንሽቀዳደም ፡ ዘንድ ፡
ይርዳን።
፱፤ ስለ፡እኛ፡ደሙን፡ያፈሰሰ፡እሱን፡አምነን፤
መዳኛችን፡ስለሚሆን፡ስለ፡**ጌታችን**፡ስለ፡
**መድኃኒታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ**፡ደማችንን፡
እናፍስስ ፤ በሁላችን ፡ አንደበት ፡ ለእርሱ ፡
ምስጋና፡ክብር፡ይሁን፡ለዘላለሙ፡አሜን።

### ዐርብ፡በነግህ፡የሚነበብ፡ምክር፡እዝናት፡ ይህ፡ነው።

፩፤ በትምክህት ፡ ሁኖ ፡ ሹመት ፡ መፈለግ ፡
ዓለማዊ፡ሥራዎችን፡መውደድ፡ለክፋት፡
ሁሉ፡ምክንያት፡ሁኖ፡ወደ፡ሲኦል፡እንድታ
ወርድ፡እነሆ፡አሁን፡አወቅን።
፪፤ ወዳጆቼ፡ሆይ፡ወደ፡ጥፋት፡ቦታ፡እንዳን
ወድቅ፡በውስጣችን፡ምቀኛ፡ሰው፡ወይም፡
ሽንጋይ፡ወይም፡ፍጹም፡ሕግን፡አፍራሽ፤እን
ዳይገኝ፡እንጠንቀቅ።
፫፤ በትምህርት፡የተወለዱትን፡በደመና፡የተጋረ
ዱትን፡መንግሥት፡ትንቢት፡መሥዋዕት፡
ቍርባን፡**የመለኮትን**፡ነገር፡መስማት፡ተሰጥ
ቷቸው፡የነበሩትን፡አይታችኋልን?
፬፤ በሕጋቸው፡ባልጸኑ፡ጊዜ፡**የእግዚአብሔርን**፡
ትእዛዝ ፡ ባልተቀበሉና ፡ በቀና ፡ መንገድ ፡
ባልሄዱ፡ጊዜ፡ትምክህታቸው፡እንዴት፡እን
ዳሳወራቸው፡ሹመትም፡እንዴት፡እንዳሰከራ
ቸውና፡በዕንቅፋት፡ደንጊያ፡ተሰነካክለው፡
ከሰይጣን፡ወጥመድ፡ውስጥ፡እንደ፡ወደቁ፡
አያችሁን? **የእግዚአብሔርን** ፡ ትእዛዝ ፡
ማፍረስ፡ለክፋት፡ሁሉ፡ምክንያት፡ናትና።
፭፤ ልዑል ፡ **እግዚአብሔር** ፡ ውድቀታቸውን ፡
ሲያስረዳ፡ያለውን፡ስማ፤እየዘለፋቸውም፡
እናንተ፡ባትሰሙኝ፡ያዘዝኳችሁን፡ባትሠሩ፡
ፍርዴንም፡ብትለውጡ፡ትእዛዜንም፡ሁሉ፡
ባትጠብቁ፡ቃል፡ኪዳኔን፡ብታጠፉ፡በእን
ደዚህ፡ያለ፡መቅሠፍት፡እበቀላችኋለሁ፡
አለ።
፮፤ ወደ፡እናንተ፡ረኃብን፡ቍስል፡ሥጋን፡
ደረመንን፡ቍስልን፡ልብን፡የሚያራኽ፡

| ዘዓርብ፡ጽባሕ። | የዓርብ፡ነግህ። |
| --- | --- |
| ዘየሐምም፡ዐይኖሙ፡ወይሰልብ፡ነፍሶሙ፡ወይዘሩ፡ዘርዖሙ፡ለከንቱ፡ወይበልዕዎ፡እለ፡ጸብእዎሙ፡ወእፌኑ፡ዲቤሆሙ፡መዐትየ፡እስከ፡ይወድቁ፡ማእከለ፡ዐሮሙ። | የዐይን፡በሽታን፡ዘራቸውንም፡በከንቱ፡የሚያጠፋ፡መቅሠፍትን፡አመጣለሁ፡የምድራቸውን፡ፍሬ፡የተጣሉአቸው፡ይበሉታል፡በጠላቶቻቸው፡መካከል፡እስከ፡ወደቁ፡ድረስ፡በላያቸው፡መዐቴን፡እልካለሁ። |
| ፯፡ ወይገርሩ፡ለእለ፡ጸልእዎሙ፡ወይነትዑ፡እንዘ፡አልቦ፡ዘይሰድዶሙ። | ፯፡ ለጠላቶቻቸውም፡ይገዛሉ፡የሚያሳድዳቸውም፡ሳይኖር፡ይሸሻሉ። |
| ፰፡ ወለእመ፡ኢሰምዑ፡ትእዛዝየ፡እምድኅረዝ፡አነ፡እዌስክ፡ሰብዓተ፡በቀለ፡ዘዘዚአሁ፡ላዕለ፡ኃጣውኢሆሙ፡ወእሰብር፡ትዕቢተ፡ልቦሙ። | ፰፡ ትእዛዜን፡ካልሰሙ፡ከእንግዲህ፡ወዲህ፡እኔ፡በኃጢአታቸው፡ላይ፡በየራሱ፡ሰባት፡በቀልን፡ጨምሬ፡የልባቸውን፡ትዕቢት፡እሰብራለሁ። |
| ፱፡ ወእሬስያ፡ለሰማይ፡ኀጺነ፡በመልዕልቴሆሙ፡ወለምድርኒ፡ብርተ፡በመትሕቴሆሙ። | ፱፡ በላያቸው፡ያለ፡ሰማይን፡ብረት፡በበታቻቸው፡ያለች፡ምድርን፡ነሀስ፡አደርጋታለሁ። |
| ፲፡ ወይከውና፡ፍናዊሆሙ፡ለከንቱ፡ወኢይትዌሰክ፡ምድሮሙ፡ኀይለ፡ወኢይሁብ፡ዕፀው፡ምድሮሙ፡ፍሬ። | ፲፡ መንገዶቻቸውም፡ለከንቱ፡ይሆናሉ፡ምድራቸውም፡በረከት፡አይጨመርበትም፡በምድራቸውም፡ያሉ፡ዕፀዋት፡አትክልቶች፡ፍሬን፡አይሰጡም። |
| ፲፩፡ ወእመ፡ሖሩ፡እሙንቱ፡ግድመ፡ግድመ፡ወኢሰምዑ፡ትእዛዝየ፡እቀሥፎሙ፡ሰብዐተ፡መቅሠፍታተ፡ካልአነ፡ዲበ፡ኃጣውኢሆሙ፡ወእፌኑ፡ላዕሌሆሙ፡አርዌ፡ዘይበልዖሙ፡ወይቀትሎሙ፡ወያሀጕሎሙ፡እንስሳሆሙ፡ወያማስን፡ፍናዊሆሙ። | ፲፩፡ እነርሱ፡አግድም፡አግድም፡በኃጢአት፡ቢሄዱ፡ትእዛዜንም፡ባይሰሙ፡በኃጢአታቸው፡ላይ፡ሌላ፡ሰባት፡መቅሠፍት፡አምጥቼ፡እቀጣቸዋለሁ፤የሚበላቸውንና፡የሚገድላቸውን፡አውሬ፡እልካለሁ፤እንስሶቻቸውንም፡መንገዳቸውንም፡የሚያጠፋ፡ይሆናል። |
| ፲፪፡ ወለእመ፡ኢተገሥጹ፡በዝንቱ፡ወጸንዑ፡ዲበ፡ጥውየቶሙ፡እዘብጠሙ፡በሰብዐቱ፡ዝብጠታት፡ዲበ፡ኃጣውኢሆሙ፡ወእመልኅ፡ዲቤሆሙ፡ሰይፈ፡ወእትቤቀሎሙ፡እስከ፡ይትመዘበር፡ሀገሮሙ። | ፲፪፡ በዚህም፡ባይገሠፁ፡በጠማማነታቸውም፡ቢጸኑ፡በኃጢአታቸው፡ላይ፡ሰባት፡መቅሠፍት፡አምጥቼ፡እቀጣቸዋለሁ፡ሀገራቸው፡እስከሚጠፋ፡ሰይፈ፡መዐቴን፡መዝዤ፡እበቀላቸዋለሁ። |
| ፲፫፡ ወእፌኑ፡ኀቤሆሙ፡ረሀበ፡ወእገብእሙ፡ውስተ፡ዕደ፡ዐሮሙ፡ወአዐጽብ፡ላዕሌሆሙ፡ሲሳየ፡ዕለቶሙ፡ወይበልዑ፡በመስፈርት፡ወኢይጸግቡ። | ፲፫፡ ወደ፡እነርሱ፡ረሀብን፡እልካለሁ፤በጠላቶቻቸውም፡እጅ፡አሳልፌ፡እሰጣቸዋለሁ፡ደርሻ፡የዕለት፡ምግባቸውን፡እስከማሳጣት፡ድረስ፡አስጨንቃቸዋለሁ፤በመጠኑ፡ተሰፍሮላቸው፡ይበላሉ፡አይጠግቡም። |
| ፲፬፡ ወለእመ፡ኢሰምዑ፡ዘንተኒ፡ወጸንዑ፡ዲበ፡ጥውየቶሙ፤አነኒ፡አሐውር፡ምስሌሆሙ፡ጠዋየ፡ወእሜክሮሙ፡ሰብዓተ፡ቅሥፈታተ፡ዲበ፡ኃጣውኢሆሙ፡እስከ፡ይበልዑ፡ሥጋ፡ውሉዶሙ፡ወአዋልዲሆሙ። | ፲፬፡ ፍርዴንም፡አልሰማ፡ብለው፡በጠማማነታቸው፡ላይ፡ቢጸኑ፡እኔም፡መከራን፡አመጣባቸዋለሁ፤የወንዶችና፡የሴቶች፡ልጆቻቸውን፡ሥጋ፡እስከሚበሉ፡ድረስ፡በኃጢአታቸው፡ላይ፡ሰባት፡መቅሠፍት፡አምጥቼ፡እፈትናቸዋለሁ። |

Scanned by CamScanner

## ዘዓርብ፡ጽባሕ።

፲፭ ወእመዘብር ፡ አህጉሪሆሙ ፡ ወአማስን ፡ ዘውስተ፡እደዊሆሙ።

፲፮ ወታስቈርሮሙ ፡ ነፍስየ ፡ ወእነስት ፡ መቅደሶሙ፡ወኢይትዌከፍ፡ቍርባኖሙ።

፲፯ ወኢያጼኑ፡መዐዛ፡ዕጣኖሙ፡ወእትቈጣዕ፡ዲበ፡ምድሮሙ፡እስከ፡ይፈርሁ፡ፀሮሙ፡በዝንቱ፡ነገር፡ወኢይነብሩ፡ውስተ፡አህጉሪሆሙ፡ወእዘርዎሙ፡ውስተ፡አሕዛብ፡ወለእለ፡ተርፉ፡እምኔሆሙ፡ውስተ፡ሀገር፡እወዲ፡ውስቴቶሙ፡ፍርሀተ፡እምነ፡ፀሮሙ፡ወይትሀወኩ፡ከመ፡ዘይነትዕ፡ወይጐይዩ፡በውስተ፡ኲናት።

፲፰ ወሶበ ፡ ኢተመይጡ ፡ እምእከዮሙ ፡ ወኢነስሑ፡እምጌጋዮሙ፡ወኢገብሩ፡ፈቃደ፡እግዚእሙ፡ወድቁ፡በገጾሙ፡ወተፈጸመ፡ላዕሌሆሙ፡ዝንቱ፡ኲሉ፡ዘተብህለ።

፲፱ ወለእመኒ፡አእመርከሙ፡አ፡ፍቁራንየ፡ከመ፡ለእለ፡ተዓደዉ፡ትእዛዘ፡እግዚአብሔር፡ደለዎሙ፡ዝንቱ፡ሀጕል፡ዕፁብ፤ይደልወነኬ፡ንትመየጥ፡እምጌጋይነ፡ወንንቃህ፡እምሀኬትነ፤ወንፍራህ፡እምኵነኔሁ፡ለእግዚእነ፡ከመ፡ንትባላህ፡በጸጋሁ።

ሎቱ፡ስብሐት፡ወአኰቴት፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

### ምንተኑ፡በል።

ተአምሪሃ፡ለእግዝእትነ፡ቅድስት፡ድንግል፡በክልኤ፡ማርያም፡ወላዲተ፡አምላክ፡ጸሎታ፡ወበረከታ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

፳ ወአሐተ፡ዕለተ፡ይቤላ፡እግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ለወላዲቱ፡እግዝእትነ፡ቅድስት፡ድንግል፡በክልኤ፡ማርያም፡አ፡ወላዲትየ፡አይኑ፡ሐዘን፡የዐቢ፡እምሐዘናት፡ዘረከቡኪ፡በእንቲአየ።

## የዓርብ፡ነግህ።

፲፭፤ በእጆቻቸው፡ያለ፡ገንዘባቸውንና፡አገሮቻቸውን፡ፈጽሜ፡አጠፋለሁ።

፲፮፤ ልቤ፡ትጸየፋቸዋለች፤መቅደሳቸውን፡አፈርሳለሁ፤ቍርባናቸውንም፡አልቀበልም።

፲፯፤ የዕጣናቸውንም፡መዐዛ፡አልቀበልም፤በዚህ፡ነገር፡ጠላቶቻቸው፡እስከሚፈሩ፡ድረስ፡በሀገራቸው፡ላይ፡እቆጣለሁ፤በሀገሮቻቸውም፡አይኖሩም፤በአሕዛብ፡ውስጥ፡እበትናቸዋለሁ፤ከእነርሱም፡የቀሩትን፡በውስጣቸው፡ከጠላቶቻቸው፡የተነሣ፡ፍርሀትን፡እጨምራለሁ፤ከጦር፡ድል፡ሁኖ፡እንደሚሸሽ፡ይታወካሉ።

፲፰፤ ከክፋታቸውና፡ከበደላቸው፡ተመልሰው፡ባልተጸጸቱ፡ጊዜ፡የጌታቸውንም፡ፈቃድ፡ባላደረጉ፡ጊዜ፡በግንባራቸው፡ፍግም፡ብለው፡ይወድቃሉ፤ይህ፡የተባለው፡ሁሉ፡በእነርሱ፡ላይ፡ይፈጸማል።

፲፱፤ ወንድሞቼ፡ሆይ፡የእግዚአብሔርን፡ትእዛዝ፡የተላለፉትን፡ይህ፡ሁሉ፡መቅሠፍት፡እንደተገባቸው፡ካወቃችሁ፡ከበደላችን፡እንመለስ፡ዘንድ፡ከስንፍናችን፡እንነቃ፡ዘንድ፡ይገባናል፤በቸርነቱም፡እንድን፡ዘንድ፡ከጌታችን፡ፍርድ፡የተነሣ፡እንፍራ።

ለእርሱም፡ክብር፡ምስጋና፡ይሁን፤ለዘላለሙ፡አሜን።

### ምንተኑ፡በል።

ልመናዋ፡በረከቷ፡ከእኛ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡ይደርብንና፡በድንጋሌ፡ሥጋ፡በድንጋሌ፡ነፍስ፡የጸናች፡አምላክን፡የወለደች፡ንጽሕት፡እመቤታችን፡ማርያም፡ያደረገችው፡ተአምር፡ይህ፡ነው።

፳፤ ከዕለታት፡በአንዲት፡ቀን፡ጌታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡በሁለት፡ወገን፡ድንግል፡የሆነች፡ቅድስት፡ማርያምን፡እናቴ፡ሆይ፡በኔ፡ምክንያት፡ከአገኙሽ፡ኀዘኖች፡የትኛው፡ኀዘን፡ይበልጣል፡አላት።

## ዘዓርብ፡ጽባሕ።

፩ ወትቤሎ ፡ እግዝእተ ፡ ኵልነ ፡ ቅድስት ፡
ድንግል ፡ በክልኤ ፡ ማርያም ፡ ወላዲተ ፡
አምላክ ፡ አ ፡ እግዚእየ ፡ ወአምላኪየ ፡
እሉ ፡ እሙንቱ ፡ ሐምስቱ ፡ ሐዘናት ፡
የዐብዩ።
፪ አሐዱ፡እምኔሆሙ፡ሶበ፡ተነበየ፡ስምዖን፡
በቤተ ፡ መቅደስ ፡ ከመ ፡ ይቀትሉከ ፡
አይሁድ።
፫ ወካልእ፡ሶበ፡ኀጣእኩከ፡እምቤተ፡መቅደስ፡
እንዘ፡እኅሥሠከ፡ሠለስተ፡ዕለታተ።
፬ ወሣልስ፡ሶበ፡እዜክር፡ከመ፡አሰሩከ፡እደዊከ፡
ወእገሪከ ፡ ወዘከመ ፡ ቀሠፉከ ፡ በዐውደ ፡
ጲላጦስ፡መስፍን።
፭ ወራብዕ ፡ ሶበ ፡ እሔሊ ፡ ከመ ፡ ሰቀሉከ ፡
ማዕከለ፡ ክልኤ፡ፈያት፡ቅንወከ፡ወዕሩቀከ፡
እምልብስ፡ምድራዊ፡እንዘ፡አንተ፡ክብረ፡
ነገሥት፡ወብዕለ፡ኵሉ፡ዓለም።

፮ ወሐምስ፡ሶበ፡እዜክር፡ከመ፡ወደዩከ፡ውስተ፡
ከርሠ ፡ መቃብር ፡ ዮሴፍ ፡ ወኒቆዲሞስ ፡
ገኒዞሙ፡በልብሰ፡ክታን።

፯ ወይቤላ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡
እግዝእትነ ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡
በክልኤ ፡ ማርያም ፡ ወላዲተ ፡ አምላክ ፡
እሎንተ ፡ ሐምስተ ፡ ሐዘናተ ፡ ዘዘከረ ፡
እንዘ፡ይብል፡አቡነ፡ዘበሰማያት፡ወሰላመ፡
ቅዱስ ፡ ገብርኤል ፡ መልአክ ፡ እነ ፡ እሠሪ ፡
ኃጢአቶ።
፰ ወለዘሂ፡ወሀበ፡ምጽዋተ፡ለነዳይ፡በስምኪ፡
አነ፡እሰምዖ፡ጸሎቶ፡ወእመጽእ፡ምስሌኪ፡
ኀቤሁ፡እምቅድመ፡ሞቱ፡እንዘ፡ሀለዉ፡
ሠለስቱ፡ዕለታት፡ወናስተርእዮ።
፱ ወሶበ፡ሰምዐ፡ደቅስዮስ፡ዘንተ፡ነገረ፡እንዘ፡
ይነግራ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡
ለወላዲቱ ፡ ድንግል ፡ ጸሐፋ ፡ ወአዘዘ ፡
ያንብብዋ፡ምእመናን።

ጸሎታ፡ወበረከታ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡
ዓለም፡አሜን።

## የዓርብ፡ነግህ።

፩ በድንጋሌ፡ሥጋ፡በድንጋሌ፡ነፍስ፡የጸናች፡
አምላክን ፡ የወለደች ፡ የሁላችን ፡ እመቤት፡
ክብርት ፡ ማርያም ፡ ፈጣሪዬ ፡ ጌታዬ ፡ ሆይ፡
በእኔ ፡ ዘንድ ፡ እኒህ ፡ አምስቱ ፡ ኀዘኖች ፡
ይበልጣሉ፡አለችው።
፪ ከአምስቱ፡አንዱ፡አይሁድ፡እንደሚገድሉህ፡
በቤተ፡መቅደስ፡ስምዖን፡ትንቢት፡በተናገረ፡
ጊዜ፡ነው።
፫ ሁለተኛውም፡ሦስት፡ቀን፡በቤተ፡መቅደስ፡
ፈልጌ፡ባጣሁህ፡ጊዜ፡ነው።
፬ ሦስተኛውም፡እጅህንና፡እግርህን፡አሥረው፡
በጲላጦስ ፡ አደባባይ ፡ የገረፉህን ፡ ግርፋት፡
ባሰብኩ፡ጊዜ፡ነው።
፭ አራተኛውም ፡ አንተ ፡ የነገሥታት ፡ ክብር፡
የዓለሙ ፡ ሁሉ ፡ ሀብት ፡ ስትሆን ፡ በዕለተ፡
ዐርብ፡ራቁትህን፡ቸንክረው፡በሁለት፡ወንበ
ዴዎች ፡ መካከል ፡ እንደሰቀሉህ ፡ ባሰብኩ፡
ጊዜ፡ነው።
፮ አምስተኛውም ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ መቃብር፡
ውስጥ፡ዮሴፍና፡ኒቆዲሞስ፡በበፍታ፡ልብስ፡
ገንዘው፡እንዳወረዱህ፡ባሰብኩ፡ጊዜ፡ነው፡
አለችው።
፯ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስም ፡ በድንጋሌ፡
ሥጋ ፡ በድንጋሌ ፡ ነፍስ ፡ የጸናች ፡ እናቱን፡
ክብርት ፡ እመቤታችን ፡ ማርያምን ፡ በእኔ፡
ምክንያት ፡ ያገኙሽን ፡ እኒህን ፡ አምስቱን፡
ኀዘኖችና፡መከራዎች፡አቡነ፡ዘበሰማያትንና፡
የገብርኤልን ፡ሰላምታ፡እየደገመ፡ያሰበውን፡
ኃጢአቱን፡እኔ፡አስተሠርይለታለሁ።
፰ በስምሽም ፡ ምጽዋት ፡ የሰጠውን ፡ እኔ፡
ጸሎቱን፡እሰማለሁ፤ከመሞቱ፡አስቀድሞ፡
በሦስተኛው፡ቀን፡ካንቺ፡ጋራ፡መጥቼ፡እንገ
ለጽለታለን፡አላት።
፱ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ለድንግል፡
እናቱ፡ይህን፡ሲናገር፡ደቅስዮስ፡ሰምቶ፡በእ
መቤታችን ፡ ተዓምር ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ፡
ጻፋት፤ምእመናንም፡ያነቧት፡ዘንድ፡አዘዘ።

ልመናዋ ፡ በረከቷ ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ለዘላለሙ፡
ይኑር፡አሜን።

ዘዓርብ፡ጽባሕ።

አርኬ።
በፈቃደ፡አቡሁ፡ወበሥምረተ፡ርእሱ፡አመ፡
ርእሰ፡ይትቀተል፤ከመ፡ተዓገሠ፡ኀፃውንተ፡
ቅዱስ፡መስቀል፤ሶበ፡ሰማዕኪ፡ማርያም፡
ወነገሩኪ፡በቃል፤ዘውኅዘ፡እምአዕይንትኪ፡
ከመ፡ውኂዘ፡ማይ፡ዘይፈለፍል፤ድንግል፡
ድንግል፡ወላዲተ፡አምላክ፡ቃል፡ይኩነኒ፡
ቤዛ፡ማየ፡አንብዕኪ፡እምሀጕል።

ወላዲተ፡አምላክ፡ማርያም፡በል።

ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ጥዑመ፡ስም፡ለዘይ
ጼውዖ፡በል።

ተአምር፡ወመንክር፡ዘገብረ፡እግዚእነ፡ወአ
ምላክነ፡ወመድኃኒነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡
ግሁሉ፡ወምሕረቱ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡
ዓለም፡አሜን።

፩ ወወሰድዎ፡ለእግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡
ወጸዶ፡ለጲላጦስ፡መስፍን፡ዘሀሎ፡ይእተ፡
አሚረ፡በኢየሩሳሌም።

፪ ወይቀውሙ፡አፍአ፡ኆኅት፡ዕደው፡ኃያላን፡
ወይጸውሩ፡አርማሐ፡ነዊኃነ።

፫ ወሶበ፡ርእዮሙ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ለእልክቱ፡
አርማሕ፡ሰገዱ፡ሎቱ፡እሙንቱ፡አርማሕ፡
ከመ፡ዘይሰግድ፡ሰብእ።

፬ ወሶበ፡ርእዩ፡አይሁድ፡ዘንተ፡ይቤልዎ፡
ለጲላጦስ፡እስመ፡ዕደው፡እለ፡ይጸውሩ፡
አርማሐ፡ወይቀውሙ፡አፍአ፡ኆኅት፡
ነሥኡ፡ሕልያነ፡እምአብያጺሁ፡ለኢየሱስ።

፭ ወይቤሎሙ፡ጲላጦስ፡እስፍንቱ፡አርማሕ፡
እለ፡ሰገዱ፡ለኢየሱስ፡ወይቤሉ፡አይሁድ፡
ስድስቱ።

፮ ወካዕበ፡ይቤሎሙ፡እስፍንቱ፡ዕደው፡እለ፡
ይጸውርዎሙ፡ወይቤሉ፡ዕደው፡ስድስቱ፡
ለለአሐዱ፡አሐዱ፡ይጸውሩ፡አሐደ፡አሐደ፡
ረምሐ።

፯ ወይቤሎሙ፡ጲላጦስ፡ኅረዩ፡ለክሙ፡ዕደወ፡
ዘተአምኑ፡ወረስዩ፡ለለአሐዱ፡ረምሐ፡
ዐሠርተ፡ዕደወ።

፰ ወእመ፡ገበርክሙ፡ዘንተ፡ናወፅአ፡ለኢየሱስ፡
ኀበ፡መካነ፡አርማሕ፡ከመ፡ንጠይቅ፡
ዘሐመይክምዎሙ፡ለአኀዊነ።

የዓርብ፡ነግህ።

አርኬ።
አካላዊ፡ቃልን፡የወለድሽ፡ድንግል፡ሆይ፡
በቅዱስ፡መስቀል፡መቸንከርን፡ታግሦ፡
በአባቱ፡ፈቃድና፡በራሱ፡ፈቃድ፡በሥጋ፡
ሞቱን፡በነገሩሽና፡በሰማሽ፡ጊዜ፡በዝቶ፡እን
ደሚፈስ፡የምንጭ፡ውኃ፡ከአይኖችሽ፡
የፈሰሰው፡የዕንባ፡ውኃ፡ከጥፋት፡ቤዛ፡
ይሁነኝ።

የአምላክ፡እናት፡ማርያም፡በል።

ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ጥዑመ፡ስም፡ለዘይ
ጼውዖ፡በል።

ይቅርታውና፡ቸርነቱ፡ከእኛ፡ጋራ፡
ለዘላለሙ፡ይኑርና፡ጌታችን፡ፈጣሪያችን፡
መድኃኒታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡
ያደረገው፡ድንቅ፡ተአምር፡ይህ፡ነው።

፩፤ በዚያን፡ጊዜ፡ጌታ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስን፡በኢ
የሩሳሌም፡ወደ፡አለው፡ወደ፡መስፍኑ፡
ጲላጦስ፡ግቢ፡ወሰዱት።

፪፤ ረጃጅም፡ጦሮችን፡የተሸከሙ፡ወንዶችም፡
ከበር፡ውጭ፡ቁመው፡ነበር።

፫፤ ጌታ፡ኢየሱስም፡እነዚያን፡ጦሮች፡ባያቸው፡
ጊዜ፡ሰው፡እንደሚሰግድ፡እነዚያ፡ጦሮች፡
ሰገዱለት።

፬፤ አይሁድም፡ይህን፡ባዩ፡ጊዜ፡ጦሮችን፡
ተሸክመው፡በደጅ፡የቆሙ፡ሰዎች፡
ከኢየሱስ፡ባልንጀሮች፡መማለጃ፡ተቀብ
ለዋል፡ብለው፡ለጲላጦስ፡ነገሩት።

፭፤ ጲላጦስም፡ለኢየሱስ፡የሰገዱ፡ጦሮች፡
ስንት፡ናቸው፡አላቸው፤አይሁድም፡
ስድስት፡ናቸው፡አሉ።

፮፤ ሁለተኛም፡የተሸከሟቸው፡ሰዎችስ፡ስንት፡
ናቸው፡አላቸው፤እነርሱም፡እያንዳንዱ፡
አንድ፡አንድ፡ጦር፡በመያዝ፡ስድስት፡
ናቸው፡አሉ።

፯፤ ጲላጦስም፡የምታምኗቸውን፡ሰዎች፡
መርጣችሁ፡ለእያንዳንዱ፡ጦር፡ዐሥር፡
ወንዶችን፡አድርጉ፡አላቸው።

፰፤ ይህንንም፡ካደረጋችሁ፡በኋላ፡ጦሮች፡
ወዳሉበት፡ቦታ፡ኢየሱስን፡እናወጣዋለን፤
ወንድሞቻችንን፡ያማችሁበትን፡እንረዳ፡
ዘንድ፡አላቸው።

Scanned by CamScanner

፯፻፳፮

## ዘዓርብ፡ጽባሕ።

፱፡ ወገብሩ ፡ አይሁድ ፡ በከመ ፡ ይቤሎሙ ፡
ጲላጦስ።
፲፡ ወኅረዩ፡እምሰብእሙ፡ዕደወ፡ኃያላነ፡እለ፡የአ
ምንዎሙ፤ወወሀብዎሙ፡ለዐሥርቱ፡ዕደው፡
አሐደ ፡ አሐደ ፡ ረምሐ ፤ ወከነ ፡ ኊልቈሙ ፡
ለዕደው፡እለ፡ይእኅዙ፡ረምሐ፡ስሳ።
፲፩፡ ወእምዝ ፡ አዘዘ ፡ ጲላጦስ ፡ ያውፅእዎ ፡
ለእግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ ኀበ ፡ መካነ ፡ አርማሕ ፤
ወሶበ፡ነጸርሙ፡ሰገዱ፡አርማሕ፡ቅድሜሁ፡
ለእግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ።
፲፪፡ ወሶበ፡ርእዩ፡አይሁድ፡ዘንተ፡ከልሑ፡ዐቢየ፡
ክላሐ፡ወይቤሉ፡ኢርኢነ፡ሥራየ፡ዘከመ፡
ሥራዩ፡ለዝ፡ብእሲ።
፲፫፡ ወይቤልዎሙ፡ሰብአ፡ሮም፡ለእለ፡ሀለዉ፡
ሀየ፡እስመ፡ሙዓዐ፡ለኵሉ፡ሥራይ፡እምኀበ፡
አይሁድ፡ውእቱ፤ሠርይዎ፡እስኩ፡አንትሙ፡
ለዝ፡ብእሲ፡ወማእዎ፡ለእመ፡ኮነ፡መሠርየ፡
በከመ፡ትቤሉ።
፲፬፡ ወይቤሉ ፡ አይሁድ ፡ ለነሰ ፡ ኢይትከሀለነ ፡
ንግበር፡ሥራየ፡ዘከመ፡ሥራዩ።
፲፭፡ ወዓዲ ፡ ሰአልዎ ፡ ለጲላጦስ ፡ ከመ ፡ የሀብ ፡
ለዐሥርቱ፡ወኀምስቱ፡ብእሲ፡አሐደ፡ረምሐ፡
ወከማሁ ፡ ይግበር ፡ ለኵሎሙ ፡ አርማሕ ፡
ወይፍትን፡እመ፡ይሰግዱ፡እልክቱ፡አርማሕ፡
ለኢየሱስ።

፲፮፡ ወገብረ ፡ ጲላጦስ ፡ በከመ ፡ አመከርዎ ፡
አይሁድ፡ወአስተአኀዘ፡ለለ፡አሐዱ፡ረምሐ፡
በበዐሥርቱ፡ወኀምስቱ፡ዕደው፡ሮማውያን፡
ጽኑዓን።
፲፯፡ ወወፅአ ፡ ጲላጦስ ፡ ኀበ ፡ መካነ ፡ አርማሕ ፡
ወነበረ፡ዲበ፡መንበር፡ወአውፅአ፡ለእግዚእ፡
ኢየሱስ፡ወሶበ፡ርእዮሙ፡ለአርማሕ፡ሰገዱ፡
ሎቱ፡ሠለስተ፡ጊዜ።
፲፰፡ ወዕደውሰ፡እለ፡ይእኅዝዎሙ፡አኀዙ፡ይስሐ
ብዎሙ፡ለአርማሕ፡በኃይል፡ወኢክህሉ፡ያኀ
ድግዎሙ፡ሰጊደ።
፲፱፡ ወሶበ፡ርእየ፡ጲላጦስ፡ዘንተ፡አኀዘ፡ፍርሀት፡
ወረዐድ ፤ ወበዕጹብ ፡ ግብር ፡ ተመይጠ ፡
ውስተ፡መካነ፡መንበሩ።
፳፡ ወአቀሞ ፡ ለእግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ ቅድሜሁ ፡
ወኵሎሙ፡አይሁድ፡ዐውዱ።

## የዓርብ፡ነግህ።

፱፡ አይሁድም፡ጲላጦስ፡እንዳላቸው፡አደረጉ።
፲፡ ከሰዎቻቸውም ፡ የሚያምኑአቸውን ፡ ኃይለ
ኞችን ፡ ሰዎች ፡ መረጡ ፤ ለዐሥር ፡ ለዐሥር፡
ወንዶች ፡ አንዳንድ ፡ ጦርን ፡ አስያዙ ፤ ጦር፡
የያዙ፡ሰዎችም፡ቍጥራቸው፡ስልሳ፡ሆነ።
፲፩፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ጲላጦስ ፡ ጌታ ፡ ኢየሱስን፡
ጦሮች ፡ ወዳሉበት ፡ ቦታ ፡ ያወጡት ፡ ዘንድ፡
አዘዘ ፤ ጌታ ፡ በአያቸውም ፡ ጊዜ ፡ ጦሮች፡
በጌታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ፊት፡ሰገዱ።
፲፪፡ አይሁድም፡ይህን፡ባዩ፡ጊዜ፡እንደዚህ፡ሰው፡
ያለ፡ሥራየኛ፡አላየንም፡ብለው፡ጮኹ።

፲፫፡ ከዚያ ፡ ያሉትም ፡ የሮም ፡ ሰዎች ፡ የሥራይ፡
ሁሉ ፡ መፍለቂያው ፡ ከአይሁድ ፡ ነውና፤እንደ
ምትሉት፡ይህ፡ሰው፡ሥራየኛ፡ከሆነ፡ሥራይ፡
አድርጉበትና ፡ እስቲ ፡ እናንተ ፡ አሸንፉት፡
አሉአቸው።
፲፬፡ አይሁድም፡እኛስ፡እርሱ፡እንደሚያደርገው፡
ሥራይ፡አንችልም፡አሉ።
፲፭፡ ዳግመኛም፡ለአሥራ፡አምስት፡ሰው፡አንድ፡
አንድ ፡ ጦር ፡ ያሲዝ ፡ ዘንድ ፡ ጲላጦስን፡
ለመኑት ፤ ጦሮችንም ፡ ሁሉ ፡ እንዲሁ፡
ለየአሥራ፡አምስት፡ሰው፡በማስያዝ፡እነዚያ፡
ጦሮች፡ለኢየሱስ፡ይሰግዱ፡እንደሆነ፡እንዲ
ፈትን፡ጲላጦስን፡ለመኑት።
፲፮፡ አይሁድ ፡ እንደመከሩትም ፡ አደረገ ፤ አያንዳ
ንዱን ፡ ጦር ፡ ጽኑዓን ፡ ለሆኑ ፡ ሮማውያን፡
ሰዎች፡በየአሥራ፡አምስቱ፡አስያዛቸው።

፲፯፡ ጲላጦስም፡ጦሮች፡ወዳሉበት፡ቦታ፡ወጥቶ፡
በወንበር ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፤ ጌታ ፡ ኢየሱስን፡
አወጣው ፤ ጦሮቹንም ፡ በአያቸው ፡ ጊዜ፡
ሦስት፡ጊዜ፡ሰገዱለት።
፲፰፡ የያዙአቸውም ፡ ሰዎች ፡ በኃይል ፡ ይጐት
ቷቸው ፡ ጀመሩ ፤ ግን ፡ መስገዱን ፡ ሊያስተዉ
አቸው፡አልቻሉም።
፲፱፡ ጲላጦስም፡ይህን፡ባየ፡ጊዜ፡ፍርሃትና፡መንቀ
ጥቀጥ ፡ አደረበት ፤ በጭንቅም ፡ ወደ ፡ ዙፋኑ፡
ተመለሰ።
፳፡ ጌታ ፡ ኢየሱስንም ፡ በፊቱ ፡ አቆመው ፤
አይሁድም፡ሁሉ፡በዙሪያው፡ነበሩ።

## ዘዓርብ፡ጽባሕ።

፳፩ ወይቤሎሙ ፡ ጲላጦስ ፡ ለአይሁድ ፡ ምንተ ፡
ትፈቅዱ፡እግበሮ፡ለንጉሥክሙ፡ዝንቱ።
፳፪ ወአውሥኡ፡አይሁድ፡ወይቤልዎ፡አልብነ ፡
ንጉሥ፡ዘእንበለ ፡ ቄሣር ፡ ወዝንቱ ፡ ንጉሥ ፡
ለሊሁ፡ርእሱ።
፳፫ ወይቤሎሙ፡ጲላጦስ፡ምንትኑ፡ግብሩ፡ዘሰማ
ዕክሙ፡ዘትፈትሑ፡ላዕሌሁ፡ፍትሐ፡ሞት።
፳፬ አውሥኡ፡ወይቤልዎ፡እስመ፡ፈወሰ፡ዱያነ፡
ወፈትሐ ፡ አዕይንተ ፡ ዕውራን ፡ በዕለተ ፡
ሰንበት፡ወሠዐረ፡ሕገ።
፳፭ ወዓዲ፡ለምጽ፡አንጽሐ፡በዕለተ፡ሰንበት።
፳፮ ወእምዝ ፡ አምጽኡ ፡ አረጋየ ፡ ዘኀለፈ ፡
መዋዕሊሁ ፡ እንዘ ፡ ይእኀዙ ፡ እዴሁ ፡
እምብዝኃ ፡ ልህቅናሁ ፡ እስመ ፡ ኢይክል ፡
ይሑር፡ባሕቲቶ።
፳፯ ወይቤልዎ፡ለጲላጦስ፡ስማዕ፡ዘይቤ፡ዝኩ፡
አረጋዊ፡ክቡር፡በውስተ፡ሕዝብነ።
፳፰ ወይቤሎ፡ጲላጦስ፡ምንተ፡ትብል፡አረጋዊ፡
ልሒቅ፡በእንተ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ።
፳፱ አውሥአ ፡ ወይቤ ፡ ውእቱ ፡ አረጋዊ ፡ አነ ፡
ርኢክዎ፡ለዝንቱ፡ብእሲ፡ፈወሰ፡መፃጕዐ፡
ዘሠላሳ፡ወሰመንቱ፡ክረምት፡እምዘደወየ፡
ወረሰዮ፡ይሑር፡በዕለተ፡ሰንበት፡እስመ፡
ሰብ፡ሰምዐ፡ቃሎ፡ቀነጸ፡እምላዕለ፡ዓራቱ፡
ከመ፡ኃየል።
፴ ወካዕበ ፡ አምጽኡ ፡ ካልአየ ፡ አረጋየ ፡
ዘይልህቅ፡ሕቀ፡እምቀዳሚ።
፴፩ ወይቤሎ ፡ ጲላጦስ ፡ አ ፡ አንተ ፡ አረጋዊ ፡
በእንተ፡ምንት፡ትከውን፡ስምዐ፡ላዕለ፡ዝ፡
ብእሲ፡እስመ፡ንሴፎ፡ዘከማከ፡አረጋዌ፡ወኢ
ይከውን፡ስምር፡ዘእንበለ፡በጽድቅ።
፴፪ አውሥአ፡ውእቱ፡አረጋዊ፡ወይቤሎ፡እንዘ፡
ይበኪ፡አ፡እግዚእነ፡ይደልዎ፡ሞት፡ለዝ፡
ብእሲ፡እስመ፡ሰዐረ፡ሕገ።
፴፫ ወይቤሎ፡ጲላጦስ፡በእፎ፡ሰዐረ፤አውሥአ፡
አረጋዊ፡ወይቤ፡እንዘ፡ሀሎኩ፡አነ፡በሀገረ፡
ቢታንያ፡ነበረ፡ብእሲ፡ዘስሙ፡አልዓዛር፡
በህየ፡ደወየ፡ወሞተ፡ወአነ፡ገነዝክዎ፡ወቀበ
ርክዎ።
፴፬ ወእምድኅረ ፡ ረቡዕ ፡ መዋዕል ፡ መጽአ ፡
ኢየሱስ፡ኀበ፡መቃብሩ፡በዕለተ፡ሰንበት፡

## የዓርብ፡ነግህ።

፳፩፤ ጲላጦስም፡አይሁድን፡ይህን፡ንጉሣችሁን፡
ምን፡እንዳደርገው፡ትወዳላችሁ፡አላቸው።
፳፪፤ አይሁድም፡ከቄሣር፡በቀር፡ንጉሥ፡የለንም፤
ይህ ፡ ለራሱ ፡ ነው ፡ ንጉሥነቱ ፡ ብለው ፡
መለሱ።
፳፫፤ ጲላጦስም፡የሰማችሁበትና፡ሞት፡የምትፈር
ዱበት፡ሥራው፡ምንድነው?አላቸው።
፳፬፤ እነርሱም ፡ መልሰው ፡ እንዲህ ፡ አሉት ፡
በሰንበት፡በሽተኞችን፡ፈወሰ፤የዕውሮችን፡
ዓይን፡አዳነ፤ይህን፡በማድረጉ፡ሕግን፡ሻረ።
፳፭፤ ደግሞም፡በሰንበት፡ቀን፡ለምጽን፡አነጻ።
፳፮፤ ከዚህም፡በኋላ፡ዘመኑ፡ያለፈበትን፡ሽማግሌ፡
እጁን ፡ ይዘው ፡ ደግፈው ፡ አመጡ ፤
ከእድሜው፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ ብቻውን ፡
ይሄድ፡ዘንድ፡አይችልም፡ነበረና።
፳፯፤ ጲላጦስንም ፡ በወገናችን ፡ ውስጥ ፡ የከበረ ፡
ይህ፡ሽማግሌ፡የሚለውን፡ስማ፡አሉት።
፳፰፤ ጲላጦስም ፡ አንተ ፡ ታላቅ ፡ ሽማግሌ ፤ ስለ ፡
ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ምን፡ትላለህ፡አለው።
፳፱፤ ያም ፡ ሽማግሌ ፡ መልሶ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤
ከታመመ ፡ ሠላሳ ፡ ስምንት ፡ ዓመት ፡
የሆነውን፡በሽተኛ፡በሰንበት፡ቀን፡ሲፈውስ፡
እኔ ፡ አይቼዋለሁ ፤ ቃሉንም ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡
ከአልጋው፡ተነሥቶ፡እንደ፡ዋልያ፡ዘለለ።
፴፤ ደግሞም ፡ ከፊተኛው ፡ እጅግ ፡ ያረጀ ፡
ሽማግሌ፡አመጡ።
፴፩፤ ጲላጦስም ፡ አንተ ፡ ሽማግሌ ፡ በዚህ ፡ ሰው ፡
ላይ፡የምትመሰክረው፡ምንድን፡ነው?እንደ፡
አንተ ፡ ያለ ፡ ሽማግሌ ፡ ለእውነት ፡ ካልሆነ ፡
በቀር ፡ ለሐሰት ፡ ምስክር ፡ እንደማይሆን ፡
ተስፋ፡እናደርጋለንና፡አለው።
፴፪፤ ይህም ፡ ሽማግሌ ፡ እያለቀሰ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡
መለሰ ፤ ጌታዬ ፡ ሆይ ፡ ሕግን ፡ አፍርሷልና ፡
ለዚህ፡ሰው፡ሞት፡ይገባዋል።
፴፫፤ ጲላጦስም፡እንዴት፡አፈረሰ፡አለው፤ሽማግ
ሌውም ፡ መልሶ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤ እኔ ፡
በቢታንያ፡ሳለሁ፡አልዓዛር፡የሚባል፡ሰው፡
ነበረ፤በዚያም፡ታሞ፡ሞተ፤እኔም፡ገንዤ፡
ቀበርሁት።
፴፬፤ ከአራት፡ቀንም፡በኋላ፡በሰንበት፡ኢየሱስ፡
ወደ ፡ መቃብሩ ፡ መጣ፤ በታላቅ ፡ ቃለም ፡

Scanned by CamScanner

## ዘዓርብ፡ጽባሕ።

ወጸውዖ፡በዓቢይ፡ቃል፡ወይቤሎ፡አልዓዛር፡
አልዓዛር፡ተንሥእ፡እሙታን፡ወነዓ፡ኀቤየ።
፴፭ ወወፅአ ፡ ኀቤሁ ፡ አልዓዛር ፡ ሕያው ፡
ወነጸርኩ፡ አነ ፡ በአዕይንትየ ፡ እንዘ ፡
ይትሐወስ፡ዕፄ፡ውስተ፡መቃብረ፡አልዓዛር፤
ወአጼነውኩ ፡ ጼና ፡ ጽዩአ ፡ ዘይወጽእ ፡
እምውስተ፡መቃብር።
፴፮ ወይቤልዎ፡አይሁድ፡ለጲላጦስ፡ምንተኑ፡
ትፈቅድ፡ስምዐ፡ዘይፈደፍድ፡እምዝ።
፴፯ አውሥአ፡ጲላጦስ፡ወይቤሎሙ፡ኦ፡ሕዝበ፡
አይሁድ፡አንሰ፡ኢረከብኩ፡ላዕለ፡ዝ፡ብእሲ፡
ጌጋየ፡ዘእፈትሕ፡ላዕሌሁ፡ፍትሐ፡ሞት፡
ወሰሚዕየ፡ኵሎ፡ነገረ፡ዘአምጻእክሙ፡
እምኀበ፡ሰማዕት፡አንሰ፡እብል፡በእንቲአሁ፡
ከመ፡ውእቱ፡**እምላክ**።
፴፰ ወጸርሑ፡አይሁድ፡ሶቤሃ፡ወይቤሉ፡መኑ፡
ዘይብል፡ኢይደልዎ፡ሞት፡ኢኮንከ፡አርኮ፡
ለቄሣር፡ንጉሥ፡ወባሕቱ፡ጸላዒሁ፡አንተ፡
እስመ፡ሰመየ፡ርእሶ፡ንጉሠ፡ህየንቴሁ።

፴፱ ወበሕጎሙ፡ለነገሥት፡ይደልዎ፡ሞት፡ለዘተ
ሰምየ፡ንጉሠ፡ዘኢኮነት፡ሎቱ፡መንግሥት።
፵ አውሥአ፡ጲላጦስ፡ወይቤሎሙ፡ለክሙ፡
ዘናለምድ፡ወንፈትሕ፡ለክሙ፡ለለኵሉ፡
ዓመት፡አሐደ፡እምእሱራን።
፵፩ ወሀሎ፡ውስተ፡ቤተ፡ሞቅሕ፡ዘስሙ፡በርባን፡
ትፈቅዱኑ፡አሕይዎ፡ለክሙ፡ወሚመ፡
**ለኢየሱስ**፡ዘይብልዎ፡**ክርስቶስ**።
፵፪ ወይቤሉ፡ኵሎሙ፡አሕዩ፡ለነ፡በርባንሃ፡
ወስቅሎ፡**ለኢየሱስ**።
፵፫ ወአንበሩ፡ዕዴሆሙ፡ላዕሌሁ፤ወይቤሉ፡**ደሙ፡
ለኢየሱስ**፡ይኩን፡ላዕሌነ፡ወላዕለ፡ውሉድነ።
ማህሉ፡ወምሕረቱ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡
ዓለም፡አሜን።

አመ፡ትመጽእ፡ለኵንኖ፡በል።

ስብሐት፡ለከ፡**ኢየሱስ**፡በአፈ፡ሰብእ፡ወመላ
እክት።
ስብሐት፡ለከ፡**ኢየሱስ**፡በኵልዔ፡ጽዱላን፡
ከዋክብት።
ስብሐት፡ለከ፡**ኢየሱስ**፡በኵልዔ፡ኵሉ፡
ዓለማት።
ስብሐት፡ለከ፡**ኢየሱስ**፡በኵልዔ፡ዕለታት፡
ወአዝማናት።
ስብሐት፡ይደሉ፡ለመስቀልከ፡ሕይወት።
እስመ፡በመስቀልከ፡ድኅነ፡ኵሉ፡ፍጥረት።

## የዓርብ፡ነግህ።

አልዓዛር፡አልዓዛር፡ከሙታን፡ተነሣ፡ወደ፡
እኔም፡ና፡ብሎ፡ጠራው።
፴፭ አልዓዛርም፡ድኖ፡ወደ፡እርሱ፡ወጣ፤በአል
ዓዛር፡መቃብርም፡ውስጥ፡ትል፡ሲርመ
ሰመስ፡እኔ፡በዐይኖቼ፡ተመለከትኩ፤
የሚከረፋ፡ሽታም፡ከመቃብሩ፡ውስጥ፡
ሲወጣ፡አሸተትኩ።
፴፮ አይሁድም፡ጲላጦስን፡ከዚህ፡የሚበልጥ፡
ምስክርነት፡ምን፡ትሻለህ፡አሉት።
፴፯ ጲላጦስም፡መልሶ፡እንዲህ፡አላቸው፤
የአይሁድ፡ወገኖች፡ሆይ፡በዚህ፡ሰው፡ላይ፡
ሞት፡የሚያስፈርድበትን፡በደል፡አላ
ገኘሁም፤ከአመጣችኋቸው፡ምስክሮች፡
ነገርን፡ሁሉ፡ሰምቼ፡**እምላክ**፡እንደ፡ሆነ፡
ስለ፡እርሱ፡እናገራለሁ፡አላቸው።
፴፰ አይሁድም፡ያን፡ጊዜ፡እንዲህ፡ብለው፡
ጮኹ፤ሞት፡አይገባውም፡የሚል፡ማን፡
ነው፤እንግዲህ፡ለንጉሥ፡ቄሳር፡አንተ፡
ጠላቱ፡እንጂ፡ወዳጁ፡አይደለህም፤በቄሳር፡
ፈንታ፡ንጉሥ፡ነኝ፡ብሏልና።
፴፱ መንግሥት፡የሱ፡ያልሆነች፡ንጉሥ፡ነኝ፡ለሚል፡
በነገሥታት፡ሕግ፡ሞት፡ይገባዋልና፡አሉ።
፵ ጲላጦስም፡መልሶ፡ከእስረኞች፡አንዳንድ፡
ልንፈታላችሁ፡በየዓመቱ፡ለእናንተ፡ያስለ
መድነው፡ልማድ፡አለ፡አላቸው።
፵፩ በወህኒ፡ቤት፡ስሙ፡በርባን፡የተባለ፡አንድ፡
እስረኛ፡አለ፤እርሱን፡ላድንላችሁ፡ትወዳላችሁን፡
ወይስ፡**ክርስቶስ**፡የተባለ፡**ኢየሱስን**፡አላቸው።
፵፪ ሁሉም፡በርባንን፡አድንልን፤**ኢየሱስን**፡ግን፡
ስቀለው፡አሉ።
፵፫ እጃቸውንም፡በላዩ፡ጭነው፡**የኢየሱስ**፡ደሙ፡
በእኛ፡ላይና፡በልጆቻችን፡ላይ፡ይሁን፡አሉ።
ይቅርታውና፡ቸርነቱ፡ከእኛ፡ጋራ፡
ለዘላለሙ፡ይሁን፡አሜን።

አመ፡ትመጽእ፡ለኰንኖ፡በል።

**ኢየሱስ፡ሆይ**፡በሰውና፡በመላእክት፡አፍ፡
ምሥጋና፡ላንተ፡ይገባል።
**ኢየሱስ፡ሆይ**፡በብሩሃን፡ከዋክብት፡ቍጥር፡
ምሥጋና፡ላንተ፡ይገባል።
**ኢየሱስ፡ሆይ**፡በዓለማት፡ሁሉ፡ቍጥር፡
ምሥጋና፡ላንተ፡ይገባል።
**ኢየሱስ፡ሆይ**፡በዕለታትና፡በዘመናት፡
ቍጥር፡ምሥጋና፡ላንተ፡ይገባል።
ሕይወት፡ለሆነው፡መስቀልህ፡ምሥጋና፡
ይገባል።
ፍጥረት፡ሁሉ፡በመስቀልህ፡ድኗልና።

Scanned by CamScanner

## ዘዓርብ፡ጽባሕ።

### ክፍል፡፫።

ይ፡ዲ፡ቅድመ፡ወንጌል

መዝ፡፳፮፡፲፪።

እስመ፡ቆሙ፡ላዕሌየ፡ሰማዕተ፡ዐመፃ፡ወሐሰት፡
ሐሰ፡ዐመፃ።

ወቦ፡እለ፡ይቤሉ።

መዝ፡፴፬፡፲፩-፲፪።

ተንሥኡ፡ላዕሌየ፡ሰማዕተ፡ዐመፃ፡ወዘኢየ
እምር፡ነበቡ፡ላዕሌየ። ፈደዩኒ፡እኪተ፡ህየንተ፡
ሠናይት።

ወንጌል፡ዘማቴዎስ።

ምዕ፡፳፯፡፩-፲፩።

ወጸቢሖ፡ተማከሩ፡ኵሎሙ፡ሊቃነ፡ካህናት፡
ወሊቃናተ፡ሕዝብ፡ከመ፡ይቅትልዎ፡ለእግዚእ፡
ኢየሱስ።

ወአሰርዎ፡ወሰድዎ፡ወመጠውዎ፡ለጲላጦስ፡
ጰንጤናዊ፡መልአከ፡አሕዛብ።

ወእምዝ፡ሶበ፡ርእየ፡ይሁዳ፡ዘአግብኦ፡ከመ፡
አርስሕዎ፡ነስሐ፡ወአግብአ፡ውእተ፡ሠላሳ፡
ብሩረ፡ለሊቃነ፡ካህናት፡ወለሊቃውንተ፡ሕዝብ፡
እንዘ፡ይብል፡አበስኩ፡ዘአግባእኩ፡ደመ፡ንጹሐ፡
ወዘአቅተልኩ፡ብእሴ፡ጻድቀ።

ወይቤልዎ፡ሚ፡ላዕሌነ፡ወሚ፡ላዕሌከ፡ለሊከ፡
አንተ፡አእምር።

## የዐርብ፡ነግህ።

### ክፍል፡፫።

ዲያቆኑ፡ከወንጌል፡በፊት።

መዝ፡፳፮፡፲፪።

የሐሰት፡ምስክሮች፡በጠላትነት፡ተነሥተውብ
ኛልና። ሐሰትም፡የዓመፃ፡አበጋዝ፡ናት፤ይበል።

እንዲህም፡የሚሉ፡አሉ።

መዝ፡፴፬፡፲፩-፲፪።

የሐሰት፡ምስክሮች፡በጠላትነት፡ተነሡብኝ።
በእኔ፡ላይም፡የማላውቀውን፡ነገር፡ተናገሩብኝ።
በጎ፡ስለአደረግሁላቸው፡ፈንታ፡ክፉ፡ብድራት፡
መለሱልኝ፡ይበል።

የማቴዎስ፡ወንጌል።

ምዕ፡፳፯፡፩-፲፩።

፩፤ ሲነጋም፡የካህናት፡አለቆች፡የሕዝቡ፡ሽማግ
ሌዎች፡ሁሉ፡ጌታ፡ኢየሱስን፡ሊገድሉት፡
ተማከሩ።

፪፤ አስረው፡ወስደውም፡ለአሕዛብ፡ሹም፡ለጴን
ጤናዊ፡ለጲላጦስ፡ሰጡት።

፫፤ ከዚህ፡በኋላ፡ያስያዘው፡ይሁዳ፡እንዳንገላቱት፡
ባየ፡ጊዜ፡ንጹሕ፡ደም፡ያስፈሰስኩ፡ጻድቅ፡ሰውን፡
ያስገደልኩ፡እኔ፡በድያለሁ፡ብሎ፡ተጸጽቶ፡
ለካህናት፡አለቆችና፡ለሕዝቡ፡ሽማግሎች፡ያን፡
የተቀበለውን፡ሠላሳ፡ብር፡መለሰ።

፬፤ እነርሱም፡እኛ፡ምን፡አግዶን፡አንተ፡ከኛ፡እኛ፡
ከአንተ፡ምን፡አለን?ለራስህ፡ዕወቅ፡አሉት።

...ሙ ነስሐ ይሁዳ ወዘረወ ...ሩረ።



ይሁዳ ተጸጽቶ ብሩን እንደበተነ።

ወገደፈ፡ውእቶ፡ብሩረ፡ውስተ፡ምኵራብ፡
ወሖረ፡ወተሐንቀ፡ወሞተ።
ወነሥኡ፡ሊቃነ፡ካህናት፡ውእተ፡ብሩረ፡
ወይቤሉ፡ኢይከውን፡ንደዮ፡ውስተ፡ቀርባን፤
እስመ፡ሤጠ፡ደም፡ውእቱ።
ወተማከሩ፡ተሣየጡ፡ቦቱ፡ምድረ፡ለብሐዊ፡
ለመቃብረ፡እንግዳ።
ወተሰምየ፡ውእቱ፡ገራህት፡ገራህተ፡ደም፡እስከ፡
ዮም።

፭፤ ያንን፡ብር፡በምኩራብ፡ውስጥ፡በትኖ፡ሂዶ፡
ታንቆ፡ሞተ።

፮፤ የካህናት፡አለቆችም፡ያንን፡ብር፡አንሥተው፡
የደም፡ዋጋ፡ነውና፡ከመባው፡ገንዘብ፡ውስጥ፡
ልንጨምረው፡አይገባንም፡አሉ።

፯፤ ተማክረውም፡ለእንግዳ፡መቃብር፡ሊሆን፡
የሸክላ፡ሠሪ፡እርሻን፡ገዙበት።

፰፤ ያም፡ምድር፡እስከ፡ዛሬ፡የደም፡ምድር፡ተብሎ፡
ተጠራ።

Scanned by CamScanner

## ዘዓርብ፡ጽባሕ።

፱፡ ወይእተ፡ አሚረ፡ በጽሐ፡ ቃል፡ ኤርምያስ፡
ነቢይ፡ዘይቤ፡ወነሥኡ፡ሠላሳ፡ብሩረ፡ሤጠ፡
ለክቡር፡ዘአክበሩ፡እምደቂቀ፡እስራኤል።

፲፡ ወወሀብዎ፡ ለገራህተ፡ ለብሐዊ፡ በከመ፡
አዘዘኒ፡እግዚአብሔር።
፲፩፡ ወቆመ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ቅድሜሁ፡ለመልአከ፡
አሕዛብ፡ ወተስእሎ፡ መልአከ፡ አሕዛብ፡
ወይቤሎ፡ አንተሁ፡ ንጉሦሙ፡ ለአይሁድ፡
ወይቤ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡አንተ፡ትቤ።
፲፪፡ ወእንዘ፡ያስተዋድይዎ፡ሊቃነ፡ካህናት፡ወሊ
ቃውንተ፡ሕዝብ፡አልቦ፡ዘያወሥአሙ፡ወኢ
ምንተኒ።
፲፫፡ ወእምዝ፡ ይቤሎ፡ ጲላጦስ፡ ኢትሰምዖኑ፡
መጠነ፡ያስተዋድዩከ።
፲፬፡ ወኢያውሥአ፡ ወኢአሐተ፡ ቃለ፡ እስከ፡
ያነክር፡ጥቀ።

ወእምዝ፡ ይበሉ፡ ካህን፡ ወዲያቆን፡
ወሕዝብ።

ወጸቢሖ፡ ተማከሩ፡ ሊቃነ፡ ካህ
ናት፡ ይስቅልዎ፡ ለኢየሱስ፡ በቀራንዮ፡
መካን።

ይካ፡ ቅዱስ፡እግዚአብሔር፡ ቅዱስ፡ኃያል፡
ቅዱስ፡ሕያው፡ዘኢይመውት።

### ወንጌል፡ዘማርቆስ።

ምዕ፡፲፭፡፩-፭።
፩፡ ወሶበ፡ ጸብሐ፡ ተማከሩ፡ ሊቃነ፡ ካህናት፡
ወረበናት፡ ወጸሐፍት፡ ወኵሉ፡ ዐውድ፡
ወሐመይዎ፡ለእግዚእ፡ኢየሱስ፡ወወሰድዎ፡
ወመጠውዎ፡ለጲላጦስ።
፪፡ ወተስእሎ፡ ጲላጦስ፡ ወይቤሎ፡ አንተኑ፡
ንጉሦሙ፡ለአይሁድ፡ወአውሥአ፡እግዚእ፡
ኢየሱስ፡ወይቤሎ፡አንተ፡ትቤ።
፫፡ ወአስተዋደይዎ፡ ሊቃነ፡ ካህናት፡ ብዙኀ፡
ወውእቱሰ፡አልቦ፡ዘአውሥአ።
፬፡ ወሐተቶ፡ካዕበ፡ጲላጦስ፡ወይቤሎ፡አልቦኑ፡
ዘትሰጠው፡እንዘ፡መጠነዝ፡ያስተዋድዩከ።
፭፡ ወኢተሰጥዎ፡ እግዚእ፡ ኢየሱስ፡ ወኢምንተኒ፡ወአንከሮ፡ጲላጦስ።

ወእምዝ፡ይበሉ፡ካህን፡ወዲያቆን፡ወሕዝብ፡
ከመ፡ቀዳሚ።

ወጸቢሖ፡ ተማከሩ፡ ሊቃነ፡ ካህናት፡
አውጽእዎ፡ አፍአ፡ ለኢየሱስ፡ ውስተ፡
ዓውደ፡ምኵናን።

ይካ፡ ቅዱስ፡እግዚአብሔር፡ ቅዱስ፡ኃያል፡
ቅዱስ፡ሕያው፡ዘኢይመውት፡ይበል።

## የዐርብ፡ነግህ።

፱፡ ያን፡ ጊዜም፡ የነቢዩ፡ የኤርምያስ፡ ቃል፡
ተፈጸመ፤ እንዲህ፡ ያለው፤ የእስራኤል፡
ልጆች፡ የተስማሙበትን፡ የክቡርን፡ ዋጋ፡
ሠላሳውን፡ብር፡ወሰዱ።
፲፡ እግዚአብሔርም፡ እንዳዘዘኝ፡ ለሸክላ፡ ሠሪ፡
እርሻ፡ሰጡት።
፲፩፡ ጌታ፡ ኢየሱስም፡ በአሕዛብ፡ አለቃ፡ ፊት፡
ቆመ፤የአሕዛብም፡አለቃ፡የአይሁድ፡ንጉሥ፡
አንተ፡ ነህን? ብሎ፡ ጠየቀው፤ ጌታ፡
ኢየሱስም፡ አንተ፡አልህ፡አለው።
፲፪፡ የካህናት፡ አለቆች፡ የሕዝቡም፡ ሹማ
ምንት፡ ሲያሳጡት፡ ምንም፡ የሰጠው፡
መልስ፡የለም።
፲፫፡ ከዚህ፡ በኋላ፡ ጲላጦስ፡ ይህን፡ ያህል፡
ሲያጣሉህ፡አትሰማምን፡አለው።
፲፬፡ መስፍኑ፡ እስኪያደንቅ፡ ድረስ፡ አንዲት፡
ቃል፡ስንኳ፡አልመለሰለትም።

ከዚህ፡ በኋላ፡ ካህኑ፡ ይምራ፤ ዲያቆኑም፡
ይመራ፤ሕዝቡ፡ይቀበሉ።

በነጋም፡ ጊዜ፡ የካህናት፡ አለቆች፡ ጌታችን፡
ኢየሱስን፡ ቀራንዮ፡ በሚባል፡ ቦታ፡
ይሰቅሉት፡ዘንድ፡ተማከሩ።

ካህኑ፡ ቅዱስ፡እግዚአብሔር፡ ቅዱስ፡ኃያል፡
ቅዱስ፡ሕያው፡ዘኢይመውት፡ይበል።

### የማርቆስ፡ወንጌል።

ምዕ፡፲፭፡፩-፭።
፩፡ በነጋ፡ ጊዜም፡ የካህናት፡ አለቆች፡ ሽማግ
ሎችና፡ የሕዝብ፡ ጸሮች፡ ሸንጎውም፡ ሁሉ፡
ተማከሩና፡ ጌታችን፡ ኢየሱስን፡ አስረው፡
ወስደው፡ለጲላጦስ፡ሰጡት።
፪፡ ጲላጦስም፡ የአይሁድ፡ ንጉሥ፡ አንተ፡ ነህን?
ብሎ፡ ጠየቀው፤ ጌታ፡ ኢየሱስም፡ መልሶ፡
አንተ፡ትላለህ፡አለው።
፫፡ የካህናት፡ አለቆችም፡ ብዙ፡ አሳጡት፤እርሱ፡
ግን፡የመለሰው፡ነገር፡የለም።
፬፡ ጲላጦስም፡ ይህን፡ ያህል፡ ሲያሳጡህ፡አንዳች፡
አትመልስምን? ብሎ፡እንደገና፡ጠየቀው።
፭፡ ጌታችን፡ ኢየሱስም፡ ጲላጦስ፡ እስኪያደ
ንቀው፡ድረስ፡ምንም፡ምን፡አልመለሰለትም።

ከዚህ፡ በኋላ፡ ካህኑና፡ ዲያቆኑ፡ ሕዝቡም፡ እን
ዳለፈው፡ይበሉ።

በነጋም፡ ጊዜ፡ የካህናት፡ አለቆች፡ ጌታ፡
ኢየሱስን፡ ከአደባባዩ፡ ወደ፡ ውጭ፡
አወጡት፤ይሰቅሉትም፡ዘንድ፡ተማከሩ።

ካህኑ፡ ቅዱስ፡እግዚአብሔር፡ ቅዱስ፡ኃያል፡
ቅዱስ፡ሕያው፡ዘኢይመውት፡ይበል።

Scanned by CamScanner

ዘዓርብ፡ጽባሕ።

ወንጌል፡ዘሉቃስ።

ምዕ፡፳፪፡፷፮–፸፩።

ወጸቢሖ ፡ ተጋብኡ ፡ ሊቃነ ፡ ካህናት ፡
መጻሕፍት፡ወሊቃናተ፡ሕዝብ፡ወወሰድዎ፡
ውስተ፡ዐውዶሙ።
ወይቤልዎ ፡ እመ ፡ አንተሁ ፡ ክርስቶስ ፡
ንግረነ፡ገሀደ ። ወይቤሎሙ ፡ እመኒ ፡ አይዳዕ
ኩክሙ፡ኢተአምኑኒ።
ወእመኒ ፡ ተስእልኩክሙ ፡ ኢትነግሩኒ ፡
ወኢ፡ተኀድጉኒ።
ወባሕቱ፡እምይእዜሰ፡ይነብር፡ወልደ፡ዕጓለ፡
እመሕያው፡በየማነ፡ኃይለ፡እግዚአብሔር።

ወይቤልዎ፡ኵሎሙ፡አንተኑ፡እንከ፡ውእቱ፡
ወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወይቤሎሙ ፡
አንትሙ፡ትብሉ፡ከመ፡አነ፡ውእቱ፡ወልደ፡
እግዚአብሔር።
ወይቤሉ ፡ ምንተ ፡ እንከ ፡ ንፈቅድ ፡
ሰማዕተ ፡ በእንቲአሁ ፡ ለሊነ ፡ ሰማዕነ ፡
እምአፉሁ።

ምዕ፡፳፫፡፩–፲፪።

ወተንሥኡ ፡ ኵሎሙ ፡ በምልአሙ ፡
ወወሰድዎ፡ኀበ፡ጲላጦስ።
ወአኀዙ ፡ ያስተዋድይዎ ፡ ወይቤሉ ፡
ረከብናሁ፡ ለዝንቱ ፡ እንዘ ፡ ያዐልዎሙ ፡
ለሕዝብነ፡ወይከልአሙ፡ኢየሀቡ፡ጸባሕተ፡
ለቄሣር፡ወይሬሲ፡ርእሶ፡ክርስቶስሃ፡ንጉሠ፡
እስራኤል።
ወሐተቶ፡ጲላጦስ፡ወተስእሎ፡ወይቤሎ፡
አንተኑ፡ንጉሦሙ፡ለአይሁድ።
ወአውሥአ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ወይቤሎ፡
አንተ፡ትብል፡ከመ፡አነ፡ውእቱ።
ወይቤሎሙ፡ጲላጦስ፡ለሊቃነ፡ካህናት፡
ወለሕዝብ፡አልቦ፡ዘረከብኩ፡አበሳ፡ላእለ፡
ዝንቱ፡ብእሲ።
ወዐውየዉ፡ወይቤሉ፡የሀውኮሙ፡ለሕዝብ፡
ወይሜህር፡በኵሉ፡ይሁዳ፡እኂዞ፡እምገሊላ፡
እስከ፡ዝየ።
ወሰሚዖ፡ጲላጦስ፡ተስእለ፡ገሊላውያኑ፡
ሁሎሙ፡ገሊላዊ፡ብእሲ፡ሁ።
ወአእሚሮ፡ከመ፡እምኵናኑ፡ሄሮድስ፡
ውእቱ፡ፈነዎ፡ኀበ፡ሄሮድስ፡እስመ፡ሀሎ፡
ውእቱ፡በኢየሩሳሌም፡በውእቱ፡መዋዕል።

የዐርብ፡ነግህ።

የሉቃስ፡ወንጌል።

ምዕ፡፳፪፡፷፮–፸፩።

፷፮፡ በነጋም፡ጊዜ፡የካህናቱ፡አለቆች፡ጻፎችና፡
የሕዝቡ፡ሽማግሎች፡ተሰብስበው፡ወደ፡አደ
ባባያቸው፡ወሰዱት።
፷፯፡ አንተ፡ክርስቶስ፡እንደሆንክ፡እባክህ፡
ገልጠህ፡ንገረን፡አሉት፤እርሱም፡እንዲህ፡
አላቸው፤ብነግራችሁም፡አታምኑኝም።
፷፰፡ ብጠይቃችሁ፡አትመልሱልኝም፤ወይም፡
አትተውኝም።
፷፱፡ ነገር፡ግን፡ከእንግዲህ፡ወዲህ፡የሰው፡ልጅ፡
ክርስቶስ፡በእግዚአብሔር፡ኃይል፡(ቀኝ)፤
ይቀመጣል።
፸፡ ሁሉም፡እንግዲያማ፡አንተ፡የእግዚአ
ብሔር፡ልጅ፡ነኽ፡አሉትና፡እኔ፡የእግዚአ
ብሔር፡ልጅ፡እንደሆንኩ፡እናንተ፡
ትላላችሁ፡አላቸው።
፸፩፡ እነርሱም፡እንግዲህ፡ስለ፡እርሱ፡ምን፡
ምስክር፡ያሻናል፤እኛ፡ራሳችን፡ከአፉ፡
ሰምተናል፡አሉ።

ምዕ፡፳፫፡፩–፲፪።

፩፡ ሁሉም፡በሙሉ፡ተነሥተው፡ወደ፡ጲላጦስ፡
ወሰዱት።
፪፡ ይህ፡ሰው፡ሕዝባችንን፡ሲያሳድም፡
ለቄሳር፡ግብር፡እንዳይሰጡ፡ሲከለክል፡
አግኝተነዋል፤ራሱንም፡የእስራኤል፡ንጉሥ፡
ክርስቶስን፡ያደርጋል፡እያሉ፡ያሳጡት፡
ጀመር።
፫፡ ጲላጦስም፡አንተ፡የአይሁድ፡ንጉሥ፡ነህን፡
ብሎ፡ጠየቀው፤መረመረው።
ጌታ፡ኢየሱስም፡እኔ፡እንደሆንኩ፡አንተ፡
ትላለህ፡አለው።
፬፡ ጲላጦስም፡ለካህናት፡አለቆችና፡ለሕዝቡ፡
በዚህ፡ሰው፡ላይ፡ያገኘሁት፡በደል፡የለም፡
አላቸው።
፭፡ ሕዝቡን፡ያውካል፤ከገሊላ፡ጀምሮ፡
እስከዚህ፡ድረስ፡በመላው፡ይሁዳ፡ያስተ
ምራል፡እያሉ፡ተንጫጩ።
፮፡ ጲላጦስም፡ገሊላ፡ሲሉ፡ሰምቶ፡ሰውዬው፡
ገሊላዊ፡እንደሆነ፡ብሎ፡ገሊላውያንን፡ጠየቀ።
፯፡ ከሄሮድስ፡ግዛት፡ውስጥ፡መሆኑንም፡አውቆ፡
ወደ፡ሄሮድስ፡ላከው፤ሄሮድስ፡በዚያ፡ወራት፡
በኢየሩሳሌም፡ነበረና።

Scanned by CamScanner

## ዘዓርብ፡ጽባሕ።

፰፡ ወሶበ፡ርእዮ፡ኄሮድስ፡ለእግዚእ፡ኢየሱስ፡
ተፈሥሐ ፡ ፈድፋደ ፡ እስመ ፡ ይፈቅድ ፡
ይርአዮ፡ እምጕንዱይ ፡ ዕለት ፡ እስመ ፡
ይሰምዕ፡ነገሮ፡ወይሴፎ፡ይርአይ፡ተአምረ፡
በኀቤሁ፡ዘይገብር።
፱፡ ወሐተቶ፡በብዙኅ፡ነገር፡አልቦ፡ዘተሰጥዎ፡
ምንተኒ፤
፲፡ ወይቀውሙ፡ሊቃነ፡ካህናት፡ወጸሐፍት፡
ወብዙኀ፡ያስተዋድይዎ።
፲፩፡ ወአስተአከዮ ፡ ኄሮድስ ፡ ወወዓልያኒሁ ፡
ወተሣለቁ፡ላዕሌሁ፡ወአልበስዎ፡ልብሰ፡
ቀይሐ፡ወፈነውዎ፡ኀበ፡ጲላጦስ።
፲፪፡ ወውእተ ፡ አሚረ ፡ ተኳነኑ ፡ ኄሮድስ ፡
ወጲላጦስ፡እስመ፡ጋዕዝ፡ቦሙ፡እምቅድም።
ወእምዝ፡ይበሉ፡ካህን፡ወዲያቆን፡ወሕዝብ፡
ከመ፡ቀዳሚ።
ወጸቢሖ፡ተማከሩ፡ሊቃነ፡ካህናት፡ሐመይዎ፡
ለኢየሱስ፡ወመጠውዎ፡ለጲላጦስ።

ይካ፡ቅዱስ፡እግዚአብሔር፡ቅዱስ፡ኃያል፡
ቅዱስ፡ሕያው፡ዘኢይመውት።

### ወንጌል፡ዘዮሐንስ።

ምዕ፲፰፡፳፰–፴።

፳፰፡ ወወሰድዎ፡ለእግዚእ፡ኢየሱስ፡እምኀበ፡
ቀያፋ፡ኀበ፡ዐውድ፡ወኢቦኡ፡አይሁድ፡
ውስተ፡ዐውደ፡ምኵናን፡እስመ፡ወድዐ፡
ጸብሐ፡ከመ፡ኢይርኰሱ፡እምቅድመ፡
ይብልዑ፡ፍሥሓ።
፳፱፡ ወወጽአ ፡ ጲላጦስ ፡ አፍአ ፡ ኀቤሆሙ ፡
ወይቤሎሙ፡ምንትኑ፡ጌጋዩ፡ለዝ፡ብእሲ፡
በዘአምጻእክምዎ፡ኀቢየ።
፴፡ ወአውሥኡ፡ወይቤልዎ፡ሶበሰ፡ኢኮነ፡
ገባሬ፡እኪት፡እምኢያግባእናሁ፡ኀቤከ።
፴፩፡ ወይቤሎሙ፡ጲላጦስ፡ንሥኡ፡አንትሙ፡
በከመ፡ሕግክሙ፡ኰንንዎ፤ወይቤልዎ፡
አይሁድ፡ለነሰ፡ኢይከውነነ፡ንቅትል፡
ወኢመነሂ።
፴፪፡ ከመ፡ይብጻሕ፡ቃሉ፡ለእግዚእ፡ኢየሱስ፡
ዘይቤ፡እንዘ፡ይኤምሮሙ፡በአይ፡ሞት፡
ሀለዎ፡ይሙት።
፴፫፡ ወቦአ፡ካዕበ፡ጲላጦስ፡ውስተ፡ዐውድ፡
ወጸውዖ፡ለእግዚእ፡ኢየሱስ፡ወይቤሎ፡
አንተኑ፡ንጉሦሙ፡ለአይሁድ።
፴፬፡ ወአውሥአ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ወይቤሎ፡ዘእ

## የዐርብ፡ነግህ።

፰፡ ሄሮድስም፡ጌታችን፡ኢየሱስን፡በአየው፡
ጊዜ፡እጅግ፡ደስ፡አለው፤ዜናውን፡
ስለሚሰማ፡ከረጅም፡ጊዜ፡ጀምሮ፡ሊያየው፡
ይወድ፡ነበርና፤የሚያደርገውንም፡ተአምር፡
ሊያይ፡ይመኝ፡ነበርና።
፱፡ በብዙ፡ነገርም፡መረመረው፤እሱ፡ግን፡
አንዲት፡ቃል፡አልመለሰለትም።
፲፡ የካህናት፡አለቆችና፡ጸሐፎችም፡ቆመው፡
በብዙ፡ያሳጡት፡ነበር።
፲፩፡ ሄድሮስም፡አክፋፋው፤ጭፍሮቹም፡ቀይ፡
ግምጃ፡አልብሰው፡ተዘባበቱበት፤ወደ፡
ጲላጦስም፡ሰደደው።
፲፪፡ በዚያም፡ወራት፡ሄሮድስና፡ጲላጦስ፡
ተስማሙ፤ከጥንት፡ጀምሮ፡ፀብ፡ነበራቸውና።
ከዚህ፡በኋላ፡ካህኑና፡ዲያቆኑ፡ሕዝቡም፡እን
ዳለፈው፡ይበሉ።
በነጋም፡ጊዜ፡የካህናት፡አለቆች፡ኢየሱስን፡
አስረው፡ለጲላጦስ፡ይሰጡት፡ዘንድ፡
ተማከሩ።
ካህኑ፡ቅዱስ፡እግዚአብሔር፡ቅዱስ፡ኃያል፡
ቅዱስ፡ሕያው፡ዘኢይመውት፡ይበል።

### የዮሐንስ፡ወንጌል።

ምዕ፲፰፡፳፰–፴።

፳፰፡ ጌታችን፡ኢየሱስን፡ከቀያፋ፡ወደ፡አደባባይ፡
ወሰዱት፤ጊዜውም፡ማለዳ፡ነበር፤አይሁድ፡
ግን፡ፈጽሞ፡ስለ፡ነጋ፡ወደ፡ፍርድ፡
አደባባይ፡አልገቡም፤ፋሲካውን፡ከመብላ
ታቸው፡በፊት፡እንዳይረክሱ።
፳፱፡ ጲላጦስም፡እነርሱ፡ወዳሉበት፡ወደ፡ውጭ፡
ወጥቶ፡ይህን፡ሰው፡ወደ፡እኔ፡ያመጣች
ሁበት፡በደሉ፡ምንድነው?አላቸው።
፴፡ ክፉ፡አድራጊ፡ባይሆንስ፡ወዳንተ፡ባላመጣ
ነውም፡ነበር፡ብለው፡መለሱለት።
፴፩፡ ጲላጦስም፡እናንተ፡ወስዳችሁ፡እንደ፡
ሕጋችሁ፡ፍረዱበት፡አላቸው፤አይሁድም፡
እኛስ፡ማንንም፡ማንን፡ልንገድል፡አይገ
ባንም፡አሉት።
፴፪፡ በምን፡ሞት፡ይሞት፡ዘንድ፡እንዳለው፡ሲያ
መለክት፡የተናገረው፡የጌታችን፡የኢየሱስ፡
ቃል፡ይደርስ፡ይፈጸም፡ዘንድ።
፴፫፡ ጲላጦስም፡እንደገና፡ወደ፡አደባባይ፡ገብቶ፡
ጌታ፡ኢየሱስን፡ጠርቶ፡የአይሁድ፡ንጉሥ፡
አንተ፡ነህን?አለው።
፴፬፡ ጌታ፡ኢየሱስም፡ይህን፡የምትለው፡ከልብህ፡

Scanned by CamScanner

## ዘዓርብ፡ጽባሕ።

ምልብከኑ : ትብል : ዘንተ : ወሚመ : በኑ :
ዘነገሩከ፡በእንቲአየ።
፴፭ ወአውሥአ : ጲላጦስ : ወይቤሎ : አነሂ : አይ
ሁዳዊኑ : አነ : አኮኑ : ሕዝብከ : ወሊቃነ :
ካህናት : አግብኡከ : ኀቤየ : ምንተኑ :
አግበርከ።
፴፮ ወአውሥአ : እግዚእ : ኢየሱስ : ወይቤሎ :
መንግሥትየሰ፡ኢኮነት : እምዝንቱ : ዓለም :
ሶበሰ፡ኮነት፡በዝንቱ : ዓለም : መንግሥትየ :
እምተበአሱ : ሊተ : ወዓልያንየ : ከመ :
ኢይግባእ : ለአይሁድ : ወይእዜሰ : ባሕቱ :
ኢኮነት፡እምዝየ፡መንግሥትየ።
፴፯ ወይቤሎ : ጲላጦስ : አንተሰኬ : ንጉሥ :
አንተ፤ ወአውሥአ : እግዚእ : ኢየሱስ :
ወይቤሎ፡ለሊከ : ትቤ : ከመ : ንጉሥ : አነ :
ወአነሰ፡በእንተ : ዝንቱ : ተወለድኩ : ወእን
በይነ፡ዝንቱ፡መጻእኩ፡ውስተ፡ዓለም፡ከመ፡
እኩን : ሰማዕተ : በጽድቅ : ወኵሉ : ዘእም
ጽድቅ፡ውእቱ፡ይሰምዐኒ፡ቃልየ።
፴፰ ወይቤሎ : ጲላጦስ : ምንትኑ : ውእቱ :
ጽድቅ፤ ወዘንተ : ብሂሎ : ወጽአ : ካዕበ :
ኀበ : አይሁድ፡ ወይቤሎሙ : አንሰ :
አልቦ : ዘረከብኩ : ላዕሌሁ : ጌጋየ :
ወኢአሐተኒ።
፴፱ ወባሕቱ፡ቦ : ልማድ : ዘናለምድ : አሕዩ :
ለክሙ፡ለለፋሲካ፡አሐደ፡እምነ፡ሙቁሓን፡
ትፈቅዱኑ፡እንከ፡አሕይዎ፡ለክሙ፡ለንጉሠ፡
አይሁድ።

፵ ወከልሑ : ካዕበ : ኵሎሙ : ወይቤሉ : አኮ :
ዘንተ : አላ : በርባንሃ : ወበርባንሰ : ሊቀ :
ፈያት፡ውእቱ።
ወእምዝ፡ይበሉ፡ካህን፡ወዲያቆን፡ወሕዝብ፡
ከመ፡ቀዳሚ።
ወጸቢሐ : ተማከሩ : ሊቃነ : ካህናት :
አውጽእዎ : አፍአ : ለኢየሱስ : ወነበረ :
ዐውደ፡ሶቤሃ።
ይካ፡ቅዱስ፡እግዚአብሔር፡ቅዱስ፡ኃያል፡
ቅዱስ፡ሕያው፡ዘኢይመውት።
ድግረ : ወንጌል : ነግህ : በዕለተ : ዓርብ :
እምግብረ፡ሕማማት፡ቅድስት፡ዘይትነበብ።
፩ ተጋብኡ : ሊቃነ : ካህናት : ውስተ : መካን :
መግብሩ፡ፍትሐ : በእንተ : መድኃኒነ : ከመ :
፪ ያግብእዎ፡ኀበ፡ጲላጦስ፡ከመ፡ይስቅሎ።
ወይሁዳሰ : ሶበ : ርእየ : ዘኮነ : ነስሐ : ላዕለ :

## የዐርብ፡ነግህ።

ነውን?ወይስ፡ስለኔ፡የነገረህ፡ሌላ፡አለ?ብሎ፡
መለሰለት።
፴፭፤ ጲላጦስም : መልሶ : እኔ : አይሁዳዊ : ነኝን?
ወገኖችህና : የካህናት : አለቆች : ለእኔ :
አሳልፈው : ሰጥተውህ : የለምን ? ምን :
ላድርግህ፡አለው።
፴፮፤ ጌታ : ኢየሱስም : የእኔ : መንግሥት : ከዚህ :
ዓለም : አይደለችም ፤ መንግሥቴስ : በዚህ :
ዓለም : ብትሆን : ኖሮ : ለአይሁድ : እንዳ
ልሰጥ፡አሽከሮቼ፡በተዋጉልኝ፡ነበር፤አሁን፡
ግን፡መንግሥቴ፡ከዚህ፡አይደለችም፡ብሎ፡
መለሰለት።
፴፯፤ ጲላጦስም : እንግዲያማ : አንተ : ንጉሥ :
ነኻ ! አለው ፤ ጌታ : ኢየሱስም : መልሶ :
እኔ፡ንጉሥ፡እንደ፡ሆንኩ፡አንተ፡ትላለህ፤
እኔ : ስለዚህ : ተወልጃለሁ ፤ ስለዚህ :
በእውነት : ልመሰክር : ወደ : ዓለም :
መጥቻለሁ፤ከእውነት፡የሆነ፡ሁሉ፡ቃሌን፡
ይሰማኛል፡አለው።
፴፰፤ ጲላጦስም : ዕውነት : ምንድነው ? አለው ፤
ይህንን : ተናግሮ : ዳግመኛ : አይሁድ :
ወዳሉበት : ወጣና : እኔ : በዚህ : ሰው : ላይ :
ምንም : በደል : አላገኘሁም ፤ አንዲት :
ስንኳን፡አላቸው።
፴፱፤ ነገር : ግን : ያስለመድነው : ልማድ : አለ ፤
እሱም : በየዓመቱ : በፋሲካ : ከእስረኞች :
አንዳንድ : የምንፈታላችሁ : እስረኛ : አለ ፤
እንግዲህ : የአይሁድን : ንጉሥ : ልፈታ
ላችሁ፡ትወዳላችሁን?
፵፤ ዳግመኛም : ሁሉም : ጮኹ ፤ የምትፈታው :
በርባንን : ነው : እንጂ : ይኸን : አይደለም :
አሉ፤በርባን፡ግን፡የሽፍቶች፡አለቃ፡ነበር
ከዚህ፡በኋላ፡ካህኑና፡ዲያቆኑ፡ሕዝቡም፡እን
ዳለፈው፡ይበሉ።
በነጋም፡ጊዜ፡የካህናት፡አለቆች፡ተማክረው፡
ጌታ፡ኢየሱስን፡ወደ፡ውጭ፡አወጡት፤ያን፡
ጊዜም፡በአደባባዩ፡ተቀመጠ።
ካህኑ፡ቅዱስ፡እግዚአብሔር፡ቅዱስ፡ኃያል፡
ቅዱስ፡ሕያው፡ዘኢይመውት፡ይበል።
ዓርብ : በነግህ : ከከበረች : ግብረ : ሕማማት :
ውስጥ፡ከወንጌል፡በኋላ፡የሚነበብ፡ይህ፡ነው።
ይሰቅለው፡ዘንድ፡ወደ፡ጲላጦስ፡አሳልፈው፡
፩፤ ሊሰጡት፡የካህናት፡አለቆች፡በአንድ፡ቦታ፡
ተሰብስበው፡በመድኃኒታችን፡ላይ፡ፈረዱ።
፪፤ ይሁዳ፡ግን፡በሠራው፡ሥራ፡ተጸጽቶ፡ንጹሕ፡

Scanned by CamScanner

## ዘዓርብ፡ጽባሕ።

ግብሩ ፡ ወአግብአ ፡ ብሩረ ፡ ኀበ ፡ ሊቃነ ፡ ካህናት፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ እስመ ፡ ንጹሐ ፡ አቅተልኩ፡አነ፤ወውእቱ፡እንበለ፡ፍትሕ።
፫፤ ወገብኩ ፡ ኀነቀ ፡ ነፍሶ ፡ በርእሱ ፡ ወፈጸመ ፡ ጌጋየ፡ በዲበ ፡ ጌጋዩ ፡ ወነሥኡ ፡ ሊቃነ ፡ ካህናት፡ ብሩረ ፡ ወተማየጡ ፡ ገራህተ ፡ ለብሐዊ፡ ከመ ፡ ይትፈጸም ፡ ዘተብህለ ፡ በእንተ፡ሠላሳ፡ብሩር፡ሤጡ፡ለንጹሕ።
፬፤ ወአቀምዎ ፡ ለኢየሱስ ፡ ቅድመ ፡ ጲላጦስ ፡ ወተስእሎ ፡ ለኢየሱስ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ እስመ ፡ አንተ ፡ ንጉሥ ፡ አውሥአ ፡ ወይቤሎ ፡ አንተ ፡ ትቤ ፡ አው ፡ ካልእ ፡ ነገረከ ፡ አ ፡ ጲላጦስ ፡ በእንተ ፡ መንግሥትየ።
፭፤ ወአስተዋደይዎ ፡ ላዕሌሁ ፡ ብዙኀ ፡ ወኢያውሥአ፡ቡሩክ፡ወኢምንተኒ፡ወይቤሎ፡ኢትሰምዖኑ፡ስምዐ፡ዝንቱ፡ሕዝብ፡ወኢከሠተ፡አፉሁ፡ከመ፡ይበል፡ቃለ።
፮፤ ወአንከረ ፡ መኰንን ፡ ፈድፋደ ፡ በእንተ ፡ አርምሞቱ ፡ ወዕማዌሁ ፡ እሮ ፡ ይከሥት ፡ አፉሁ፡ በግዕ ፡ ዘመጽአ ፡ ከመ ፡ ያእትት ፡ ኃጢአተ፡ዓለም።
፯፤ አስምዐ ፡ በእንቲአሁ ፡ ኢሳይያስ ፡ እስመ ፡ ፍትሑ ፡ ትትነሣእ ፡ ከመ ፡ በግዕ ፡ ተፈጸመት ፡ ዮም ፡ ዛቲ ፡ ትንቢት ፡ በማዕከለ፡እስራኤል።
፰፤ ይበክዩ ፡ በላዕሌኪ ፡ ውሉድኪ ፡ ዮም ፡ ኢየሩሳሌም፡ዘቀተልኪ፡ነቢያተ፡ኢኮነ፡ውእቱ፡ነቢየ ፡ አላ ፡ አምላክ ፡ በደሙ ፡ ይደመስስ ፡ ጌጋየ።

ክርስቶስ፡መድኃኒነ፡መጽአ፡ወሐመ፡ወበሕማሚሁ፡አድኃነነ።

ማኅተመ፡ጸሎትስ፡ወኵሉ፡ሥርዓቱ፡ከመ፡ቀዳሚ።

## ምዕራፍ፡፶፪።

ትእዛዝ ፡ ወእምዝ ፡ ይትጋብኡ ፡ በሰለስቱ ፡ ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ፡ለጸሎት፡ወይበል፡መራሒ፡በ፱፡ሃሌ፡ሃሌ፡ሃሌ፡ሃሌ፡ሉያ፡ሃሌ፡ሃሌ፡

## የዐርብ፡ነግህ።

ሰው ፡ አስገደልኩ ፡ እያለ ፡ ለካህናት ፡ አለቆች ፡ ብሩን ፡ መለሰ ፤ ይኸውም ፡ ያለ ፍርድ፡ነው።
፫፤ ይሁዳም ፡ በገዛ ፡ ራሱ ፡ ታንቆ ፡ በመሞቱ ፡ በበደል ፡ ላይ ፡ በደልን ፡ ፈጸመ ፤ ስለ ፡ ንጹሕ ፡ ጌታ ፡ ሽያጭ ፡ በነቢይ ፡ የተነገረው ፡ ይፈጸም ፡ ዘንድ ፡ የካህናት ፡ አለቆች ፡ ብሩን ፡ ወስደው ፡ የሸክላ፡ሠሪ፡መሬት፡ገዙበት።
፬፤ ጌታ ፡ ኢየሱስንም ፡ በጲላጦስ ፡ ፊት ፡ አቆሙት፤ እርሱም ፡ አንተ ፡ ንጉሥ ፡ ነህን? ብሎ ፡ ጠየቀው ፡ ጌታም ፡ መልሶ ፡ ጲላጦስ ፡ ሆይ፥ አንተ ፡ አልክ ? ወይስ ፡ ስለ ፡ እኔ ፡ መንግሥት ፡ ሌላ ፡ የነገረህ ፡ አለ ? ብሎ ፡ መለሰለት።
፭፤ በእርሱም ፡ ላይ ፡ አብዝተው ፡ ነገር ፡ ይሠሩ ፡ ነበር ፤ ቡሩክ ፡ ጌታ ፡ ምንም ፡ ምን ፡ አልመለሰም፤ ጲላጦስም ፡ ሕዝቡ ፡ የሚመሰክሩብህን፡ አትሰማምን ? አለው ፤ ጌታም፡ቃልን፡ ይናገር፡ዘንድ፡አፉን፡አልገለጠም።
፮፤ ገዢውም፡ስለ፡ዝምታውና፡ስለ፡ትዕግሥቱ፡ እጅግ ፡ አደነቀ ፤ የዓለምን፡ ኃጢአት፡ ያስወግድ፡ዘንድ፡የመጣ፡በግ፡እንዴት፡አንደበቱን፡በነገር፡ይገልጻል።
፯፤ ስለ ፡ እርሱም ፡ ኢሳይያስ ፡ ሰውነቱ ፡ እንደ ፡ በግ፡ ወደ ፡ ሞት ፡ ተወሰደች ፡ ብሎ ፡ የመሠከራት ፡ ያቺ ፡ ትንቢት ፡ ዛሬ ፡ በእስራኤል ፡ መካከል፡ተፈጸመች።
፰፤ ነቢያትን ፡ የምትገድሊ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ልጆችሽ ፡ በአንቺ ፡ ላይ ፡ ያለቅሳሉ ፤ እርሱ ፡ ግን፡ ነቢይ ፡ አይደለም ፤ በደሙ ፡ የኃጢአትን፡ በደል ፡ የሚደመስስ ፡ አምላክ ፡ ነው ፡ እንጂ።

መድኃኒታችን ፡ ክርስቶስ ፡ ሰው ፡ ሁኖ ፡ መከራ፡ ተቀበለ፤በመከራውም፡አዳነን።

የጸሎቱ ፡ መፈጸሚያ ፡ ሥርዓት ፡ እንደ ፡ መጀመሪያው፡ነው።

## ምዕራፍ፡፶፪።

ትእዛዝ ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ዓርብ ፡ በሦስት ፡ ሰዓት ፡ ለጸሎት፡ ይሰብሰቡ ፤ መሪው ፡ ይህን ፡ መዝሙር ፡ በዘጠኝ ፡ ሃሌታ ፡ ይበል፤

Scanned by CamScanner

በ፫፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

ሃሌ፡ሉያ፡ሃሌ፡ሃሌ፡ሃሌ፡ሉያ፡አርዐተ፡መስቀሉ፡ጾረ፡አርዐተ፡መስቀሉ፡ጾረ፡ይሰቅልዎ፡ሖረ፡ዮ፡ዮ፡ዮ፡ከመ፡ኪያነ፡ይቤዙ፡**እግዚእ**፡ከነ፡ገብረ።

ወእምዝ፡ለከ፡ኃይል፡ይበሉ።

## ክፍል፡፩።

### ምንባብ፡ኦሪት፡ዘልደት።

ምዕ፡፵፰፡፩-፲፱።

፩ ወኮነ፡እምድኅረ፡ዝንቱ፡ነገር፡ይቤልዎ፡ለዮሴፍ፡ደክመ፡አቡነ፡ወነሥአ፡ዮሴፍ፡ክልኤተ፡ደቂቆ፡ምናሴሃ፡ወኤፍሬምሃ።

፪ ወይቤልዎ፡ለእስራኤል፡ናሁ፡ወልድከ፡ዮሴፍ፡ይመጽእ፡ኀቤከ። ወተኀየለ፡እስራኤል፡ወተንሥአ፡ነበረ፡ዲበ፡ምስካቢሁ።

፫ ወይቤሎ፡ያዕቆብ፡ለዮሴፍ፡**አምላኪየ**፡ዘአስተርአየኒ፡በሎዛ፡በምድረ፡ከነዓን፡ባረከኒ።

፬ ወይቤለኒ፡ናሁ፡አነ፡አበዝኀከ፡ወአስተባዝኀከ፡ወእገብረከ፡ማኅበረ፡አሕዛብ፡ወእሁበከሃ፡ለዛቲ፡ምድር፡ወለዘርእከ፡እምድኅሬከ፡ከመ፡ይምልክዋ፡ለዓለም።

፭ ወይእዜኒ፡እሉ፡ደቂቅከ፡ክልኤቱ፡ኤፍሬም፡ወምናሴ፡እለ፡ተወልዱ፡ለከ፡በብሔረ፡ግብጽ፡ዘእንበለ፡እምጻእ፡አነ፡ዝየ፡ኀቤከ፡ከመ፡ሮቤል፡ወስምዖን፡ሊተ፡እሙንቱ።

፮ ወእመ፡ቦ፡ዘወለድከ፡እምይእዜ፡ይኩኑ፡በስመ፡አኀዊሆሙ፡ይሰመዩ፡ወይኩኑ፡ውስተ፡ክፍለ፡አኀዊሆሙ።

፯ ወአመ፡መጻእኩ፡አነ፡እመስጴጦምያ፡ዘሶርያ፡ሞተት፡ራኄል፡እምከ፡በምድረ፡ከነዓን፡በፍኖት፡ሶበ፡ቀረብኩ፡ኀበ፡ምርዋጸ፡አፍራስ፡ብሔረ፡ኤፍራታ፡ለበጺሐ፡ኤፍራታ፡ወቀበርክዋ፡ውስተ፡ፍኖት፡ዘምርዋጸ፡አፍራስ፡ዘስሙ፡ቤተ፡ልሔም።

፰ ወሶበ፡ርእየ፡እስራኤል፡ደቂቆ፡ለዮሴፍ

፺፻፴፫

ዓርብ፡መዓልት፡በ፫፡ሰዓት።

ቅድመ፡ዓለም፡የነበረ፡ዛሬም፡ያለ፡ወደፊትም፡ዓለምን፡አሳልፎ፡የሚኖር፡መስቀሉን፡ተሸክሞ፡ይሰቅሉት፡ዘንድ፡ሄደ፤ ወዮ፡ወዮ፡ወዮ፡እኛን፡ያድን፡ዘንድ፡**ጌታ**፡ባርያ፡ሆነ።

ከዚህ፡በኋላ፡ለከ፡ኃይል፡ይበሉ።

## ክፍል፡፩።

### ምንባብ፡ኦሪት፡ዘፍጥረት።

ምዕ፡፵፰፡፩-፲፱።

፩፤ ከዚህ፡ነገር፡በኋላ፡እንዲህ፡ሆነ፤ወንድሞቼ፡አባታችን፡ደከመ፡ብለው፡ለዮሴፍ፡ነገሩት፤ ዮሴፍም፡ሁለቱን፡ልጆቹን፡ኤፍሬምንና፡ምናሴን፡ይዞ፡ሄደ።

፪፤ ያዕቆብን፡እነሆ፡ልጅህ፡ዮሴፍ፡ወዳንተ፡መጣ፡አሉት፤ ያዕቆብም፡ተበረታትቶ፡ተነሥቶ፡በአልጋው፡ላይ፡ተቀመጠ።

፫፤ ያዕቆብም፡ዮሴፍን፡በከነዓን፡ምድር፡በሎዛ፡የታየኝ፡**ፈጣሪዬ**፡ባረከኝ፡አለው።

፬፤ እነሆ፡እኔ፡ፈጽሜ፡አበዛሃለሁ፤የአሕዛብም፡አባት፡አደርግሃለሁ።ይቺንም፡አገር፡ላንተ፡እሰጥሃለሁ፤ከአንተም፡በኋላ፡ለዘላለሙ፡ይገዟት፡ዘንድ፡ለልጆችህ፡እሰጣታለሁ፡አለኝ።

፭፤ አሁንም፡እኔ፡ካንተ፡ዘንድ፡ወደዚህ፡ሳልመጣ፡በግብጽ፡አገር፡የተወለዱልህ፡እሊህ፡ሁለቱ፡ልጆችህ፡ምናሴና፡ኤፍሬም፡ለእኔ፡እንደ፡ስምዖንና፡እንደ፡ሮቤል፡ናቸው።

፮፤ ከእንግዲህም፡ወዲህ፡የምትወልዳቸው፡ልጆች፡ቢኖሩ፡በወንድሞቻቸው፡ስም፡ይጠሩ፤በወንድሞቻቸውም፡እጣ፡ይግቡ።

፯፤ እኔ፡ከሶርያ፡ወንዞች፡መካከል፡በመጣሁ፡ጊዜ፡ኤፍራታ፡ለመድረስ፡ወደ፡ፈረስ፡መግሪያ፡ወደ፡ኤፍራታ፡በቀረብኩ፡ጊዜ፡እናትህ፡ራሄል፡በከነዓን፡ጎዳና፡ሞተች፤ ስሙ፡ቤተ፡ልሔም፡በሚባል፡የፈረስ፡መግሪያ፡በሆነ፡ጎዳናም፡ቀበርኋት።

፰፤ ያዕቆብም፡የዮሴፍን፡ልጆች፡ባየ፡ጊዜ፡

ይቤሎ፡ምንትከ፡እሉ።
፱፡ ወይቤሎ ፡ ዮሴፍ ፡ ለአቡሁ ፡ ደቂቅየ ፡ ዘወ
ሀበኒ፡ እግዚአብሔር ፡ በዝየ ፡ ወይ
ቤሎ ፡ ያዕቆብ ፡ አምጽኦሙ ፡ ኀቤየ ፡ ከመ ፡
እባርኮሙ።
፲፡ ወአዕይንቲሁ ፡ ለእስራኤል ፡ ክብዳ ፡
ወተከደና፡እምርስእ፡ወኢይክል፡ከሚቶተ፦
ወነጽሮ።ወአቅረቦሙ፡ኀቤሁ፡ወሐቀፎሙ፡
ወሰአሞሙ።
፲፩፡ ወይቤሎ፡እስራኤል፡ለዮሴፍ፡ናሁ፡ኢተፈ
ለጥኩ፡እምገጽከ፡ወናሁ፡ዘርዐከኒ፡አርአየኒ፡
እግዚአብሔር።
፲፪፡ ወአውጽኦሙ ፡ ዮሴፍ ፡ እማዕከለ ፡
ብረኪሁ ፡ ወሰገደ ፡ ሎቱ ፡ በገጹ ፡ ውስተ ፡
ምድር።
፲፫፡ ወነሥኦሙ ፡ ዮሴፍ ፡ ለክልኤሆሙ ፡
ደቂቁ ፡ ወአቀሞ ፡ ለኤፍሬም ፡ በየማኑ ፡ ኀበ ፡
ፀጋመ ፡ እስራኤል ፡ ወለምናሴ ፡ አቀሞ ፡
በፀጋሙ ፡ ኀበ ፡ የማነ ፡ እስራኤል ፡ ወአቅ
ረቦሙ፡ኀበ፡አቡሁ።
፲፬፡ ወሰፍሐ፡እስራኤል፡እዴሁ፡እንተ፡የማን፡
አንበረ፡ላዕለ፡ርእሰ፡ኤፍሬም፡ወውእቱ፡
ይንእስ፡እምነ፡እኁሁ፤ወእዴሁ፡እንተ፡
ፀጋም፡አንበረ፡ላዕለ፡ርእሰ፡ምናሴ፡ወአስተ
ኀለፈ፡እዴሁ፡ወባረኮሙ።
፲፭፡ ወይቤ፡ውእቱ፡እግዚአብሔር፡ዘአሥመርዎ፡
አበውየ፡ቅድሜሁ፡አብርሃም፡ወይሥሐቅ፡
ወእግዚአብሔር፡ውእቱ፡ዘሐፀነኒ፡ወሴሰየኒ፡
እምንእስየ ፡ እስከ ፡ ይእዜ ፡ ወእስከ ፡ ዛቲ ፡
ዕለት።
፲፮፡ ወመልአከ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘአድኀነኒ ፡
እምኵሉ፡እኪት፡ውእቱ፡ለይባርኮሙ፡ለእሉ፡
ሕፃናት ፡ ወይሰመይ ፡ ስምየ ፡ በላዕሌሆሙ ፡
ወስመ ፡ አበውየ ፡ አብርሃም ፡ ወይስሐቅ ፡
ይብዝኁ ፡ ወይትባዝኁ ፡ ወይምልኡ ፡ ዲበ ፡
ምድር።
፲፯፡ ወሶበ፡ርእየ፡ዮሴፍ፡ከመ፡አንበረ፡አቡሁ፡
እዴሁ፡እንተ፡የማን፡ላዕለ፡ርእሰ፡ኤፍሬም፡
ወእዴሁ፡እንተ፡ፀጋም፡ላዕለ፡ርእሰ፡ምናሴ፡
ኮነ ፡ ሎቱ ፡ ክቡደ ። ወአኀዘ ፡ ዮሴፍ ፡ እደ ፡
አቡሁ ፡ ያስተኀልፍ ፡ እምርእሰ ፡ ኤፍሬም ፡
ላዕለ፡ርእሰ፡ምናሴ።



እሊህ፡ምኖችህ፡ናቸው፡አለው።
፱፡ ዮሴፍም ፡ አባቱን ፡ በዚህ ፡ እግዚአብሔር፡
የሰጠኝ፡ልጆቼ፡ናቸው፡አለው፤ያዕቆብም፡
እመርቃቸው፡ዘንድ፡ወደ፡እኔ፡አምጣቸው፡
አለው።
፲፡ የያዕቆብ ፡ ዐይኖች ፡ ከእርጅና ፡ የተነሣ፡
ፈዘው፡ተሸፍነው፡ነበር፤ዐይኑንም፡ገልጦ፡
ማየት፡አይችልም፡ነበር፤ወደ፡እርሱም፡አቀ
ረባቸው፡እቅፍ፡አድርጎም፡ሳማቸው።
፲፩፡ ያዕቆብም፡ዮሴፍን፡እነሆ፡ከፊትህ፡አልተለ
የሁም፤ልጆችህንም፡እግዚአብሔር፡አሳየኝ፡
አለው።
፲፪፡ ዮሴፍም፡ከጉልበቱ፡መካከል፡አወጣቸውና፡
እግር ፡ ከግንባር ፡ አድርጎ ፡ በምድር ፡ ላይ፡
ሰገደለት።
፲፫፡ ዮሴፍም ፡ ሁለቱ ፡ ልጆቹን ፡ አምጥቶ ፡
ኤፍሬምን ፡ በያዕቆብ ፡ ግራ ፡ በእርሱ ፡ ቀኝ፡
አቆመው ፤ ምናሴንም ፡ በእርሱ ፡ ግራ፡
በያዕቆብ ፡ ቀኝ ፡ አቆመው ። ወደ ፡ አባቱም፡
አቀረባቸው።
፲፬፡ ያዕቆብም፡ቀኝ፡እጁን፡ዘርግቶ፡በኤፍሬም፡
ራስ፡ላይ፡አኖረ፤እርሱም፡ከወንድሙ፡የሚያንስ፡
ነበር ፤ ግራ ፡ እጁንም ፡ በምናሴ ፡ ራስ ፡ ላይ፡
አኖረ።እጆቹንም፡አስተላልፎ፡(አመሳቅሎ)፡
ባረካቸው።
፲፭፡ እንዲህ፡አለ፤አባቶቼ፡አብርሃምና፡ይስሐቅ፡
በፊቱ ፡ ያገለገሉት ፡ እርሱ ፡ እግዚአብሔር፡
ከሕፃንነቴ፡ጀምሮ፡እስከዚች፡ቀን፡ድረስ፡
የተንከባከበኝና ፡ የመገበኝ ፡ እርሱ ፡ እግዚአ
ብሔር፡ነው።
፲፮፡ ከክፉ፡ነገር፡ሁሉ፡ያዳነኝ፡የእግዚአብሔር፡
መልአክ ፡ እነዚህን ፡ ልጆች ፡ እሱ ፡ ይባር
ካቸው፤ ያከብራቸው ፡ ስሜ ፡ ያባቶቼ ፡ የይሥ
ሐቅና፡የአብርሃም፡ስምም፡በእነሱ፡ይጠራ፤
ይብዙ ፡ የብዙ ፡ ብዙም ፡ ይሁኑ ፤ በዚህ ፡
ዓለምም፡ይምሉ፡አለው።
፲፯፡ ዮሴፍም ፡ አባቱ ፡ ቀኝ ፡ እጁን ፡ በኤፍሬም፡
ራስ፡ ላይ ፡ ግራ ፡ እጁን ፡ በምናሴ ፡ ራስ ፡
እንዳኖረ ፡ ባየ፡ ጊዜ ፡ ከባድ ፡ ነገር ፡ ሆነ
በት ፤ የአባቱን ፡ እጅ፡ ይዞ ፡ ከኤፍሬም ፡
ራስ ፡ ላይ ፡ ወደ ፡ ምናሴ ፡ ራስ ፡ ሊያስተ
ላልፍ፡ጀመር።

Scanned by CamScanner

ሰ፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

፳፮ ወይቤሎ፡ዮሴፍ፡ለአቡሁ፡አኮ፡ከመ፡ዝ፡
አባ፡እስመ፡ዝንቱ፡በኵርየ፡አንብር፡እዴከ፡
እንተ፡የማን፡ላዕሌሁ።
፳፯ ወአበዮ፡ወይቤሎ፡እስራኤል፡አአምር፡
ወልድየ፡አአምር።ዝኒ፡ይከውን፡ዓቢየ፡አላ፡
እኁሁ፡ዘይንዕስ፡የዓብዮ፡ወዘርዑ፡ብዙኃ፡
አሕዛበ፡ይከውን።

ዘኢሳይያስ፡ነቢይ፡በረከቱ፡አምላኩ፡
ትኩን፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡
አሜን።

ምዕ፡፷፫፡፩–፲፱፡

መኑ፡ውእቱ፡ዝንቱ፡ዘወጽአ፡እምኤዶም፡
ቀይሐ፡አልባስ፡እምባሶር፡መካሕ፡ብእሲ፡
ወኃያል፡ወግሩም፡በልብሰቱ።አንሰ፡ዘእት
ቃቀሥ፡በእንተ፡ጽድቅ፡ወእፈትሕ፡
ለአድኅኖ።

ለምንት፡ቄሐ፡አልባሲከ፡ወክዳንከኒ፡ዘከመ፡
ወጽአ፡እምክያድ።

ወይቤለኒ፡ሶበ፡ርኢኩ፡ከመ፡አልቦ፡
ዘይረድእ፡ወአልቦ፡ዘያድኅን፡ቀጥቀጥ
ክዎሙ፡ለአሕዛብ፡በመዓትየ።ወኬድ
ክዎሙ፡ከመ፡ጽንጉነ፡መርኅብ፡በእንተ፡
ዝንቱ፡ተነዝኀ፡ደሞሙ፡ውስተ፡አልባስየ፡
ወኵሉ፡ክዳንየ፡ተሴረየ፡በደም።
እስመ፡በጽሐት፡ዕለተ፡ፍዳሆሙ፤
ወመጽአት፡ዕለተ፡ቤዛ።

ወርኢኩ፡ከመ፡አልቦ፡ዘይረድእ፡ወአእ
መርኩ፡ከመ፡አልቦ፡ዘይትዌከፍ፡ወአድ
ኀኖሙ፡በመዝራዕትየ፤ወመጽአት፡መዓትየ።
ወኬደቶሙ፡መቅሠፍትየ፡ወከዓውኩ፡
ደሞሙ፡ውስተ፡ምድር።
ወተዘከርኩ፡ሣህሎ፡ለእግዚአ
ብሔር፡በኵሉ፡ዕሴቱ፡ለእግዚአብሔር፡
ጻድቅ፡ወኄር፡ለቤተ፡እስራኤል፡ወያ
መጽእ፡ለነ፡ሣህሎ፡በከመ፡ብዝኀ፡
ጽድቁ።
ወይቤ፡አኮኑ፡ሕዝብየ፡ውሉድየ፡እሙንቱ፡

ዓርብ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

፳፮፡ ዮሴፍም፡አባቱን፡አባቴ፡እንዲህ፡አይደለም፡
በኵር፡ልጄ፡ይህ፡ነውና፡ቀኝ፡እጅህን፡
በእርሱ፡ላይ፡አኑር፡አለው።
፳፯፡ ያዕቆብም፡ይህ፡ታላቅ፡ወገን፡ይሆናል፤ግን፡
ታናሽ፡ወንድሙ፡ይበልጠዋል፤ልጁም፡የልጅ፡
ልጁም፡ብዙ፡ወገን፡ይሆናል፡እንጂ፡አውቃለሁ፡
ልጄ፡አውቃለሁ፡አይሆንም፡አለው።

የአምላኩ፡በረከት፡ከእኛ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡
ትኑርና፡ነቢዩ፡ኢሳይያስ፡የተናገረው፡
ትንቢት፡ይህ፡ነው።

ምዕ፡፷፫፡፩–፲፱፡

፩፡ ቀይ፡ልብስን፡ለብሶ፡ከባሶር፡ከኤዶም፡ያለ፡
የወጣ፡የሚመካ፡ኃይለኛ፡ሰው፡በአለባ
በሱም፡ግሩም፡የሆነ፡ይህ፡ማነው?ሲል፡
ከነቢዩ፡የተገኘ፡ጥያቄ፡ይህ፡ነው፤ስለ፡
ጽድቅ፡የምከራከር፡ስለ፡ድኅነትም፡
የምፈርድ፡እኔ፡ነኝ።
፪፡ ልብስህ፡ለምን፡ቀላ?መጐናጸፊያህስ፡
ከወይን፡ዓውድማ፡እንደ፡ወጣ፡ለምን፡
በደም፡ታለለ?
፫፡ እኔም፡የሚረዳ፡የሚያድን፡እንደሌለ፡
በአየሁ፡ጊዜ፡አሕዛብን፡ተቆጥቼ፡አጠፋ
ኋቸው፤እንደ፡አደባባይም፡ጭቃ፡ረገጥ
ኋቸው፤ስለዚህ፡ደማቸው፡በልብሴ፡ላይ፡
ተረጨ፤መጐናጸፊያየም፡ሁሉ፡በደም፡
ታለለ።
፬፡ ብድራታቸውን፡የሚመልሱባት፡ቀን፡ደርሳ
ለችና፤እኔም፡እሳቸውን፡የምቤዥባት፡ቀን፡
መጥታለችና።
፭፡ የሚረዳ፡እንደሌለ፡አይቼ፡በረድኤት፡የሚቀ
በልም፡እንደሌለ፡አውቄ፤በሥልጣኔ፡አድና
ቸዋለሁ፤ቍጣዬም፡መጣች።
፮፡ መቅሠፍቴም፡አጠፋቻቸው፤ደማቸውንም፡
በምድር፡ላይ፡አፈሰስኩ።
፯፡ እውነተኛ፡ቸር፡የሚሆን፡እግዚአብሔር፡ለእ
ስራኤል፡ወገን፡ባደረገው፡ቸርነቱ፡ሁሉ፡የእ
ግዚአብሔርን፡ይቅርታ፡አሰብኩ፤እንደ፡
ቸርነቱ፡ብዛት፡መጠን፡ይቅርታውን፡
ያመጣልና።
፰፡ ወገኖቼ፡ልጆቼ፡አይደሉምን?ካልከዱኝስ፡

Scanned by CamScanner

በ፫፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

በ፫፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ፡ እምነ፡ ዘቀዳሚ፡ ቃለ፡ ወልድ፡ ዘይትነበብ፡ ...

እምነ፡ እደ፡ ተቃዋሚ፡ ኀያላን፡ ምጽንዓት፡ አድኀኖሙ፡ እምኵሉ፡
ወእመሰ፡ ኢክህዱኒ፡ አድኀኖሙ፡ እምኵሉ፡
ምንዳቤሆሙ።
፱፡ አኮ፡ በተንባል፡ ወአኮ፡ በመልአክ፡ አላ፡
ለሊሁ፡ያድኅኖሙ፡እስመ፡ያፈቅሮሙ፡ወይ
ምህኮሙ፡ውእቱ፡ቤዘዎሙ፡ወተወክፎሙ፡
ወአክበሮሙ፡ በኵሉ፡ መዋዕሊሆሙ፡
ለዓለም።
፲፡ እሙንቱሰ፡ ዐለውዎ፡ ወአምዕዕዎ፡
ለመንፈስ፡ ቅዱስ፡ ውእቱኒ፡ ቀተሎሙ፡
ወኮኖሙ፡ፀሮሙ።
፲፩፡ ወተዘከረ፡ መዋዕለ፡ ዓለም፡ እንዘ፡
ይብል፡ፈነውኩ፡መልአኪየ፡ቅድመ፡ገጾሙ፡
አመ፡ ወጽኡ፡ እምግብጽ፡ በእደ፡ ኖላዌ፡
አባግዕ።
፲፪፡ ወዘበጥኩ፡ ማየ፡ በየማን፡ ሙሴ፡ ወጸንዐ፡
ወተሠጠ፡ማይ፡እምቅድመ፡ገጹ፡ወረሰየ፡
ሎቱ፡ስመ፡ዘለዓለም።
፲፫፡ ወአኅለፎሙ፡እንተ፡ማእከለ፡ቀላይ፡ከመ፡
ፈረስ፡በገዳም።
፲፬፡ ወኢደክሙ፡ ከመ፡ እንስሳ፡ በሐቅል።
ወወረደ፡ መንፈስ፡ እምኀበ፡ እግዚአ
ብሔር፡ ወመርሆሙ፤ ወከመዝ፡ አው
ጻእከ፡ ሕዝበከ፡ ወረሰይከ፡ ለከ፡ ስመ፡
ስብሐቲከ።
፲፭፡ ተመየጥ፡ እምሰማይ፡ ወርኢ፡ ቤተ፡
መቅደስከ፡ ወስብሐቲከ። አይቴ፡ ውእቱ፡
ቅንዓትከ፡ ወኀይልከ፡ ወአይቴ፡ ውእቱ፡
ብዝኀ፡ ምሕረትከ፡ ወሣህልከ፡ እስመ፡
ተዓገሥከነ።
፲፮፡ ወአንተ፡ውእቱ፡አቡነ፡አብርሃምሰ፡ኢያእ
መረነ፡ ወእስራኤልኒ፡ ኢጠየቀነ። አንተ፡
ዳእሙ፡ አቡነ፡ አድኅነነ፡ እምትካት፡
ወተሰምየ፡ስምከ፡ላዕሌነ።
፲፯፡ በእንተ፡ምንት፡አስሐትከነ፡እግዚአ፡ እምፍ
ኖትከ፡ ሠናይት፡ ወአጽናዕከ፡ ልበነ፡ ከመ፡
ኢንፍራህከ፤ ተመየጠሙ፡ ለአግብርቲከ፡
ወለሕዝበ፡ርስትከ።
፲፰፡ ከመ፡ንርከብ፡ሕዳጠ፡መክፈልተ፡ወርስተ፡
ውስተ፡ደብረ፡መቅደስከ።
፲፱፡ እስመ፡ ኮነ፡ ከመ፡ ትካት፡ ከመ፡ አመ፡
ኢኮንከነ፡ ወከመ፡ አመ፡ ኢተሰምየ፡ ስምከ፡
በላዕሌነ።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፫፡ሰዓት።

ከመከራቸው፡ሁሉ፡አድናቸዋለሁ።

፱፡ እሱ፡ ያድናቸዋል፡ እንጂ፡ በአማላጅ፡
በአለቃ፡የሚያድናቸው፡አይደለም፤ይወዳቸ
ዋልና፤ ይራራላቸዋል፤ እርሱ፡ በረድኤት፡
ተቀብሎ፡አዳናቸው፤ባለ፡ዘመናቸው፡ሁሉ፡
ለዘላለም፡አከበራቸው።
፲፡ እነርሳቸው፡ ግን፡ ካዱት፤ መንፈስ፡
ቅዱስንም፡ አሳዘኑት፤ እሱም፡ ገደላቸው፤
ጠላትም፡ሆናቸው።
፲፩፡ በጎችን፡(እስራኤልን)፡በሚጠብቅ፡እረኛ፡
እጅ፡(በሙሴ፡ሥልጣን)፡ከግብጽ፡በወጡ፡
ጊዜ፡ መልእክተኛዬ፡ ሙሴን፡ በፊታቸው፡
ላክሁ፡ብሎ፡የቀደመውን፤ዘመን፡አሰበ።
፲፪፡ በሙሴ፡እጅ፡ውኃን፡ከፈልሁ፤ውኃውም፡
በፊቱ፡ተከፍሎ፡ጸና፤ለዘለዓለም፡ስምንም፡
አስጠራ።
፲፫፡ ፈረስን፡በዱር፡እንደሚያሠማሩ፡በጥልቁ፡
መካከል፡አሳለፋቸው።
፲፬፡ እንደ፡ እንስሳትም፡ በምድረ፡ በዳ፡ አልደ
ከሙም፤መንፈስ፡ረድኤት፡ከእግዚአብሔር፡
ዘንድ፡ወርዶ፡መራቸው፤እንዲህ፡አድርገህ፡
ወገኖችህን፡አወጣህ፤ጌትነትህም፡ሊታወቅ፡
ስምህን፡አስጠራህ።
፲፭፡ ከቸልታ፡ ተመልሰህ፡ ማደሪያህ፡ ቤተ፡
መቅደስን፡እይ፤ተአምራትህንም፡ግለጥ፤በአ
ምልኮትህ፡ ትቀና፡ የነበረው፡ ቅናትህ፡
ኃይልህስ፡ ወዴት፡ ነው? ቸል፡ ብለሃልና፡
ብዙ፡ቸርነትህና፡ይቅርታህስ፡ወዴት፡አለ።
፲፮፡ አባታችን፡ አንተ፡ ነህ፤ ከጥንት፡ ጀምሮ፡
ስምህ፡ በእኛ፡ ላይ፡ ተጠርቷልና፤ አንተ፡
አባታችን፡አድነን፡እንጂ፡አብርሃምስ፡አላወ
ቀንም፤እስራኤልም፡አላሰበንም።
፲፯፡ አቤቱ፡ ከበጎ፡ ሥራህ፡ ስለምን፡ አወጣኸን፤
እንዳንፈራህስ፡ልቡናችንን፡ስለምን፡አጸናህ?
ለማደሪያህ፡ ወገኖችና፡ ለእኛ፡ ለባሮችህ፡
ከመዓት፡ወደ፡ምሕረት፡ተመለስልን።
፲፰፡ በማደሪያህ፡በኢየሩሳሌም፡ጥቂት፡ርስትና፡
ፈንታ፡እናገኝ፡ዘንድ።
፲፱፡ ረዳት፡ ባልሆንከን፡ ስምህም፡ በእኛ፡
ባለተጠራ፡ጊዜ፡እንደ፡ወትሮው፡ሁነናልና፡
ከመዐት፡ወደ፡ምሕረት፡ተመለስልን።

Scanned by CamScanner

## በ፫፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

ምዕ፤፷፬፡፩–፬።

መሰ፡አርኀውከ፡ሰማየ፡ይርዕዱ፡አድባር፡
እምኔከ።
መ፡ይትመሰው፡መዐረ፡ግራ፡እምገጸ፡
እሳት፡ከማሁ፡ትበልዖሙ፡እሳት፡ለዐርከ፡ወይ
ትዐውቅ፡ስምከ፡በኀቤሆሙ፡ወይደነግፁ፡
አሕዛብ፡እምቅድመ፡ገጽከ።
ሶበ፡ገበርከ፡ስብሐተከ፡ይርዕዱ፡አድባር፡
እም፡እምፍጥረተ፡ዓለም።

ኢርኢነ፡ወኢሰማዕነ፡ባዕደ፡አምላከ፡ዘእን
በሌከ፡ወትገብር፡ምሕረተከ፡ለእለ፡ይሴፈዉ፡
ግህለከ።

ትርጓሜ፡ትንቢተ፡ኢሳይያስ፡ነቢይ፡
መኑ፡ዝንቱ፡እስከ፡ኀበ፡ይብል፡ይሴ
ፈዉ፡ግህለከ።

ይቤ፡መተርጕም፡ይቤ፡መኑ፡ዝንቱ፡
ዘወጽአ፡እምኤዶም፡ዘንተ፡ይቤ፡ነቢይ፡
በእንተ፡እግዚአብሔር፡እግዚእን፡ኢየሱስ፡
ክርስቶስ፡ሎቱ፡ስብሐት፡እስመ፡ኤዶም፡
እምአድያመ፡ገሊላ።

ወአመሰ፡አይሁድ፡ኮኑ፡ይቤሉ፡እስመ፡ውእቱ፡
እምገሊላ፡ወኮኑ፡ይቤሉ፡በበይናቲሆሙ፡
በእንተ፡ቅንአት፡ኀሡ፡ውስተ፡መጻሕፍት፡
ከመ፡ኢይትነሣእ፡ነቢይ፡እምገሊላ።
ወተርጐምዎ፡ካዕበ፡በእንተ፡ኤዶም፡
ኀበ፡ሰማይ፡ከመ፡ቃለ፡ዳዊት፡
ነቢይ፡መኑ፡ይወስደኒ፡ሀገረ፡ጥቅም፡
ወመኑ፡ይመርሐኒ፡እስከ፡ኤዶም
ያስ፡እስመ፡ክልኤሆን፡ቃላት፡ይት
መየጣ፡በትንቢት፡ኀበ፡እግዚእን፡
ክርስቶስ።
ይቤ፡ወአልባሲሁኒ፡ቀይሕ፡ዘእምባሦር፡
ከመ፡እግዚአብሔር፡በነቢይ፡ዘይከውን፡
ጊዜ፡ሕማማቲሁ፡ማሕየውያት፡አመ፡
አልበስዎ፡ሐራ፡ኄሮድስ፡ወጲላጦስ፡ልብሰ፡
ግላት፡ቀይሐ፡ወተሣለቁ፡ቦቱ፡ወተወከፈ፡
እግዚእን፡እምኔሆሙ፡በፈቃዱ፡ዝከተ፡
ከመ፡ይፈጽም፡ትንቢተ፡ነቢያት።
ይቤ፡ሠናይ፡ከመዝ፡በልብሰቱ፡ወከመዝ፡

## ዓርብ፡መዓልት፡በ፫፡ሰዓት።

ምዕ፤፷፬፡፩–፬።

፩፤ ሰማይን፡ብትከፍት፡ግን፡ከአንተ፡የተነሣ፡
ተራሮች፡(ነገሥታት)፡ይንቀጠቀጣሉ።
፪፤ ሰም፡(አደሮ፡ማር)፡በእሳት፡ፊት፡እንዲቀልጥ፡
እንደዚሁ፡ጠላቶችህን፡እሳት፡ትበላቸዋለች፤
ስምህም፡በእነሳቸው፡ዘንድ፡ይታወቃል፤
አሕዛብም፡ከፊትህ፡የተነሣ፡ይደነግጣሉ።
፫፤ ተአምራትህንም፡በአደረግህ፡ጊዜ፡ከጥንት፡
ጀምሮ፡የነበሩት፡ተራሮች፡(ነገሥታት)፡ይንቀ
ጠቀጣሉ።

፬፤ ያላንተ፡ሌላ፡ፈጣሪ፡አላየንም፤አልሰማንም፤
ይቅርታህንም፡ተስፋ፡ለሚያደርጉ፡ሰዎች፡ቸር
ነትህን፡ታደርግላቸዋለህ።

መኑ፡ዝንቱ፡ከሚለው፡ጀምሮ፡ይሴፈው፡
ግህለከ፡እስከሚለው፡የኢሳይያስ፡ትንቢት፡
ምሥጢራዊ፡ትርጓሜ፡ይህ፡ነው።

፩፤ ተርጓሚው፡ይህ፡ማነው? ከኤዶም፡የወጣ፡
አለ፤ ነቢዩ፡ይህን፡ስለ፡ክብር፡ባለቤት፡ስለ፡
እግዚአብሔር፡ወልድ፡ስለ፡ጌታችን፡ኢየሱስ፡
ክርስቶስ፡ተናገረ፤ ኤዶም፡ከገሊላ፡አውራ
ጃዎች፡ናትና።
፪፤ ምንም፡አይሁድ፡የገሊላ፡ሰው፡ነውና፡ከመቅ
ናታቸው፡የተነሣ፡እርስ፡በርሳቸው፡ከገሊላ፡
ነቢይ፡እንደማይነሣ፡እስኪ፡መጻሕፍትን፡
መርምሩ፡ቢሉም።
፫፤ ዳግመኛም፡ዳዊት፡ቅጥር፡ወዳለበት፡አገር፡
ማን፡ይወስደኛል? ወደ፡ኤዶምያስስ፡ማን፡
መርቶ፡ያደርሰኛል? ብሎ፡እንደ፡ተናገረ፡
ኤዶምን፡ሰማይ፡ብለው፡ተርጕመውታል፤
ሁለቱም፡ቃሎች፡በትንቢት፡ስለ፡ጌታችን፡
ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ይተረጐማሉና።

፬፤ ልብሶቹም፡ከባሶር፡የተገኙ፡ቀይ፡ግምጃ፡አለ፤
ሕይወት፡በሆነች፡በሕማሙ፡ጊዜ፡የሄሮድስና፡
የጲላጦስ፡ጭፍሮች፡ቀይ፡ግምጃ፡አልብሰው፡
እንዲህ፡በተዘባበቱበት፡ጊዜ፡እግዚአብሔር፡
በነቢዩ፡አድሮ፡የሚሆነውን፡ገለጠ፡ጌታችንም፡
የነቢያትን፡ቃል፡ይፈጽም፡ዘንድ፡ከእነሱ፡
ይህን፡ሁሉ፡መከራ፡በፈቃዱ፡ተቀበለ።
፭፡ በአለባበሱ፡መልካም፡የሆነ፡አለ፡ይኸንንም

Scanned by CamScanner

## በ፲፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

ካዕበ፡ይትረጐም፡ኪያሁ እግዚእ፡ኢየሱስ፡
ክርስቶስሃ፡እስመ፡ውእቱ፡በአማን፡ተሠገወ፡
ወውእቱ፡በተሠግዎቱ፡ይሜኒ፡እምኩሉ፡
ዘተወልደ፡እምአዳም።

፮፡ ወከማሁ፡ይቤ፡ዳዊት፡ነቢይ፡ይሜኒ፡ላሕዩ፡
ፈድፋደ፡እምኩሎሙ፡ውሉደ፡ዕጓለ፡
እመሕያው።
፯፡ ይቤ፡ግሩም፡ወኃያል፡ይትረጐም፡ዘንተ፡
ኃይለ፡መለኮቱ፡እንተ፡ኢትትረአይ።

፰፡ ይቤ፡አንስ፡እትዋቀሥ፡በእንተ፡ጽድቅ፡
ወእፈትሕ፡ለአድኅኖ፡ይትረጐም፡ዘንተ፡
እስመ፡እግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ለሊሁ፡
ስብሐት፡እስመ፡ይነግር፡ለአይሁድ፡ነገረ፡
ጽድቅ፡ወይስሕቦሙ፡ለሕግ፡ፍጽምት፡
ከመ፡ይግበሩ፡ፈቃዶ፡ወይሑሩ፡በጽድቅ፡
ወኢፈቀዱ፡ዝክተ፡ወኢተወክፉ፡እምኔሁ፡
በእንተ፡ዑረተ፡አልባቢሆሙ፡ወፈቃዳ
ቲሆሙ፡ሙሱናት።

፱፡ ይቤ፡እፈትሕ፡ለአድኅኖ፡ይትረጐም፡ዘንተ፡
ከመ፡ፍትሕ፡ውስተ፡እደ፡እግዚአብሔር፡
መድኅኒነ፡ክርስቶስ፡በከመ፡ይቤ፡በወንጌል፡
ቅዱስ፡እስመ፡አብሰ፡ኢይኴንን፡ወኢመነሂ፡
አላ፡ወሀበ፡ለወልዱ፡ኵሎ፡ኵነኔሁ፡ከመ፡
ኵሉ፡ያክብርዎ፡ለወልድ፡በከመ፡ያከብርዎ፡
ለአብ።
፲፡ ይቤ፡ወኬድክዎሙ፡ለአሕዛብ፡በመዓትየ፡
ወከዐውኩ፡ደሞሙ፡ውስተ፡ምድር፡
ይትረጐም፡ዘንተ፡ከመ፡አብሐ፡ላዕለ፡
አይሁድ፡በእንተ፡ፅውግናሆሙ፡ወእከየ፡አል
ባቢሆሙ፡ወንጉሥ፡ሮም፡አጥወቆሙ፡
ወቀተሎሙ፡በሰይፍ፡ወከና፡ደማቲሆሙ፡
ዲበ፡ምድር፡ከመ፡ማይ።
፲፩፡ ይቤ፡እስመ፡በጽሒቶሙ፡ዕለተ፡ፍዳሆሙ፡
ይትረጐም፡ዘንተ፡ከመ፡ውእቱ፡ተዐገሦሙ፡
ከመ፡ይትመየጡ፡ወይነስሑ፡ወኢተመይጡ፡
ወፈደዮሙ፡እንከ፡በውስተ፡ዛቲ፡ዓለም፡
በገዘንቱ፡ሞት፡መሪር፡ወበደኃሪት፡ኵነኔ፡
ዘለዓለም።

## ዓርብ፡መዓልት፡በ፲፡ሰዓት።

ጌታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስን፡እንደሆነ፡
እርሱን፡ዳግመኛ፡ይተረጐማል፡እርሱ፡
በእውነት፡ሰው፡ሁኖአልና፡ሰው፡
በመሆኑም፡ከአዳም፡ከተወለደው፡ሁሉ፡
መልኩ፡ደምግባቱ፡ያምራልና።
፮፡ እንዲሁም፡ዳዊት፡መልኩ፡ከሰው፡ልጆች፡
ሁሉ፡መልክ፡እጅግ፡ያምራል፡ብሎአልና።

፯፡ ኃይለኛ፡ሰው፡በአለባበሱም፡ግሩም፡የሆነ፡
አለ፤ይኸንንም፡የማትመረመር፡የመለኮት፡
ኃይል፡እንደሆነች፡ይተረጐማል።
፰፡ እኔ፡ስለ፡እውነት፡እከራከራለሁ፤ፈርጄም፡
አድናለሁ፡አለ፤ይህንንም፡እንዲህ፡ይተረ
ጐማል፤የክብር፡ባለቤት፡ጌታችን፡ኢየሱስ፡
ክርስቶስ፡አይሁድን፡እውነተኛ፡ትምህርትን፡
ያስተምራቸውና፡ፍጽምት፡ወደ፡ሆነች፡ሕገ፡
ወንጌል፡ይስባቸው፡ነበርና፤ፈቃዱን፡ይፈ
ጽሙ፡ዘንድ፡በእውነተኛ፡መንገድም፡ይሄዱ፡
ዘንድ፡እነርሱ፡ግን፡አልወደዱም፤ስለ፡ልቡ
ናቸው፡ድንቁርና፡ትምህርቱን፡አልተቀበሉ
ትም፤የሚጠፋበትንም፡ፈቃዳቸውን፡ፈጸሙ፡
፱፡ ለማዳን፡እፈርዳለሁ፡አለ፤ይኸንንም፡ፍርድ፡
በመድኃኒታችን፡በእግዚአብሔር፡ክርስቶስ፡
እጅ፡እንደሆነ፡ይተረጐማል፤በከበረ፡
ወንጌል፡አብ፡በማንም፡በማን፡አይፈርድም፤
ፍርዱን፡ሁሉ፡ለልጁ፡ሰጠው፡እንጂ፤ሰዎች፡
ሁሉ፡አብን፡እንደሚያከብሩት፡ወልድንም፡
ያከብሩት፡ዘንድ፡እንዳለ።
፲፡ አሕዛብን፡በመዐቴ፡ረገጥኋቸው፤ደማቸ
ውንም፡በምድር፡ላይ፡አፈሰስሁ፡አለ፤
ይህንንም፡እንዲህ፡ይተረጐማል፤ስለ፡ጠማማ
ነታቸውና፡ስለ፡ልባቸው፡ክፋት፡በአይሁድ፡
ላይ፡በአሠለጠነው፡ጊዜ፡የሮም፡ንጉሥ፡
አስጨንቆ፡ይዞ፡በሰይፍ፡ገደላቸው፤
ደማቸውም፡በምድር፡ላይ፡እንደ፡ውኃ፡ፈሰሰ።
፲፩፡ ብድራታቸውን፡የሚቀበሉባት፡ቀን፡ደረሰ
ለችና፡አለ፤ይኸንንም፡እንዲህ፡ይተረጐማል፤
ተመልሰው፡ንስሐ፡ይገቡ፡እንደሆነ፡እንደታ
ተመልሰው፡ንስሐ፡ይገቡ፡እንደሆነ፡እንደታ
ሣቸው፡እነርሱ፡ግን፡አልተመለሱም፤ስለዚህ፡
በዚች፡ዓለም፡በጦር፡መጥፋትን፡ከፈላቸው፤
በኋለኛይቱም፡ዘመን፡ዘለዓለማዊ፡ፍርድን፡
ይፈርድባቸዋል።

በ፲፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

መአቱከ፡ በእንተ ፡ ክህደቶሙ ፡ ቦቱ ፡
ወአጸጸ፡ሃይማኖቶሙ፡ ወኢተመይጦቶሙ፡
ለጽድቅ።
ይቤ፡ወመጽአት፡ ዕለተ ፡ ቤዛ ፡ ይተረጐም ፡
ዘንተ፡ዕለተ፡ስቅለት፡ዘእግዚእን፡ኢየሱስ፡
ክርስቶስ፡እስመ፡ኮነት፡መድኃኒተ፡ለአዳም፡
ወለዘርዑ፡ወለዘመዱ፡በውእቱ፡ዕለት።

ይቤ፡ወርኢኩ፡ከመ፡አልቦ፡ዘይረድእ፡ወአእ
መርኩ፡ከመ፡አልቦ፡ዘይትዌከፍ፡ይተረጐም፡
ዘንተ፡ካዕበ፡ ጊዜ ፡ ሕማማት ፡ እግዚእን ፡
እስመ፡ ኵሎሙ ፡ ስንዕዋነ ፡ ኮኑ ፡ ላዕሌሁ ፡
ወአኮ፡ምስሌሁ።
ወአምቅድመ፡ውእቱ፡ጊዜ፡ኮኑ፡ይፈትዉ፡
ይስምዑ፡እምኔሁ፡ቃሎ።
ይቤ፡ወአእመርኩ፡ከመ፡አልቦ፡ዘይትዌከፍ፡
ይተረጐም፡ካዕበ፡ዘንተ፡በእንተ፡ኵሎሙ፡
አርድእት፡እስመ፡ጐዩ፡ኵሎሙ፡ወአልቦ፡
ዘተርፈ፡ አሐዱሂ ፡ እምኔሆሙ ፡ ዘእንበለ ፡
ዮሐንስ።
ወአዘዘ፡ ይሑር ፡ ውስተ ፡ መካኑ ፡ ከመ ፡
ይትፈጸም፡ቃለ፡ነቢያት።
በእንተዝ፡ ይቤ ፡ እግዚእን ፡ ናሁ ፡ በጽሐ ፡
ሰዓት፡ወሰበ፡በጽሐ፡ትዘረዉ፡ኵልክሙ፡
ለለዙሉ፡አሐዱ፡አሐዱ፡እምኔክሙ፡ኀበ፡
መካኑ፡ወተኀድጉኒ፡ባሕቲትየ፡ወኢኮንኩ፡
ባሕቲትየ፡እስመ፡አብ፡ምስሌየ፡ውእቱ።
ይቤ ፡ ወአድኀኖሙ ፡ በመዝራዕትየ ፡
ይተረጐም፡ዘንተ፡ኃይሎ፡ልዕልተ፡ወመዝ
ራዕቶ፡ጽንዕተ።
ይቤ፡ወአእኰቶ፡ ለእግዚአብሔር ፡በእንተ፡
ኵሉ፡ዘዓሰየኒ፡ይተረጐም፡ዘንተ፡በእንተ፡
ትንሣኤሁ፡ቅድስት፡እማዕከለ፡ምውታን።

ወበእንተዝ፡ይቤ፡ዳዊት፡እስመ፡ኢተኀድጋ፡
ውስተ ፡ ሲኦል ፡ ለነፍስየ ፡ ወኢትሁቦ ፡
ለጻድቅከ፡ይርአይ፡ሙስና።
ወንሰአሎ፡ ለእግዚእን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡
ዘተሰቅለ፡በእንቲአነ፡ለመድኃኒትነ፡ከመ፡
ያርሕቅ፡እምኔነ፡መዐቶ፡ወይሣሀል፡ላዕሌነ፡
በምሕረቱ።
ሎቱ፡ ስብሐት ፡ እስከ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡
አሜን።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፲፡ሰዓት።

፲፪፤ ይኸውም፡እርሱን፡ስለ፡መካዳቸውና፡ስለ፡
ሃይማኖታቸው፡ጉድለት፡ወደ፡እውነት፡ባለ
መመለሳቸው፡ነው።
፲፫፤ የምቤዠባት፡ቀን፡መጣች፡አለ፤ይኸንንም፡
ጌታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፤የሚሰቀልባት፡
ቀን ፡ እንደሆነች ፡ ይተረጕማል ፤ ይችም ፡
ለአዳምና፡ለልጆቹ፡ለወገኖቹ፡በዚች፡ቀን፡
ድኅነት፡ሁናለችና።
፲፬፤ የሚረዳ፡እንደሌለ፡አይቼ፡በረድኤት፡የሚቀ
በልም ፡ እንደሌለ ፡ አውቄ ፡ አለ ፤ ይኸንን ፡
በጌታችን ፡በመከራው፡ጊዜ፡ከእርሱ፡ጋር፡
ያይደለ፡ሁሉም፡በእርሱ፡ላይ፡አንድ፡ሁነው፡
እንደተስማሙበት፡ይተረጕማል።
፲፭፤ ከዚህ፡ጊዜ፡አስቀድሞ፡ትምህርቱን፡ይሰሙ፡
ዘንድ፡ይመኙ፡ነበር።
፲፮፤ መከራ፡የሚቀበል፡እንደሌለ፡አወቅሁ፡አለ፤
ይኸንንም፡ዳግመኛ፡ስለ፡ሐዋርያት፡ይተረ
ጕማል ፤ ሁሉም ፡ ሸሽተዋልና ፡ ከዮሐንስ ፡
በቀር፡አንድም፡እንኳን፡የቀረ፡የለምና።

፲፯፤ የነቢያትም ፡ ቃል ፡ ይፈጸም ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡
ቦታው፡ይሄድ፡ዘንድ፡አዘዘው።
፲፰፤ ስለዚህ፡ጌታችን ፡እነሆ፡ጊዜው፡ይደርሳል፤
በደረሰም፡ጊዜ፡ከእናንተም፡ሁላችሁ፡እያን
ዳንዳችሁ ፡ በየቦታው ፡ ትበተናላችሁ ፤
ብቻዬን፡ትተዉኛላችሁ፤እኔ፡ግን፡ብቻዬን፡
አይደለሁም፤አብ፡ከእኔ፡ጋራ፡ነውና።
፲፱፤ በሥልጣኔ፡አድናቸዋለሁ፡አለ፤ይኸንንም፡
የጸናች፡ሥልጣኑ፡ገናና፡የሆነች፡ኃይሉ፡እን
ደሆነች፡ይተረጕማል።
፳፤ እግዚአብሔርን ፡ስለ፡አደረገልኝ፡ስጦታ፡
ሁሉ ፡ አመሰግነዋለሁ ፡ አለ ፤ ይኸንን ፡
ከሙታን፡ተለይቶ፡ስለተነሣበት፡ስለ፡ልዩ፡
ትንሣኤው፡ይተረጕማል።
፳፩፤ ስለዚህም፡ዳዊት፡ነፍሴን፡በሲኦል፡አትተዋ
ትምና፡ልጅህንም፡ሙስና፡መቃብርን፡ያይ፡
ዘንድ፡አሳልፈህ፡አትሰጠውምና፡አለ።
፳፪፤ ስለ፡ድኅነታችን፡ለእኛ፡ሲል፡የተሰቀለውን፡
ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ መዐቱን ፡
ከእኛ ፡ ያርቅ ፡ ዘንድ ፡ በቸርነቱም ፡ ይቅር ፡
ይለን፡ዘንድ፡እንለምነው።
እስከ፡ዘላለሙም፡ለእርሱ፡ክብር፡ምስጋና፡
ይሁን፡አሜን።

Scanned by CamScanner

በ፫፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

ዘኢሳይያስ፡ነቢይ፡በረከተ፡እምላኩ፡ትኩን፡
ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ምዕ፡፭፡፱-፲፮።

፱፡ ወእመኒ፡ አብዛኀክሙ፡ አብያተ፡ ይከውኑ፡
መዝበረ፡ ወእንዘ፡ ዐበይት፡ ወሠናያን፡
እሙንቱ፡አልቦ፡ዘይነብር፡ውስቴቶሙ።
፲፡ እስመ፡ኢያሰልጡ፡ዐሠርቱ፡ዕምደ፡አባዕር፡
ወኢይገብሩ፡አሐደ፡ጻሕበ፡ወዘዘርዐ፡ስድሰ፡
ያእቱ፡ሥልሰ።
፲፩፡ አሌ፡ሎሙ፡ለእለ፡ይገይሡ፡በጽባሕ፡ቤተ፡
መያሲ፡ ወይውዕሉ፡ ውስተ፡ ስታይ፡ ወያነ
ድዖሙ፡ወይን።
፲፪፡ ወይሰትይዎ፡ ለወይን፡ እንዘ፡ የኀልዩ፡
በመሰንቆ፡ ወበከበሮ፡ ወበዕንዚራ፡ ወኢይ
ኔጽሩ፡ግብረ፡እግዚአብሔር፡ ወኢይሬእዩ፡
ተግባረ፡እደዊሁ።

፲፫፡ ወበእንተ፡ዝንቱ፡ተፄወወ፡ሕዝብየ፡እስመ፡
ኢያእመርዎ፡ለእግዚአብሔር፡ወበዝኁ፡አብ
ድንቲሆሙ፡በረሀብ፡ወበጽምአ፡ማይ።
፲፬፡ ወአርሐበ፡ሞት፡ነፍሶ፡ወአብቀወ፡አፉሁ፡
ሲኦል፡ ከመ፡ ኢያትርፍ፡ ወይወርዱ፡
ውስቴቱ፡ክቡራን፡ወዐበይት፡ወአብዕልት፡
ወኃጥአን።
፲፭፡ ወየኀሥር፡ ሰብእ፡ ወየሐረትም፡ ዕጓለ፡
እመሕያው፡ወየኀሥራ፡አዕይንተ፡ዕቡያን።

፲፮፡ ወይትሌዓል፡ እግዚአብሔር፡ ጸባዖት፡
በጽድቅ፡ ወበርትዕ፡ ወይሴባሕ፡ አምላክ፡
ቅዱስ፡በጽድቅ፡ወበርትዕ።

ዘኢሳይያስ፡ነቢይ፡በረከተ፡እምላኩ፡ትኩን፡
ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ምዕ፡፶፡፬-፱።

፬፡ እግዚአብሔር፡እግዚእ፡ ወሀበኒ፡ ልሳነ፡
ጥበብ፡ ከመ፡ አእምር፡ ቃለ፡ ዘእነብብ፡
አንቅሀኒ፡ በጽባሕ፡ ወወሰከኒ፡ እዝነ፡ በዘእ
ሰምዕ።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፫፡ሰዓት።

የአምላኩ፡ በረከት፡ ከእኛ፡ ጋራ፡ ለዘላለሙ፡
ትኑርና፡ ነቢዩ፡ ኢሳይያስ፡ የተናገረው፡
ትንቢት፡ይህ፡ነው።

ምዕ፡፭፡፱-፲፮።

፱፡ ቤቶችን፡ አብዝታችሁ፡ ብትሠሩ፡ የፈረሱ፡
ይሆናሉ፤እነርሳቸውም፡ታላላቆችና፡ያማሩ፡
ሲሆኑ፡በውስጣቸው፡የሚኖር፡የለም።
፲፡ አሥር፡ጥማድ፡በሮች፡ግዳጅ፡አይፈጽሙም፤
አንድ፡ፊቀንም፡አይመሉም፤ስድስት፡ጫን፡
የዘራ፡ሰው፡ሦስት፡ጫን፡ያገባልና።
፲፩፡ ሲነጋ፡ወደ፡መሸተኛ፡ቤት፡ለሚገሠግሡ፡በመ
ጠጥም፡ቤት፡ለሚውሉ፡መጠጥ፡ልባቸውን፡
ለሚያነድዳቸው፡ሰዎች፡ወዮላቸው።
፲፪፡ በከበሮና፡በመሰንቆ፡እየዘፈኑ፡በገና፡እየደ
ረደሩ፡ወይንን፡ለሚጠጡት፡የእግዚአብሔ
ርንም፡ሥነ፡ፍጥረት፡ለማይመለከቱ፡እጁም፡
ያደረገችውን፡ ለማያስተውሉ፡ ሰዎች፡
ወዮላቸው።
፲፫፡ ስለዚህ፡ ወገኖቼ፡ እግዚአብሔርን፡
በአምልኮ፡ አላወቁትምና፡ ተማረኩ፤በውኃ፡
ጥምና፡በረኃብ፡አልቀው፡ሬሳቸው፡በዛ።
፲፬፡ ሞት፡ ሆዱን፡ አሰፋ፤ መቃብርም፡ እንዳይ
ስቀር፡አፉን፡ከፈተ፤ሹማምንትና፡ክቡራን፡
ድኆችና፡ባለጸጎችም፡ወደርሱ፡ይወርዳሉ።

፲፭፡ ሰውም፡ ይዋረዳል፤ የሰው፡ ልጅ፡ ይጐሰ
ቍላል፤ የትዕቢተኞች፡ ዐይኖችም፡ በሞት፡
ይፈስሳሉ።
፲፮፡ አሸናፊ፡እግዚአብሔር፡በእውነት፡በሚገባ፡
ከፍ፡ከፍ፡ይላል፤ልዩ፡ፈጣሪ፡የሆነ፡እግዚአ
ብሔርም፡በእውነት፡በሚገባ፡ይመሰገናል።

የአምላኩ፡ በረከት፡ ከእኛ፡ ጋር፡ ለዘላለሙ፡
ትኑርና፡ ነቢዩ፡ ኢሳይያስ፡ የተናገረው፡
ትንቢት፡ይህ፡ነው።

ምዕ፡፶፡፬-፱።

፬፡ የምናገረውን፡ ነገር፡ አውቅ፡ ዘንድ፡ ፈጥሮ፡
ገዥ፡የሚሆን፡እግዚአብሔር፡ጥበብን፡የምናገ
ርበትን፡አንደበት፡ይሰጠኛል፤ፈጥኖ፡አነቃኝ፤
ትምህርቱን፡ በማዳምጥበት፡ ገንዘብ፡ በዕዝነ፡
ሥጋ፡ላይ፡ዕዝነ፡ልቡናን፡ጨመረልኝ።

Scanned by CamScanner

በ፫፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

ወተማኅጸ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይከሥተኒ ፡
እዝንየ ፤ ወአንስ ፡ ኢይከህደኒ ፡ ወኢይትዋ
ኃለፍኩ።
መጠውኩ ፡ ዘባንየ ፡ ለመቅሠፍት ፡ ወመልታ
ሕቶየኒ ፡ ለጽፍዐት ፡ ወኢሜጥኩ ፡ ገጽየ ፡ እም
ኀፍረተ፡ምራቅ።
ወእግዚአብሔር ፡ እግዚእ ፡ ረዳኤ ፡ ኮነኒ ፡
በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ኢተኀፈርኩ ፤ ወረሰይኩ ፡
ገጽየ ፡ ከመ ፡ ኰኵሕ ፡ ጽኑዕ ፤ ወአእመርኩ ፡
ከመ ፡ ኢይትኀፈር ፡ እስመ ፡ አልጸቀ ፡ ዘያጸ
ድቀኒ።
መኑ፡ውእቱ፡ዘይትዋቀሠኒ፡ይምጻእ፡ኅቡረ፤
ወመኑ፡ውእቱ፡ዘይሳነነኒ፡ወዘይቀርበኒ።
ናሁ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይረድአኒ ፡ መኑ ፡
የሐሥም ፡ ላዕሌየ ፤ ናሁ ፡ ኵልክሙ ፡ ከመ ፡
ልብስ፡ትበልዩ፡ወከመ፡ፃፄ፡ዘይበልዕ፡ዕፀ፡
ከማሁ፡ትትበልዑ።

ዘኢሳይያስ፡ነቢይ፡በረከተ፡አምላኩ፡ትኩን፡
ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ምዕ፤፫፤፱–፲፭።

አሌ፡ላ፡ለነፍሶሙ፡እስመ፡መከሩ፡እኩየ፡
ምክረ፡ላዕለ፡ነፍሶሙ።

ወመከሩ፡እንዘ፡ይብሉ፡ንሥዐሮ፡ለጻድቅ፡
እስመ ፡ ዕፁብ ፡ ወክቡድ ፡ ውእቱ ፡ ለነ ፡
ወይእዜኒ፡ይብልዑ፡ማእረረ፡ምግባሮሙ።
አሌ፡ሎ፡ለኃጥእ፡በእከዩ፤ወበከመ፡ዕከየ፡
ግብረ፡እንደዊሆሙ፡ይረክቡ፡ሕዝብየ፡መኳ
ንንቲክሙ ፡ ያጽሕቡክሙ ፡ ወይሴለጣ ፡
ላዕሌክሙ፡አንስት።
አሊ፡ያስተበፅዑክሙ፡ያስሕቱክሙ፡ወይደ
መስሱ፡አሠረ፡እገሪክሙ።
ወባሕቱ፡ይእዜ፡ይትነሣእ፡እግዚአብሔር፡
ለኰንኖ፡ወያቀውሞሙ፡ለሕዝቡ፡ከመ፡ይት
ዋቀሦሙ።
ወይመጽእ፡እግዚአብሔር፡ለሊሁ፡ምስለ፡ሊቃ
ውንት፡ሕዝቡ፡ወምስለ፡መላእክቲሁ፤ወይ
ቤሉ፡አንትሙ፡አውዐይክሙ፡ወይንየ፡ወበር
በረ፡ነዳይ፡መላእክሙ፡ውስተ፡አብያቲክሙ።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፫፡ሰዓት።

፭፤ የእግዚአብሔርም፡ተግሣጽ፡ዕዝነ፡ልቡናየን፡
ይገልጥልኛል፤እኔስ፡ነቢይነቴን፡አልክድም፤
በሐሰትም፡ነገር፡አልከራከርም።
፮፤ ጀርባዬን፡ለግርፋት፡ፊቴን፡ለጽፋት፡ሰጠሁ፤
ምራቅንም፡ከማፈር፡የተነሣ፡ፊቴን፡አልመ
ለስኩም።
፯፤ ፈጥሮ፡ገዥ፡የሚሆን፡እግዚአብሔር፡ግን፡
ረዳት፡ሆነኝ፤ስለዚህም፡ነገር፡አላፈርሁም፤
ፊቴንም፡እንደ፡ጽኑ፡አለት፡አደረግሁ፤የሚ
ያነሣኝ፡እግዚአብሔር፡ደርሷልና፡ፈርሼ፡
እንዳልቀር፡አወቅሁ።
፰፤ የሚከራከረኝ፡ማነው? እስኪ፡አንድነት፡
ይምጣ፤የሚጣላኝ፡የሚቀርበኝስ፡ማነው።
፱፤ እነሆ፡እግዚአብሔር፡ይረዳኛል፤በእኔ፡ክፉ፡
ነገር፡የሚያደርግ፡ማነው?እነሆ፡ሁላችሁ፡
እንደ፡ልብስ፡ታረጃላችሁ፤ነቀዝ፡እንደ
በላው፡እንጨትም፡ትሆናላችሁ።

የአምላኩ፡በረከት፡ከእኛ፡ጋር፡ለዘላለሙ፡
ትኑርና፡ነቢዩ፡ኢሳይያስ፡የተናገረው፡
ትንቢት፡ይህ፡ነው።

ምዕ፤፫፤፱–፲፭።

፱፤ በሰውነታቸው፡መከራ፡ለማምጣት፡ክፉ፡
ምክርን፡መክረዋልና፡ለሰውነታቸው፡
ወዮላት።
፲፤ በእኛ፡ጭንቅ፡ነው፤ክቡድ፡ነውና፡ጻድቁን፡
እናጥፋው፡ብለው፡መከሩ፤አሁንም፡የሥራ
ቸውን፡ፍሬ፡ይብሉ።
፲፩፤ ለኃጢአተኛ፡ሰው፡በክፋቱ፡ወዮለት፤
ወገኖቼም፡እንደ፡እጃቸው፡ሥራ፡መጠን፡
መከራ፡ይቀበላሉ፤መኳንንቶቻችሁ፡ያስጨ
ንቋችኋል፤ሴቶችም፡በላያችሁ፡ይሠለጥናሉ።
፲፪፤ የሚያመሰግኑአችሁ፡ሰዎች፡ያስቷችኋል፤የእ
ግራችሁንም፡ፍለጋ፡ያጠፋሉ።
፲፫፤ ነገር፡ግን፡ዛሬ፡እግዚአብሔር፡ለመፍረድ፡
ይነሣል፤ይወቅሣቸው፡ዘንድ፡ወገኖቹን፡
በፊቱ፡ያቆማቸዋል።
፲፬፤ እሱ፡እግዚአብሔር፡ከአለቆችና፡ከሕዝቡ፡
አለቆች፡ጋር፡መጥቶ፡እናንተ፡ወይኔን፡አቃ
ጠላችሁ፤(ሕጌን)፡አፈረሳችሁ፤የድኃውንም፡
ገንዘብ፡በቤታችሁ፡መላችሁ።

Scanned by CamScanner

በ፫፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

፲፰፤ ለምንት፡ትገፍዕዎሙ፡ለሕዝብየ፡ወታስተ
ኀፍሩ፡ገጸ፡ነዳይ።

ዘሚክያስ፡ነቢይ፡በረከቱ፡እምላኩ፡ትኩን፡
ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ምዕ፯፡፱-፳።

፱፤ ተማኅጸ፡እግዚአብሔር፡እንሰ፡ተዐገሥኩ፡
እስመ፡አበስኩ፡ሎቱ፡እስከ፡ያጸድቀኒ፡
ፍትሕየ፡ወይገብር፡ሊተ፡ቅሥትየ፡
ወያገብአኒ፡ውስተ፡ብርሃን፡ወእሬእያ፡
ለጽድቁ።

፲፤ ወትሬኢ፡ጸላእትየ፡ወትለብስ፡ኀፍረተ፡
እንተ፡ትብለኒ፡አይቴ፡ውእቱ፡እግዚአ
ብሔር፡አምላክከ፡ወይሬእያ፡አዕይንትየ፡
ይእዜ፡ትከውን፡ከመ፡ጽንጕን፡ዘይከይዱ፡
ውስተ፡ፍኖት።

፲፩፤ ወታጠፍአኪ፡ይእቲ፡ዕለት፡ወትማስን፡
ሕገግኪ፡ይእተ፡ዕለተ፡ወይትዐጸዋ፡
አህጉርኪ፡ዕኑዓት።

፲፪፤ ወይትካፈልዎን፡ፋርስ፡ለአህጉርኪ፡
ጽኑዓት፡እምጢሮስ፡እስከ፡ፈለገ፡ሶርያ፡ወእ
ምባሕር፡እስከ፡ባሕር፡ወእምአድባር፡እስከ፡
አድባር።

፲፫፤ ወትማስን፡ምድር፡ምስለ፡ኵሉ፡ዘይነብራ፡
በእንተ፡እከየ፡ምግባሮሙ።

፲፬፤ ረዐይ፡ሕዝበከ፡በበትርከ፡ወነገደ፡አባግዐ፡
ርስትከ፡ወየኀድሩ፡ባሕቲቶሙ፡ወይትረዐዩ፡
ውስተ፡ያም፡ዘማእከለ፡ቀርሜሎስ፡ዘባሳን፡
ወገለዓድ፡ከመ፡አመ፡መዋዕለ፡ዓለም።

፲፭፤ ወበከመ፡መዋዕል፡ዘአመ፡ዐርገ፡እምግብጽ፡
ትሬእዩ፡መንክረ።

፲፮፤ ወይርአዩ፡አሕዛብ፡ወይትኀፈሩ፡በኵሉ፡
ኀይሎሙ፡ወይወድዩ፡እደዊሆሙ፡ዲበ፡
አፉሆሙ፡ወይጠይዐ፡እዘኒሆሙ።

፲፯፤ ወይልሕሱ፡መሬተ፡ከመ፡አርዌ፡ምድር፡
ወይቀምሑ፡ሐመደ፡ወይትከወሱ፡በው
ስተ፡ማዕገቶሙ፡ወይደነግፁ፡እምእግዚአ
ብሔር፡አምላክነ፡ያዐወይዩ፡ወይፈርሁ፡
እምኔሁ።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፫፡ሰዓት።

፲፰፤ ወገኖቼን፡ለምን፡ትበድሏቸዋላችሁ፤የድኃ
ውንስ፡ፊት፡ለምን፡ታሳፍራላችሁ፡ይላል።

የአምላኩ፡በረከት፡ከእኛ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፤
ትኑርና፡ነቢዩ፡ሚክያስ፡የተናገረው፤
ትንቢት፡ይህ፡ነው።

ምዕ፯፡፱-፳።

፱፤ እሱን፡በድያለሁና፡ፍርዴን፡እስኪፈር
ድልኝ፡ድረስ፡ነገሬንም፡እስኪያደርግልኝ፤
ድረስ፡እግዚአብሔር፡ያመጣብኝን፡መከራ፡
እኔ፡ታገሥኩ፤እርሱም፡ወደ፡ተድላ፤
ደስታው፡ይመልሰኛል፤እኔም፡ቸርነቱ፡ተደ
ርጋልኝ፡አያታለሁ።

፲፤ ፈጣሪህ፡እግዚአብሔር፡የት፡ነው፤
የምትለኝ፡ጠላቴ፡የኔን፡ተድላ፡ደስታ፤
አይተህ፡ኀፍረት፡ጕስቍልናን፡ትለብሳለህ፤
የእኔም፡ዐይኖቼ፡የአንተን፡ጥፋት፡ያያሉ፤
ዛሬ፡በመንገድ፡እንደሚረግጡት፡ጭቃ፤
ትሆናለህ።

፲፩፤ ያቺ፡ቀን፡አንቺን፡ታጠፋሻለች፤በዚያችም፡
ቀን፡ሕግሽ፡ሥርዓትሽ፡ትጠፋለች፤የጸኑ፡
አገሮችሽ፡ይዘጋሉ።

፲፪፤ የፋርስ፡ሰዎች፡ከጢሮስ፡እስከ፡ሶርያ፡ወንዝ፡
ድረስ፡ከባሕርም፡እስከ፡ባሕር፡ድረስ፡ከተራ
ሮችም፡እስከ፡ተራሮች፡ድረስ፡የጸኑ፡አገ
ሮችሽን፡ይካፈሉታል።

፲፫፤ ስለ፡ክፉ፡ሥራቸውም፡ምድር፡ከሚኖርባት፡
ሰው፡ሁሉ፡ጋራ፡ትጠፋለች።

፲፬፤ በሥልጣንህ፡ወገኖችህን፡ጠብቅ፤ርስትህን፡
የወረሱ፡የወገኖችህንም፡ወገን፡ጠብቅ፤
ብቻቸውን፡ይኖራሉ፤እንደ፡ቀድሞው፡ዘመን፡
የገለዓድና፡የባሳን፡ዕፃ፡በምትሆን፡በቀር
ሜሎስ፡መካከል፡ወደ፡ዛፉ፡ሁሉ፡ይሰማራሉ።

፲፭፤ አባቶቻችሁም፡ከግብጽ፡እንደወጡበት፡
ዘመን፡ተአምራቱን፡ታያላችሁ።

፲፮፤ አሕዛብም፡ይህን፡አይተው፡በሠራዊቶቻቸው፡
ሁሉ፡ያፍራሉ፤እጃቸውንም፡በአፋቸው፡ላይ፡
ያኖሩታል፤ጆሮአቸውንም፡ይቀቅራሉ።

፲፯፤ በምድር፡እንደሚሄድ፡እባብ፡መሬቱን፡
ይልሳሉ፤አመድንም፡ይቅማሉ፤በከባቢ
ጠራቸውም፡ይጠፋሉ፤ከፈጣሪያችን፡ከእግዚ
አብሔር፡የተነሣ፡ይደነግጣሉ፤ከእርሱም፡
የተነሣ፡ፈርተው፡ይጮሃሉ።

በ፲፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

፲፰ መኑ፡አምላክ፡ከማከ፡ዘያአትት፡ኃጢአተ፡ ወይትዓደ፡ አበሳሆሙ፡ ለእለ፡ ረከሱ፡ ወለእለ፡ተርፉ፡ወኢያጸንእ፡ስምዐ፡መዓቱ፡ እስመ፡ፈቃዴ፡ምሕረት፡ውእቱ።

፲፱ ይትመየጠነ፡ወይሣህለነ፡ወያስጥሞን፡ለኀጣውኢነ፡ወይወርዎ፡ውስተ፡ቀላየ፡ባሕር፡ ለአበሳነ።

፳ ወትሁብ፡ጽድቀ፡ለያዕቆብ፡ወሣህለ፡ለአብርሃም፡ በከመ፡ መሐልከ፡ ለአበዊነ፡ በመዋዕለ፡ትካት።

ዘኢዮብ፡ጻድቅ፡በረከተ፡አምላኩ፡ትኩን፡ ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ምዕ፡፳፱፡፳፩–፳፭።

፳፩ ወይሰምዑኒ፡ወያረምሙ፡በምክረ፡ዚአየ።

፳፪ ወኢይደግሙ፡በዲበ፡ነገርየ፡ወይትሐሠዩ፡ ሶበ፡እትናገሮሙ።

፳፫ ከመ፡ምድር፡ጽምእት፡እንተ፡ትሴፎ፡ ዝናመ፡ከማሁ፡እሙንቱሂ፡ለነገረ፡ዚአየ።

፳፬ ወኢይትአመኑ፡እመ፡ሠሐቁ፡ምስሌሆሙ፡ ወኢይወድቅ፡ብርሃነ፡ገጽየ።

፳፭ ኀሪሥየ፡ ፍናቶሙ፡ ነበርኩ፡ እንዘ፡ እኴንኖሙ፡ ወነበርኩ፡ ከመ፡ ንጉሥ፡ ባሕቲትየ፡ ወእንዘ፡ ይበክዩ፡ ይትናዘዙ፡ ብየ።

ምዕ፡፴፡፩–፫።

፩ ወይእዜሰ፡ትሑታን፡ይሥሕቁኒ፡ወዮምሰ፡ ይምዕዱኒ፡በባሕቲቶሙ፡እለ፡መነንክዎሙ፡ ለአበዊሆሙ፡ ወእለ፡ ኢሐሰብክዎሙ፡ ወኢከመ፡ከለባተ፡መራዕይየ።

፪ ወለምንት፡ ሊተ፡ ኃይለ፡ እደዊሆሙ፡ ወይመጽእ፡ላዕሌሆሙ፡ሞት።

፫ ወያስተፍእሙ፡እምረኃብ፡እንዘ፡ይልሕሱ፡ እለ፡ያመሥጡ፡እምነ፡በድው፡ትማልም፡ በሥራሕ፡ወበኀሣር።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፲፡ሰዓት።

፲፰፤ ከሞት፡የቀሩትንና፡በኃጢአት፡የረከሱትን፡ኃጢአታቸውን፡ የሚያስተሰርይ፡ በደላቸውን፡የሚሠውር፡እንዳንተ፡ያለ፡ፈጣሪ፡ማነው?እርሱ፡ይቅርታን፡ይወዳልና፡የቊጣውንም፡ምስክርነት፡አያጸናም።

፲፱፤ ከመዐት፡ ወደ፡ ምሕረት፡ ይመለስልናል፤ ይቅርም፡ ይለናል፤ በደላችንና፡ኃጢአታችንንም፡ወደ፡ባሕር፡ወርውሮ፡ያስጥምልናል።

፳፤ በቀድሞ፡ዘመን፡ለአባቶቻችን፡እንደ፡ማልህላቸው፡መጠን፡ለአብርሃም፡ይቅርታን፡ለያዕቆብም፡ቸርነትን፡ትሰጠዋለህ።

የአምላኩ፡በረከት፡ከእኛ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡ ትኑርና፡ጻድቁ፡ኢዮብ፡የተናገረው፡ይህ፡ነው።

ምዕ፡፳፱፡፳፩–፳፭።

፳፩፤ እኔን፡ፈጽመው፡ሰምተውኝ፡በእኔ፡ምክር፡ ጸጥ፡ይሉ፡ነበር።

፳፪፤ በእኔ፡ነገር፡ላይ፡ነገር፡አይጨምሩበትም፡ ነበር፤በተናገርኳቸውም፡ጊዜ፡ደስ፡ይላቸው፡ ነበር።

፳፫፤ የተጸማች፡ምድር፡ዝናምን፡ተስፋ፡እንድታደርገው፡እነርሱም፡የእኔን፡ነገር፡ተስፋ፡ ያደርጉት፡ነበር።

፳፬፤ ከእነርሱ፡ጋር፡በሳቅሁ፡ጊዜ፡አያምኑኝም፡ ነበር፤ተድላ፡ደስታዬም፡አልጠፋም፡ነበር።

፳፭፤ ሥራቸውን፡ መርምሬ፡ ልፈርድላቸው፡ ተቀምጬ፡ነበር፤ንጉሥ፡ብቻውን፡እንዲቀመጥ፡ ብቻዬን፡ ተቀምጬ፡ ነበር፤ መከራም፡ አግኝቷቸው፡ባዘኑ፡ጊዜ፡በእኔ፡ ይረጋጉ፡ነበር።

ምዕ፡፴፡፩–፫።

፩፤ ዛሬ፡ግን፡የተዋረዱ፡ሰዎች፡ይሥቁብኛል፤ ያላባቶቻቸውን፡የናቅኋቸው፡እነርሱንም፡ያላ ሰብኋቸው፡እንደ፡ውሻ፡መንጋዎችም፡የቈጠርኋቸው፡እነዚህ፡ዛሬ፡ለብቻ፡ይዘው፡ይመክሩኛል።

፪፤ ኃይለ፡ቃላቸውስ፡ለምኔ፡ነው? አሁንም፡ ሞት፡ይመጣባቸዋል።

፫፤ በፍጹም፡ መከራ፡ ተይዘው፡ ትናንት፡ በምድረ፡ በዳ፡ ይቆሙ፡ የነበሩ፡ እነዚህ፡ ከረኃብ፡የተነሣ፡እየተሰደዱ፡ይቀላውጣሉ።

Scanned by CamScanner

በ፫፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

፬፡ እለ ፡ ይዋሕዩ ፡ ወይስእሉ ፡ ወያስተፍእሙ ፡ እለ፡በተታሕሎ፡የሐይዉ ፡ ኀሡራን ፡ ወዐማ ዕያን ፡ ወጽኑሳን ፡ እምኵሉ ፡ ሠናይ ፡ እለ ፡ ሥርወ፡ዕፅ፡ይሜጽሩ፡እምዐቢይ፡ረኃብ።

፭፡ ተንሥኡ ፡ ላዕሌየ ፡ ሰረቅት ፡ እለ ፡ አብያቲሆሙ፡ውስተ፡ግበበ፡ኰኵሕ።

፮፡ ወይጸውዑ ፡ ማእከለ ፡ መጽአሞ ፡ ወይትኀብኡ፡ውስተ፡ሣዕረ፡ገዳም።

፯፡ አብድ ፡ ውሉድ ፡ ወአልቦሙ ፡ ስም ፡ እስመ ፡ ጥፉአን፡እምድር፡ወጥቡብ፡እንተ፡ጠፍአት፡እምድር።

፰፡ ወይእዜሰ፡መሰንቆ፡ኮንክዎሙ፡ወአነ፡መሐድምቶሙ።

፱፡ ወያስቈርሩኒ ፡ ወይርኅቁ ፡ እምኔየ ፡ ወኢይትሐከዩ፡ወሪቀ፡ምራቅ፡ውስተ፡ገጽየ።

ትርጓሜ፡ዘኢዮብ።

ወይሰምዑኒ ፡ እስከ ፡ ኀበ ፡ ይብል ፡ ውስተ ፡ ገጽየ።

፩፡ ይቤ፡መተርጉም፡ወይሰምዑኒ፡ወያረምሙ፡በምክረ፡ዚአየ፡ይተረጐም፡ዘንተ፡እስመ፡ሕዝበ፡አይሁድ፡ኮኑ፡ይኔጽሩ፡ምግባራተ፡መድኀን ፡ ወተአምራተ ፡ ወመድምማተ ፡ እንተ፡ኮነ፡ይገብሮን፡ወኮኑ፡ይትዔወሩ፡እምውእቱ፡ወኮነ፡ይመክሮሙ፡በዘቦቱ፡መድኃኒት፡ዚአሆሙ፡በብሂሎቱ፡ሎሙ፡እስመ፡ብርሃን፡ሀሎ፡ምስሌክሙ፡መዋዕለ፡ኅዳጠ፡ወሑሩ፡በብርሃን፡እምጣነ፡ብክሙ፡ብርሃን፡ከመ፡ኢይርከብክሙ፡ጽልመት።

፴፱፡ ይቤ ፡ ካዕበ ፡ ኀሡ ፡ መጻሕፍተ ፡ እስመ ፡ እማንቲ፡ስምዕ፡በእንቲአየ።

፴፯፡ ወይቤሎሙ ፡ ካዕበ ፡ ለእመሰ ፡ ኢገበርኩ ፡ ግብረ፡አቡየ፡ኢትእመኑ፡ብየ፡ወለእመሰ፡ኮንኩ፡ዘእገብር፡እመ፡ኪያየ፡ኢአመንክሙ፡በግብርየ፡እመኑ፡ከመ፡ታእምሩ፡ወትጠይቁ፡ከመ፡አነ፡በአብ፡ወአብ፡ብየ፡ወኢሰምዑ፡እምኔሁ፡ወኢተወክፉ፡ምክሮ።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፫፡ሰዓት።

፬፡ የሰውን ፡ ቤት ፡ የሚጐበኙ ፡ ሂደውም ፡ የሚለምኑ፡ቀላውጠውም፡ሲበሉ፡የሚኖሩ፡እነ ዚህ፡የጐሰቈሉ፡በደለኞች፡ናቸው፤ከጽኑ፡ረ ብም፡የተነሣ፡የዕንጨት፡ሥር፡የሚያላምጡ፤

፭፡ እነዚህ፡ከበጎ፡ነገሮች፡ሁሉ፡የተቸገሩ፡ናቸው፡ ቤታቸውን፡በገደል፡በዋሻ፡ያደረጉ፡እነዚህ፡ ሌቦች፡በእኔ፡በጠላትነት፡ተነሡብኝ።

፮፡ በደስክ፡መካከል፡ይጮኻሉ፤በምድረ፡በዳ፡ ቁያም፡ተሠውረው፡ይኖራሉ።

፯፡ ከዚህ፡ዓለም፡ጠፍተዋልና፡ከልቡናቸውም፡ ጥበብ፡ጠፍታለችና፡ለሰነፎች፡ልጆች፡ስ ስም፡የላቸውም።

፰፡ ዛሬ ፡ ግን ፡ መሰንቆ ፡ ሆንኋቸው ፤ መተረቻ ቸውም፡ሆኜአለሁ።

፱፡ እኔንም ፡ ተጸይፈው ፡ ከእኔ ፡ ይርቃሉ፤ በፊቴም፡ ምራቃቸውን ፡ እንትፍ ፡ ማለ ቸውን፡አይሰለቹም።

ወይሰምዑኒ ፡ ከሚለው ፡ ጀምሮ ፡ ውስተ፡ ገጽየ፡እስከሚለው፡ድረስ፤የጻድቁ፡የኢዮብ፡ ቃል፡ምሥጢራዊ፡ትርጓሜ፡ይህ፡ነው።

፩፡ ተርጓሚው ፡ እኔን ፡ ፈጽመው ፡ ሰምተውኝ፡ በኔ ፡ ምክንያት ፡ ጸጥ ፡ ይሉ ፡ ነበር ፡ አለ፡ የአይሁድ ፡ ወገኖች ፡ የመድኃኒታችንን፡ ሥራዎቹን፡እንደሚያዩና፡የሚሠራቸውን፡ አስደናቂ፡የሆኑ፡ተአምራቶቹንም፡አይተው፡ ከማመን፡ቸል፡እንደሚሉ፡እርሱም፡ጥቂት፡ ጊዜ ፡ ከእናንተ ፡ ጋር ፡ ብርሃን ፡ አለና፡ ከእናንተ፡ ጋር ፡ ብርሃን ፡ ሳለ ፡ ጨለማ፡ሳያገ ኛችሁ፡በብርሃን፡ተመላለሱ፡በማለቱ፡የሚ ድኑበትን፡ይመክራቸው፡እንደ፡ነበር፡ይተረ ጐማል።

፴፱፡ ዳግመኛም፡መጻሕፍትን፡መርምሩ፤እነርሱ፡ ስለ፡እኔ፡ምስክሮች፡ናቸውና፡አለ።

፴፯፡ ዳግመኛም፡እኔ፡የአባቴን፡ሥራ፡ካልሠራሁ፡ አትመኑብኝ፤ነገር፡ግን፡የምሠራ፡ከሆነ፡እኔ፡ በአብ ፡ አብም ፡ በእኔ ፡ ህልው ፡ እንደሆነ፡ ታውቁ ፡ ትረዱ ፡ ዘንድ ፡ በሥራዬ ፡ እመኑ፡ አላቸው፤ነገር፡ግን፡እነርሱ፡ትምህርቱንና፡ ምክሩን፡አልተቀበሉትም።

| በ፫፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ። | ዓርብ፡መዓልት፡በ፫፡ሰዓት። |
|---|---|
| ፬ ይቤ ፡ ወይትሐሠዩ ፡ ሶበ ፡ እትናገሮሙ ፡ ይተረጐም፡ዘንተ፡ከመ፡ኮኑ፡ይፈትዉ፡ነገሮ፡ ወይፈትዉ ፡ ካዕበ ፡ ከመ ፡ ይግበር ፡ በቅድሜሆሙ፡ተአምረ፡ከመ፡ይርአይዋ፡ወአኮ፡ ከመ ፡ ይእመኑ ፡ ቦቱ ፡ አላ ፡ በእንተ ፡ ፍትወታተ፡አልባቢሆሙ። | ፬፡ በምናገራቸው ፡ ጊዜ ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ፡ አለ ፤ ቃሉ ፡ እንደሚጥማቸው ፡ በፊታቸውም ፡ ተአምራት ፡ ያደርግላቸው ፡ ዘንድ ፡ እንደ ሚወዱ ፡ ይህንን ፡ ይተረጐማል ፤ ያምኑበት ፡ ዘንድ ፡ ያይደለ ፡ ልባቸውን ፡ ደስ ፡ እንዲለው ፡ ነው፡እንጂ። |
| ፭ እስመ፡ኮኑ፡ጽኑዓነ፡በአልባቢሆሙ፡እስመ፡ ጥቀ፡በነበ፡ኀለፍት፡ወአኮሰ፡ዘጽኑሐት። | ፭፡ በነዋሪ ፡ ነገሮች ፡ ያይደለ ፡ በኀላፊ ፡ ነገሮች ፡ ላይ፡ልቡናቸው፡እጅግ፡የጸና፡ነውና። |
| ፮ ወበእንተ፡ውእቱ፡ይቤሎሙ፡ **እግዚእ** ፡አኮ፡ ዘተኀሥሡኒ ፡ በእንተ ፡ ርእዮትክሙ ፡ ተአምራተ ፡ አላ ፡ በበሊዖትክሙ ፡ ኅብስተ ፡ ወጸጊቦትክሙ። | ፮፡ ስለዚህም ፡ **ጌታ** ፡ አይሁድን ፡ የምትፈልጉኝ ፡ ተአምራትን ፡ ስለ ፡ አያችሁ ፡ አይደለም ፤ እንጀራ ፡ ስለ ፡ በላችሁና ፡ ስለጠገባችሁ ፡ ነው ፡ እንጂ፡እንዳላቸው። |
| ፯ ወአምከሮሙ ፡ በቃሉ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ ተዓቀቡ፡ ወኢትትገበሩ ፡ ለመብልዕ ፡ ኀላፊ ፡ አላ፡ለመብልዕ፡ዘይነብር፡ለዓለም። | ፯፡ በቃሉም ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ እንደመከራቸው ፡ ተጠበቁ ፤ ለኀላፊው ፡ መብል ፡ አትድከሙ ፤ ለዘላለም ፡ ለሚኖር ፡ መብል ፡ ሥሩ ፤ ድከሙ ፡ እንጂ ፡ ብሎ። |
| ፰ ይቤ፡ኢየአምኑ፡አመ፡ሠሐቁ፡ምስሌሆሙ፤ ይተረጐም ፡ ዘንተ ፡ እስመ ፡ **እግዚእ** ፡ ኮነ ፡ ይትዋረድ፡ምስለ፡ሕዝበ፡አይሁድ፡ወይትናገሮሙ ፡ በተሣህሎ ፡ በዘይከውን ፡ እምነገር ፤ ወኢኮነ ፡ ከመ ፡ መምህራኒሆሙ ፤ ወምስለ ፡ ውእቱኒ፡ኮኑ፡ይፈቅዱ፡ውግረቶ። | ፰፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ በሳቅሁ ፡ ጊዜ ፡ አያምኑኝም ፡ ነበር ፡ አለ ፤ **ጌታችን** ፡ ራሱን ፡ ዝቅ ፡ አድርጎ ፡ ከአይሁድ ፡ ጋር ፡ ይቅርታ ፡ ባለው ፡ አነጋገር ፡ ይናገራቸው ፡ እንደነበር ፡ እንደ ፡ መምህሮቻ ቸውም ፡ እንዳይደለ ፡ ከዚህም ፡ ሁሉ ፡ ጋር ፡ ሊወግሩት፡እንደሚወዱ። |
| ፱ ወኮነ፡ይብሎሙ፡አርአይኩክሙ፡ብዙኃተ፡ ምግባራተ፡ሠናያተ፡ዘእምአቡየ፤ወበእንተ፡ አይ፡ምግባር፡ዘትዌግሩኒ። | ፱፡ እርሱም ፡ ከአባቴ ፡ ዘንድ ፡ የሆነ ፡ ብዙ ፡ መልካም ፡ ሥራዎችን ፡ አሳየኋችሁ ፤ ከእነርሱ፡በየትኛው፡ሥራ፡ትወግሩኛላችሁ፡ ይላቸው፡እንደነበር፡ይህንን፡ይተረጐማል። |
| ፲ ወኮነ ፡ መፍቀሬ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው ፡ ዘኢይፈቅድ ጥፍአተ ፡ ፍጥረቱ ፡ ይትዋረድ ፡ ምስሌሆሙ ፡ ለዝሉፉ ፡ ለሙ ፡ ምሕረት ፡ እምኔሁ። | ፲፡ ሰውን ፡ የሚወድ ፡ እርሱ ፡ የፍጥረቱን ፡ ጥፋት ፡ የማይወድ ፡ ሁልጊዜ ፡ ራሱን ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ ዝቅ ፡ አድርጎ ፡ ይመክራቸው ፡ ነበር ፤ ቢያውቁስ፡ኑሮ፡ድኅነታቸው፡ከእርሱ፡ነበር። |
| ፲፩ ይቤ ፡ ወኢይወድቅ ፡ ብርሃነ ፡ ገጽየ ፡ ይተረጐም፡ ከመ ፡ ኮነ ፡ ውእቱ ፡ ኀቤሆሙ ፡ ከመ፡አብ፡መስተሳልም፡ላዕለ፡ውሉዱ፡ዮጊ፡ ለእመ ፡ ረከበ ፡ እምኔሆሙ ፡ ዘየሐውር ፡ በብርሃን ፡ አው ፡ አሐደ ፡ በምግባር ፡ ብሩህ ፡ በቅድሜሁ፡ወኢሀሎ፡እንከ። | ፲፩፡ ተድላ ፡ ደስታዬ ፡ አልጠፋም ፡ ነበር ፡ አለ ፤ ልጆቹን ፡ እንደሚወድ ፡ አባት ፡ እነርሱን ፡ ይወዳቸው ፡ እንደነበረ ፡ ይተረጐማል ፤ ምንአልባት ፡ በሃይማኖት ፡ የሚጸና ፡ ቢገኝ ፡ ወይም ፡ ብሩህ ፡ በሆነ ፡ ምግባር ፡ በፊቱ ፡ የሚገኝ ፡ ቢኖር፡ብሎ፡ግን፡አልተገኘም። |
| ፲፪ ይቤ ፡ ወይእዜሰ ፡ ትሑታን ፡ ይሥሕቁኒ ፡ ይተረጐም ፡ ዘንተ ፡ ሐራ ፡ ጲላጦስ ፡ ወሐራ ፡ ሄሮድስ ፡ ወወዐልተ ፡ ካህናት ፡ ዘተዐገሠ ፡ እምኔሆሙ ፡ **መድኅን** ፡ ዘገብርዎ ፡ እምእኩያት፡ምግባራቲሆሙ፡በፈቃዱ። | ፲፪፡ ዛሬ ፡ ግን ፡ የተዋረዱ ፡ ሰዎች ፡ ይስቁብኛል ፡ አለ፤ ይህንንም ፡ የጲላጦስና ፡ የሄሮድስ ፡ ጭፍሮች ፡ የካህናትም ፡ ሎሌዎች ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ ከአደረጓቸው ፡ ክፉዎች ፡ ሥራዎች ፡ **መድኅን** ፡ በፈቃዱ ፡ እንደ ፡ ታገሠ ፡ ይህንን ፡ ይተረጐማል። |

Scanned by CamScanner

በ፫፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

፲፫፡ ይቤ ፡ እለ ፡ መነንክዎሙ ፡ ለአበዊሆሙ ፡
ይተረጐም፡ዘንተ፡ካህናተ፡አይሁድ፡ወመም
ሀራነ ፡ ሕግ ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ መነኖሙ ፡
ወአእተተ ፡ ክህነቶሙ ፡ ወወሀበ ፡ ለእለ ፡
የአምኑ፡ቦቱ።
፲፬፡ ይቤ፡አኅድጎሙ፡ይተረጐም፡ከመ፡ይሴስል፡
ውእቱ፡ወያርሕቆሙ፡እምኔሁ፡በአእምሮቱ፡
በእንተ፡ሐጸጸ፡እምነቶሙ፡ቦቱ።

፲፭፡ ይቤ፡ወኢየሐስቦሙ፡ወኢ፡ከመ፡ከለባተ፡
መራዕይ፡ይተረጐም፡እስመ፡ኮኑ፡ይሰመዩ፡
ኖሎተ፡ሕዝብ፡ወእለ፡ያስተርእዩ፡በእንቲ
ኣሆሙ፡በገሀድ፤ወኮና፡ኀቡዓቲሆሙ፡ከመ፡
ተዘላት።
፲፮፡ እስመ፡ኮኑ፡ያጸውርዎሙ፡ክቡዳተ፡ላዕለ፡
ኃጣውኢሆሙ ፡ ወእሙቱሰ ፡ ስጡማን ፡
ውስቴታ፡ወኢይገብሩ፡ምንተኒ፡እምኔሃ።

፲፯፡ ወቃሉ፡ለነቢይ፡ኢይደልዎሙ፡ይኩኑ፡ከመ፡
ከለባተ፡ኖሎት፡ይተረጐም፡ከመ፡ከለባተ፡
ኖሎት ፡ በእንተ ፡ ትምህርቶሙ ፡ ምስለ ፡
ኖሎት፡አጋእዝቲሆሙ፡ወዐቂቦቶሙ፡ሎሙ፤
እምከመ፡ርእዩ፡ዘኮነ፡እምነ፡መርዔቶሙ፡
ዘገደፉ፡አጋዕዝቲሆሙ፤እስመ፡ውእቶሙ፡
ይመክሩ፡በእንቲአሁ፡እምለፌ፡ወእምለፌ፡
ወያፈርህዎ ፡ ከመ ፡ ይሚጥዎ ፡ እስከ ፡
ያገብእዎ፡ኀበ፡መርዔት።

፲፰፡ ወካዕበ ፡ ውእቶሙ ፡ ይትገሁ ፡ በእንተ
መርዔት ፡ ከመ ፡ ኢይትመሠጥ ፡ ምንትኒ ፡
እምኔሆሙ፡ወኢይትሀጐል፡ምንትኒ።
፲፱፡ ወለእመ ፡ ኮኑ ፡ አራዊት ፡ ኀጡአነ ፡ ልቡና ፡
ወንባብ ፡ ወልሙዳን ፡ በግዕዘሙ ፡ ለበሊዐ ፡
ሥጋ፡እንስሳ፡ወዕጓለ፡እመሕያው፡ዐቀቡ፡
እንስሳሆሙ፡ዘተረክበ።
፳፡ ወለኖሎተ፡እስራኤልሰ፡በካልዕ፡እምዝንቱ፡
አኀሰ፡ከለባተ፡እምኔሆሙ።

፳፩፡ ይቤ፡ተንሥኡ፡ላዕሌየ፡ሰረቅት፡ይተረጐም፡
ዘንተ፡ከመ፡ተንሥኡ፡ላዕሌሁ፡ውእቶሙ፡
በቅድመ፡ጲላጦስ፡ወከልሑ፡ኵሎሙ፡እንዘ፡
ይብሉ፡ስቅሎ።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፫፡ሰዓት።

፲፫፡ አባቶቻቸውን ፡ የናቅኋቸው ፡ አለ ፤ የአይ
ሁድን፡ ካህናት ፡ የኦሪትንም ፡ መምህራን ፡
እርሱ ፡ ንቋቸዋልና ፤ ክህነታቸውንም ፡
ከእሳቸው፡አስወግዶ፡ለየሚያምኑበት፡እንደ፡
ሰጠ፡ይህንንም፤ይተረጕማል።
፲፬፡ እተዋቸዋለሁ ፡ አለ ፤ እምነተ ፡ ጎደሎዎች ፡
መሆናቸውን፡ስለሚያውቅ፡በረድኤት፡እንደ
ሚለያቸውና፡ከእርሱም፡እንደሚያርቃቸው፡
ይተረጕማል።
፲፭፡ እነርሱንም፡ያላሰብኋቸው፡እንደ፡ውሻም፡መን
ጋዎች፡የቈጠርኋቸው፡አለ፤ይህን፡እነርሱ፡
የሕዝቡ ፡ ጠባቂዎች ፡ እንደሆኑ ፡ በግልጥ ፡
ይታያሉ ፤ በውስጣቸው ፡ ግን ፡ ነጣቂ ፡ ተኩላ
ዎች፡ሁነው፡ይገኛሉ፡ብሎ፡ይተረጕማል።
፲፮፡ ሕዝቡን ፡ ተስፋ ፡ የሚያስቀርጥ ፡ በኃጢአ
ታቸው ፡ ላይ ፡ ከባድ ፡ ነገር ፡ ያሸክሟቸዋል ፡
እነርሱ ፡ ግን ፡ በኃጢአት ፡ ባሕር ፡ የሰጠሙ ፡
ሁነው፡ከበጎ፡ሥራ፡ምንም፡ምን፡አይሠሩም።
፲፯፡ እንደ፡ነቢዩ፡ቃል፡ከእረኞች፡ጋር፡የሚውሉ
ውሾችን ፡ ይሆኑ ፡ ዘንድ ፡ አይገባቸውም ፤
እረኞችን ፡ ስለሚከተሉ ፡ ውሾች ፡ ከጌቶ
ቻቸው፡ እረኞች ፡ ስለተማሩት ፡ ስለ ፡ ጥበቃ
ቸውም ፡ እንዲህ ፡ ይተረጕማል ፤ እነርሱ ፡
ጌቶቻቸው ፡ የጣሉትን ፡ ከመንጋው ፡ ውስጥ ፡
የባዘነና ፡ የጠፋ ፡ ያዩ ፡ እንደሆነ ፡ ስለ ፡ እርሱ ፡
ያስባሉ፤ወደ፡መንጋውም፡መልሰው፡እስከ
ገቡት ፡ ድረስ ፡ ከወዲያ ፡ ከወዲህ ፡ በመከበብ ፡
በማስፈራራት፡ያመጡታል።
፲፰፡ ዳግመኛም ፡ ከመንጋው ፡ ውስጥ ፡ ምንም ፡
ምን፡ በአውሬ ፡ ተነጥቆ ፡ እንዳይበላና ፡ እንዳ
ይጠፋ፡ተግተው፡ይጠብቃሉ።
፲፱፡ አእምሮና ፡ ቃል ፡ መናገር የሌላቸው ፡ በጠባ
ያቸው ፡ የሰውና ፡ የእንስሳ ፡ ሥጋ ፡ መብላትን ፡
የለመዱ ፡ ሲሆኑ ፡ እንስሶቻቸውን ፡ ጠብቀው ፡
ተገኙ።
፳፡ የእስራኤልን፡ጠባቆች፡ካህናተ፡አይሁድን፡
ግን ፡ በሌላ ፡ በኩል ፡ ውሾች ፡ ከእነርሱ ፡
እንዲሻሉ፡አስረዳ።
፳፩፡ ሌቦች ፡ ተነሡብኝ ፡ አለ ፤ ይህንንም ፡
በጲላጦስ፡ ፊት ፡ ሁሉም ፡ በጠላትነት ፡
ተነሥተው ፡ ስቀለው ፡ ስቀለው ፡ ብለው ፡
እንደጮኹ፡ይተረጕማል።

## በ፫፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

፳፪ ወበእንተዝ ፡ ሰመዮሙ ፡ ሰረቅተ ፡ እስመ ፡
ሰራቂ፡ብዙኃት፡ምኑናት፡ቦቱ፡ውስቴቱ።
፳፫ በከመ፡ይቤ፡እግዚእ፡ሎቱ፡ስብሐት፡እስመ፡
ኢይመጽእ፡ሰራቂ፡ዘእንበለ፡ዳእሙ፡ከመ፡
ይሰርቅ፡ወይቅትል፡ወያህጕል።
፳፬ ይቤ፡እለ፡አብያቲሆሙ፡ውስተ፡ኰኵሕ፡
ይተረጐም ፡ ዝከተ ፡ ልበሙ ፡ እብናዊተ ፡
እንተ፡ኢትለመልም።
፳፭ ይቤ፡አብድ፡ውሉድ፡ውእቱኬ፡በከመ፡ንቤ፡
ከመ፡ውእቶሙ ፡ ውሉደ ፡ ካህናት ፡ ወመም
ህራን፡እለ፡መነኖሙ፡እግዚአብሔር፡ወአር
ሐቆሙ።
፳፮ ይቤ፡ወጥበብ፡እንተ፡ጠፍአት፡እምድር፡
ይተረጐም፡ዘንተ፡እንተ፡ጠፍአት፡እሳተ፡
ሃይማኖት፡ዘውስቴቶሙ ፡ ወቈረት ፡ ከመ፡
ሐመድ፡በእንተ፡አቅሞ፡ፈቃዶሙ፡ወነደት፡
እሳተ፡ሃይማኖት፡ዘበክርስቶስ፡ውስተ፡አል
ባቢሆሙ፡ለምእመናን፡ቦቱ።

፳፯ ወበእንተዝ፡ይቤ፡ጳውሎስ፡ሐዋርያ፡እንዘ፡
ይኤዝዝ፡ለምእመናን ፡ ከመ ፡ ኢያጥፍኡ ፡
መንፈሰ፡ዘውስቴቶሙ ፡ ከመ ፡ እለ ፡ ኮኑ ፡
ምእመናን።
፳፰ ይቤ ፡ ያስቈርሩኒ ፡ ወይርሕቁ ፡ እምኔየ ፡
ይተረጐም፡ዘንተ፡ከመ፡ጸልእዎ፡ውእቶሙ፡
በእንተ ፡ ሕሊናሁ ፡ ዘኢይሰነዐው ፡ ምስለ ፡
ሕሊናሆሙ፤ወውእቱ፡መስተፃርር፡ሎሙ፡
ወመዝለፊሆሙ፡በእንተ፡ምግባራቲሆሙ፡
እኩያት፤ወጸልእዎ፡በእንተ፡እበዲሆሙ፡
እስመ፡ሰሎሞን፡ጠቢብ፡ይብል፡ዝልፎ፡
ለጠቢብ፡ከመ፡ይወስክ፡ጥበበ፡ወአብድሰ፡
ለእመ፡ገሠጽኮ፡ይጸልአከ።
፳፱ ይርሕቁ ፡ እምኔየ ፡ ይተረጐም ፡ ዘንተ ፡
ከሀደቶሙ፡ኪያሁ።
፴ ይቤ፡ወኢይትሀከዩ፡ወሪቀ፡ምራቅ፡ውስተ፡
ገጽየ፡ይተረጐም፡ዘንተ፡ዘኮነት፡በጊዜ፡
ሕማመ፡መድኀን፡ማሕየዊት፡እስመ፡
ነገሮ፡መንፈስ፡ቅዱስ፡ለነቢይ፡ዘኮነ፡ወዘ
ይከውን፡በውእቱ፡ጊዜ፤ወነበበ፡በእን
ቲአሁ።
፴፩ ወብሂሎቱ፡ኢያከበሩኒ፡እስመ፡ውእቶሙ፡

## ዓርብ፡መዓልት፡በ፫፡ሰዓት።

፳፪፤ ስለዚህም ፡ ሌቦች ፡ አላቸው ፤ ሌባ ፡ ብዙ ፡
የተሠረቁ፡ገንዘቦች፡ይገኙበታልና።
፳፫፤ የክብር ፡ ባለቤት ፡ ጌታችን ፡ ሌባ ፡ ሊሰርቅ ፡
ሊያርድ ፡ ሊያጠፋ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡
አይመጣም፡እንዳለ።
፳፬፤ ቤታቸውን፡በገደል፡ዋሻ፡አደረጉ፡አለ፤የማ
ትለመልም ፡ እንደ ፡ ደንጊያ ፡ የጸናች ፡
ልባቸው፡እንደሆነች፡ይህንን፡ይተረጕማል።
፳፭፤ ሰነፎች፡ልጆች፡አለ፤ይህንንም፡እንደ፡ተናገ
ርነው፡እግዚአብሔር፡የናቃቸውና፡ከእርሱ፡
ያራቃቸው ፡ የካህናቱና ፡ የመምህራኑ ፡
ልጆች፡እንደሆኑ፡ይተረጕማል።
፳፮፤ ከልቡናቸው ፡ ጥበብ ፡ ጠፍታለች ፡ አለ ፤
ይኸንንም ፡ ሐሳባቸውን ፡ ስለ ፡ ማጽናት ፡
ሃይማኖት ፡ እሳት ፡ ከውስጣቸው ፡ እንደ ፡
ጠፋች፤እንደ፡አመድም፡እንደ፡ቀዘቀዘች፤
በክርስቶስ ፡ ያመኑ ፡ ምእመናን ፡ ግን ፡
ሃይማኖት ፡ እሳት ፡ በውስጣቸው ፡ እንደ ፡
ጋለች፡ይተረጕማል።
፳፯፤ ስለዚህም፡ሐዋርያው፡ጳውሎስ፡አማንያን፡
የሆኑትን ፡ ረቂቅ ፡ እሳት ፡ ሃይማኖትን ፡
ከልባቸው፡እንዳያጠፉ፡እንዲህ፡ተናገረ።

፳፰፤ እኔንም ፡ ተጸይፈው ፡ ከእኔ ፡ ይርቃሉ ፡ አለ ፤
ይኸንንም ፡ ኀሳቡ ፡ ከኀሳባቸው ፡ ስለማይ
ስማማ፡እንደጠሉት፡ይተረጕማል፤እርሱ፡
ስለ፡ክፉ፡ሥራቸው፡የሚዘልፋቸውና፡የሚ
ጠላቸው፡ሁኖአልና፤ጥበበኛው፡ሰሎሞን፡
ብልህን ፤ ዕውቀትን ፡ ይጨምር ፡ ዘንድ ፡
ገሥጸው ፤ ሰነፍን ፡ ግን ፡ ብትገሥጸው ፡
ይጠላሃል ፡ እንዳለ ፤ ስለ ፡ ስንፍናቸው ፡
ጠሉት።
፳፱፤ ከእኔ፡ይርቃሉ፡አለ፤ይህንንም፡እርሱን፡ስለ፡
መካዳቸው፡ይተረጕማል።
፴፤ በፊቴም ፡ ምራቃቸውን ፡ እንትፍ ፡ ማለታ
ቸውን ፡ አይታክቱም ፡ አለ ፤ ሕይወት ፡
በምትሆን፡በመድኃኒታችን፡በሕማሙ፡ጊዜ፡
የሆነችውን፡ይተረጕማል፤መንፈስ፡ቅዱስ፡
የኾነውንና ፡ የሚሆነውን ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡
ለነቢዩ፡ገልጦለት፡ስለ፡እርሱ፡ተናግሮአልና።
ለነቢዩ፡ገልጦለት፡ስለ፡እርሱ፡ተናግሮአልና።
፴፩፤ አላከበሩኝም፡ማለቱም፡ከዚህ፡አስቀድሞ፡

Scanned by CamScanner

## በ፫፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

እምቅድመ፡ውእቱ፡ጊዜ፡ኮኑ፡ያከብርዎ፡ ወይሰምይዎ፡ መምህረ፡ ኄረ፡ ወፈቀዱ፡ ይረስይዎ፡ ንጉሠ፡ ወነጸፉ፡ አልባሲሆሙ፡ ታሕተ፡ሰኰናተ፡እደጉ።

፴፪፤ ወበዝንቱሰ፡ ጊዜ፡ ሰሰለት፡ ኀፍረት፡ እምኔሆሙ፡ ወያራ፡ አልባቢሆሙ፤ ወኮኑ፡ ሰካርያነ፡እምቅንዓት፡ወገብሩ፡ዘፈተወት፡ ልበሙ፡ወዘአምከሮሙ፡ሰይጣን።

፴፫፤ ወተዐገሠ፡ **እግዚእ**፡ ውእተ፡ ኵሎ፡ እምኔሆሙ፡ በእንተ፡ ውእቱ፡ ሥርዓት፡ ወፈጽሞ፡ትንቢተ፡ነቢያቲሁ።

፴፬፤ ወንህነሰ፡ንስአል፡ምሕረተ፡ዚአሁ፡ኵልነ፡ ከመ፡ ይሥረይ፡ ኃጣውኢነ፡ በስእለታ፡ **ለማርያም፡እግዝእትነ**፡ ወይዕቀበነ፡ እስከ፡ ለዝላፉ፡እምሰይጣን፡ፀርነ።

ሎቱ፡ ስብሐት፡ እስከ፡ ለዓለመ፡ ዓለም፡ አሜን።

### ትእዛዝ።

በሠለስቱ፡ሰዓት፡ዘዓርብ፡ይግበሩ፡ካህናት፡ ዐራተ፡ ወይክድኑ፡ በአልባስ፡ ወያልዕሉ፡ ሥዕለ፡ስቅለት፡ላዕለ፡መስቀል፡ወያቅሙ፡ መስቀለ፡ በየማኑ፡ ወበፀጋሙ፡ ወይንጽፉ፡ ጽጌ፡ረዳ፡ ወያንብሩ፡ ወንጌለ፡ ወያብርሁ፡ መባርህተ፡ሠምዕ፡ወይስቅሉ፡ማዕጠንታተ፡ ቅድመ፡ሥዕለ፡ስቅለት፡ወያሰርግዉ፡ቤተ፡ ክርስቲያን፡በአልባሰ፡ዲባጋት፡ወበክዳናተ፡ ጸሕል (ማህፈዳት)፤ ወያቅድሙ፡ ጸሎተ፡ ሠለስቱ፡ሰዓት፡ዘዕለተ፡ዐርብ።

**(ይካ)**፡ በዜማ፡ ግፍያሙ፡ **እግዚእ**፡ ለእለ፡ ይገፍዑኒ፤ጽብአሙ፡**እግዚእ**፡ ለእለ፡ይጸብኡኒ፤ ግፍያሙ፡**እግዚእ**፡ ለእለ፡ይገፍዑኒ፡፫፡ጊዜ፡ በል፡ **(ይሕ)**፡ ግፍያሙ፡ እግዚእ፡ ለእለ፡ ይገፍዑኒ፤ጽብአሙ፡**እግዚእ**፡ ለእለ፡ይጸብኡኒ፤ ግፍያሙ፡**እግዚእ**፡ ለእለ፡ይገፍዑኒ፡፫፡ጊዜ።

**(ይዲ)**፡ ወያንብብ፡ ዲያቆን፡ መዝሙረ፡ ዳዊት፡ዘ፴ወ፬፤በቃል፡ማኅዘኒ።

## ዓርብ፡መዓልት፡በ፫፡ሰዓት።

ያከብሩት፡ እንደነበር፡ ቸር፡ መምህርም፡ ብለው፡ እንዲጠሩት፡ ሊያነግሡትም፡ ወደው፡ ከአህያው፡ ሰኰና፡ በታች፡ ልብሳ ቸውን፡ያነጥፉ፡ነበር።

፴፪፤ በዚህ፡ ሰዓት፡ ግን፡ እርሱን፡ ማፈራቸው፡ ቀርቶ፡ ልቡናቸው፡ ታወረ፤ ከመቅናታ ቸውም፡የተነሣ፡በቅናት፡ሰክረው፡ሰይጣን፡ የመከራቸውን፡ልባቸውም፡የተመኘችውን፡ ፈጸሙ።

፴፫፤ **ጌታም**፡ የሥጋዌውን፡ ሥርዓት፡ የነቢያቶ ቹንም፡ ትንቢት፡ ስለ፡ መፈጸም፡ ከእነርሱ፡ ይህን፡ሁሉ፡ታገሠ።

፴፬፤ እኛ፡ግን፡ሁላችን፡ኃጢአታችንን፡ያስተሰርይ ልን፡ዘንድ፡የእርሱን፡ይቅርታ፡እንለምን፤**በእ መቤታችን፡ማርያም**፡ ልመናም፡ከጠላታችን፡ ሰይጣን፡እስከ፡ዘላለሙ፡ይጠብቀን፡ዘንድ።

ለእርሱ፡ እስከ፡ ዘላለሙ፡ ክብር፡ ምስጋና፡ ይሁን፡አሜን።

### ትእዛዝ።

ዐርብ፡ በሦስት፡ ሰዓት፡ ካህናቱ፡ አልጋ፡ ሠርተው፡ በልብስ፡ ይሸፍኑ፤ የስቅለቱንም፡ ሥዕል፡ በመስቀል፡ ላይ፡ ከፍ፡ አድርገው፡ ያቁሙ፤ በቀኝና፡ በግራ፡ ጽጌረዳ፡ ይነስንሱ፤ የወንጌልንም፡ መጽሐፍ፡ በአራቱ፡ ላይ፡ ያኑሩ፤ የሰም፡ መብራቶችንም፡ ያብሩ፤ በስቅለቱ፡ ሥዕል፡ ፊትም፡ ጽንሓሓዎችን፡ ይስቀሉ፤ በግምጃ፡ ልብሶችም፡ ቤተ፡ክርስቲ ያኑን፡ ያስጊጡ፤ ጸሕሎችንም፡ በመሸፈ ኛቸው፡ያስጊጡ።

ይበል፡**ካህን**፡ በዜማ፡**አቤቱ**፡ ሳልበድላቸው፡ የሚበድሉኝን፡ አጥፋቸው፤ ሳልጣላቸው፡ የሚጣሉኝን፡ **አቤቱ**፡ ተጣላቸው፤ ሳልገ ፋቸው፡ የሚገፉኝን፡ **አቤቱ**፡ ግፋቸው፤ **ሕዝቡም**፡ ይህንኑ፡ ቃል፡ ሦስት፡ ጊዜ፡ ይቀበሉ።

ከዚህ፡በኋላ፡**ዲያቆን**፡ መዝሙር፡ሠላሳ፡አራ ትን፡(በቃል፡ማኅዘኒ)፡በውርድ፡ንባብ፡ይበል፡

Scanned by CamScanner

በ፱፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

፩ ግፍዖሙ ፡ እግዚኦ ፡ ለእለ ፡ ይገፍዑኒ ፤
ጸብአሙ፡እግዚኦ፡ለእለ፡ይጸብኡኒ።
፪ ነሣእ፡ወልታ፡ወኲናተ፡ወተንሥእ፡ውስተ፡
ረዲኦትየ።
፫ ምላኅ፡ሰይፈከ፡ወዕግቶሙ፡ለእለ፡ሮዱኒ፤
በል፡ለነፍስየ፡አነ፡ውእቱ፡ረዳኢኪ።
፬ ለይትኀፈሩ ፡ ወይኅሥሩ ፡ ኵሎሙ ፡ እለ ፡
የኀሥሥዋ፡ለነፍስየ፤ለይግብኡ፡ድኅሬሆሙ፡
ወይትኀፈሩ፡እለ፡መከሩ፡እኩየ፡ላዕሌየ።
(ይ፡ካ)፡ግፍዖሙ፡(ይ፡ሕ)፡ከማሁ።

፭ ይ፡ዲ፡ለይኩኑ፡ከመ፡ጸበል፡ዘቅድመ፡ገጸ፡
ነፋስ፤ወመልአከ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለይሣ
ቅዮሙ።
፮ ለትኩን ፡ ፍኖቶሙ ፡ ዳኅፀ ፡ ወጽልመተ ።
ወመልአከ፡እግዚአብሔር፡ለይስድዶሙ ።
እስመ፡በከንቱ፡ኀብኡ፡ሊተ፡መሥገርተ፡
ያጥፍኡኒ።
፯ ወበከንቱ ፡ አመንዘዝዋ ፡ ለነፍስየ ፤ ለትም
ጽኦሙ ፡ መሥገርት ፡ እንተ ፡ ኢያእመሩ ።
(ይካ)፡ግፍዖሙ፡(ይሕ)፡ከማሁ።
፰ (ይዲ)፡ወተአኀዘሙ ፡ መሥገርት ፡ እንተ ፡
ኀብኡ፤
ወይደቁ፡ውስተ፡ይእቲ፡መሥገርት።
፱ ነፍስየሰ ፡ ትትፌሣህ ፡ በእግዚአብሔር ፤
ወትትሐሠይ፡በአድኅኖቱ።
፲ ኵሉ፡አዕፅምትየ ፡ ይብሉከ ፤ እግዚኦ መኑ ፡
ከማከ።
ታድኅኖ፡ለነዳይ፡እምእደ፡ዘይትዔገሎ።

(ይካ)፡ግፍዖሙ፡(ይሕ)፡ከማሁ።
፲፩ (ይዲ)፡ለነዳይ ፡ ወለምስኪን ፡ እምእደ ፡
ዘይመሥጦ።
ተንሥኡ፡ላዕሌየ፡ሰማዕተ፡ዐመፃ።
፲፪ ወዘኢየአምር፡ነበቡ፡ላዕሌየ።
ፈደዩኒ፡እኪተ፡ህየንተ፡ሠናይት።
፲፫ ወአኀጥእዋ፡ውሉደ፡ለነፍስየ።
ወአንሰ፡ሶበ፡አስርሑኒ፡ለበስኩ፡ሠቀ።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

፩ አቤቱ ፡ የሚበድሉኝን ፡ በድላቸው ፤ አቤቱ ፡
የሚጣሉኝን፡ተጣላቸው።
፪ ጋሻ ፡ ጦርህን ፡ ይዘህ ፡ እኔን ፡ ወደ ፡ መርዳት ፡
ተነሣ።
፫ ሰይፍህን ፡ መዘህ ፡ የከበቡኝን ፡ ክበባቸው ፤
ሰውነቴን፡ረዳትሽ፡እኔ፡ነኝ፡በላት።
፬ ሰውነቴን ፡ ለማጥፋት ፡ የሚሿት ፡ ሁሉ ፡
ይፈሩ፤ይዋረዱም።በእኔ፡ላይ፡ክፉ፡የመከሩ፡
ይፈሩ፤ወደኋላቸውም፡ይመለሱ።
ካህኑ ፡ ግፍዖሙ ፡ ይበል ፡ ሕዝቡ ፡ እንደሱ ፡
ይበሉ።
፭ ዲያቆኑ፡በነፋስ፡ፊት፡እንዳለ፡ትቢያ፡ይሁኑ።
የእግዚአብሔር ፡ መልአክም ፡ መከራ ፡ ያጽና
ባቸው።
፮ ጎዳናቸው፡ዳጥና፡ጨለማ፡ትሁንባቸው፤የእ
ግዚአብሔርም ፡ መልአክ ፡ ያሳድዳቸው ፤
በከንቱ ፡ ያጠፉኝ ፡ ዘንድ ፡ ወጥመዳቸውን ፡
ሸምቀው፡ብኛልና።
፯ ሰውነቴን ፡ በከንቱ ፡ አበሳጭተዋታልና ፤
ያላወቋት፡ወጥመድ፡ትምጣባቸው፡ይበል።
(ይካ)፡ግፍዖሙ፡(ይሕ)፡ከማሁ።
፰ ዲ፡የሸሸጓትም፡ወጥመድ፡ትያዛቸው።

በዚያች፡ወጥመድም፡ውስጥ፡ይውደቁ።
፱ ሰውነት ፡ ግን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ደስ ፡
ይላታል፡በማዳኑም፡ሐሤት፡ታደርጋለች።
፲ አጥንቶቼ ፡ ሁሉ ፡ አቤቱ ፡ እንዳንተ ፡ ማነው ፡
ይሉሃል።
ድኃውን ፡ ከሚቀማው ፡ እጅ ፡ ታድነዋለህ ፡
ይበል።
(ይካ)፡ግፍዖሙ፡(ይሕ)፡ከማሁ።
፲፩ ዲ ፡ ድሃውንና ፡ ችግረኛውን ፡ ከሚነጥቀው ፡
እጅ፡ታድነዋለህ።
የሐሰት፡ምስክሮች፡በእኔ፡ላይ፡ተነሡብኝ።
፲፪ በእኔ፡ላይም፡የማላውቀውን፡ነገር፡ተናገሩብኝ።
በጎ ፡ ስላደረግሁላቸው ፡ ፈንታ ፡ የክፉ ፡
ብድራት፡መለሱልኝ።
፲፫ ለሰውነቴም፡ልጆችን፡አሳጥዋት።
እኔ፡ግን፡በአደከሙኝ፡ጊዜ፡ማቅን፡ለበስኩ።

Scanned by CamScanner

በ፫፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

ወአሕመምክዋ፡በጾም፡ለነፍስየ።
፲፬፡ (ይካ)፡ግፍዖሙ፡(ይሕ)፡ከማሁ።
(ይዲ)፡ወጸሎትየኒ፡ገብአ፡ውስተ፡ሕፅንየ።
፲፭፡ ከመ ፡ ዘለአኀውየ ፡ ወለቢጽየ ፡ ከማሁ ፡
አድሎኩ።
ከመ ፡ ዘይላሑ ፡ ወይቴክዝ ፡ ከማሁ ፡
አትሐትኩ፡ርእስየ።
ተጋብኡ፡ላዕሌየ፡ወተፈሥሑ።
፲፮፡ ተማከሩ፡ይቅሥፉኒ፡ወኢያእመርኩ።

ተሰብሩኒ፡ወኢደንገፁ።
፲፯፡ ፈተኑኒ፡ወተሣለቁ፡ላዕሌየ፡ወሠሐቁኒ።

(ይካ)፡ግፍዖሙ፡(ይሕ)፡ከማሁ።
፲፰፡ (ይዲ)፡ወሐቀዩ፡ስነኒሆሙ፡ላዕሌየ።
እግዚኦ፡ማእዜኑ፡ትፌትሕ፡ሊተ።
አድኅና፡ለነፍስየ፡እምእከየ፡ምግባሮሙ።
ወእምአናብስት፡ለብሕቱትየ።
፲፱፡ እገኒ፡ለከ፡እግዚኦ፡በውስተ፡ማኅበር፡ዐቢይ።
ወእሴብሐከ፡በውስተ፡ሕዝብ፡ክቡድ።
፳፡ ወኢይትፈሥሑ ፡ ላዕሌየ ፡ እለ ፡ ይጸልዑኒ ፡
በዐመፃ።
(ይካ)፡ግፍዖሙ፡(ይሕ)፡ከማሁ።
፳፩፡ (ይዲ) ፡ እለ ፡ ይፃረሩኒ ፡ በከንቱ ፡ ወይትቃ
ጸቡኒ፡በአዕይንቲሆሙ።
እስመ፡ሊተሰ፡ሰላመ፡ይትናገሩኒ።
፳፪፡ ወይመክሩ፡በቍጽር፡ያመንስዉኒ።
ወአብቀዉ፡አፉሆሙ፡ላዕሌየ።
፳፫፡ ወይቤሉ ፡ ዕንቋዕ ፡ ዕንቋዕ ፡ ርኢናሁ ፡ በአዕይ
ንቲነ።
ርኢ፡እግዚኦ፡ ወኢታርምም።
እግዚኦ፡ኢትርሐቅ፡እምኔየ።
(ይካ)፡ ግፍዖሙ፡(ይሕ)፡ ከማሁ።
፳፬፡ (ይዲ) ፡ ተንሥእ ፡ እግዚኦ ፡ ወአጽምዕ ፡
ፍትሕየ።
አምላኪየ፡ወእግዚእየ፡ ውስተ፡ቅሥትየ።
፳፭፡ ፍታሕ ፡ ሊተ ፡ እግዚኦ አምላኪየ ፡ በከመ ፡
ጽድቅከ።
ወኢይትፈሥሑ፡ላዕሌየ።
ወኢይበሉ፡በልቦሙ፡ዕንቋዕ፡ዕንቋዕ፡ላዕለ፡
ነፍስየ።
፳፮፡ ወኢይበሉ፡ውኅጥናሁ።
ለይትኀፈሩ ፡ ወይኅሰሩ ፡ እለ ፡ ይትፌሥሑ ፡
በሕማምየ።
(ይካ)፡ ግፍዖሙ፡(ይሕ)፡ ከማሁ።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፫፡ሰዓት።

፲፬፡ ሰውነቴንም፡በጾም፡አደከምኋት፡ይበል።
(ይካ)፡ግፍዖሙ፡(ይሕ)፡ከማሁ።
፲፭፡ (ዲ)፡ ጸሎቴም ፡ ወደብብቴ ፡ ተመለሰ። ለወን
ድሞቼና ፡ ለባልንጀሮቼ ፡ እንዲሁ ፡ አደላሁ
ላቸው።
እንደሚያዝንና ፡ እንደሚያለቅስ ፡ እንዲሁ፡
ራሴን፡ዝቅ፡አደረግሁ።
በእኔ፡ላይ፡ተሰበሰቡ፡ደስም፡አላቸው።
፲፮፡ ይገርፉኝ፡ዘንድ፡መከሩብኝ፡እኔ፡ግን፡አላወ
ቅሁም።
ድል፡ተነሡ፡አልደነገጡም።
፲፯፡ ፈተኑኝ ፡ በእኔ ፡ ላይም ፡ ዘበቱ ፤ ሳቁብኝም፡
ይበል።
(ይካ)፡ግፍዖሙ፡(ይሕ)፡ከማሁ።
፲፰፡ (ዲ)፡ ጥርሶቻቸውን፡በእኔ፡ላይ፡አፏጩብኝ።
አቤቱ፡ የምትፈርድልኝ፡መቼ፡ነው።
ሰውነቴን፡ከክፉ፡ሥራቸው፡አድናት።
ብቸኝነቴን፡ከአንበሶች፡አድናት።
፲፱፡ አቤቱ፡ በታላቅ፡ማኅበር፡እገዛልሃለሁ።
በብዙ፡ጉባዔም፡አመሰግንሃለሁ።
፳፡ በአመፅ፡የሚጠሉኝም፡በእኔ፡ላይ፡ደስ፡አይ
በላቸው፡ይበል።
(ይካ)፡ግፍዖሙ፡(ይሕ)፡ከማሁ።
፳፩፡ (ዲ)፡ በከንቱ፡የሚጠሉኝ፡በዐይናቸው፡የሚ
ጠቃቀሱብኝ፡ደስ፡አይበላቸው።
ለእኔ፡ግን፡ሰላምን፡ይናገሩኛልና።
፳፪፡ በተቈጠረ፡ጠፍር፡ሊገርፉኝ፡ይመክሩብኛል።
አፋቸውንም፡በእኔ፡ላይ፡ከፈቱ።
፳፫፡ እሰይ ፡ እሰይ ፡ እነሆ ፡ ባይናችን ፡ ተዋርዶ፡
አየነው፡ይላሉ።
አቤቱ፤ እይ፤ ተመልከት፡ዝምም፡አትበል።
አቤቱ፡ ከእኔ፡በረድኤት፡አትራቅ፡ይበል።
(ይ፡ካ)፡ ግፍዖሙ፡(ይ፡ሕ)፡ ከማሁ።
፳፬፡ (ዲ) ፡ አቤቱ ፡ ተነሥ ፡ ፍርድንም ፡
አድምጥ።
ፈጣሪዬ፡ጌታዬ፡ በክርክሬ፡ጊዜ።
፳፭፡ አቤቱ ፡ ፈጣሪዬ ፡ እንደ ፡ እውነተኛነትህ፡
ፍረድልኝ።
በእኔ፡ላይም፡ደስ፡አይበላቸው።
በሰውነቴ፡ላይም፡በልባቸው፡እሰይ፡እሰይ፡
አይበሉ።
፳፮፡ እንደ፡ጥሀሎ፡ዋጥነው፡አይበሉ።
በእኔ ፡ መከራ ፡ ደስ ፡ የሚላቸው ፡ ይፈሩ፡
ይዋረዱ፡ይበል።
(ይ፡ካ)፡ ግፍዖሙ፡(ይ፡ሕ)፡ ከማሁ።

Scanned by CamScanner

በ፫፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

፳፯ (ዲ)፡ወይልበሱ፡ኀፍረተ፡ወኀሳረ፡እለ፡
የዐብዩ፡አፉሆሙ፡ላዕሌየ።

፳፰ ለይትፈሥሑ፡ወይትሐሰዩ፡እለ፡ይፈቅድዋ፡
ለጽድቅየ።

፳፱ ወይበሉ፡በኵሉ፡ጊዜ፡ዐቢይ፡እግዚአ
ብሔር።

እለ፡ይፈቅዱ፡ሰላመ፡ገብርከ።

፴ ልሳንየ፡ያነብብ፡ጽድቀከ።
ወኵሎ፡አሚረ፡ስብሐቲከ።
ስብሐት፡ለአብ፡ወወልድ፡ወመንፈስ፡
ቅዱስ፡ለዓለም፡ወለዓለመ፡ዓለም።

## ክፍል፡፪።

### ጸሎት፡ዘስምዖን፡ዐምዳዊ።

፩ አ፡እግዚእየ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ዘተወከፍከ፡
ጽፍዐተ፡ወምራቀ፡ላዕለ፡ገጽከ፡አሥርቅ፡
ላዕሌየ፡ሥነ፡ስብሐቲከ፡ዘይሠርቅ፡
እምውእቱ፡ገጽከ፡ዘተወክፈ፡ምራቀ፡
አምአፈ፡ርኩሳን።

፪ አ፡እግዚእየ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ዘመጦከ፡
ገጸከ፡ለእለ፡ይወርቁ፡ላዕሌከ፡ወይጸፍዑከ፡
እስእለከ፡ከመ፡ታሥርቅ፡ብርሃነከ፡ላዕለ፡
ገብርከ።

ዘይጼኑ፡መዐዛከ፡ወዘያሐዩ፡አንተ፡ውእቱ፡
አስካለ፡ሕይወት።

፫ አ፡እግዚእየ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡አሥርቅ፡
ውስተ፡ኅሊናየ፡ብርሃነከ፡አምላካዌ፡
ወሥረይ፡አበሳየ፡ወኃጢአትየ፡ዘገበርኩ፡
ወአድኅነኒ፡እምእኩይ፡ዘይፈቅድ፡ሀጕለ፡
ለነፍስየ፡ወረስየኒ፡እግበር፡ፈቃደከ፡ወእት
ቀደስ፡በስምከ፡ወእሕየው፡ብከ።

፬ አ፡መዝገበ፡ሠናያት፡ወሕይወት፤አ፡
እግዚእየ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ዘተወከፍከ፡
ዝብጠታተ፡ወቅሥፈታተ፡በእንተ፡አዳም፡
አድኅነኒ፡እመቅሠፍተ፡ጸላኢ፡ወእመሥ
ገርቱ፡ለእኩይ፡እስመ፡እምኀቤከ፡ውእቱ፡
መዊእ።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፫፡ሰዓት።

፳፯፤ (ዲ)፡በእኔ፡ላይም፡በአፋቸው፡የሚታበ
ዩብኝ፡ኀፍረትን፡ተዋርደው፡እንደ፡ሸማ፡
ይልበሱ።

፳፰፤ ድኅነቴን፡የሚወዱት፡ግን፡ፈጽሞ፡ደስ፡
ይበላቸው።

፳፱፤ ሁልጊዜም፡እግዚአብሔር፡ገናና፡አምላክ፡
ነው፡ይበሉ።

የአገልጋይህን፡ሰላም፡የሚወዱ፡ፈጽሞ፡
ደስ፡ይበላቸው።

፴፤ አንደበቴ፡ጽድቅህን፡ይናገራል።
ሁልጊዜም፡ምስጋናህን፡ይናገራል።
ለአብ፡ለወልድ፡ለመንፈስ፡ቅዱስ፡ምስጋና፡
ክብር፡ለዘላለሙ፡በእውነት፡ይገባል።

## ክፍል፡፪።

### የዓምዳዊ፡ስምዖን፡ጸሎት።

፩፤ በጥፊ፡መመታትንና፡ምራቅን፡በፊትህ፡የተ
ቀበልክ፡ጌታዬ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ሆይ፡
ከርኵሳን፡አፍ፡ምራቅን፡ከተቀበለው፡
ፊትህ፡የሚወጣውን፡የጌትነትህን፡ብርሃን፡
በእኔ፡ላይ፡አብራ።

፪፤ ለሚተፉብህና፡በጥፊ፡ለሚመቱህ፡ፊትህን፡
የሰጠህ፡ጌታዬ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ሆይ፡
በእኔ፡በባርያህ፡ላይ፡የጌትነትህን፡ብርሃን፡
ታበራ፡ዘንድ፡እለምንሃለሁ።
መዐዛህ፡የሚሸትና፡የሚያድን፡የሕይወት፡
ፍሬ፡አንተ፡ነህና።

፫፤ ጌታዬ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ሆይ፡በልቡናዬ፡
ውስጥ፡አምላካዊ፡ብርሃንህን፡አብራልኝ፤
የሠራሁትንም፡ኃጢአቴን፡በደሌን፡
አቃልልኝ፤ነፍሴን፡ለማጥፋት፡ከሚፈልግ፡
ከክፉ፡ጠላትም፡አድነኝ፤ፈቃድህን፡
የማደርግ፡በስምህም፡የምከብር፡በአንተም፡
ሕያው፡የምሆን፡አድርገኝ።

፬፤ የበጎ፡ነገርና፡የሕይወት፡መዝገብ፡የሆንከ፡
ጌታዬ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ሆይ፤ስለ፡አዳም፡
መደብደብን፡መገረፍን፡የተቀበልክ፡
ከጠላት፡ግርፋት፡ከክፉ፡ዲያብሎስ፡
ወጥመድም፡አድነኝ፤ድል፡አድራጊነት፡
ከአንተ፡ዘንድ፡ነውና።

Scanned by CamScanner

በ፲፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

፭፤ አ፡እግዚእየ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ዘጾርከ፡ዐምደ፡ወክበደ፡ዓለም፡ወአግዐዝከ፡ዓለመ፡እምግብርናት፡ወሜጥከ፡ኅበ፡ርስተ፡ሕይወት፡አግዕዘኒ፤ወሚጠኒ፡ኅቤከ፡በምሕረትከ።

፮፤ አ፡እግዚእየ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ዘተቀጸልከ፡አክሊለ፡ሦክ፡አስተቀጽለኒ፡አክሊለ፡መድኃኒት፡ወመዊእ።

፯፤ አ፡እግዚእየ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ዘአልበሱከ፡ልብሰ፡ለይ፡ለተሣልቆ፡አድኅነኒ፡እምሥላቀ፡ኃጢአት፡ወአልብሰኒ፡ስርጋዌ፡ሕይወት።

፰፤ አ፡እግዚእየ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ዘሰገዱ፡ለከ፡ማኅበረ፡አይሁድ፡እንዘ፡ይሣለቁከ፡ረስየኒ፡ከመ፡እስግድ፡ለከ፡በመንፈስ፡እትቀደስ፡ወእሕየው፡ብከ፡እስመ፡አንተ፡ውእቱ፡ሕያው፡ወቅዱስ።

፱፤ አ፡እግዚእየ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ዘመተሩ፡ላዕሌከ፡ፍትሐ፡ሞት፡እስመ፡አንተ፡ዘመጻእከ፡ከመ፡ታድኅኖ፡ለአዳም፡እምፍትሐ፡ሞት፡ዘምቱር፡ላዕሌሁ፡በእንተ፡ኃጢአቱ፡ፍትሐኒ፡እማእሰረ፡ኃጢአት፡ለገብርከ፡እኅሌ።

፲፤ አ፡እግዚእየ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ዘአጾሩከ፡መስቀለ፡ወአውጽኡከ፡እምኢየሩሳሌም፡ወወሰዱከ፡እስከ፡ጎልጎታ፡ከመ፡ትኩን፡መሥዋዕተ፤ረስያ፡ለነፍስየ፡ከመ፡ትኩን፡ለከ፡መሥዋዕተከ፡ወረስየኒ፡እጽልእ፡ለዝንቱ፡ዓለም፡ወአፍቅሮ፡ለስምከ፡ቅዱስ፡ወረስየኒ፡ካዕበ፡ድልወ፡ከመ፡እትልዎ፡በኵሉ፡ልብየ፡ወእትሉ፡በአሠርከ።

፲፩፤ አ፡እግዚእየ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ዘጾርከ፡መስቀለ፡ወሖርከ፡መካነ፡ጎልጎታ፡ከመ፡ትኩን፡መሥዋዕተ፡ወታግዕዝ፡ኵሎ፡ዓለመ፡ሀበኒ፡ከመ፡እጹር፡አርዑተ፡ኵሉ፡ትእዛዝከ፡ወእሑር፡ድኅረ፡አሠራቲከ፡ቅዱሳት፡ከመ፡እትቀደስ፡በኀቤሆሙ፡ወእሕየው፡በሙ፡ጸሎቱ፡ወበረከቱ፡የሀሉ፡ምስለ፡ኵልነ፡ሰማዕያን፡ወአንባብያን፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፲፡ሰዓት።

፭፤ ግንድ፡የተሸከምክ፡የዓለምንም፡ከቡድ፡ኃጢአት፡ተሸክመህ፡ከግዞት፡ዓለምን፡ነፃ፡ያወጣህ፡ወደ፡ሕይወት፡ርስትም፡የመለስክ፡ጌታዬ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ሆይ፤በቸርነትህ፡ወዳንተ፡በነፃነት፡መልሰኝ።

፮፤ የእሾህ፡አክሊል፡የተቀዳጀህ፡ጌታዬ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ሆይ፡የድልና፡የድኅነትን፡አክሊል፡አቀዳጀኝ።

፯፤ ለመዘባበቻ፡ቀይ፡ግምጃ፡ያለበሱህ፡ጌታዬ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ሆይ፡ለኃጢአት፡መዘባበቻ፡ከመሆን፡አድነኝ፤የሕይወትንም፡ሽልማት፡አልብሰኝ።

፰፤ የአይሁድ፡ማኅበር፡እየተዘባበቱ፡የሰገዱልህ፡ጌታዬ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ሆይ፡በመንፈስ፡እንድሰግድልህ፡በአንተም፡እንድከብር፡ሕያው፡እንድሆን፡አድርገኝ፤አንተ፡ሕያው፡ክቡር፡ነህና።

፱፤ ጌታዬ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ሆይ፤የሞት፡ፍርድን፡በአንተ፡ላይ፡የቆረጡብህ፡ስለ፡ኃጢአቱ፡ከተቆረጠበት፡የሞት፡ፍርድ፡አዳምን፡ልታድነው፡መጥተሃልና፡እኔ፡እኅሌ፡ባርያህን፡ከኃጢአት፡ማሠሪያ፡ፍታኝ።

፲፤ ጌታዬ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ሆይ፡መሥዋዕት፡ትሆን፡ዘንድ፡መስቀል፡አሸክመው፡ከኢየሩሳሌም፡አውጥተው፡እስከ፡ጎልጎታ፡የወሰዱህ፤መሥዋዕት፡ትሆን፡ዘንድ፡እንደ፡ወሰዱህ፡ሰውነቴ፡ለአንተ፡እንደ፡መሥዋዕት፡ሆና፡እንድትቀርብ፡አድርጋት፤ይህንንም፡ዓለም፡እጠላው፡ዘንድ፤ቅዱስ፡ስምህንም፡እወደው፡ዘንድ፤ዳግመኛም፡በፍጹም፡ልቡናዬ፡ስምህን፡አመሰግነው፡ዘንድ፡ፍለጋህንም፡እከተል፡ዘንድ፡ዝግጁ፡አድርገኝ።

፲፩፤ መሥዋዕት፡ሁነህ፡ዓለምን፡ሁሉ፡ነፃ፡ታወጣ፡ዘንድ፡መስቀል፡ተሸክመህ፡ጎልጎታ፡ወደሚባል፡ቦታ፡የሄድክ፡ጌታዬ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ሆይ፡እከብርባቸውና፡ሕያው፡እሆንባቸው፡ዘንድ፡የትዕዛዞችህን፡ሁሉ፡ቀንበር፡ተሸክሜ፡በተለዩ፡ፍለጋዎችህ፡ኋላ፡እሄድ፡ዘንድ፡ዕድልን፡ስጠኝ፤በአንባቢዎችና፡በሰሚዎች፡ላይ፡ልመናው፡በረከቱ፡ለዘላለሙ፡ይኑር፡አሜን።

Scanned by CamScanner

በ፲፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

ድርሳን ፡ ዘዮሐንስ ፡ አፈወርቅ ፡ ጸሎቱ ፡ ወበረከቱ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡ አሜን።

፩ ይቤ፡ሊቀ፡ካህናቲነሰ፡ምኩር፡በኵሉ፡ወበእ ንተዝ፡የአምር፡አቅዲሙ፡ዘይከውን፡ወቦቱ፡ ክሂል፡ከመ፡ይሳተፍ፡ሕማመነ።

፪ ይቤ ፡ ተመከረ ፡ በአምሳሊነ ፡ ዘእንበለ ፡ ኃጢአት።

፫ ነጸር፡አ፡ፍቁር፡ዘከመ፡ተብህለ፡ቀዳሚ፡ተዛ ውዖትነ፡ምስሌሁ።

፬ ወይእዜሰ፡አስተማሰለነ ፡ ቦቱ ፡ ወአግሀደ ፡ ከመ፡ውእቱ፡ተሰደ፡ወወረቁ፡ውስተ፡ገጹ፡ ወፀረፉ ፡ ላዕሌሁ ፡ ወሐመይዎ ፡ ከመ ፡ ይሰቅልዎ።

፭ ወብሂሎቱሰ ፡ በአምሳሊነ ፡ እንዘ ፡ አልቦ ፡ ኀጢአት፡ያኤምር፡ኀበ፡ክሂሎቱ፡ወከመ፡ ውእቱ፡ጾረ፡ኃጣውኢነ፡ወተዓገሠ፡ምንዳቤ፡ ወሐዘነ፡እንዘ፡አልቦ፡ኃጢአት።

ጸሎቱ፡ወበረከቱ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ ዓለም፡አሜን።

ድርሳን፡ዘቅዱስ፡ቄርሎስ።

፩ ጳላድዮስ፡ይቤ፡ወይብሉኬ፡መሐድምተ፡ ይመስል ፡ ዝ ፡ ነገር ፡ ዘይብል ፡ ሐመ ፡ ወኢሐመ፡እስመ፡ለእመ፡ኢሐመ፡አምላክ፡ ውእቱ ፡ ወእመ ፡ ሐመ ፡ እፎ ፡ ትብልዎ ፡ አምላክ፡ውእቱ።

፪ አላ ፡ ዘሐመ ፡ እምዘርዐ ፡ ዳዊት ፡ ውእቱ ፤ ይቤ ፡ ቄርሎስ ፡ ወእፎ ፡ ዝንቱ ፡ ኢኮነ ፡ ትዝልፍተ ፡ ሕሊና ፡ ስኡን ፡ ከመዝ ፡ አሚን።

፫ አስመ፡ኮነ፡ዘከመ፡አሐዱ፡እምኔነ፡ብእሲ፡ ዘመጠዎ፡እግዚአብሔር፡አብ፡በእንቲአነ፡ ማእከላይ፡ዘኀውሥ፡ላዕሌሁ፡ክብረ፡ወልድ፡ ወበተቃርቦ፡ክብሩ፡አላ፡ዘበእንቲአነ፡ኮነ፡ ከማነ።

፬ ዘላዕል፡እምኵሉ፡ፍጥረት፡እምሕላዌሁ፡

ዓርብ፡መዓልት፡በ፲፡ሰዓት።

ጸሎቱ ፡ በረከቱ ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ለዘላለሙ ፡ ይኑርና ፡ ዮሐንስ ፡ አፈ ፡ ወርቅ ፡ የደረሰው ፡ ድርሳን፡ይህ፡ነው።

፩፤ ሊቀ ፡ ካህናታችን ፡ ግን ፡ በሁሉ ፡ የተፈተነ ፡ ነው ፤ ስለዚህም ፡ የሚሆነውን ፡ አስቀድሞ ፡ ያውቃል፤መከራችንንም፡ሊቀበል፡ችሎታ፡ አለው።

፪፤ ደግሞ ፡ በእኛ ፡ አምሳል ፡ ሁኖ ፡ ከኃጢአት ፡ በቀር፡ተፈተነ፡አለ።

፫፤ ወዳጅ፡ሆይ፡አስቀድሞ፡ከእርሱ፡ጋር፡የተነ ጋገርነውምን፡እንደ፡ተባለ፡ተመልከት።

፬፤ ዛሬ፡ግን፡እንድንመስለው፡አደረገ፤እርሱ፡ እንደ፡ተሰደደ፤በፊቱም፡ላይ፡እንደተፉበት፤ እንደ ፡ ሰደቡት ፡ ይሰቅሉትም ፡ ዘንድ ፡ እንዳ ሰሩት፡ገለጸ።

፭፤ ኃጢአት ፡ ሳይኖርበት ፡ በእኛ ፡ አምሳል ፡ መከራ ፡ ተቀበለ ፡ ያለው ፡ ግን ፡ ችሎታውን ፡ ያመለክታል፤ኃጢአትም፡ሳይኖርበት፡ኃጢ አታችንን ፡ እንደተሸከመ ፡ መከራውን ፡ ሐዘኑንም፡እንደ፡ታገሠ፡ያመለክታል።

ጸሎቱ ፡ በረከቱ ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ለዘላለሙ ፡ ይኑር፡አሜን።

ቅዱስ፡ቄርሎስ፡የደረሰው፡ድርሳን፡ ይህ፡ነው።

፩፤ ጳላድዮስ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤ ታመመ ፤ አልታ መመም፡የሚሉት፡ነገር፡ተረት፡ይመስላል፤ የማይታመም፡ ከሆነ ፡ አምላክ ፡ ነው ፤ የሚታመም፡ከሆነ፡ግን፡እንዴት፡አምላክ፡ ነው፡ትሉታላችሁ፡ይላሉና።

፪፤ የታመመው፡ከዳዊት፡ዘር፡ነው፡ይላሉ፡እንጂ፤ ቄርሎስም፡እንዲህ፡ማለት፡በሥጋ፡ታመመ፡ በመለኮቱ፡አልታመም፡እንዲባል፡ማወቅና፡ መረዳት ፡ የተሳነው ፡ ልቡና ፡ ያስገኘውና ፡ ያነቃው፡ክህደት፡እንደምን፡አይደል?

፫፤ እግዚአብሔር ፡ አብ ፡ ስለ ፡ እኛ ፡ ለሕማም ፡ ለሞት፡አሳልፎ፡የሰጠውን፡እግዚአብሔር፡ ቃል ፡ መናፍቃን ፡ በጎድረት ፡ የከበረ ፡ ከእኛ ፡ እንደ ፡ አንዱ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ እንዲያምኑበት።

፬፤ እርሱም ፡ ከአብ ፡ ባሕርይ ፡ የተወለደ ፡

Scanned by CamScanner

በ፲፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

ለአብ፡ተወልደ፡ቃል፡ከመ፡ያስተርኢ፡ቤዛ፡
ለኵሉ፡ሕይወት፡እስመ፡መድኃኒት፡ውእቱ፡
ለዓለም ፤ ሕማማተ ፡ ፈቀደ ፡ ዘከሐከ ፡
እምሕማም፡በመለኮቱ።

፭፡ ተሠገወ ፡ ሥጋ ፡ እንተ ፡ ተሐምም ፡ ወእን
ቲአሁ፡ረሰየ፡ከመ፡ሕማማትሂ፡እሊአሁ፡
ይሰመይ ፤ እስመ ፡ ኢኮነ ፡ ዘካልእ ፡ ሥጋ ፡
ዘሐመ፡አላ፡ዚአሁ።

እምከመኬ፡በዛቲ፡ፍናት፡ትሥጉት፡ይትበሀል፡
፮፡ ሐመ፡በሥጋ፡ወኢሐመ፡በመለኮቱ።
ፈድፈደ ፡ ነገሮሙ ፡ ለዕልዋን ፡ ወኃይለ ፡
፯፡ ምሥጢር፡ዘእንበለ፡ጥበብ፡ይትሜየኑ፡ወይ
መስሎሙ ፡ ውዱሳን ፡ እሙንቱ ፡ እንዘ ፡
ይብሉ፡ይጼዐል፡እመ፡ንቤሎ፡በሥጋ፡ሐመ።

፰፡ አላ፡ለነሰ፡ለርቱዓን፡ክብር፡ወስብሐት።
፱፡ ወከመሰ፡ይኄይስ፡እሞት፡ወእሙስና፡እንዘ፡
ሕይወት፡ውእቱ፡ወማሕየዊ፡ከመ፡አምላክ፡
ሰማዕተ፡ኮኖ፡ትንሣኤ ፤ እስመ ፡ አንሥአ ፡
ሥጋሁ።

፲፡ ወይቤ፡ክቡር፡ጳውሎስ፡እስመ፡ኢየኀፍር፡
በወንጌል ፡ እስመ ፡ ኃይለ ፡ እግዚአብሔር ፡
ውእቱ፡ወመድኃኒት፡ለኵሉ፡ዘየአምን።

፲፩፡ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ ነገር ፡ ዘበመስቀል ፡ ለእለ ፡
ተሀጕሉ ፡ እበድ ፡ ውእቱ ፡ ወለነሰ ፡ ለእለ ፡
ንድኅን፡ኃይለ፡እግዚአብሔር፡ውእቱ።

፲፪፡ ወሎሙኒ፡ለአይሁድ፡ወለአረሚ፡ክርስቶስ፡
ኃይለ፡እግዚአብሔር፡ወጥበብ፡ውእቱ።

፲፫፡ ወዓዲ፡ውእቱኒ፡ወልድ፡እንዘ፡ሀሎ፡ይዕርግ፡
ውስተ፡መድኃኒት፡መስቀል፡ይቤ፡ይእዜ፡
ተሰብሐ፡ወልደ፡ዕጓለ፡እመሕያው፡እግዚአ
ብሔርኒ፡ይሴባሕ፡ቦቱ፡ወእግዚአብሔር፡
ይሴብሖ፡በርእሱ።

፲፬፡ ወሰቤሃ፡ይሴባሕ፡እስመ፡ተንሥአ፡ወዌወየ፡
ለሲኦል፡ወዘንተ፡ኢያርኀቀ፡ወኢያጕንደየ፡
እምሕማሙ።

በረከቱ፡ትኩን፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡
አሜን።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፲፡ሰዓት።

ከፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ በላይ ፡ የሆነ ፡ እርሱ፡
ለዓለሙ፡ሁሉ፡መድኃኒት፡ነውና ፤ ቤዛ፡ሆኖ፡
ይገለጥ ፡ ዘንድ ፡ ለሰው ፡ ሁሉ ፡ ሕይወት፡
ሊሆን፡ ከመለኮቱ ፡ ባሕርይ ፡ ወዷያ ፡ የራቀ፡
ሕማምን፡ወዶ፡ተቀበለ፡እንጂ።

፭፡ የሚታመም ፡ ሥጋን ፡ ተዋሕዶ ፡ ሰው ፡ ሆነ፤
ባሕርየ ፡ ሰብእንም ፡ ከባሕርየ ፡ መለኮቱ፡
አንድ ፡ አደረጋት ፤ ሕማማት ፡ ገንዘቡ፡
ይሆኑ፡ ዘንድ ፡ መከራ ፡ የተቀበለው ፡ ሥጋ፡
የሌላ፡ያይደለ፡የራሱ፡ነው፡እንጂ።

፮፡ እንዲህም፡ከሆነ፡እንግዲህ፡በሥጋ፡ታመመ፡
በመለኮቱ፡አልታመመም፡ይባላል።

፯፡ የመናፍቃንም ፡ ነገራቸው ፡ ብዙ ፡ ነው፤
የኃይለ ፡ ቃሉንም ፡ ምሥጢር ፡ አያስተ
ውሉም፤ እኛ ፡ በሥጋ ፡ ታመመ ፡ ብንለው፡
ስድብ፡ነው፤እያሉ፡እነርሱ፡ያከበሩ፡የሚመ
ስላቸው፡ያለዕውቀት፡ይተናኰላሉ።

፰፡ ለእኛ፡ለቅኖች፡ግን፡ክብር፡ጌትነት፡ነው።
፱፡ አምላክ ፡ ነውና ፤ ሕይወትና ፡ አዳኝ፡ሲሆን፡
ከሞትና፡ከጥፋት፡ሥልጣኑ፡እንደሚሻልና፡
እንዲበልጥ ፡ ትንሣኤው ፡ ምስክር ፡ ሆነው፤
ሥጋውን፡አንሥቷልና።

፲፡ የከበረ፡ጳውሎስ፡ለሚያምን፡ሁሉ፡የእግዚአ
ብሔር፡ኃይል፡ሕይወት፡መድኃኒት፡ነውና፡
በወንጌል፡አላፍርም፡አለ።

፲፩፡ ዳግመኛም ፡ ክርስቶስ ፡ መከራ ፡ የመቀበሉ፡
ነገር፡ባላመኑ፡ሰዎች፡ዘንድ፡ስንፍና፡ነው፤
ባመን ፡ በእኛ ፡ ዘንድ ፡ ግን ፡ የእግዚአብሔር፡
ኃይል፡ነው።

፲፪፡ ለእነርሱም፡ለአይሁድና፡ለአረሚ፡ቢያምኑ፡
ክርስቶስ፡የእግዚአብሔር፡ኃይል፡ጥበብም፡
ነው።

፲፫፡ ደግሞ፡ራሱ፡ወልድ፡ወደ፡አዳኝ፡መስቀል፡
ሊወጣ ፡ ሳለ ፡ ዛሬ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ክርስቶስ፡
ተመሰገነ፤ተገለጸ፤እግዚአብሔርም፡ይመሰ
ንበታል ፤ እግዚአብሔርም ፡ ደግሞ ፡ በራሱ፡
ይገልጸዋል ፡ አለ ፤ በመስቀል ፡ በትንሣኤ፡
በዕርገት።

፲፬፡ ተነሥቶ፡ሲኦልን፡በዝብዟታልና፤ያን፡ጊዜ፡
በክብር ፡ በጌትነት ፡ ይገለጣል ፤ ይኸንም፡
ከሕማሙ፡አላራቀውም፡አላዘገየውም።

በረከቱ ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ለዘላለሙ ፡ ትኑር፡
አሜን።

Scanned by CamScanner

በ፫፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

ድርሳን፡ዘቅዱስ፡አትናቴዎስ፡ሐዋርያዊ፡ ሊቀ፡ጳጳሳት፡ዘሀገረ፡እስክንድርያ።

ምዕ፤፴፤፴፩—፴፬።

፴፩ ወሰሎሙ፡አበዊነ፡መሀሩነ፡እንዘ፡ይብሉ፡ እስመ፡ሥጋ፡ኢኮነ፡ቃለ፡በሕላዌሁ፡አላ፡ ውእቱ፡ሥጋሁ፡ለቃል፤ወለውእቱ፡ሥጋ፡ ገሰሰ፡ቶማስ፡ድኅረ፡ተንሥአ፡እምነ፡ ምውታን፡ወርእየ፡ውስቴቱ፡አሠረ፡ ቅንዋት፡ዘተዓገሠ፡ቃል፡እንዘ፡ቅንው፡ በሥጋሁ።

፴፪ ወእምከሀለ፡ከመ፡ኢይትቀኖ፡ሥጋሁ፡ ውስተ፡ቅንዋት፤ወባሕቱ፡ቃል፡ዘኢኮነ፡ ሥጋ፡በሕላዌሁ፡ሐሰበ፡ሕማመ፡ሥጋሁ፡ ሎቱ፡ወከማሁ፡ሶበ፡ጸፍዖ፡ሐራዊ፡ መልታሕቶ፡ሥጋዌ፡ይቤሎ፡ቃል፡ ተዋሒዶ፡ምስለ፡ሥጋሁ፡ለምንትኑ፡ ትዘብጠኒ፡ረሰዮ፡ሕማመ፡ሥጋሁ፡ሎቱ።

፴፫ ወዘኢይትረከብ፡በሕላዌሁ፡ይቤ፡ መጠውኩ፡ዘባንየ፡ለቅሥፈት፡ወመልታ ሕቴየ፡ለጽፍዐት፤ወኢሜጥኩ፡ገጽየ፡እምኀ ፍረተ፡ምራቅ።

፴፬ ወኵሎ፡ሕማመ፡ዘበጽአ፡ላዕለ፡ሥጋሁ፡ ለቃል፡ኮነ፡ቃል፡ይትዌከፎ፡ከመ፡ዘሎቱ፡ ተዋሒዶ፡ምስለ፡ሥጋሁ፡ከመ፡ንሕነኒ፡ ንክሀል፡ንሳተፍ፡መለኮቶ፡ለወልድ።

ምዕ፤፹፫፤፩—፫።

፩ ወካዕበ፡ይቤ፡በውስተ፡ድርሳኑ፡ዘደረሰ፡ በእንተ፡ሕማሙ፡ማሕየዊት፡ወጥንቱ፡ ቅዱስ፡ያዕቆብ፡ኤጲስቆጶስ፡ዘሀገረ፡ሥሩግ፡ ኦ፡ወልደ፡እግዚአብሔር፡ሕያው፡ቃል፡ ዘኮነ፡መሥዋዕተ፡በእንተ፡ኀጣውኢነ።

፪ ፈጠረ፡ሎቱ፡እንግድዓ፡በከርሠ፡ድንግል፡ ከመ፡በቱ፡ትጹሮ፡ድንግል፡በዘተአምር፡ ምሥጢር፡ፆሮ፡በእንግድዓሁ፡ለበግዕ፡ ዘተሀጕለ፡ወማሰነ፤ወጾሮ፡በእንግድዓሁ፡

ዓርብ፡መዓልት፡በ፫፡ሰዓት።

የእስክንድርያ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡ሐዋርያዊ፡አት ናቴዎስ፡የደረሰው፡ድርሳን፡ይህ፡ነው።

ምዕ፤፴፤፴፩—፴፬።

፴፩፤ አባቶቻችንም ሁሉ፤ሥጋ፡በባሕርዩ፡ቃል፡ አይደለም፤ቃል፡የነሣው፡ሥጋ፡ነው፡እንጂ፡ ብለው፡አስተማሩን፤ይህንንም፡ሥጋ፡ ከሙታን፡ተለይቶ፡ከተነሣ፡በኋላ፡ቶማስ፡ ዳሰሰው፤በሥጋው፡ሲቸነከር፡ቃል፡ታግሦ፡ የተቀበለውን፡የችንካሩን፡እትራትም፡ በእርሱ፡አየ።

፴፪፤ ሥጋውም፡በችንካር፡እንዳይቸነከር፡ ማድረግ፡በተቻለው፡ነበር፤በባሕርዩ፡ሥጋ፡ ያልነበረ፡ቃል፡ሥጋን፡ስለ፡ተዋሐደ፡ የሥጋ፡ሕማምን፡ለእርሱ፡ገንዘብ፡አደረገ፡ እንጂ፤እንደዚሁም፡ሐራዊ፡ሥጋዊ፡ፊቱን፡ በጥፊ፡በመታው፡ጊዜ፡ቃል፡ከሥጋው፡ጋር፡ አንድ፡ሁኖ፡ለምን፡ትመታኛለህ፡አለው፤ የሥጋውን፡ሕማም፡ለርሱ፡ገንዘብ፡አድርጎ።

፴፫፤ በባሕርዩ፡የማይመረመር፡እርሱ፡ጀርባዬን፡ ለግርፋት፡ፊቴን፡ለጽፋት፡ሰጠሁ፤ከሚያ ሳፍር፡ምራቅም፡ፊቴን፡አልመለስኩም፡ አለ።

፴፬፤ ቃል፡በተዋሐደው፡ሥጋ፡የተደረገ፡ሕማምን፡ ሁሉ፡ከሥጋ፡ጋር፡ተዋሕዶ፡የርሱ፡ገንዘብ፡ እንደሆነ፡አድርጎ፡ቃል፡ይቀበለው፡ነበር፤ እኛም፡የወልድ፡መለኮትን፡መምሰልን፡ ገንዘብ፡እናደርግ፡ዘንድ።

ምዕ፤፹፫፤፩—፫።

፩፤ የሥሩግ፡ኤጲስቆጶስ፡ቅዱስ፡ያዕቆብ፡ስለማ ኀየዊት፡ሕማሙ፡በደረሰው፡ድርሳን፡ ዳግመኛ፡እንዲህ፡አለ፤ኃጢአታችንን፡ለማስ ተሥረይ፡መሥዋዕት፡የሆነ፡የእግዚአ ብሔር፡የባሕርይ፡ልጅ፡ሕያው፡ቃል፡ወዮ! ምን፡ይደንቅ።

፪፤ በምታውቀው፡ምሥጢር፡ድንግል፡ ታዝለው፡ታቅፈው፡ዘንድ፡በድንግል፡ ማሕፀን፡ለርሱ፡ደረትን፡ፈጠረ፤በፍዳ፡ ተይዞ፡ተጎድቶ፡የነበረ፡የአዳምን፡ባሕርይ።

Scanned by CamScanner

## በ፲፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

ለረድእ፡ዘያፈቅሮ።

፲፩፤ ዘአልቦቱ፡ሥጋ፡ነሥአ፡አባለ፡ሶበ፡ተሠገወ፤ ወቦቱ ፡ አኀዝዎ ፡ ከመ ፡ ይፈጽሙ ፡ መፍቅዶሙ።

ፈጠረ ፡ አፈ ፡ ወምራቀ ፡ ከመ ፡ ይክሥት ፡ አዕይንተ፡ዕውራን፡ወልሳነ፡ፈጠረ፡ከመ፡ ይስድድ፡አጋንንተ፡ወያውጽአሙ፡ክልኤተ፡ መዛርዓ ፡ ከመ ፡ ይሕቅፍ ፡ ቦሙ ፡ ዐምደ ፡ በውስተ፡ዐውደ፡ፍትሕ።

፲፪፤ ወዓዲ፡ዘባነ፡ፈጠረ፡ከመ፡ይትወከፍ፡ቦቱ፡ ቅሥፈተ፡እምነ፡መኰንን።

፲፫፤ ፈጠረ ፡ ሎቱ ፡ እንግድዓ ፡ ከመ ፡ ይጹሮ ፡ ለረድእ ፡ ድንግል ፤ ወበጽሐ ፡ ኀበ ፡ ኵሉ ፡ ግብር፡ከመ፡ያግዕዘነ።

በረከቶሙ ፡ ለእሉ ፡ መምህራን ፡ የሀሉ ፡ ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

በስመ፡አብ፡ወወልድ፡ወመንፈስ፡ቅዱስ፡ አሐዱ፡አምላክ።

፲፬፤ ድርሳን ዘደረሰ፡አባ፡ያዕቆብ፡ኤጲስቆጶስ፡ ዘሥሩግ፡በእንተ፡አብርሃም፡አቡነ፡ዐርከ፡ እግዚአብሔር ፡ ወበእንተ ፡ አቅርቦቱ ፡ ይሥሐቅሃ፡ወልዶ።

፲፭፤ ወእፎ ፡ ቤዘዎ ፡ እግዚአብሔር ፡ በበግዕ ፡ በሰላመ፡እግዚአብሔር፡አሜን።

፲፮፤ ለምሥጢርከ ፡ ዐባይ ፡ አ ፡ ወልደ ፡ እግዚአ ብሔር፡ኅሊናየ፡ይፈቅድ፡ያእምራ።

፲፯፤ ሀበኒ፡እንከ፡አእምሮ፡ከመ፡እክሥታ፡ለሰማ ዕያን፡ይትፈሥሑ፡ባቲ።

፲፰፤ ሐዘነ ፡ ሞትከ ፡ ይጼውዐኒ ፡ ከመ ፡ እንግር ፡ ዜናከ ፤ ሀበኒ ፡ ሊተ ፡ ኀይለ ፡ ከመ ፡ እሑር ፡ በውስተ፡ድርሳንከ፡በዘይደሉ።

## ዓርብ፡መዓልት፡በ፲፡ሰዓት።

ገንዘብ ፡ አደረገ ፤ የሚወደው ፡ ደቀ ፡ መዝሙ ርንም፡በደረቱ፡አስጠጋው።

፲፩፤ ሥጋ ፡ የሌለው ፡ እርሱ ፡ ሰው ፡ ልሁን ፡ ባለ፡ ጊዜ፡ሥጋን፡ነሣ፤ፈቃዳቸውንም፡ይፈጽሙ፡ ዘንድ፡በሥጋ፡ያዙት፤

የዕውሮችን ፡ ዐይን ፡ ያበራ ፡ ዘንድ ፡ አፍንና፡ ምራቅን ፡ ፈጠረ ፤ አጋንንትን ፡ አስወጥቶ፡ ይሰድ ፡ ዘንድ ፡ አንደበትን ፡ ፈጠረ ፤ በፍርድ፡ ዓደባባይ ፡ ዓምደ ፡ ቄሳርን ፡ (መስቀልን)፡ይታ ቀፍባቸው፡ዘንድ፡ሁለት፡ክንዶችን፡ፈጠረ።

፲፪፤ ዳግመኛ፡ከጲላጦስ፡ግርፋትን፡ይቀበልበት፡ ዘንድ፡ዠርባን፡ፈጠረ።

፲፫፤ ድንግል፡ዮሐንስን፡ወደ፡እርሱ፡ያስጠጋው፡ ዘንድ፡ደረትን፡ፈጠረ፤ያድነን፡ዘንድ፡የሰው ነትን፡ሥራ፡ሁሉ፡ሠራ።

የእነዚህ ፡ መምህራን ፡ በረከት ፡ ከእኛ፡ ጋራ፡ ለዘላለሙ፡ይኑር፡አሜን።

አንድ ፡ አምላክ ፡ በሆነ ፡ በአብ ፡ በወልድ፡ በመንፈስ፡ቅዱስ፡ስም።

፲፬፤ የእግዚአብሔር ፡ ወዳጅ ፡ ስለሆነው ፡ ስለ፡ አባታችን ፡ አብርሃም ፡ ልጁ ፡ ይሥሐቅን፡ መሥዋዕት ፡ አድርጎ ፡ ስለማቅረቡ ፤ የስሩግ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ አባ ፡ ያዕቆብ ፡ የደረሰው ፡ ድርሳን፡ይህ፡ነው።

፲፭፤ በእግዚአብሔር፡አንድነት፡በእውነት፡እግዚ አብሔር፡በበግ፡እንዴት፡እንደ፡አዳነው።

፲፮፤ የእግዚአብሔር፡ልጅ፡ሆይ፤ታላቁን፡ምሥ ጢርህን ፡ ልቡናዬ ፡ ያውቃት ፡ ዘንድ ፡ ይወዳል።

፲፯፤ ደስ፡ይሰኙባት፡ዘንድ፡ለሰሚዎች፡እንድገል ጽላቸው፡እንግዲህ፡ዕውቀት፡ስጠኝ።

፲፰፤ ዜናህን ፡ እናገር ፡ ዘንድ ፡ የሞትህ ፡ ሐዘን፡ ይጠራኛል ፤ በሚገባ ፡ በድርሳንህ ፡ ውስጥ፡ በመሄድ፡እገልጸው፡ዘንድ፡ኃይልን፡ስጠኝ።

Scanned by CamScanner

በ፲፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

፯ ኦሳንዮ፡ ድኩም፡ ይፈቅድ፡ ከመ፡ ይንግር፡
ዜናከ፡በከመ፡ኮነ፡ይፈቅድ፡ይርአይ፡ዕለተከ፡
ለእመ፡ ኮነ፡ ጽድቀ፡ ርእየ፡ ዕለተከ፡
ወተፈሥሐ፡ቦቱ።

፰ ወአንሂ፡ድኩም፡ካዕበ፡እሬኢ፡ድርሳነከ፡ወእ
ትፌሣሕ፡ቦቱ፡በከመ፡ተፈሥሐ፡አብርሃም፡
በአእምሮ፡ምሥጢርከ።
፱ እስመ፡ኮነት፡ሎቱ፡አምሳለ፡ወተፈሥሐ፡
ዓዲ፡በጸጋ፡ኂሩትከ፡ሶበ፡ከሠትካሃ፡ሎቱ።

፲ ኦ፡ወልደ፡እግዚአብሔር፡ዐቢይ፡ምሥጢር፡
ወመንክር፡ሠረቀ፡እምኔከ፡በውእቱ፡ዕፅ፡
ዘተአስረ፡ቦቱ፡በግዕ፡ሶበ፡ፈትሐ፡ክሣደ፡
ይሥሐቅ፡ወሬዛ።
፲፩ እስመ፡ኮነ፡አረጋዊ፡ይፈቱ፡ከመ፡ይርአይ፡
ዕለተ፡ወልደ፡እግዚአብሔር፡እሮ፡ይሠርቅ፡
ውእቱ፡መድኃኒት፡በእደዊሁ፡ለእግዚእነ።

፲፪ ወሶበ፡ኮነ፡ኀሊናየ፡ውዑየ፡በዝንቱ፡ግብር፡
ሠረቀ፡ሠናይ፡ምሥጢር፡ምስለ፡ስባሔያት።

፲፫ አብል፡እንከ፡እምይእዜ፡እሮ፡ወማእዜ፡
ወበአይ፡አምሳል፡ርእየ፡ውእተ፡ዕለተ፡
አረጋዊ፡ወተፈሥሐ፡ቦቱ።
፲፬ ነዋ፡ዜና፡ይሥሐቅ፡ትበውእ፡ውስተ፡ዕመቀ፡
ልብ፡ምሳሌ፡ሰረቅት።
፲፭ ወሶበ፡ተነበት፡አይኑ፡ልሳን፡ይትናገር፡
ኪያሃ፡በምሥጢር፡ንኅድግ፡ቃለ፡በእንተ፡
ይሥሐቅ፡ወበተፍጻሜቱ፡ይበጽሕ፡ዜናሁ።

፲፮ ኅድጊ፡እረሲ፡ዜናሁ፡ነባቢተ፡መልእክተ፡በእ
ንተ፡ቅትለተ፡ይሥሐቅ፡ወእሁበከ፡ኀትመታ።
፲፯ ወእምይእዜሰ፡አስተርአየ፡ድርሳነ፡ወልድ፡
ጥዩቀ፡በእንተ፡አብርሃም።
፲፰ ይቤ፡እግዚአብሔር፡አብርሃም፡አብርሃም፡
ወይቤ፡አብርሃም፡ነየ፡አነ፡እግዚእየ፡
ወይቤሎ፡እግዚእ፡ንሣእ፡ወልደከ፡
ዘባሕቲቱ፡ለከ፡ወሡዖ፡ሊተ፡በውስተ፡
ደብር፡ዘአርእየከ፡አነ።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፲፡ሰዓት።

፯፤ መሥዋዕት፡ የምትሆንበትን፡ ቀንህን፡
እውነት፡እንደሆነ፡ያውቅ፡ዘንድ፡እንደ፡
ወደደ፡እውነትም፡ሆኖ፡ዕለትህን፡አይቶ፡
ደስ፡እንደተሰኘበት፡ደካማው፡እንደበቴ፡
ዜናህን፡ይናገር፡ዘንድ፡ይወዳል።
፰፤ አብርሃም፡ ምሥጢርህን፡ በማወቅ፡ ደስ፡
እንዳለው፡እኔም፡ደካማው፡ዳግመኛ፡በድር
ሳንህ፡አይቼ፡እደሰትበታለሁ።
፱፤ በቸርነትህ፡ስጦታ፡እርሷን፡በገለጽክለት፡
ጊዜ፡ምሳሌ፡ሁናለታለችና፡ደግሞ፡ደስ፡
አለው።
፲፤ የእግዚአብሔር፡ልጅ፡ሆይ፡የጎልማሳው፡
የይሥሐቅ፡አንገት፡በተፈታ፡ጊዜ፤በጉ፡የታ
ሰረበት፡ ታላቅና፡ ድንቅ፡ ምሥጢር፡
በዕንጨት፡ውስጥ፡ከአንተ፡ተገለጸ።
፲፩፤ የእግዚአብሔርን፡ልጅ፡ቀን፡ያይ፡ዘንድና፤
ያ፡መድኃኒትም፡በጌታችን፡እጅ፡እንዴት፡
እንደሚገኝ፡አረጋዊ፡አብርሃም፡ይመኝ፡
ነበረና።
፲፪፤ የልቤ፡ሐሳብ፡በዚህ፡ሥራ፡ተሟሙቆ፡የተን
ቀሳቀሰ፡ ከሆነ፡ ከምስጋናዎች፡ ጋራ፡
መልካም፡ምሥጢር፡ተገለጸ።
፲፫፤ እንግዲህ፡ከዛሬ፡ጀምሮ፡እንዴት፡መቼ፡
በምን፡ አምሳል፡ ያንን፡ ቀን፡ አረጋዊ፡
አብርሃም፡አይቶ፡ተደሰተ፡እላለሁ።
፲፬፤ እነሆ፡የይሥሐቅ፡ዜና፡እንደ፡ሌቦች፡ምሳሌ፡
በልብ፡ጥልቅነት፡ትገባለች።
፲፭፤ በተነገረችም፡ጊዜ፡እንደምን፡ያለ፡አንደበት፡
እርሷን፡ በምሥጢር፡ ይናገራል፤ ስለ፡
ይሥሐቅ፡መናገርን፡እንተው፤በፍጻሜው፡
ዜናው፡ይደርሳልና።
፲፮፤ ስለ፡ይሥሐቅ፡ሞት፡መጨረሻዋን፡ሕያዊት፡
መልእክት፡አድርጌ፡እሰጥሃለሁና፡ተወኝ።
፲፯፤ አሁን፡ግን፡ስለ፡ወልድ፡የተደረሰው፡ስለ፡
አብርሃም፡የጎላ፡የተረዳ፡ነው።
፲፰፤ እግዚአብሔር፡አብርሃም፡አብርሃም፡ብሎ፡
ጠራው፤አብርሃምም፡እነሆኝ፡እኔ፡አለሁ፡
ጌታዬ፡ አለ፤ እግዚአብሔርም፡ ላንተ፡
ብቻውን፡የሆነውን፡ልጅህን፡እኔ፡በማሳይህ፡
ተራራ፡ላይ፡ወስደህ፡ሠዋልኝ፡አለው።

## በ፫፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

፲፰፤ አኮ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፈቂዶ ፡ ወየኀሥሥ ፡ ኪያሁ ፡ ሠዊዖቶ ፡ ለይስሐቅ ፡ አላ ፡ ከመ ፡ ይኩን፡ አርአያ ፡ ወአምሳለ ፡ ለቅትለተ ፡ ወልደ፡እግዚአብሔር፡ዐቢይ።

፲፱፤ ኢየኀድገኒ ፡ ይስሐቅ ፡ አትርፍ ፡ ዜናሁ ፡ ምንተኒ፤እስመ ፡ ምግባራቲሁ ፡ ይሜህራኒ ፡ ከመ ፡ እንብብ ፡ በአእምሮ ፡ ፍካሬ ፡ ዝንቱ ፡ ድርሳን፡ውእቱኬ፡ለእግዚእነ።

፳፤ ወባቲ፡ዓዲ፡ዜና፡ይሥሐቅ፡ገብሩ፡ወልደ፡ መካን።

፳፩፤ አመ ፡ ይቤሎ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለአቡሁ ፤ ንሣእ፡ ወልደከ ፡ ዘባሕቲቱ ፡ ለከ ፤ ወሑዖ ፡ ሊተ፡በኀበ፡ደብር፡ዘአርእየከ፡አነ።

፳፪፤ እወ፡በአማን፡ለእመ፡ኢኮነ፡ዐቢየ፡ዝንቱ፡ ምሥጢር ፡ እፎ ፡ እምሐረዶ ፡ ወለምንት ፡ ዘኢአበየ፡ወልድኒ፡እምአቡሁ፡ለተሠውዖ።

፳፫፤ ወባሕቱ ፡ ረሰየ ፡ ውእቱ ፡ መቅድመ ፡ ወአምሳለ፡ለቅትለተ፡ክርስቶስ፡ ወአመክሮ ፡ እግዚአብሔር ፡ በዝንቱ ፡ መከራ ፤ ወመጻ ሕፍት፡ዓዲ፡ይዜንዉ፡ከመ፡አመከሮ፡እግዚ አብሔር ፡ ለአብርሃም ፡ ወከማሁ ፡ ጸሐፈ ፡ ሙሴኒ።

፳፬፤ አ፡ዘትሜህር፡አእምር፡ኃይለ፡ምሥጢሩ፡ ለነገር፡ለጠይቆ።

፳፭፤ ለምንት፡ፈቀደ፡እግዚአብሔር፡ ያመክሮ ፡ ለአብርሃም።

፳፮፤ ወለእመ፡ኮነ፡ዘኢየአምሮ፡ለውእቱ፡ጻድቅ፡ ለምንት ፡ ረሰዮ ፡ ዐርከ ፡ አላ ፡ በእንተ ፡ ምሥጢር፡አምላካዊ፡ ዘአርአየ፡ኀሢሦቶ፡ ለይሥሐቅ።

፳፯፤ እስመ፡ኮነ፡አብርሃም፡ይትሜነይ፡ከመ፡ ይርአይ፡ዕለተ፡ወልደ፡እግዚአብሔር፤ ወበእ ንተዝ፡ገብረ፡ዘንተ፡ምግባረ።

፳፰፤ ወበእንተዝ ፡ ተዐገሠ ፡ ይስሐቅ ፡ ዘዋህድ ፡ ለአቡሁ ፡ አምሳለ ፡ ዋህድ ፡ ወልድ ፡ ከመ ይትፈጻሕ፡አረጋዊ፡በዕለተ፡ስቅለት።

፳፱፤ ወእምይእዜሰ ፡ ርዕየ ፡ እንከ ፡ አብርሃም ፡ ምሥጢራተ፡መለኮት፡ ወዘእንበለ፡ድካም፡ ርእየ፡ፍኖተ፡ዘበአማን፤ነጽር፡አ፡ጠቢብ፡

## ዓርብ፡መዓልት፡በ፫፡ሰዓት።

፲፰፤ እግዚአብሔር ፡ እሱን ፡ ይስሐቅን ፡ መሠዋቱን፡ፈልጎ፡አይደለም፤ለታላቁ፡ለእግ ዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ መገደል ፡ አርአያና፡ አምሳል፡ይሆን፡ዘንድ፡ነው፡እንጂ።

፲፱፤ ዜናውን፡አስቀር፡ዘንድ፡ይሥሐቅ፡ምንም፡ አይተወኝም፤በማስተዋል፡የዚህን፡ድርሳን፡ ትርጉም ፡ እናገር ፡ ዘንድ ፡ ሥራዎቹ፡ ይመሩኛል፤እርሱም፡ለጌታችን፡ነው።

፳፤ የመካኒቱ፡ልጅ፡የባሪያው፡የይሥሐቅ፡ዜና፡ ዳግመኛም፡አለባት።

፳፩፤ እግዚአብሔር፡ አባቱ፡አብርሃምን፤ለአንተ፡ ብቻውን፡የሆነውን፡ልጅህን፡ወስደህ፡እኔ፡ በማሳይህ፡ተራራ፡ሠዋልኝ፡ባለው፡ጊዜ።

፳፪፤ አዎን፤በእውነት፡ይህ፡ምሥጢር፡ታላቅ፡ባይ ሆን፡እንዴት፡ሊያርደው፡ቆረጠ?ልጅስ፡አልታ ረድም፡ብሎ፡አባቱን፡ለምን፡እምቢ፡አላለም

፳፫፤ ነገር ፡ ግን ፡ ለክርስቶስ ፡ መገደል፡እርሱን፡ አስቀድሞ፡ምሳሌ፡አደረገ፤በዚህም፡ፈተና፡ እግዚአብሔር፡ ፈተነው፤እግዚአብሔርም፡ አብርሃምን ፡ እንደፈተነው ፡ መጻሕፍት፡ ይናገራሉ፤ሙሴም፡እንደዚሁ፡ጽፎአል።

፳፬፤ የምታስተምር ፡ ሆይ ፡ የነገሩን ፡ ምሥጢር፡ ለመረዳት፡አስተውል።

፳፭፤ አብርሃምን ፡ ይፈትነው ፡ ዘንድ ፡ እግዚአ ብሔር፡ ለምን፡ወደደ?

፳፮፤ ይህን ፡ ጻድቅ ፡ የማያውቀው ፡ ከሆነ ፡ ለምን፡ ወዳጅ ፡ አደረገው? ይሥሐቅን ፡ መፈለጉን፡ ያሳየ ፡ ስለ ፡ አምላካዊ ፡ ምሥጢር ፡ ነው፡ እንጂ።

፳፯፤ አብርሃም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ልጅ ፡ ቀን፡ ያይ፡ዘንድ፡ይመኝ፡ነበረና፤ስለዚህም፡ይህን፡ ሥራ፡ሠራ።

፳፰፤ ስለዚህም ፡ በወልድ ፡ ዋህድ ፡ አምሳል ፡ ለአባቱ ፡ አንድ ፡ የሆነ ፡ ይሥሐቅ ፡ ታገሠ፡ አረጋዊ፡አብርሃምም፡የወልድ፡የስቅለቱን፡ ዕለት፡ምሳሌ፡አይቶ፡ደስ፡ይለው፡ዘንድ።

፳፱፤ ከዛሬም ፡ ጀምሮ ፡ አብርሃም ፡ የመለኮትን፡ ምሥጢር ፡ አየ ፤ ያለ ፡ ድካምም ፡ እውነተ ኛውን፡መንገድ፡አየ፤አወቀ፤ብልህ፡አዋቂ፡ ሆይ ፡ እምነቱ ፡ እንዴት ፡ የጸናች ፡

Scanned by CamScanner

## በ፫፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

እፎ፡ከነት፡አሚኖቱ፡ጽንዕተ፡ወኢአበየ፡ እምዘተአዘዘ፡ቦቱ፡ወኢምንተኒ፡በገጽ፡ እምገጸት።

፴ ወሶበ፡መጽአ፡ኀቤሁ፡ቃል፡ዘይብል፡ሡዕ፡ ወልደከ፡ሊተ፡ወእምከነ፡ለሖቱ፡ተዋሥኦ፡ ብዙኀ፡ለእግዚኡ፡ለእመ፡ፈቀደ፡ተዋሥኦ፡ ምስሌሁ፡እምደለዎ፡እንከ፡ይሚጥ፡ቃሎ፡ ለዘተናገረ፡ምስሌሁ፡ቃለ፡አላ፡ኢያውሥአ፡ ምንተኒ።

፴፩ ወእምከህለ፡ይበሎ፡ወሀብከኒ፡ኪያሁ፡ ወባረከ፡ላዕሌሁ፡ሊተ፡ወትቤለኒ፡ከመ፡ ውእቱ፡ይበዝኀ፡ወይትባዛኀ፡ወይፈሪ፡ በዲበ፡ምድር፤ወእፎ፡ይፈሪ፡ወይትባዛኀ፡ በዲበ፡ምድር።

፴፪ ወለእመ፡አነ፡ጠባሕክዎ፡ተፀርዐ፡እንከ፡ ኪዳንከ።

፴፫ ወለእመ፡ኢጠባሕክዎ፡ዐለውኩከ፡እንከ፡ ወዓዲ፡ይቤ፡አረጋዊ፡ለወልዱ፡እመ፡ በጻሕኩ፡በመጥባሕትየ፡ኀበ፡ክሣድከ፡ ሐሰውኩኬ፡ከመ፡አንተ፡ትወርሳ፡ለምድር።

፴፬ ወይቤ፡ዓዲ፡አንተ፡እግዚኦ፡ዘወሀብከኒዮ፡ በከመ፡ተሰፋከ፡አጠይቀኒ፡እስኩ፡በአይ፡ አዝማን፡ብእሲ፡ዘጠብሐ፡ወልዶ፡በመጥ ባሕት፡እፎ፡ወማእዜ፡ተሰምዐ፡በቀቲል፡ ከመ፡ይትፈጸም፡በከመ፡ትቤ።

፴፭ መኑ፡ዘጠብሐ፡ወልዶ፡ወፈድፈደ፡ዘርዐ፡ እምድኅረ፡ጠብሐ፡ኪያሁ።

፴፮ ወባሕቱ፡ኢይቤ፡አረጋዊ፡ምንተኒ፡እምዛቲ፡ ቃል፡ወኢኀለየ፡ባቲ፤እስመ፡ብዙኀ፡ አፍቀሮ፡ውእቱ፡ለእግዚኡ።

፴፯ ወበእንተዝ፡ኢፈቀደ፡ይኅሥሥ፡እምእ ግዚኡ፡ወይሰአል፡እስመ፡ውእቱ፡ አምሳሊሁ፡ለእግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ ከነ፡ይኔጽር፡መንክረ፡ወውእቱ፡ይትዔገሥ፡ ወኢይሴአል፡በእንተ፡ምንትኒ።

፴፰ ወረገዐ፡ኀሊናሁ፡በነፍሱ፡ወይብል፡ ዛቲ፡ዕለት፡ዘፈቀድኩ፡እርአያ፡ወእት ፈሣሕ፡ባቲ።

## ዓርብ፡መዓልት፡በ፫፡ሰዓት።

እንደሆነች፡ተመልከት፤ከታዘዘበትም፡ እምቢ፡ብሎ፡ከሥራ፡በማናቸውም፡ሥራ፡ ፊቱን፡አልመለሰም።

፴፤ ልጅህን፡ሠዋልኝ፡የሚል፡ቃል፡ወደ፡እርሱ፡ በመጣ፡ጊዜ፡የተናገረውን፡ቃል፡ይለውጥ፡ ዘንድ፡ቢወድ፡ብዙ፡መመላለስ፡በሆነ፡ ነበረ፤እንግዲህ፡ከእርሱ፡ጋር፡መመላለስና፡ መልስ፡መስጠት፡በተገባውም፡ነበር፤ ምንም፡አልመለሰም፡እንጂ።

፴፩፤ አቤቱ፡እርሱን፡ሰጠኸኝ፤በላዩም፡በረከት፡ አሳደርክ፤እርሱም፡እንዲበዛና፡እንዲባዛ፡ በምድርም፡ላይ፡እንደሚያፈራ፡ብለኸኝ፡ አልነበረምን?ይለው፡ዘንድ፡በቻለ፡ነበር፤ በምድር፡ላይስ፡እንደምን፡ዘሩ፡ሊበዛ፡ ይችላል?

፴፪፤ እኔ፡ከሠዋሁትም፡እንግዲህ፡ቃል፡ኪዳንህ፡ ተቋረጠ፡አደለምን?

፴፫፤ ባልሠዋውም፡ትእዛዝህን፡አፈረስኩ፤ ዳግመኛም፡አረጋዊ፡አብርሃም፡ልጁን፡ ሾተሌን፡በአንገትህ፡ላይ፡ባሳርፍ፡አንተ፡ ምድርን፡ትወርሳታለህ፡ያልሁትን፡ ዋሸቻለኋ!

፴፬፤ ዳግመኛም፡አቤቱ፡አንተ፡እንደ፡ተስፋህ፡ እሱን፡ለኔ፡ሰጠኸኝ፤እስኪ፡አስረዳኝ፤ሰው፡ ልጁን፡በሾተል፡ያረደው፡በየትኛው፡ዘመን፡ ነው? አንተ፡እንደ፡አልክ፡በመግደል፡ ይፈጸም፡ዘንድ፡መቼ፡ተሰማ፡ቢል።

፴፭፤ ልጁንስ፡አርዶ፡ከአረደው፡በኋላ፡ዘሩ፡የበዛ፡ ወዴት፡አለ፡ቢል፡ኖሮ።

፴፮፤ ነገር፡ግን፡አረጋዊ፡አብርሃም፡ከዚች፡ቃል፡ ምንም፡ምን፡አልተናገረም፤ፈጽሞ፡አላሰ ባትም፤ጌታውን፡እርሱ፡እጅግ፡ወዶታልና።

፴፯፤ ስለዚህም፡ጌታውን፡ሊጠይቅ፡አልፈለገም፡ የጌታችን፡የኢየሱስ፡ክርስቶስ፡አምሳል፡ ነውና፡ድንቅ፡ነገርን፡የሚመለከት፡ሆነ፤ እርሱም፡ይታገሥ፡ነበር፤በምንም፡በምን፡ አልተጠያየቀም።

፴፰፤ ሐሳቡም፡በሰውነቱ፡ውስጥ፡ጸጥ፡አለ፤ ይህችን፡ቀን፡አይቼ፡ደስ፡ልሰኝባት፡የፈለ ግኋት፡ናት፡ይል፡ነበር።

Scanned by CamScanner

## በ፫፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

፴፱፡ ወይቤሎ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለአብርሃም ፡
ተፈሣሕ፡ወተሐሠይ፡በቅትለተ፡ወልድከ፡
እስመ፡ውእቱ፡ይትሜሰል፡ለኅቡዓትየ።
፵፡ ወኢትምሀኮ ፡ ለወልድከ ፡ እስመ ፡ አነሂ ፡
ኢይምህኮ፡ለፍቁር፡ወልድየ።
፵፩፡ ሡዖ ፡ ሊተ ፡ እስመ ፡ አነሂ ፡ ከማሁ ፡ እሬሲ ፡
እምድኅረ፡መዋዕል።
፵፪፡ ኢትኅዝን ፡ በእንተ ፡ ወልድከ ፡ በከመ ፡ አነ ፡
ኢየኀዝን ፡ በእንተ ፡ ዋህድ ፡ ወልድየ ፡
ፈድፋደ፡ እምወልድከ ፡ ይሥሐቅ ፡ ዋህድከ ፡
ወውእቱ፡ አምላክከ።
፵፫፡ ካዕበ ፡ ዑቅ ፡ ሶበ ፡ በጽሐ ፡ ወልድከ ፡ ኀበ ፡
ጥብሐት ፡ ኢተኀሊ ፡ በግብሩ ፡ ከመ ፡ ኢትት
ወለጥ ፡ ብከ ፡ አምሳሊሁ ፡ ለክርስቶስ ፡ ዑቅ ፡
ኢትርዐድ ፡ ሶበ ፡ ተመጠውከ ፡ መጥባሕተ ፡
ከመ፡ትሕርድ፡ቦቱ።

፵፬፡ ወከመ ፡ ኢታማስን ፡ አምሳለ ፡ ዘታመስል ፡
ቦቱ፡ ዑቅ ፡ ከመ ፡ ኢይደመር ፡ ኀዘን ፡ ውስተ ፡
ኀሊናከ ፡ በጊዜ ፡ ጥብሐትከ ፡ ኪያሁ ፡ ከመ ፡
ኢይትሀጐል፡ግብርከ።
፵፭፡ ወበእንተዝ ፡ ዐርገ ፡ አረጋዊ ፡ ውእቱ ፡
ወወልዱ፡ በፍሥሓ ፡ ከመ ፡ ይጥብሖ ፡ ወበአ
ፍጥኖ፡ከመ፡ይፈጽም፡ፍኖቶ።
፵፮፡ ወኢያጠየቃ ፡ ለሣራ ፡ ብእሲቱ ፡ ከመ ፡
ኢትኅዝን ፡ እስመ ፡ ይእቲ ፡ ዐፅም ፡ ዕብስት ፡
ወመስተሣህልት ፡ በእንተ ፡ ፍቁራ ፡
ዘባሕቲቱ፡ላቲ፡ዘኮነ፡ምሥጢረ፡ማዕከሌሁ፡
ወማዕከለ፡እግዚኡ።

፵፯፡ ኢአመረ ፡ ለአሐዱሂ ፡ ወወፅአ ፡ እንከ ፡
አረጋዊ፡ኀበ፡ፍኖቱ፡በጕጕአ፡በከመ፡አዘዞ፡
እግዚኡ፡ኀበአ፡ቃሎ፡እመፃምርቱ፡በጊዜ፡
ፀአቱ።
፵፰፡ ወኢከሠተ ፡ ላቲ ፡ ወኢምንተኒ ፡ እምክሩ ፡
ሠናይ ፡ እስከ ፡ ገብረ ፡ ዘኢአመራ ፡ ዘንተ ፡
ምሥጢረ ፡ እስመ ፡ ዓፅም ፡ ዕብስት ፡ ይእቲ ፡
ከመ ፡ ኢታበድብድ ፡ በእንተ ፡ ወልዳ ፡
ወበእንተ፡ጥብሐቱ፡ንጹሕ።

## ዓርብ፡መዓልት፡በ፫፡ሰዓት።

፴፱፡ እግዚአብሔርም ፡ አብርሃምን ፡ በልጅህ ፡
መገደል ፡ ፈጽሞ ፡ ደስ ፡ ይበልህ፤እርሱ፡ለተሸ
ሸገው፡ምሥጢሬ፡አምሳል፡ነውና፡አለው፡
፵፡ ልጅህንም፡አትራራለት፤እኔም፡ለምወደው፡
ልጄ፡አልራራለትምና።
፵፩፡ ሠዋልኝ፡እኔም፡ከዘመናት፡በኋላ፡እንዲሁ፡
ልጄን፡እሠዋለሁና።
፵፪፡ አትዘን፤እኔ፡ስለ፡አንዱ፡ልጄ፡እንዳላዘንኩ፡
ከአንድ ፡ ልጅህ ፡ ከይሥሐቅ ፡ የሚበልጥ፡
እርሱም፡ አምላክህ፡ነው።

፵፫፡ ዳግመኛም ፡ አለው ፤ ዕወቅ ፤ ተጠንቀቅ፤
ልጅህ፡ ለመታረድ፡በቀረበ፡ጊዜ፡በሥራው፡
ላይ፡ምንም፡አታስብ፤ የክርስቶስ፡አምሳል፡
እንዳትለወጥብህ ፡ ታርድበት ፡ ዘንድ ፡
ሾተሉን፡ በወሰድህ፡ጊዜ፡እንዳትንቀጠቀጥ፡
ዕወቅ።
፵፬፡ የምትሠራትን ፡ ምሳሌ ፡ እንዳታበላሽ፡
አስተውል ፤ እርሱንም ፡ በምታርድ ፡ ጊዜ፡
በልብህ ፡ ሐዘን ፡ እንዳይገባ ፡ ሥራህም፡እንዳ
ይጠፋ፡ዕወቅ።
፵፭፡ ስለዚህም፡ሽማግሌው፡እርሱ፡ልጁን፡ይዞ፡
በደስታ ፡ ይሠዋው ፡ ዘንድ ፡ ሥራውን፡
ሊፈጽም፡በፍጥነት፡ወጣ።
፵፮፡ ለሚስቱ ፡ ለሣራ ፡ አልገለጸላትም ፤ እንዳ
ታዝን፡ ደካማ ፡ ፍጥረት ፡ ናትና ፡ ለእርሷ፡
አንድ ፡ ብቻ ፡ ስለሆነው ፡ ስለ ፡ ተወዳጅ፡
ልጅዋ፡ርኅርኅት፡ናትና፤በእርሱና፡በጌታው፡
መካከል ፡ ያለውንም ፡ ምሥጢር ፡ አልገለጸ
ላትም።
፵፯፡ ለአንዱም ፡ አላመለከተም ፤ ጌታው ፡ እንዳ
ዘዘው ፡ ወደ ፡ ጉዞው ፡ በችኮላ ፡ ወጣ፤
በሚወጣም፡ጊዜ፡የጌታውን፡ቃል፡ከሚስቱ፡
ሸሸገ።
፵፰፡ የሠወረውን ፡ ይህን ፡ ምሥጢሩን ፡ እስከ፡
ፈጸመ ፡ ድረስ ፡ ከበጎ ፡ ምክሩ ፡ ምንም፡ምን፡
አልገለጸላትም ፤ እርስዋ ፡ ልምሾ ፡ አጥንት፡
ናት ፤ ማለት ፡ ደካማ ፡ ፍጥረት ፡ ናትና ፡ ስለ፡
ልጅዋ፡ንጹሕ፡መሥዋዕት፡ለመሆንም፡ስለ፡
መታረዱ፡እንዳትርበደበድ።

Scanned by CamScanner

## በ፲፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

፵፱ ኀዘለ፡ምክሮ፡እምአረጊት፡ከመ፡ኢይርከባ፡ዘረከባ፡ለእማ፡ሔዋን፡ሰረቆ፡እንከ፡ለገብር፡እምእሙ፡መከን፡ከመ፡ኢትሕምም፡እንከ፡አረጊት፡በእንተ፡ፍቁር፡ወልዳ።

፶ ለአከ፡ኀበ፡ወልዱ፡ይንግሮ፡ወይቤሎ፡ነዐ፡ንሑር፡ኦ፡ወልድየ፡ከመ፡ንፈጽም፡ዘተአዘዝነ፡ቦቱ።

፶፩ ወኢያለበዋ፡እንከ፡ለእሙ፡ሣራ፡በጊዜ፡፡ፀአቱ፡ኀበ፡አቡሁ፡ወኢ፡ለወራዙት፡ለእለ፡ነሥአሙ፡ምስሌሁ፡ኢያለበዎሙ።

፶፪ ዓዲ፡እግዚአብሔር፡ወአብርሃም፡አረጋዊ፡እንከ፡ባሕቲቶሙ፡የአምሩ፡ግብሮ።

፶፫ ወሶበ፡ጸውዖ፡ለይስሐቅ፡ለተጠብሖ፡ኢያንዘኖ፡እንከ፡ነሥአ፡ለይስሐቅ፡ወሖረ፡ከመ፡ይፈጽም፡ምሥጢረ፡ዘተአዘዘ፡ቦቱ።

፶፬ ሰበረ፡ዕፀወ፡ወአጸሮ፡ወነሥአ፡ካህን፡ሠዋዒ፡ምስሌሁ፡ባሕቲቶ፡ወሰሐለ፡መጥባሕቶ፡ወተደለወ፡ከመ፡ይቅርዖ፡ለወልዱ፡ዘባሕቲቱ፡ሎቱ።

፶፭ በዝኒ፡እንከ፡አንከሮቶሙ፡ለደቅ፡እለ፡ሀለዉ፡ምስሌሁ፡ሶበ፡ርእዩ፡ጕጕአቶ፡በፍኖት፡አንከሩ፡እምኔሁ፡ሶበ፡ኢዜነዎሙ፡ኀበ፡አይ፡ብሔር፡ይፈቅድ።

፶፮ ወኢተሀበለ፡አሐዱ፡እምኔሆሙ፡ከመ፡ይሰአሎ፡በእንተ፡ግብሩ።

፶፯ ሖረ፡ጻድቅ፡ውስተ፡ፍኖተ፡ቀትል፡እንዘ፡ምስሌሁ፡ይስሐቅ።

፶፰ ወእንዘ፡የሐውር፡ውእቱ፡ዐገቶ፡ምሥጢረ፡መለኮት፡እምኵሉ፡ገጽ፡ሰሐቦ፡ኀዘን፡በፍኖት፡ዘየሐውር፡ባቲ፡ከመ፡ይዕርግ፡ወይትፈማሕ፡በይእቲ፡ትንሣኤ፡ዘርእየ፡በሕይወቱ፡በይሥሐቅ፡ወልዱ።

፶፱ ሖረ፡ሠለስተ፡ዕለታተ፡ለሕማመ፡ሞት፡ወኢያነዘኖ፡ዝክረ፡ቀትለ፡ዋህድ፡ወልዱ።

፷ መኑ፡እንከ፡ዘይትዔገሥ፡ወኢይሰበር፡ኃይሉ፡እንዘ፡ይስሕቦ፡ለወልዱ፡ወፍቁሩ፡ከመ፡ይሕርዶ፡በመጥባሕት፤ወለእመኒ፡

## ዓርብ፡መዓልት፡በ፲፡ሰዓት።

፵፱ እናቷ፡ሔዋንን፡ያገኘ፡ስህተት፡እንዳያገኛት፡ከእናቱ፡ምክሩን፡ሰወረ፤ከመካን፡እናቱም፡ይሥሐቅን፡ሰረቀ፤በሽምግልና፡ያለች፡እናቱ፡ስለ፡ውድ፡ልጅዋ፡በሐዘን፡እንዳትሠቃይ።

፶ ይነግረው፡ዘንድ፡ወደ፡ልጁ፡ላከ፤የታዘዝን በትን፡እንፈጽም፡ዘንድ፡ልጄ፡ሆይ፡ና፡ብሎ።

፶፩ እርሱም፡ወደ፡አባቱ፡በሚወጣ፡ጊዜ፡ለእናቱ፡አላሳሰባትም፤ከእርሱ፡ጋር፡ለወሰዳቸው፡ጎልማሶችም፡ቢሆን፡አልነገራቸውም።

፶፪ ሥራውን፡ሽማግሌው፡አብርሃምና፡እግዚአብሔር፡ብቻቸውን፡ያውቁታል፡እንጂ።

፶፫ ይሥሐቅንም፡ለመታረድ፡በጠራው፡ጊዜ፡አላሸበረውም፤የታዘዘበትን፡ምሥጢሩን፡ይፈጽም፡ዘንድ፡ወሰደው፡እንጂ።

፶፬ ዕንጨትም፡ሰብሮ፡አሸከመው፤መሥዋዕት፡አቅራቢውም፡ካህን፡ብቻውን፡ወሰደው፤ሾተሉንም፡ሳለ፤ለእርሱም፡ብቸኛ፡የሆነ፡ልጁን፡ይሠዋው፡ዘንድ፡ተዘጋጀ።

፶፭ እንግዲህ፡ከርሱ፡ጋራ፡ያሉ፡ሎሌዎች፡በመንገድ፡ላይ፡ችኮላውን፡በአዩ፡ጊዜ፡አድናቆታቸው፡በዛ፤ወደየት፡አገር፡ለመሄድ፡እንደሚፈልግ፡ባልነገራቸው፡ጊዜ።

፶፮ ከእነርሳቸውም፡አንዱ፡እንኳን፡ስለሥራው፡ሊጠይቀው፡አልደፈረም።

፶፯ ደጉ፡አብርሃም፡ይሥሐቅ፡ከርሱ፡ጋራ፡እያለ፡የመግደል፡(የመሠዋት)፡መንገድን፡ተጓዘ።

፶፰ በሚጓዝም፡ጊዜ፡መለኮታዊ፡ምሥጢር፡በሁሉ፡አቅጣጫ፡ከበበው፤በልጁ፡በይሥሐቅ፡በሕይወቱ፡በሚያየው፡በዚያች፡ትንሣኤ፡ደስ፡ይለው፡ዘንድ፡ወደ፡ተራራው፡እንዲወጣ፡ኃዘን፡ሳበው።

፶፱ ለሞት፡ሕማምም፡ሦስት፡ቀኖች፡ያህል፡ተጓዘ፤የአንድ፡ልጁም፡የመሞት፡ማሰብ፡አላሳዘነውም።

፷ የሚወደውን፡ልጁን፡በሾተል፡ያርደው፡ዘንድ፡ሊስበው፡የሚታገሥ፡ማነው? ልቡ፡ኃይሉስ፡የማይሸበር፡ማን፡ነው? ልቡ፡

በ፲፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

ዘኮነ፡ልቡ፡ከመ፡እብን፡ኢየሐዝን።

፳፩፤ ተናገሮ፡ይሥሐቅ፡ለአቡሁ፡ነገረ፡ዘምሉእ፡ ሕይወተ፡ወኢየአምር፡ውእቱሰ፡ዘይገብር፡ ቦቱ፡ወኢኀበ፡አይቴ፡ይወስዶ።

፳፪፤ ወበእንተዝ ፡ ኮነ ፡ ይትናገር ፡ ዘእንበለ ፡ ፍርሃት፡እምነ፡መጥባሕት።

፳፫፤ ወአረጋዊሰ ፡ ድልው ፡ ውእቱ ፡ ለኃምዮቱ ፡ ወፈቀደ፡ከመ፡ይክዐው፡ደሞ፡በመጥባሕት።

፳፬፤ ወይሥሐቅሰ፡ይትናገር፡ምስለ፡አቡሁ፡ከመ፡ ዘሀሎ ፡ ሀየንቴሁ ፡ ዘይረክብ ፡ ለተጠብሖ ፡ እስመ ፡ ኢየአምር ፡ ግብሮ ፡ ወአቡሁሰ ፡ ይጌሊ፡ ማእዜ ፡ ወእፎ ፡ የአምሮ ፡ ወኮነ ፡ ይሥሐቅ ፡ ይትፌሣሕ ፡ እስመ ፡ ኀቡእ ፡ እምኔሁ፡ዝ፡ግብር።

፳፭፤ ወእንዘ ፡ የሐውሩ ፡ በፍኖት ፡ ኮኑ ፡ መስተፋ ጥናነ ፡ በሐዊር ፡ ወምስለ ፡ ዝ ፡ ኵሉ ፡ ኮኑ ፡ ይትናገሩ፡ብዙኀ።

፳፮፤ ወይቤሉ ፡ ካልአን ፡ እመምህራን ፡ ከመ ፡ ውእቶሙ፡በሠለስቱ፡ዕለት፡ሖሩ፡ዐሠርተ፡ ምዕተ፡ምዕራፈ።

፳፯፤ ርእዩኬ፡ኀበ፡ጻማ፡አረጋዊ፡ወትዕግሥቶሂ፡ ብዙኀ።

፳፰፤ ወይሥሐቅሰ፡ወሬዛ፡ኢኀደገ፡ተናግሮተ፡ ምስለ፡አቡሁ፡በኵሉ፡ፍኖት፡ኢይቤሎ፡አ፡ አባ፡ኀበ፡አይኑ፡ተሐውር፡እምዝየ፡ዳእሙ፡ ኮነ፡ይሴአሎ፡በእንተ፡በግዕ፡ዘይጠባሕ፡ ወይቤሎ፡አይቴሁ፡በግዑ፡ዘይጠባሕ፡ወዘታ ቀርቦ።

፳፱፤ ወከማሁ ፡ ካዕበ ፡ ተሰእሎ ፡ በእንተ ፡ ኑኀ ፡ ፍኖት ፡ ወይቤሎ ፡ እስፍንቱ ፡ ዕለት ፡ ለነ ፡ እንዘ፡ ነሐውር ፡ አ ፡ አባ ፡ ወአኮ ፡ ዘንደክም ፡ ወአልቦኑ፡ተፍጻሜት፡ለፍኖትነ።

፴፤ አይቴኑ፡ብሔራ፡ዘፈቀድከ፡ከመ፡ትሑር፡ ኀቤሃ፡ወንህነ፡ከመዝ፡ጕጉአን፡ዘከመዝ፡ ጕጕአ፡አው፡ቦኑ፡አሐዱ፡እምነገሥት፡እለ፡ መጽኡ፡ኀቤነ፡ለአከ፡ኀቤከ፡ከመ፡ትብጻሕ፡ ኀቤሁ፡ወአነ፡ምስሌከ።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፲፡ሰዓት።

እንደ፡ደንጊያ፡የጸና፡የማያዝን፡ከሆነ፡ነው፡ እንጂ።

፳፩፤ ይሥሐቅም ፡ አባቱን ፡ ሕይወትን ፡ የተመላ፡ ነገርን ፡ ተናገረው ፤ እርሱ ፡ ግን ፡ አባቱ ፡ ምን፡ እንደሚያደርግበት ፡ ወደየትም ፡ እንደሚወ ስደው፡አያውቅም።

፳፪፤ ስለዚህም ፡ በሾተል ፡ ከመታረድ ፡ ያለ፡ መፍራት፡የሚናገር፡ሆነ።

፳፫፤ ሽማግሌውም ፡ ሊያስረው ፡ ተዘጋጅቷል፤ በሾተልም፡አርዶ፡ደሙን፡ለማፍሰስ፡ወደደ።

፳፬፤ ይሥሐቅ ፡ ግን ፡ ስለ ፡ እርሱ ፡ ለመሥዋዕት፡ የሚታረድ ፡ ከአባቱ ፡ ጋራ ፡ እንዳለ ፡ አድርጎ፡ ይናገራል ፤ የሚሠራውን ፡ አያውቅምና፡ አባቱም ፡ መቼ ፡ እንዴት ፡ እንደሚያደርግ፡ ያውቀዋል ፤ ይህ ፡ ሥራ ፡ ከእርሱ ፡ ስውር፡ ነውና፤ይሥሐቅ፡ደስ፡የሚለው፡ሆነ።

፳፭፤ ሲሄዱም ፡ በመገሥገሥ ፡ የሚፋጠኑ ፡ ሆኑ፤ ከዚህም፡ሁሉ፡ጋር፡ብዙ፡ይነጋገሩ፡ነበር።

፳፮፤ ከመምህራን ፡ ሌሎችም ፡ እነርሱ ፡ በሦስት፡ ቀን፡አንድ፡ሺህ፡ምዕራፍ፡ሄዱ፡ይላሉ።

፳፯፤ የሽማግሌውን ፡ የአብርሃምን ፡ ድካሙንና፡ ብዙ፡የሆነ፡ትዕግሥቱን፡እዩዋ!

፳፰፤ ይሥሐቅም ፡ በጉዞአቸው ፡ ሁሉ ፡ ከአባቱ፡ ጋራ ፡ መነጋገርን ፡ አልተወም ፤ አባት ፡ ሆይ፡ ወዴት ፡ ትሄዳለህ ፡ አላለውም ፤ ስለሚታረ ደውም ፡ በግ ፡ ይጠይቀው ፡ ነበረ ፡ እንጂ፡ አርደህ፡ለመሥዋዕት፡የምታቀርበው፡በግ፡ ወዴት፡ነው፡ይለው፡ነበር።

፳፱፤ ስለ፡መንገዱ፡ርዝመትም፡ደግሞ፡ጠየቀው፤ አባት፡ሆይ፡ስንጓዝ፡ለእኛ፡ዛሬ፡ስንት፡ቀን፡ ነው? ግን ፤ የምንደክም ፡ አይደለም ፤ መንገዱ ችንስ፡ፍጻሜ፡የለውምን፡አለው።

፴፤ ወደ ፡ እርሷ ፡ ትሄድ ፡ ዘንድ ፡ የወደድካት፡ ሀገሪቱ ፡ ወዴት ፡ ናት ? እኛም ፡ እንደዚህ፡ በችኮላ ፡ እንጓዛለን ፤ ወይም ፡ ከነገሥታት፡ ወደእኛ ፡ የመጡ ፡ኑረው ፡ እኔም ፡ ከአንተ፡ ጋራ፡ ሁኜ ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ትደርስ ፡ ዘንድ፡ የላከብህ፡አለን።

Scanned by CamScanner

| ፱ኛ፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ። | ዓርብ፡መዓልት፡በ፱ኛ፡ሰዓት። |
|---|---|
| ፷፩ አው፡ቃል፡ዘጸውዐከ፡ቀዲሙ፡እምቤተ፡አቡከ፡ውእቱ፡እንጋ፡ዘጸውዐከ፡ወአውጽአከ፡ምስሌሁ፡ፍጡነ። | ፷፩ ወይም፡ቀድሞ፡ከአባትህ፡ቤት፡የጠራህ፡ቃል፡እርሱ፡ጠርቶህ፡በፍጥነት፡ከእርሱ፡ጋራ፡ያወጣህ፡ይሆናል። |
| ፷፪ አንሰኬ፡አእመርኩ፡ከመ፡ፍኖትነ፡ድኅነት፡ይእቲ። | ፷፪ እኔ፡ግን፡መንገዳችን፡ለድኅነት፡እንደሆነች፡አወቅሁ። |
| ፷፫ ወበእንተዝ፡እሬኢ፡ኪያከ፡በምግባሪከ፡ወኀሊናከ፡ትጌጉእ፡ከመ፡ታጥሪ፡በቍዔተ፤ ወሐዊሮትከኒ፡ፍጽምት፡ይእቲ፡ከመ፡ዘእኀስባ። | ፷፫ ስለዚህም፡ጥቅም፡ያለውን፡ነገር፡ገንዘብ፡ታደርግ፡ዘንድ፡አንተን፡በሐሳብህም፡በሥራህም፡ስትቸኩል፡አየሁ፤መንገድህም፡እንደማስባት፡ፍጽምት፡ናት። |
| ፷፬ ከመዝ፡ኮነ፡ይሥሐቅ፡ይትናገር፡ምስለ፡አቡሁ፡ዘንተ፡ነገረ፡ጥዑመ፡ወዘይመስሎ። | ፷፬ ይሥሐቅም፡ይህን፡ጣዕም፡ያለውን፡ነገርና፡ይህንንም፡የመሰለ፡ከአባቱ፡ጋራ፡የሚናገር፡ሆነ። |
| ፷፭ ወአረጋዊሰ፡ኮነ፡ይዴምር፡ቃሎ፡በካልእ፡ቃል፡ከመ፡ኢያግብእ፡አውሥአተ፡ነገሩ። | ፷፭ ሽማግሌውም፡ትክክለኛውን፡እንዳይመልስ፡ስለት፡ቃሉን፡ወደሌላ፡ይለውጠው፡ነበር። |
| ፷፮ ወከመዝ፡ያወሥእ፡ካልአ፡ነገረ፡ወኮነ፡ይፄልጥ፡ነገሮ፡በኵሉ፡ምክንያት፡ወተጸምሞ፡ከመ፡ዘኢይሰምዕ፡ቃሎ። | ፷፮ እንደዚሁም፡ሌላ፡ነገር፡መልስ፡እየሰጠ፡በምክንያት፡ሁሉ፡ነገሩን፡ይለውጥ፡ነበር፤ ቃሉንም፡እንደማይሰማ፡ቸል፡ይል፡ነበር። |
| ፷፯ ሖረ፡ቦቱ፡አብርሃም፡ሠለስተ፡ዕለተ፡በጻማ፡ዕጹብ፡ወበዝንቱ፡ኵሉ፡ኢፈከረ፡ሎቱ፡አውሥአተ፡ነገሩ፡። | ፷፯ አብርሃምም፡ጭንቅ፡በሆነ፡ድካም፡ሦስት፡ቀን፡ተጓዘ፤በዚህ፡ሁሉ፡ለጥያቄው፡መልስ፡በመስጠት፡ነገሩን፡አልገለጸለትም። |
| ፷፰ ወሶበ፡ተፈጸመት፡ፍኖተ፡ንጉሥ፡በምልአ፡ዘእንበለ፡አሐዱ፡ባሕቲቱ፡ይብል፡በእንተ፡ጥበሐት። | ፷፰ የንጉሡም፡ጉዞ፡በተፈጸመች፡ጊዜ፡ከብቻው፡ከአንዱ፡በቀር፡ማለት፡ስለማረድ፡ብቻ፡ይናገራል። |
| ፷፱ ወነበበ፡እግዚአብሔር፡ለአብርሃም፡እንዘ፡ይብል፡ዕርግ፡ኀበ፡ዝንቱ፡ደብር፡ዘበውስቴቱ፡ይከውን፡መድኃኒተ፡ዓለም። | ፷፱ እግዚአብሔርም፡እንዲህ፡ሲል፡አነጋገረው፤ በውስጡ፡የዓለም፡ድኅነት፡ወደሚደረግበት፡ወደዚህ፡ተራራ፡ውጣ። |
| ፸ ዕርግ፡ዝየ፡ወነጽር፡ቅቱለ፡ወሕያወ፡ንቡረ፡ላዕለ፡ምሥዋዕ፡ወቍርባነ፡ንጹሐ፡ወጥቡሐ፡ዘእንበለ፡መጥባሕት። | ፸ ወደዚያም፡ወጥተህ፡ምውትና፡ሕያው፡ሁኖ፡በመሠዊያ፡ላይ፡ያለውን፡ያለ፡ሾተልም፡የታረደውን፡ንጹሕ፡ቍርባን፡ተመልከት። |
| ፸፩ ነዓ፡ትርአይ፡ዕለተ፡ወልድ፡ማሕየዊ፡ዘስውር፡ወክሡቶ፡አንተኒ፡ይእዜ፡በቅትለተ፡ዋህድከ። | ፸፩ ና፡ስውር፡የሆነውን፡የማሕየዊ፡የወልድን፡ቀን፡ታይ፡ዘንድ፤ በአንድ፡ልጅህ፡መገደልም፡ዛሬ፡አንተ፡ግለጸው። |
| ፸፪ ነዓ፡ትርአያ፡ለጽድቅ፡ወትጠይቃ፡ወአምዝ፡ትከውን፡እንከ፡ዘመሰልከ፡ዘሀሎ፡ይኩን፡ነዮን፡ዝየ፡ኅቡራት፡ወንቡራት። | ፸፪ እውነትንም፡አይተህ፡ትረዳት፡ዘንድ፡ና፤ እንግዲህም፡ይሆን፡ዘንድ፡ያለው፡ምሳሌውን፡የሠራኸው፡ይሆናል፤እነርሱም፡ከዚህ፡በአንድነት፡ተቀምጠዋል። |
| ፸፫ ነዓ፡እንከ፡ትርአይ፡አምሳለ፡ወተሀሉ፡ምስሌከ፡አምሳል፡ዐባይ፡ዘወልደ፡ | ፸፫ እንግዲህ፡ምሳሌዋን፡ታይ፡ዘንድ፤ የእግዚአ እርሷም፡ከአንተ፡ጋራ፡ትኑር፤ |

በ፲፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

እግዚአብሔር፡ዘየ፡ተፍጻሜተ፡ፍኖትከ።

፹፬፡ ነዓ ፡ አ ፡ ብእሲ ፡ ኀበ ፡ ዛቲ ፡ መርስ ፡ ዘኮነት ፡
ምዕራፈ፡ሐመርከ።

፹፭፡ ነዓ፡አ፡ኖትያዊ፡ኀበ፡ዝንቱ፡ደብር፡ከመ፡
ትፈጽም ፡ ምሥጢራተ ፡ ኀበ፡እተ ፡ ዐቅ ፡
ኢትኅልፍ ፡ እምኔሁ ፡ ከመ ፡ ካልእ ፡
መምዕላይ፡ ውስተ ፡ ዝንቱ ፡ መካን ፡
ይትከዐው፡ደሙ፡ለንጹሕ።

፹፮፡ ነዓ ፡ ዓዲ ፡ አንተኒ ፡ ክስት ፡ ደመ ፡
ምሥጢራት፡ በውስቴቱ ፡ ወሑር ፡ እምዝየ ፡
በአማን።

፹፯፡ እስመ፡ደብር፡ዘዐርገ፡ውስቴቱ፡ይሥሐቅ፡
ምስለ፡አብርሃም፡አቡሁ፡ውእቱ፡ጎልጎታ፡
ቅድስት።

፹፰፡ ወኀበ፡መካነ፡መስቀል፡ተአስረ፡ይሥሐቅ፡
ወዕፅ ፡ ዘተአስረ ፡ ባቲ ፡ በግዕ ፡ ይእቲ ፡ ዕፅ ፡
ዘሠረፀት፡ውስተ፡ጽዮን፡ለመስቀለ፡ወልደ፡
እግዚአብሔር ፡ ወኀበ ፡ ምቅዋመ ፡ እእጋረ ፡
ይሥሐቅ ፡ ህየ ፡ እንከ ፡ ተቀንዋ ፡ እደዊሁ ፡
ወእገሪሁ ፡ ለወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወኀበ ፡
ተሰሕለ ፡ መጥባሕት ፡ ላዕለ ፡ ይሥሐቅ ፡ ህየ ፡
ተሰሕለ፡ኲናት፡ላዕለ፡ወልደ፡እግዚአብሔር፡
እስመ ፡ ይደልዎ ፡ እንከ ፡ ለገብር ፡ ከመ ፡
ይቅድም፡ይጺሕ፡ፍኖተ፡እግዚኡ፡ቅድሜሁ፡
እስመ፡ውእቱ፡ይመጽእ፡ወይከውን፡ቅቱለ፡
ወጥቡሐ፡በእንተ፡ኃጥኣን።

፹፱፡ ወእንዘ፡የሐውር፡አብርሃም፡ርእየ፡ውእቱ፡
ራእየ፡ላዕለ፡ደብር፡ወሖረ፡ኀቤሁ፡በከመ፡
በግዕ፡ኀቡእ፡ቅጽበተ፡ጸውዖ፡ለይሥሐቅ፡
ኀበ፡መጥባሕት።

፺፡ ርእየ ፡ አብርሃም ፡ ኀበ ፡ ራእይ ፡ መልዕልተ ፡
ደብር፡ከመ፡ሰራቂ፡ወሖረ፡ኀቤሁ።

፺፩፡ ወእምዝ ፡ አእመረ ፡ አብርሃም ፡ መካነ ፡
ዘይደሉ፡ከመ፡ይኩን፡ውስቴታ፡ምሥጢር።

፺፪፡ ወለእመሰ፡ኢኮነ፡ዝንቱ፡ከመዝ፡በከመ፡ንቤ፡
መኑ ፡ እንከ ፡ ዘአርአዮ ፡ ደብረ ፡

ዓርብ፡መዓልት፡በ፲፡ሰዓት።

ብሔር፡ልጅ፡ ታላቁ፡ምሳሌ፡በጉዞህ፡ፍጻሜ፡
በዚህ፡ይሆናል።

፹፬፡ አብርሃም ፡ ሆይ ፡ ለጉዞህ ፡ ማረፊያ ፡ ወደሆ
ነችው፡ወደዚች፡ወደብ፡ና።

፹፭፡ ዋናተኛ ፡ ሆይ ፡ የተሸሸጉ ፡ ምሥጢሮችን፡
ትፈጽም፡ዘንድ፡ወደዚህ፡ተራራ፡ና፤እንደ
ሌላው ፡ እንደተነቀፈው ፡ ተራራ ፡ እንዳታ
ልፈው፡ተጠንቀቅ፤የንጹሑ፡ደሙ፡በዚሁ፡
ቦታ፡ውስጥ፡ይፈሳልና።

፹፮፡ ዳግመኛም ፡ አንተ ፡ ና ፡ በውስጡ ፡
በምሥጢር፡ያለውን፡ደም፡ግለጽ፡ከዚህም፡
ሂድ።

፹፯፡ ይሥሐቅ፡ከአባቱ፡ጋራ፡የወጣበት፡ተራራ፡
የከበረች፡ጎልጎታ፡ናት።

፹፰፡ ይሥሐቅም ፡ በመስቀል ፡ ቦታ ፡ ታሰረ፤
በጉም፡ የታሰረባት ፡ ዕንጨት ፡ ለእግዚአ
ብሔር ፡ ልጅ ፡ መስቀል ፡ የሆነች ፡ በጽዮን፡
የበቀለች ፡ ናት ፤ የይሥሐቅ ፡ እግሮች፡
በቆሙበት ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ በዚያ፡
እጆቹና ፡ እግሮቹ ፡ ተቸነከሩ ፤ ሾተሉም፡
በይሥሐቅ ፡ ላይ ፡ በተሳለበት ፡ በእግዚአ
ብሔር ፡ ልጅ ፡ ላይ ፡ በዚያ ፡ ጦር ፡ ተሳለ፤
አገልጋይ ፡ ባሪያ ፡ ከጌታው ፡ ፊት ፡ ቀድሞ፡
መንገድ ፡ ይጠርግ ፡ ዘንድ ፡ ይገባዋልና፤
እርሱ፡ ስለ ፡ ኃጥአን ፡ ሙቶ ፡ መሥዋዕት፡
ይሆን፡ዘንድ፡ይመጣልና።

፹፱፡ አብርሃምም ፡ ሲሄድ ፡ በተራራው ፡ ላይ፡
ምልክት ፡ አየ ፡ ወደርሱም ፡ ሄደ ፡ የተሸሸገ፡
በግ ፡ እንደአለ ፡ ሁኖ ፡ ይሥሐቅን ፡ ወደ፡
ሾተሉ፡ጠቀሰው።

፺፡ አብርሃምም፡በተራራው፡ላይ፡ወደ፡አለው፡
ራእይ፡እንደ፡ሌባ፡ሰረቅ፡እያደረገ፡እየ፡
ወደ፡እርሱ፡ሄደ።

፺፩፡ ከዚህም፡በውስጡ፡ምሥጢር፡ይፈጸምበት፡
ዘንድ፡የሚገባ፡ቦታ፡እንደሆነ፡አብርሃም፡
አወቀ።

፺፪፡ ይህ፡እንደዚህ፡እንዳልነው፡ባይሆን፡ኖሮ፡
የሚሄድበትን፡ተራራ፡ማን፡አሳየው?

Scanned by CamScanner

በ፲፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

ዘእግዚአብሔር፡ ኀቤሁ ፤ እስመ ፡ ይቤሎ ፡እግዚአ
ብሔር፡ ሡዖ፡ሊተ፡ለወልድከ፡ኀበ፡ደብር፡
ዘአርእየከ፡አነ።
፺፫ ወኢይቤሎ፡ሡዕ፡ሊተ፡መሥዋዕተ፡ኀበ፡
እንተ፡ደብር፡ወበእንተዝ፡ከሠተ፡ሎቱ፡እግ
ዚአብሔር፡ ግብረ፡እምቅድመ፡ይብጻሕ፡
ኀቤሁ፡ከመ፡ኢይኅልፍ፡እምኔሁ፡በከመ፡
ተዓደዎሙ፡ለካልአን፡አድባር፡ከመ፡ይሡዖ፡
ለይሥሐቅ፡ኀበ፡ደብረ፡ጎልጎታ፡እምቅድመ፡
ይሰቀል፡ውስቴቱ፡ክርስቶስ፡ወልደ፡እግዚአ
ብሔር፡ ኮነ፡ይሴፎ፡አብርሃም፡ተፍጻሜተ፡
ሠለስቱ፡ዕለታት።
፺፬ ወእንዘ፡የሐውር፡ኮነ፡ይብል፡ማእዜ፡ወእፎ፡
እሬኢ፡ውእተ፡ደብረ፡ወሖረ፡ቀዳሚተ፡
ዕለተ፡ወካልእታሂ፡ወኢርእየ፡ምንተኒ፡
እምዘኮነ፡ይሴፎ።
፺፭ ወኮነ፡ጸድቅ፡ያስተማስል፡መቃብረ፡ወልድ፡
እስመ፡እግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ ሞአ፡
ለሞት፡በሣልስት፡ዕለት፡ወወጽአ፡እምነ፡
ሲኦል።

፺፮ ከማሁኬ፡ቀተሎ፡ለይሥሐቅኒ፡አቡሁ፡
በሐረት፡በውእቶን፡ሠላስ፡ዕለታት፡ከመ፡
ይትፈጸማ፡ምሥጢራት፤ወእምዝ፡
ይትነሣእ።
፺፯ ወኮነ፡እንከ፡አብርሃም፡ይጸንሕ፡ከመ፡
ይርአዮ፡ክሡተ፡በውስተ፡ውእቱ፡ደብር።
፺፰ ወሶበ፡ተኀብአ፡እምኔሁ፡ምሥጢር፡
በክልኤቱ፡ዕለታት፡ወእምዝ፡አስተርአዮ፡
በሣልስት፡ዕለት።
፺፱ ወኮነ፡እንከ፡አብርሃም፡ያስተፋጥን፡
ወይቤሎሙ፡ለደቂ፡ንበሩ፡ዝየ፡እስከ፡
ነዐርግ፡አነ፡ወወልድየ፡ውስተ፡ደብር፡
ንጸሊ፤ወእምድኅረ፡ጸለዮትነ፡ንገብእ፡
ኀቤክሙ።
፻ በአይቴ፡እንጋ፡ኀሊና፡ዘኮነ፡ይኄሊ፡
አብርሃም፡ኮነሁ፡ይትሔዘብ፡ከመ፡ይገብእ፡
ወልዱ፡ምስሌሁ፡እምውእቱ፡ደብር።
፻፩ ወበእንተ፡ዝንቱ፡አዘዞሙ፡ለደቅ፡ይንበሩ፡
መትሕተ፡ደብር።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፲፡ሰዓት።

እግዚአብሔር፡ እኔ፡በማሳይህ፡ተራራ፡ላይ፡
ልጅህን፡ሠዋልኝ፡ብሎታልና።

፺፫፤ ዕገሌ ፡ በሚባል ፡ ተራራ ፡ መሥዋዕት ፡
ሠዋልኝ፡ አላለውም ፤ ስለዚህ፡ወደ፡እርሱ፡
ሳይደርስ፡የሚሠራውን፡ገለጸለት ፤ ከእርሱ፡
አልፎ፡እንዳይሄድ፡ሌሎችን፡ተራራዎች፡እን
ዳለፋቸው፡የእግዚአብሔር፡ልጅ፡ክርስቶስ፡
በውስጡ ፡ ከመሰቀሉ ፡ አስቀድሞ ፡
ይሥሐቅን፡ በጎልጎታ ፡ ይሠዋው ፡ ዘንድ ፡
አብርሃም፡የሦስቱን፡ቀን፡ፍጻሜ፡ተስፋ፡
የሚያደርግ፡ሆነ።
፺፬፤ ሲሄድም፡ያንን፡ተራራ፡መቼ፡እንዴት፡
አየዋለሁ፡የሚል፡ሆነ ፤ በመጀመሪያይቱ፡
ቀን፡ ሄደ ፤ በሁለተኛይቱም፡ቀን፡ተጓዘ ፤
ተስፋ፡ያደረገውን፡ምንም፡ምን፡አላየም።
፺፭፤ ደጉ፡አብርሃምም፡የወልድን፡ መቃብር፡
አምሳል፡ሠራ ፤ጌታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡
በመቃብር ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ አድሮ ፡ በሦስ
ተኛው፡ ቀን ፡ ሞትን ፡ ድል ፡ አድርጎ ፡
ከመቃብር፡ወጥቷልና።
፺፮፤ እንደዚሁም ፡ በእነዚያ ፡ በሦስት ፡ ቀኖች ፡
ውስጥ ፡ ይሥሐቅን ፡ አባቱ ፡ በኅሊናው ፡
ገድሎት፡ሰንብቷል ፤ምሥጢሮች፡ፍጹማን፡
ይሆኑ፡ዘንድ፡ከዚህ፡በኋላም፡ይነሣል።
፺፯፤ እንግዲህ፡በዚያ፡ተራራ፡ውስጥ፡በግልጽ፡
ያየው፡ዘንድ፡አብርሃም፡የሚጠብቅ፡ሆነ።
፺፰፤ በሁለቱ ፡ ቀኖች ፡ ምሥጢሩ ፡ ከእርሱ ፡
ቢሰወርም፡ከዚያም፡በሦስተኛው፡ቀን፡ተገ
ለጸለት።
፺፱፤ እንግዲህ፡አብርሃም፡የሚፋጠን፡ሆነ ፤ሎሌዎ
ቹንም፡እኔና፡ልጄ፡ወደ፡ተራራው፡ወጥተን፡
እስከምንጸልይ፡ከዚህ፡ተቀመጡ ፤ አላቸው ፤
ከጸለይንም ፡ በኋላ ፡ ወደእናንተ ፡ እንመለ
ሳለን።
፻፤ አብርሃም፡በምን፡ኀሳብ፡የሚያስብ፡ሆነ ፤
እንጃ፡ልጁ፡ከእርሱ፡ጋራ፡ከተራራው፡እንደ
ሚመለስ፡ይጠራጠር፡ነበረን?
፻፩፤ ስለዚህም፡ከተራራው፡በታች፡ይቀመጡ፡
ዘንድ፡ሎሌዎቹን፡አዘዛቸው።

Scanned by CamScanner

በ፫፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

፲፪፡ ነበበትኑ፡እንጋ፡ትንቢት፡በላዕለ፡ልሳኑ፡
በሀየ፡አው፡በኑ፡ከነ፡የሀድኦ፡ለወልዱ፡ከመ፡
ኢይፍራህ፡አው፡በኑ፡ይኄሊ፡ምስለ፡
ትውክልቱ፡በእግዚአብሔር፡ከመ፡ውእቱ፡
ሶበ፡ሐረደ፡ይገብእ፡ወይትነሣእ፡ወይወርድ፡
ምስሌሁ፡እምውስተ፡ደብር፡እስመ፡ኮነት፡
ምስሌሁ፡ኵላ፡ምግባሩ፡መፍርሀተ፡ወመን
ክርተ።

፲፫፡ እፎኑ፡ኮነ፡ይብል፡በአእምሮቱ፡ንሰግድ፡ለእ
ግዚአብሔር፡ወንገብእ፤ወውእቱሰ፡አጾሮ፡
መጥባሕተ፡ከመ፡ይክዐው፡ባቲ፡ደሞ።

፲፬፡ ወበእንተዝ፡ይቤሎሙ፡ለደቁ፡አነ፡
ወወልድየ፡ይሥሐቅ፡ነዐርግ፡ከመ፡ንስግድ፡
ለእግዚአብሔር፡በውእቱ፡ደብር፡ወንት
መየጥ፡ኀቤክሙ፡እስመ፡ኢይደሉ፡ከመ፡
ይዕርግ፡ምስሌነ፡መኑሂ፡ውስተ፡ዝንቱ፡
ደብር፡ንበሩ፡ውስተ፡መካንክሙ፡እስመ፡
ብነ፡ምሥጢር፡ዐቢይ፡ውስተ፡ርዕሰ፡ደብር፡
ወፍኖትነ፡ኀበ፡እግዚአብሔር።

፲፭፡ ወኮነ፡አብርሃም፡ይሥሕል፡መጥ
ባሕተ፡ወይቤ፡አሐዱ፡ለካልኡ፡ለምንትኑ፡
ዘከልአነ፡እግዚእነ፡ለዐሪግ፡ምስ
ሌሁ፡ኢገብረ፡ምስሌነ፡ከመዝ፡
ወኢምንተኒ።

፲፮፡ ወኮነ፡እንዘ፡ይወስደነ፡ውስተ፡ኵሉ፡ኀበ፡
ዘሖረ፡ኵሎ፡ጊዜ፡ወለእመ፡ኮነ፡እንዘ፡
ይሰግድ፡ለእግዚአብሔር፡አምላኩ፡ወለም
ንትኑ፡ዘተደለወ፡ወዘይፈቅድ፡ይሡዕ፡
መሥዋዕተ፡ወኢንሬኢ፡ምስሌሁ፡በግዐ፡
ዘያቀርብ።

፲፯፡ ለምንትኬ፡ዘነሥአ፡ለይሥሐቅ፡ባሕቲቶ፡
ውኀበ፡አይኑ፡መካን፡ይሰግዱ።

፲፰፡ ወዐርገ፡አብርሃም፡እንዘ፡ይትፌሣሕ፡ወይት
ሐሠይ፡ኀበ፡ደብር፡ወምስሌሁ፡ወልዱ፡
እንዘ፡ይትፌሣሕ።

፲፱፡ ወአንቃዕደወ፡አዕይንቲሁ፡ውስተ፡
ሰማይ።

፳፡ ወራእይሰ፡ዘርእዮ፡በኀበ፡ደብር፡ያንበሉብል፡
በፈቃዱ፡ወኢክሀለ፡ይሚጥ፡አዕይንቲሁ፡
እምኔሁ።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፫፡ሰዓት።

፲፪፡ እንደበቱ፡ትንቢት፡ተናገረችን፤ወይም፡
እንዳይፈራ፡ልጁን፡ጸጥ፡ሊያደርገው፡
ነውን፤ ወይም፡በአረደው፡ጊዜ፡ከእ
ለው፡እምነቱ፡ጋራ፡እግዚአብሔር፡እን
ደሚያስነሣለትና፡ከእርሱ፡ጋራ፡ከተራራው፡
ተመልሶ፡እንደሚወርድ፡ያስብ፡ነበረን፤
ከእርሱ፡ጋራ፡ሥራው፡ሁላ፡የምታስፈራና፡
የምታስደንቅ፡ነበረችና።

፲፫፡ በብልሃቱ፡ለእግዚአብሔር፡ሰግደን፡እንመለ
ሳለን፡እንዴት፡አለ፤እርሱም፡ደሙን፡
ያፈስባት፡ዘንድ፡ሾተሉን፡አሸከመው።

፲፬፡ ስለዚህም፡ወጥተን፡በዚያ፡ተራራ፡እኔና፡
ልጄ፡ይሥሐቅ፡ለእግዚአብሔር፡ሰግደን፡
ወደናንተ፡እንመለሳለን፡አላቸው፤
ለሎሌዎቹ፡ወደዚያ፡ተራራ፡ማንም፡ከእኛ፡
ጋራ፡ሊወጣ፡አይገባውምና፤ከዚህ፡
ከቦታችሁ፡ተቀመጡ፤በተራራው፡ራስ፡ላይ፡
ታላቅ፡ምሥጢር፡አለንና፤መንገዳችንም፡
ወደ፡እግዚአብሔር፡ነው።

፲፭፡ አብርሃምም፡ሾተሉን፡ይስል፡ነበር፤
አንዱም፡ ባልንጀራውን፡ለምንድነው፡
ጌታችን፡ከእርሱ፡ጋራ፡መውጣት፡የከለ
ከለን፤እንደዚህ፡ምንም፡ምን፡አድርጐ፡
አያውቅም፡ይል፡ነበር።

፲፮፡ ወደ፡ሄደበት፡ሁሉ፡ሁልጊዜ፡ሲወ
ስደን፡ነበር፤ለፈጣሪው፡እግዚአ
ብሔር፡እየሰገደ፡ከሆነ፡መሥዋዕት፡
ይሠዋ፡ዘንድ፡ወዶ፡የተዘጋጀ፡ለምን
ድነው? የሚያቀርበውን፡በግ፡ግን፡ከእ
ርሱ፡ጋራ፡አናይም።

፲፯፡ ይሥሐቅንስ፡ብቻውን፡ለምን፡ወሰደው፤
ወዴትስ፡ቦታ፡ይሰግዳሉ።

፲፰፡ አብርሃምም፡ፈጽሞ፡ደስ፡እያለው፡ወደ፡
ተራራው፡ወጣ፤ልጁም፡ከእርሱ፡ጋራ፡ደስ፡
እያለው።

፲፱፡ በዐይኖቹም፡ቀና፡ብሎ፡ወደ፡ሰማይ፡
ተመለከተ።

፳፡ በተራራውም፡ላይ፡ያየው፡ራእይ፡በራሱ፡
ፈቃድ፡ቦግ፡ቦግ፡ይል፡ነበር፤ከእርሱም፡
ዐይኑን፡ይመልስ፡ዘንድ፡አልተቻለውም።

Scanned by CamScanner

## በ፫፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

ወሶበ፡እንከ፡አረጋዊ፡ስኩረ፡እምሥጢረ፡መለኮት፡ዘፈልፈለት፡ሎቱ፡እምኅልኅታ፡ወሶበ፡ይልህብ፡ማዕከለ፡እደዊሁ፡ዐምደ፡መስቀል፡ወበእንተዝ፡ተኀህለወ፡ላዕለ፡ክልኤቱ፡ደቂ፡ከመ፡ኢይዕርጉ፡ምስሌሁ፡አላ፡ይዕርግ፡ባሕቲቶ፡ከመ፡ይርአይ፡ዕለተ፡ወልድ።

ወሶበ፡ዓዲ፡ይትዓቀብ፡ከመ፡ይርአይ፡መዐርዒረ፡ስቴ፡ጥዕምተ፡ባሕቲቶ።

ወበእንተዝ፡ይብሎሙ፡ለደቂ፡ጽንሑኒ፡ዝየ፡እስከ፡ንገብእ፡ክልኤነ፡ኀቤክሙ፡እምድኅረ፡ጸልዮትነ።

ወሶበ፡እንከ፡አረጋዊ፡ይሥሕል፡መጥባሕተ፡ከመ፡ይሕርድ፡ባቲ፡ፍቁሮ፡ወልቡ፡ዕጉሥ፡ከመ፡ያውርዶ፡ምስሌሁ፡ወያግብእ፡በጊዜሁ።

ወኢኮነኬ፡ዘየአምር፡ዘከመ፡እፎ፡ይድኅን።

ወባሕቱ፡ኮነ፡ትውክልቱ፡ላዕለ፡እግዚአብሔር። ነሥአ፡ለሕፃን፡ወአጾሮ፡ዕፀ፡ወአዕረጎ፡ምስሌሁ፡ወውእቱ፡ይጸውር፡መጥባሕተ፡ወእሳተ።

ይእዜ፡አእመርነ፡ከመ፡መስቀለ፡ወልድ፡ምስለ፡ምሥጢራት፡ሀለወት፡ህየ፡ምስለ፡ተ።

ወበእንተዝ፡ጾረ፡ይሥሐቅ፡ዕፀ፡ባሕቲቶ። ጸዊሮቱ፡ለይሥሐቅ፡ዕፀ፡ዲበ፡መትከፍቱ፡አምሳለ፡ጸዊሮቱ፡ለእግዚእነ፡ክርስቶስ፡ዕፀ፡መስቀል፡ሶበ፡አኮ፡እፎ፡ዘኢይቤ፡አሐዱ፡እምአግብርት፡ጹር፡አንተ፡ዕፀ፡ወዕርግ፡ኀበ፡ደብር፡ወግባእ፡ውስተ፡መካንከ።

ወባሕቱ፡ምሥጢረ፡እግዚእ፡ኢያብሐቶ፡ከመ፡ይግበር፡ዘንተ።

ወከማሁ፡ሖረ፡ይሥሐቅ፡ጸዊሮ፡ቅድሜሁ፡አምሳለ፡ዚአሁ፡ዕፀ።

አሰሬ፡ልሳነ፡ላሕም፡ፍቁር፡በአርዐተ

## ዓርብ፡መዓልት፡በ፫፡ሰዓት።

፻፲፩፤ አረጋዊ፡አብርሃምም፡ከኅልኅታ፡ከተገለጸ ችለት፡መለኮታዊ፡ምሥጢር፡የተነሳ፡የሰከረ፡ሆነ፤በእጆቹ፡መካከል፡ምሥጢረ፡መስቀል፡ይሟሟቅ፡ነበር፤ስለዚህም፡ከእርሱ፡ጋራ፡እንዳይወጡ፡ሁለቱን፡ሎሌዎች፡ሸነገለ፤የእግዚአብሔርን፡ልጅ፡ቀን፡ያይ፡ዘንድ፡ብቻውን፡ሊወጣ፡ነው፡እንጂ።

፻፲፪፤ ዳግመኛም፡ደስ፡የምታሰኝ፡ረቂቅ፡ምሥጢርን፡ብቻውን፡ያይ፡ዘንድ፡የሚጠነቀቅ፡ሆነ።

፻፲፫፤ ስለዚህም፡አገልጋዮቹን፡ከጸለይን፡በኋላ፡ወደ፡እናንተ፡እስክንመለስ፡ድረስ፡ከዚህ፡ቆዩን፡አላቸው።

፻፲፬፤ ሽማግሌውም፡ውድ፡ልጁን፡ያርድባት፡ዘንድ፡ሾተሊቱን፡የሚስል፡ሆነ፤ልቡም፡ይታገሣል፤በጊዜው፡ጊዜ፡ከእርሱ፡ጋራ፡መልሶ፡እንደሚያወርደው፡አውቆ።

፻፲፭፤ እንዴት፡እንደሚድን፡ግን፡አያውቅም፡ነበር።

፻፲፮፤ ነገር፡ግን፡እምነቱ፡በእግዚአብሔር፡ላይ፡የጸና፡ነው፤ሕፃኑንም፡ዕንጨቱን፡አሸከም፡ከእርሱ፡ጋራ፡ይዞት፡ወጣ፤እርሱም፡ሾተልና፡እሳት፡ተሸከመ።

፻፲፯፤ የወልድ፡መስቀል፡ምሳሌነቷ፡ከምሥጢር፡ጋራ፡ከዚያ፡እንዳለች፡ዛሬ፡አወቅን።

፻፲፰፤ ስለዚህም፡ይሥሐቅ፡ብቻውን፡ዕንጨቱን፡ተሸከመ፤የይሥሐቅ፡በትከሻው፡ላይ፡ዕንጨትን፡መሸከም፡የጌታችን፡የክርስቶስ፡ዕፀ፡መስቀልን፡የመሸከሙ፡አምሳል፡ነው፤ያ፡ባይሆን፡ኖሮ፡ከአገልጋዮች፡አንዱን፡አንተ፡ዕንጨቱን፡ተሸከም፤ወደ፡ተራራውም፡ውጣ፤አድርሰህ፡ወደ፡ቦታህ፡ተመለስ፡እንዴት፡አይለውም፡ነበር?

፻፲፱፤ ነገር፡ግን፡ይህን፡ያደርግ፡ዘንድ፡የጌታ፡ምሥጢር፡አላሰናበተችውም።

፻፳፤ እንዲሁም፡ይሥሐቅ፡በጌታ፡አምሳል፡ዕንጨት፡ተሸክሞ፡በፊቱ፡ሄደ።

፻፳፩፤ ለታላቁ፡በሬ፡መታረድ፡ይመስል፡ዘንድ

በ፫፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

ሐዘናት፡ከመ፡ይትማሰል፡በተሠውዖቱ፡
ለዐቢይ፡ላሕም።
፻፷፪ ዘሎን፡ግብራተ፡ይሥሐቅ፡ከና፡
አምሳለ፡ግብራተ፡መድኃኒነ፡ኢየሱስ፡
ክርስቶስ።
፻፷፫ ተአዚዞ፡ማኅተመ፡ወልድ፡መድኃኒነ፡
ረሰዮ፡በውስተ፡አክሊለ፡ሐዘናት፡ኄረ፡
በውስተ፡ፍኖተ፡ቀትለ፡ወልደ፡እግዚአ
ብሔር፡ሖረ፡ይሥሐቅ፡ንጹሕ።
፻፷፬ ወበእንተዝ፡ጸረ፡ዕፀ፡ወጾረ፡አቡሁ፡እሳተ፡
ወመጥባሕተ።
፻፷፭ ወወጠነ፡ሕፃን፡የኀሊ፡ከመ፡ምንተኑ፡
ይሴአል፡በእንተ፡ኀቡአት፡ይቤሎ፡
ምሥጢር፡ኀቡእ፡ንቃህ፡ወአእምር፡ከመ፡
አንተ፡ተሐውር፡ለግብረ፡አቡከ፡ዘውእቱ፡
ገባሪሁ።
፻፷፮ ርእየ፡ይሥሐቅ፡ኀበ፡መጥባሕት፡ከመ፡
ተሥሕለት፡በከመ፡ይሰሐል፡ለጥብሐት፡
ወአረጋዊሰ፡ጸዋሪሃ፡ዘምስለ፡እሳት።
፻፷፯ ይቤ፡ይሥሐቅ፡ነዋ፡ነየ፡ዝንቱ፡ንዋየ፡
መሥዋዕት፡ዘአስተዳለወ፡አቡየ፡ወአልቦ፡
ዘእሬኢ፡በግዐ።
፻፷፰ አጥበበ፡እግዚአ፡ከመ፡ይንብብ፡
በአእምሮ፤ ወጸርሐ፡ኀበ፡አቡሁ፡አብ
ርሃም፡እንዘ፡ይብል፡አ፡አባ፡ወአ
ውሥአ፡በብዙኅ፡ፍቅር፡ነየ፡አ፡
ወልድየ።
፻፷፱ ወእምዝ፡መጽአ፡ኀቤሁ፡ከመ፡ይትረአዩ፡
ገጸ፡በገጽ፡ከመ፡ምሒረ፡አበው፡ላዕለ፡
ውሉድ።
፻፸ ወሶበ፡ይቤሎ፡ነየ፡አነ፡አ፡ወልድየ፡
ኮነ፡እንከ፡ይሴአሎ፡ከመ፡ጠቢብ፡እንዘ፡
ይብል፡አ፡አባ፡ነዋ፡ዕፀሰ፡ወመጥባሕት፡
ለመሥዋዕት፡አይቴኑ፡እንከ፡በግዑ፡
ዘታቀርበ።
፻፸፩ ነያ፡መጥባሕት፡በልኅት፡ለጥብሐት፡
አይቴኑ፡እንከ፡ዘይጠባሕ፡ባቲ፡አላ፡
ለእመ፡ኮነ፡አሐዱ፡እምኔነ፤ነዋ፡ካዕበ፡
እሳት፡ምስሌነ።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፫፡ሰዓት።

የተወዳጁን፡ላም፡የይሥሐቅን፡እንደበት፡
በሐዘን፡ቀንበር፡አሰረ።
፻፷፪ የይሥሐቅ፡ሥራዎች፡ሁሉ፡ለመድኃኒ
ታችን፡ለኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ሥራዎች፡
ምሳሌዎች፡ሆኑ።
፻፷፫ እሽ፡በጄ፡ብሎ፡የመድኃኒታችንን፡
የወልድን፡ማኅተም፡የተመረጠ፡የሐዘን፡
ዘውድ፡አድርጎ፡በእግዚአብሔር፡ልጅ፡
የሞት፡መንገድ፡ንጹሕ፡ይሥሐቅ፡ተጓዘ።
፻፷፬ ስለዚህም፡እርሱ፡ዕንጨቱን፡ተሸከመ፤
አባቱ፡ሾተሉንና፡እሳቱን፡ተሸከመ።
፻፷፭ ስውር፡ስለሆነውም፡ምሥጢር፡ምን፡እንደ
ሚጠይቅ፡ሕፃኑ፡ማሰብ፡ጀመረ፤የተሸሸ
ገውም፡ምሥጢር፡አባትህ፡ለሚፈጽመው፡
ሥራ፡አንተ፡ንቃ፡ዕወቅም፡ሠሪውም፡
እርሱ፡ነው፡አለው።
፻፷፮ ይሥሐቅም፡ለማረድ፡እንደ፡ተሳለች፡ወደ፡
ሾተሊቱ፡ተመለከተ፤ከእሳት፡ጋራ፡የተሸከ
ማትም፡ሽማግሌው፡አብርሃም፡እንደ፡ሆነ።
፻፷፯ ይሥሐቅም፡እነሆ፡እኔ፡አለሁኝ፤ይህ፡
አባቴ፡ያዘጋጀው፡የመሥዋዕት፡ዕቃ፡አለ፤
የማየው፡በግ፡የለም፡አለ።
፻፷፰ በማስተዋል፡ይናገር፡ዘንድ፡ጌታ፡ጥበብን፡
ሰጠው፤ወደ፡አባቱ፡ወደ፡አብርሃም፡
አባት፡ሆይ፤እያለ፡ጮኸ፤አባቱም፡
በፍጹም፡ፍቅር፡እነሆኝ፡ልጄ፡ሆይ፤ብሎ፡
መለሰለት።
፻፷፱ ከዚህም፡በኋላ፡አባቶች፡ለልጆች፡እንደ
ሚራሩ፡ፊት፡ለፊት፡ይተያዩ፡ዘንድ፡ወደ፡
እርሱ፡መጣ።
፻፸ እነሆኝ፡ልጄ፡ሆይ፤በአለው፡ጊዜ፡እነሆ፡
ለመሥዋዕት፡ሥራ፡የሚያገለግል፡
ዕንጨት፡ሾተል፡አለ፤እንግዲህ፡ለመሥ
ዋዕት፡የምታቀርበው፡በግ፡ወዴት፡አለ፤
እያለ፡እንደ፡ብልህ፡የሚጠይቀው፡ሆነ።
፻፸፩ እነኋት፡ለማረድ፡ሾተሊቱ፡ተሳለች፤
እንግዲህ፡የሚታረድባት፡ወዴት፡ነው፤
ከሁለታችን፡አንዱ፡ቢሆን፡ነው፡እንጂ፤
እነሆ፡ዳግመኛም፡እሳት፡ከእኛ፡ጋራ፡አለ።

Scanned by CamScanner

| በ፫፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ። | ዓርብ፡መዓልት፡በ፫፡ሰዓት። |
| --- | --- |
| ለዐቆት፡ጽንሐሕ፡ዘይበልዖ፡እሳት፡ነዋ፡ ዲቤከ፡አምሳለ፡ክህነት። | ፯፻፴፪፤ እሳት፡በልቶት፡የሚሸትተው፡መዐዛውስ፡ ወዴት፡ነው?እነሆ፡በአንተ፡ላይ፡የክህነት፡ አምሳል፡አለ። |
| ወአይቴት፡እንከ፡መሥዋዕት፡ዘታቀርቦ፡ ወአልብከ፡ዝየ፡ዘታቀርብ፡ምንተኒ፡ ዘእንበለ፡እነ። | ፯፻፴፫፤ እንግዲህ፡የምታቀርበው፡መሥዋዕት፡ ወዴት፡ነው?ከዚህ፡ከእኔ፡በቀር፡ምንም፡ ምን፡የምታቀርበው፡የለህም። |
| ዓለት፡ኢይሬኢ፡ዝየ፡መንገሌነ፡እንስሳ፡ ከመ፡ንንሣእ፡እምኔሁ፡በግዐ፡አነ፡እኄሊ፡ ከመ፡አነ፡ውእቱ፡በግዕ፡ዘታቀርቦ፡ለመሥ ዋዕት። | ፯፻፴፬፤ ከውስጡ፡በግ፡እንወስድ፡ዘንድ፡በዚህ፡በአ ካባቢያችን፡የማየው፡መንጋ፡የለም፤ግን፡ ለመሥዋዕት፡የምታቀርበው፡በግ፡እኔ፡ እንደ፡ሆንኩ፡አስባለሁ። |
| ርኢከሆሙ፡ለአድባር፡እለ፡ኀለፍኖሙ፡ ከመ፡አልቦሙ፡አልሕምት፡ወኢ፡ካልእ፡ እንስሳ። | ፯፻፴፭፤ ያለፍናቸውንም፡ተራራዎች፡በውስ ጣቸው፡ላሞች፡ወይም፡ሌሎች፡እንስሶች፡ እንደሌሉባቸው፡አይቻቸዋለሁ። |
| ወበከመሰ፡አአምር፡አንተኬ፡ትፈቅድ፡ ትጥብሐኒ፡ኪያየ፡ህየንተ፡እንስሳ፤ ለምንት፡ዘኢኀረይከ፡እመርዔትነ፡በግዐ፡ ተባዕተ፡ንጹሐ፡ወሥቡሐ፡ታቅርብ፡ መሥዋዕተ። | ፯፻፴፮፤ እንደሚመስለኝስ፡አንተ፡እኔን፡ስለ፡ እንስሳ፡ልታርደኝ፡ትፈቅዳለህ፤ መሥዋዕት፡አድርገህ፡የምታቀርበው፡ ንጹሕ፡የሰባ፡ወንድ፡ጠቦት፡ለምን፡ከመን ጋዎቻችን፡ውስጥ፡አልመረጥህም? |
| ወአይቴ፡እንከ፡በግዕ፡ዘታቀርቦ፡ወሶበ፡ አኮ፡ዘእከውን፡አነ፡በከመ፡እቤለከ። | ፯፻፴፯፤ እንዳልኩህ፡እኔ፡የምሠዋ፡ካልሆን፡ለመሥ ዋዕት፡የምታቀርበው፡በግ፡ወዴት፡አለ? |
| ዘንተ፡ነገረ፡ጥዑመ፡ኮነ፡ይትናገሮ፡ ይሥሐቅ፡ለጻድቅ፡አብርሃም፡አቡሁ። | ፯፻፴፰፤ ለአባቱ፡ለጻድቁ፡አብርሃም፡ይህን፡ጣዕም፡ ያለውን፡ነገር፡ይስሐቅ፡ይናገረው፡ነበር። |
| ወኢያሕዘኖ፡እንከ፡ዝንቱ፡እምደለዎኑ፡ እንከ፡አቡሁ፡ይበሎ፡ኢትሕዝን፡ወልድየ፡ እንዘ፡መሥዋዕተ፡ትሴአል፡ወትብል፡ አይቴ፡በግዕ፡አ፡አባ። | ፯፻፴፱፤ እንግዲህ፡አባቱ፡አዝኖለት፡ሊተወው፡አል ወደደም፤ልጄ፡ሆይ፡በጉ፡ወዴት፡ነው? በማለት፡መሥዋዕቱን፡ስትጠይቅ፡አትዘን፡ ይለው፡ዘንድ፡ባልተገባውም፡ነበር። |
| ወመኑ፡እንከ፡ዘርኁቅ፡እምሕረት፡ዘኢየ ሐዝን፡ሶበ፡ሰምዐ፡ስእለታተ፡ወልደ፡ መካን፡አሐዱ፡ለአቡሁ | ፯፻፵፤ መካን፡የወለደችውን፡የአንድ፡ልጁን፡ ምልጃ፡በሰማ፡ጊዜ፡ከርኅራኄ፡የሚርቅ፡ የማያዝን፡ማን፡ነው? |
| መኑ፡ውእቱ፡ዘጽኑዕ፡ልቡ፡ከመ፡እብን፡ ወኢየሐምም፡በእንተ፡ዋህዱ፡እንዘ፡ ውእቱ፡ይትናገር፡ለአረጋዊ። | ፯፻፵፩፤ ልቡ፡እንደ፡ደንጊያ፡የጸናለት፡ማን፡ነው? እርሱ፡ሲናገር፡ስለ፡አንድ፡ልጁ፡ልቡ፡የማ ይጨነቅ፡ማን፡ነው? |
| መኑ፡ውእቱ፡ይቡስ፡ሐቅል፡ዘኢሰትየ፡ አፍቅሮ፡ውሉድ፤ ወሰምዐ፡ስእለታተ፡ ይሥሐቅ፡ወልዱ፡አቡሁ፡ወኢያንብዓ፡አዕ ይንቲሁ። | ፯፻፵፪፤ የልጆች፡ፍቅር፡ያላደረበት፡ልቡ፡እንደ፡ በረሀ፡ደረቅ፡የሆነ፡ማን፡ነው?አባቱም፡ የልጁን፡የይሥሐቅን፡ምልጃዎች፡ሰማ፤ ነገር፡ግን፡ዐይኖቹ፡ዕንባን፡አላፈሰሱም፡ |

Scanned by CamScanner

## በ፫፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

፻፶፫፤ ወእምዝ፡ አውሥአ፡ አብርሃም፡ ለወልዱ፡ እንዘ፡ ይብሎ፡ እግዚአብሔር፡ የኀሥሥ፡ ሎቱ፡መሥዋዕተ።

፻፶፬፤ ኵሉ፡ ነገር፡ ይሥሐቅ፡ ዘተናገረ፡ ቦቱ፡ ለአቡሁ፡ እምድኅረ፡ ተሰብአ፡ በከመ፡ ጸውዖ፡ወልድ፡ ለአቡሁ፡በውስተ፡ስእለቱ፡ እንዘ፡ይብል፡አ፡አባ።

፻፶፭፤ ከማሁ፡ ይሥሐቅኒ፡ ይቤ፡ ለአ ብርሃም፡ አቡሁ፡ አ፡ አባ፡ አይቴ፡ በግዑ፡ ዘታቀርቦ፡ መሥዋዕተ፡ ለእ ግዚአብሔር፡ አምሳለ፡ ቃለ፡ እግዚ አነ፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ዘይቤ፡ አ፡ አባ፡ ለእመ፡ ይትከሀል፡ ይኅልፍ፡ እምኔየ፡ዝንቱ፡ጽዋዕ።

፻፶፮፤ በአሐዱ፡ ጸጋ፡ አክበርዎ፡ ክልኤሆሙ፡ ለመለኮት። ይቤ፡አብርሃም፡ሶበ፡ተስእሎ፡ ወልዱ፡ በእንተ፡ መሥዋዕት፡ እስመ፡ ያስተዴሉ፡ ሊተ፡ እግዚአብሔር፡ መሥዋዕተ፡ወኢኮነ፡ሊተሰ፡ዘአኃሥሥ፡ አነ፡ በግዐ፡ ዘንነሥእ፡ ምስሌነ፤ እግዚአ ብሔር፡ ይረሲ፡ ዘፈቀደ፡ እስመ፡ ኵሉ፡ ይትከሃል፡በኀቤሁ።

፻፶፯፤ አንሰ፡ አዐርግ፡ በከመ፡ አዘዘኒ፡ እግዚአ ብሔር፡ወበከመ፡አመረኒ።

፻፶፰፤ ወበግዕ፡ዘአስተዳለወ፡ምስሌሁ፡ድልው፡ ውእቱ፡ አንሰ፡ ምስሌየ፡ መጥባሕት፡ ወሀሎ፡ምስሌሁ፡በግዕ፡ወአንተ፡ትሬእዮ፡ ወእግዚአብሔር፡ ይሬኢ፡ ሎቱ፡ በግዐ፡ ኄረ።

፻፶፱፤ ነዋ፡ ገባር፡ ይደፍን፡ ዘርዐ፡ ውስተ፡ ምድር፡ ወይትዌከል፡ ላዕለ፡ እግዚአ ብሔር።

፻፷፤ ወሶበ፡ በጽሐ፡ ካህን፡ እንዘ፡ ምስሌሁ፡ በግዕ፡ ኀበ፡ ርዕሰ፡ ደብር፡ ወበህየ፡ አስተርአየ፡ አኰቴተ፡ ምሥጢራት፡ ክሡተ፡ ኀበ፡ መካነ፡ ጸልበ፡ አቀሞ፡ ህየ፡ ወአርአዮ፡ ዘከመ፡ እፎ፡ የሐ ንጽ፡ምሥዋዐ።

፻፷፩፤ ወይቤሎ፡እግዚአብሔር፡ ዝንቱ፡ ውእቱ፡ መካን፡ዘምሥዋዕ፡ዐቢይ።

## ዓርብ፡መዓልት፡በ፫፡ሰዓት።

፻፶፫፤ ከዚህ፡በኋላም፡አብርሃም፡እግዚአብሔር፡ ለእርሱ፡መሥዋዕቱን፡ይሻል፡ብሎ፡ለልጁ፡ መለሰለት።

፻፶፬፤ ይሥሐቅ፡ ለአባቱ፡ የተናገረበት፡ነገር፡ ሁሉ፡ ወልድ፡ ሰው፡ ከሆነ፡ በኋላ፡ በልመናው፡ ውስጥ፡ አባት፡ ሆይ፡ ብሎ፡ አባቱ፡አብን፡እንደ፡ጠራው፡ነው።

፻፶፭፤ እንደዚሁ፡ይሥሐቅ፡አባቱ፡አብርሃምን፡ አባት፡ ሆይ፡ ለእግዚአብሔር፡ መሥዋ ዕትን፡ አድርገህ፡ የምታቀርበው፡ በግ፡ ወዴት፡ ነው ? አለ ። በአካላዊ፡ ቃል፡ በጌታችን፡በኢየሱስ፡ክርስቶስ፡አምሳል፡ አባት፡ሆይ፡ቢቻል፡ይህ፡የሞት፡ጽዋ፡ ከእኔ፡ይለፍ፡ያለው፡ነው።

፻፶፮፤ በአንድ፡ ቃል፡ ሁለቱም፡ መለኮትን፡ አከበሩት፤ አብርሃም፡ ስለ፡ መሥዋዕት፡ ልጁ፡ በጠየቀው፡ ጊዜ፡መሥዋዕቱን፡እግዚአብሔር፡ያዘጋጅ ልኛል፡ እኔ፡ በጉን፡ የምፈልግና፡ ከእኛ፡ ጋራ፡ የምወስድ፡ አይደለም፤ እግዚአብ ሔርም፡ የወደደውን፡ ያድርግ፡ በእርሱ፡ ዘንድ፡ሁሉ፡ይቻላልና፡አለ።

፻፶፯፤ እኔ፡እግዚአብሔር፡እንዳዘዘኝና፡እንዳመለ ከተኝ፡ወደ፡ተራራው፡እወጣለሁ።

፻፶፰፤ ለመሥዋዕት፡ ያዘጋጀው፡ በጉ፡ ከእርሱ፡ ጋራ፡ነው፤ከእኔ፡ጋራ፡ያለ፡ሾተል፡ነው፤ በጉ፡ ከእርሱ፡ ጋራ፡ እንዳለ፡ አንተ፡ ታየዋለህ፤ እግዚአብሔርም፡ ለራሱ፡ በጐውን፡በግ፡ያያል።

፻፶፱፤ እነሆ፡ ገበሬ፡ ዘሩን፡ በምድር፡ ውስጥ፡ ይዘራል፤ እምነቱንም፡ በእግዚአብሔር፡ ላይ፡ያደርጋል።

፻፷፤ ካህኑ፡አብርሃምም፡መሥዋዕቱ፡ከእርሱ፡ ጋራ፡ ሳለ፡ ወደ፡ ተራራው፡ ራስ፡ በደረሰ፡ ጊዜ፡ የሥጋውና፡ የደሙ፡ ምሥጢር፡ በግልጽ፡ታየ፤በመስቀሉም፡በታ፡በዚያ፡ አቆመው፤መሠዊያውንም፡እንዴት፡እንደ ሚሠራ፡አሳየው።

፻፷፩፤ እግዚአብሔርም፡ የትልቁ፡መሠዊያ፡በታ፡ ይህ፡ነው፡አለው።

Scanned by CamScanner

## በ፫፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

ወቀርበ፡አብርሃም፡ወአንበረ፡እሳተ፡ወመጥ ሐተ፡ላዕለ፡ርእሰ፡ደብር፡ወርእየ፡ ገበ፡ይትፌቀድ፡ይሕንጽ፡ምሥዋዐ፡ ለግብሐቱ።

ወቀርበ፡ርሱየ፡ሃይማኖት፡ወአስ ተናበረ፡መሠረተ፡ከመ፡ይሕንጽ፡ሕየ፡ ቤተ፡ምሥጢራት፡ዘሀለወት፡ትኩን፡ በጎልጎታ።

ወሶበ፡ርእየ፡ይሥሐቅ፡ኀበ፡አቡሁ፡ መየገብር፡አውረደ፡ዕፀ፡እመትከፍቱ፡ ገበ፡ምድር፡ወኮነ፡ያቀርብ፡ሎቱ፡ እእባነ።

ርእዮ፡ለካህን፡እንዘ፡የሐንጽ፡መሥ ዋዐ፡ወረሰየ፡ምስሌሁ፡እዴሁ፡ከመ፡ ይሕንጽ፡ወከመ፡ይትፈጸም፡ፍጡነ፡ግብረ፡ ዚአሁ።

አብርሃም፡ዘኮነ፡ካህነ፡ካዕበ፡ ኮነ፡ነዳቄ፡ዘውእቱ፡አቡሁ፡ ለበግዕ፡ወመሥዋዕትኒ፡ይሥሐቅ፡ ገባሬ፡ውእቱ፡ውስተ፡እእ ባን።

ድልወት፡ሎቱ፡እንከ፡ከመ፡ይሕንጽ፡ ምሥዋዐ፡ለስቅለቱ። እስመ፡በዝንቱ፡ ይከውን፡አምሳለ፡ወልደ፡እግዚአብሔር፡ በፈቃዱ፡ይመውት፡ሶበ፡ተሰብአ።

ወሶበ፡ተፈጸመ፡ሕንፃ፡ነበቦ፡እግዚአ ብሔር፡ለአብርሃም፡ከመ፡ይፈጽም፡ ዘተአዘዘ፡ቦቱ።

ወይቤሎ፡ምንትኑ፡ዘያቀውመከ፡ደይ፡ እዴከ፡ወተንሥእ፡ውስተ፡ግብርከ።

ወቀርበ፡አብርሃም፡ወወጥሐ፡ዕፀ፡ መልእልተ፡አእባን፡ወፈጸመ፡ኵሎ፡ግብሮ፡ ዘእንበለ፡ጥብሐት፡ባሕቲቱ።

ቆመ፡ሕፃን፡ከመ፡ይርአይ፡ዘይ ገብር፡አቡሁ፡ወእፎ፡ያዐርግ፡መሥ ዋዕተ።

ይቤሎ፡ይሥሐቅ፡አ፡አባ፡አንሰ፡እሬኢ፡ ከመ፡ተፈጸመ፡ኵሉ፡ዘእንበለ፡መሥዋዕት፡ ባሕቲቱ።

ወለእመ፡ትፈቅድ፡ትሠዐኒ፡ኪያየ፡አንሰ፡ ኢየአብየከ፡ነየ፡አነ፡እቀውም፡ማእከለ፡ እዴከ፡ግብር፡ይእዜ፡ዘፈቀድከ

፺፪፻፫

## ዓርብ፡መዓልት፡በ፫፡ሰዓት።

፻፶፩፤ አብርሃምም፡ቀረበ፤በተራራውም፡ራስ፡ ሾተሉንና፡እሳቱን፡አኖረ፤ለሚያርድ በትም፡መሠዊያ፡ይሠራ፡ዘንድ፡ወደሚፈ ቅደው፡ቦታ፡አየ።

፻፶፪፤ በሃይማኖት፡ጌጽ፡የተሸለመ፡አብርሃምም፡ የምሥጢር፡ቤት፡ትሆን፡ዘንድ፡ባላት፡ በጎልጎታ፡በዚያ፡ይሠራ፡ዘንድ፡መሠረቱን፡ አከናወነ።

፻፶፫፤ ይሥሐቅም፡ወደ፡አባቱ፡ወደሚሠራውም፡ በአየ፡ጊዜ፡ዕንጨቱን፡ከትከሻው፡ላይ፡ ወደ፡ምድር፡አወረደ፤ደንጊያዎችንም፡ያቀ ርብለት፡ነበር።

፻፶፬፤ መሠዊያውንም፡ካህኑ፡ሲሠራ፡አይቶ፡ ከእርሱ፡ጋራ፡ይሠራ፡ዘንድ፡ሥራውንም፡ በፍጥነት፡ይፈጸም፡ዘንድ፡እጁን፡ለሥራ፡ አስተባበረ።

፻፶፭፤ ካህን፡የሆነው፡አብርሃም፡ዳግመኛ፡ መሠዊያ፡የሚያንጽ፡ሆነ፤እርሱም፡የመሥ ዋዕት፡አባት፡ነው፤መሥዋዕት፡የሚሆነው፡ ይሥሐቅም፡በደንጊያው፡ክፍል፡ሠራተኛ፡ ነበር።

፻፶፮፤ እንግዲህ፡ለሚሰቀልበት፡መሠዊያ፡ይሠራ፡ ዘንድ፡ይገባዋል፤ሰው፡በሆነ፡ጊዜ፡የእግዚ አብሔር፡ልጅ፡በዚሁ፡አይነት፡ሁኖ፡ በፈቃዱ፡ይሞታልና።

፻፶፯፤ ሥራውም፡በተፈጸመ፡ጊዜ፡የታዘዘውን፡ ይፈጽም፡ዘንድ፡አብርሃምን፡እግዚአ ብሔር፡ተናገረው።

፻፶፰፤ የሚያቆምህ፡ምንድን፡ነው፡እጅህን፡አንቀ ሳቅስ፡ወደ፡ሥራህም፡ተነሣ፡አለው።

፻፶፱፤ አብርሃምም፡ቀርቦ፡በደንጊያው፡ላይ፡ እንጨቱን፡ረበረበ፤ከብቻው፡ከመሥ ዋዕት፡በቀር፡ሥራውን፡ሁሉ፡ፈጸመ።

፻፷፤ መሥዋዕቱን፡እንዴት፡እንደሚያሳርግ፡ አባቱ፡የሚሠራውን፡ያይ፡ዘንድ፡ሕፃኑ፡ ቆመ።

፻፷፩፤ ይሥሐቅ፡አባት፡ሆይ፡ከብቻው፡ መሥዋዕት፡በቀር፡ሁሉም፡እንደ፡ ተፈጸመ፡አያለሁ፡አለው።

፻፷፪፤ እኔን፡ትሠዋኝ፡ዘንድ፡ብትወድ፡እነሆ፡እኔ፡ እምቢ፡አልልህም፤በእጅህ፡መካከል፡ ቁሜአለሁ፤አሁን፡የወደድከውን፡በእኔ

Scanned by CamScanner

፻፸፬

## በ፲፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

ላዕሌየ፡ለእመ፡ነሣእከ፡መጥባሕተ፡በእን
ቲአየ፡ኢየአብየከ፡እንከ።

፻፳፬፤ ነዋ፡ዝ፡ኵሉ፡ተፈጸመ፡ዘእንበለ፡ጥብሐት፡ ባሕቲቱ። ወለእመ፡አነ፡ውእቱ፡ዘዕሠዋዕ፡ መኑ፡ ይከልአከ፡ ወዘከመዝ፡ ነገረ፡ ኮነ፡ ይሥሐቅ፡ይትናገር፡ምስለ፡አቡሁ፡ወዘይ በዝኑ፡እምዝ።

፻፳፭፤ ወለእመ ፡ ፈቀደ ፡ ይጕየይ ፡ እምኔሁ ፡ እምክህለ፡እስመ፡ወሬዛ፡ውእቱ።

፻፳፮፤ ወባሕቱ ፡ ኮነ ፡ ህዱአ ፡ እስከ ፡ ለመጥ ኀመዮ ፡ ወአትሐተ ፡ ርእሶ ፡ ለመጥ ባሕት።

፻፳፯፤ ወኢኮነ፡ሕፃነ፡ወኢሕጹጸ፡አእምሮ፡አላ፡ ውእቱ ፡ ወሬዛ ፡ በኃይሉ ፡ ወጠቢብ ፡ በንባቡ።

፻፳፰፤ ወሶበ፡ይሴአሎ፡አቡሁ፡ቃለ፡ያወሥእ፡ በእንቲአሁ፡ በአእምሮ ፡ ወሶበ ፡ ርእየ ፡ ሐብለ፡ ማእሰር ፡ ከመ ፡ በጽሐ ፡ ጊዜሁ ፡ አሰረ ፡ እደዊሁ ፡ ድኅሬተ ፡ ለሊሁ ፡ ወውእቱኬ ፡ በጽሐ ፡ በፈቃዱ ፡ ለተ ጠብሖ።

፻፳፱፤ እምኢክህለ ፡ አረጋዊ ፡ ልሂቅ ፡ አሲረ ፡ ወሬዛ ፡ አላ ፡ ውእቱ ፡ አምሳለ ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔር፡ አመ ፡ ስቅ ለት።

፻፴፤ ወበእንተዝ፡አትሐተ፡ርእሶ፡ከመ፡ይኩን፡ መሥዋዕተ ፡ ሕይወት ፡ ወጽድቅ ፡ ወይክሥት፡አምሳለ፡ንጉሥ፡ዘይትቀተል፡ በፈቃዱ።

፻፴፩፤ ወበእንተዝ ፡ ኮነ ፡ ይፈቅድ ፡ ከመ ፡ ኢይማስን፡ አምሳል ፡ በጊዜ ፡ ቀትል ፡ ወጥብሐት ፡ ወክዕወተ ፡ ደም ፡ እስመ ፡ ውእቱ፡ ኮነ ፡ ነሥአ ፡ ከመ ፡ ያዕርጎ ፡ መሥዋዕተ፡ዲበ፡ጎልጎታ።

፻፴፪፤ ወኮነ፡ይጸይሕ፡ፍኖተ፡ቅድመ፡ወልደ፡ ንጉሥ ፡ ዘበአማን ፡ መርዓዊ ፡ ዘሰቁል ፡ ወለእመ፡ውእቱ፡ኢኮነ፡በጊዜ፡ቅትለተ፡ ዋህዱ፡ፍሡሐ፡እምኢደለዎ፡ሎቱ፡ከመ፡ ይዕርግ።

፻፴፫፤ ወባሕቱ ፡ አዕረጎ ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔር

## ዓርብ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

ላይ ፡ አድርግ ፤ በእኔ ፡ ላይ ፡ ሾተል ፡ ብታነሣም፡እንግዲህ፡እምቢ፡አልልህም።

፻፳፬፤ ከብቻው ፡ ከመሠዋት ፡ በቀር ፡ ይህ ፡ እነሆ ፡ ሁሉ ፡ ተፈጸመ ፤ የምሠዋውም ፡ እኔ ፡ ከሆንኩ፡ ማነው ፡ የሚከለክልህ ፤ እንደዚህ፡ ያለውን፡ነገር፡ከዚህም፡የሚበዛ፡ይሥሐቅ፡ ከአባቱ፡ጋራ፡ይናገር፡ነበር።

፻፳፭፤ ሊሸሽም ፡ ቢወድ ፡ በቻለ ፡ ነበር ፤ ጎልማሳ፡ ነውና።

፻፳፮፤ ነገር፡ግን፡እስከ፡አሰረው፡ድረስ፡ጸጥ፡አለ፤ ራሱንም ፡ ለመሥዋዕትነት ፡ ዘንበል ፡ አድርጎ፡ሰጠ።

፻፳፯፤ አእምሮው ፡ ያልተስተካከለ ፡ ሕፃን ፡ አይደለም ፤ በሰውነቱ ፡ ጎልማሳ ፡ በንግግሩ፡ ብልሕ፡አዋቂ፡ነው፡እንጂ።

፻፳፰፤ አባቱም ፡ ቃልን ፡ በጠየቀው ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ እርሱ ፡ በትክክል ፡ ይመልስለታል ፤ የማሰሪ ያውንም ፡ ገመድ ፡ በአየ ፡ ጊዜ ፡ ጊዜው ፡ እንደ፡ ደረሰ ፡ እርሱ ፡ ራሱ ፡ እጆቹን ፡ የኋሊት፡ አሰረ ፤ እርሱም ፡ በፈቃዱ ፡ ለመሠዋት፡ቀረበ።

፻፳፱፤ ሽማግሌው ፡ ጎልማሳውን ፡ ማሰር ፡ ባልቻለም ፡ ነበረ ፤ በስቅለቱ ፡ ለሚሆነው ፡ ለእግዚአብሔር፡ልጅ፡ አምሳል ፡ ስለ ሆነ ፡ ነው፡እንጂ።

፻፴፤ ስለዚህም ፡ የሕይወትና ፡ የእውነት ፡ መሥዋዕት፡ይሆን፡ዘንድ፡በፈቃዱ፡የሚሠ ዋውን ፡ ንጉሥ ፡ አምሳል ፡ ይገልጽ ፡ ዘንድ ፡ ራሱን፡ለመሠዋት፡ዝቅ፡አደረገ።

፻፴፩፤ ስለዚህ ፡ በመገደልና ፡ በመሠዋት ፡ ጊዜ ፡ ደም ፡ በሚፈስም ፡ ጊዜ ፡ ምሳሌነቱ ፡ እንዳ ይጠፋ ፡ እርሱ ፡ በጎልጎታ ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ መሥዋዕት ፡ አድርጎ ፡ ሊያሳርገው ፡ ወስዶ ታልና።

፻፴፪፤ በሚሰቀለው ፡ ሙሽራ ፡ በእውነተኛው ፡ ንጉሥ ፡ ልጅ ፡ ፊት ፡ መንገድ ፡ ይጠርጋልና፤ በአንድ፡ልጁም፡መሠዋት፡ጊዜ፡ደስተኛ፡ ባይሆን፡ለዚህ፡ሥራ፡ይወጣ፡ዘንድ፡ባልተ ገባውም፡ነበር።

፻፴፫፤ ተራራውን ፡ በምሥጢሩ ፡ ደም ፡ ይረጭ ፡

Scanned by CamScanner

## በ፲፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

ከመ ፡ ይንሣእ ፡ ደብረ ፡ በደመ ፡ ምሥ
ጢር።

ወበእንተዝ ፡ ኮነ ፡ ዕጉሠ ፡ ከመ ፡ ርግብ ፡
በቅድመ፡መጥባሕት።

ወለእመ፡ኢኮነ፡ውእቱ፡ጽምወ፡እምኮነ፡
አምሳሉ፡ሙሱን።

ወለእመ ፡ ኢኮነ ፡ ውእቱ ፡ ከመ ፡ በግዕ ፡
በቅድመ ፡ ዘይቀርፆ ፡ ወኢከሠተ ፡ አፉሁ ፡
በሕማሙ፡እመኢተመሰሎ።

አርመመ ፡ ምሥጢር ፡ ወኢነበበ ።
ያደቶ ፡ አምሳለ ፡ ወልድ ፡ እምኵሉ ፡
ገጽ ፡ ወኮኑ ፡ ይብልዎ ፡ ተዐገሥ ፡ ወን
በር ። ልህበ ፡ ውስቴቱ ፡ ብርሃነ ፡ ሕይ
ወት ፡ ወጽልበተ ፡ አምሳለ ፡ ወልደ ፡ እግ
ዚአብሔር፡ ወነደ፡ በፍቅረ፡ወልድ፡ ከመ፡
ይኩን፡መሥዋዕተ።

ወበከመ፡ኢጐየ፡ይሥሐቅ፡እመጥባሕት፡
ከመ ፡ ኢይዕሉ ፡ አምሳለ ፡ ክርስቶስ ፡
አህድአ፡ ርእሶ ፡ ወወሀበ ፡ በፈቃዱ ፡
ለአቡሁ፡ ከመ ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡
ዘይቤ፡ለአቡሁ፡ኢይኩን፡ፈቃደ፡ዚአየ፡
ወባሕቱ፡ፈቃደ፡ዚአከ፡ለይኩን።

ወአብርሃምሰ ፡ ርእየ ፡ ላዕለ ፡ ወልዱ ፡
ወምሥዋዕ፡ይልህብ፡ወአንቃዕደወ፡አዕይ
ንቲሁ ፡ ላዕለ ፡ ወፈጸመ ፡ ኵሎ ፡ ግብሮ ፡
ዘእንበለ፡ጥብሐት፡ባሕቲቱ።

ወእምዝ ፡ ርእየ ፡ ኀበ ፡ ዋህዱ ፡ በፍቅር ፡
ወከማሁ፡ሕፃንኒ፡ኀበ፡አቡሁ፡ኮነ፡ይሬኢ፡
በክብር።

ነጸረ ፡ ካህን ፡ መሥዋዕተ ፡ ወበ
ግዕኒ ፡ አእመረ ፡ ዘይከውን ፡ ቦቱ ፡ ወዘ
እንበለ ፡ ይጸውዖ ፡ ቀርበ፡ ኀቤሁ ፡
በፍቅር ። ወአሰረ ፡ እደዊሁ ፡ በር
እሱ ፡ ወአትሐተ ፡ ርእሶ ፡ ለመጥ
ባሕት ፡ በፈቃዱ ፡ ወቀደመ ፡ ውእቱ ፡
አብርሃም ፡ እንዘ ፡ ኢየኀፍር ፡ ወኢያ
ሌዕል፡አዕይንቲሁ።

ወከነ፡ሶበ፡ቀርበ፡አቡሁ፡ኀበ፡ምሥዋዕ፡
ይቀድም፡እምኔሁ፡ከመ፡ይእስር፡ለሊሁ፡
ርእሶ።

## ዓርብ፡መዓልት፡በ፲፡ሰዓት።

ዘንድ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ አሳረገው ፡
እንጂ።

፻፷፬፤ ስለዚህም ፡ በመሠዋት ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ የዋህ ፡
ርግብ፡ታጋሽ፡ሆነ።

፻፷፭፤ እርሱ ፡ ጭምት ፡ (ትዕግሥተኛ) ፡ ባይሆን ፡
ምሳሌነቱ፡ብላሽ፡በሆነ፡ነበር።

፻፷፮፤ በሚሸልቱት ፡ ፊት ፡ እድማይናገር ፡ በግ ፡
ባይሆን፡ኖሮ፡በመከራው፡ባልመሰለውም፡
ነበር

፻፷፯፤ አምላካዊ ፡ ምሥጢር፡ዝም፡አሰኛችው፡አል
ተናገረም ፤ የወልድም ፡ አምሳል ፡ በአራቱ ፡
ማዕዘን ፡ ዞረችው ፤ ምሥጢራትም ፡ ታገሥ ፡
ተቀመጥ ፡ የሚሉት ፡ ሆኑ ፤ የሕይወት ፡
ብርሃንም ፡ በውስጡ ፡ ተሟሟቀ ፤ የእግዚአ
ብሔር ፡ ልጅ ፡ መስቀልም ፡ በወልድ ፡ ፍቅር፡
መሥዋዕት፡ይሆን፡ዘንድ፡ተቃጠለ።

፻፷፰፤ ይሥሐቅ፡ከመሠዋት፡እንዳልሸሸ፡የክርስ
ቶስን፡ አምሳል፡እንዳይለውጥ፡ጸጥ፡ብሎ፡
ራሱን ፡ በፈቃዱ ፡ ለአባቱ ፡ እንደ ፡ ሰጠ ፤
የእኔ፡ ፈቃድ ፡ ያይደለ ፡ ያንተ ፡ ፈቃድ ፡
ይሁን ፡ እንጂ ፡ እንዳለ ፤ እንደ እግዚአ
ብሔር፡ልጅ፡ አምሳል፡ነው።

፻፷፱፤ አብርሃምም፡በልጁ፡ላይ፡ተመለከተ፤መሠ
ዊያውም ፡ ይሟሟቅ ፡ ነበር ፤ ዐይኖቹንም ፡
ወደ፡ላይ፡አነሣ፡ከመሠዋት፡ብቻ፡በቀር፡
ሥራውን፡ሁሉ፡አከናወነ።

፻፸፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ አብርሃም ፡ ወደ ፡ አንድ ፡
ልጁ ፡ በፍቅር ፡ ተመለከተ ፤ ሕፃኑም ፡ ወደ ፡
አባቱ፡በአክብሮት፡የሚመለከት፡ሆነ።

፻፸፩፤ ካህን ፡ አብርሃም ፡ መሥዋዕቱን ፡ ይሥ
ሐቅን፡ ተመለከተ ፤ በግዕ ፡ ይሥሐቅም፡
በእርሱ፡ላይ፡የሚደረግበትን፡አወቀ፤ሳይ
ጠራውም ፡ ወደ ፡ አባቱ ፡ በፍቅር ፡ ቀረበ ፤
ራሱ ፡ እጆቹን ፡ አሰረ ፤ ለመሠዋትም ፡
በፈቃዱ ፡ ራሱን ፡ ዝቅ ፡ አደረገ ፤ አብር
ሃምም፡ ሳያፍርና ፡ ዐይኖቹን ፡ ቀና ፡
ሳያደርግ፡ቀደም፡አለ።

፻፸፪፤ እንዲህም፡ሆነ፤አባቱ፡ወደ፡መሠዊያው፡
በቀረበ ፡ ጊዜ ፡ ይሥሐቅ ፡ ራሱን ፡ በራሱ ፡
ያስር፡ዘንድ፡ከእርሱ፡ይቀድም፡ነበር።

Scanned by CamScanner

| በ፫፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ። | ዓርብ፡መዓልት፡በ፫፡ሰዓት። |
|---|---|
| ፻፹፫፤ ወእምዝ ፡ ቀርበ ፡ አብርሃም ፡ እንዘ ፡ ይትፌሣሕ ፡ ወነሥአ ፡ ለይሥሐቅ ፡ ወኀመዮ። | ፻፹፫፤ ከዚያም ፡ አብርሃም ፡ ደስ ፡ እያለው ፡ ቀረበ ፤ ይሥሐቅንም ፡ ወስዶ ፡ አሰረው። |
| ፻፹፬፤ ወአዕረጎ ፡ ዲበ ፡ ምሥዋዕ ፡ ወይቤሎ ፡ ኢትሕዝንኬ ፡ አ ፡ ወልድየ ፡ እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ አዘዘኒ ፡ ከመ ፡ አዕርገ ፡ መሥዋዕተ፡ሎቱ። | ፻፹፬፤ በመሠዊያው ፡ ላይም ፡ አወጣው ፤ ልጄ ፡ ሆይ፡ አትዘን ፤ ለእርሱ ፡ መሥዋዕት ፡ አድርጌ፡እንዳሳርግህ፡እግዚአብሔር፡አዝዞ ኛልና፡አለው። |
| ፻፹፭፤ ወበእንተዝ፡አነ፡አቀርበከ፡ሎቱ፡ወሑር፡ አ፡ወልድየ፡ወፍቁርየ፡ጽንሐኒ፡ውስተ፡ መንግሥተ፡ሰማያት፡እስከ፡እትራከበከ፡ አነ፡እምላኪየ፡ውእቱ፡ይፈቅደከ፡ከመ፡ ትሑር፡ኀቤሁ።ኢትሕዝንኬ፡አ፡ወልድየ፡ እስመ ፡ ኢተአምር ፡ ኀበ ፡ አይ ፡ ብዕል ፡ ተሐውር፡አንተ። | ፻፹፭፤ ስለዚህም ፡ ለእርሱ ፡ እሠዋሃለሁ ፤ ልጄ ፡ ወዳጄ ፡ ሆይ ፡ እኔ ፡ እስከምገናኝህ ፡ ድረስ፡ ሂደህ ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ጠብቀኝ፤ ወደ፡እርሱ፡ትሄድ፡ዘንድ፡ፈጣሪዬ፡ይፈቅ ድሀልና፤ልጄ፡ሆይ፡አትዘን፡ወደየትኛው፡ ብልጽግና ፡ እንደምትሄድ ፡ አንተ ፡ አታው ቅምና። |
| ፻፹፮፤ እስመ ፡ አነ ፡ እፌንወከ ፡ ኀበ ፡ ንጉሠ ፡ መልዕልት፡ወዕመቅ። | ፻፹፮፤ ወደ ፡ ሰማይና ፡ ወደ ፡ ምድር፡ንጉሥ፡እኔ፡ እልክሀለሁና። |
| ፻፹፯፤ አውሥአ፡ይሥሐቅ፡እንዘ፡ይብል፡እፎ፡ ይደልወኒ፡አ፡አባ፡ከመ፡እሕዝን፡እንዘ፡ አንተ፡ትፈቅድ፡ትረስየኒ፡ውስተ፡ዐቢይ፡ ብዕል። | ፻፹፯፤ ይሥሐቅም ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መለሰለት፤ አባት ፡ ሆ ፡ አንተ ፡ በታላቅ ፡ ክብር ፡ ውስጥ፡ስታ፦ርገኝ፡አዝን፡ዘንድ፡እንዴት፡ ይገባኛል? |
| ፻፹፰፤ ሞት፡ዘአነ፡ውስቴቱ፡ይእዜ፡ኢኮነ፡ሞተ፡ አላ፡ረባሕ፡ወሕይወት። | ፻፹፰፤ አሁን ፡ እኔ ፡ በውስጡ ፡ ያለሁበት ፡ ሞት ፡ ሞት፡አይደለም።ጥቅምና፡ሕይወት፡ነው፡ እንጂ። |
| ፻፹፱፤ ይጼኑ፡ሊተ፡መዐዛ፡ሠናይ፡ወይጥዕመኒ፡ ሰማዕኩ፡ከመ፡ሞት፡መሪር፡ለዘይጥዕሞ፡ ወዛቲሰ፡ሞት፡ዘአነ፡እፈቅድ፡እጥዐማ፡ ጥዕምት፡ይእቲ።አስተጠዓምክዋ፡እንከ፡ ጥቀ ፡ ወኢኮነ ፡ መዓርኒ ፡ ከመ ፡ ጣዕማ ፡ በኀቤየ። | ፻፹፱፤ በጎ፡መዐዛም፡ሸተተኝ፤ጣፈጠኝም፤ሞት፡ መራራ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሰምቼ ፡ ነበር፤እኔ፡ ልቀምሳት ፡ የምፈልጋት ፡ ሞት ፡ ግን ፡ እጅግ፡ ጣፋጭ ፡ ናት ፤ አጣጣምኳት ፡ በእኔ ፡ ዘንድ፡ማር፡እንኳን፡እንደ፡እርሷ፡ጣዕም፡ አልሆነም። |
| ፻፺፤ ወበከመሰ፡እኄሊ፡እስመ፡ሐዳስ፡ሕይወት፡ ትፈልፍል፡ሊተ፡እምኔሃ።አንሰ፡ኢይትዐ አስተርአየ፡ሊተ፡እምታሕተ፡መጥባሕት፡ ወቀኒ፡ሐዘነ፡ሞት፡አላ፡ዐቢይ፡ምሕረት፡ ወኢይተርናፍ፡እንከ፡እመዊት፡ዘኮነ፡ከዊኖ፡ እምቀሪብ፡ኀበ፡ዝንቱ፡ሞት፡ኀበ፡ሀለወ፡ ውእቱ። | ፻፺፤ እንደማስበውም፡ከእርስዋ፡አዲስ፡ሕይወት፡ ይመነጭልኛል ፡ እኮን ፤ እኔ ፡ የሞት፡ሐዘን፡ አይታወቀኝም ፤ ታላቅ ፡ ምሕረት ፡ ከመሠዋት፡በታች፡ተገለጸልኝ፡እንጂ፤የሆነ፡ ሆኖ ፡ እንግዲህ ፡ ከመሞት ፡ ይህ፡ ሞት ፡ወደ፡ አለበት፡ከመቅረብ፡አልቀርም። |
| ፻፺፩፤ ፈጽም፡ይእዜ፡ፈቃደከ፡ላዕሌየ፡አ፡ካህን፡ ዘድልው፡ለመሥዋዕት፡ትሩፍ። | ፻፺፩፤ ፍጹም፡መሥዋዕት፡ለማቅረብ፡ዝግጁ፡የሆንክ፡ ካህን፡ሆይ፤አሁን፡ፈቃድህን፡ፈጽም። |
| ፻፺፪፤ ወአንሥአ ፡ አብርሃም ፡ እዴሁ ፡ ወነሥአ ፡ | ፻፺፪፤ አብርሃምም ፡ እጁን ፡ አንሥቶ ፡ ይሠዋው ፡ |

Scanned by CamScanner

በ፫፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

መጥባሕተ ፡ ከመ ፡ ይሕርዶ ፡ ወተሐፅበ ፡
እዴሁ፡በደም፡ዘይፈቅድ፡ይክዐዎ፡ህየ።
፻፺፫ ወካነ ፡ ከመ ፡ ዘሐረዶ ፡ ወገደፈ ፡ በድኖ ፡
ወጠብሖ፡ለወሬዛ፡በኀሊናሁ፡እምቅድመ፡
ገቢር፡ዘእንበለ፡ሐዘን።
፻፺፬ ወበከመ ፡ እድ ፡ ጕጕዕት ፡ ከዐወት ፡ ደመ ፡
ዋህዱ።
፻፺፭ ወሶበ፡ተፈጸማ፡ኵሎን፡ግብራት፡ዘውእቱ፡
አምሳሊሁ ፡ ለክርስቶስ ፡ ዘእንበለ ፡
መጥባሕት ፤ ወእምዝ ፡ ረሰየ ፡ አብርሃም ፡
መጥባሕቶ ፡ ውስተ ፡ ክሣደ ፡ ይሥሐቅ ፡
ሕፃን።
፻፺፮ ወመጽአ ፡ ቃል ፡ ወይቤሎ ፡ አ ፡ አብርሃም ፡
ኢትፈጽም ፡ መጥባሕተ ፡ ዲበ ፡ ክሣደ ፡
ይሥሐቅ፡ሕፃን።
፻፺፯ ወከልአ፡ውእቱ፡ቃል፡ለመጥባሕት፡ከመ፡
ኢይሕርዶ ክልኤ ፡ ጊዜ ፡ አይድዖ ፡ ውእቱ ፡
ቃል፡ከመ፡ኢያንሳሕስሕ፡መጥባሕተ፡ዲበ፡
ክሣደ፡ሕፃን።
፻፺፰ ወሜጠ፡ኀበ፡ፀጋሙ፡ከመ፡ኢያንሳሕስሕ፡
ዲበ፡ክሣደ፡ሕፃን።
፻፺፱ ወበውእቶን ፡ ቃላት ፡ መትልዋት ፡
ተከልአት፡ ሶቤሃ ፡ እደ ፡ አረጋዊ ፡
እምጠቢሕ።
፪፻ ወክልኤቱ ፡ አስተብቍዖታት ፡ ዘሰምዖን ፡
ከልአሁ፡እምሐሪድ።
፪፻፩ ጸውዖ፡መልአክ፡ለአብርሃም፡እንዘ፡ይብል፡
ኢትስፋሕ ፡ እዴከ ፡ ላዕለ ፡ ሕፃን ፡ ወኢት
ቅረቦ ፡ ለጠቢሕ ፡ እስመ ፡ አንተ ፡ በጻሕከ ፡
ውስተ ፡ ፍኖተ ፡ ምሥጢራት ፡ ዐቢይ ፡
ወኢትሑር፡እንከ፡ካልአ፡ምሕዋረ፡እስመ፡
ኢትክል።
፪፻፪ ወኢይከውን፡መድኃኒተ፡ዓለም፡በክዕወተ፡
ደመ፡ይሥሐቅ፡ወልድከ፡አንሥእ፡መጥባ
ሕተከ ፡ እምነ ፡ የዋህ ፡ ወፍትሖ ፡ እምነ ፡
ማእሰሩ፡ለይረድ፡እምደብር።
፪፻፫ እስመ ፡ በደመ ፡ ዝንቱ ፡ ድኩም ፡ ኢይድኅን ፡
ኵሉ ፡ ዓለም ፡ ወአልቦቱ ፡ ሥልጣን ፡ ከመ ፡
የሀብ ፡ ሕይወተ ፡ ወፍትሖ ፡ እንከ ፡ ወኅድጎ ፡
ይሑር፡ፍኖቶ።
፪፻፬ ነዋ ፡ ሀለወት ፡ መጽሔተ ፡ ምሥጢራት ፡
ዝየ ፡ ቅረብ ፡ ኀቤሃ ፡ ወርኢ ፡ አምሳለ ፡
ዘበአማን።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፫፡ሰዓት።

ዘንድ፡ሾተሉን፡ያዘ፤በዚያ፡ያፈሰው፡ዘንድ፡
በሚፈልገው፡ደም፡እጁን፡ታጠበ።
፻፺፫ አርዶ፡በድኑን፡እንደ፡ጣለውም፡ሆነ፤ከማ
ድረግም፡በፊት፡ጐልማሳውን፡ያለ፡ሐዘን፡
በኀሳቡ፡አርዶታል።
፻፺፬ የምትቸኵል ፡ እጅ ፡ የአንድ ፡ ልጁን ፡ ደም ፡
እንደ፡አፈሰሰች።
፻፺፭ ሥራዎችም ፡ ሁሉ ፡ በተፈጸሙ ፡ ጊዜ ፡
ይኸውም ፡ የክርስቶስ ፡ አምሳል ፡ ነበር ፤
ከመሠዋት ፡ በቀር ፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡
አብርሃም፡ሾተሉን፡በሕፃኑ፡አንገት፡ላይ፡
አደረገ።
፻፺፮ ከሰማይም ፡ ቃል ፡ መጣ ፤ አብርሃም ፡ ሆይ ፡
በሕፃኑ ፡ ይሥሐቅ ፡ አንገት ፡ ላይ ፡ ስለት ፡
መሳብን፡አትፈጽም፡አለው።
፻፺፯ እንዳይሠዋውም፡በሕፃኑ፡አንገት፡ላይም፡
ሾተሉን፡እንዳያንቀሳቅስ፡ያ፡ቃል፡ሁለት፡
ጊዜ፡ከለከለው።
፻፺፰ በሕፃኑ ፡ አንገት ፡ ላይም ፡ ሾተሉን ፡ እንዳ
ይስብ፡ወደ፡ግራው፡መለሰው።
፻፺፱ በእነዚያም ፡ በተከታታይ ፡ ቃሎች ፡ የሽማ
ግሌው፡እጅ፡ከመሠዋት፡ተከለከለች።
፪፻ የሰማቸው ፡ ሁለቱ ፡ ቃሎችም ፡ ከመሠዋት ፡
ከለከሉት።
፪፻፩ መልአክም ፡ አብርሃምን ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡
ጠራው፤በሕፃኑ፡ላይም፡እጅህን፡አትዘርጋ፡
ለማረድም ፡ አትቅረበው ፤ አንተ ፡ ወደ ፡
ትልቅ ፡ ምሥጢር ፡ ውስጥ ፡ ደርሰሃልና ፡
እንግዲህ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ አቅጣጫ ፡ ትሄድ ፡
ዘንድ፡አትችልምና።
፪፻፪ በልጅህ ፡ በይሥሐቅ ፡ ደም ፡ መፍሰስ ፡
የዓለም፡ ድኅነት ፡ አይሆንምና ፡ ከየዋሁ ፡
ይሥሐቅ፡ላይ፡ሾተልህን፡አንሣ፤እንግዲህ፡
ከማሰሪያው፡ፍታውና፡ከተራራው፡ወርዶ፡
ይሂድ።
፪፻፫ በዚህ፡በደካማው፡ደም፡የዓለም፡ምርኮ፡አይ
መለስምና፤ሕይወትንም፡ሊሰጥ፡ሥልጣን፡
የለውምና ፡ እንግዲህ ፡ ፈትተህ ፡ ተወው ፡
መንገዱን፡ይሂድ።
፪፻፬ እነሆ ፡ ከዚህ ፡ የምሥጢር ፡ መነጽር ፡ አለች፤
ወደ ፡ እስዋ ፡ ቀርበህ ፡ እውነተኛውን ፡
አምሳል፡ተመልከት።

Scanned by CamScanner

በ፲፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

፪፻፭፡ ከመዝ፡ ይቤ፡ **እግዚአብሔር**፡ አነኒ፡ እሜጡ፡ ወልድየ፡ ወኢይምህክ፡ ለዘባሕቲቱ፡ ሊተ፡ ወእሬስዮ፡ ቤዛ፡ ዓለም፡ ወኢየሐዝን፡ በእንቲአሁ።

፪፻፮፡ ይእዜኒ፡ ወሀብኩከ፡ አምሳሊሁ፡ ከመ፡ ትትፌሣሕ፡ ቦቱ፡ ወዕቀቦ፡ እንከ፡ እስከ፡ ተፍጻሜት።

፪፻፯፡ እስመ፡ ኢክህለ፡ ዝንቱ፡ ድኩም፡ ከመ፡ ይጺውዋ፡ ለሲኦል፡ ወዘሊተሰ፡ ዋህድየ፡ ይወርድ፡ወይሰልባ፡ኵሎ፡መዛግብቲሃ።

፪፻፰፡ ወለይሥሐቅሰ፡አልቦቱ፡ኃይል፡ኀበ፡ፍኖተ፡ሞት፡በዊእ።

፪፻፱፡ ወጽኑዐ፡ ኃይልሰ፡ ይወርድ፡ ወይዘርዋ፡ ለሲኦል፡ወያጠፍኣ፡ወያመዘብራ።

፪፻፲፡ ወሶበ፡ቦአ፡ይሥሐቅ፡ኀበ፡ምውታን፡ኢይበቍዖሙ፡ወኢምንትኒ።

፪፻፲፩፡ ወልድየ፡ ጽኑዐ፡ ኃይል፡ ይበውእ፡ ወያወጽኦሙ፡ ከመ፡ ኃያል፡ ወጽኑዕ፡ ወልድከሰ፡ ይከውን፡መሥዋዕተ፡ወአኮ፡ዘቦቱ፡በቍዔት፡ ለሰብእ።

፪፻፲፪፡ ወሊቀ፡ ክህናትሰ፡ ይጠባሕ፡ ወይከውን፡ **መድኃኒተ**፡ ለኵሉ፡ዓለም።

፪፻፲፫፡ ኢይከውን፡ሎቱ፡ለዊዋ፡መድኃኒት፡በገብር፡ ወኢትሕርዶ፡እንከ፡አላ፡ተዓገሥ፡ እስመ፡ ወልደ፡ንጉሥ፡ያድኅን፡ፍጥረቶ።

፪፻፲፬፡ ወተፈሥሐ፡አብርሃም፡በዕለተ፡**ወልደ፡እግዚአብሔር**፡ ዘርእየ፡በአምሳለ፡ወልዱ።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፲፡ሰዓት።

፪፻፭፡ **እግዚአብሔርም**፡ እንዲህ፡ አለ፤ እኔም፡ ለእኔ፡ አንድ፡ የሆነውን፡ ልጄን፡ አሳልፌ፡ እሰጣ ለሁ፤አልራራለትም፤ለዓለምም፡መድኅኒት፡አደርጋ ዋለሁ፤ስለ፡እርሱም፡አላዝንም።

፪፻፮፡ በእርሱ፡ ደስ፡ ይልህ፡ ዘንድ፡ አሁን፡ ምሳሌውን፡ ገለጽሁልህ፤ እስከ፡ መጨረሻም፡ እንዲህ፡ጠብቀው።

፪፻፯፡ ይህ፡ ደካማው፡ ልጅህ፡ በሲኦል፡ ያሉትን፡ ነፍሳት፡ ሊማርክ፡ አይችልምና፡ የእኔ፡ አንድ፡ ልጄ፡ ግን፡ ወርዶ፡ ያደለበችውን፡ ሁሉ፡ ይበዘ ብዛታል።

፪፻፰፡ ይሥሐቅማ፡ ወደ፡ ሞት፡ መንገድ፡ ይገባ፡ ዘንድ፡ኃይል፡የለውም።

፪፻፱፡ የኃይል፡ ባለቤት፡ ልጄ፡ ግን፡ ወርዶ፡ ሲኦልን፡ ይበትናታል፡ያፈርሳታል።

፪፻፲፡ ይሥሐቅም፡ ወደ፡ ሙታን፡ ከተማ በገባ፡ ጊዜ፡ ፈጽሞ፡ምንም፡ምን፡አይጠቅማቸውም።

፪፻፲፩፡ የኃይል፡ ባለቤት፡ ልጄ፡ ጽኑዕ፡ ኃያል፡ እንደ፡ መሆኑ፡ ይገባል፤ ያወጣቸዋልም፤ ልጅህ፡ ግን፡ መሥዋዕት፡ መሆን፡ ይችላል፤ ሰውን፡ ለማዳን፡ ግን፡ችሎታ፡የለውም።

፪፻፲፪፡ ሊቀ፡ ካህናቱ፡ ልጄ፡ ግን፡ መሥዋዕት፡ ሆኖ፡ ለዓለሙ፡ሁሉ፡**መድኃኒት**፡ ይሆናል።

፪፻፲፫፡ በፍጡር፡ ደም፡ ለምርኮኞች፡ መድኃኒትነት፡ አይሆንምና፡ አትረደው፤ እንግዲህ፡ ታገሥ፡ እንጂ፤የንጉሥ፡ልጅ፡ፍጥረቱን፡ያድናልና።

፪፻፲፬፡ አብርሃምም፡ በልጁ፡ አምሳል፡ በአየው፡ **በእግዚአብሔር፡ልጅ**፡ ቀን፡ደስ፡አለው።

ዘከመ ከልአ መልአከ እግዚአብሔር ለአብርሃም ከመ ኢይሡዖ ለይስሐቅ ወልዱ።



የእግዚአብሔር መልአክ አብርሃምን ልጁ ይስሐቅን እንዳይሠዋው እንደከለከለው

ዘከመ፡ ከልአ፡ መልአከ፡ **እግዚአብሔር**፡ ለአብርሃም፡ከመ፡ኢይሡዖ፡ለይስሐቅ፡ወልዱ።

፪፻፲፭፡ አእመረ፡ኵሎ፡ግብሮ፡ስቅለት፡ወአምሳለ፡ ወፈከረ፡ ሎቱ፡ ምሥጢራተ፡ ኀቡአተ፡ ለጠቢሐ፡ወልዱ።

፪፻፲፮፡ ወኮነ፡ይኄሊ፡ቦቱ፡በአምሳል፡ዘሀየ፡ወእንዘ፡ ይኄሊ፡ ውእቱ፡ እፎ፡ ወማእዜ፡ ወአይቴ፡ ወእንዘ፡ ከመዝ፡ ውእቱ፡ ናሁ፡ በግዕ፡ እኁዝ፡ በአዕጹቀ፡ዕፅ።

፪፻፲፯፡ ወአስተርአዮ፡ በግዕ፡ ልደተ፡ ወቅትለተ፡ ወትንሣኤ፡ወኵሎ፡ምሥጢረ፡ዘሀሎ፡ይኩን።

አብርሃም፡ልጁ፡ይስሐቅን፡እንዳይሰዋው፡**የእግዚአብሔር**፡ መልአክ፡እንደከለከለው።

፪፻፲፭፡ ምሳሌውንና፡ የስቅለትን፡ ሥራዎች፡ ሁሉ፡ አወቀ፤ ልጁን፡ ለመሠዋት፡ የተሸሸጉትን፡ ምሥጢራትን፡ገለጸለት።

፪፻፲፮፡ በዚያም፡ ሳለ፡ በምሳሌው፡ የሚያስብ፡ ሆነ፤ እርሱም፡ እንዴት? መቼ? ወዴት? ይሆን፡ እያለ፡ ሲያስብ፤ በእንደዚህ፡ ያለ፡ ሐሳብ፡ ሳለ፡ እነሆ፡ በእንጨት፡ሐረግ፡በግ፡ተይዞ፡ተገኘ።

፪፻፲፯፡ በጉ፡ልደትን፡ሞትን፡ትንሣኤን፡ይሆን፡ዘንድ፡ ያለውን፡ምሥጢር፡ሁሉ፡አሳየው።

Scanned by CamScanner

## በ፲፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

፪፻፲፰ ተንሥአ፡ ይሥሐቅ ፡ ወአርአየ፡ ርእሶ ፡
ሎቱ፡ ወአለበዎ ፡ ዘይከውን ፡ ሎቱ ፤
ወይቤሎ ፡ ለእመ ፡ ትፈቅድ ፡ ትርአዮ ፡
ለመሲሕ፡ ዝ፡ውእቱ፡ጊዜሁ፡ርኢ፡ዕለቶ፡
ይእዜ፡ወተፈሣሕ።
፪፻፲፱ ወለእመ፡ፈቀድከ፡ትርአይ፡ዕለቶ፡ነጽር፡
ዘንተ፡ዕፀ፡ወእመሂ፡ፈቀድከ፡ትርአይ፡
ቅትለቶሂ ፡ ወትንሣኤሁ ፡ ዝ ፡ ውእቱ ፡
ቅድሜከ፡እስመ፡ልደቱ፡ከመ፡ዝንቱ፡
በግዕ፡ዘእንበለ፡ትድምርት፤ወትንሣኤሁ፡
በከመ፡ድኅነ፡ይሥሓቅ፡ወሬዛ፡እምጥ
ብሐት።
፪፻፳ ወበእንተ፡አፍቅሮቱ፡ኪያከ፡ከሠተ፡ለከ፡
ልደቶ፡ወሞቶ፡ወአመረከ፡ዘከመ፡እፎ፡
ይከውን፡መሥዋዕት፡እንተ፡ውስተ፡
ምሥዋዕ፡ወዓዲ፡እምልደተ፡ዕፀ፡
ተአምር፡ዘንተ፡ኢትሬኢኑ፡ዘከመ፡እምአ
ዕጹቅ፡ንጹሓት፡ወጽኑዓት፡ኮነ፡ልደተ፡
በግዕ።
፪፻፳፩ ፍታሕ፡ ይእዜኒ ፡ ክሣደ ፡ ይሥሐቅ ፡
ወኅድጎ፡ ይሖር ፡ በሰላም ፡ እስመ ፡
አእመርከ፡ዘከመ፡እፎ፡ይመውእ፡ለሞት፡
ወልደ፡እግዚአብሔር።
፪፻፳፪ ነዋ፡ዝንቱ፡ልደቱ፡ወስቅለቱ፡ማዕከለ፡
እደዊከ፡ርኢ፡ወለቡ፡ቃላተ፡ዘይቤለከ፡
ዑቅ ፡ ወኢትአብስ ፡ ወኢትጥብሖ ፡
ለይሥሐቅ፡ዘውእቱ፡እምሩካቤ፡አላ፡
ፍትሖ፡ ወጥብሖ ፡ ለበግዕ ፡ ዘእንበለ ፡
ትድምርት።
፪፻፳፫ ንዛህ፡ምሥዋዐ፡በደመ፡ምሥጢራት፡
ወረሲ፡ ሰላመ ፡ ወተፈሣሕ ፡ በእንተ ፡
ጽድቅ፡ዘተከሥተ፡ለከ፡ዮም።
፪፻፳፬ ቀርበ፡እንከ፡አብርሃም፡ወፈትሐ፡ወልዶ፡
ወአሰሮ፡ለበግዕ።
፪፻፳፭ ወተመሰለ፡ሎቱ፡አምሳለ፡ካልዕ፡ካዕበ፡
ለጻድቅ፡ ዘከመ ፡ ይፈትሕ ፡ ክርስቶስ ፡
ማእሰረ፡አምልኮ፡ጣዖታት፤ወአንተኒ፡
ፍታሕ፡ማእሰረ፡ይሥሐቅ።
፪፻፳፮ ኮነ፡እንከ፡ይሥሐቅ፡እሱረ፡በማእሰረ፡
ሰይጣን፡እስከ፡በጽሐ፡ወልድ፡ ዘኢኮነ፡
በተዋስበ፡ወበተከ፡ማዕሰሪሁ።
፪፻፳፯ ወእምዝ፡ ጦብሐ ፡ አብርሃም ፡ በግዐ ፡
ምሥጢራት ፡ ወድኅነ ፡ ይሥሐቅ ፡
ወተፈሥሐ፡አብርሃም፡አቡሁ፡በእንተ፡
ሕይወተ፡ወልዱ፡ዋህድ።

## ዓርብ፡መዓልት፡በ፲፡ሰዓት።

፪፻፲፰፤ ይሥሐቅም፡ተነሥቶ፡ራሱን፡አሳየው፤
ለእርሱ ፡ የሚሆነውንም ፡ ልብ ፡ አስደ
ረገው፤መሲሕ፡ክርስቶስን፡ታየው፡ዘንድ፡
ጊዜው፡ይህ፡ነው፤የእርሱንም፡ቀን፡ዛሬ፡
አይተህ፡ደስ፡ይበልህ፡አለው።
፪፻፲፱፤ ቀኑንም፡ታይ፡ዘንድ፡ከወደድክ፡ይኸንን፡
እንጨት፡ተመልከት፤ሞቱንና፡ትንሣኤ
ውንም፡ታይ፡ዘንድ፡ብትፈልግ፡ይኸው፡
በፊትህ፡ነው፤ልደቱ፡እንደዚህ፡በግ፡ያለ፡
ዘር ፡ መገኘት ፡ ሲሆን ፡ ትንሣኤውም ፡
ጎልማሳው፡ይሥሐቅ፡ከመሠዋት፡ድኖ፡
እንደ፡መነሣቱ፡ነው።
፪፻፳፤ አንተንም፡ስለ፡መውደዱ፡ልደቱንና፡
ሞቱን፡ገለጸልህ፤በመሠዊያ፡ውስጥም፡
እንዴት ፡ እንደሚሠዋ ፡ አመለከተህ፤
ዳግመኛም ፡ ከእንጨት ፡ ከተወለደው ፡
በግ፡ ይህን ፡ ታውቃለህ፤የበጉ፡ልደት፡
ንጹሐንና፡ጽኑዓን፡ከሆኑ፡ሐረጎች፡እንደ፡
ሆነ፡አታይምን።
፪፻፳፩፤ አሁን፡ይሥሐቅን፡አንገቱን፡ፍታውና፡
ተወው፤በሰላም፡ይሂድ፤የእግዚአብሔር፡
ልጅ፡ ሞትን፡እንዴት፡ድል፡እንደሚያደ
ርገው፡አውቀሃልና።
፪፻፳፪፤ እነሆ፡ይህ፡ልደቱ፡ስቅለቱ፡በእጆችህ፡
መካከል፡ነው፤እይ፡እወቅ፡ያለህን፡ቃል፡
አስተውል፤አትበድል፤በዘር፡በሩካቤ፡
የሆነውን፡ይሥሐቅን፡አትሠዋው፤አሰና
ብተው፤ያለ፡ዘር፡ያለ፡ሩካቤ፡የተገኘውን፡
በጉን፡ሠዋው፡እንጂ።
፪፻፳፫፤ መሠዊያውንም ፡ በምሥጢሩ ፡ ደም ፡
ረጭተህ፡ፍቅር፡አንድነትን፡አድርግ፤
ዕውነተኛውንም፡አምሳል፡ስለ፡ገለጸልህ፡
ዛሬ፡ደስ፡ይበልህ።
፪፻፳፬፤ እንግዲህ፡አብርሃም፡ቀረበ፤ልጁንም፡
ፈትቶ፡በጉን፡አሰረው።
፪፻፳፭፤ ሁለተኛም፡ለጻድቁ፡አብርሃም፡በሌላ፡
አምሳል ፡ ተመሰለለት፤ክርስቶስ፡ የአ
ምልኮ፡ጣዖታትን፡ማሰሪያ፡እንደሚፈታ፡
አንተም፡የይሥሐቅን፡ማሰሪያ፡ፍታ።
፪፻፳፮፤ እንግዲህ፡ይሥሐቅ፡በሰይጣን፡ማሰሪያ፡
የታሰረ፡ሁኖ፡ነበር፤ያለ፡ዘር፡ያለ፡ሩካቤ፡
የተገኘው፡ወልድ፡ እስከ፡መጣና፡ማሰሪ
ያውን፡እስከ፡ቆረጠ፡ድረስ።
፪፻፳፯፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ አብርሃም ፡ የምሥ
ጢሩን፡በግ፡አረደ፤ይሥሐቅም፡ዳነ፤አብ
ርሃምም፡ስለ፡አንድ፡ልጁ፡መዳን፡ደስ፡
አለው።

Scanned by CamScanner

በ፲፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

፻፳፫፡ ወይቤ፡ካዕበ፡በሩክ፡ውእቱ፡እምላክነ፡ ወእግዚእነ፡ ወመልእክ፡ መድኃኒትነ፡ ወሀቤ፡ፍሥሓ፡ወሰዳዴ፡ሐዘን።

፻፳፬፡ ሎቱ፡ስብሐት፡ወክብር፡ለዓለመ፡ዓለም፡ አሜን።

፻፴፡ ወይረሲ፡ እግዚአብሔር፡ ማኅደሮ፡ ለአቡነ፡ አባ፡ ሰላማ፡ ጳጳስ፡ ርቱዐ፡ ሃይማኖት፡ዘተርጎሞ፡ለዝንቱ፡ድርሳን፡ እምዐረቢ፡ለግዕዝ፡ምስሌሆሙ፡ድርገተ፡ አሜን።

ወካዕበ፡ይቤ፡አቡነ፡ቅዱስ፡አትናቴዎስ፡ ሐዋርያዊ፡በውስተ፡ድርሳኑ፡ዘተናገረ፡ ቦቱ፡ምስለ፡አይሁድ፡በእንተ፡እግዚእነ፡ ኢየሱስ፡ክርስቶስ።

፩፡ ይቤ፡ እስመ፡ አብ፡ ፈጣሪ፡ መጠዎ፡ ለወልዱ፡ፍቁሩ፡በእንተ፡ፍጥረቱ፡ለመድ ኃኒቶሙ።

፪፡ ወጾረ፡ ሕማማተ፡ ሞት፡ በትስብእቱ፡ በከመ፡አምሳለ፡በግዕ፡ዘስቁል፡ላዕለ፡ዕፀ፡ ሳቤቅ።

፫፡ ወኢበጽሐ፡እንከ፡እምዝንቱ፡ኵሉ፡ወኢ ምንተኒ፡ኀበ፡መለኮቱ፡በከመ፡ኢበጽሐ፡ መጥባሕት፡ወሞት፡ለይሥሐቅ።

፬፡ ወበከመ፡ አቅረበ፡ ይሥሐቅ፡ ለተሠ ውዖቱ፡ዕፀ፡አምሳለ፡ዘፆረ፡ክርስቶስ፡ዕፀ፡ መስቀል።

፭፡ ወክልኤቱ፡ ደቅ፡ እለ፡ ነሥአሙ፡ አብርሃም፡ ምስሌሁ፡ አምሳለ፡ ክልኤቱ፡ ፈያት፡እለ፡ተሰቅሉ፡ምስለ፡ክርስቶስ።

፮፡ ወመጥባሕት፡አምሳለ፡ኲናት፤ ወእሳት፡ አምሳለ፡መለኮት፡ ወስብሐት፡ለእግዚአ ብሔር፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ድርሳን፡ ወትምህርት፡ ዘአበዊነ፡ ሐዋርያት፡ቅዱሳን፡ዘመሀሩነ።

፩፡ ወእምዝ፡ሰምዐት፡አብሮቅላ፡ብእሲተ፡ ጲላጦስ፡ዘከመ፡ መጠውዎ፡ ለእግዚእ፡ ኢየሱስ፡ኀበ፡ጲላጦስ፡ወዘከመ፡አስተዋ

፪፡ ደይዎ፡አይሁድ፡ኀቤሁ። ወቦቱ፡ ለጲላጦስ፡ ክልኤቲ፡ አዋልድ፡ ወበሐማት፡ክልኤሆን።

፫፡ ወአልቦ፡ ዘተናገሮ፡ ቃለ፡ እምአመ፡ ተወልዳ፡እስከ፡አመ፡አግብእዎ፡ለእግዚእ፡ ኢየሱስ፡ኀበ፡ዐውደ፡ምኵናን፡ለአሐቲ፡

ዓርብ፡መዓልት፡በ፲፡ሰዓት።

፻፳፫፡ ዳግመኛም፡እምላካችንና፡ጌታችን፡የሕይ ወታችን፡አበጋዝ፡ክቡር፡ምስጉን፡ነው፣ ሐዘንን፡ የሚያርቅ፡ ተድላ፡ ደስታን፡ የሚሰጥ፡ነው፡አለ።

፻፳፬፡ ለእርሱ፡ ክብር፡ ምስጋና፡ ይሁን፡ ለዘላለሙ፡አሜን።

፻፴፡ ይህን፡ ድርሳን፡ ከዐረብኛ፡ ወደ፡ ግዕዝ፡ የመለሰውን፡ሃይማኖቱ፡የቀና፡የጳጳሱን፡ የአባ፡ ሰላማን፡ ማደሪያ፡ እግዚአብሔር፡ ከእነርሳቸው፡ ጋር፡ አንድነት፡ ያድርግ፤ አሜን።

ዳግመኛም፡ሐዋርያዊ፡አባታችን፡ቅዱስ፡ አትናቴዎስ፡ ስለ፡ ጌታችን፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ከአይሁድ፡ ጋር፡ በተነጋገ ረበት፡ድርሳኑ፡እንዲህ፡አለ።

፩፡ ፈጣሪ፡ አብ፡ ስለ፡ ፍጥረታቱ፡ ለድኅነ ታቸው፡የሚወደውን፡ልጁን፡ለሕማም፡ ለሞት፡አሳልፎ፡ሰጠው።

፪፡ በዕፀ፡ ሳቤቅ፡ ላይ፡ በተሰቀለው፡ በግ፡ አምሳል፡ እንዲሁ፡ መከራ፡ ሞትን፡ በሥጋው፡ተሸከመ።

፫፡ ሾተልና፡ሞት፡ይሥሐቅን፡እንዳልደረሰበት፡ እግዚአብሔር፡ ቃልን፡ በሥጋው፡ እንጂ፡ በመለኮቱ፡ምንም፡ምን፡አላገኘውም።

፬፡ ይሥሐቅ፡ የሚሠዋበትን፡ ዕንጨት፡ ተሸክሞ፡ እንዳቀረበ፡ ክርስቶስ፡ ለተሸ ከመው፡ዕፀ፡መስቀል፡አምሳል፡ሆነ።

፭፡ አብርሃም፡ ከእርሱ፡ ጋር፡ የወሰዳቸው፡ ሁለቱ፡ ሎሌዎች፡ ከክርስቶስ፡ ጋራ፡ የተሰ ቀሉ፡የሁለቱ፡ወንበዴዎች፡ምሳሌ፡ናቸው።

፮፡ ሾተልም፡የተወጋበት፡ጦር፡ምሳሌ፡ነው፤እሳት፡ የመለኮት፡ ምሳሌ፡ ነው፤ ለእግዚአብሔርም፡ ክብር፡ምስጋና፡ለዘላለሙ፡ይሁን፡አሜን።

የከበሩ፡ አባቶቻችን፡ ሐዋርያት፡ የደረሱት፡ ድርሳንና፡ ያስተማሩት፡ ትምህርት፡ ይህ፡ ነው።

፩፡ ከዚህ፡ በኋላ፡ የጲላጦስ፡ ሚስት፡ አብሮቅላ፡ ጌታ፡ኢየሱስን፡ ለጲላጦስ፡አሳልፈው፡እንደ ሰጡትና፡ በእርሱ፡ ዘንድ፡ እንደ፡ ከሰሱትም፡ ሰማች።

፪፡ ለጲላጦስም፡ ሁለት፡ ሴቶች፡ ልጆች፡ ነበሩት፤ ሁለቱም ዲዳዎች፡ነበሩ።

፫፡ እነርሱም፡ ከተወለዱ፡ ጀምሮ፡ ጌታ፡ ኢየሱስን፡ ወደ፡ ፍርድ፡ አደባባይ፡ እስከ፡ አቀረቡት፡ ድረስ፡ ቃልን፡ የተናገ

Scanned by CamScanner

በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

ስሙ፡መከራ፡ወለካልእታ፡ዶርታ።

ወእግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ ፈትሐ ፡ አፉሆን ፡
ወአርትዐ ፡ ልሳኖን ፡ ወተናገራ ፡ በቃል ፡
አሚሃ።

ወሰምዐት ፡ እሞን ፡ እንዘ ፡ ይብላሃ ፡ ንግሪዮ ፡
ለጲላጦስ ፡ አቡነ ፡ ወበሊዮ ፡ ዑቅአ ፡ ወኢት
ግበር ፡ እኩየ ፡ ወኢተአብስ ፡ ወኢትትፌሣሕ ፡
በእንተ ፡ ስቅለቱ ፡ ወሞቱ ፡ ለእግዚእነ ፡
ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡
ሕያው ፡ አምላክ ፡ ሕያዋን ፡ ወሙታን።

ወውእቱ ፡ ይፈትሕ ፡ ወይኴንን ፡ ላዕሌከ ፡
ወለኵሉ ፡ ዓለም ፡ በምልኡ ፡ አመ ፡ ዕለተ ፡ ፍዳ ፡
ወአመ ፡ ዕለተ ፡ ደይን ፡ ኀበ ፡ አልቦ ፡ አድልዎ።

ወኢትንብብ ፡ ቃለ ፡ ሕሡመ ፡ ላዕሌሁ ፡ ከመ ፡
ኢይመጡከ ፡ ለመላእክተ ፡ ጽልመት ፡ ውስተ ፡
ገሃነም።

ወሰበ ፡ ሰምዐት ፡ አብሮቅላ ፡ ብእሲተ ፡
ጲላጦስ ፡ ዘንተ ፡ ቃለ ፡ እምአዋልዲሃ ፡ አስተዐ
ጸበት ፡ ወአእኰተቶ ፡ ለእግዚአብሔር።

ወትቤሎን ፡ ለከሩኑሳ ፡ ወለአምናራ ፡ አሐቲሃ ፡
ወፋትኩራ ፡ ብእሲተ ፡ እኁሃ ፡ ንዓ ፡ አስተፋጠ
ነክን ፡ ወሑራ ፡ ኀበ ፡ ጲላጦስ ፡ ወዜንዎሁ ፡
ዘንተ ፡ ነገረ ፡ ዘከመ ፡ ሰማዕክን ፡ እምኀበ ፡
እላንቱ ፡ አዋልዲሁ ፡ እለ ፡ ተናገራ ፡ በእንተ ፡
ኢየሱስ ፡ ወአነሂ ፡ ርኢኩ ፡ በዛቲ ፡ ሌሊት ፡
ወሐለምኩ ፡ ዐቢየ ፡ ሕልመ ፤ በእንቲአሁ ፡
ሑራ ፡ ወንግራሁ ፡ ኵሎ ፡ ዘኮነ።

ወሖራ ፡ ወነገራሁ ፡ ኵሎ ፡ ዘኮነ ፤ ወሰሚዖ ፡
ጲላጦስ ፡ ዘንተ ፡ ነገረ ፡ አንከረ ፡ ወአስተዐጸበ ፡
ፈድፋደ።

ወሀለዉ ፡ ሀየ ፡ ኀበ ፡ ዐውደ ፡ ቅሥት ፡ አዶሮ
ከናዲ ፡ ወልደ ፡ ጲላጦስ ፡ ወአውሎጊስ ፡
እኁሁ ፡ ጸርሑ ፡ እንዘ ፡ ይብሉ ፡ አማን ፡ ወልደ ፡
እግዚአብሔር ፡ ውእቱ ፡ ዝንቱ።

ወርኢነ ፡ ንሕነ ፡ ዮም ፡ ብርሃነ ፡ ወኃይለ ፡
በውስተ ፡ ገጹ ፡ ወአልቦ ፡ ዘይትማሰሎ ፡ በዲበ ፡
ምድር።

ዓርብ ፡ መዓልት ፡ በ፱ ፡ ሰዓት።

ሩበት ፡ ጊዜ ፡ የለም ፤ የአንዷቱ ፡ ስሟ ፡ መከራ ፡
የሁለተኛይቱም ፡ ዶርታ ፡ ይባላል።

፩፤ ጌታ ፡ ኢየሱስ ፡ አፋቸውን ፡ ፈትቶ ፡ አንደበታ
ቸውን ፡ አርትቶላቸው ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ በቃላቸው ፡
ተናገሩ።

፪፤ ዕወቅ ፡ ተጠንቀቅ ፡ ክፉ ፡ እንዳትሠራ ፤ እንዳት
በድል ፡ በሕያዋንና ፡ በሙታን ፡ ላይ ፡
በሚፈርድ ፡ በሕያው ፡ እግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡
በጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በመሰቀሉና ፡
በመሞቱ ፡ ደስ ፡ እንዳይልህ ፡ ብለሽ ፡ ለአባ
ታችን ፡ ለጲላጦስ ፡ ንገሪው ፡ ብለው ፡ ሲናገሩ ፡
እናታቸው ፡ ሰማች።

፫፤ እርሱ ፡ በአንተ ፡ ላይና ፡ በዓለሙ ፡ ሁሉ ፡
አድልዎ ፡ በሌለባት ፡ በዚያች ፡ በፍርድና ፡
በቁርጥ ፡ ቀን ፡ ይፈርዳል።

፬፤ በገሃነም ፡ ሥቃይ ፡ ለሚያጸኑ ፡ ለጨለማ ፡
መላእክት ፡ እንዳይሰጥህ ፡ ክፉ ፡ ቃል ፡ በእርሱ ፡
ላይ ፡ እንዳትናገር ፡ ብለሽ ፡ ንገሪው ፡ ሲሉ ፡
ሰማች።

፭፤ የጲላጦስ ፡ ሚስት ፡ አብሮቅላም ፡ ከልጆቿ ፡
ይህን ፡ ቃል ፡ በሰማች ፡ ጊዜ ፡ አደነቀች ፤ እግዚ
አብሔርንም ፡ አመሰገነች።

፮፤ እኅቶቿን ፡ ከሩኑሳና ፡ አምናራን ፡ የወንድሟን ፡
ሚስት ፡ ፋትኩራን ፡ ኑ ፡ ፈጥናችሁም ፡ ወደ ፡
ጲላጦስ ፡ ሂዳችሁ ፡ ስለ ፡ ኢየሱስ ፡ ልጆቼ ፡
ሲናገሩ ፡ እንደሰማችሁ ፡ የተናገሩትን ፡ ይህን ፡
ነገር ፡ ንገሩት ፤ እኔም ፡ በዚች ፡ ሌሊት ፡ ስለ ፡
እርሱ ፡ ግሩም ፡ ሕልም ፡ አይቻለሁ ፤ ሂዳችሁ ፡
የሆነውን ፡ ሁሉ ፡ ንገሩት ፡ አለቻቸው።

፯፤ ሂደውም ፡ የሆነውን ፡ ሁሉ ፡ ነገሩት ፤
ጲላጦስም ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ሰምቶ ፡ እጅግ ፡
አደነቀ።

፰፤ በዚያ ፡ በአደባባዩ ፡ የጲላጦስ ፡ ልጅ ፡ አዶሮኮ
ናዲና ፡ ወንድሙ ፡ አውሎጊስ ፡ ነበሩ ፤ እነርሱ ፡
ይህ ፡ በእውነት ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ነው ፡
ብለው ፡ ጮኹ።

፱፤ እኛ ፡ በፊቱ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ብርሃንና ፡ ግርማን ፡
አይተናል ፤ በምድር ፡ ላይም ፡ የሚመስለው ፡
የለም ፡ አሉ።

Scanned by CamScanner

## በ፲፩፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

፲፫፤ ወእምዝ ፡ ጸሐፈት ፡ አብሮቅላ ፡ ብእሲቱ ፡ ጲላጦስ፡መኰንን፡መልእክተ፡ኀበ፡ዐበይተ፡ አይሁድ ፡ ወኀበ ፡ ጸሐፍቶሙ ፡ ዘይብል ፡ ከመዝ፡ አነ ፡ ወሰብእ ፡ ቤትየ ፡ ኵሎሙ ፡ ተደለውነ ፡ ከመ ፡ ንሙት ፡ በእንተ ፡ ሰሙ ፡ ለኢየሱስ ፡ ለእመ ፡ ኢፈቀድክሙ ፡ ታሕይውዎ፡ ዐቁ ፡ ለርእስክሙ ፤ ወኢኮነ ፡ ውእቱ፡ውስተ፡ዝንቱ፡ዓለም፡ወኢይመጽእ፡ ሕሡም፡ላዕሌሁ።

፲፬፤ ወተበሀሉ ፡ አይሁድ ፡ በበይናቲሆሙ ርእዩ ፡ ሥራዮ፡ለኢየሱስ፡በእንተዝ፡ቃል፡ዘመጽአ፡ እምዛቲ፡ብእሲት፡ወዘከመ፡ለአከት፡ኀቤነ፡ ኀበ፡ዐውደ፡ቅሥት።

፲፭፤ ወእግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ ነሥአ ፡ በእዴሁ ፡ መጽሐፈ፡መልእክት፡ዘለአከት፡አብሮቅላ፡ ብእሲተ ፡ ጲላጦስ ፡ ሜጣ ፡ ወወለጣ ፡ ወደምሰሳ፡ በእደዊሁ ፡ ቅዱሳት ፡ ወመልዓ ፡ ዘጽሑፍ፡በመንፈስ፡ቅዱስ።

፲፮፤ ወለአከ፡ኀቤሃ፡እንዘ፡ይብል፡ብዕዕት፡አንቲ፡ ብእሲት፡መፍቀሪተ፡እግዚአብሔር፡ ዐቢይ፡ ሃይማኖትኪ ፡ ወቃል ፡ ዘትብሊ ፤ አማንየ ፡ እብለኪ ፡ እሁበኪ ፡ ዐስበኪ ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማያት፡ወእኈልቆሙ፡ለደቂቅኪ፡ወለአዋልድኪ ፡ ምስለ ፡ ምዕት ፡ ደናግል ፡ እለ ፡ አንሶሰዋ፡ምስለ፡ማርያም፡ እምየ።

፲፯፤ ወአንቲ፡ፈቀድኪ፡ከመ፡ትመጥዊ፡ነፍሰኪ፡ ወኵሎሙ፡ሰብአ፡ቤትኪ፡በእንቲአየ።

፲፰፤ ወአነ፡እኈልቁኪ፡ወእኈልቆሙ፡ለደቂቅኪ፡ ወለሰብአ፡ቤትኪ፡ምስለ፡ኵሎሙ፡ሰማዕት።

፲፱፤ ወእምድኅረዝ ፡ አውሥአሙ ፡ ጲላጦስ ፡ መኰንን ፡ ለአይሁድ ፡ ምንተ ፡ ትፈቅዱ ፡ እግበር ፡ ለክሙ ፡ ኢየሱስሃ ፡ ወይቤሉ ፡ አይሁድ፡ስቅሎ፡ስቅሎ።

፳፤ ወይቤሎሙ ፡ ጲላጦስ ፡ ለአይሁድ ፡ ዛቲ ፡ ዕለት፡ በዐልክሙ ፡ ውብክሙ ፡ ልማድ ፡ ንኅድግ ፡ ወናሕዩ ፡ አሐደ ፡ እምእሱራን ፡ ወስምዑ ፡ እምኔየ ፡ ንኅድጎ ፡ ለኢየሱስ ፡ ይሑር፡ዳኅነ።

## ዓርብ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

፲፫፤ ከዚህም፡በኋላ፡የገዥው፡የጲላጦስ፡ሚስት፡ አብሮቅላ፡ወደ፡አይሁድ፡ታላላቆችና፡ወደ፡ ጸፎቻቸውም፡እንዲህ፡ስትል፡መልእክት፡ ጸፈች ፤ እኔና ፡ ቤተሰቦቼ ፡ ሁሉም ፡ ስለ ፡ ኢየሱስም፡እንሞት፡ዘንድ፡ተዘጋጅተናል፤ በሕይወት ፡ ልትተዉት ፡ ካልወደዳችሁ ፡ ለራሳችሁ ፡ ዕወቁ ፤ እርሱ ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ አይደለም ፤ በእርሱ ፡ ላይም ፡ ክፉ ፡ አይመጣም።

፲፬፤ አይሁድም፡እርስ፡በርሳቸው፡ከዚች፡ሴት፡ ወደ፡እኛ፡ስለ፡መጣው፡ቃል፡ወደ፡እኛም፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ አደባባይ ፡ እንደላከች፡የኢየሱስን፡ ሥራዩን፡እዩ፡ተባባሉ።

፲፭፤ ጌታ ፡ ኢየሱስም ፡ የጲላጦስ ፡ ሚስት ፡ የላከችውን ፡ የመልእክት ፡ ደብዳቤ ፡ በእጁ ፡ ያዘ፤ ንጹሐን፡በሆኑ፡እጆቹ፡ጽሑፉንም፡ደመሰሰ፤ ለወጠ፤በመንፈስ፡ቅዱስም፡በውስጡ፡ጻፈ፡ ቃልን፡መላት።

፲፮፤ እንዲህ፡ብሎም፡ወደ፡እርሷ፡ላከ፤እግዚአብሔርን፡ የምትወጂ፡አንቺ፡ሴት፡ሃይማኖትሽ፡ ፍጹም ፡ የሆነ ፡ የተመሰገንሽ ፡ ነሽ ፤ ይህ፡ የምትዪው፡ቃል፡እውነት፡ነውና፤እኔ፡በመንግሥተ ፡ ሰማይ ፡ ዋጋሽን ፡ እንደምሰጥሽ፡ በእውነት ፡ እነግርሻለሁ ፤ ሴቶች ፡ ልጆችሽንም፡ ከእናቴ ፡ ጋር ፡ ከተመላለሱ ፡ ከመቶ፡ ደናግል፡ጋር፡እቈጥራቸዋለሁ፡አላት።

፲፯፤ አንቺም፡ከቤተ፡ሰቦችሽ፡ሁሉ፡ጋር፡ስለ፡እኔ፡ ነፍስሽን፡ለሞት፡ልትሰጭ፡ወደሻል።

፲፰፤ እኔም፡አንቺን፡ልጆችሽንና፡ቤተሰቦችሽን፡ ሁሉ፡ከሰማዕታት፡ጋር፡እቈጥራችኋለሁ።

፲፱፤ ከዚህም፡በኋላ፡ዳኛው፡ጲላጦስ፡ኢየሱስን፡ ምን፡እንዳደርግላችሁ፡ትሻላችሁ፡ብሎ፡መለሰላቸው ፤ አይሁድም ፡ ስቀለው ፡ ስቀለው ፡ አሉ።

፳፤ ጲላጦስም፡ይቺ፡ቀን፡በዐላችሁ፡ናት፤ከእስረኞችም ፡ አንዳንድ ፡ ሰው ፡ ልናድንላችሁ ፡ ልማድ ፡ አላችሁ ፤ እኔንም ፡ ስሙኝ ፡ ኢየሱስን ፡ እንተወውና ፡ በደኅና ፡ ይሂድ ፡ አላቸው።

በ፲፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

፳፩ ወአውሥእዎ፡ ሕዝበ፡ አይሁድ፡ ለጲላጦስ፡
ወይቤልዎ ፡ ኢይከውን ፡ ከመ፡ዝ ፡ አላ ፡
በርባንሃ፡አሕዩ፡**ወለኢየሱስ፡**ስቅሎ።

፳፪ ወሶበሂ፡ አዘዘ፡ ጲላጦስ፡ መስፍን፡ ከመ፡
ያምጽኡ፡ማየ፡በጸሕል፡ቅድሜሁ።

፳፫ ወኀደጋ፡ለሕገ፡ሙሴ፡ወተኀፅበ፡እደዊሁ፡
በብርሃነ፡ፀሐይ፡በቅድመ፡ኵሉ፡ሕዝብ፡
እንዘ፡ ይብል ፡ ንጹሕ ፡ አነ ፡ እምደሙ ፡
ለዝብእሲ፡ጻድቅ፡ወኵሎሙ፡ሰብአ፡ቤትየ፡
ንጹሐን፡እምደመ፡ዝንቱ፡ጻድቅ።

፳፬ ወተመይጠ፡ጲላጦስ፡ኀበ፡**እግዚእ፡ኢየሱስ፡**
ወይቤሎ፡ኢትሬኢኑ፡እንዘ፡ እትበአስ፡በእን
ቲአከ፡ምስለ፡ሕዝበ፡አይሁድ፡ወኢተከ
ሀለኒ፡ከመ፡አድኅንከ፡እምኔሆሙ።

፳፭ ሶበሰ፡ክህልኩ፡አድኅንከ፡እመጠውኩ፡
ነፍስየ፡በእንቲአከ፡ወአነ፡ንጹሕ፡እምደመ፡
ዚአከ፡አ፡ጻድቅ፡ወአነ፡እስእል፡ኀቤከ፡**አ፡
እግዚእየ፡ወመድኃኒተ፡** ነፍስየ ፡ **ወመድ
ኃኒተ፡**ኵሉ፡ዓለም።

፳፮ ወሶበ፡ተዐርገ፡ኀበ፡አቡከ፡ኢታርኅቀኒ፡እም
ሕረትከ፡ወአንሰ፡ኢፈቀድኩ፡ትኩን፡ዛቲ፡
ፍትሕ፡በመዋዕልየ፡ወኢፈተውኩ፡ደምከ፡
ንጹሕ፡ይትከዐው፡በምልክናየ።

፳፯ ወለእመ፡ኢኮነ፡በምልክናሁ፡ለሄሮድስ፡
ወፈትሐ ፡ ውእቱ ፡ መኰንን ፡ በፍትሐ ፡
ንጉሥ፡ ጢባርዮስ፡ እምቅድሜየ ፡ ውእቱ ፡
ዘለአከ፡ይንሣእ፡ሢመተ፡ዛቲ፡ሀገር።

፳፰ ወበእንተ፡ዝንቱ፡ዘመጠውኩከ፡ለአይሁድ፡
በእንተ፡ዘአዘዘ፡ሄሮድስ።

፳፱ ወይቤሎ ፡ **እግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡** አንሰ ፡
ለእመርኩ፡ዘንተ፡ዘኮነ፡በፍትሐ፡ንጉሥ፡
ወሊተሰ ፡ መንግሥትየ ፡ እምላዕሉ ፡
ወእምኀበ፡**አብ፡** አነ፡**ወአብ፡** አሐዱ፡ንህነ።

፴ ወበእንተዝ፡ ተወለድኩ፡ ውስተ፡ ዓለም፡
ከመ፡ እመጡ፡ ነፍስየ፡ ቤዛ፡ ኵሉ፡ ወይት
ከዐው፡ ደምየ፡ በእንተ፡ ቤዛ፡ ብዙኃን፡
ወአንተሰ፡ ንጹሕ፡ እምደመ፡ ዚአየ፡
ወኵሎሙ፡ሰብአ፡ቤትከ፡ንጹሐን።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፲፡ሰዓት።

፳፩ የአይሁድም፡ወገኖች፡ለጲላጦስ፡እንዲህ፡ ብለው፡ መለሱለት፤ እንዲህ፡ አይደለም፤ በርባንን፡ አድን፡ እንጂ፡ **ኢየሱስንስ፡** ስቀለው።

፳፪ ያን፡ጊዜም፡ጲላጦስ፡በስን፡በብርት፡ውኃ፡ ያመጡ፡ዘንድ፡አዘዘ።

፳፫ የሙሴንም፡ሕግ፡ተዋት፤በፀሐይ፡ብርሃን፡ በሕዝቡም፡ሁሉ፡ፊት፡ከዚህ፡ጻድቅ፡ሰው፡ ደም፡ንጹሕ፡ነኝ፡ብሎ፡እጆቹን፡ታጠበ፤ቤተ ሰቦቹም፡ሁሉ፡ከዚህ፡ጻድቅ፡ሰው፡ደም፡ ንጹሐን፡ናቸው።

፳፬ ጲላጦስም፡ወደ፡**ጌታ፡ኢየሱስ፡**መለሰ፡ብሎ፡ ከአይሁድ፡ወገኖች፡ጋር፡ስለ፡አንተ፡ስጣላ፡ አታይምን ? ከእነርሱም፡ላድንህ፡አልተቻ ለኝም፡አለው።

፳፭ ላድንህስ፡የሚቻለኝ፡ከሆነ፡ስለ፡አንተ፡ ነፍሴን፡በሰጠሁ፡ነበር፤ጻድቅ፡ሆይ፡እኔ፡ ከደምህ፡ንጹሕ፡ነኝ፤**ጌታዬ፡ሆይ፤** የነፍሴ፡ **መድኃኒት፡** የዓለሙ፡ ሁሉ፡ **መድኃኒት፡** የምትሆን፡ወደ፡አንተ፡እለምናለሁ።

፳፮ ወደ፡አባትህም፡በወጣህ፡ጊዜ፡ከምሕረትህ፡ ከቸርነትህ፡አታርቀኝ፤በእኔ፡ግዛትና፡በእኔ፡ አደባባይ፡ንጹሕ፡ደምህ፡ይፈስ፡ዘንድ፡እኔ፡ አልወደድኩም።

፳፯ በሄሮድስ፡ ዳኝነት፡ ባይሆንም፡ በንጉሥ፡ ጢባርዮስ፡ ትእዛዝ፡ ከእኔ፡ አስቀድሞ፡ የዚችን፡ አገር፡ ሹመት፡ ይሾም፡ ዘንድ፡ ተልኳልና፡እርሱ፡እንድትሞት፡ፈረደ።

፳፰ ስለዚህም፡ለአይሁድ፡አሳልፌ፡የሰጠሁህ፡ ሄሮድስ፡ስለ፡አዘዘ፡ነው።

፳፱ **ጌታ፡ኢየሱስም፡** ይህ፡በንጉሥ፡ፍርድ፡ እንደ፡ሆነ፡አውቃለሁ፤የእኔ፡መንግሥት፡ ግን፡ከላይ፡**ከአብ፡** ዘንድ፡ናት፤እኔና፡**አብ፡** አንድ፡ነን።

፴ ስለዚህም፡በዓለም፡ውስጥ፡ተወለድኩ፤ስለ፡ ብዙዎች፡ቤዛ፡ነፍሴን፡አሳልፌ፡ለሞት፡ እሰጥ፡ዘንድ፡አንተ፡ግን፡ከደሜ፡ንጹሕ፡ ነህ፤ቤተሰቦችህም፡ሁሉ፡ንጹሐን፡ናቸው፡ አለው።

Scanned by CamScanner

## በ፫፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

፲፩፤ ወእምዝ ፡ ሰምዐ ፡ አይሁድ ፡ ዘንተ ፡ ነገረ ፡
እንዘ፡ይብሎ፡**እግዚእ፡ኢየሱስ**፡ለጲላጦስ፡
መልአ፡ቅንአት፡ወመዐት፡ውስተ፡ልቦሙ፤
ወኮኑ፡ከመ፡አንበሳ፡ዘይጥሕር፡ወይመስጥ፡
ወከልሑ ፡ ኵሎሙ ፡ ኀበ ፡ ጲላጦስ ፡ እንዘ ፡
ይብሉ፡ሀበነ፡**ኢየሱስሃ**፡ፀረነ፡ወዕድወነ።

፲፪፤ ወእመሰ ፡ ፈቀድከ ፡ ታሕይዎ ፡ ለዝንቱ ፡
ኢኮንከ፡ዐርኮ፡ለቄሳር፡ንጉሥ።

፲፫፤ ወሶበ ፡ ሰምዐ ፡ ጲላጦስ ፡ ዘንተ ፡ ዐውያተ ፡
ወጽራሐ፡ከመ፡ነደ፡በመዐት፡ልቦሙ፡ከመ፡
እሳት ፡ ጸርሐ ፡ ጲላጦስ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡
አልብየ፡ አበሳ ፡ ወኃጢአት ፡ ምንትኒ ፡
ንሥእዎ ፡ አንትሙ ፡ ወኰንንዎ ፡ በከመ ፡
ሕግክሙ።

፲፬፤ ወጸርሑ፡ኵሎሙ፡እንዘ፡ይብሉ፡ይደልዎ፡
ሞት፡እስመ፡ውእቱ፡ረሰየ፡ርእሶ፡**ወልደ፡እግ
ዚአብሔር**።

፲፭፤ ወሶቤሃ፡ነሥአ፡ጲላጦስ፡ለውሐ፡ወጸሐፈ፡
እንዘ ፡ ይብል ፡ ዝውእቱ ፡ ንጉሦሙ ፡
ለአይሁድ።

፲፮፤ ወውእተ ፡ ጊዜ ፡ መጠዎሙ ፡ ጲላጦስ ፡
ለሕዝበ፡ አይሁድ ፤ ወሶቤሃ ፡ አዕረቅዎ ፡
ልብሶ፡ ወተካፈሉ ፡ አልባሲሁ ፤ ወዘበጥዎ ፡
በጥብጣቤ፡አርባዕቱ፡ሐራ።

፲፯፤ ወእምድኅረ ፡ ውእቱ ፡ አልበስዎ ፡ ካልአ ፡
ልብሰ ፡ ቀይሐ ፡ ወአውጽእዎ ፡ አፍአ ፡ ኀበ ፡
ሕዝበ፡አይሁድ፡ወይትቃጸብዎ፡ላዕሌሁ።

፲፰፤ ወደከመ፡**እግዚእ፡ኢየሱስ**፡ ንዘ፡የሐውር፡
ጸዊሮ፡መስቀለ።

፲፱፤ ወበጽሐ፡ኀበ፡ሀለወት፡ንስቲት፡ባሕር፡በም
ሥራቃቲሃ፡ለኢየሩሳሌም፡ወስማ፡ኤዶማቅ፡
ወትርጓሜሃ ፡ ለይእቲ ፡ መካነ ፡ ቃየል ፡
ወአቤል።

፳፤ ወገፍዕዎ ፡ በገጹ ፡ ዲበ ፡ ምድር ፡
**ለኢየሱስ** ፡ ወዘበጥዎ ፡ አይሁድ ፡ ወፈቀዱ ፡
የአኅዝዎ።

## ዓርብ፡መዓልት፡በ፫፡ሰዓት።

፲፩፤ ከዚያም ፡ **ጌታ ፡ ኢየሱስ** ፡ ለጲላጦስ ፡ ይህን፡
ሲናገረው ፡ አይሁድ ፡ ሰሙ ፤ በልባቸውም፡
ቅንዓትና፡ቁጣ፡መላባቸው፤እንደሚያገሳና፡
እንደሚነጥቅ ፡ አንበሳም ፡ ሆነው ፡ ሁሉም፡
ጠላታችንንና ፡ ባላጋራችንን ፡ **ኢየሱስን** ፡
ስጠን፡እያሉ፡ወደ፡ጲላጦስ፡ጮኹ።

፲፪፤ እርሱን ፡ ልታድነው ፡ ብትወድ ፡ የንጉሥ፡
ቄሳር፡ወዳጁ፡አይደለህም።

፲፫፤ ጲላጦስም ፡ ጩኸታቸውን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ፡
ልባቸውም ፡ በቁጣ ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ መን
ደዱን ፡ አይቶ ፡ እኔ ፡ ምንም ፡ ምን ፡ በደልና፡
ኃጢአት ፡ የለብኝም ፤ እናንተ ፡ እንደ ፡
ሕጋችሁ ፡ ወስዳችሁ ፡ ፍረዱበት ፡ ብሎ ፡
ጮኸ።

፲፬፤ ሁሉም ፡ እርሱ ፡ **የእግዚአብሔር ፡ ልጅ** ፡ ነኝ፡
ብሏልና፡ሞት፡ይገባዋል፡እያሉ፡ጮኹ።

፲፭፤ ያን ፡ ጊዜም ፡ ጲላጦስ ፡ ሰሌዳ ፡ ወስዶ ፡ ይህ፡
የአይሁድ፡ንጉሣቸው፡ነው፡ብሎ፡ጻፈ።

፲፮፤ በዚያን፡ጊዜም፡ለአይሁድ፡ወገን፡አሳልፎ፡
ሰጣቸው ፤ ወዲያውኑ ፡ ልብሱን ፡ ገፍፈው፡
ተካፈሉት ፤ አራቱ ፡ የጭፍራ ፡ አለቆችም፡
በጅራፍ፡ገረፉት፤ደበደቡትም።

፲፯፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ሌላ ፡ ቀይ ፡ ልብስ፡
አልብሰው፡የአይሁድ፡ሕዝብ፡ወደአሉበት፡
አወጡት ፤ እየተጠቃቀሱም ፡ ይዘብቱበት፡
ነበር።

፲፰፤ **ጌታ ፡ ኢየሱስም** ፡ መስቀሉን ፡ ተሸክሞ፡
ሲሄድ፡ደከመ።

፲፱፤ በኢየሩሳሌምም ፡ በስተምሥራቅ ፡ ስሟ፡
ኤዶማቅ ፡ የሚባል ፡ ትንሽ ፡ ባሕር ፡ አለች፤
ትርጓሜዋም ፡ የቃየልና ፡ የአቤል ፡ ቦታ፡
ማለት፡ነው፤ወደዚያችም፡ደረሰ።

፳፤ **ጌታ ፡ ኢየሱስንም** ፡ ከምድር ፡ ላይ ፡ በፊቱ፡
ደፉት ፤ አይሁድም ፡ ይዘው ፡ አብዝተው፡
ደበደቡት።

Scanned by CamScanner

## በ፫፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

፹፩ ወጸርሐ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡በቃሉ፡ወይቤ፡
አባ፡ርኢ፡ዘይገብሩ፡ላዕሌየ፡ውሉደ፡ዐመፃ፡
ወሕዝብ፡ኃጥአን፡ወውእቶሙ፡ገብሩ፡
ላዕሌየ፡በከመ፡ፈቀዱ።

፹፪ ወተጋብኡ፡ላዕሌየ፡ከለባት፡ብዙኃን፡
ወአኃዙኒ፡ማኅበሮሙ፡ለእኩያን፡ወአንተ፡
አምላኪየ፡ኢትርሐቅ፡እምኔየ።
፹፫ ነጽር፡ላዕሌየ፡ወላዕለ፡ሕማምየ።
፹፬ ወእምዝ፡መጽአ፡ሳውል፡እምሰብአ፡
ጠርሴስ፡ምስለ፡አርባዕቱ፡ሐራ፡ጲላጦስ፡
ወምስሌሆሙ፡አምጽኡ፡አክሊለ፡ዘሦክ፡
ወፀፈርዎ፡ከመ፡ሰርጐ፡ዕንቍ፡ወአንበሩ፡
መልዕልተ፡ርእሱ።

፹፭ ወሰሐብዎ፡ላዕለ፡ምድር፡እስከ፡ይስእን፡
ሐዊረ፡እምብዝኃ፡ቅሥፈታት፡ዘረከቦ፡
ወተሠትረ፡ኵሉ፡ሥጋሁ።

፹፮ ወአኀዝዎ፡ለስምዖን፡ቀሬናዊ፡ወአዘዝዎ፡
ይጹር፡መስቀሎ፡ለመድኀን፡ወወሰድዎ፡ወአ
ብጽሕዎ፡ኀበ፡መካን፡ዘስሙ፡ቀራንዮ፡
እንዘ፡ይተልውዎ፡ብዙኃን፡ዕደው።

፹፯ ወአንስትኒ፡ይበክያ፡ላዕሌሁ፡ወየሐዝና፡በእ
ንቲአሁ፡ዐቢየ፡ሐዘነ።
፹፰ ወተመይጠ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ወይቤሎን፡
አዋልደ፡ኢየሩሳሌም፡ኢትብክያ፡ላዕሌየ፡
አላ፡ብክያ፡ላዕለ፡ርእስክን፡ወላዕለ፡
ውሉድክን።
፹፱ ወውእተ፡አሚረ፡ትብላ፡ብፁዓት፡መካናት፡
እለ፡ኢወለዳ፡ወአጥባት፡እለ፡ኢሐፀና።

፺ ወትብልዎሙ፡ለአድባር፡ደቂ፡ላዕሌነ፡ወለአ
ውግር፡ድፍኑነ።
፺፩ ወእንዘ፡ይብሎን፡ዘንተ፡አብጽሕዎ፡
ጎልጎታ፡ዘስሙ፡ቀራንዮ፡መቃብረ፡አዳም፡
ኀበ፡ሰአልዎ፡አይሁድ፡ለጲላጦስ፡በእንተ፡
በርባን፡ከመ፡ይኅድግ፡ሎሙ።
፺፪ ወለከልኤቱ፡ፈያት፡እለ፡ነበሩ፡ኀበ፡ቤተ፡

## ዓርብ፡መዓልት፡በ፫፡ሰዓት።

፹፩ ጌታ፡ኢየሱስም፡እንዲህ፡ብሎ፡ጮኸ፤
አባት፡ሆይ፤እኒህ፡የዐመፅ፡ልጆች፡ኃጢአ
ተኞች፡ሕዝቦች፡በእኔ፡ላይ፡የሚያደርጉትን፡
እይ፡ተመልከት፤እነርሱም፡በእኔ፡ላይ፡የወደ
ዱትን፡ሁሉ፡አደረጉ።
፹፪ ብዙ፡ውሾችም፡በእኔ፡ላይ፡ተሰበሰቡ፤
የክፉዎች፡ማኅበርም፡በአንድነት፡ያዙኝ፤
አንተ፡አምላኪየ፡ግን፡ከእኔ፡አትራቅ።
፹፫ ወደ፡እኔና፡ወደ፡መከራዬም፡ተመልከት።
፹፬ ከዚህ፡በኋላ፡ከጠርሴስ፡ሰዎች፡ወገን፡የሆነ፡
ሳውል፡የሚባል፡ከአራቱ፡ከጲላጦስ፡
ጭፍሮች፡ጋር፡መጣ፤ከእርሳቸውም፡ጋር፡
የእሾህ፡አክሊል፡አመጡ፤በዕንቍ፡
እንዳጌጠ፡አድርገው፡በራሱ፡ላይ፡
አቀዳጁት።
፹፭ በምድር፡ላይም፡ጐተቱት፤ከአገኘው፡
ከግርፋት፡ብዛት፡የተነሣ፡መሄድ፡እስከሚ
ሳነው፡ድረስ፡ሥጋውም፡ሁሉ፡ተሰነጣጠቀ፤
ተገማመሰ።
፹፮ የቀሬና፡(የቀራንዮ)፡ሰው፡የሆነ፡ስምዖ
ንንም፡ይዘው፡የመድኀኑን፡መስቀል፡
ይሸከም፡ዘንድ፡አዘዙት፤ብዙ፡ሰዎችም፡እየ
ተከተሉት፡ስሙ፡ቀራንዮ፡ወደሚባል፡ቦታ፡
ወስደው፡አደረሱት።
፹፯ ሴቶችም፡ስለእርሱ፡እጅግ፡አዝነው፡
ፈጽመው፡ያለቅሱ፡ነበር።
፹፰ ጌታ፡ኢየሱስም፡ወደ፡እነርሱ፡ዘወር፡ብሎ፡
እንዲህ፡አላቸው፤የኢየሩሳሌም፡ልጆች፡
ሆይ፤ለራሳችሁና፡ለልጆቻችሁ፡አልቅሱ፤
እንጂ፡ለእኔ፡አታልቅሱልኝ፡አላቸው።
፹፱ ያን፡ጊዜ፡ያልወለዱ፡መካኖች፤ያላጠቡ፡
ያላሳደጉ፡ጡቶች፡የተመሰገኑ፡ናቸው፡
ትላላችሁ።
፺ ተራሮችን፡በላያችን፡ውደቁ፤ኮረብቶችንም፡
ተጫኑን፡ትልዋቸዋላችሁ።
፺፩ ይህንንም፡ሲላቸው፡አይሁድ፡በርባንን፡ያድ
ንላቸው፡ዘንድ፡ጲላጦስን፡ወደ፡ለመኑበት፡
የአዳም፡መቃብር፡ወደ፡አለበት፡ስሙ፡
ቀራንዮ፡ወደሚባለው፡ወደ፡ጎልጎታ፡
አደረሱት።
፺፪ ከበርባን፡ጋር፡በግዞት፡ቤት፡የነበሩ፡

Scanned by CamScanner

## በ፫፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

ምቅሐ፡ምስለ፡በርባን፡ለአሐዱ፡ስሙ፡እው፡
ሴምብያ፡እምሰብእ፡እንጢኪዶ፡ዘሰመይና፡
ወተርጕምና፡ቀኑስጣስ።
፶፫፡ ወለካልኡ ፡ ስሙ ፡ ሰሊኮኒሊዳኪ ፡ ወዝ ፡
ውእቱ፡ እምሰብእ ፡ ኤፌሶን ፡ ዘተርጕምዎ ፡
ወሰመይዎ ፡ ዴማስ ፤ ወአውዕእዎሙ ፡ እንዘ ፡
ይጸውሩ ፡ መስቀለ ፡ ከመ ፡ ይቅትልዎሙ ፡
ምስለ ፡ **ኢየሱስ** ፡ ወአብልዕዎሙ ፡ ወአስተ
ይዎሙ ፡ ዘያሰክር ፡ አይሁድ ፡ በከመ ፡ ሕገ ፡
አሪቶሙ።

፶፬፡ **ለእግዚእነሰ**፡ኢገብሩ፡ከማሆሙ፡እምብዝኀ፡
በቀል፡ወገደፍዎ፡በቅድሜሆሙ፡በማዕከለ፡
ሊቃነ፡ካህናት፡ወሕዝበ፡እስራኤል።

፶፭፡ ወሰገዱ ፡ ወሠሐቁ ፡ ላዕሌሁ ፡ ወተማከሩ ፡
እኩየ፡ምክረ፡ዘኢይገብሩ፡በባዕድ፡ከማሁ።
ሣህሉ፡ወምሕረቱ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡
ዓለም፡አሜን።

### ሃይማኖተ፡አበው።

ምዕ፡፳፩፡፩–፲፫።

፩፡ ይቤ፡ቅዱስ፡ጎርጎርዮስ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡ነባቤ፡
**መለኮት**፡በውስተ፡ድርሳኑ፡በእንተ፡**ወልድ**፡ ፣
ፍቁር።

፪፡ እስመ፡ኵሎሙ፡ነቢያት፡ኢክህሉ፡በጺሐ፡
አእምሮቱ፡ ለዘኢይትረከብ ፡ ወአስተርአየ ፡
**እግዚአብሔር ፡ ቃል** ፡ ልደተ ፡ ዕጓለ ፡
እመሕያው ፡ ወበልደቱ ፡ ኢተፈትሐ ፡
ማኅተመ፡ድንግልናሃ፡ለወላዲቱ።
፫፡ ቦአ፡ውስተ፡ዓለም፡እምድንግልና፡ወላዲቱ፡
ድንግል፡ወኢማሰነ፡በልደቱ፡ድንግልናሃ።
ወኢርኅበ፡ከርሠ፡ድንግል፡እንተ፡ጾረቶ፡አላ፡
ዐቀባ፡ከመ፡ቀዳሚ።

፬፡ አስተርአየ ፡ በሥጋ ፡ እንዘ ፡ ኢያስተርኢ ፡
በሀላዌ፡**መለኮቱ**፡ እሙንቱ፡ ያስተርኢ፡ ዘሀሎ፡
በኵሉ ፡ መካን ፡ ወእንዘ ፡ ምሉዕ ፡ ውእቱ ፡
በውስተ ፡ ኵሉ ፡ ወአልቦ ፡ መካን ፡ ዘዕሩቅ ፡
እምኔሁ።

## ዓርብ፡መዓልት፡በ፫፡ሰዓት።

ሁለቱ ፡ ወንበዴዎች ፡ አንዱ ፡ ከእንጢኪዶ፡
ሰዎች ፡ ወገን ፡ የሆነ ፡ ስሙ ፡ ሴምብያ፡
የሚባል፡የስሙ፡ትርጓሜ፡ቀኑስጣስ፡የሆነ፡
፶፫፡ የሁለተኛውም ፡ ስሙ ፡ ሰሊኮኒሊዳኪ ፡
እርሱም፡ከኤፌሶን፡ሰዎች፡ወገን፡የሆነ፡በት
ርጓሜውም ፡ ዴማስ ፡ ብለው ፡ የሚጠሩት፡
እነዚህን ፡ **ከጌታ ፡ ከኢየሱስ** ፡ ጋር ፡ ሊገድ
ሏቸው ፡ መስቀያቸውን ፡ አሸከመው ፡ አወጡ
አቸው፤እንደ፡ኦሪታቸውም፡ሕግ፡አይሁድ፡
አብልተው ፡ የሚያሰክርም ፡ መጠጥ ፡ አጠጡ
አቸው።
፶፬፡ ከብዙ፡በቀላቸውም፡የተነሣ፡**ለጌታችን**፡ግን፡
እንደነርሱ ፡ አላደረጉለትም ፤ በካህናት ፡
አለቆችና ፡ በእሥራኤል ፡ ሕዝብ ፡ መካከል፡
ጣሉት።
፶፭፡ በመዘበት ፡ ሰገዱለት ፤ በሌላ ፡ ላይ ፡ የማያደር
ጉትን፡በእርሱ፡ላይ፡ክፉ፡ምክር፡ተማከሩ።
ቸርነቱ፡ይቅርታው፡ከእኛ፡ጋር፡ለዘላለሙ፡
ይኑር፡አሜን።

### የአባቶች፡ሃይማኖት።

ምዕ፡፳፩፡፩–፲፫።

፩፡ የአንድነትን፡የሦስትነትን፡ነገር፡የተናገረ፡
ሊቀ፡ጳጳሳት፡ቅዱስ፡ጎርጎርዮስ፡የተወደደ፡
**የወልድን** ፡ ነገር ፡ በተናገረበት ፡ አንቀጹ፡
ዳግመኛ፡እንዲህ፡አለ።
፪፡ ነቢያት ፡ ሁሉ ፡ የማይመረመር ፡ እርሱን፡
መርምሮ ፡ ወደ ፡ ማወቅ ፡ መድረስ ፡ ባይቻ
ላቸው ፡ **እግዚአብሔር ፡ ቃል** ፡ ከሰው ፡ በተወ
ለደው ፡ ልደት ፡ ታየ፤በመወለዱም፡የእናቱን፡
ማኅተመ፡ድንግልናዋን፡አልለወጠውም።
፫፡ ከእናቱ ፡ በድንግልና ፡ ተወልዶ ፡ ወደዚህ፡
ዓለም ፡ ገባ ፤ በመወለዱም ፡ ድንግልናዋ፡አል
ተለወጠም፤የወሰነችው፡የድንግል፡ማኅፀን፡
አልተለወጠም ፡ እንደ ፡ ቀድሞው ፡ አጸናት፡
እንጂ።
፬፡ በባሕርዩ ፡ **መለኮቱ** ፡ የማይታይ ፡ ሲሆን፡
በሥጋ፡ታየ፤በሁሉ፡ምሉዕ፡ሲሆን፡እርሱም፡
የሌለበት፡ ቦታ ፡ የሌለ ፡ ሲሆን ፡ በቦታው ፡
ሁሉ፡ ምሉዕ ፡ የሚሆን ፡ እርሱ፡ እንደምን፡
ይታያል።

Scanned by CamScanner

በ፫፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

ኢሥምረ ፡ በማኑኤል ፡ ከመ ፡ ይጽብአ ፡
፭ ለጸላኢ፡በኀይለ፡መለኮቱ፡እላ፡በሥጋ፡ዘይት
ዓከፍ፡ሞተ፤ወበእንተዝ፡ጸሐፈ፡ጳውሎስ፡
ሐዋርያ፡ኀበ፡ሰብእ፡ዕብራውያን፡እንዘ፡
ይብል፡እስመ፡ደቂቅ፡ተሳተፍዎ፡በሥጋ፡
ወደም፡ወውእቱሂ፡ዓዲ፡ኮነ፡ከማሆሙ።
ወእፎኑ ፡ ይከውን ፡ ትንሣኤ ፡ እንበለ ፡
፮ ይቅድም፡ መዊት ፡ ዘይከውን ፡ እምቅድመ ፡
ትንሣኤ፤ ወእፎኑመ ፡ ይትከሀል ፡ መዊት ፡
ዘእንበለ ፡ ዳዕሙ ፡ በልብሰተ ፡ ሥጋ ፡
ዘይመውት፡እስመ፡መለኮት፡ኢይመውት።
፯ ኢኮነ፡ጥንተ፡ልደቱ፡እምአብ፡በሕማም፡
ወከማሁ ፡ ኢይረክቦ ፡ ሕማመ ፡ ሞት ፡
በመለኮቱ፡ ወኮነ፡ተፀንሶቱ፡እምድንግል፡
ዘእንበለ፡ዘርዕ፡ወበሞቱሂ፡ኢረከቦ፡ሙስና።

፲፬ ጽሑፍ፡በወንጌለ፡ማርቆስ፡ዘይብል፡ከመ፡
ውእቱ፡ተሀውከ፡ወተከዘ፤ሁከትሰ፡ወትካዝ፡
ሕማመ፡ነፍስ፡ውእቱ፡ዘከመ፡ይትዐወቅ፡
ሕማመ፡ሥጋሁ፡ዘውእቱ፡ረሀብ፡ወጽምእ፡
ወድካም፡በሐዊረ፡ፍኖት፡ወእለ፡ተርፉ፡
ሕማማት፡ዘተወክፎሙ፡እሙነ፡ወእኮ፡
በምትሐት፤ከመዝ፡ነአምን፡በሕማመ፡ነፍስ፡
ዘውእቱ፡ሁከት፡ወትካዝ።
፲፭ ወበስቁረተ፡ቅንዋት፡ዘተቀነዋ፡እደዊሁ፡
ወእገሪሁ፡በከመ፡ይቤ፡ኢሳይያስ፡ነቢይ፡
ውእቱ፡ነሥአ፡ደዌነ፡ወጾረ፡ሕማመነ፡
ወሐመ፡በእንቲአነ፡ወበእንተ፡ኃጣውኢነ፤
ወካዕበ፡ይቤ፡ብእሲ፡ድውይ፡እንዘ፡
ኢልማዱ፡ውእቱ፡ወበቍስለ፡ዚአሁ፡ሐዮነ፡
ቍስለነ።

፲፮ እመቦ፡ዘይብል፡ከመ፡መለኮት፡ሐመ፡
በቅሥፈት፡አው፡በቅንዋት፡አው፡በኵሉ፡
ደዌያት፡ውጉዘ፡ለይኩን።

ምዕ፤፰፤፳፯-፴።

፳፯ ወካዕበ፡ይቤ፡ቅዱስ፡ቄርሎስ፡ርኅበ፡ወጸምአ፡
ኖመ፡ወነቅሐ፡ከመ፡ሥርዓተ፡ዕጓለ፡
እመሕያው፡ደከመ፡እምሐዊረ፡ፍኖት፡በልዐ፡
ወሰትየ፡በከየ፡ወተከዘ፡ተሀውከ፡ወእስተ
ብቍዐ፡ዘከመ፡ሥርዓተ፡ዕጓለ፡እመሕያው፡

ዓርብ፡መዓልት፡በ፫፡ሰዓት።

፭፤ በማኑኤል፡በመለኮቱ፡ኃይል፡ዲያብሎስን፡
ድል፡ሊነሣው፡አልወደደም፤ሞት፡በሚስ
ማማው፡ሥጋ፡ነው፡እንጂ፤ስለዚህም፡
ሐዋርያው፡ጳውሎስ፡ሰዎች፡ነፍስን፡ሥጋን፡
በመዋሐድ፡መሰሉት፤እርሱም፡እንደነርሱ፡
ሆነ፡ብሎ፡ለዕብራውያን፡ሰዎች፡ጻፈ።
፮፤ ከትንሣኤ፡አስቀድሞ፡የሚሆን፡ሞት፡
ሳይቀድም፡ትንሣኤ፡እንደምን፡ይደረጋል?
መሞትስ፡እንደምን፡ይቻላል? የሚሞት፡
ሥጋን፡በመልበስ፡ነው፡እንጂ፤መለኮት፡አይ
ሞትምና።
፯፤ ከአብ፡የተወለደው፡ጥንታዊ፡ልደቱ፡
በሕፀፅ፡አይደለም፤በልደቱ፡ሕፀፅ፡እንደሌ
ለበት፡በመለኮቱ፡ሕማም፡ሞት፡አያገ
ኘውም፤ከድንግልም፡መፀነሱ፡ያለ፡ዘር፡ሆነ፤
በሞቱም፡መለወጥ፡አላገኘውም።
፲፬፤ እርሱ፡እንደ፡አዘነ፡እንደ፡ተከዘ፡በማርቆስ፡
ወንጌል፡ተጽፏል፤ሐዘን፡ትካዝ፡የነፍስ፡
ሕማም፡ነው፤መራብ፡መጠማት፡ጐዳና፡
በመሄድ፡መድከም፡በሐሰት፡ያይደለ፡
በእውነት፡የተቀበላቸው፡የቀሩት፡ሕማማት፡
የሥጋ፡እንደሆኑ፡እንዲታወቅ፡የነፍስን፡
ሕማም፡እንዲሀ፡እናምናለን፡ይኸውም፡
ሁከት፡ትካዝ፡ነው።
፲፭፤ እጆቹን፡እግሮቹን፡በተቸነከረባቸው፡
ችንካሮች፡መወጋቱንም፡እናምናለን፤ነቢዩ፡
ኢሳይያስ፡እርሱ፡ደዌያችንን፡ወሰደ፤ሕማማ
ችንንም፡ተሸከመ፤እኛን፡ለማዳን፡ኃጢአታ
ችንንም፡ለማስተስረይ፡መከራ፡ተቀበለ፡
እንዳለ፤በባሕርዩ፡ሕማም፡የሌለበት፡ሲሆን፤
በሥጋ፡የታመመ፡ነው፤በእርሱ፡ከመከራ፡
ሥጋ፡ከመከራ፡ነፍስ፡ድነናል፡አለ።
፲፮፤ በተገረፈና፡በተቸነከረም፡ጊዜ፤በመከራው፡
ሁሉ፡መለኮትን፡ሕማም፡ተሰማው፡የሚል፡
ሰው፡ቢኖር፡የተለየ፡የተወገዘ፡ይሁን።

ምዕ፤፰፤፳፯-፴።

፳፯፤ ዳግመኛም፡ቅዱስ፡ቄርሎስ፡እንዲህ፡አለ፤
ተራበ፡ተጠማ፡ለሰው፡እንደሚገባ፡
አንቀላፋ፡ነቃ፡መንገድን፡በመሄድ፡ደከመ፡
በላ፡ጠጣ፡አለቀሰ፡ተከዘ፡አዘነ፡ይህ፡ጽዋ፡
ሞት፡ከእርሱ፡ያልፍ፡ዘንድ፡ለሰው፡እንደ፡

Scanned by CamScanner

በ፱፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

ከመ፡ይሕልፍ፡እምኔሁ፡ዘንቱ፡ጽዋዕ።
፳፰፤ ሐመ፡ወጥዕመ፡ሞተ፡በሥጋ፡በፈቃዱ፡ዕፀ፡
መስቀል፡እንዘ፡አሐዱ፡ውእቱ፡ምስለ፡
ሥጋ፡ዘቦቱ፡ጥዕመ፡ሞተ፡ወቦቱ፡ፈጸመ፡
ዘንተ፡ሥርዓተ፡ከመ፡ዘሎቱ፡አሐዱ፡ሕላዌ፡
መለኮት፡ምስለ፡ሥጋ፡እምአመ፡ኅደረ፡
ውስተ፡ከርሥ።
፳፱፤ ወለሊሁ፡ዓዲ፡ዘከመ፡ሥርዓተ፡ህላዌ፡
መለኮቱ፡ዘኢይትረከብ፡ያጸግብ፡ኵሎ፡
ኢይርኅብ፡ወኢይጸምእ፡ኢይደክም፡ወኢይ
ነውም፡ኢየሐምም፡ወኢይመውት፡
ወይሁብ፡ሕይወተ፡ለኵሉ።
፴፤ ወካዕበ፡ወረደ፡ውስተ፡መካናት፡እንተ፡
መትሕተ፡ምድር፡ከመ፡ያግዕዝ፡ነፍሳተ፡
ሰብእ፡እለ፡ሀለዋ፡ህየ፤ ወዔወወ፡ሲኦለ፡
በመለኮቱ።

ዓዲ፡እመልእክተ፡ሲኖዲቆን፡ዘአቡነ፡
ሱንትዮስ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡ዘለእስክን
ድርያ።

ምዕ፡፻፲፡፴፱–፵፤
፴፩፤ ወተወልደ፡እምብእሲት፡ድንግል፡እንተ፡
እምዘመድነ፡ወተወከፈ፡ረኃበ፡ወጽምአ፡
በልዐ፡ወሰትየ፡ኖመ፡ወደከመ፡ሐመ፡
ወተሰቅለ፡ወተቀነዋ፡እደዊሁ፡ወእገሪሁ፡
ወተረግዘ፡ገቦሁ፡በኲናት፤
ወለሊሁ፡ውእቱ፡ከመ፡ዝንቱ፡ውእቱ፡
አሐዱ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ዘተወልደ፡
እምአብ፡እምቅድመ፡ኵሉ፡ዓለም።
ወለሊሁ፡ውእቱ፡ከመ፡ዘተወልደ፡እምእግዝ
እትነ፡ማርያም፡በድኅሪ፡መዋዕል፡በከመ፡
አቅደምነ፡ወንቤ፡አኮ፡ካልእ፡ምስሌሁ፡አላ፡
ለሊሁ፡ውእቱ፡ዳእሙ፤ ወኢንብል፡እንከ፡
ከመ፡አሐዱ፡ገብረ፡ግብረ፡መለኮታዌ፡
ወካልኡ፡ካዕበ፡ገብረ፡ግብረ፡ትስብእታዌ፡
አላ፡በከመ፡ንቤ፡እስመ፡ለሊሁ፡ውእቱ፡
ወልድ፡ዋህድ፡ገብረ፡ግብረ፡ዘመለኮትሂ፡
ወዘትስብእትሂ፡ወአኮ፡በካልእ።
፴፪፤ ወይቤ፡ቅዱስ፡ማሬ፡ኤራቅሊስ፡ርእሰ፡ኤጲስ፡
ቆጶሳት፡ዘቍስጥንጥንያ፡ዘፈለሰ፡እምብሔረ፡
ኪስኪስ፡በመልእክቱ፡ኀበ፡ብሔረ

ዓርብ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

ሚገባ፡መላልሶ፡ማለደ።
፳፰፤ ታመመ፤ ሞትን፡ከተቀበለበት፡ከሥጋ፡ጋር፡
አንድ፡ሁኖ፡በመስቀል፡ላይ፡በፈቃዱ፡
በሥጋ፡ሞተ፤ አንድ፡ባሕርየ፡መለኮት፡
ሥጋን፡ተዋሕዶ፡በማሕፀን፡ካደረ፡ጀምሮ፡
ሥጋ፡ገንዘቡ፡እንደመሆኑ፡በሥጋ፡ይኸንን፡
ሥርዓት፡ፈጸመ።
፳፱፤ ለማይመረመር፡ለመለኮቱ፡ባሕርይ፡እንደ
ሚገባ፡ደግሞ፡እርሱ፡ኅብስት፡አበርክቶ፡
ሁሉን፡ያጠግባል፤ አይራብም፡አይጠማም፡
አይደክምም፡አያንቀላፋም፡አይታመምም፡
አይሞትም፡ሕይወትን፡ለሁሉ፡ይሰጣል።
፴፤ ዳግመኛ፡በዚያ፡በሲኦል፡ተግዘው፡
ያሉ፡ነፍሳትን፡ያድን፡ዘንድ፡በአካለ፡ነፍስ፡
ወደ፡ሲኦል፡ወረደ፤ በመለኮቱም፡ሲኦልን፡
በዘበዘ።

ዳግመኛ፡ወደ፡እርሱ፡ተልኮለት፡ለነበረው፡
መልእክት፡መልስ፡አድርጎ፡አባታችን፡የእ
ስክንድርያ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡ሱንትዮስ፡
የላከው፡ሲኖዶሳዊ፡መልእክት፡ይህ፡ነው።

ምዕ፡፻፲፡፴፱–፵።
፴፩፤ ከእኛ፡ወገን፡ከምትሆን፡ከድንግል፡
ማርያም፡ተወለደ፤ ተራበ፤ ተጠማ፤ በላ፤ ጠጣ፤
ተኛ፡ደከመ፤ ታመመ፤ ተሰቀለ፤ እጆቹ፡
እግሮቹ፡ተቸነከሩ፤ ጎኑን፡በጦር፡ተወጋ፤

እርሱ፡መቼም፡መች፡አንድ፡ነው፤ ዓለም፡
ሁሉ፡ሳይፈጠር፡ከአብ፡የተወለደ፡ይህ፡
አንዱ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ነው፤
በኋላ፡ዘመንም፡ከእመቤታችን፡ከማርያም፡
የተወለደ፡ያው፡እርሱ፡ነው፤ አስቀድመን፡
እንደተናገርን፡እርሱ፡ብቻ፡ነው፡እንጂ፡
ከእርሱ፡ጋር፡ያለ፡ሌላ፡ሁለተኛ፡የለም፤
እንዲሁም፡አንዱ፡መለኮታዊ፡ሥራን፡ሠራ፡
ዳግመኛም፡ደግሞ፡ሰብአዊ፡ሥራን፡ሠራ፡
አንልም፤ እንደ፡ተናገርን፡አንድ፡ወልድ፡
እሱ፡ነውና፤ የአምላክነትንም፡የሰውነትም፡
ሥራ፡ሠራ፡እንጂ፤ ሌላም፡አይደለም።
፴፪፤ ከኪስኪስ፡የሄደ፡የቍስጥንጥንያ፡ኤጲስቆ
ጳሳት፡አለቃ፡እግዚአብሔርን፡የሚያገለግል፡
ቅዱስ፡ኤራቅሊስ፡ወደ፡አርማንያ፡በላከው፡

Scanned by CamScanner

በ፫፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

አርማንዮ፡እንዘ፡ይብል፡ከመዝ፡ኢትበሉኬ፡
ከመ፡ንህነ፡ንዌስክ፡እሎንተ፡ግብራተ፡
ዘአልቦቱ፡ሕማም፡ኀበ፡ዘሎቱ፡ሕማም፡
ወመዊት፤ወኢንዌስክ፡ለዘየሐምም፡ኀበ፡
ዘኢየሐምም።
ጸሎቶሙ፡ወበረከቶሙ፡ለእሉ፡መምህራን፡
የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ተግሣጽ፡ዘይትነበብ፡በሠለስቱ፡ሰዓት፡
ዘዐርብ።

፩ ወለእመ፡ኮነ፡ዝንቱ፡ነገር፡ትን
ቢተ፡ወጥንቃቄ፡አበው፡ቀደመ፡
ነጊረ፡ወገሠጸ፡ለነ፡ለአለብዎትነ፡
ከመ፡እግዚእነ፡ሎቱ፡ስብሐት፡
ዘተሰብአ፡በእንቲአነ፡ወአስተርአየ፡
ዲበ፡ምድር፡ለአሠንዮ፡መድኃኒትነ።
ወተወክፈ፡ሕማመ፡በሥጋ፡ዘነሥአ፡
እምዘመድነ፡ከመ፡ያንጽሐነ፡እምጌ
ጋይነ፡ወያንግፈነ፡እምፀርነ፡ወይጺሕ፡
ለነ፡ፍኖተ፡መድኃኒትነ።

፪ መፍትው፡ለነ፡ናዕቢ፡ኀልዮ፡
በአንብቦ፡ወንለቡ፡ፍካሬሃ፡ለነገር፡
ወንትረከብ፡ውስተ፡ዝክራ፡እንዘ፡
ንኄሊ፡ወዲበ፡አውሥኦተ፡ዝክራ፡
ስሉን።

፫ ወለእመ፡ኮነ፡ነዳየ፡እምንዋየ፡ዝንቱ፡ዓለም፡
ትሬእዮ፡እማእከለ፡አብዕልት፡ውፁአ፡
ወቅድመ፡ክቡራን፡ሕዙነ፡ወሕሡመ፡
እስመ፡አልቦ፡ክሂሎት፡ከመ፡ይትዓረይ፡
በጥሪቶሙ፡ወኢከመ፡ይትረሰይ፡በትር
ሲቶሙ፡ሶበ፡እሙንቱ፡ይበልዕ፡ወይሰትዩ፡
ወይኤዝዙ፡ወይትፌግዑ፡ወይትፌሥሑ።
ወእሉ፡ነዳያን፡ይጼነሱ፡በምግባሪሆሙ።
ወይሰትዩ፡መሪረ፡ንዴቶሙ፡ወይረክቡ፡
እኪተ፡ዘአልቦ፡መጠን።

፬ እስመ፡ንህነ፡ንብል፡ምግባረ፡ክልኤሆሙ፡
ፍጡነ፡የኀልፍ፡ወምግባር፡ዘኢይነብር።

፭ ወንዴትሰ፡እምትምህርተ፡ሕግ፡ወተጸንሶ፡
እምሰሚዐ፡ነገረ፡መለኮት።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፫፡ሰዓት።

መልእክቱ፡እንዲህ፡ብሎ፡ተናገረ፤እነዚህን፡
ነገሮች፡ሕማም፡የሌለበትን፡ሕማም፡ሞት፡
ካለበት፡እንደምንቀላቅል፡አድርጋችሁ፡
አትናገሩ፤የሚታመመውን፡ከማይታ
መመው፡አናደባልቅም።
የእነዚህ፡መምህራን፡በረከታቸው፡ጸሎታቸው፡
ከእኛ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡ይኑር፡አሜን።

ዐርብ፡በሦስት፡ሰዓት፡የሚነበብ፡ተግሣጽ፡
ምክር፡ምዕዳን።

፩፤ ይህ፡ነገር፡ትንቢት፡ቢሆንም፡እኛን፡ለማስ
ተማርና፡ልብ፡ለማስደረግ፡ጌታችን፡የክብር፡
ባለቤት፡ስለ፡እኛ፡ሰው፡የሆነ፤ለበጎ፡ድኅነታ
ችንም፡በምድር፡ላይ፡የተገለጠ፤ከበደላ
ችንም፡ያነጻን፡ዘንድ፡ከባሕርያችን፡
በነሣው፡ሥጋ፡መከራን፡የተቀበለ፤ከጠላታ
ችንም፡እጅ፡ያድነን፡ዘንድ፡የድኅነትንም፡
መንገድ፡ይጠርግልን፡ዘንድ፡እንደሆነ፡
አባቶች፡ነቢያት፡ያስተማሩትን፡በጥንቃቄ፡
መናገርን፡አስቀደመ።

፪፤ መጻሕፍትን፡በማንበብ፡ዕውቀታችንን፡ከፍ፡
እናደርግ፡ዘንድ፤የነገሩንንም፡ምሥጢር፡እናስ
ተውል፡ዘንድ። ለእኛ፡ይገባናል፤እርሷን፡
በማሰብ፡ሁነን፡ሥውር፡የሆነ፡የመታሰቢንም፡
መልስ፡አዘጋጅተን፡እንገኝ፡ዘንድ።

፫፤ ከዚህ፡ዓለም፡ገንዘብ፡ድኃ፡ቢሆን፡ከባለጸጎች፡
መካከል፡የወጣ፡የተለየ፡ሁኖ፡በከበርቴ
ዎችም፡ፊት፡ያዘነ፡የከፋው፡ሁኖ፡ታየዋለህ፤
በጥሪት፡ሊስተካከላቸው፡በሽልማታቸው፡
ሊሸለም፡በጌጣቸው፡ሊያጌጥ፡ችሎታ፡
የለውምና፤እነርሱ፡በሚበሉና፡በሚጠጡ፡
በሚያዝዙ፡ፈጽመው፡በሚደሰቱ፡ጊዜ፡
እነዚያ፡ድሆች፡በኑሮአቸው፡ይቸገራሉ፤
መራራ፡ድኅነታቸውንም፡ይነከሩበታል።
መጠን፡የሌለውንም፡ክፉ፡ችግር፡ያገኛሉ።

፬፤ እኛ፡የሁለቱም፡ሥራ፡ፈጥኖ፡ያልፋል፡
እንላለን፤ነዋሪ፡ሥራ፡አይደለምና።

፭፤ ድኅነት፡ግን፡ሕግን፡ከአለመማር፤ችግርም፡
የአምላክን፡ነገር፡ካለመስማት፡ነው።

Scanned by CamScanner

## በ፫፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

፩፡ ወሚ ፡ መጠን ፡ ትካዝ ፡ ዘይቴክዙ ፡ ወሚ ፡ መጠን ፡ ሥቃይ ፡ ዘይደልዎሙ ፡ ወሚ ፡ መጠን፡ ማዕርገ ፡ ኀሱረ ፡ ይኔ ጽሩ ፡ ወየኀስሩ ፡ ወየሐጽጹ ፡ ለበጺሖታ ፡ እስመ ፡ ዘኢየአምር ፡ ሕገ ፡ በከመ ፡ ይደሉ ፡ እፎ፡ይክል፡ገቢሮታ።

፪፡ ወበከመ ፡ ብዑላን ፡ በንዋየ ፡ ዓለም ፡ ይትዐወቁ፡ በብዙኀ ፡ ጥሪቶሙ ፡ በዘ ዘኢአሁ ፡ ሞገስ ፤ ወእፎ፡ ይትሜከሑ ፡ ወይትዐ ዲበ ፡ እለ ፡ ከማሆሙ ፡ ወይትዐ ረቁ ፡ ሊቃውንተ ፡ ወመኳንንተ ፡ ወመሳፍንተ።

፫፡ ወበዘከመዝ ፡ እለ ፡ ብዑላን ፡ በነገራተ ፡ መለኮት ፡ ታዐውቆሙ ፡ ይእቲ ፡ ቃል ፡ ጥንቁቀ፡ፈድፋደ፡እምእሉ።

፬፡ ቅድመ ፡ ትሜህሮሙ ፡ ፈቃደ ፡ እግ ዚአብሔር ፡ ወበዳግም ፡ ሐዊረ ፡ በፍኖተ ፡ ርትዕ።

፭፡ ካዕበ ፡ ይትቀሐዉ ፡ ወያፈደፍዱ ፡ ወይትሌዐሉ ፡ ወይሠርቁ ፡ እስከ ፡ ሶበ ፡ ይትኤዘዞሙ ፡ ኵሉ ፡ ዘተፈጥረ ፡ ወያስተ ርኢያ ፡ ሎሙ ፡ ክቡራት ፡ ወይትዬዋሃ ፡ ሎሙ፡ዕጹባት፡ወይጸያሃ፡ሎሙ፡መብእሳት፡ ወይትቀነዩ፡ሎሙ፡አብዕልት፡በንዋዮሙ፡ ወይፈርህዎሙ፡ነገሥት፡በእንተ፡ዘተአዘዙ፡ ለፈጣሪሆሙ ፡ ያስተዴሉ ፡ ሎሙ ፡ ሞገሰ ፡ መለኮት።

፮፡ ወይብጽሑ፡ውስተ፡ምንባረ፡ገነት፡ወይትራ ከብዎሙ ፡ መላእክት ፡ ፍሡሐን ፡ በገጽ ፡ ፍሡሕ ፡ ወበአስኬማ ፡ ብሩህ ፡ በከመ ፡ ይትቄበሉ፡አብዕልት፡ቢጸሙ።

፯፡ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ከመዝ ፡ መፍትው ፡ ለነ ፡ ናፍቅሮን፡ ለሰሚዐ ፡ ምዕዳን ፡ ወንለቡ ፡ ፍካሬ ፡ ነገራት ፡ ወንትባደር ፡ ለዐቂቦቶሙ ፡ እንዘ ፡ ንትሐሠይ ፡ ወንትኤዘዝ ፡ በሕገጊሃ ፡ በፍሥሓ።

## ዓርብ፡መዓልት፡በ፫፡ሰዓት።

፩፡ የሚያዝኑት ፡ ሐዘን ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ይሆን፤የሚ ገባቸውስ ፡ ቅጣት ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ይሆን፤ምን፡ ያህልስ ፡ የተጐሳቈለ ፡ ደረጃ ፡ ይመለከቱ፡ ይሆን፤ወደ፡እርሷ፡በመድረስም፡ይዋረዳሉ፤ ሕግን ፡ በሚገባ ፡ የማያውቅ ፡ ሊሠራት ፡ እንዴት፡ይችላል?

፪፡ ባለጸጎች ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ገንዘብ ፡ በብዙ ፡ ጥሪ ታቸውም ፡ እንዲታወቁ ፤ በየሁሉ ፡ ዘንድም፡ መወደድ፡እንዳላቸው፡እንደርሳቸው፡ባሉት፡ ላይ ፡ እንዴት ፡ እንደሚመኩ ፡ ይታወቃሉ፤ ሊቃውንቱን ፡ መኳንንቱን ፡ መሳፍንቱን፡ ወዳጅ፡ባልንጀራ፡ያደርጋሉና።

፫፡ በእንደዚህም፡የባለጸጎችን፡ምሳሌ፡አድርጋ፡ ይቺ፡ ቃል ፡ በብዙ ፡ ጥንቃቄ፡ለእነርሱ፡የአም ላክን፡ነገሮች፡ታሳውቃቸዋለች።

፬፡ አስቀድማ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ፈቃድ ፡ ማወቅን ፡ ታስተምራቸዋለች ፤ ደግሞ፡ በቀና፡ መንገድ፡መሄድን።

፭፡ ዳግመኛም ፡ ለትሩፋት ፡ ለገድል ፡ የሚፋ ከሩና ፡ እጅግ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ የሚሉ ፡ ፍጥረቱ፡ ሁሉ ፡ እስከሚታዘዝላቸው ፡ ድረስ ፡ የከበሩ፡ ነገሮችም፡እስቲገለጹላቸው፡ድረስ፡አስፈሪ፡ አስጨናቂ፡የሆኑ፡አራዊት፡እስቲገሩላቸው፡ ድረስ፡ሻካራ፡ጐጣጐጥ፡መንገድ፡እስኪጠረ ግላቸው ፡ ድረስ ፡ ሀብታሞች ፡ በገንዘባቸው፡ እስከሚያገለግሏቸው ፡ ድረስ ፡ ነገሥታቱም፡ እስከሚፈሩአቸው ፡ ለፈጣሪያቸው ፡ ስለ ታዘዙ፡እምላካዊ ፡ ግርማ፡(ረድኤት)፡ያሳድር ባቸዋል።

፮፡ በገነትም ፡ ውስጥ ፡ ወደ ፡ መኖር ፡ ይደርሳሉ፤ ባለጸጎች፡ባለንጀራቸውን፡ደስ፡ብሏቸው፡እን ደሚቀበሉ፡መላእክትም፡በብሩህ፡ገጽ፡ብሩህ፡ ትጥቅ፡አስኬማ፡ይዘው፡ይገናኟቸዋል።

፯፡ እንዲሁም ፡ ከሆነ ፡ መጻሕፍት ፡ የሚመክ ሩንን፡ መስማት ፡ የነገሩንንም ፡ ምሥጢር፡ ማስተዋል ፡ ለእኛ ፡ ይገባናል ፤ ደስ፡እያለንም፡ እነርሱን ፡ ለመጠበቅ ፡ እንሽቀዳደም ፤ ለሥርዓቷ፡ለሕጓ፡በደስታ፡ሁነን፡እንታዘዝ።

## በ፫፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

፲፫ ወእፎ፡መንክር፡እስመ፡እለ፡የዐቅቡ፡መሐድ
ምታተ፡ወይሰምዑ፡ነገረ፡ነግድ፡ትሬእዮሙ፡
ይትናገሩ ፡ በውስተ ፡ አብያቲሆሙ ፡
ወይዜንዉ፡ባቲ፡ለአነዊሆሙ፡ወይሰነዐዉ፡
በነገሮታ፡ወይትሜከሑ።

፲፬ ወከመዝ፡እለ፡የሐትቱ፡በእንተ፡ክዱናት፡
ወየኀሥሡ ፡ በእንተ ፡ መዛግብት ፡ ወመድ
ፍናት፡ኅቡአት፡ትሬእዮሙ፡ሶበ፡ረከቡ፡
ኀሰቲተ፡እምነ፡ወርቅ፡አው፡በስውር፡
ወንኡስ፡እምወርቅ፡ክቡር፡ይትፌሥሑ፡
ቦቱ፡ወይትሐሠዩ።

፲፭ ወንህነሰ ፡ ኢገበርነ ፡ከመዝ ፡ ለነገራተ ፡
እግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡።
ዘሎቱ፡ክብር፡ወስብሐት፡ወውዳሴ፡ይደሉ፡
ምስለ፡አቡሁ፡ወመንፈሱ፡ቅዱስ፡ኵሎ፡
ጊዜ፡ይእዜኒ፡ወዘልፈኒ፡ወለዓለመ፡ዓለም፡
አሜን፤ወአሜን፡ለይኩን፡ለይኩን።

### ላሐ፡ማርያም።

**በስመ፡አብ፡ወወልድ፡ወመንፈስ፡ቅዱስ፡፩፡
አምላክ።**

፩ ድርሳን፡ዘደረሰ፡አባ፡ሕርያቆስ፡ኤጲስቆጶስ፡
ዘሀገረ፡ብህንሳ፡በእንተ፡ክብራ፡ለድንግል፡
ንጽሕት፡ማርያም፡ወብካያ፡ወላሓ፡በእንተ፡
ስቅለተ፡ወልዳ፡ወበእንተ፡ርደቱ፡ውስተ፡
መቃብር፡አመ፡ሐረት፡ወኢረከበት፡ሥጋሁ፡
በዕለተ፡ትንሣኤሁ፡ቅድስት፡ሶበ፡ተንሥአ፡
እሙታን፡በሰላመ፡እግዚአብሔር። ጸሎታ፡
ወበረከታ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡
አሜን።

፪ ይቤ፡ብካዩ፡ለያዕቆብ፡ሊቀ፡አበው፡ተሐደሰ፡
ዮም፡አ፡ፍቁራንየ።

፫ ለምንት ፡ ኢትበኪ ፡ ማርያም ፡ ድንግል ፡
ላዕለ ፡ ወልዳ ፡ ፍቁር ፡ ዘፀንሰቶ ፡ በድን
ግልናሃ።

፬ ለምንት ፡ ኢትበኪ ፡ ማርያም ፡ በእንተ ፡
ዘሐመት፡ቦቱ።

፭ ለምንት፡ኢትበኪ፡ማርያም፡ድንግል፡ላዕለ፡
ዘወሀበቶ፡ጥባ፡ድንግልናዊ።

፮ ለምንት፡ኢትበኪ፡ማርያም፡ድንግል።

## ዓርብ፡መዓልት፡በ፫፡ሰዓት።

፲፫ ተረቶችን፡የሚያጠናቅሩና፡እንግዳ፡ነገርን፡
የሚሰሙ፡በየቤቶቻቸው፡ሲናገሩትና፡ከባል
ንጀሮቻቸው ፡ ጋር ፡ ዕንቆቅልሽ ፡ ሲጫወ
ቱባት፡ በነገርዋም፡ሲስማሙ፡ሲመኩባት፡
እንዴት፡ድንቅ፡እንደሆነ፡ታያቸዋለች።

፲፬ እንዲሁም፡በምድር፡ውስጥ፡ስለ፡ተሸሸጉ፡
መአድናት፡የሚመረምሩትን፡ስታያቸው፡
ተሠውሮ፡ከነበረው፡ወርቅ፡ትንሽ፡ያገኙ፡
እንደሆነ፡ወይም፡በስውር፡ከተቀመጠውና
ከከበረው፡ወርቅ፡ከማግኘታው፡የተነሣ፡
ፈጽመው፡ደስ፡ይሰኙበታል።

፲፭ እኛ፡ግን፡የጌታችንን፡የኢየሱስ፡ክርስቶስን፡
ነገሮች፡እንዲህ፡አላደረግንም።
ለእርሱ ፡ ክብር ፡ ጌትነት ፡ ምስጋናም ፡
ከባሕርይ፡አባቱና፡ከቅዱስ፡መንፈሱ፡ጋር፡
ሁልጊዜ ፡ ዛሬም ፡ ዘወትርም ፡ ለዘላለሙ ፡
ይገባል፤በእውነት፡ይሁን፡ይደርግ።

### የማርያም፡ሐዘን።

**አንድ ፡ አምላክ ፡ በሆነ ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡
በመንፍስ፡ቅዱስ፡ስም።**

፩ በእግዚአብሔር ፡ ፍቅር ፡ አንድነት ፡
የድንግል፡ ንጽሕት ፡ ማርያም ፡ ልመናዋ ፡
ክብርዋ፡ከእኛ፡ጋር፡ለዘላለሙ፡በእውነት፡
ይደርብንና፤ስለ፡ልጅዋ፡መሰቀልና፡ወደ፡
መቃብርም፡መውረድ፡በከበረች፡በትንሣ
ኤውም፡ቀን፡በተነሣ፡ጊዜ፡ሒዳ፡ሥጋውን፡
ባለማግኘቷ፡ስለ፡አለቀሰችው፡ልቅሶና፡ስለ፡
ክብርዋ፡የብህንሳ፡ሀገር፡ኤጲስቆጶስ፡አባ፡
ሕርያቆስ፡የደረሰው፡ድርሳን፡ይህ፡ነው።

፪ ወዳጆቼ፡ሆይ፡የአባቶች፡አለቃ፡የያዕቆብ፡
ልቅሶ፡ዛሬ፡ታደሰ፡አለ።

፫ በድንግልና፡ፀንሳ፡በድንግልና፡ለወለደችው፡
ለተወዳጅ፡ልጅዋ፡ድንግል፡ማርያም፡ ለምን፡
አታለቅስም።

፬ መከራ፡ስለተቀበለችበት፡ድንግል፡ማርያም፡
ለምን፡አታለቅስም።

፭ የድንግልና፡ጡቷን፡ለአጠባችው፡ድንግል፡
ማርያም፡ ለምን፡አታለቅስ።

፮ በቤተ ፡ ልሔም ፡ በበረት ፡ ስለወለደችው ፡

## በ፫፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

በእንተ፡ዘወለደቶ፡በጎል፡በቤተ፡ልሔም።
ለምንት፡ኢትበኪ፡ማርያም፡ድንግል፡ላዕለ፡
፯፡ ወልዳ፡ፍቁር፡በእንተ፡ዘጸረቶ፡ተሥዐተ፡
እውራኀ።
፰፡ ለእመ፡ኮነት፡ራኄል፡ትበኪ፡ላዕለ፡ውሉድ፡
ዘኢሰዐመቶሙ፡ግሙራ። ለምንት፡
ኢትበኪ፡ማርያም፡ድንግል፡ላዕለ፡ዘጸረቶ፡
ውስተ፡ሕፅና፡በከመ፡ነፍሉ፡ሰብእ።
፱፡ ለእመ፡ኮነት፡ራሔል፡ትበኪ፡ላዕለ፡ውሉድ፡
ዘኢጕየት፡በሙ፡እመካን፡ውስተ፡መካን።
፲፡ ለምንት፡ኢትበኪ ማርያም፡ድንግል፡ላዕለ፡
ወልዳ፡ዘጕየት፡ቦቱ፡እምሀገር፡ኀበ፡ሀገር።
፲፩፡ ለእመ፡ራሔል፡ትበኪ፡ላዕለ፡ውሉድ፡ዘኢር
እየት፡መቃብሪሆሙ፡ግሙራ።
፲፪፡ ለምንት፡ኢትበኪ ማርያም፡ድንግል፡ላዕለ፡
እንቀጸ፡መቃብር፡ዘወልዳ፡ዋህድ።
፲፫፡ ተሐደሰ፡ዮም፡ብካይ፡ዘአረጋዊ፡
በዐለ፡ጽሕም፡ሠናይ፡እምኀበ፡ወለት፡
ድንግል።
፲፬፡ ኢርእየ፡ያዕቆብ፡ኀበ፡ዮሴፍ፡ሶበ፡አሰርዎ፡
አኀዊሁ።
፲፭፡ ወድንግልሰ፡ርእየቶ፡ለወልዳ፡እንዘ፡ቅንው፡
ላዕለ፡ዕፀ፡መስቀል።
፲፮፡ ኢርእየ፡ያዕቆብ፡ኀበ፡ዮሴፍ፡እንዘ፡ውእቱ፡
ውስተ፡ግብ፡ርሒብ፡ከመ፡ይብኪ፡ላዕሌሁ።
፲፯፡ ወድንግልሰ፡ርእየቶ፡ለወልዳ፡እንዘ፡ስቁል፡
ማዕከለ፡ጉባዔ፡አይሁድ።
፲፰፡ ኢርእየ፡ያዕቆብ፡ኀበ፡ዮሴፍ፡እንዘ፡
ያዐርቅዎ፡አልባሲሁ፡አኀዊሁ፤
፲፱፡ ወድንግልሰ፡ርእየቶ፡ለወልዳ፡እንዘ፡ዕሩቅ፡
ማዕከለ፡አይሁድ፡ኅጡአነ፡ምክር።
፳፡ ኢርእዮ፡ያዕቆብ፡ለዮሴፍ፡እንዘ፡ይሠይጥዎ፡
አኀዊሁ፡ለዕሥራ፡ብሩር።
፳፩፡ ወድንግልሰ፡ርእየቶ፡ለወልዳ፡እንዘ፡
ይሠይጦ፡ይሁዳ፡ለሠላሳ፡ብሩር።
፳፪፡ በደመ፡ባዕድ፡በከየ፡ላዕሌሁ፡ያዕቆብ፡
ወልብሱ፡ሥጡጥ፡ዘኢሠጠጥዎ፡አራዊት።
፳፫፡ ወደምሰ፡አምላካዊ፡ዮም፡ውኁዝ፡
ላዕለ፡ኰኵሕ፡ዘትበኪ፡ድንግል፡
በእንቲአሁ።

## ዓርብ፡መዓልት፡በ፫፡ሰዓት።

ልጅዋ፡ድንግል፡ማርያም፡ለምን፡አታለቅስ።
፯፡ በማኅፀንዋ፡ዘጠኝ፡ወር፡ከአምስት፡ቀን፡ለተ
ሸከመችው፡ተወዳጅ፡ልጅዋ፡ድንግል፡
ማርያም፡ለምን፡አታለቅስ።
፰፡ ከቶ፡ወልዳ፡ላልሳመቻቸው፡ልጆች፡ራሔል፡
የምታለቅስ፡ከሆነ፤እንደ፡ሰው፡ሁሉ፡
በብብቷ፡ለተሸከመችው፡ልጅዋ፡ድንግል፡
ማርያም፡ለምን፡አታለቅስ።
፱፡ ከቦታ፡ወደቦታ፡ይዛ፡ላልተሰደደችባቸው፡
ልጆች፡ራሔል፡የምታለቅስ፡ከሆነ።
፲፡ ከሀገር፡ወደ፡ሀገር፡አዝላ፡ለተሰደደችበት፡
ልጅዋ፡ድንግል፡ማርያም፡ለምን፡አታለቅስ።
፲፩፡ ከቶ፡መቃብራቸውን፡ላላአየች፡ልጆቿ፡
ራሔል፡የምታለቅስ፡ከሆነ።
፲፪፡ በአንድ፡ልጅዋ፡መቃብር፡ደጃፍ፡ላይ፡
ድንግል፡ማርያም፡ለምን፡አታለቅስ።
፲፫፡ የባለ፡መልካም፡ጽሕም፡ሽማግሌ፡የያዕቆብ፡
ልቅሶ፡በብላቴናይቱ፡ድንግል፡ዘንድ፡ዛሬ፡
ታደሰ።
፲፬፡ ወንድሞቹ፡ባሰሩት፡ጊዜ፡ያዕቆብ፡ወደ፡
ዮሴፍ፡አልተመለከተም።
፲፭፡ ድንግል፡ግን፡ልጅዋን፡በዕንጨት፡መስቀል፡
ላይ፡ተቸንክሮ፡አየችው።
፲፮፡ ዮሴፍ፡በሰፊ፡ጉድጓድ፡ውስጥ፡ሳለ፡ያዕቆብ፡
በላዩ፡ያለቅስ፡ዘንድ፡ወደ፡ዮሴፍ፡አላየም።
፲፯፡ ድንግል፡ግን፡በአይሁድ፡ጉባዔ፡መካከል፡
ተሰቅሎ፡ልጅዋን፡አየችው።
፲፰፡ ዮሴፍን፡ወንድሞቹ፡ልብሱን፡ገፈው፡ሲያራ
ቁቱት፡ያዕቆብ፡አላየም።
፲፱፡ ድንግል፡ግን፡በጎ፡ምክር፡በሌላቸው፡
በአይሁድ፡መካከል፡ልብሱን፡ተገፎ፡
ራቁቱን፡ሁኖ፡አየችው።
፳፡ ወንድሞቹ፡ዮሴፍን፡በሃያ፡ብር፡ሲሸጡት፡
ያዕቆብ፡አላየም።
፳፩፡ ድንግል፡ግን፡ይሁዳ፡ልጅዋን፡በሠላሳ፡ብር፡
ሲሸጠው፡አየች።
፳፪ አራዊት፡ባልቀደዱት፡ልብሱና፡በሌላ፡ደም፡
ላይ፡ያዕቆብ፡አለቀሰ።
፳፫፡ አምላካዊ፡ደም፡ግን፡ድንግል፡ማርያም፡
ስለእርሱ፡በላዩ፡የምታለቅስበት፡በቀራንዮ፡
አለት፡ላይ፡የፈሰሰው፡ነው።

Scanned by CamScanner

## በ፱፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

፳፬ ወባዕደ፡ልብሰ፡ዘርእየት፡ድንግል፡ዮም፡ዘአ
ልበስዎ ፡ ለወልዳ ፡ ወኮኑ ፡ ይትካፈሉ ፡
አልባሲሁ፡በበይናቲሆሙ።
፳፭ አኀዊሁ ፡ ለዮሴፍ ፡ በከዩ ፡ ወነስሐ ፡ ሶበ ፡
ሤጥዎ፡ለእኁሆሙ።
፳፮ ወደቂቀ፡እስራኤልሰ፡ኢበከዩ፡ሶበ፡ሤጡ፡
እግዚእሙ።
፳፯ ደቂቀ ፡ ያዕቆብ ፡ ተፈሥሑ ፡ ሶበ ፡ ነግሠ ፡
እኁሆሙ።
፳፰ ወአይሁድሰ፡ኢተፈሥሑ፡ሶበ፡ተንሥአ፡
እግዚእሙ፡እምነ፡ምውታን።
፳፱ በአማን፡አ፡ድንግል፡ላሕኪ፡ጥዑም፡ላዕለ፡
መቃብረ ፡ ወልድኪ ፡ ወቃልኪ ፡ ሠናይ ፡
ማእከለ፡መላእክት፡ሶበ፡ዜነዉኪ፡ወይቤሉ፡
አ፡ማርያም፡ ለምንት ፡ ትነብሪ ፡ ወምንተ ፡
ትገብሪ።

፴ ናሁ ፡ ለወልድኪ ፡ አቀምዎ ፡ ቅድመ ፡
መኰንን፡ ይኴንንዎ ፡ ወይሜንንዎ ፡ ሊቃነ ፡
ካህናተ ፡ አይሁድ ፡ አ ፡ ማርያም ፡ ምንተ ፡
ትገብሪ ፡ ናሁ ፡ ወልድኪ ፡ ውስተ ፡ ዓውደ ፡
ፍትሕ ፡ እንዘ ፡ ያዐርቅዎ ፡ እም
ልብሱ፡ክቡር።
፴፩ አ፡ወለተ ፡ ኢያቄም ፡ ለምንት ፡ ትነብሪ ፡
ወምንተ ፡ ትገብሪ ፡ ናሁ ፡ ይጸውር ፡ ዕፀ ፡
መስቀል፡ባሕቲቶ፡ውስተ፡መርሕባ፡ለኢየሩ
ሳሌም ። አልቦ ፡ ወኢአሐዱ ፡ ዘይቀርብ ፡
ኀቤሁ።
፴፪ አ፡ርግብ፡ዘሐና፡ለምንት፡ትነብሪ፡ወምንተ፡
ትገብሪ ፡ ናሁ ፡ ወልድኪ ፡ ውስተ ፡ መካነ ፡
ቀራንዮ፡ዘይቀውም፡እንዘ፡ይሰቅልዎ።
፴፫ አ ፡ ዘርዐ ፡ ዳዊት ፡ ለምንት ፡ አልዐልዎ ፡
ለወልድኪ፡ላዕለ፡መስቀል።
፴፬ በአማን ፡ አ ፡ እግዝእት ፡ ድንግል ፡ ላሕኪ ፡
ዮም፡ጥዑም፡ውስተ፡ቤተ፡ዮሐንስ፡እንዘ፡
ትባኪ።
፴፭ አ፡ለዝንቱ፡ዜናዊ፡መሪር፡ዘመጽአ፡ኀቤየ፡
ዮም፡ይመርር፡እምዘዜነውዎሙ፡ለኢዮብ፡
ወለያዕቆብ፡እስራኤል።
፴፮ አ፡ለዝንቱ፡ዜናዊ፡እኩይ፡ዘይመጽእ፡ኀቤየ፡
ዮም።

## ዓርብ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

፳፬፤ ድንግል፡ግን፡ዛሬ፡ያየችው፡ልጅዋን፡ያለበ
ሱትን፡ሌላ፡ልብስ፡ነበረ፤የራሱን፡ልብስ፡
ግን፡እርስ፡በርሳቸው፡ተካፈሉት።
፳፭፤ የዮሴፍ፡ወንድሞች፡ወንድማቸው፡ዮሴፍን፡
በሸጡት፡ጊዜ፡አለቀሱ፤ተጸጸቱ።
፳፮፤ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ግን ፡ ጌታቸውን ፡
በሸጡት፡ጊዜ፡አላለቀሱም፤አልተጸጸቱም።
፳፯፤ የያዕቆብ ፡ ልጆች ፡ ወንድማቸው ፡ በነገሠ ፡
ጊዜ፡ተደሰቱ።
፳፰፤ አይሁድ፡ግን፡ጌታቸው፡ከሙታን፡ተለይቶ፡
በተነሣ፡ጊዜ፡ደስ፡አላላቸውም።
፳፱፤ ድንግል ፡ ሆይ ፤ በእውነት ፡ በልጅሽ ፡
መቃብር፡ ላይ ፡ ልቅሶሽ ፡ ጣዕም ፡ ያለው ፡
አሳዛኝ፡ነበረ፤ማርያም፡ሆይ፡ለምን፡ተቀም
ጠሻል ? ምን ፡ ታደርጊያለሽ ፡ ብለው ፡
የልጅሽን፡መሰቀሉን፡በነገሩሽ፡ጊዜ፡በመላ
እክት፡መካከልም፡ቃልሽ፡ያማረ፡ነበር።
፴፤ እነሆ ፤ ልጅሽን ፡ በመኰንኑ ፡ ፊት ፡ አቁመ
ውታል፤የአይሁድ፡ሊቃነ፡ካህናትም፡ያሰቃ
ዩታል፡ያቃልሉታል፤ማርያም፡ሆይ፡ምን፡
ታደርጊያለሽ ፡ እነሆ ፡ ልጅሽን ፡ በፍርድ፡
አደባባይ፡መካከል፡ልብሱን፡ገፈው፡እያራ
ቆቱት፡ነው።
፴፩፤ የኢያቄም፡ልጅ፡ማርያም፡ሆይ፡ለምን፡ተቀ
ምጠሻል፤ምንስ፡ታደርጊያለሽ፤እነሆ፡በኢየ
ሩሳሌም ፡ ሜዳ ፡ የሚሰቀልበትን ፡ ግንድ ፡
ብቻውን፡ተሸክሞአል፤አንድ፡እንኳ፡ወደ፡
እርሱ፡የሚቀርብ፡የለም።
፴፪፤ የሐና፡ርግብ፡ሆይ፡ለምን፡ተቀመጥሽ?የምት
ሰሪውስ ፡ ምንድን ፡ ነው ? እነሆ ፡ ልጅሽን ፡
ሰቅለውት፡በቀራንዮ፡ቦታ፡ቁሞአል።
፴፫፤ የዳዊት፡ዘር፡ሆይ፡ልጅሽን፡በመስቀል፡ላይ፡
ለምን፡ከፍ፡ከፍ፡አደረጉት።
፴፬፤ እመቤት፡ድንግል፡ሆይ፡በዮሐንስ፡ቤት፡
ዛሬ፡ ልቅሶሽ ፡ በእውነት ፡ ጣዕም ፡ ያለው ፡
ነበረ፤እንዲህ፡ስትዪ።
፴፭፤ ወዮ፡ለዚህ፡መራራ፡ወሬ፡ነጋሪ፡ለኢዮብና፡
እስራኤል፡ለተባለ፡ያዕቆብ፡ከአረዱቸው፡
መርዶ፡የመረረ፡ነው።
፴፮፤ ዛሬ፡ወደእኔ፡ለሚመጣ፡ለዚህ፡ለክፉ፡ወሬ፡
ወዮ።

## በ፲፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

፴፯፤ አ፡ወልድየ፡ የዐጽብ፡እምዘዜነውዎ፡ለሎጥ፡
አመ፡ሶበ፡አውዐዩ፡ሀገሮ።

፴፰፤ አ፡ለዝንቱ፡ሰብከት፡እሕማሚ፡ዘበጽሐ፡
ላዕሌየ፡ዮም።

፴፱፤ አ፡ወልድየ፡ የዐቢ፡እምዘዜነውዎሙ፡
በሞተ፡ኃያላነ፡እስራኤል።

፵፤ አ፡ለዝንቱ፡ዜናዊ፡ዘመጽአ፡ኀቤየ፡በዝንቱ፡
ዜና፡እኩይ።

፵፩፤ አ፡ወልድየ፡ ናሁ፡ሠላሳ፡ዓመት፡እንዘ፡
ትናገዘኒ፡ወኢተክህለኒ፡እገሥጽከ፡ወኢአ
መንኩከ፡እሐተ፡ሰዓተ፡እስከ፡መጽአ፡
ዜናከ፡ኀቤየ፡ዮም።

፵፪፤ አ፡ወልድየ፡ ይእቲ፡ሰሎሜ፡ጥንቱ፡ለኵሉ፡
ሐዘንየ፡እንሰ፡ኢይወጽእ፡እምቤትየ፡ከመ፡
እርአዮ፡ለመኰንን፡ወኢይቀውም፡ቅድመ፡
ፈታሒ።

፵፫፤ ወኢርኢኩ፡ሰራቄ፡ዘይመትሩ፡ርእሶ፡ወኢፈ
ያታዌ፡ከመ፡ይቅትልዎ።

፵፬፤ ወኢርኢኩ፡ቀራንዮ፡ግሙራ፡ወኢየአምር፡
መካነ፡ጎልጎታ፡ወኢቆምኩ፡ኀበ፡እለ፡
ይትበአሱ፡ዘልፈ።አ፡ወልድየ፡ ኢርኢኩ፡
ፍትሐ፡እኩየ፡ወኢቆምኩ፡ውስተ፡ማኅበረ፡
ፍትሕ፡ለገዘሉፉ።

፵፭፤ አ፡ወልድየ፡ ኢየአምር፡ዐመፃ፡ዘገበርኩ፡
ብከ።ወአንሰ፡ውስተ፡ቤተ፡ዮሐንስ።

፵፮፤ አ፡ወልድየ፡ ወፍቁርየ፡ወእንተ፡
ዐጸደ፡ሐና፡ሊቀ፡ካህናት፡ዜናከ፡
መሪር።

፵፯፤ አ፡ወልድየ፡ ፍቁርየ፡ዮም፡አእተትከ፡
እምኔየ፡ግዕዝየ።

፵፰፤ ዜነዉኒ፡በእንተ፡ልደትከ፡በናዝሬት፤
ወይእዜሰ፡ዜነዉኒ፡በዛቲ፡እኪት፡በኢየሩ
ሳሌም።

፵፱፤ በጽሐኒ፡ሰብከት፡ሠናይ፡በቤተ፡ዮሴፍ፡
ወበጽሐኒ፡ዜና፡ሞትከ፡በቤተ፡ዮሐንስ።

፶፤ አ፡ወልድየ፡ ፍቁርየ፡አንሰ፡ነበርኩ፡እንዘ፡
እትፌሣሕ፡በልብየ።

፶፩፤ ወእብል፡ኵሎ፡ዕለተ፡ጌሠመ፡ይበ
ጽሕ፡ፋሲካ፡ከመ፡ንግበር፡በዓለ፡
ወንትመየጥ፡ውስቲ፡ብሔርነ፡ወበጽሐኒ፡
ፋሲካየ።

## ዓርብ፡መዓልት፡በ፲፡ሰዓት።

፴፯፤ ልጄ፡ሆይ፡ አገሩን፡በእቃጠሉ፡ጊዜ፡ለሎጥ፡
ከአረዱት፡መርዶ፡ያስጨንቃል።

፴፰፤ በእኔ፡ላይ፡ለደረሰው፡ለዚህ፡አስጨናቂ፡
ስብከት፡ወዮ።

፴፱፤ ልጄ፡ሆይ፡ ስለ፡ኃያላነ፡እስራኤል፡ሞት፡ከአ
ረዱአቸው፡መርዶ፡ይበልጣል።

፵፤ በዚህ፡በክፉ፡ወሬ፡ወደእኔ፡ለመጣው፡
ለዚህ፡ወሬ፡ነጋሪ፡ወዮ።

፵፩፤ ልጄ፡ሆይ፡ እነሆ፡ስታረጋጋኝ፡ሠላሳ፡
ዓመት፡ ይሆናል፤ ልገሥጽህም፡አልተቻ
ለኝም፤ዛሬ፡ወደ፡እኔ፡ወሬህ፡እስከመጣ፡
ድረስ፡ወጥተህ፡እስከምትገባ፡አንዲት፡
ሰዓት፡እንኳ፡አላመንኩህም።

፵፪፤ ልጄ፡ሆይ፡ ለሐዘኔ፡ሁሉ፡ጥንቱ፡
ሰሎሜ፡ናት፤እኔ፡ዳኛውን፡አየው፡ዘንድ፡
ከቤቴ፡አልወጣም፤በፈራጁም፡ፊት፡
አልቆምም።

፵፫፤ ሌባውን፡ራሱን፡ሲቆርጡት፡ሽፍታውንም፡
ይገድሉት፡ዘንድ፡ሲፈርዱበት፡አላየሁም።

፵፬፤ ከቶ፡ቀራንዮን፡አላየሁትም፤የጎልጎታንም፡
ቦታ፡አላውቅም፤ሁል፡ጊዜም፡በሚጣ
ሉበት፡ቦታ፡አልቆምኩም፤ልጄ፡ሆይ፡ክፉ፡
የሆነ፡ፍርድ፡አላየሁም፤በፍርድ፡አደባ
ባይም፡ከቶ፡ለዘላለሙ፡አልቆምኩም።

፵፭፤ ልጄ፡ሆይ፡ ያደረኩብህን፡ግፍ፡አላውቅም፡
እኔም፡በዮሐንስ፡ቤት፡ነበርኩ።

፵፮፤ ልጄ፡ወዳጄ፡ሆይ፡ በሊቀ፡ካህናቱ፡በሐና፡
ግቢ፡የተቀበልከው፡ግፍ፡ወሬው፡መራራ፡
ነው።

፵፯፤ ልጄ፡ወዳጄ፡ሆይ፡ ዛሬ፡ከእኔ፡ላይ፡ነጻነቴን፡
አስወገድክ፤

፵፰፤ ስለልደትህ፡በናዝሬት፡መልካም፡
የምስራች፡ነገሩኝ፤ዛሬ፡ግን፡በኢየሩሳሌም፡
ይህችን፡ክፉ፡መርዶ፡አረዱኝ።

፵፱፤ በዮሴፍ፡ቤት፡መልካም፡ዜና፡ደረሰኝ፤
በዮሐንስ፡ቤት፡ግን፡የሞት፡ዜና፡መጣልኝ።

፶፤ ልጄ፡ወዳጄ፡ሆይ፡ እኔ፡በልቤ፡ደስ፡እያለኝ፡
ተቀምጬ፡ነበር።

፶፩፤ በየዕለቱ፡ፋሲካ፡ደርሶአል፤በዓሉን፡
እናከብር፡ዘንድ፡ወደሀገራችንም፡እንመለ
ሳለን፡እያልኩ፡ነበር፤የዚህ፡ዓይነት፡
ፋሲካም፡ደረሰኝ።

Scanned by CamScanner

በ፲፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

፶፪ ኦ ፡ ፍቁርየ ፡ ወልድየ ፡ በብካይ ፡ ወሐዘን ፡ በዓልየ ፡ ተመይጠ ፡ ኀበ ፡ ላሕ ፤ ወፋሲካየ ፡ በሕማመ፡ልብ።

፶፫ ዘትትሂ፡ላሐ፡ኮነት፡ትገብር፡ድንግል፡በቤተ፡ ዮሐንስ ፡ ሶበ ፡ መጽአ ፡ ላዕሌሃ ፡ ዜና ፡ ሐዘን ፡ በእንተ፡ወልዳ።

፶፬ ወኮነት ፡ ተኀሥሥ ፡ አሐደ ፡ እምሐዋርያት ፡ ንጹሐን፡ከመ፡ይሕር፡ምስሌሃ፡ወኢረከበት፡ እስመ ፡ ኵሎሙ ፡ ጐዩ ፡ ወኀደግዎ ፡ እምፍ ርሃተ፡አይሁድ።

፶፭ ወሐተተት፡በእንተ፡ጴጥሮስ፡ከመ፡ይሑር፡ ምስሌሃ ፡ ወይቤልዋ ፡ ውእቱሰ ፡ ክህደ ፡ ወልደኪ ፡ ወይቤ ፡ ኢየአምሮ ፡ በእንተ ፡ ፍርሃተ፡ሊቃነ፡ካህናት፡ወሖረ፡ወተኀብአ።

፶፮ ወካዕበ ፡ ሐተተት ፡ በእንተ ፡ ያዕቆብ ፡ እኁሁ ፡ ለእግዚእነ ፡ ወነገርዋ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ጐየ ፡ ወኀደገ ፡ ልብሶ ፡ በደብር ፡ ዘአኀዝዎ።

፶፯ ወኀሠሠቶ፡ለእንድርያስ፤ወይቤልዋ፡እስመ፡ ውእቱሰ፡ኢመጽአ፡ምስሌሁ፡ውስተ፡ሀገር፤ ወከማሁ፡ቶማስኒ፡ጐየ፡ወሖረ።

፶፰ ወሐተተት ፡ በእንተ ፡ በርተሎሜዎስ ፡ ወነገርዋ፡ከመ፡ውእቱ፡ጐየ፡እምነ፡ኵሉ፡ አኀዊሁ።

፶፱ ወሐተተት ፡ በእንተ ፡ ፊልጶስ ፡ ወይቤልዋ ፡ እስመ፡ውእቱ፡ሶበ፡ርእየ፡ጸዳለ፡ፓናት፡ ወመሐትወ፡ጐየ፡ፈሪሆ።

፷ ወሐተተት ፡ በእንተ ፡ ያዕቆብ ፡ እኁሁ ፡ ለዮሐንስ፡ወነገርዋ፡ከመ፡ውእቱ፡ኢቆመ፡ አሐተ፡ጊዜ።

፷፩ ወሐተተት፡በእንተ፡ማቴዎስ፡ወይቤልዋ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ፈርሀ ፡ እምአይሁድ ፡ ወሊቃነ፡ ካህናት ፡ ፈድፋደ ፡ እምኵሎሙ ፤ ውእቶሙሰ ፡ ይጸልእዎ ፡ በእንተ ፡ ዘኮነ ፡ ይነሥእ ፡ እምኔሆሙ ፡ ጸባሕተ ፡ ወጐየ ፡ በጽልመተ፡ሌሊት።

፷፪ ወሐተተት፡በእንተ፡ኵሎሙ፡ወኢረከበት፡ አሐደ፡እምኔሆሙ፡ዘእንበለ፡ዮሐንስ፡ዘሖረ፡ ምስሌሁ፡ኀበ፡ቀራንዮ፡ወጎልጎታ።

፷፫ ወድንግልሰ፡ ተመይጠት፡ኀበ፡ላሓ፡ወብካያ፡ ዳግመ ፡ ምዕረ ፡ በእንተ ፡ ዘኢረከበት ፡ አሐደ

ዓርብ፡መዓልት፡በ፲፡ሰዓት።

፶፪ ልጄ ፡ ወዳጄ ፡ ሆይ ፡ በእንባና ፡ በሐዘን ፡ በዓሌ ፡ ወደ ፡ ልቅሶ ፡ ተመለሰ ፤ ፋሲካየም ፡ ወደልብ ፡ ሐዘን።

፶፫ በዮሐንስ፡ቤት፡ሳለች፡ስለ፡ልጅዋ፡የመከራ፡ ወሬ ፡ በመጣበት ፡ ጊዜ ፡ ድንግል ፡ እመቤ ታችን፡ ይኸንን፡ልቅሶ፡ታለቅስ፡ነበር።

፶፬ ከእርስዋ ፡ ጋራ ፡ ይሔድ ፡ ዘንድ ፡ ከንጹሐን ፡ ሐዋርያት ፡ አንድ ፡ ፈለገች ፤ አላገኘችም ፤ አይሁድን ፡ ከመፍራት ፡ የተነሳ ፡ ሁሉም ፡ ትተውት፡ሸሽተዋልና።

፶፭ ከእርስዋ፡ጋራ፡ይሔድ፡ዘንድ፡ስለ፡ጴጥሮስ፡ መረመረች ፤ እርሱማ ፡ የካህናት ፡ አለቆችን ፡ ከመፍራቱ ፡ የተነሳ ፡ ልጅሽን ፡ ክዶ ፡ አላው ቀውም፡አለ፤ሒዶም፡ተሸሽጓል፡አልዋት።

፶፮ ዳግመኛም ፡ ስለ ፡ ጌታችን ፡ ወንድም ፡ ስለ ፡ ያዕቆብ ፡ መረመረች ፤ ለያዙት ፡ ሰዎች ፡ በተራራ ፡ ላይ ፡ ልብሱን ፡ ትቶ ፡ እንደ ፡ ሸሸ ፡ ነገርዋት።

፶፯ እንድርያስንም ፡ ፈለገችው ፤ እርሱስ ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ አብሮት ፡ አልመጣም ፡ አልዋት ፤ እንደዚሁ፡ቶማስም፡ሸሽቶ፡ሔደ።

፶፰ ስለ ፡ በርተሎሜዎስም ፡ ጠየቀች ፤ እርሱም ፡ ከወንድሞቹ ፡ አስቀድሞ ፡ እንደሸሸ ፡ ነገርዋት።

፶፱ ስለ ፡ ፊልጶስም ፡ ጠየቀች ፤ እርሱም ፡ የፋና ዎችን ፡ ውጋገንና ፡ መብራቶችን ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ፈርቶ፡እንደሸሸ፡ነገርዋት።

፷ ስለ ፡ ዮሐንስ ፡ ወንድም ፡ ስለ ፡ ያዕቆብ ፡ መረመረች፤አንድ፡ጊዜ፡ስንኳ፡እንዳልቆመ፡ ነገርዋት።

፷፩ ስለ ፡ ማቴዎስም ፡ መረመረች ፤ እርሱም ፡ ግብር፡ ስለሚቀበላቸው ፡ አይሁድንና ፡ የካህናት ፡ አለቆችን ፡ እጅግ ፡ ስለፈራ ፤ እነርሱም፡ስለሚጠሉት፡በሌሊት፡ጨለማ፡ እንደሸሸ፡ነገርዋት።

፷፪ ስለ ፡ ሁሉም ፡ መረመረች ፤ አብሮ ፡ ወደ ፡ ቀራንዮና፡ወደጎልጎታ፡ከሔደው፡ከዮሐንስ፡ በቀር፡አንድም፡አላገኘችም።

፷፫ ድንግልም ፡ ከልጅዋ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቶች ፡ ከዮሐንስ፡በቀር፡አንድ፡እንኳ፡ባለማግኘቷ፡

Scanned by CamScanner

በ፲፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

እምአርድእት ፡ ወልዳ ፡ ዘእንበለ ፡ ዮሐንስ።

፳፬፤ ወበከየት፡እንዘ፡ትብል፡አሌ፡ሊተ፡ወልድየ፡ ፍቁር፡እስመ፡አኀዊከ፡ጐዩ፡ወተኀብኡ፡ ወኀደጉከ።

፳፭፤ ወኮንኩ፡እትሔዘበከ፡ኵሎ፡ዕለተ፡አ፡አቡየ፡ ጴጥሮስ፡ከመ፡ኢትክሐድ፡እግዚእከ፡ወኢ ወሀብከ ፡ በእንቲአሁ ፡ ወርቀ ፡ ወብሩረ ። ለምንት፡ክሀድኮ፡ለእግዚእከ፡ፍጡነ።

፳፮፤ ወኢወሀበከ፡ሐመረ፡ወኢኀዳፌ፡ለምንት፡ ክሀድኮ፡ለመምሀርከ፡ወእግዚእከ፡ዮም፡ወኢ ወሀበከ ፡ ምንተ ፡ ሀየንቴሁ ፡ ወልደ ፡ ወኢወለተ።

፳፯፤ ለምንት ፡ ክሀድኮ ፡ ለወልድየ ፡ አ ፡ ጴጥሮስ፡ወኢ፡ወሀብከ፡በእንቲአሁ፡እኀወ፡ ወዐርከ።

፳፰፤ ለምንት፡ኮነ፡ልብከ፡ቀሊለ፡በዝንቱ፡ኵሉ፤ ኢርኢከ፡አ፡ጴጥሮስ፡ዳግመ፡መስቀለ፡ከመ፡ ትብል ፡ ውእቱ ፡ ሊተ ፡ እስከ ፡ ፈራህከ ፡ ወክህድከ፡ፍጡነ፤ወወሀበከ፡ልሳነ፡ዘከመ፡ ኀጺን፡በሊህ።

፳፱፤ ወአንተሰ ፡ አ ፡ ጴጥሮስ ፡ አምሐውኮ ፡ ወመሰውኮ፡ዘእንበለ፡እሳት፡ወኢ፡ነሃቢ።

፴፤ ወወሀበ ፡ ጸጋ ፡ ለገጽከ ፡ አ ፡ ጴጥሮስ ፡ ፈድፋደ ፡ እምኵሉ ፡ ሰብእ ፡ ኢተዐገሥከ ፡ ይእዜ ፡ ከመ ፡ ትጹር ፡ አሐደ ፡ ጽፍዐተ ፡ በእንተ፡እግዚእከ፡ዘወሀበከ፡አዕይንተ፡ዘኢ ይማስን፡ብርሃናተ።

፴፩፤ አ ፡ ጴጥሮስ ፡ ኢፈራህከ ፡ ሶበ ፡ ክህድኮ ፡ ለወልድየ፡ዘወሀበከ፡መራኁተ፡መንግሥተ፡ ሰማያት ፡ ወኢተዐገሥከ ፡ ውስተ ፡ ዐውደ ፡ ሊቀ፡ካህናት ። ሜመከ፡ ምእመነ ፡ ወኖላዌ ፡ ለኵሉ፡ዓለም፡ህየንቴሁ።

፴፪፤ አ ፡ ጴጥሮስ ፡ ኢጾርከ ፡ መከራ ፡ ንስቲተ ፡ አሐተ፡ጊዜ፡በእንተ፡እግዚእከ።

፴፫፤ ረሰየከ ፡ አ ፡ ጴጥሮስ ፡ ከመ ፡ ትኩን ፡ አበ ፡ ለኵሉ፡ዓለም፡ወአንተሂ፡ኢገበርከ፡ፍቅረ፡ አኃው፡ለወልድየ፡አሐተ፡ጊዜ።

፴፬፤ አንበረ፡እዴሁ፡እምላካዊት፡ዲበ፡ርእስከ፡ አ፡ጴጥሮስ፡ኢፈቀድከ፡ይእዜ፡ያንብሩ፡ዲበ፡

ዓርብ፡መዓልት፡በ፲፡ሰዓት።

እንደገና፡ዳግም፡ወደ፡ጽኑ፡ልቅሶና፡ሐዘን፡ ተመለሰች።

፳፬፤ እንዲህ፡እያለችም፡አለቀሰች፤ልጄ፡ወዳጄ፡ ሆይ ፡ ወዮልኝ ፡ ወንድሞችህ ፡ ሸሹ ፡ ትተውህም፡ተሸሸጉ።

፳፭፤ አባቴ፡ጴጥሮስ፡ሆይ፡ጌታህን፡እንዳትክድ፡ ሁልቀን፡እጠራጠርህ፡ነበር፤ስለ፡እርሱ፡ ወርቅ ፡ ብር ፡ አልሰጠህ ፡ ለምን ፡ ጌታህን፡ ፈጥነህ፡ካድከው።

፳፮፤ ስለርሱ ፡ መርከብ ፡ ወይም ፡ ቀዛፊ ፡ አልሰ ጠህም፤መምህርህንና፡ጌታህን፡ዛሬ፡ለምን፡ ካድከው ፡ ስለርሱ ፡ ምንም ፡ አልሰጠህም፡ ወንድ፡ልጅም፡ቢሆን፡ወይም፡ሴት፡ልጅ።

፳፯፤ ጴጥሮስ ፡ ሆይ ፡ ስለ ፡ እርሱ ፡ ወንድምን፡ ወይም፡ ወዳጅን ፡ አልሰጠህም ፡ ልጄን፡ ለምን፡ካድከው።

፳፰፤ በዚህ ፡ ሁሉ ፡ ልብህ ፡ ለምን ፡ ቀላል ፡ ሆነ፤ ጴጥሮስ፡ሆይ፡እስከ፡ፈራህና፡ፈጥነህ፡እስከ፡ ካድክ ፡ ድረስ ፡ ለእኔ ፡ ነው ፡ ትል ፡ ዘንድ፡ በድጋሚ ፡ ሌላ ፡ መስቀል ፡ አላየህ፤እንደ፡ ብረትም፡የተሳለ፡አንደበት፡ሰጥቶህ፡ነበር።

፳፱፤ ጴጥሮስ፡ሆይ፡አንተስ፡ያለ፡እሳትና፡ያለአን ጥረኛም፡ፈጽመህ፡አቀለጥከው።

፴፤ ጴጥሮስ፡ሆይ፡ከሰው፡ሁሉ፡ለገጽህ፡ግርማ፡ ሰጥቶህ ፡ ነበር ፤ ብርሃናቸው ፡ የማይጠፋ፡ ዓይኖችን ፡ የሰጠህ ፡ ሲሆን ፡ ስለጌታህ፡ አንዲት፡ጥፊ፡ትቀበል፡ዘንድ፡ዛሬ፡አልታገ ሥከም።

፴፩፤ ጴጥሮስ ፡ ሆይ ፡ የመንግሥተ ፡ ሰማያትን፡ መክፈቻ፡የሰጠህን፡ልጄን፡በካድከው፡ጊዜ፡ አልፈራህም፤በሊቀ፡ካህናቱም፡ግቢ፡አልታ ገሥከም፤በእርሱ፡ፈንታም፡ለዓለሙ፡ሁሉ፡ የታመነ፡ጠባቂ፡አድርጎ፡ሾመህ።

፴፪፤ ጴጥሮስ ፡ ሆይ ፡ ስለ ፡ ጌታህ ፡ አንድ ፡ ጊዜ፡ እንኳ፡ጥቂት፡መከራ፡አልተቀበልክም።

፴፫፤ ጴጥሮስ፡ሆይ፡ለዓለሙ፡ሁሉ፡አባት፡ትሆን፡ ዘንድ፡ሾመህ፤አንተ፡ግን፡ለልጄ፡የወንድማ ማችነት፡ፍቅርን፡አላደረግህም።

፴፬፤ ጴጥሮስ፡ሆይ፡አምላካዊ፡እጁን፡በራስህ፡ ላይ፡ጫነ፤አንተ፡ግን፡ከመካድህ፡በፊት፡ዛሬ

በ፲፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

ርእስከ፡አክሊለ፡ሦከ፡እምቅድመ፡ትክሐዶ፡
ለወልድየ።
፸፭ ኃሊ ፡ አ ፡ ጴጥሮስ ፡ ከመ ፡ ወልድየ ፡
ኢኮነ ፡ እግዚእከ ፡ አላ ፡ ዐርክከ ። ኢኮነ ፡
ድልወ ፡ ለከ፡ ከመ ፡ ትክሀዶ ፡ ለወልድየ ፡
ከመዝ።
፸፮ ወለእመ ፡ ኮንከ ፡ አ ፡ ጴጥሮስ ፡ ከመ ፡ አቡየ ፡
ዮሴፍ ፡ ዘረከቦ ፡ ዝንቱ ፡ ኵሉ ፡ ድካም ፡
ምስሌነ።
፸፯ ወለእመ፡ሰሐቡከ፡ከማሁ፡ኀበ፡ሄሮድስ፡አ፡
ጴጥሮስ፡ወለእመ፡ኮንከ፡ተወካፌ፡ድካም፡
ምስሌነ፡በምድረ፡ግብጽ፡እንጋ፡እምኢክ
ሀልከ፡ትዕግሥተ፡ከማሁ።
፸፰ ጠለ፡ሰማይ፡ይረድ፡ዲበ፡አዕፅምቲከ፡አ፡
አቡየ፡ዮሴፍ፡ጻድቅ።
፸፱ ወዕፀ፡ሕይወት፡ትሴሰይ፡ነፍስከ።እስመ፡
ተዐገሥከ፡ምስሌነ፡ውስተ፡ምንዳቤ፡ወኢክ
ሀድኮ፡ለወልድየ፡ከመ፡ጴጥሮስ።
፹ አ፡ጴጥሮስ፡ኢወሰዱከ፡ኀበ፡ምኵናን፡ወኢ
አቀሙከ፡በቅድመ፡ሥልጣናት፡ወክሀድኮ፡
ፍጡነ፡ለእግዚእከ።
፹፩ ወሶበ፡ከመዝ፡ትበኪ፡ድንግል፡ብካየ፡
በቤተ፡ዮሐንስ፡ወመጽአ፡ዮሐንስ፡እንዘ፡
ይበኪ፡ወረከባ፡እንዘ፡ትበኪ።
፹፪ ወነበሩ፡እንከ፡ክልኤሆሙ፡እንዘ፡ይበክዩ፡
በበይናቲሆሙ፡ድንግል፡ወዮሐንስ፡ላዕለ፡
እግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ።
፹፫ ወይቤላ፡ዮሐንስ፡ለድንግል፡አ፡እምየ፡
ኢትብክዩ፡በእንተ፡ዘክህዶ፡ጴጥሮስ፡ለእግ
ዚእነ፡አልቦ፡ነውር፡ላዕሌሁ፡ከመ፡ይሁዳ፡
ዘአግብኦ።
፹፬ እስመ ፡ ሰማዕክዎ ፡ ለመምህርየ ፡ በጊዜ ፡
ድራር፡እንዘ፡ይብሎ፡አ፡ጴጥሮስ፡ሠልሰ፡
ትክህደኒ።
፹፭ ወይቤሎ ፡ ጴጥሮስ ፡ ሐሰ ፡ ለከ ፡
እግዚኦ፡ይኩን፡ለከ፡ከመዝ፡እግዚእየ፡
ወአምላኪየ ፡ ኢይከህደከ ፡ እስከ ፡ ለዓ
ለም ፡ አላ ፡ ይኄይሰኒ ፡ ከመ ፡ እሙት ፡
ወኢይኩን ፡ ሊተ ፡ ከመዝ ፡ አላ፡ እሜጡ ፡
ነፍስየ፡በእንቲአከ።
፹፮ ወሰማዕክዎ ፡ ቀዳሚ ፡ ለመምህርነ ፡ እንዘ ፡
ይጌሥፆ ፡ ለመምህርየ ፡ ጴጥሮስ ፡ ሠለስተ ፡
ጊዜ።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፲፡ሰዓት።

በራስህ ፡ ላይ ፡ የእሾህ ፡ አክሊል ፡ ይጭኑብህ ፡
ዘንድ፡አልፈቀድክም።
፸፭ ጴጥሮስ ፡ ሆይ ፡ ልጄ ፡ ለአንተ ፡ ወዳጅህ ፡
እንጅ፡ እንደ ፡ ጌታህ ፡ እንዳልሆነ ፡ አስብ ፤
ልጄን፡እንደዚህ፡ትክደው፡ዘንድ፡ለአንተ፡
አግባብ፡አይደለም።
፸፮ ጴጥሮስ ፡ ሆይ ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡
ድካም፡ እንዳገኘው ፡ እንደ ፡ አባቴ ፡ ዮሴፍ ፡
ብትሆን፡ኖሮ።
፸፯ ጴጥሮስ፡ሆይ፡እንደ፡እርሱ፡ወደ፡ኄሮድስ፡
ቢጎትቱህ፡በግብጽ፡ምድርም፡ከእኛ፡ጋራ፡
መከራ ፡ ተቀባይ ፡ ብትሆን ፡ እንደ ፡ እርሱ ፡
መታገሥ፡ባልቻልክም፡ነበር፡እንጃ።
፸፰ አባቴ ፡ ጻድቁ ፡ ዮሴፍ ፡ ሆይ ፡ በአጥንቶችህ ፡
ላይ፡የሰማይ፡ጠል፡ይውረድ።
፸፱ ነፍስህም፡ዕፀ፡ሕይወትን፡ትመገብ፤ከእኛ፡
ጋራ ፡ ታግሠህ ፡ መከራ ፡ ስትቀበል ፡ እንደ ፡
ጴጥሮስ፡ልጄን፡አልካድከውምና።
፹ ጴጥሮስ፡ሆይ፡ወደ፡ፍርድ፡አደባባይ፡አልወ
ሰዱህ ፡ በባለ ፡ ሥልጣኖችም ፡ ፊት ፡
አላቆሙህ፡ፈጥነህ፡ጌታህን፡ካድከው።
፹፩ ድንግል ፡ በዮሐንስ ፡ ቤት ፡ እንደዚህ ፡
ስታለቅስ ፡ ሳለ ፡ ዮሐንስ ፡ እያለቀሰ ፡ መጣ ፡
እርሷንም፡እያለቀሰች፡አገኛት።
፹፪ ድንግል ፡ እመቤታችንና ፡ ዮሐንስም ፡ ስለ ፡
ጌታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡እርስ፡በርሳቸው፡
እየተላቀሱ፡ሁለቱም፡አብረው፡ነበሩ።
፹፫ ዮሐንስም ፡ ድንግልን ፡ እናቴ ፡ ሆይ ፡
ጌታችንን፡ ጴጥሮስ፡ስለካደው፡አታልቅሺ፡
አላት፤አሳልፎ፡እንደ፡ሰጠው፡እንደ፡ይሁዳ፡
ነውር፡የለበትምና።
፹፬ በአራት፡ጊዜ፡ጴጥሮስ፡ሆይ፡ሦስት፡ጊዜ፡
ትክደኛለህ ፡ ሲለው ፡ መምህሬን ፡ ሰምቻ
ለሁና።
፹፭ ጴጥሮስም፡እንደዚህ፡በአንተ፡ላይ፡ይደረግ፡
ዘንድ፡አይገባም፤ጌታዬ፡ፈጣሪዬም፡እስከ፡
ዘላለሙ ፡ ድረስ ፡ አልክድህም ፤ መሞት ፡
ይሻለኛል ፤ እንደዚህም ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡
አይሆንም፤ስለ፡አንተ፡ነፍሴን፡አሳልፌ፡
እሰጣለሁ፡እንጂ።
፹፮ ከዚህ ፡ ቀደምም ፡ መምህራችን ፡ ጌታ ፡
መምህሬ ፡ ጴጥሮስን ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡
ሲገሥፀው፡ሰምቻለሁ።

## በ፫፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

፹፯፤ ወይቤሎ፡ሑር፡እምድኅሬየ፡ሰይጣን፡ኮንከ፡
ሊተ፡ዕቅፍትየ፡እስመ፡አንተ፡ኢትኄሊ፡
ዘእግዚአብሔር፡አላ፡ዘሰብእ።
ዘእግዚአብሔር፡አ፡እግዝእትየ፡ወእምየ፡
፹፰፤ ወይእዜኒ፡አ፡እግዝእትየ፡ወእምየ፡
ኢትብክዪ፡በእንተ፡አቡየ፡ጴጥሮስ፡እስመ፡
ክህደቱ፡ይከውን፡ንስሐ፡ለኵሎሙ፡
ኃጥአን፤ እስመ፡ውእቱ፡ሐሰወ፡ቃሎ፡
ዘአምነ፡በቃለ፡እግዚእ።
በረከተ፡ሐዘና፡ወጻጋ፡ማየ፡አንብዕ፡
ዘውኅዘ፡ እምዐይና፡የሀሉ፡ምስሌነ፡
ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

### ምንተኑ፡በል።

ተአምሪሃ፡ለእግዝእትነ፡ቅድስት፡ድንግል፡
በክልኤ፡ማርያም፡ወላዲተ፡አምላክ፡ጸሎታ፡
ወበረከታ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡
አሜን።

፩፤ ወሀሎ፡አሐዱ፡ንጉሥ፡ዘስሙ፡ጢባርዮስ፡
ዘሮሜ፡ዘበመዋዕሊሁ፡ተሰቅለ፡እግዚእነ፡
ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡እንዘ፡ኢየአምር፡
ጢባርዮስ።
፪፤ ወሶበ፡ሰምዐ፡ከመ፡ሰቀልዎ፡አይሁድ፡በኢየ
ሩሳሌም፡ለእግዚእነ፡በመባሕተ፡ጲላጦስ፡
ዘሤሞ፡ጢባርዮስ፡መስፍነ፡ለኢየሩሳሌም።
፫፤ ወኮነኖ፡ዐቢየ፡ኵነኔ፡በእንተ፡ዘአብሐሙ፡
ለአይሁድ፡ይስቅልዎ፡ለእግዚእነ።

፬፤ ወአዘዘ፡ከመ፡ይምትሩ፡ርእሶ፡ወገብሩ፡
ከማሁ፡ላዕሌሁ፤እስመ፡ዐቢየ፡ሐዘነ፡አኅዘ፡
ይሕዝን፡ጢባርዮስ፡በእንተ፡ሞቱ፡ለእግ
ዚእነ።
፭፤ ወኮነ፡ሶበ፡ሞተ፡ወልዱ፡ለጢባርዮስ፡ውዕየ፡
ልቡ፡በሞተ፡ወልዱ።
፮፤ ወእምዝ፡ተዘከረ፡ንጉሥ፡መንክራተ፡ዘእግ
ዚእነ፡ዘከመ፡አንሥአ፡ሙታነ፡ወካልአተሂ፡
ተአምራተ፡ዘገብረ፡ተማከረ፡ንጉሥ፡ምስለ፡
ብእሲቱ፡ከመ፡ይፈንውዎ፡ለወልዶሙ፡
ምውት፡እምአመ፡ሞተ፡በሠለስቱ፡አውራኅ፡
ኀበ፡መቃብረ፡እግዚእነ፡ከመ፡ያንሥአ፡በመ
ቃብሪሁ።

## ዓርብ፡መዓልት፡በ፫፡ሰዓት።

፹፯፤ ሰይጣን፡ባላጋራዬ፡ወግድ፡ከኋላዬ፤ዕንቅፋት፡
ሁነህብኛልና፡ሰው፡ሰውኛውን፡እንጂ፡የእግ
ዚአብሔርን፡አታስብምና፡አለው።
፹፰፤ አሁንም፡እመቤቴ፡እናቴ፡ሆይ፡ስለ፡አባቴ፡
ጴጥሮስ፡መካድ፡አታልቅሺ፤ለኃጢአ
ተኞች፡ሁሉ፡ለንስሐ፡ምሳሌ፡ነውና፤
በቃሉ፡ያመነውን፡የጌታችንን፡ቃል፡አስተ
ባብሎ፡ነበርና።
በሐዘኗ፡የሚገኝ፡በረከት፡ከዐይንዋ፡
የፈሰሰ፡የዕንባ፡ውኃ፡ጸጋ፡ለዘላለሙ፡ከእኛ፡
ጋራ፡ይኑር፡አሜን።

### ምንተኑ፡በል።

ልመናዋ፡ክብርዋ፡ለዘላለሙ፡በእኛ፡ላይ፡
በእውነት፡ይደርብንና፡በሁለት፡ወገን፡
ድንግል፡የምትሆን፡አምላክን፡የወለደች፡
ቅድስት፡ድንግል፡እመቤታችን፡ማርያም፡
ያደረገችው፡ተአምር፡ይህ፡ነው።
፩፤ እርሱ፡ሳያውቅ፡ጌታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡
በተሰቀለበት፡ዘመን፡የነበረ፡ስሙ፡
ጢባርዮስ፡የሚባል፡አንድ፡የሮሜ፡ንጉሥ፡
ነበረ።
፪፤ ለኢየሩሳሌም፡መስፍን፡አድርጎ፡በሾመው፡
በጲላጦስ፡መብት፡ጌታችንን፡አይሁድ፡
እንደ፡ሰቀሉት፡በሰማ፡ጊዜ።
፫፤ ጌታችንን፡ይሰቅሉት፡ዘንድ፡አይሁድን፡ስለ
አሠለጠናቸው፡ጲላጦስን፡ታላቅ፡ቅጣት፡
ቀጣው።
፬፤ ራሱንም፡ይቆርጡት፡ዘንድ፡አዘዘ፤
እንዲሁም፡አደረጉበት፤ስለ፡ጌታችን፡
ሞትም፡ጢባርዮስ፡ታላቅ፡ሐዘን፡ያዝን፡
ጀመረ።
፭፤ ጢባርዮስ፡ልጁ፡በሞተ፡ጊዜ፡በልጁ፡ሞት፡
ልቡ፡በሐዘን፡ተቃጠለ።
፮፤ ከዚህ፡በኋላም፡የጌታችንን፡ድንቆች፡ተአም
ራቶችን፡አሰበ፤ሙታኖችን፡እንዳሥነሳ፡ያደ
ረጋቸውን፡ሌሎች፡ተአምራቶችን፡አስቦ፡
ከሞተ፡ሦስት፡ወር፡የሆነውን፡ልጃቸውን፡
በመቃብሩ፡ሊያነሣላቸው፡ወደ ጌታችን፡
መቃብር፡ይልኩት፡ዘንድ፡ንጉሡ፡ከሚስቱ፡
ጋራ፡ተማከረ።

Scanned by CamScanner

በ፫፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

፯ ነሥአ፡ክርታሰ፡ንጉሥ፡ወጸሐፈ፡ከመዝ፡
እንዘ፡ይብል፡እምጢባርዮስ፡ንጉሠ፡ምድር፡
ትብጻሕ፡ኀበ፡ንጉሠ፡ሰማያት።
ወእሰግድ፡ለከ፡ኦ፡እግዚእየ፡ኢየሱስ፡
፰ ክርስቶስ፡ንጉሠ፡ነገሥት፡እስመ፡ሰማዕኩ፡
ሰምዐ፡እምብእሲ፡ዘስሙ፡ጲላጦስ፡ዘከመ፡
አንሣእከ፡ሙታነ፡ወአመንኩ፡ብከ፤
ወረከብኩ፡ካዕበ፡ስምዐ፡በእንቲአከ፡
ዘጽሑፍ፡ከመ፡አንሣእኮ፡ለአልዓዛር፡
እመቃብር፡እምድኅረ፡ረቡዕ፡መዋዕል።
፱ ወናሁ፡መቃብሪከኒ፡ዮም፡ይገብር፡
ተአምራተ፡ወያነሥእ፡ሙታነ፡በእንተ፡
ዘነደረ፡ውስቴቱ፡ሥጋከ፡ቅዱስ።
፲ ወበእንተዝ፡አነ፡አመንኩ፡ብከ፡ከመ፡አንተ፡
ወልደ፡እግዚአብሔር፡ሕያው፡ወከመ፡
አንተ፡ውስተ፡ሰማያት፡ከማሁ፡ውስተ፡
ምድርኒ።
፲፩ ኦ፡እግዚእየ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ተመጠውእ፡
ስእለተ፡ገብርከ፡ጢባርዮስ፡በምሕረትከ።
፲፪ ወሶበ፡ጸሐፈ፡ንጉሥ፡ጢባርዮስ፡መልእክቶ፡
ፈነወ፡ኀበ፡ጥብርንዮስ፡ኢየሩሳሌም፡ምስለ፡
ወልዱ፡ዘሞተ፡ወአብዕዎ፡ውስተ፡
መቃብሪሁ፡ለእግዚእነ፡ምስለ፡አስከሬኑ፡
ወዐጸውዎ፡በእብን፡ወነበረ፡ህየ፡አርባዕተ፡
ዕለተ።
፲፫ ወእምድኅረ፡አርባዕቱ፡ዕለት፡ተንሥአ፡ወአ
ንኰራኰራ፡ለእብን፡ወነበረ፡ዲቤሃ፤
ወተፈሥሐ፡ኀጽዋኒሁ፡ወአግብርቲሁ፡
በሕይወተ፡እግዚአሙ።
፲፬ ወእምዝ፡ተመይጠ፡ወልደ፡ንጉሥ፡ኀበ፡
አቡሁ፡ወእሙ፡ሀገረ፡ሮሜ።
፲፭ ወከነ፡ፍሥሓ፡ዐቢይ፡ወሰብሕዎ፡ለእግዚአ
ብሔር፡ኵሎሙ፡እለ፡ርእይዎ፡ለወልደ፡
ንጉሥ፡ዘተንሥአ፡እሙታን።
፲፮ ወእምድኅረ፡ኅዳጥ፡ዕለት፡ተናገረት፡
ንግሥት፡ብእሲተ፡ጢባርዮስ፡እንዘ፡ትብል፡
ምስሌሁ፡ለጢባርዮስ፡ኦ፡እግዚእየ፡ንጉሥ፡
አንተ፡ተአምር፡ከመ፡አልቦ፡ዘገብረ፡ሠናየ፡
ዘየዐቢ፡እምዘገብረ፡ምስሌነ፡እግዚእነ፡
ኢየሱስ፡ክርስቶስ።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፫፡ሰዓት።

፯፤ ክርታስ፡(ወረቀት)፡ወስዶ፡እንዲህ፡ብሎ፡
ጻፈ፤ ከምድር፡ንጉሥ፡ከጢባርዮስ፡ወደ፡
ሰማያት፡ንጉሥ፡ትድረስ።
፰፤ የነገሥታት፡ንጉሥ፡ጌታዬ፡ኢየሱስ፡
ክርስቶስ፡ሆይ፡እሰግድልሃለሁ፤ ጲላጦስ፡
ከሚባል፡ሰው፡ሙታንን፡እንዳነሣህ፡ምስክ
ርነቱን፡ሰምቻለሁና፡እምኜብሃለሁ፤
ዳግመኛም፡ከአራት፡ቀን፡በኋላ፡አልዓዛርን፡
ከመቃብር፡እንዳነሣኸው፡ስለ፡አንተ፡
የተጻፈ፡ምስክር፡አግኝቻለሁና።
፱፤ እነሆ፡ዛሬም፡ቢሆን፡ተአምራትን፡በማድረግ፡
መቃብርህ፡የከበረ፡ሥጋህ፡ስለአደረበት፡
ሙታንን፡ያነሣል፡ማለትን፡ሰምቻለሁና።
፲፤ ስለዚህ፡አንተ፡የሕያው፡እግዚአብሔር፡
ልጅ፡እንደ፡ሆንክ፡እኔ፡አመንኩብህ፤
አንተም፡በሰማይ፡እንዲሁም፡በምድር፡
እንዳለህ፡አመንኩብህ።
፲፩፤ ጌታዬ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ሆይ፡በቸርነትህ፡
የባርያህ፡የጢባርዮስን፡ልመና፡ተቀበል።
፲፪፤ ንጉሥ፡ጢባርዮስም፡በጻፈ፡ጊዜ፡ወደ፡ጥብር
ንዮስ፡ወደ፡ኢየሩሳሌም፡ከልጁ፡በድን፡ጋራ፡
መልእክቱን፡ላከ፤ ከቃሬዛውም፡ጋራ፡ከጌታ፡
መቃብር፡ውስጥ፡መልእክቱን፡አስገብተው፡
በደንጊያ፡ገጠሙት፤ በዚያም፡አራት፡ቀን፡
ተቀመጠ።
፲፫፤ ከአራት፡ቀንም፡በኋላ፡ተነሣ፤ ደንጊያይ
ቱንም፡ገልብጦ፡በላይዋ፡ተቀመጠ፤ በጌታ
ቸውም፡መዳን፡ጃንደረቦቹና፡አገልጋዮቹ፡
ደስ፡አላቸው።
፲፬፤ ከዚህም፡በኋላ፡የንጉሥ፡ልጅ፡እናትና፡
አባቱ፡ወደአሉበት፡ወደ፡ሮሜ፡ከተማ፡
ተመለሰ።
፲፭፤ ታላቅ፡ደስታም፡ሆነ፤ ከሞት፡የተነሣውን፡
የንጉሡን፡ልጅ፡ያዩ፡ሁሉ፡እግዚአብሔርን፡
አመሰገኑት።
፲፮፤ ከብዙ፡ቀንም፡በኋላ፡የንጉሥ፡ጢባርዮስ፡
ሚስት፡ንግሥቲቱ፡ከጢባርዮስ፡ጋር፡ተነጋ
ገረች፤ ጌታዬ፡ንጉሥ፡ሆይ፡ጌታችን፡
ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ለእኛ፡ካደረገው፡
መልካም፡ሥራ፡የሚበልጥ፡እንደሌለ፡አንተ፡
ታውቃለህ፡አለችው።

በ፫፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

፲፯፡ ወእምድኅረ፡ ተንሥአ፡ እሙታን፡ እንሥእ፡ ለነ፡ለወልድነ፡እሙታን።

፲፰፡ ወእመሰ፡ ነገረ፡ አመትከ፡ ይኤድመከ፡ እ፡ እግዚእየ፡ ንጉሥ፡ ለእከ፡ ኢየሩሳሌም፡ ከመ፡ ያምጽእዋ፡ለእግዝእትነ፡ማርያም፡ወላዲተ፡ ክርስቶስ፡ እስመ፡ ዜነዉነ፡ ከመ፡ ሕያውት፡ ይእቲ፡ወሀለወት፡በሀገረ፡ይሁዳ።

፲፱፡ አዘዘ፡ ከመ፡ ያምጽእዋ፡ ዝየ፡ ኀቤነ፡ ከመ፡ ትግበር፡ ላዕሌሃ፡ አከሊለ፡ መንግሥት፡ ወይኩን፡ንብረታ፡ዝየ፡ውስተ፡ሀገርነ።

፳፡ ወንሰግድ፡ላቲ፡ ኵልነ፡ ከመ፡ እኩን፡ አነ፡ ላቲ፡ አመተ፡ ወአንተኒ፡ ገብረ፡ ከመ፡ ኢይግበሩ፡ አይሁድ፡ እኩያን፡ ላዕሌሃ፡ ዘገብሩ፡ላዕለ፡ወልዳ።

፳፩፡ ወሶበ፡ ትቤ፡ ንግሥት፡ ከመዝ፡ ተፈሥሐ፡ ልበ፡ንጉሥ፡ በነገራ፡ ወለአከ፡ ኢየሩሳሌም፡ ሠራዊተ፡ ወሐራ፡ ወአዋልደ፡ ብዙኃተ፡ ወኀጽዋነ፡ እስመ፡ መሰሎሙ፡ ድንግል፡ ዘታፈቅር፡መንግሥተዝ፡ዓለም።

፳፪፡ ወመድኃኒነሰ፡ አስተርአዮሙ፡ ለአርዳኢሁ፡ ሐዋርያት፡ንጹሐን፡ወለእሙ፡ድንግል፡ወአ ለበዎሙ፡ ምሥጢረ፡ ብዙኀ፡ ወዜነዎሙ፡ በእንተ፡ ቃለ፡ ንጉሥ፡ ዘከመ፡ ይፈቅድ፡ ይንሥአ፡ለእሙ።

፳፫፡ ወአዘዘ፡ለዮሐንስ፡ይሑር፡ኀበ፡ንጉሥ፡ወመ ድኃኒነ፡ ተመይጠ፡ ኀበ፡ እሙ፡ ድንግል፡ ወይቤላ፡ እ፡ ወላዲትየ፡ ተንሥኢ፡ ቁሚ፡ ከመ፡እንሣእኪ፡ኀበ፡ዕረፍት፡ሰማያዊ፡ከመ፡ ትርአዪ፡ ዘመንክር፡ ውዳሴ፡ ዚአየ፡ ዘይት ሌዓል፡እመንግሥተ፡ኵሉ፡ዓለም።

፳፬፡ ደከምኪ፡ ምስሌየ፡ እ፡ እምየ፡ ወጾርክኒ፡ እመካን፡ ውስተ፡ መካን፡ ንዒ፡ ከመ፡ ታንሶስዊ፡ውስተ፡መንግሥትየ፡ዘበአማን፡ ዘላዕሉ፡ኢየሩሳሌም።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፫፡ሰዓት።

፲፯፡ ከሙታን ፡ ተለይቶ ፡ ከተነሣ ፡ በኋላም ፡ ልጃችንን፡እስነሣልን።

፲፰፡ ንጉሥ፡ሆይ፡የእኔ፡የአገልጋይህን፡ቃል፡ደስ ብሎህ ፡ የምትቀበለው ፡ ከሆነ ፤ ክርስቶስን፡ የወለደች፡እመቤታችን፡ማርያም፡በይሁዳ፡ ሀገር ፡ በሕይወት ፡ እንዳለች፡ ነግረውናልና፡ ያመጡዋት፡ዘንድ፡ወደ፡ኢየሩሳሌም፡ላክ።

፲፱፡ መኖሪያዋ፡በዚህ፡በሀገራችን፡ውስጥ፡ይሆን፡ ዘንድ፤የመንግሥትንም፡ዘውድ፡ታቀዳጃት፡ ዘንድ፤ወደ፡እኛ፡እንዲያመጡአት፡እዘዝ።

፳፡ ከፉዎች ፡ አይሁድ ፡ በልጅዋ ፡ ላይ ፡ እንዳ ደረጉ፡ እንዳያደርጉባት ፡ እኔ ፡ ገረድ ፡ ደንገጡር፡አንተ፡ቋሚ፡ለጓሚ፡ሆነን፡እናገለ ግላታለን፤እንሰግድላታለን።

፳፩፡ ንግሥቲቱ፡እንዲህ፡በአለች፡ጊዜ፡በነገርዋ፡ የንጉሡ፡ልብ፡ደስ፡ተሰኘ፤ሠራዊትን፡ወታ ደሮችን፡ብዙዎች፡ሴቶች፡ልጆችን፡ጃንደረ ቦችን፡ወደ፡ኢየሩሳሌም፡ላከ፤ድንግል፡እመ ቤታችን ፡ የዚህን ፡ ዓለም ፡ መንግሥት፡ የምትሻ፡መስሎአቸው፡ነበርና።

፳፪፡ መድኃኒታችን ፡ ግን ፡ ለደቀ ፡ መዛሙርቱ፡ ለንጹሐን ፡ ሐዋርያትና ፡ ለድንግል ፡ እናቱ፡ ተገለጸላቸው ፤ ብዙ ፡ ምሥጢርንም ፡ አስረ ዳቸው ፤ እናቱንም ፡ ይወስዳት ፡ ዘንድ፡ እንደሚሻ፡ስለ፡ንጉሡ፡የመልእክት፡ቃል፡ ነገራቸው።

፳፫፡ ወደ ፡ ንጉሡም ፡ ይሄድ ፡ ዘንድ ፡ ዮሐንስን፡ አዘዘው ፤ ወደ ፡ ድንግል ፡ እናቱም ፡ መለስ፡ ብሎ ፡ ከዓለም ፡ መንግሥታት ፡ ሁሉ፡ የሚበልጥ፡ድንቅ፡የሆነውን፡ክብሬን፡ታዪ፡ ዘንድ፡ወደ፡ሰማያዊ፡ዕረፍት፡እንድወስድሽ፡ እናቴ፡ሆይ፡ተነሺ፡ቁሚ፡አላት።

፳፬፡ እናቴ፡ሆይ፡ከአንዱ፡ቦታ፡ወደ፡አንዱ፡ቦታ፡ እኔን ፡ በመሸከም ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ደክመሻል፡ እውነተኛ፡በሆነው፡በላይኛው፡መንግሥቴ፡ በኢየሩሳሌም፡ትመላለሺ፡ዘንድ፡ነዪ።

Scanned by CamScanner

በ፫፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

ወአምድኅረ ፡ ይቤ ፡ መድኅን ፡ ለወላዲቱ ፡
ድንግል ፡ ፈነዋ ፡ ቅድሜሁ ፡ ወጸርዋ ፡ እለ ፡
ሱራፌል ፡ በከነፊሆሙ ፡ ወይቤልዎ ፡
አርድእቱ ፡ ለእግዚእነ ፡ ለምንት ፡ ከመዝ ፡
ትፈለየነ፡አኮኑ፡አንተ፡ትቤ፡አዐርግ፡ሰማየ፡
ኀበ፡አቡየ፡ወአቡክሙ፡ወኢየኀድገክሙ፡
ዕጓለ፡ማውታ፡ትኩኑ፡ወካዕበ፡ትነሥኡ፡
ለአምክ፡እምኔነ፡እንተ፡ትናዝዘነ፡በኵሉ፡
ኀዘን።

ወይቤሎሙ፡መድኅን፡አ፡ፍቁራን፡ቅዱሳን፡
ወንጹሓን፡ኢይምሰልክሙ፡ዘነሣእክዋ፡
ከመ፡ርኢክምዋ፡እንዘ፡ተዓርግ፡ሰማየ፡
ከማሁ፡ካዕበ፡ትመጽእ፡ኀቤክሙ፡ወትሬ
እይዋ።

ወእምድኅረሰ፡ርኢክምዋ፡ትመውት፡ከመ፡
ኵሉ፡ዕጓለ፡እመሕያው፡ወእሁባ፡ሕይወተ፡
ዘለዓለም።

ወተዓርግ፡ሰማየ፡ኀበ፡ማኅደራ፡እንተ፡
በላዕሉ፡ኢየሩሳሌም፡ሰማያዊት።

ወእምድኅረ፡ይቤ፡ዘንተ፡ለአርዳኢሁ፡
ተመይጠ፡ኀበ፡ዮሐንስ፡ፍቁሩ።

ወይቤሎ፡ናሁ፡ተሐውር፡ኀበ፡ጢባርዮስ፡
ንጉሥ፡ከመ፡ትኩን፡ስምዐ፡በኵሉ፡ግብር፡
ዘርኢከ፡እምኔየ።

ወበከመ፡ገብሩ፡አይሁድ፡ላዕሌየ፡እንዘ፡
ሀሎኩ፡ዲበ፡ዕፀ፡መስቀል።

ወእምድኅረ፡ይቤ፡መድኅን፡ክርስቶስ፡
ዘንተ፡ለአርዳኢሁ፡ቅዱሳን፡ተሠወረ፡
እምኔሆሙ።

ወሶቤሃ፡መጽኡ፡ሠራዊተ፡ንጉሥ፡ወሐራ፡
ኢየሩሳሌም፡ምስለ፡አዋልድ፡ኀጽዋት፡
ብዙኃት፡ወአክሊለ፡መንግሥት፡ወልብሰ፡
ክቡር፡ዘድልው፡ለመንግሥት፤ወኃሠሥዋ፡
ለድንግል፡ውስተ፡ኵሉ፡ምድረ፡ይሁዳ፡
ወኢረከብዋ፡እስመ፡ዐርገት፡ውስተ፡
ሰማይ።

ስብሐት፡ወበረከት፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡
ዓለም፡አሜን።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፫፡ሰዓት።

፳፭፤ መድኃኒታችንም፡ለድንግል፡እናቱ፡ይህን፡ካለ፡በኋላ፡በፊቱ፡ላካት፤ሱራፌልም፡በክንፎቻቸው፡ተሸከሙአት፤ የጌታችንም፡ደቀ፡መዛሙርት፡አንተ፡ወደ፡አባቴ፡ወደ፡አባታችሁ፤ወደ፡ሰማይ፡አርጋለሁ፤የሙት፡ልጆች፡ትሆኑ፡ዘንድ፡አልተዋችሁም፤ ብለህ፡ አልነበረምን፡ዳግመኛም፡በሁሉ፡ነገር፡የምታጽናናን፡እናትህን፡ከእኛ፡ዘንድ፡ወሰድኻት፡አሉት።

፳፮፤ መድኃኒታችንም፡የተወደዳችሁ፡ቅዱሳን፡ንጹሐን፡ወዳጆቼ፡ሆይ፡አሁን፡ወደ፡ሰማይ፡ስታርግ፡እንደአያችኋት፡እንዲሁ፡ወደ፡እናንተ፡ተመልሳ፡ስትመጣ፡ታይዋታላችሁና፤ የወሰድኋት፡ አይምሰላችሁ፡አላቸው።

፳፯፤ ከአያችኋትም፡በኋላ፡እንደ፡ሰው፡ሁሉ፡ትሞታለች፡የዘላለም፡ሕይወትንም፡እሰጣታለሁ።

፳፰፤ ከሁሉ፡በላይ፡ወደምትገኘው፡ወደ፡ማደሪያዋ፡ወደ፡ኢየሩሳሌም፡ሰማያዊት፡ታርጋለች፡አላቸው።

፳፱፤ ለደቀ፡መዛሙርቱም፡ይህን፡ካላቸው፡በኋላ፡ወደሚወደው፡ወደ፡ዮሐንስ፡ተመለሰ።

፴፤ እነሆ፡ከእኔ፡በአየኸው፡ሥራ፡ሁሉ፡ምስክር፡ ትሆን፡ዘንድ፡ወደ፡ንጉሥ፡ጢባርዮስ፡ሂድ፡አለው።

፴፩፤ በመስቀል፡ዕንጨትም፡እያለሁ፡እንዳደረጉብኝ፡ታሳየው፡ዘንድ።

፴፪፤ መድኅን፡ክርስቶስም፡ለደቀ፡መዛሙርቱ፡ይህን፡ከተናገረ፡በኋላ፡ከእርሳቸው፡ተሠወረ።

፴፫፤ ያን፡ጊዜም፡የንጉሥ፡ሠራዊትና፡ወታደሮች፡ከሴቶች፡ጋራም፡ብዙዎች፡ጃንደረቦች፡ለመንግሥት፡የሚገባውን፡የከበረ፡ልብስና፡ዘውድ፡ተሸክመው፡ወደ፡ኢየሩሳሌም፡መጡ፤ በይሁዳ፡ሀገርም፡ውስጥ፡ሁሉ፡ድንግልን፡ፈለጉዋት፤ አላገኙዋትም፤ ወደ፡ሰማይ፡አርጋለችና።

ልመናዋ፡ክብርዋ፡ከእኛ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡ይኑር፡አሜን።

Scanned by CamScanner

### በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ጥዑመ፡ስም፡በል።

ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ጥዑመ፡ስም፡በል፡ ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ጥዑመ፡ስም፡በል፡ ...

ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ጥዑመ፡ስም፡በል።

ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ጥዑመ፡ስም፡ዘገብረ፡እግዚእነ፡ወአ
ተአምር፡ወመንክር፡ዘገብረ፡እግዚእነ፡ወአ
ምላክነ፡ወመድኃኒነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡
ማሀሉ፡ወምሕረቱ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡
ዓለም፡አሜን።

፩፡ ወእንዘ፡ይትናገሮሙ፡ጲላጦስ፡ለአይሁድ፡
መጽአ፡መልእክት፡እምኀበ፡ብእሲቱ፡
ዘይብል፡ዕቀብአ፡ነፍሰከ፡እምዝንቱ፡ጻድቅ፡
ወኢትግበር፡ላዕሌሁ፡እኩየ፡እስመ፡ፃመውኩ፡
በእንቲአሁ፡ብዙኀ፡ወተሐወኩ፡ጥቀ።

፪፡ ወበጊዜሃ፡አምጽአ፡ጲላጦስ፡ማየ፡
በንብቲራ፡ወተኀፅበ፡እዴሁ፡በቅድሜሆሙ፡
ለማኅበረ፡አይሁድ።

፫፡ ወይቤ፡ንጹሕ፡አነ፡እምደሙ፡ለዝ፡ብእሲ፡
ጻድቅ፡አንትሙ፡ተአምሩ፡ዘትገብሩ፡ቦቱ።

፬፡ ወካዕበ፡ጸርሑ፡ወይቤሉ፡ደሙ፡ላዕሌነ፡
ወላዕለ፡ውሉድነ።

፭፡ ወይቤሎሙ፡ጲላጦስ፡ተመጠውዎ፡
ለሊክሙ፡ወፍትሑ፡ላዕሌሁ፡በከመ፡ይኤዝዘክሙ፡ሕግክሙ፡አንሰ፡ኢረከብኩ፡
ምክንያተ፡ላዕሌሁ፡በዘእኴንኖ።

፮፡ ወአኀዘ፡ጲላጦስ፡እዴሁ፡ለእግዚእ፡ኢየሱስ፡
ወወሰዶ፡እንተ፡ባሕቲቱ፡ወይቤሎ፡አንተኑ፡
ንጉሦሙ፡ለአይሁድ፡ወአውሥአ፡እግዚእ፡
ኢየሱስ፡ወይቤሎ፡እምልብከኑ፡ትብል፡
ዘንተ፡ወሚመ፡ነገሩከ፡ካልአን።

፯፡ ወይቤሎ፡ጲላጦስ፡ኢተአምርኑ፡ከመ፡ብየ፡
ሥልጣን፡እቅትልከ፡ወአሕዩከ፡አውሥአ፡
እግዚእ፡ኢየሱስ፡ወይቤሎ፡አልብከ፡
ሥልጣን፡ላዕሌየ፡ለእመ፡ኢተውህበከ፡
እምሰማይ፡እስመ፡በእንተ፡ዝንቱ፡መጻእኩ፡
ወበጻሕኩ፡ውስተ፡ዓለም፡ወበእንተዝ፡
ተሠጎኩ፡እምሰብእ፡ወተትሕትኩ፡
እትወለድ፡ወእትሐፀን።

፰፡ ወይቤሎ፡ጲላጦስ፡ንግረኒ፡ጽድቀ፡ቦኑ፡
አንተ፡ንጉሠ፡አይሁድ፡ወአውሥአ፡
እግዚእ፡ኢየሱስ፡ወይቤሎ፡አንተ፡ትቤ፡
ከመ፡አነ፡ንጉሠ፡አይሁድ፡ወአንሰ፡

### ዓርብ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ጥዑመ፡ስም፡በል።

ይቅርታውና፡ቸርነቱ፡ከእኛ፡ጋራ፡
ለዘላለሙ፡በእውነት፡ይኑርና፡ጌታችን፡
ላካችንና፡መድኃኒታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡
ያደረገው፡ድንቅ፡ተአምር፡ይህ፡ነው።

፩፡ ጲላጦስም፡አይሁድን፡እየተናገራቸው፡ሳለ፡
ከዚህ፡ከጻድቅ፡ሰው፡ሰውነትህን፡ጠብቅ፡
በእርሱ፡ላይም፡ክፉ፡ሥራ፡እንዳትሠራ፡ስለ
እርሱም፡እጅግ፡ብዙ፡ስሰቃይ፡አድሬአ
ለሁና፡የሚል፡መልእክት፡ከሚስቱ፡ዘንድ፡
መጣ።

፪፡ ያንጊዜም፡ጲላጦስ፡ውኃ፡በሎስሎስት፡
አስመጥቶ፡በአይሁድ፡ጉባኤ፡ፊት፡እጁን፡
ታጠበ።

፫፡ በእርሱ፡ላይ፡የምታደርጉትን፡እናንተ፡ታው
ቃላችሁ፤እኔ፡ከዚህ፡ጻድቅ፡ሰው፡ደም፡
ንጹሕ፡ነኝ፡አለ።

፬፡ ዳግመኛም፡ደሙ፡በእኛና፡በልጆቻችን፡ላይ፡
ይሁን፡ብለው፡ጮኹ።

፭፡ ጲላጦስም፡እናንተ፡ራሳችሁ፡ተቀበሉት፡
ሕጋችሁ፡እንደሚያዛችሁ፡ፍረዱበት፤እኔ፡
በምፈርድበት፡ገንዘብ፡ምክንያት፡አላ
ኘሁም፡አላቸው።

፮፡ ጲላጦስም፡የጌታችን፡የኢየሱስን፡እጅ፡ይዞ፡
ለብቻውም፡ገለል፡አድርጎ፡የአይሁድ፡
ንጉሣቸው፡አንተ፡ነህን፡አለው፤ጌታ፡
ኢየሱስም፡መለሰ፤ይህን፡የምትናገር፡ከልብህ፡
ነውን፡ወይስ፡ሌሎች፡ነገሩህ፡አለው።

፯፡ ጲላጦስም፡ልገድልህም፡ሆነ፡ላድንህ፡
ሥልጣን፡እንዳለኝ፡አታውቅምን፡አለው፤
ጌታ፡ኢየሱስም፡መለሰ፤ከሰማይ፡ካልተ
ሰጠህ፡በቀር፡በእኔ፡ላይ፡ሥልጣን፡የለህም፤
ስለዚህም፡ወደ፡ዓለም፡መጣሁ፤ለዚችም፡
ሰዓት፡ደረስኩ፤ከልዕልና፡ዝቅ፡ብዬ፡
የሰውን፡ባሕርይ፡ገንዘብ፡አድርጌ፡ተወልጄ፡
አድግ፡ዘንድ፡መጣሁ፡አለው።

፰፡ ጲላጦስም፡በውኑ፡የአይሁድ፡ንጉሥ፡
አንተ፡እንደሆንክ፡እውነቱን፡ንገረኝ፡
አለው፤ጌታ፡ኢየሱስም፡እኔ፡የአይሁድ፡
ንጉሥ፡እንደሆንኩ፡አንተ፡አልክ፤እኔስ፡

Scanned by CamScanner

## በ፫፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

ኢኮንኩ ፡ ንጉሠ ፡ አይሁድ ፡ ባሕቲቶሙ ፡
ወባሕቱ፡ንጉሠ፡ኵሉ፡ዓለም፡አነ።

፱ ወሶበ ፡ ሰምዐ ፡ ጲላጦስ ፡ ዘንተ ፡ እምኔሁ ፡
ደንገፀ፡ወቢየ፡ድንጋጼ።

፲ ወይቤሎሙ፡ለአይሁድ፡አነ፡አሐዩ፡ዘንተ፡
ብእሴ ፡ እስመ ፡ ኢረከብኩ ፡ ላዕሌሁ ፡
ምክንያተ፡ዘይደሉ፡ለሞት።

፲፩ ወአውሥኡ፡አይሁድ፡ወይቤሉ፡ይደልዎ፡
ይሰቀል፡በእንተ፡ዘረሰየ፡ርእሶ፡ንጉሠ፡እንዘ፡
ኢመጠኑ።

፲፪ ወቀርበ ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ ኀበ ፡ እግዚእ ፡
ኢየሱስ፡ ወይቤሎ፡እመሰ ክርስቶስ፡ አንተ፡
ንግረነ፡ገሀደ፡አውሥአ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡
እወ፡አነ፡ክርስቶስ፡መድኃኔ፡ዓለም።

፲፫ ወይቤሎሙ ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ ለማኅበረ ፡
አይሁድ፡ኢትፍቅዱ፡እምይእዜ፡ሰማዕተ፡
ሰማዕኩ፡አነ፡ፅርፈቶ፡ወአምነ፡በቃሉ፡
ወሰመየ፡ርእሶ፡ክርስቶስሃ፡እግዚአብሔር፡
ዘይመጽእ፡ለመድኃኒተ፡ዓለም።

፲፬ ወሠጠጠ፡ልብሶ፡ሊቀ፡ካህናት፡ወሶቤሃ፡
ሰሐብዎ፡ አይሁድ ፡ ለእግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡
ወአሰርዎ፡ድኅሪተ፡ወከደኑ፡ገጾ፡ወጸፍዑ፡
መልታሕቶ ፡ ወይቤልዎ ፡ ተነበይ ፡ ለነ ፡
ክርስቶስ፡ መኑ፡ጸፍዐከ፡መልታሕቴከ።

፲፭ ወውእቱሰ ፡ ኢያውሥአሙ ፡ ወኢምንተኒ ፡
ወኰርዕዎ ፡ ርእሶ ፡ በኀለት ፡ ወእምዝ ፡
ቀሠፍዎ፡ዘባኖ፡በአስዋጥ።

፲፮ ወይተልዎ፡ዘይንእስ፡እምአርዳኢሁ፡ወሶበ፡
ርእየ፡ከመ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ገብአ፡ውስተ፡
እደዊሆሙ፡ለአይሁድ፡ጐየ፡እንዘ፡ይርእድ፡
ወዝንቱ፡ግብሮሙ፡ለአይሁድ፡በሌሊተ፡
ዐርብ፡ወብዙኀ፡ቍራ፡ለይእቲ፡ሌሊት።

፲፯ ወበጽሐ፡ህየ፡ስምዖን፡ኬፋ፡ወቦአ፡ዐጸደ፡
መካን፡ወረከበ፡ፍሕመ፡ብቁፀ፡ወነበረ፡ህየ፡
ይሰኀን።

፲፰ ወይቤሉ፡አይሁድ፡እለ፡ሀለዉ፡ህየ፡ዝንቱ፡
እምአርዳኢሁ፡ለናዝራዊ።

## ዓርብ፡መዓልት፡በ፫፡ሰዓት።

የአይሁድ ፡ ብቻ ፡ ንጉሥ ፡ አይደለሁም ፤
ለዓለሙ፡ሁሉ፡ንጉሥ፡ነኝ፡እንጂ፡አለው።

፱፤ ጲላጦስም ፡ ይህን ፡ ከእርሱ ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡
ታላቅ፡ድንጋጤ፡ደነገጠ።

፲፤ አይሁድንም፡እኔ፡ይህን፡ሰው፡አድነዋለሁ፤
ለሞት ፡ የሚያበቃ ፡ ምክንያት ፡ አላገኘሁበ
ትምና፡አላቸው።

፲፩፤ አይሁድም ፡ መለሱ ፤ ደረጃውና ፡ መጠኑ ፡
ሳይሆን ፡ ራሱን ፡ ንጉሥ ፡ ስለአደረገ ፡ ሞት ፡
ይገባዋል፡አሉ።

፲፪፤ ሊቀ፡ካህናቱም፡ወደ፡ጌታ፡ኢየሱስ፡ቀረብ፡
ብሎ ፡ ክርስቶስ ፡ አንተ ፡ ከሆንክ ፡ በግልጥ ፡
ንገረን ፡ አለው ፤ ጌታ ፡ ኢየሱስም ፡ መልሶ ፡
ዓለምን ፡ የማድን ፡ (የዓለም ፡ መድኃኒት) ፡
ክርስቶስ፡ አዎ፡እኔ፡ነኝ፡አለው።

፲፫፤ ሊቀ፡ካህናቱም፡ለአይሁድ፡ጉባዔ፡አሁንስ፡
ምስክር፡ አትሹ፤ በቃሉም፡ አመነ፤ ዓለምን፡
ለማዳን፡የሚመጣው፡ክርስቶስ፡የተባለው፡
እግዚአብሔር፡እኔ፡ነኝ፡ሲል፡ስድቡን፡እኔ፡
ሰማሁ፡አላቸው።

፲፬፤ ሊቀ፡ካህናቱም፡ልብሱን፡ቀደደ፤ያንጊዜም፡
አይሁድ ፡ ጌታ ፡ ኢየሱስን ፡ ጎተቱት ፤
የኋሊትም ፡ አሰሩት ፤ ፊቱንም ፡ ሸፍነው ፡
በጥፊ፡ እየመቱ፡ክርስቶስ፡ሆይ፡ጉንጭህን፡
በጥፊ፡የመታህ፡ማነው፡ንገረን፡አሉት።

፲፭፤ እርሱ፡ግን፡ምንም፡ምን፡አልመለሰላቸውም፤
ራሱንም ፡ በዘንግ ፡ መቱት ፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡
ጀርባውን፡በሳንባ፡ጠለፍ፡ገረፉት።

፲፮፤ ከደቀ ፡ መዛሙርቱም የሚያንሰው ፡ ያዕቆብ ፡
ይከተለው ፡ ነበር ፤ ጌታ ፡ ኢየሱስም ፡
በአይሁድ፡እጅ፡እንደገባ፡በአየ፡ጊዜ፡እየተን
ቀጠቀጠ፡ሸሸ፤በዓርብ፡ሌሊትም፡የአይሁድ፡
ሥራቸው ፡ ይህ ፡ ነበር ፤ ያቺ ፡ የዐርብ ፡
ሌሊትም፡ቅዝቃዜዋ፡ፅኑዕ፡ነበር።

፲፯፤ ስምዖን ፡ ኬፋም ፡ ከዚያ ፡ ደረሰ ፤ ወደ ፡ ግቢ ፡
ወዳለው፡ቦታ፡ገባ፤የእሳትም፡ፍም፡አግኝቶ፡
ሊሞቅ፡ተቀመጠ።

፲፰፤ ከዚያ ፡ ያሉ ፡ አይሁድም ፡ ይህ ፡ ከናዝሬቱ ፡
ሰው፡ደቀ፡መዛሙርት፡ውስጥ፡ነው፡አሉ።

Scanned by CamScanner

## በ፫፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

፲፱፡ ወሶበ ፡ ሰምዖሙ ፡ ጴጥሮስ ፡ መሐለ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ አንሰ ፡ ኢየአምሮ ፡ ለውእቱ ፡ ብእሲ ፡ ወኢየአምር፡ነገረ፡ዘትብሉ።

፳፡ ወሖረ ፡ ስምዖን ፡ ኀበ ፡ ካልእ ፡ መካን ፡ ወረከብዎ፡ካልኣን፡እምአይሁድ፡ወይቤሉ፡ በበይናቲሆሙ ፡ ዝንቱ ፡ አረጋዊ ፡ እምአር ዳኢሁ ፡ ለገሊላዊ ፡ ውእቱ ፡ ወክህደ ፡ ካዕበ ፡ ወይቤ፡ኢየአምሮ፡ለዝ፡ብእሲ።

፳፩፡ ወእምዝ፡ሖረ፡እምህየ፡ኀበ፡ካልእ፡መካን፡ ወርእየቶ ፡ አሐቲ ፡ ወለት ፡ እምአይሁድ ፤ ወትቤ ፡ ርኢክዎ ፡ ለዝ ፡ አረጋዊ ፡ ምስለ ፡ ዘሰመየ ፡ ርእሶ ፡ ንጉሠ ፡ ወይቤ ፡ ስምዖን ፡ ኢየአምሮ።

፳፪፡ ወክህደ፡ሠለስተ፡ጊዜ፡ወረገመ፡ርእሶ፡ከመ፡ ዘኢየአምሮ ፡ ለእግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ ወነቀወ ፡ ዶርሆ፡በይእቲ፡ሰዓት።

፳፫፡ ወተመይጠ ፡ እግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ ወርእዮ ፡ ለስምዖን ፡ ጴጥሮስ ፡ ወተዘከረ ፡ ስምዖን ፡ ጴጥሮስ፡ነገሮ፡ለእግዚእ፡ኢየሱስ፡ዘይቤሎ፡ እምቅድመ፡ይንቁ፡ዶርሆ፡ትክህደኒ፡ሥልሰ።

፳፬፡ ወወጺአ ፡ በከየ ፡ ብካየ ፡ መሪረ ፡ ወተከዕወ ፡ እምኔሁ፡አንብዕ፡ብዙኅ፡ከመ፡ማይ፡ወይቤ፡ አሌ ፡ ሊተ ፡ እስመ ፡ ወደቁ ፡ እማዕርግየ ፡ ልዑል፡ዘተውህበኒ፡ሊተ።

፳፭፡ አሌ፡ሊተ፡እስመ፡ተፈለጥኩ፡እምኈልቈ፡ ዐሠርቱ፡ወክልኤቱ፡አርዳእ።

፳፮፡ አሌ፡ሊተ፡እስመ፡ኮንኩ፡ቢጸ፡ለአይሁድ።

፳፯፡ አሌ፡ሊተ፡እስመ፡ተኃጕልኩ፡እምሢመት፡ ቅድስት።

፳፰፡ ወበውእቱ፡ጊዜ፡ኮኑ፡አይሁድ፡ይኴንንዎ፡ ግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡በዘዘዚአሁ፡ ሥነኔ፡ዕጹብ፡እስመ፡ኰነንዎ፡እምሴተ፡ ሌሊት፡እስከ፡ሠለስቱ፡ሰዓተ፡መዐልት።

፳፱፡ ወእምዝ፡አምጽኡ፡ልብሰ፡ሜላተ፡እምአ ልባስ፡ነገሥት፡ወአልበስዎ፡ለእግዚእነ።

፴፡ ወዓዲ ፡ አልበስዎ ፡ ላዕሌሁ ፡ ልብሰ ፡ አሮን ፡ ወወደዩ ፡ ዲበ ፡ ርእሱ ፡ አክሊለ ፡ ሦክ።

## ዓርብ፡መዓልት፡በ፫፡ሰዓት።

፲፱፡ ጴጥሮስም፡በሰማቸው፡ጊዜ፡ያንን፡ሰው፡እኔ፡ አላውቀውም ፡ ብሎ ፡ ማለ ፤ የምትሉትንም፡ ነገር፡አላውቅም፡አለ።

፳፡ ከዚያም፡ተነሥቶ፡ወደ፡ሌላ፡ቦታ፡ሄደ፤ከአ ይሁድም ፡ ሌሎች አገኙት ፤ እርስ ፡ በርሳ ቸውም ፡ ይህ ፡ ሽማግሌ ፡ ከገሊላዊው ፡ ተማሪዎች፡ውስጥ፡ነው፡አሉ፤ይህን፡ሰው፡ አላውቀውም፡ብሎ፡ሁለተኛ፡ካደ።

፳፩፡ ከዚያም፡ወደ፡ሌላ፡ቦታ፡ሄደ፤ከአይሁድም፡ ወገን፡አንዲት፡ሴት፡ልጅ፡አየችው፤ይህን፡ ሽማግሌ፡ራሱን፡ንጉሥ፡ካደረገው፡ጋራ፡ አይቼዋለሁ፡አለች፤ስምዖን፡ጴጥሮስም፡አላ ውቀውም፡አለ።

፳፪፡ ጌታ፡ኢየሱስንም፡እንደማያውቀው፡ራሱን፡ እየረገመ ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ካደ ፤ በዚያችም፡ ሰዓት፡ዶሮ፡ጮኸ።

፳፫፡ ጌታ ፡ ኢየሱስም ፡ መለስ ፡ ብሎ ፡ ስምዖን፡ ጴጥሮስን፡አየው፤ስምዖን፡ጴጥሮስም፡ዶሮ፡ ሳይጮኽ፡ሦስት፡ጊዜ፡ትክደኛለህ፡ያለውን፡ የጌታ፡ኢየሱስን፡ነገር፡አሰበ።

፳፬፡ ወደ ፡ ውጭም ፡ ወጥቶ ፡ መራራ ፡ ልቅሶ፡ አለቀሰ፤ከእርሱም፡ብዙ፡ዕንባ፡እንደ፡ውኃ፡ ፈሰሰ ፤ ወዮልኝ ፡ ከተሰጠኝ ፡ ከከፍተኛ፡ ማዕርጌ፡ወድቄያለሁና፡አለ።

፳፭፡ ከዐሥራ፡ሁለቱም፡ደቀ፡መዛሙርት፡ተለይ ቼአለሁና፡ወዮልኝ።

፳፮፡ ለአይሁድም ፡ ባልንጀራ ፡ ሁኜአለሁና፡ ወዮልኝ።

፳፯፡ ከከበረች ፡ ሹመትም ፡ ተሰናክያለሁና፡ ወዮልኝ፡አለ።

፳፰፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ጌታ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን፡ ልዩ፡ልዩ፡በሆነ፡ሥቃይ፡ያሠቃዩት፡ነበር፤ ከሌሊቱ፡ምሽት፡ጀምሮ፡እስከ፡ቀኑ፡ሦስት፡ ሰዓት፡ድረስ፡ያሠቃዩት፡ነበርና።

፳፱፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ነገሥታት ፡ የሚለብሱትን፡ ነጭ ፡ ሐር ፡ ልብስ ፡ አምጥተው ፡ ጌታችንን፡ አለበሱት።

፴፡ ዳግመኛም ፡ የአሮንን ፡ ልብስ ፡ በላዩ ፡ አለበሱት፤በራሱም፡ላይ፡የእሾህ፡አክሊል፡ ደፉበት።

Scanned by CamScanner

## በ፫፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

፴፩ ወሐሩ፡ ኀበ፡ መካነ፡ ዘሀለወት፡ ውስቴታ፡ ታቦተ፡ስምዕ፡ወነሥኡ፡እሐደ፡ዕፀ፡እምነ፡ ዕፀው፡ዘይጸውሩ፡ ቦቱ፡ ታቦተ ወዐበጥዎ፡ ለብእሲ፡ ዘይሰመይ፡ ስምዖን፡ ቀሬናዊ፡ ወአጸርዎ፡ውእተ፡ዕፀ፡ወሐሩ፡ውስተ፡ገነት፡ እንተ፡ሀለወት፡እምሀገር፡አፍአ፡ዘትሰመይ፡ ጎልጎታ።

፴፪ ወሀለወት፡ ህየ፡ ኰኵሕ፡ መቃብሪሁ፡ ለአዳም፡ይእቲ፡ዘአንበረ፡ሥጋሁ፡መልአከ፡ እግዚአብሔር፡ ውስቴታ፡ ወተከልዎ፡ ህየ፡ ለዕፀ፡ መስቀል፡ በማዕከለ፡ ምድር፡ ከመ፡ ይትፈጸም፡ ቃለ፡ ነቢይ፡ ሙሴ፡ ዘይቤ፡ ትሬእይዎ፡ለመድኃኒትክሙ፡ስቁለ፡ቅድመ፡ አዕይንቲክሙ።

፴፫ ወምክንያተ፡ልብሰ፡አሮን፡ዘአልበስዎ፡ለእግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ከመ፡ያፈልስ፡ መንግሥተ፡ ወክህነተ፡ ወትንቢተ፡ እምኔሆሙ፡ወይሁቦሙ፡ለካልአን።

፴፬ ወሰቀልዎ፡ለእግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ ዲበ፡ውእቱ፡ዕፀ፡መስቀል።

፴፭ ወአምጽአ፡ጲላጦስ፡ሰሌዳ፡ዘዕፅ፡ወቀረጸ፡ ውስቴቱ፡ ዜናሁ፡ ለእግዚእነ፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ወምክንያተ፡ ሞቱ፤ ወጸሐፈ፡ በአንጻረ፡ርእሱ፡ዘይብል፡ዝንቱ፡ውእቱ፡ ንጉሦሙ፡ለአይሁድ።

፴፮ ወይቤልዎ፡ አይሁድ፡ ለጲላጦስ፡ ኢትጽሐፍ፡ ከመዝ፡ አላ፡ ጸሐፍ፡ እንዘ፡ ትብል፡ከመ፡ውእቱ፡ይቤ፡ንጉሠ፡አይሁድ፡ አነ።

፴፯ አውሥአ፡ ጲላጦስ፡ ወይቤ፡ ዘጸሐፍኩ፡ ጸሐፍኩ፡በውስተ፡ውእቱ፡ሰሌዳ።

፴፰ ወጽሑፍ፡በጽርእ፡ወበዕብራይስጥ፡ወበሮማ ይስጥ።

፴፱ ወምክንያተ፡ጽሕፈቱስ፡በሠለስቱ፡ልሳናት፡ እስመ፡ጲላጦስ፡ሮማዊ፡ውእቱ፡ወሄሮድስ፡ ጽርእዊ፡ ወቀያፋ፡ ሊቀ፡ ካህናት፡ ዘይእቲ፡ ዓመት፡ዕብራዊ፡ውእቱ።

ሣህሉ፡ወምሕረቱ፡የሃሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ ዓለም፡አሜን።

## ዓርብ፡መዓልት፡በ፫፡ሰዓት።

፴፩፤ የምስክሩም፡ ታቦት፡ ወዳለችበት፡ ቦታ፡ ሄደው፡ ታቦቷን፡ከሚሸከሙበት፡አንዱን፡ ዕንጨት፡ ወሰዱ፤ የቀሬን፡ ሰው፡ የሚሆን፡ ስምዖን፡ የተባለውን፡ አስገድደው፡ መስቀሉን፡ አሸከሙት፤ ከከተማ፡ ውጭ፡ ወዳለችው፡ ጎልጎታ፡ ወደ፡ ተባለች፡ የአት ክልት፡ቦታም፡ወሰዱት።

፴፪፤ በዚያም፡ የእግዚአብሔር ፡ መልአክ፡ ሥጋውን፡ ያኖረበት፡ የአዳም፡ መቃብር፡ የሆነች፡ ዋሻ፡ አለች፤ የመስቀሉንም፡ እንጨት፡ በዚያ፡ በምድር፡ መካከል፡ ተከሉት፤ መድኃኒታችሁን፡ በዓይናችሁ፡ ፊት፡ተሰቅሎ፡ታዩታላችሁ፡ያለው፡የነቢይ፡ ሙሴ፡ቃል፡ይፈጸም፡ዘንድ።

፴፫፤ ለጌታችን፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ የአሮንን፡ ልብስ፡ ያለበሱበት፡ ምክንያት፡ ክህነትን፡ መንግሥትን፡ ትንቢትን፡ ከእነሱ፡ ወስዶ፡ ለሚያምኑት፡ ለሌሎች፡ ይሰጣቸው፡ዘንድ፡ አለውና፡ነው።

፴፬፤ በዚያም፡የእንጨት፡መስቀል፡ላይ፡ጌታችን፡ ኢየሱስ፡ክርስቶስን፡ሰቀሉት።

፴፭፤ ጲላጦስም፡ የዕንጨት፡ ሠሌዳ፡ አምጥቶ፡ የጌታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስን፡ዜናና፡የሞ ተበትንም፡ምክንያት፡ጻፈ፤ከራሱ፡በላይም፡ አኖረው፤ ጽሑፉም፡ “ይህ፡ የአይሁድ፡ ንጉሣቸው፡ነው”፡የሚል፡ነበር።

፴፮፤ አይሁድም፡ጲላጦስን፡ንጉሥ፡ነው፡ብለህ፡ እንደዚህ፡ አትጻፍ፤ እርሱ፡ ንጉሥ፡ ነኝ፡ እንዳለ፡ጻፍ፡እንጂ፡አሉት።

፴፯፤ ጲላጦስም፡ በዚህ፡ በሠሌዳ፡ የጻፍኩትን፡ ጻፍኩ፡ብሎ፡መለሰላቸው።

፴፰፤ ጽሕፈቱም፡ በግሪክ፡ በዕብራይስጥ፡ በሮማ ይስጥ፡ነው።

፴፱፤ በሦስቱ፡ ቋንቋ፡ የተጻፈበት፡ ምክንያት፡ ጲላጦስ፡ሮማዊ፡ሄሮድስ፡ግሪካዊ፡በዚያች፡ ዓመት፡ ሊቀ፡ ካህናት፡ የነበረው፡ ቀያፋም፡ ዕብራዊ፡ነበርና።

ይቅርታው፡ቸርነቱ፡ከእኛ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡ ይኑር፡አሜን።

በ፫፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

ክፍል፡፫።

ይ፡ዲ፡ቅድመ፡ወንጌል።

መዝ፡፳፩፡፲፮።

ዐገቱኒ ፡ ከለባት ፡ ብዙኃን ። ወአኀዙኒ ፡ ማኅበሮሙ ፡ ለእኩያን ። ቀነዉኒ ፡ እደውየ ፡ ወእገርየ።

ወንጌል፡ዘማቴዎስ።

ምዕ፡፳፯፡፲፭–፳፮።

፲፭፡ ወበ ፡ ልማድ ፡ ለመስፍን ፡ ለለበዐል ፡ ያሕዩ ፡ ሎሙ ፡ ለሕዝብ ፡ አሐደ ፡ እምነ ፡ ሙቁሓን ፡ ዘፈቀዱ።

፲፮፡ ወበ፡አሜሃ፡ሙቁሕ፡ዘስሙ፡በርባን፡ስሙዕ፡ ወየአምሮ፡ኵሉ፡ሰብእ።

፲፯፡ ወእንዘ ፡ ጉቡኣን ፡ እሙንቱ ፡ ይቤሎሙ ፡ ጲላጦስ ፡ ለሕዝብ ፡ መነ ፡ ትፈቅዱ ፡ አሕዩ ፡ ለክሙ ፡ በርባንሃኑ ፡ ወሚመ ፡ ኢየሱስሃኑ ዘይብልዎ፡ክርስቶስ።

፲፰፡ እስመ ፡ የአምር ፡ ከመ ፡ በቅንአቶሙ ፡ አግብእዎ።

፲፱፡ ወእንዘ፡ይነብር፡ጲላጦስ፡ዐውደ፡ለአከት፡ ኀቤሁ ፡ ብእሲቱ ፡ እንዘ ፡ ትብል ፡ ዑቅአ ፡ ኢተአብስ፡ወኢትትሐለፍ፡ላዕለ፡ውእቱ፡ ጻድቅ ፡ እስመ ፡ ብዙኃ ፡ ሐመምኩ ፡ ዮም ፡ በሕልም፡በእንቲአሁ።

፳፡ ወሊቃነ ፡ ካህናትሰ ፡ ወረበናት ፡ ሄጥዎሙ ፡ ወአሆ፡አበልዎሙ፡ለሕዝብ፡ከመ፡በርባንሃ፡ ይስአሉ ፡ ያሕዩ ፡ ሎሙ ፡ ወኢየሱስሃ ፡ ይስቅሉ።

፳፩፡ ወአውሥአ ፡ መስፍን ፡ ወይቤሎሙ ፡ መነ ፡ ትፈቅዱ ፡ እምክልኤሆሙ ፡ አሕዩ ፡ ለክሙ ፡ ወይቤሉ፡በርባንሃ።

፳፪፡ ወይቤሎሙ፡ጲላጦስ፡ምንተ፡እንከ፡እረስዮ፡ ለኢየሱስ ፡ ዘተብህለ ፡ ክርስቶስ ፡ ወይቤሉ ፡ ኵሎሙ፡ስቅሎ።

፳፫፡ ወይቤሎሙ፡መስፍን፡ምንተ፡እኩየ፡ገብረ፡ ወአፈድፈዱ፡ጸሪሐ፡እንዘ፡ይብሉ፡ስቅሎ፡ ስቅሎ።

፳፬፡ ወእምዝ ፡ ርእዮ ፡ ጲላጦስ ፡ ከመ ፡ አልቦ ፡ ዘይበቍዕ፡ዘእንበለ፡ዳዕሙ፡ዘይበዝኅ፡ሀከክ፡ ፈድፋደ፡ነሥአ፡ማየ፡ወተኀፅበ፡እዴሁ፡በቅ ድሜሆሙ፡ለሕዝብ፡እንዘ፡ይብል፡ንጹሕ፡

ዓርብ፡መዓልት፡በ፫፡ሰዓት።

ክፍል፡፫።

ዲያቆን፡ከወንጌል፡አስቀድሞ።

መዝ፡፳፩፡፲፮።

ብዙ ፡ የሆኑ ፡ ውሾች ፡ ከበቡኝ ፡ የክፉዎች ፡ ማኅበርም ፡ በአንድነት ፡ ሁነው ፡ ያዙኝ ፡ እጆቼንና፡እግሮቼን፡ቸነከሩኝ።

የማቴዎስ፡ወንጌል።

ምዕ፡፳፯፡፲፭–፳፮።

፲፭፡ በየበዓሉም፡ለሕዝቡ፡ከእስረኞች፡መካከል፡ አንዱን ፡ የወደዱትን ፡ እንዲፈታላቸው ፡ ለመስፍኑ፡ልማድ፡ነበረው።

፲፮፡ ያን፡ጊዜም፡ስመ፡ጥር፡የታወቀ፡የሽፍቶች፡ አለቃ ፡ በርባን ፡ የሚባል ፡ እስረኛ ፡ ነበር ፡ ሁሉም፡ያውቀው፡ነበር።

፲፯፡ እነርሱም ፡ ተሰብስበው ፡ ሳሉ ፡ ጲላጦስ ፡ ሕዝቡን፡ማንን፡ላድንላችሁ፡ትወዳላችሁ፤ በርባንን ፡ ወይስ ፡ ክርስቶስ ፡ የሚሉት ፡ ኢየሱስን፡አላቸው።

፲፰፡ በቅንዓት፡አሳልፈው፡እንደ፡ሰጡት፡ያውቅ፡ ነበርና።

፲፱፡ ጲላጦስ፡በአደባባይ፡ተቀምጦ፡ሳለ፡በዚህ፡ ጻድቅ፡ሰው፡ላይ፡ተላልፈህ፡እንዳትበድል፡ ዕወቅ፤በዚች፡ሌሊት፡በህልሜ፡ስለ፡እርሱ፡ ብዙ ፡ ተሠቃይቻለሁና ፡ ስትል ፡ ሚስቱ ፡ ላከችበት።

፳፡ የካህናት ፡ አለቆችና ፡ ሽማግሌዎች ፡ ግን ፡ ሕዝቡን ፡ አታለሏቸው ፤ በርባንን ፡ ሊያድን ላቸው ፡ እንዲለምኑ ፡ ኢየሱስንም ፡ እንዲ ሰቅሉ፡እሺ፡በጄ፡አሰኙአቸው።

፳፩፡ መስፍኑም ፡ መልሶ ፡ ከሁለቱ ፡ ማንን ፡ ላድን ላችሁ ፡ ትወዳላችሁ ? አላቸው ፤ እነርሱም ፡ በርባንን፡አሉ።

፳፪፡ ጲላጦስም ፡ እንግዲያ ፡ ክርስቶስ ፡ የተባለ ፡ ኢየሱስን፡ምን፡ላድርገው፡አላቸው፤ሁሉም፡ ስቀለው፡አሉ።

፳፫፡ መስፍኑም፡ምን፡ክፉ፡ሥራ፡ሠራ፡አላቸው፤ እነርሱ ፡ ግን ፡ ስቀለው ፡ ስቀለው ፡ እያሉ ፡ ጩኸትን፡አበዙ።

፳፬፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ጲላጦስ ፡ ፀብ ፡ ክርክር ፡ ከሚበዛ ፡ በቀር ፡ የሚጠቅም ፡ ነገር ፡ እንደሌለ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ውኃ ፡ ወስዶ ፡ እኔ ፡ ከዚህ ፡ ጻድቅ ፡ ሰው ፡ ደም ፡ ንጹሕ ፡ ነኝ ፡

Scanned by CamScanner

በ፫፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

...አ፡እምደሙ፡ ለዝ ፡ ጻድቅ ፡ ወአንትሙ ፡
...ለክሙ፡አእምሩ።
...ወአውሥኡ፡ወይቤሉ፡ኵሉ፡ ሕዝብ ፡ ደሙ ፡
...ሉዴኑ፡ወላእለ፡ውሉድነ።



...ዘ ጲላጦስ እዴሁ ... ለሕዝብ::

ጲላጦስ በሕዝቡ ፊት እጁን እንደ ታጠበ::

...ወእምዝ፡አሕየወ፡ሎሙ፡በርባንሃ፡ወቀሠፎ፡
ለእግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ ወመጠዎሙ ፡
ይሰቅልዎ።
ወእምዝ፡ይበሉ፡ካህን፡ወዲያቆን፡ወሕዝብ፡
...ሙ፡ቀዳሚ።
ጊዜ፡ሠለስቱ፡ሰዓት፡ አኀዝዎ ፡ ለኢየሱስ ፡
ወወሰድዎ፡ይሰቅልዎ።
ይ፡ካ፡ ቅዱስ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቅዱስ ፡
ኃያል፡ቅዱስ፡ ሕያው ፡ ዘኢይመውት ፡ ፫ ፡
ጊዜ።

## ወንጌል፡ዘማርቆስ።

ምዕ፤፲፭፥፮–፲፩።

...ወለለበዓል፡ ያሐዩ ፡ ሎሙ ፡ አሐደ ፡ እምነ ፡
...ሙቁሐን፡ዘአብደሩ።
...ወሀሎ፡ አሐዱ ፡ ብእሲ ፡ ዘስሙ ፡ በርባን ፡
...ሙቁሕ፡ምስለ፡እለ፡ገብሩ፡ሀከከ፡ወምስለ፡
...ቀተልተ፡ነፍስ።
...ወዐርጉ፡ሕዝብ፡ወከልሑ፡ወሰአሉ፡ይግበር፡
...ሎሙ፡በከመ፡ያለምድ።
...ወአውሥአ፡ጲላጦስ፡ወይቤሎሙ፡ትፈቅዱኑ፡
...አሕይዎ፡ለክሙ፡ለንጉሠ፡አይሁድ።
...እስመ ፡ የአምር ፡ ከመ ፡ በቅንአቶሙ ፡
...አግብእዎ፡ሊቃነ፡ካህናት።
...ወሊቃነ፡ ካህናትሰ ፡ ሆከዎሙ ፡ ለሕዝብ ፡
...ከመ፡ በርባንሀ ፡ ይስአሉ ፡ ያሕዩ ፡
...ሎሙ።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፫፡ሰዓት።

እናንተ ፡ ለራሳችሁ ፡ ዕወቁ ፡ ብሎ ፡ በሕዝቡ ፡
ፊት፡እጁን፡ታጠበ።
፳፭፤ ሕዝቡም ፡ ሁሉ ፡ መልሰው ፡ ደሙ ፡ በእኛና ፡
በልጆቻችን፡ላይ፡ይሁን፡አሉ።

፳፮፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በርባንን ፡ ፈታላቸው ፤ ጌታ ፡
ኢየሱስን ፡ ግን ፡ ገርፎ ፡ ሊሰቅሉት ፡ አሳልፎ ፡
ሰጣቸው።
ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ካህኑ ፡ ዲያቆኑ ፡ ሕዝቡ ፡ እንዳ
ለፈው ፡ ይበሉ።
ሦስት፡ሰዓት፡በሆነ፡ጊዜ፡ኢየሱስን፡ይዘው፡
ይሰቅሉት፡ዘንድ፡ወሰዱት።
ካህኑ ፡ ቅዱስ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቅዱስ ፡ ኃያል ፡
ቅዱስ፡ሕያው፡ዘኢይመውት፡ይበል፡ሦስት፡
ጊዜ።

## የማርቆስ፡ወንጌል።

ምዕ፤፲፭፥፮–፲፩።

፮፤ በበዐልም ፡ ከእስረኞች ፡ የመረጡትን ፡
አንዱን፡ይፈታላቸው፡ነበር።
፯፤ ከነፍስ፡ገዳዮችና፡ከከፉ፡አድራጊዎች፡ጋር፡
የታሰረ፡ስሙ፡በርባን፡የሚባል፡አንድ፡ሰው፡
ነበር።
፰፤ ሕዝቡም ፡ እንደ ፡ ልማዱ ፡ ያደርግላቸው ፡
ዘንድ፡ወጥተው፡እየጮኹ፡ለመኑ።
፱፤ ጲላጦስም፡መልሶ፡የአይሁድን፡ንጉሥ፡ላድ
ንላችሁ፡ትወዳላችሁን፡አላቸው።
፲፤ የካህናት ፡ አለቆች ፡ ቀንተው ፡ አሳልፈው ፡
እንደ፡ሰጡት፡ያውቅ፡ነበርና።
፲፩፤ የካህናት፡አለቆች፡ግን፡በርባንን፡እንዲያድን
ላቸው፡ይለምኑት፡ዘንድ፡ሕዝቡን፡አነሣሡ
አቸው።

Scanned by CamScanner

በ፫፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

፲፪ ወካዕበ፡አውሥአ፡ጲላጦስ፡ወይቤሎሙ፡ምንተ፡እንከ፡ትፈቅዱ፡እረስዮ፡ለዘተብሀለ፡ንጉሠ፡አይሁድ።
፲፫ ወካዕበ፡ከልሑ፡ኵሎሙ፡ወይቤሉ፡ስቅሎ።
፲፬ ወይቤሎሙ፡ጲላጦስ፡ምንተ፡እኩየ፡ገብረ፡ወፈድፋደ፡ጸርሑ፡ወይቤሉ፡ስቅሎ።

፲፭ ወመከረ፡ጲላጦስ፡ይግበር፡ፈቃዶሙ፡ለሕዝብ፡ወአሕየወ፡ሎሙ፡በርባንሀ፡ወቀሠፎ፡ለእግዚእ፡ኢየሱስ፡ወወሀቦሙ፡ይስቅልዎ።

ወእምዝ፡ይበሉ፡ካህን፡ወዲያቆን፡ወሕዝብ፡ከመ፡ቀዳሚ።
ጊዜ፡ሠለስቱ፡ሰዓት፡አሕየወ፡ሎሙ፡በርባንሃ፡ወወሀቦሙ፡ኢየሱስሃ፡ይስቅሉ።
ይ፡ካ፡ቅዱስ፡እግዚአብሔር፡ቅዱስ፡ኃያል፡ቅዱስ፡ሕያው፡ዘኢይመውት፡፫፡ጊዜ።

ወንጌል፡ዘሉቃስ።

ምዕ፡፳፫፡፲፫–፳፭።

፲፫ ወጸውአሙ፡ጲላጦስ፡ለሊቃነ፡ካህናት፡ወለመኳንንተ፡ሕዝብ።
፲፬ ወይቤሎሙ፡አምጻእክምዎ፡ኀቤየ፡ለዝንቱ፡ብእሲ፡ከመ፡ዐላዌ፡ሕዝብ፡ወናሁ፡አነ፡ሐተትክዎ፡በቅድሜክሙ፡ወአልቦ፡ዘረከብኩ፡ሎቱ፡ጌጋየ፡ለዝንቱ፡ብእሲ፡እምዘ፡አንትሙ፡አስተዋደይክምዎ።
፲፭ ወኀበ፡ሄሮድስሂ፡ፈነውክዎ፡ወውእቱ፡ፈነዎ፡ኀቤነ፡ወናሁ፡አልቦ፡ዘገብረ፡በዘይመውት።
፲፮ እቅሥሮኬ፡ወእኅድጎ።
፲፯ ወቦ፡ልማድ፡በበዐል፡ያሕዩ፡ሎሙ፡አሐደ፡እምነ፡ሙቁሓን።
፲፰ ወዐውየዉ፡ኵሎሙ፡ኅቡረ፡በምልዖሙ፡ወይቤሉ፡እእትቶ፡ለዝ፡ወስቅሎ፡ወአሕዩ፡ለነ፡በርባንሃ።
፲፱ ወውእቱሰ፡በርባን፡ዘገብረ፡ሀከከ፡በውስተ፡ሀገር፡ወበቀቲል፡ነፍስ፡ተሞቅሐ።
፳ ወካዕበ፡ይቤሎሙ፡ጲላጦስ፡ትፈቅዱኑ፡አሕይዎ፡ለክሙ፡ለኢየሱስ።
፳፩ ወዐውየዉ፡ወይቤሉ፡ስቅሎ፡ስቅሎ።
፳፪ ወይቤሎሙ፡ጲላጦስ፡በሣልስ፡ምንተ፡

ዓርብ፡መዓልት፡በ፫፡ሰዓት።

፲፪ ጲላጦስም፡እንደገና፡መልሶ፡እንግዲህ፡የአይሁድ፡ንጉሥ፡የተባለውን፡ምን፡ላደርገው፡ትወዳላችሁ፡አላቸው።
፲፫ ሁሉም፡እንደገና፡ስቀለው፡እያሉ፡ጮኹ።
፲፬ ጲላጦስም፡ምን፡ክፉ፡ሥራ፡ሠራ፡አላቸው፤ እነርሱ፡ግን፡ስቀለው፡እያሉ፡አብዝተው፡ጮኹ።
፲፭ ጲላጦስም፡የሕዝቡን፡ፈቃድ፡ያደርግ፡ዘንድ፡አስቦ፡በርባንን፡ፈታላቸው፡ጌታ፡ኢየሱስን፡ግን፡ገርፎ፡ሊሰቅሉት፡ሰጣቸው።

ከዚህ፡በኋላ፡ካህኑ፡ዲያቆኑና፡ሕዝቡ፡እንደ፡ለፊው፡ይበሉ።
ሦስት፡ሰዓት፡በሆነ፡ጊዜ፡በርባንን፡አደና፡ኢየሱስን፡ይሰቅሉት፡ዘንድ፡ሰጣቸው።
ካህኑ፡ቅዱስ፡እግዚአብሔር፡ቅዱስ፡ኃያል፡ቅዱስ፡ሕያው፡ዘኢይመውት፡፫፡ጊዜ፡ይበል።

የሉቃስ፡ወንጌል።

ምዕ፡፳፫፡፲፫–፳፭።

፲፫ ጲላጦስም፡የካህናት፡አለቆችንና፡የሕዝቡን፡ሹማምንት፡ጠራቸው።
፲፬ እንዲህም፡አላቸው፤ ሕዝብን፡ያሳድማል፡ብላችሁ፡ይህን፡ሰው፡ወደ፡እኔ፡አመጣችሁት፤ እነሆም፡በፊታችሁ፡መረመርኩት፡ግን፡እናንተ፡ካቀረባችሁበት፡ክስ፡በዚህ፡ሰው፡ላይ፡ያገኘሁት፡በደል፡የለም።
፲፭ ወደ፡ሄሮድስም፡ላክሁት፡እርሱም፡ወደ፡እኛ፡መልሶ፡ላከው፡እነሆም፡ለሞት፡የሚያበቃው፡የሠራው፡በደል፡የለም።
፲፮ ገርፌ፡ልተወው፡አለ።
፲፯ በየበዓሉ፡ከእስረኞች፡አንዳንድ፡ሊፈታላቸው፡ልማድ፡ነበር።
፲፰ ሁሉም፡በሙሉ፡ይህን፡ወዲያ፡ስቀለው፡በርባንን፡ፍታልን፡ብለው፡ጮኹ።
፲፱ ያ፡በርባን፡ግን፡በሀገር፡ሁከት፡ያደረገና፡ነፍስን፡በመግደል፡የታሰረ፡ነበር።
፳ ጲላጦስም፡እንደገና፡ኢየሱስን፡ልፈታላችሁ፡ትወዳላችሁን፡አላቸው።
፳፩ ስቀለው፡ስቀለው፡ብለው፡ጮኹ።
፳፪ ጲላጦስም፡ለሦስተኛ፡ጊዜ፡ምን፡ክፉ፡

Scanned by CamScanner

በ፱፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

...ዘ፡ግብረ፡ናሁ፡አልቦ፡ዘረከብኩ፡በላዕሌሁ፡
...ዘይመውት ፡ እቀሥፎኬ ፡ እንከሰ ፡ ወአ
...ልዎ።
...ወጸርሑ፡በዐቢይ፡ቃል፡ወሰአሉ፡ወይቤሉ፡
...ይስቅልዎ፤ወኀየለ፡ቃሎሙ፡ወቃለ፡ሊቃነ፡
...ካህናት።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

ነገር ፡ አደረገ ? እነሆ ፡ ለሞት ፡ የሚያበቃ ፡
ምክንያት ፡ አላገኘሁበትም ፤ እንኪያስ ፡ ልግረ
ፈውና፡ልተወው?አላቸው።
፳፫ እንዲሰቅሉትም ፡ በታላቅ ፡ ድምፅ ፡ እየጮኹ ፡
ለመኑት፤የካህናት፡አለቆችና፡የሕዝቡም፡ቃል፡
በረታ።



በመ ቀሠፍዎ ሐራ
ጲላጦስ ለእግዚእን::

የጲላጦስ ጭፍሮች
ጌታችንን እንደገረፉት::

፳፬ ...ሐነፆ፡ጲላጦስ፡ከመ፡ይኩኖሙ፡(ፈቃዶሙ)
ለሰአሎሙ።
፳፭ ወአሕየወ፡ሎሙ፡ዘሰአልዎ፡ዘበቀቲለ፡ነፍስ፡
ወበበረ፡ሁከት ፡ ተሞቅሐ ፡ **ወኢየሱስሃ** ፡
መጠዎሙ፡ለፈቃዶሙ።
**ወእምዝ፡ይበሉ፡** ካህን ፡ ወዲያቆን ፡ ወሕዝብ ፡
ከመ፡ቀዳሚ።
ጊዜ፡ሠለስቱ ፡ ሰዓት ፡ ወሰድዎ ፡ **ለኢየሱስ** ፡
ውስተ፡ዓውደ፡ምኵናን።
**ካህን፡**ቅዱስ፡እግ፡ቅ፡ኃ፡ቅ፡ሕ፡ዘኢ፡ይበል።

፳፬ ጲላጦስም ፡ ፈቃዳቸውን ፡ ይፈጽም ፡ ዘንድ ፡
ፈረደበት።
፳፭ የለመኑትን ፡ ነፍስ ፡ በመግደልና ፡ ሁከት ፡
በማድረግ ፡ የታሰረውን ፡ በርባንን ፡ ፈታላቸው ፤
**ኢየሱስን፡**ግን፡ለፈቃዳቸው፡አሳልፎ፡ሰጣቸው።
**ከዚህ ፡ በኋላ ፡** ካህኑ ፡ ዲያቆኑና ፡ ሕዝቡ ፡ እንዳ
ለፈው፡ይበሉ።
ሦስት፡ሰዓት፡በሆነ፡ጊዜ፡**ጌታ፡ኢየሱስን፡**ወደ፡
ፍርድ፡ዐደባባይ፡ወሰዱት።
**ካህኑ፡**ቅዱስ፡እግ፡ቅ፡ኃ፡ቅ፡ሕ፡ዘኢ፡ይበል።

## ወንጌል፡ዘዮሐንስ።

ምዕ፤፲፱፤፩—፲፪።

፩ ወእምዝ፡ነሥአ፡ጲላጦስ፡**ለእግዚእ፡ኢየሱስ፡**
ወቀሠፎ።
፪ ወፀፈሩ ፡ ሐራ ፡ አክሊለ ፡ ዘሦክ ፡ ወአስተ
ቀጸልዎ ፡ ላእለ ፡ ርእሱ ፡ ወአልበስዎ ፡ ልብሰ ፡
ሜላት።
፫ ወይመጽኡ፡ኀቤሁ፡ወይቤልዎ፡በሐከ፡ንጉሠ፡
አይሁድ፡ወይጸፍዕዎ፡ገጾ።
፬ ወወጽአ፡ካዕበ፡ጲላጦስ፡አፍአ፡ወይቤሎሙ፡ናሁ፡
አወጽአ፡ለክሙ ፡ አፍአ ፡ ከመ ፡ ታእምሩ ፡ ከመ ፡
አልቦ፡ዘረከብኩ፡ላእሌሁ፡ጌጋይ፡ወኢአሐተኒ።
፭ ወወጽአ ፡ **እግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡** አፍአ ፡ እንዘ ፡
ይትቄጸል ፡ አክሊለ ፡ ሦክ ፡ ወይለብስ ፡ ሜላተ ፡
ወይቤሎሙ፡ጲላጦስ፡ነዋ፡ውእቱ፡ብእሲ።
፮ ወሶበ ፡ ርእይዎ ፡ ሊቃነ ፡ ካህናት ፡ ወወዓልያ
ኒሆሙ፡ ከልሑ ፡ ወይቤሉ ፡ ስቅሎ ፡ ስቅሎ ፤
ወይቤሎሙ ፡ ጲላጦስ ፡ ንሥእዎ ፡ ለሊክሙ ፡
ወስቅልዎ፡አንሰ፡ኢረከብኩ፡ላዕሌሁ፡ጌጋየ።

## የዮሐንስ፡ወንጌል።

ምዕ፤፲፱፤፩—፲፪።

፩ ከዚህ፡በኋላ፡ጲላጦስ፡ጌታ፡ኢየሱስን፡ወስዶ፡
ገረፈው።
፪ ጭፍሮችም ፡ የእሾህ ፡ አክሊል ፡ ጐንጕነው ፡
በራሱ፡ ላይ ፡ ደፉበት ፤ የነጭ ፡ ሐር ፡ መጐናጸ
ፊያም፡አለበሱት።
፫ ወደ ፡ እርሱም ፡ እየመጡ ፡ የአይሁድ ፡ ንጉሥ ፡
እንዴት ፡ ነህ ፡ ይሉት ፡ ነበር ፤ ፊቱንም ፡ በጥፊ ፡
ይመቱት፡ነበር።
፬ ጲላጦስ ፡ እንደገና ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ወጥቶ ፡ እነሆ፡
በእርሱ፡ላይ፡አንዳች፡በደል፡እንዳላገኘሁ፡ታውቁ፡
ዘንድ፡ወደ፡ውጭ፡አወጣላችኋለሁ፡አላቸው።
፭ **ጌታ፡ኢየሱስም፡** የእሾህ፡አክሊል፡ደፍቶ፡ነጭ፡
ሐር ፡ ለብሶ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ወጣ ፤ ጲላጦስም ፡ ያ ፡
ሰው፡ይኸው፡አላቸው።
፮ የካህናት፡አለቆችና፡ሎሌዎቻቸውም፡ባዩት፡ጊዜ፡
ስቀለው ፡ ስቀለው ፡ እያሉ ፡ ጮኹ ፤ ጲላጦስም ፡
እናንተ፡ራሳችሁ፡ውሰዱና፡ስቀሉት፡እኔ፡በእርሱ፡
ላይ፡በደል፡አላገኘሁም፡አላቸው።

Scanned by CamScanner

## በ፫፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

፯ ወአውሥኡ፡ አይሁድ፡ ወይቤልዎ፡ ንሕነሰ፡
ሕግ፡ ብነ፤ ወበከመ፡ ሕግነ፡ ርቱዕ፡ ይሙት፡
እስመ፡ **ወልደ፡እግዚአብሔር፡** ረሰየ፡ርእሶ።
፰ ወሰሚዖ፡ ጲላጦስ፡ ዘንተ፡ ነገረ፡ ፈርሀ፡
ፈድፋደ።
፱ ወቦአ፡ ካዕበ፡ ኀበ፡ ዐውድ፡ ወይቤሎ፡
**ለእግዚእ፡ኢየሱስ፡** እምአይቴ፡አንተ፡ወኢተ
ሰጥዎ፡**እግዚእ፡ኢየሱስ፡** ወኢምንተኒ።
፲ ወይቤሎ፡ ጲላጦስ፡ ሊተኒ፡ ኢትትናገበኒሁ፡
ኢተአምርሁ፡ ከመ፡ ብውህ፡ ሊተ፡ እስቅ
ልከሂ፡ወብውህ፡ሊተ፡አሕዩከሂ።
፲፩ ወአውሥአ፡ **እግዚእ፡ ኢየሱስ፡** ወይቤሎ፡
ኢኮንከ፡ብውሀ፡ላእሌየ፡ወኢምንተኒ፡እመ
ኢተውህበ፡ ለከ፡ እምሰማይ፤ ወበእንተ፡
ዝንቱ፡ ለዘአግብአኒ፡ኀቤከ፡ዘየዓቢ፡ ጌጋይ፡
ላዕሌሁ።
፲፪ ወበእንተዝ፡ ፈቀደ፡ ጲላጦስ፡ ያሕይዎ፤
ወከልሑ፡ አይሁድ፡ ወይቤሉ፡ እመ፡
አሕየውኮ፡ለዝንቱ፡ኢኮንከ፡ዐርኮ፡ለቄሣር፡
እስመ፡ኵሉ፡ዘያነግሥ፡ርእሶ፡ዐላዊ፡ነጋሢ፡
ውእቱ።
**ወእምዝ፡ይበሉ፡** ካህን፡ወዲያቆን፡ወሕዝብ፡
ከመ፡ቀዳሚ።
ጊዜ፡ ሠለስቱ፡ ሰዓት፡ ቀሰፎ፡ ጲላጦስ፡
**ለኢየሱስ፡** ወመጠዎሙ፡ይስቅልዎ።
**ካህኑ፡** ቅ፡እግ፡ቅ፡ኃ፡ቅ፡ሕ፡ዘኢይ፡፫፡ጊዜ፡
በል።

ድኅረ፡ወንጌል፡**በሠለስቱ፡ሰዓት፡**
**እምዕለተ፡ዐርብ፡ዘይትነበብ።**

፩ አንሰ፡ ተደመምኩ፡ ምስለ፡ ዝንቱ፡ ነቢይ፡
ዐቢይ።
፪ ዝ፡ቃል፡ዘኢሳይያስ፡ነቢይ፡ቀደመ፡ርእየ፡
ምሥጢረ፡በእንተ፡ሕማማተ፡መድኃኒት፡
**ዘለእግዚአብሔር፡ቃል።**
፫ ይቤ፡ መኑ፡ ውእቱ፡ ዝንቱ፡ ዘወጽአ፡
እምኤዶም፡ወአልባሲሁ፡ቀይሐት፡እምነ፡
ባሦር፡ለቢሶ፡ልብሰ፡ሠናየ፡ከመዝ።
፬ ወልብሱ፡በደመ፡ኮል፡ወፐፐራ፡ሥርግው፡
ከመ፡ዘየዐርግ፡እምጸዐር፡ቅቡዕ፡በደመ፡
አስካል።
፭ አማን፡አማን፡ቃለ፡ነቢይ፡ዘአስተርአየ፡
ዘንተ፡እምቅድመ፡ዛቲ፡መዋዕል፡በአማን፡
ውእቱ፡**ቃለ፡አምላክ።**
፮ **መድኃኒነ፡ ኢየሱስ፡** ከመ፡ ሠርዮ፡ ለኀሊስ፡
ሥጋ፡ ብእሲ፡ ብሉይ፡ ዘለአቡነ፡ አዳም፡

## ዓርብ፡መዓልት፡በ፫፡ሰዓት።

፯ አይሁድም፡ እኛ፡ ሕግ፡ አለን፤ እንደ፡
ሕጋችንም፡ ሊሞት፡ይገባል፤ ራሱን፡**የእግዚአ
ብሔር፡ልጅ፡**አድርጓልና፡ብለው፡መለሱለት።
፰ ጲላጦስም፡ ይህን፡ ነገር፡ ሰምቶ፡ እጅግ፡
ፈራ።
፱ ደግሞም፡ ወደ፡ አደባባይ፡ ተመለሰና፡**ጌታ፡
ኢየሱስን፡** ከወዴት፡ ነህ? አለው፡ **ጌታ፡
ኢየሱስ፡**ግን፡ምንም፡አልመለሰለትም።
፲ ጲላጦስም፡ ለእኔም፡ አትመልስልኝም?
ልገድልህ፡ሥልጣን፡እንዳለኝ፡ላድንህስ፡እን
ዲቻለኝ፡አታውቅምን፡አለው።
፲፩ **ጌታ፡ ኢየሱስም፡** ከሰማይ፡ ካልተሰጠህ፡
በቀር፡ በእኔ፡ ላይ፡ ሥልጣን፡ የለህም፤
ስለዚህም፡ላንተ፡አሳልፎ፡በሰጠኝ፡ሰው፡
ታላቅ፡በደል፡አለበት፡አለው።
፲፪ ስለዚህም፡ ጲላጦስ፡ ሊያድነው፡ ወደደ፤
አይሁድ፡ ግን፡ ይህን፡ ካዳንከው፡ የቄሣር፡
ባለሟል፡ አይደለህም፡ ንጉሥ፡ ነኝ፡ የሚል፡
ሰው፡ ሁሉ፡ በንጉሥ፡ ላይ፡ የሚያምፅ፡ነውና፡
ብለው፡ጮኹ።
**ከዚህ፡ በኋላ፡** ካህኑ፡ ዲያቆኑና፡ ሕዝቡ፡ እንዳ
ለፊው፡ይበሉ።
ሦስት፡ ሰዓት፡ በሆነ፡ ጊዜ፡ **ጌታ፡ ኢየሱስን፡**
ገርፎ፡ይሰቅሉት፡ዘንድ፡ሰጣቸው።
**ካህኑ፡** ቅ፡እግ፡ቅ፡ኃ፡ቅ፡ሕ፡ዘኢይ፡ይበል፡፫፡
ጊዜ።

**ዐርብ፡በሦስት፡ሰዓት፡** ከወንጌል፡በኋላ፡
የሚነበብ።

፩ ከዚህ፣ ከታላቁ፡ ነቢይ፡ ጋር፡ እኔ፡ እደነ
ቃለሁ።
፪ ይህ፡ ቃል፡ የነቢዩ፡ ኢሳይያስ፡ ነው፡ እርሱ፡
**የእግዚአብሔር፡ ቃል፡**
መድኃኒት፡ የሆነች፡ የሕማሙን፡ምሥጢር፡አስቀድሞ፡አየ።
፫ ከሥጋ፡የሆነ፡መልካም፡ልብስን፡የለበሰ፡እን
ደዚህም፡ ልብሶቹ፡ የቀሉ፡ ከኤዶም፡ የወጣ፡
ይህ፡ማነው?አለ።
፬ ልብሱም፡ በእንኮይ፡ በእንዶድ፡ በቀይ፡
ቀለም፡ ዘህነን፡ ደም፡ የታለለ፡ ከፃዕር፡ ውስጥ፡
የወጣ፡ የወይን፡ ዘለላ፡ ደምም፡ የተቀባ፡ ነው።
፭ ከዚች፡ ዘመን፡ አስቀድሞ፡ በነቢይ፡ ቃል፡
የተገለጠ፡ ይህ፡ በእውነት፡ እውነተኛ፡
**የአምላክ፡ ቃል፡** ነው።
፮ **መድኃኒታችን፡ ኢየሱስ፡** ከፍጥረት፡
የሚቀድም፡ የአባታችን፡ የአዳምን፡ የብሉይ፡

Scanned by CamScanner

በ፮፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

ቀዳሚ፡ፍጥረት።
መለኮት ፡ ልዑል ፡ አሐደ ፡ ኮነ ፡ ምስለ ፡
ትስብእት ፡ ወኢ·ተወለጠ ፡ ዘኢይትረከብ ፡
ወኢይትዌለጥ፡ይእቲ፡እንተ፡ኮነት፡አሐደ፡
ምስለ፡ አምላክ።
ሥጠ፡መፀቶ፡ላእለ፡ዕብራውያን፡ወኬዶሙ፡
በጻዕር፡ወበመፀት።
ምሕረቶ፡ወጽድቆ፡ረሰየ፡ሎሙ፡ለአሕዛብ፡
እልክቱ ፡ እለ ፡ ገብሮሙ ፡ ሎቱ ፡ ሕዝበ ፡
ሐዲሰ።
ወለእስራኤልሰ ፡ ካዕበ ፡ ኦኀዞሙ ፡ ዑረተ ፡
ልብ፡እስከ፡ማኅለቅት።
ክርስቶስ፡መድኃኒነ፡መጽአ፡ወሐመ፡ወበሕ
ማማቲሁ፡አድኃነነ።
ማኅተመ፡ጸሎትሰ፡ኀትም፡በከመ፡ኀተምከ፡
በጊዜ፡ነግህ።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፮፡ሰዓት።

ሰው፡ሥጋን፡ከባሕርዩ፡አዋሕዶ፡ለበሰ።
፯፤ ልዑል መለኮትም፡ከትስብእት፡ጋር፡አንድ፡
ባሕርይ ፡ ሆነ ፤ አልተለወጠም ፤ ይህቺም ፡
ከአምላክ ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ የሆነች ፡ ተዋሕዶ ፡
የማትለወጥ፡የማትመረመር፡ናት።
፰፤ ቍጣውን ፡ በዕብራውያን ፡ ላይ ፡ ጨመረ ፡
በፍጹም፡መከራም፡ረገጣቸው።
፱፤ ምሕረቱን ፡ ቸርነቱንም ፡ ለአሕዛብ ፡ አደረገ
ላቸው ፤ እነርሱም ፡ አዲስ ፡ ወገኖች ፡ ያደረ
ጋቸው፡ናቸው።
፲፤ እስራኤልን ፡ ግን ፡ እስከ ፡ መጨረሻ ፡ ድረስ ፡
የልብ፡ድንቁርና፡ያዛቸው።
መድኃኒታችን ፡ ክርስቶስ ፡ ሰው ፡ ሁኖ ፡
መከራ፡ተቀበለ፡በመከራውም፡አዳነን።
የጸሎቱን ፡ መፈጸሚያ ፡ በነግህ ፡ እንደ ፡
ፈጸምከ፡ፈጽም።

## ምዕራፍ፡፶፫።

ትእዛዝ ፡ ወእምዝ ፡ ይትጋብኡ ፡ ካህናት ፡
ውስተ፡ቤተ፡ክርስቲያን፡ቅድስት፡በዕለተ፡
ዐርብ ፡ በጊዜ ፡ ስድስቱ ፡ ሰዓት ፡ ለሥርዐተ ፡
ጸሎት ፡ ወይጸልዩ ፡ በከመ ፡ ጸለዩ ፡ በዕለተ ፡
ሐሙስ፡ጊዜ፡ስድስቱ፡ሰዓት።
ወይበል ፡ መራሒ ፡ በ፱ቱ ፡ ሃሌታ ፡ ተሰቅለ ፡
ተሰቅለ፡ተሰቅለ፡ወሐመ፡ቤዛ፡ኵሉ፡ኮነ፡
ዬ ፡ ዬ ፡ ዬ ፡ በመስቀሉ ፡ ቤዘወነ ፡ እሞት ፡
ባልሐነ።
ወይበሉ፡ለከ፡ኃይል።

### ክፍል፡፩።
### ኦሪት፡ዘኍልቍ።

ምዕ፡፳፩፡፩–፱።

ወሰምዐ፡ከነዓን፡ንጉሠ፡አራድ፡ዘይነብር፡
ውስተ፡አዜብ፡ከመ፡መጽኡ፡እስራኤል፡
እንተ፡ፍኖተ፡አታርን፡ወተቃተሎሙ፡ለእስ
ራኤል፡ወማህረከ፡እምኔሆሙ፡ፄዋ።
ወበፅዐ ፡ እስራኤል ፡ ብፅዐተ ፡ ለእግዚአ
ብሔር፡ወይቤሉ፡ለእመ፡አግብአ፡እግዚአ
ብሔር፡ለዝንቱ፡ሕዝብ፡ለነ፡ናዐልሎ፡ሎቱ፡
ወለአህጉሪሁ።
ወሰምዐ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃሎሙ ፡ ለእስ
ራኤል ፡ ወአግብአሙ ፡ ለከነዓን ፡ ውስተ ፡

## ምዕራፍ፡፶፫።

ትእዛዝ ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በከበረች ፡ ቤተ ፡
ክርስቲያን ፡ ውስጥ ፡ ዐርብ ፡ በስድስት ፡
ሰዓት ፡ ካህናቱ፡ ለጸሎት ፡ ሥርዓት ፡ ይሰብሰቡ ፤
ሐሙስ ፡ በስድስት ፡ ሰዓት ፡ እንደጸለዩት ፡
ይጸልዩ።
መሪው ፡ በ፱ ፡ ሃሌታ ፡ ይበል ፡ ቅድመ ፡ ዓለም ፡
የነበረ ፡ ዛሬም፡ ያለ ፤ ዓለምን ፡ አሳልፎ ፡ የሚኖር ፡
ተሰቀለ ፤ ታመመ ፤ የዓለም ፡ ቤዛ ፡ ሆነ ፤ ወዮ ፡ ወዮ ፡
ወዮ ፤ በመስቀሉ፡አዳነን፡ከሞትም፡ነፃ፡አወጣን።
ለከ፡ኃይልም፡ይበሉ።

### ክፍል፡፩።
### ኦሪት፡ዘኍልቍ።

ምዕ፡፳፩፡፩–፱።

፩፤ በአዜብ ፡ የሚኖር ፡ ከነናዊው ፡ የአራድ ፡
ንጉሥ፡ እስራኤል ፡ በአታርን ፡ ጎዳና ፡ እንደ ፡
መጡ፡ሰምቶ፡እስራኤልን፡ተዋጋቸው፤ከእሳ
ቸውም፡ምርኮን፡ማረከ።
፪፤ እግዚአብሔር ፡ ይኸንን ፡ ወገን ፡ በእጃችን ፡
ቢጥልልን፡ሰውንም፡አገሩንም፡ጉልት፡እናደ
ርግለታለን ፡ ብለው ፡ እስራኤል ፡ ለእግዚአ
ብሔር፡ስእለትን፡ተሳሉ።
፫፤ እግዚአብሔርም ፡ የእስራኤልን ፡ ልመና
ቸውን፡ሰምቶ፡የከነዓንን፡ሰዎች፡በእጃቸው፡